# አለንጋና ምስር



@BOOKALEM

# አለንጋና ምስር

እና

## ሌሎች አጫጭር ታሪኮች

አዳም ረታ

@BOOKALEM

© አዳም ረታ - ሚያዝያ 2004
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ ሕትመት - ጥር 2001
ሁለተኛ ሕትመት - ሰኔ 2004



@BOOKALEM

ገፀ በረከትነቱ፡

ለእንቴ (ለፍቅርተ)



@BOOKALEM

# ይዘት


| | |
|---|---|
| ሦስት ቀኖች | 7 |
| ትዝታ | 21 |
| ዘላን | 27 |
| አብዲ | 71 |
| ጋለሞቶች | 87 |
| የብሩከታዊት ጠጠር | 101 |
| እንጀራዬን | 123 |
| ከሰማያዊ ወደ ቦቢ | 127 |
| ከልጅቷ | 139 |
| የድንች መዋሰዕት | 145 |
| ጭጉሳ፡ ወደፊት ወደኋላ | 155 |
| አለንጋና ምስር | 171 |
| ደብዳቤዎች | 199 |
| ኢዮሄ ጊዜ | 213 |
| እቾሎኒ | 231 |
| ያ ሐመልማል | 251 |
| እግርና ዜጋ | 271 |

@BOOKALEM

# ሦስት ቀኖች

**እ**ለፈ፣ ራቀ፣ ተዘነጋ የተባለን ጉዳይ እንደ ጠንካራ ቁም ነገር አንስቼ ሆን ብዬ አውርቼው አላውቅም:: ሲያወሩ እንኳን ያንገፈግፈኛል:: ምክንያቴ ግን አያልቅ 'ለእንጀራ' አርኪዮሎጂስት ኾኜአለሁ:: ለምን ታሪክ እንደምፈራ አላውቅም:: ተረት ነገራ የትረካን ምንነት ያላመደችኝ አያቴ መሽቶ ስታወራን......ጉጆአችን ውስጥ በእሳቱ የሚፈጠር አንጉል ብርሐንና ጥላ ፊቷ ላይ እየወደቀ......ትንሽ አስፈሪ ካላስመሰላት በስተቀር የምታምር ነበረች:: ይሄም የእስዋ ትዝታ እየኮረኮረ አስበርግጎ እንቅልፍ ስለነሳኝም አይደለም::

ዕውነትን ስለምፈራ ይሆን? ዕውነትን ፈርቼ ይሆን? ምድር ላይ ትንሽ ኖሮ ተመጣጣኝ ያልኾነ ስህተት የሰራ ትውልድ ውስጥ ስለበቀልኩ? በማነሳው የታሪክ መረጃ ውስጥ ሁሉ ኢምንት ራሴን ስለማገኝ?---ብዙ መብቱን ተጠቅሞ ትንሽ ግዴታውን መወጣት የከበደው ቀላል ስለሆንኩ? የቀትር ቀን የመክሰር እስሙን የሚስብ- ......ዋቢ የሌለው ዝንጀሮ ስለተባልኩ?......ወይስ ራሱን ትልቅ ያደረገ፣ ሃያኛው ክፍለ-ዘመን ውስጥ ዘግይቶ የበቀለ የድንቅንሽ ውሽማ ብለው ስለሚያሙኝ? የሌሎች ሰዎች ታሪክም ስለሚያስፈራኝ ይሆን? ይፈራረስ አጥንታቸው፣ ቀርፀው የጣሉት እንጨታቸው፣ ድንጋያቸው፣ ባልጩቱና ምኑ ምኑ ሁሉ ፊቴን በልጥጦ ማንነቴን 'ይሄውልህ' ስለሚለኝ? እንደ መስታወት ሆኖ ወሬኛነቴን ስለሚያሳየኝ?



@BOOKALEM

ታሪክ......ያስፈራኛል::

በዲግሪዬ የተጋረድኩ......እኔ የኮፒ ልጅ:: የኮፒ ኮፒ ልጅ:: የኮፒ ኮፒ

ልጅ......ኮርጅ......ኮርጅ......ኮርልጅ......ኮርልጅ......ኮልጅ......ኮል ጅ...... ኮሊጅ......ኮሊጅ::

ግን እንጀራ ኾኖ ለዕለት ጥርስ መሰለፍ ስላለብኝ......አርኪዮሎጂስት ኾኜአለሁ---የነጋ ጠባ ምክንያቴ---'በደንብ ያበላል' ተብሎ:: ሆድ የምንፈራውን ያሰራናል አይደል? ከምንጠላው ያስተቃቅፈናል አይደል?

ታሪክ ያስፈራኛል:: 'ስለምን እንዲህ ኾነ?' ሲሉኝ፣ የነገር መነሻ ሲጠይቁኝ እፈራለሁ:: ራሴን ይጨምር አይጨምር እንደኾነ አሰላስላለሁ:: ረግጬው የመጣሁት ዕውነት ከተቀጠቀጠበት አፈር ላይ እንደ ጎሚት (አባብ) ተነስቶ ይሆን? እያልኩ::

ታሪክ ያስፈራኛል......

ግን እንጀራ ኾኖ ለዕለት ጥርስ መሰለፍ ስላለብኝ......አርኪዮሎጂስት ኾኜአለሁ---የነጋ ጠባ ምክንያቴ---'በደንብ ያበላል' ተብሎ:: ሆድ የምንፈራውን ያሰራናል አይደል? ዛሬ ከምንጠላውና ከምንሸሸው ያስተቃቅፈናል አይደል?

* * *

አንድ ጊዜ የኢትዮጵያን የማዕከላዊ ዘመን ታሪክ ለማጥናት ከሰነ ጽሁፎች፣ ከመፃሕፍትና ከትውፊት መረጃዎች በመነሳት ካርታዎች አዘጋጅቼ፣ በነዚህም በመመራት ጥንት ሕንፃዎች ነበሩበት ተብሎ እተገመተበት ከሐረር ከተማ በስተደቡብ ከሚገኝ አንድ ቆላማ ቦታ ላይ ቁፋሮ እንዲካሄድ አዘዝኩ::

መስክ ሥራ ላይ እንዳለን በመጀመሪያው ሁለት ሳምንታት ውስጥ የሠራናቸው ነገሮችን ስንገመግም የቦታ ስህተት መፍጠራችንን ስለተረዳሁ ብዙ የለፋንበትን ቦታ ትተን ወደ ሌላ አንድ ሸለቆ ተንቀሳቅሰን አዲሱን ቁፈራ መጀመር ግድ ኾነብን:: ጥቂት ሳምንታት እንደሠራን አንድ ያለችሎታው የወር አበል ጥቅም ብቻ እንዲያገኝ በሥራ አስኪያጁ የተመደበ አብሮን የመጣ 'ሞላ' የተባለ ጉረምሳ /በዘመድ ስለተቀጠረ በጣም ነው የምጠላው/ እየሮጠ መጥቶ አንዲት ከቆዳ የተሰፋች የኪስ ቦርሳ እጄ ላይ አስቀመጠ::

"ይሄ እኮ የዘመኑ ቦርሳ ነው......የእኛ ዘመን፣ እኛ የምንኖርበት ጊዜ" አልኩት ብዙ ያልተረዳው እንዳለ ለመግለጽና ጆል ቢጤ ነህ ለማለት::

"ወረቀቱ ጋሼ......"

"የምን ወረቀት? አይተኸዋል?" አልኩት

ዝም አለ።

"በሙሉ ተመልክተኸዋል?" አልኩት! ቦርሳው በመነካካቱ ነው መሰለኝ የተበተነው አቧራ አንገቴን እያሳከከኝ።

ሞላን ገላመጥኩትና ወረቀቶቹን ከቦርሳው እያወጣሁ ድንኳኔ ውስጥ ቁጭ አልኩ።

"ወደ ሥራህ ሂድ" አልኩት......በጣቴ ብዙ ሰዎች እየቆፈሩ በአቧራ ወደሚታጠኑበት ሸለቆ እያሳየሁት።

ወረቀቶቹ ትንንሽ ቁርጥራጮች ናቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደተረዳሁት ሁሉም በእጅ ፅሑፍ የተሞሉ ነበሩ። የእጅ ፅሑፎቹ የሚመሳሰሉ ቢሆንም ከፊሎቹ ግን ማንም እንዲያነባቸው ኾነው በጥራት አልተፃፉም። ሁሉም ጠርዛቸው በአቧራ የተሸፈነ ሲሆን እውስጥ ያሉት፣ የቦርሳው ቆዳ የጋረዳቸው ንፁህ ነጫጭ ነበሩ። አንድ ሁለቱን ካነበብኳቸው በኋላ ሠፊ ጉጉት አድሮብኝ የበለጠ ለማወቅ......

"ሞላ! ሞላ" ብዬ ተጣራሁ።

በምኔው እንደሰማኝ አላውቅም ተመልሶ እየሮጠ መጣ......በጣም በፍጥነት......ሺህ ጠጠሮችን በሸራ ጫማው እየመታ እየበታተነ። ድንኳኔ ሲደርስ ፍሬን መያዝ አቅቶት እላዬ ላይ ሊወጣ ነበር።

"ቀስ......ቀስ......"

ሞላን ከኋላው ተከትሎት የመጣው አቧራ ያደፈ ጋቢ እንደለበሰ ሽማግሌ ሽው ብሎ ድንኳኔ ውስጥ ገባ።

"የት አገኘኸው?" አልኩት። የምተነፍሰውን አየር ሞላ አስከትሎት ከመጣው አቧራ ለማፅዳት አንድ እጄን እያራገብኩ።

"ዋሻ ነገር መሰለኝ......የጅብ ጉድጓድ ወይም የሌላ አውሬ"

"ታሳየኛለህ?" አልኩት።

እሱ እየመራኝ ተሳስተን መጀመሪያ ወደቆፈርንበት ቦታ ሄድን።

ጉብታ ናት። ወገቧ ላይ ወደ ጫፍም ሳይደርስ ወደ መሬትም ሳይቀርብ ከመሃል ቀልበ-ቢስ የመሰለ፣ ቅጠሎቹ የረገፉ ግዙፍ ግራር ቆሞአል። ዛፉ ቅርፊቱ ተልጦ አልቆ ዋናው ግንዱ ጠቁሮ ይታያል። ስንጠጋው ቅርንጫፎቹ ላይ ተቀምጠው ፀሐይ እየሞቁ የነበሩ ጥቂት ወፎች ባስደነገጠኝ ድንገተኛነት ተነስተው በረሩ።

"እኛ እዚ ጋ ነበር መቆፈር የጀመርነው......ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከዚህ ዋሻ ጋር ተገናኘን" አለ ሞላ።

ወደአሳየኝ ዋሻ ወይም ጉድጓድ ቀድሞኝ ገባና እንድከተለው ጠራኝ። ጥቂት ርቀት ወደታች ቁልቁል እስከንወርድ ድረስ ሙቀት ነበር። ከዚያ በኋላ የቀይ አፈር፣ የዝቅጠተ ዓለት ሽታና ቅዝቃዜ

ወረረኝ:: የሞላን ዳናና ትንፋሽ እያዳመጥኩ በሆዴ እየተሳብኩ ተከተልኩት:: አንድ ሶስት ሜትሮች ያህል እንደሄድን፡

"ይቆዩ" አለኝ::

እንደ ኤሊ ቀስ እያለ እየተሳበ ወደ ሩቅ ጨለማው ውስጥ ጠፋ:: ፊቴን በእጄ እየበሉባ እየጠረግሁ......እሱ በሄደበት አቅጣጫ በጥንቃቄ አተኮርኩ:: እየዳኸ ፊትለፊቴ ሲሄድ በእግሩ የገፋቸው ጠጠሮች እፊቴ ለፊቴ......ወይም አልፈውኝ ብዙ ሳይርቁ ይቆማሉ:: የማይታይ ወርዋሪ አእምሮዬ ውስጥ መጣ:: የጨለማ ውስጥ ተፈናካች:: ራሱን የሚመች ቦታ ሰውሮ የሚያጠቃ:: ሞላን በዘመድ ይኼን ስራ ስለያዘ ተበሳጭቼ በብልግና አስተናግጄዋለሁ፣ ይህቺም ተላላኪነት ስራ ሆና ትጉሕ ሰራተኛነቱን አጣጥዬበታለሁ፣ ሰዎች ፊት አዋርጄዋለሁ:: ድፍረቱን በስልጣኔዩ፣ ትኩስ መንፈሱን በቀዝቃዛ የፌዝ ሳቅ አብርጄበታለሁ:: ስራ አስኪያጁ በዚህች ምድር ላይ ትንሽ በልቶ እንዲያድር ረዳውና ምን ይጠበስ? እንኳን ሰው እግዜር ያዳላል:: 'መከሰቻ ቦታ ያጣ ቂማውን ዛሬ ቢወጣውስ?' አልኩ ለራሴ:: በጨለማ ባሕር ውስጥ ብቻዬን እንደቀረሁ ተሰማኝ:: መንፈሴ እርዳታ ፈልጉ ወደቱበው ግድግዳ ተጠጋሁ:: ቅዝቃዜውና ሸካራነቱ ሊያጽናናኝ ቢሞክርም አልተቀበልኩትም::

"ጋሼ በፈቃዱ" ብሎ ተጣራ:: ድምፁን ከሩቅ የላከው ይመስላል::

ዞሬ ወደመጣሁበት መመለስ አልችልም:: የቱቦው ጠባብነት እንደልብ አያዞርም:: ስሜ ሲጠራ ድምፁ ጆሮዬ እንዳልደረሰ ሁሉ ዝም አልኩኝ::

"ጋሼ በፍቃዱ አይሰሙኝም?" አለ ከቅድሙ ቀረብ ብሎ "እዩት......" አለ ነጭ የሰው ራስ ቅል አንድ እጄ መሃል አስቀምጦ::

ያየሁት ትንሽ ቆይቼ ነበር:: ሄዶበት ከነበረበት አቅጣጫ የሚፈሰው ብርሃን በጥቂቱ ያሳያል::

"ሙሉ የሰው ሰውነት......ይመስለኛል......አጥንት" አለ የራስ ቅሉን አሸክሞኝ ወደመጣበት እየዳኸ ተመለሰ:: የራስ ቅሉን ወደ ጎን ወርውሬ ከኋላው ቀስ እያልኩ ተከተልኩት::

......ትንፋሹን እያዳመጥኩ ሁለት ትንሽ ደቂቃዎች ያህል በልፋት ካለፍን በኋላ ሰፋ ያለ ቦታ ላይ ደረስን:: እዚህ አካባቢ ያለው አፈር የተለየ ነው:: ልጁ ቀበቶው ላይ ይዞአት በነበረ አካፋ አፈር እየዛቀ የተያያዙ አጥንቶች አወጣ::

"ወንድ ነው" አለኝ::

አጥንቱን ቀስ አርጎ አነሳው::......የአፅሙን ቅርፅ የያዙ አፈሮች ከላዩ ላይ ረገፉ:: ጥቋቁር ነፍሳቶች እየተሽለኮለኩ ወጡ:: ግራ ገባኝ::



@BOOKALEM

"አይዞአችሁ......ተቀመጡ" አልኩ::

"ሊያስጨርሱን ነው እንዴ ጋሼ?" አለ አንድ ተማሪ::

ከዚያ የኾነው ነገር ሁሉ ህልም ነው የሚመስለው::......የቤቱን ጣሪያ የሚንበገበግ እሳት እንደ ትኩስ ቂጣ ጉርዶት ሄደ:: የተለጡ የቆርቆሮ ቅድዳጆች ከመሐላችን ወደቁ::......ልጆቹ በአንዲቷ በር ለመውጣት......ትንቅንቅ ጀመሩ::

አይኖቼን ጨፍኜ አስባለሁ:: አሁንም አሁንም:: ሕልም ሕልም:: ከዚያ በመስኮት ለመዝለል የሮጥኩ ይመስለኛል......

ሌላ ሁለተኛ እሳት ተወነጨፈ:: አንድ በርና ሁለት መስኮቶች ደግፎ የያዘው ግድግዳ ተቦድሶ ማሾው ወደቀ:: ቀጭን የነዳጅ እሽት ከድንጋይ መለሉ ላይ ተነስታ......መጀመሪያ ዐይኖቼ ስር በሚለዋወጠው ብርሐንና ጨለማ ጨርት መሰለኝ:: ትግ ያለው ብርሃን ሲከስም ሁለት ጎረምሳ ልጆች......የሚንበገበግ ጀርባቸውን ይዘው እየጮሁ ወደቁ:: አንዲት ሌላ ልጅ ተገንጥሎ ከወደቀው የዛገው በር ላይ ግራ እጅዋን አጥታ በጀርባዋ ተዘርግታለች:: አመድና አፈራ አሳይዋ ላይ ይረግፋል:: ጥቁር ነጭ ጨሰ በዓይዋ ላይ እንደ ደመና እየተሳበ ያልፋል:: ትሙት ትዳን አላውቅም:: ከሚነድ ማገሩ የተገጠለ የጣሪያ ቆርቆሮ ጀርባው ላይ የወደቀበት ዕድሜው አራት አመት የማይሞላው ልጅ ይጮሃል:: ሁል ጊዜ ሙና ከምትባል ከአንዲት ጠይም ልጅ ጋር የሚመጣ ነው:: ስለሚወዳት ወደምታጠናበት ይዛው ትመጣለች:: የምትማረው አቅሮአት ነው:: ሔጄ ላነሳው ፈለግሁ:: ለቅሶው፣ ዋይታው......የሚቃጠለው እንጨት......በእሳት መያያዝ የጀመሩት የተሰባበሩ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች......አስፈሩኝ:: እኔን ወደ ውጭ እንድወጣ የሚስበኝ ነገር በረታ:: ልጁን ትቼ መስኮቱን ለመዝለል ስሞክር ሌላ እሳት......ተደገመ:: የተንጠላጠልኩበት መስኮት ከሥሩ ተነሳ:: ከዚያ በኋላ ለብዙ ሰዓታት የት እንዳለሁ፣ ምን እንደሆንኩ ሳላውቅ እዛው የወደቅሁበት ቆየሁ::

ጳግሜዊው ወረቀት:

ከስመጥኩበት ሰመመን ስወጣ ይህች አሁን ያለሁባት ጉድጓድ ትዝ አለችኝ:: ጨለማው እየለቀቀ መሬት ገና ቡላ እንደመሰለች ነው:: በጀርባዬ ከተኛሁበት መሬት እሳቱ ላይ የወደቀውን መስኮት በቀስታ አንስቼ ወደ ጎን ጣልኩ:: ሰማያዊ የጂንስ ሸሚዜ በደም ተነክሮአል:: ደመነፍሴ ነግሮኝ ግራ እጄን ወደ ፊቴ ሰድጄ ሰዳበስ የደረቀ ደም አጋጠመኝ:: ቀስ እያልኩ በአንድ እጄ ሰውነቴን ዳሰስኩ:: ከግንባሬ ትንሽ ከፍ ብሎ ፀጉሬ በደም ተነክሮአል:: ይጠዘጥዘኛል:: እነበርኩበት ቁስሌን እየዳበስኩ ተጋድሜ ቆየሁ:: እዚህ በረሐ ውስጥ የጠፋሁ መሰለኝ......የሰማዩ ስፋት፣ የመልክአ ምድሩ ፀጥታ:: በአእምሮዬ የመሸሻዬን መንገድ ዕርቀት ለካሁ:: ጥንካሬዬን ገመትኩ:: ተስፋ ቆረጥኩ::



@BOOKALEM

ብዙ ሳልቆይ ተነስቼ ቆምኩ:: ዞር ዞር ብዬ አየሁ:: ትምህርት ቤቷ የተጀመረ ግንብ መስላለች:: ሕፃናቱ የት እንደሄዱ ማሰብ አልፈለግሁም:: ሳስተምራቸው ኖሬ ለአንዲት ቀውጢ ሰዐት ነፍሳቸውን ማዳን ባለመቻሌ አፈርኩ::

አስተምርባት የነበረችው ክፍል ውስጥ ገባሁ:: የሞተ ወይም ቆስሎ መንሳት ያቃተው ሕፃን ለመፈለግ ዴስኮቹና ጠረጴዛዎች ተከምረው ከወደቁበት ጥግ እያነሳሁ ወደ ሌላ አቅጣጫ መወርወር ጀመርኩ:: ሙና የምትባለዋን ልጅ በከፊል የተቃጠለ ዴስክ ስር ወድቃ አየኋት:: በእሳት የነደደ ደረቷ ላይ በሆነ ተአምር ተቃጥሎ ያላለቀ የደብተር ግማሽ ተዘርግቷል:: አንገቷ ወደ ትከሻዋ ዘንበል ብሎአል! ቀጭን የደም ምንጭ ቅጠል ከመሰለ አፍዋ እስከ አንገቷ ድረስ ወርዶአል:: ነፍሷ የወጣችበት ትንሽ መንገድ ይመስላል:: በቆቃ በሚያነዳቸው አይኖቼ እሷን በማየት ላይ ሳለሁ የሰው ድምፅ ሰማሁ:: ድፍረት ተከናንቦ የነበረው ልቤ የፍርሃት ሙቅ ገባው:: ሲጉዱ አልረዳኋቸውም ያልኳቸው ሕፃናት ምስሎች ሁሉ ከሃሳቤ ጠፉ:: የት/ቤቱን ፍርስራሽ ከለላ አድርጌ ድምፅ ወደ መጣበት ተመለከትኩ:: ተራርቀው የሚሄዱ ሁለት የሲያድ ባሬ ወታደሮች ናቸው:: በጣም ታጥቀዋል:: ራቅ ብሎ ከኋላ ታንክ ይከተላቸዋል::

የሞተችው ልጅ እንዳትታይ እንጨት እላይዋ ላይ ለመደረብ ስሰቤ ……ድንገት ድምፅ ቢፈጥር ብዬ ፈርቼ ተውኩት……ወደ መሬት ወርጄ እየተምጓቸሁ ሰዎቹ የሚሄዱበትን አቅጣጫ ተመለከትኩ:: ወደ ከተማው መግቢያ ያለችው ረባዳ ውስጥ ገቡ:: በድንገት ዘወትር እሁድ፣ እሁድ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር እየሄድን የምንጫወትባት ዋሻ ቢጤ ትዝ አለችኝ:: ጓደኛዬን ሳስታውስ ሕዝቡ ትዝ አለኝ:: የአካባቢው ዝምታ ባጉነበስኩበት ተጫነኝ:: ቀና ብዬ ወታደሮቹ የሄዱበትን አቅጣጫ አየሁ:: ወታደሮቹ አይታዩኝም:: ታንኩ በፈረሱ ቤቶች ላይ እየተንከባለለ ይከተላቸዋል::

"ሰዎች ወደ የት ጠፉ!" ሲል እሰማዋለሁ አንድ ሰው ከታንኩ አናት ራሱን አሾልኮ አውጥቶ::

"ወደሚቀጥለው ከተማ ተሰደዋል……"

"ማን ነገረህ?"

"የእኛ ወኪሎች ናቸው……እዚያኛው ቤት ሄደህ እንጋግር"…… በሱማሊኛ ነው የሚያወሩት::

ወደ እኔ አቅጣጫ ሊመጣ የነበረው ታንክ በተቃራኒ በኩል መገስገስ ጀመረ:: እንዳጉነበስኩ ፊቴን እጆቼ ላይ አድርጌ ወደ ውጭ በከባድ ተነፈስኩ……

በላይ፣ አምሃ፣ መርጋ፣ እማማ ዘውዴ፣ አህመዲን……ውሸት መሰለኝ:: ቀና ብዬ አካባቢዬን አየሁ:: ዘወትር የምትወጣው ፀሐይ ከአድማስ ብቅ ብላለች:: እንደ ሁልጊዜው ፀሐይ ልትወጣ ነው:: ግን ለብዙው ጉላለች:: ለአምሃ……ለመርጋ……ለአደም:: ለእኔ ጉላለች::



@BOOKALEM

ወደዚች ት/ቤት ሕፃናት አይመጡም፡፡ የእማማ ዘውዴ የሰንቀላል ጥብስ፣ የፍየል ወተት ቁርስ የለም፡፡ እምሃ ጆክ አያረግም፡፡ እኔም አልበትም፡፡ የሚያነክሱ አህዮችና ሞት ከተማዎን ወረዋታል፡፡ አህመዲን በርጫ አያደርግም፡፡ የበላይ የሮዝማን ሲጋራ ሽታ አፍንጫዬ ድረስ መጣ......በዚህ ስቆታ ውስጥ እንደአሳሳሩ ሚስጢር ይሰማኛል......በላይ፣ እምሃ፣ መርጋ፣ እማማ ዘውዴ፣ አህመዲን......እንዳጉነበስኩ ስቅስቅ ብዬ ማልቀስ እንደጀመርኩ ውሸት መሰለኝና ወዲያው አቆምኩ፡፡

ወደ ዋሻው ለመሄድ ፈራሁ፡፡ መሸሽ ጠላሁ፡፡ መሞት ፈራሁ፡፡ እየዳህኩ ከት/ቤቷ ፍራሽ ወጣሁ፡፡ ዙሪያዬን አየሁ፡፡ ማንም የለም፡፡ ወታደሮቹ ወደ ወረዱበት አቅጣጫ ቆሜ አይቼ ወደ ሸጥዋ ውስጥ ለመግባት መሮጥ ጀመርኩ፡፡ ልደርስ ስል ከኋላዬ የሰው ጩኸትና የተኩስ ድምፅ ሰማሁ፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ወደ ኋላዬ ዞር ብዬ አየሁ፡፡ በስተግራዬ በሰልፍ ተያይዘው የሚመጡ ሌሎች ወታደሮች ከተማዎን በትንሹ ከጋረዳት የድንጋይ ኮረብታ ላይ ወደ እኔ አቅጣጫ እየሮጡ......

ጥይቶች እግሬ አካባቢ አፏጩ፡፡ ጭንቅላቴ ዞረ፡፡ ወደ ቁልቁለቱ ገብቼ መንደርደር ጀመርኩ፡፡ ተኩሳቸው ሊያገኝኝ አልቻለም፡፡ ወደ ዋሻዋ አቅጣጫ ሮጥኩ፡፡ ዋሻዋ ለመድረስ ወደ ቀኝ እጥፍ አልኩ፡፡ ቀጠር እንዳለን ሁሉ መግቢያ ቀዳዳዋ ተከፍቶ ወደምትጠብቀኝ ዋሻ ተወርውሬ ገባሁ፡፡ ገና ገባዬ መሬት እንደነካ ሮኬት ሳይሆን አይቀርም የዋሻውን የላይ ክንፈር መታው፡፡ በጭንቀት አይኖቼን ጨፍኜ ቆየሁና ከወደቅሁበት ቀና አልኩ፡፡ ዋሻዋ ጨለማለች፡፡ የአፈርና የድንጋይ ናዳ ተንከባሎ የዋሻውን መግቢያ እንደደፈነው ገባኝ፡፡ ድሮ የማውቃት ዋሻ አልመሰለችኝም፡፡ እኔም ውስጤ ጨለመብኝ......

ምን ያህል ጊዜ ተኝቼ ወይም ራሴን ስቼ እንደነበር አላውቅም......

እየተኛሁ ስባንን ቆየሁ፡፡ ከመሃል ራበኝ፡፡ ለምጄው የማላውቅ ሀይነት ረሃብ......

የዋሻውን ግድግዳ በዳበሳ አጠናሁ፡፡ ጭንቅላቴ ተንተርሶት የነበረው አፈር ጥብቅ ያለኝና ጓል የሚበዛው ስለኝና የበሩ አቅጣጫ መሆኑን ገምቼ በድፍንፍኑ ወደ ዋሻው ውስጥ አፈሩን በእጆቼ መጉተት ጀመርኩ፡፡ ብዙም አፈር ወደ ዋሻው ውስጥ ሳልሰበስብ ጣቶቼን አመመኝ፡፡ በረሃብ የታጠፈው ሆዴን ቁርጠት ጀመረው፡፡ ተጣጥፌ እተኃለትኩበት ፊቴን ጭኔ ላይ ደፍቼ ለረዥም ጊዜ ቆየሁ......

### ሳልሳዊው ወረቀት፡

"ጉስማዬ!" የእናቴ ስም ነው፡፡ ቅፅል ስሟ ሆኖ ግን የመታወቂያ ስሟም ነበር፡፡ በመጀመሪያ በልጅነቷ አካባቢዋን ስለምትፈራ እናቷ ቤት እንግዳ በመጣ ቁጥር እየሮጠች ሄዳ እናቷ ጉያ ውትፍ፣ ጉስም ትል ነበር---ጉስማዬ አሏት፡፡ አባቴ አሰፋ ይባላሉ፡፡ እኔ ተስፋዬ እባላለሁ፡፡



@BOOKALEM

ተስፋዬ አስተ:: እድሜዬ 25 ወይም 26 ነው:: እርግጠኛ አይደለሁም:: ረዥም ነህ ይሉኛል:: አይመስለኝም:: ጭንቅላቴ ጭብጦ ስለምታክል ሎጋ እመስል ይሆናል እንጂ አጭር ነኝ:: ቆንጆ ነህ ይሉኛል:: አይደለሁም:: በረሃ ውስጥ ወሲብ ያቃጠላቸው ሴቶች ሀይኖቻቸውን ጋርደአቸው ወይ ከግመሎች ጋር አወዳድረውኝ ካልሆነ በስተቀር አስቀያሚ ነኝ:: አፍንጫዬ ብቻ እዚህ በእጆቼ የምገለብጠውን የድንጋይ ጓል ይመስላል--የተጠረመሰ፣ ሸካራና በጣም ትልቅ:: ብሩህ አእምሮ አለው ይሉኛል:: የለኝም:: መንደር ውስጥ ከሚንከራተቱ ሰብዶችና የወባ ትንኞች ትንሽ ስለምሻል ይሆናል:: ከዝንጀሮ ቆንጆ መራርጠው::

እዚህች የበረሃ ከተማ ለማስተማር ከመጣሁ ሰባት አመት አለፈኝ::

<u>አርባዕተኛው ወረቀት፡</u>

የቲያትረኛ ቡድን አባል ነበርኩ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ:: በየከተሞቹ እየዞርን ቲያትርና ሙዚቃ እናሳይ ነበር:: እኛ ብቅ ብለን ትርኢት የምናሳየው ሕዝብ ለሚቀጥሉት አሥራ አምስት ቀናት ነጋ ጠባ በተለምዶ የሚያወራውን ትቶ፡

"ዮቹ ሸላይ......እሳት ልጅ ናት" እያለ ያወራል::

ከአብዮቱ በኋላ ተበታተንን:: እያንዳንዱ ወጣት የራሱን እምነት እየያዘ ተሰወረ:: የሙዚቃ ቡድን መሪያችን የነበረው እቃዎቹን በሙሉ ሸጦ ቡና ለመነገድ ሲጓዝ ወረደ:: ብዙው የተበተነ ቡድኑ መፍረሱ ቅሬታ ያሳደረበት አይመስለኝም:: ወይ ተገናኝተን የልባችንን ስለአልተጨዋወትን ይሆናል:: አብዱላሂ_________ውስጥ ገብቷል ሲባል እሰማ ነበር:: መዝሙር በቢነት ቡድናችን ውስጥ የሕብረት ዝማሬና ሶሎ ዘፈኖች ውስጥ የቅዳሴን ዜማ እስገብቶ ስለአሰራን ቅፅል ስሙን 'መዝሙር' አልነው:: እናት አባቱ ያወጡለትን ስም አለማስታወሴ አይገርመኝም:: እሱም______ውስጥ ገብቶአል ሲባል እሰማለሁ:: እስከነጭራሽ አውራጃችን የነበረችው ዝምተኛዋ ብዙ ወንዶች የሚፈልጓት ኢየሩሳሌም የት እንዳለች አላውቅም:: እኔ እዚህ የተበተነ ቡድን ውስጥ ሽለላ፣ ቀረርቶ እሰማ ነበር:: ዝላዬና ቀጣዬ ያስደሰታቸው አባቶች፣ ሴትነታቸውን ያስደነገጣቸው ልጃገረዶች (ሁሉም ፈሪዎች ሲሆኑ ይችላሉ) ተመልካች ፊት ጀግንነት የሚወዱ ለመምሰል መሰለኝ መድረክ ላይ እየወጡ ይሸልሙኝ ነበር:: እስካሁን የማልረሳት ሴት ልጅ አለች:: የራስዋን የወርቅ ሐብል አውልቃ የሰጠችኝ:: በልቤ እየሳቅኩ ፊቴን አኮሳትሬ፣ ጋሻዬን ከፍ ዝቅ እያደረግሁ፣ ጦሬን እየሰበቅሁ፣

"እጥፍጥፍ ያለው አንደኑጠላ
እናት ወለደች ይበቃል ብላ"

እያልኩኝ በመዝፈን ጀርባ ከወጠርናት ጋቢ ከምታክል ድንኳናችን አድርጌላት፣ መድረክ መለስ ብላ ገብታ ስሟን ነግራኝ ተቀወቀችኝ::

"ስሜ የሺእመቤት ነው" አለችኝ::



@BOOKALEM

እስከ ዛሬ ምንም አይገባኝም:: እኔ የምፎክረው ዝነኛ ለመኾን ነበር:: ባላንጣ በሌለበት ድ'ም ማቅራራቱ ይቀላል:: ጦር የሚሰበቀው ባዶ አየር ላይ ነው:: በዚህም ላይ የሺእመቤትን ከመሰሉ ቆንጆ ልጃገረዶች ጋር መተዋወቅ አለ:: አሁን ዛሬ ግን አንድዋን ስንኳ ከዚህች ዋሻ ውጥቼ ማንጓረት አቃተኝ:: የሺእመቤት የሰጠችኝን የወርቅ ሃብል እስተማሪ የነበርኩ ጊዜ ገንዘብ ቸግሮኝ ይሁን ለቅብጠት ሸጨ በልቸዋለሁ::.....እንዚያ ደፋር ፖለቲከኛ የሆኑ ጓደኞቼ ይዋጉ ይሆን?

የሺእመቤት ጀግና.....ፎካሪ.....ሸላይ.....መኾን የምትችል መስሉአት ይሆናል:: የጀግና ምስል ፈጥሮ ብቻ ለራስ ፈሪነትን ማፅደቅ ለየሺእመቤት ብቻ የደረሳት ጣጣ ወይም ሰዳ ነው ያለው ማነው? የቲያትር ተመልካች አስጮህ.....አዘልል 'እሰይ.....የእኔ ግሥላ' ላሰኝ የነበርኩት ልጅ፣ የጀግና ምስል የነበርኩት ልጅ ከርሞ ከርሞ እንደ ዛሬው ዓይነት ገጭ ገው ነገር ሲከሰት 'በየሺእመቤታዊ ሰዳ' ብቻ የምገለፅ ጠባብ ቢጤ ሳልሆን አልቀረሁም:: ቢረባም ባይረባም እንደ ጓደኞቼ የሚመስሉኝን ሌሎች ሰዎች ፈልጌ አልተሰበሰብኩም:: እና የአገሬን የውስጥ ጠላትም ይሁን የውጭ ጠላት አልወጋሁም::

ድሮ መጨረስ የሚገባኝን ንትርክ እዚህ ቀውጢ ጊዜ ውስጥ ማስላሰሉ ራሴን አስገርሞኛል::

እዚያው ሐረር ከተማ እንኳን ረባም አልረባም ፍልስፍናው ሲጠና.....እኔ ከወረዳ ከተማ እየመጣሁ የየሺእመቤቶችን ሐብት እየሸጥኩ ወይን ጠጅና ኪኖቶ እጠጣ ነበር::

__አምስተኛው ወረቀት:__

ከተደበቅሁበት ዋሻ ቱቦ በመሰለው ጉድጓድ ውስጥ እየተሳብኩ ወደ ውጭ ልወጣ ብሞክር አልቻልኩም:: ዋሻዋ ከአንድ ሰአት በላይ ብርሃን አትሆንም:: ሟት ሁለት ሰአት ወይም ሶስት ሰአት ላይ ነው ብዬ እገምታለሁ:: አጠገቤ ከውጭ በኩል የሚርመሰመስ የሞተር ድምፅ ይሰማል::

የምቀርበውና የሚቀርበኝ አስተማሪው ጓደኛዬ አህመዲን የት ደርሶ ይሆን? አዎ፣ እኔ ልጆቹን ለማስጠናት ስሄድ እሱ ከቤት ጓደኛው ጋር ለጫት እንገናኝ እቤታችን ቀርቶ ነበር:: የሱማሌ ወታደር ራቀታቸውን ቢይዛቸውስ? በሲኒማ ያየኋቸው የተማረኩ ሰዎች የሚሰቃዩባቸው መንገዶች ተራ በተራ ትዝ አሉኝ::

ጓደኛው ሱማሌ ስለኾነች ታድነው ይሆናል::

__ስድስተኛው ወረቀት:__

ሚስጥር የሚያውቅ ሰው ይሕችን ደብዳቤ ቢያገኛት እወዳለሁ:: ስሜ አደባባይ ተነዝቶ....."ማን ሞተ? ማን ይባላል? እሱ?.....ፎካሪው ፈሪ ነኝ ብሎ ሞተ? ፈሪ?.....እሱ?" እንዲሉ::



@BOOKALEM

ታሪክን ለጀግኖች ብቻ ማን እንደሰጣቸው ባላውቅም ለእኔ አይነቱ ምኞቱን በልቡ እንጂ በድርጊት ለማይኖር ፈሪ ታሪክ የለውም:: «ፈሪ ነኝ» ብሎ ያመነ አለ?

እንደ እኔ ደብዳቤ ባይጽፍም---መሃይም በመሆኑ ወይም እንደበቱ የተሳሰረ፣ ማውራት የሚሳነው ወይም ማውራትም መፃፍም የማይፈልግ ወይም የማይሆንለት መንፈሰ ተዝቃ!! ፈሪም ይኖራል:: ወይም ከጉልበተኛ የወገን ፣በዛም ሥር ፈሪነቱን የደበቀ ይኖራል:: ፈሪ ብዙ ቴክኒክ አለው መሰል ጭንብል አጥልቆ በመሃላችሁ የሚመላለስበት...... ከቀዘቀዘ ይልቅ እንዲህ እንደ እኔ ትንሽ የነደደ ፈሪ መኖሩን ሳይሻል ይቀራል?

ይህቺ መግለጫዬ በድብቅ ትያዝ:: እጅግ በድብቅ::

<u>ሰባተኛው ወረቀት:</u>

ድካሙ ደግሞ በርትቶብኛል:: ስንተኛ ቀኔ መሆኑ ቢምታታብኝም አራት ጊዜ እንቀላፍቼ አስፈሪ ቅዠት ቀስቅሶኝ ተነስቼአለሁ:: የእንቅልፌም ቅርጽ እየተለዋወጠ የመጣ ይመስለኛል::

መጀመሪያ ስተኛ......ሕልሜ ሁሉ ማሳደድ ነበረበት---ጥቁር ቀጫጭን ረዣዥም ሰዎች ሲያሳድዱኝ......ጥርሶቻቸውን ገሸልጠው---ያስፈራራሉ:: እኔም የማያልቅ የሚያደክም ሩጫ በርጥ::

ሁለተኛ ጊዜም የሕልሜ ሴራ ከመጀመሪያው እምብዛም አልተለወጠም:: ጊዜው ግን ያጠረ ይመስለኛል:: ያየኋቸውን ሕልሞች በዝርዝር መጥራት አልችልም:: የመጨረሻዎቹ......ያደፋፍራሉ:: ሲያባርሩኝ የነበሩትን ሰዎች ሳባርር......ግን አልደረስባቸውም::

<u>ስምንተኛው ወረቀት:</u>

እነዚያን የትምህርት ቤቴን ሕፃናት ትናንት በሕልሜ ደግሜ አየኋቸው:: አድገው፣ ትላልቅ ሰዎች ሁነው:: የፈሰሰው ደማቸው አልደረቀም:: ገና ይፈሳል:: የተተዳደዱ ዳርዳራቸውን በእሳት የተበሉ ደብተሮቻቸውን ይዘዋል:: ሁለት ናቸው---ሙናና ደ'ሞ ሌላ ሁለተኛ ሙና:: ሁለት ሙናዎች:: ሌላ ሙና:: ከሙና በኋላ ሌላ ሙና:: ግን ሰልፋቸው አያልቅም......ከጉድጓድ እንደሚወጣ ጉንዳን:: ትክ ብለው ያዩኝና ያልፋሉ:: ምን አድርግ እንደሚሉ አልገባኝም:: እንደ ላብ በፊታቸውና በግንባራቸው የሚፈሰውን ደም ለመጥረግ ስጠጋ ይሸሹኛል:: ያም ሆኖ ግን እያዩኝ ያልፋሉ:: ወደ ራሴ አየሁ:: ራቁቴን ነው የቆምኩት:: ብልቴ የለም:: በቦታው ፋንታ የጫት ቅጠል የሚመስል ደረቅ ሐረግ ተተብትቦአል:: ከሰውነቴ ውስጥ እሾህ ወደ ውጭ የበቀለ መሰለኝ:: እየጮኽኩ ተነሳሁ::

የሞትኩ መሰለኝ ነበር::



@BOOKALEM

ነሞ ራ ______________

<u>ተሳዕተኛው ወረቀት፡</u>

ወታደሮቹ ከጉድጓድ የወጣ ድምፅ ሰምተው ነው መሰለኝ ወደ ዋሻው ውስጥ ተኮሱ:: መግባት የፈሩት ብዙ የተደበቀ ሰው ያለ መስሎአቸው ይሆናል:: ሲጨንቃቸው መውጣታቸው አይቀርም በሚል ግምት እየጠበቁ ይሆናልም ብዬ ገመትኩ::

መፃፊያ እርሳሴን አጥብቄ መያዝ አልቻልኩም:: ወደ ውጭ ብወጣ ሱማሊዎች ከእኔ ምንም የሚያገኙት ነገር የለም:: ወይም የሚናር መስሎአቸው ሊያሰቃዩኝ ይችላሉ::

'ከሌለ ታዲያ ለምን ተደበቅህ?' ቢሉኝ......

'ፈርቼ' ብላቸውስ::

የሚሸሸው ሰው ሁሉ አቅም አጥሮት ሳይሆን 'ፈርቶ' ነው በማለት ይበልጥ ሊፎልሉ ይችላሉ:: አልወጣም ከዚህች ቦታ......አልወጣትም ......ምላሴ ተሳስቶ የእነሱን ልብ ከሚያደብር እዚሁ ልጥፋ:: ይህቺን ደብዳቤ ግን አደራ ደብቁልኝ:: የተበላሸ ሰው የፃፈት ስለኾነ ጠብቋት:: እዚህች ዋሻ ውስጥ ቀርቼ ትከሻዬ ለአተላ አትደርስ ይሆናል:: ከዚህ ማምለጥ ችዬ ላለፈው ፈሪነቴ እንደ ቅጣት ኢትዮጵያን አተላ በገንቦ ተሸክሜ ባደርስ::

'ባለአተላው!'

ወይ በዚህ ጉዛዜዬ ፈሪዎችን በለማጋለጥ አንድ ቀንም በሕይወት እንዳልቀይ ነገር ይፈተፍቱብኝ ይሆናል:: አንዳንዴ የፈሪም ሕይወት እንደ ጀግና ህይወት አጭር ትሆናለች:: ብዙዎችን ታስፈራለች:: ያኔ ይሆን 'ታደልን' የምንለው?

በልቤ የታመቀው ሁሉ ነገር ግን ጨርሶ አልወጣልኝም:: ምኑ ያልቃል? አቅም ካገኘሁ እጽፋታለሁ:: ሙታን በሚኖሩበት ጨለማ ጉድጓድ ሄፍ አብርቼ ጥቁር ሰሌዳ ሰቅዬ......እነዚያን ሕፃናት ለማስተማር እደፍር ይሆን? ገላዬ ላይ ያለው እሾህ ቢረግፍልኝ......ብልቴ ተመልሶ ቢያቆጠቁጥ......እነዚያ ወጣቶች ቢሰቁልኝ:: እነ ሙና......

......ወረቀቶቹን አንብቤ ከጨረስኩ በኋላ ልዩ ነገር እንደማገኝባቸው ሁሉ አገላብጬ አየኋቸው:: ልጁ በአንድ እግሩ የዋሻውን አፍ እየናደ ያየኛል::

"አንብበኸዋል አይደለም?" አልኩት

"አዎ:: ትንሽ"

አሁንም በእግሩ የዋሻውን አፍ መናድ አላቆመም:: በእያንዳንዱ እርግጫ አፈር እየናደ ብዙ ብርሃን የሚያስገባ ይመስላል::

"እዚያ ትምህርት ቤት ነበር መሰለኝ የሚያስተምረው......"

"እዚህ አካባቢ ሌላ የለም፣ እሱ መኾን አለበት......ስለ ሰውዬው መጠየቅ ፈለገን ጋሼ?"



@BOOKALEM

"እይ……ይበቃል፡፡ እኛ የምናውቀውን አያውቁም፡፡ እሱ ያልነገረን ነገር ቢኖር ተራ ዝርዝር ነው"

በዋሻው ቀዳዳ ወደ ውጭ ሳይ ቆየሁና ለልጁ እንዲወጣ ምልክት ሰጠሁት፡፡ ተከታትለን ወደ ድንኳን ሠፈራችን ሔድን፡፡

------ // -----

*መስከረም 1976*
*አዲስ አበባ*

ነም፡ቃ፡ም፡ስ፡ ______

የኃየረልዒ ብለ ::ሚቆ-ወዒለ የ-ወቀ-ወጉሚየ ኛረ ::ልዒበዒ.....
"-ወየ ጋዘጋዘ ሓቶ ጋ

ቶበልሚ ዮወጾየረ ጆለለ ጉሀየቆ ጓሰ ጭ-ጠ ጓወ ጾጾቀ ጠሾየ
::የጓሐ የቾኃኃሣ የደየጓ ጓወ የለቶቲበቶ ::ፉ.

--- ‖ ---

ወፎዩ ሚኃዘበሙ
ሀበለ በጾለ



@BOOKALEM

# ትዝታ

**የ**ታላቅ እኅቴ ድፍረት የቤቱን በር ደፍ ሲደርስ እያለቀሰ ይቆማል:: በአባቱ ፍየሌ ጺም ቆርጦ በልኩዕ በእናቱ ረገድም ሻሽ ተከልሎ መኝታ ክፍሉ ሲት ወደጆቹን ማስገባት ላይከብደዋል:: ሁለቱንም ወላጆቹን ይፈራቸዋል:: አንድ ትዳሚ ሰለት ግድ ነኝ።

አስራ አንድ ሰአት ተኩል አካባቢ መኝታ ክፍሌ ውስጥ ፍራሽን ከአልጋዬ አውርጄ መሬት አንጥፌ፣ ሚዚቃ ከፍቼ፣ ሰንደል አጤሼ፣ ጋቢዬን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጌ ለጭኔ ክበድ ያለ መጽሐፍ ዘርግቼ ጫት እየቃምኩ አነባለሁ:: በንባብ ስሜቴ ውስጥ እየሰጠምኩ እያለሁ በር ተንኳኳ:: የቴፑን ድምፅ ዝቅ አድርጌ ማን እንደኾነ ጠየቅሁ::

ስሙን ሳይናገር በፉጨት ብቻ እኅቴ እሱ እንደኾነ ጠቀመኝና ጋቢዬን ከትከሻዬ ሳላወርድ እየጐተትኩ በመኝታ ስባዶ እግሬ ሔጄ በሩን ከፈትኩለት:: ሲገባ እንኳን አላየሁትም:: ከልምዱ ብቻ እሱ መሆኑን በመረዳት ጀርባዬን አዙሬ ወደ ነበርኩበት ለመቀመጥ ስመቻች በጨዋኚና በማይደክም ድምፁ:

"ስማ ዴቭ ይህችን ልጅ ተዋወቃት" አለኝ::

"ፍሬ ሕይወት" አለችኝ::

ዞር አልኩ:: ፊቷን በትንሹ ደፋ አድርጋ ስለነበር ብዙዋም አቋሟም ግልጽ ኾኖ አይታየኝም:: ከማንበቢያዋ ጠረጴዛ የሚሥራጨው ብርሃን ወደ እኔ ተስቦ የመጣውን እጅዋን እንኳን ያሳየኝ በአይን ብልጠጣ ልምምጥ ነው::



@BOOKALEM

"ዳዊት" አልኳት መለስ ብዬ 'ካየኋት' በኋላ::

"እንዴ መብራት አታበራም እንዴ? ጨለማ ውስጥ እንደ እብድ! ፍሬ መጣሁ እሺ:: አጫውታት» ብሎ ወጣ::

በተከፈተው በር አጎቴና ያመጣት ሴት እሽኩኩ ብለው ያስገቡት ቀዝቃዛ አየር እንደ ማሕፀን ትሞቅ የነበረችው ክፍሌ ውስጥ ተጠቀጠቀባት:: በስተግራዬ 'ፍሬ' የተባለች ልጅ ጭኖቿ ዙሪያ ቀሚሷን ሰብስባ እንዲት ግርምቡድ ላይ ቁጭ አለች:: የተዘጋውን ቴፕ መልሼ ስላልከፈትኩትና ሲገቡ የነበረው ትንሽ ትርምስም ስለበረደ ዝምታ ቤቱን ሞላው:: እኔም እስዋም በጣም ባልጎሉ ሳሎች ጉሮሮአችንን አፀዳዳን---እኔ የጫቴን ፍርስራሽ ልውጥ:: የእስዋን አላውቅም:: ከዚያ ደጓሳ ዝምታ:: ሳልና ሳል:: ከዚያ ዝምታ......

ደብዛዛ ብርሃን ካለበት አቅጣጫ የፍሬ ሕይወት አንድ እጅ ወደ ፊትዋ እየተንሳፈፈ ሲያልፍ---የራሱ ነፃነት እንዳለው ሁሉ---አንድ ነገር ብልጭ አለ:: ደቃቃ ነገር የፈለቀ መሰለኝ:: ቀለበት:: የወርቅ፣ የብር ወይ የሌላ ዓይነት ብረታብረት:: አንድ ጣትዋን ቅባት ነክቶት ወይም ያልደረቀ የምራቅ ነጥብ ሰፍሮበት ይሆናል:: ለብቻዬ ፈገግ አልኩ::

......ለራሴ ፈገግ ማለቴ ሲታወቀኝ በልቤ:

'ምን ያስቀዋል?' ትል ይሆን? አልኩ

ለዚህ ድርጊቴ የወንጀለኛነት ስሜት ተሰምቶኝ ምን ልናገር ብዬ ሳስብ የመጣልኝ ቃል 'ተጫወቺ' የሚል ነበር::

'ተጫወቺ' ብዬ ልናገር ስል አሁንም በግራ አይኔ ጥግ እጅዋ ከአፍዋ ተምዘግዝጉ ወርዶ ጭኗ ላይ ሲያርፍ ታየኝ::

ቀደም ሲል ብልጭ ያለው ጌጥ ይሁን እርጥበት ነገር ባለመኖሩ፤

'አይኔ ይሆናል' አልኩ::

እንግዳዋን ለመርሳትና ማንበቤን ለመቀጠል ሙከራ ሳደርግ የአጎቴ መኝታ ክፍል ጣውላ በር ከውጭ ሲከፈት ተሰማኝ::

'አሁን እማማ ብትመጣስ?' አልኩ በሃሳቤ.

ያነበብኩት የመሰለኝን አንድ ገጽ ስገልጥ የሚንጠራራው የፍሬ ሕይወት አንድ እግር (ቀኙ ይሁን ግራው ዘሩን ያልተረዳሁት) የተቀመጥኩበትን ፍራሽ በቀስታ ነክቶት ቆመ:: ቀስ አድርጌ በአይኖቼ ጥግ አየሁ:: ተረከዙ ረገርም የኾነ ነጭ ጫማ አድርጋለች:: አይኖቼን በቀስታ ወደ ላይ ወሰድኩ.....እንዲያመቸኝ ከመፅሐፌ የገፀ እናት ላይ ያለ መስመር የሚያነብ በመምሰል ቀስ እያልኩ ደረጃ በደረጃ ወደ ላይ ስወጣ ያደረገችው ረገርም ካልሲ ጉልበቷ ላይ ሲደርስ አቆመና ቀሚሱ ደርዝ ላይ በፍቅር የተለጠፈ ነጭ የውስጥ ልብስ አየሁ::



@BOOKALEM

በመደናገጥ አይኖቼን በትክክል ወደ መጽሐፉ መለስኩ::

'ብትቆም ምን ይመስላል?' ከሚማምችዋ ጋር በሃሳቤ ልበላት ሞከርኩ:: የዘረጋችውን እግሯን ሰበሰበችና በሃይል ወደ ውጭ ተነፈሰች:: ከእግሯ በላይ ያለው ገላዋን ለማየት ጓጓሁ:: ማንበቢያ መቀመጫዬ እንዳልተመቸኝ በመምሰል በመንቃነቅ ተስተካከልኩና በጎሪጥ ደብዘዝ ባለው ብርሃን ውስጥ ወደሚነቃነቀው ምስልዋ አይኖቼን ጣልኩ.....ትንፋሼ ለትንሽ ጊዜ እጥር እጥር አለና የተለመደ እርምጃውን ቀጠለ:: ወላ ታላላቅ ጡቶች አሏት:: የለበሰችውን ስስ ቀሚስ በጣጥሰው ለመውጣት እንደዛቱ ሁሉ ያልተከለሉበት፣ ያልተጋረዱበት መሳሪያ የለም:: በታላቅ ልምምጥና ማባበል እንደተያዙ ዓይነት:: ቢያመልጡባትስ?......ከደረቷ ላይ ተነስተው ብር ቢሉ በአየር ላይ......እስዋ ቆማ ስታለቅስ ሺህ ወንዶች በተለይ ጋሼ ረዥም ኮቱ ከኋላው እየተውለበለበ---ጥዝዝዝ---ወደ አየር ውስጥ---ተከትለዋቸው::

ቦርሳዋን ከጠረጴዛ ላይ አነሳች......ከፈተች::......ጆሮዬ ቀጥ ብሎ ያዳምጣል:: ቆሻሻ ከአፍንጫዋ አወጣች::

ፊቷን ማየት ጓጓሁ::

ቀና ለማለት በአእምሮዬ ምክንያቶች ማሰላሰል ጀመርኩ::

'ታዲያስ!' ብላት

ድሮ የት አውቃታለሁ::

'ስምሽን ማን አልሽኝ?' ልበላት

'ኖ'[1] ለእኔ ግድ አልሰጠውም......ከአንድ ጊዜ በላይ መንገር አያስፈልግም' ብትል

'ከአጎቴ ጋር ከተዋወቃችሁ ቆያችሁ?' ልበላት

'እም! /ወይም አልቆየንም/' ብላኝ---ለእኔ፣ በልብዋ ግን፡ 'ምን አገባው:: አጉቴን አይጠይቅም' ብትል::......'ደሞስ አጉቱ ስለ እኔ ሳይነግረው እንዴት ቀረ? አይወደኝም ማለት ነው?---አጎቴ' ብትልስ

'ተጫወቺ' ብልስ

'ምን ጅሉ ነው:: የተባለ ይላል' ብትለኝስ

በዚህ የሃሳቦች (የብትለኝና የብላትስ) ንትርክ ረዢም ጊዜ ያሳለፍኩ መስሎኝ ከፈጠርኩት ኩንስንስ ዝምታ ጋር ተደባልቆ እፍረት ወረረኝ:: ፊቴንም ከማነበው መጽሐፍ ተቃንቶ ሌላ ነገር ላይ ሲያፈጥ (ገረባና የሲጋራ ፓኮ ላይ) በማግኘቴ አፈርኩ:: ቶሎ ብዬ ምንም ትዕይንት ወደሌለው ፍራሼ አጉነበስኩ::

---

[1] አይ (እንግሊዘኛ)

የአጐቴ ፉጨት ከመኝታ ቤቱ አለሁበት ድረስ ይሰማል:: ሁሌ ጊዜ የሚያፏጯት ዜማ ናት:: ጠዋት ከአልጋው ሲነሳ ፊቱን ሳይታጠብ ፒጃማውን እያወለቀ ያፏጫታል......

ከእናቱ ጋር ተከራርፈው እጁን ኪሱ ከቶ ወደ ውጭ እየወጣ ያፏጫታል......

በእልህ ተከራክሮ ቀይቶ ቢረታም ባይረታም......ያፏጫታል::

«......ማማዬ......ማማዬ......አንቺ ልጅ ማማዬ»

ፍርሃት ካለሁበት ቦታ ስላሳደደኝ ዜማው ውስጥ መንኩሼ እያዳመጥኩት ነበር::

የልጅቷ የአንድ እግሯ ጣቶች ይነቃነቃሉ:: ሆን ብላም ይሁን አይሁን እግሯንም ጣቶችዋንም ታነቃንቃለች::

በልብዋ: 'ከፈራ የአንሶላውን ጫፍ ማነቃነቄን መነሻ በማድረግ ቀና ብሎ አያየኝም?' ትል ይሆናል::

"ዴቭ ተጫወቱ!" አጎቴ ከመኝታ ቤቱ ትዕዛዝ የመሰለ ነገር ጮኸ::

ክፍሉን እያዘጋጀ መኾን አለበት:: ምራቄ ትን ሊለኝ ነበር:: እስዋም እንዳልተመቻት ያህል ተነቃነቀች:: የተቀመጠችበት ወንበር ተንጣጣ::

*ማማዬ......ማማዬ ......ፉጨት*

ቴፑ......ቴፑ ትዝ አለኝ::

ድምፁ የጠፋውን ቴፕ የምከፍት መስዬ ከተቀመጥሁበት ወደ ፊት ተወጥሬ የምፈልገውን ከፈፀምኩ በኋላ ስመለስ በጨረፍታም ቢሆን ፊቷን ማየት እችላለሁ ብዬ ገመትኩ:: እንደዚያ ማድረጌን የምታውቅብኝ መስሎኝ ጥቂት ብፈራም ድርጊቱን ለመፈፀም ስዘጋጅ የአጎቴ ፉጨት ከየት እንደመጣ ሳላውቅ መኝታ ቤቴ በር ላይ አንባረቀ::

ያጠራቀምኳትን ትንሽ ድፍረቴን ድንጋጤ ሰረቃት::

በሩን ሳያንኳኳ በርግዶ ገባ:: ፍሬ ሕይወት ከተቀመጠችበት ተነሳች:: ለማየት የጓጓሁት ገጽዋ ለጥቂት አመለጠኝ:: ፀጉሯ ወገቧ ላይ ይደርሳል:: እቤት ውስጥ እንኳን ነፋስ እንደነካው ሐር ይንዘረዘራል::

"ተጫወታችሁ? ለምን ሙዚቃ አልከፈትክም?" አለኝ::

መልስም ሳልሰጠው መጽሐፌን ወደ ጐን ወርውሬ ፊት ለፊቴ ያለ ግድግዳ ላይ አፈጠጥኩ:: ጉንጬ ውስጥ ያስቀመጥኩት ጫት

(ግቢ...



@BOOKALEM

ሳላሳምጠው ቆይቶ እንደጠጠረ ታወቀኝ:: ባመልካች ጣቴ ከጉንጩና ከመንጋጋዬ መሃል ፈንቅዬ አውጥቼ ክፍሉ እስኪደነቁር ድረስ ማላመጥ ጀመርኩ::

ምን እንደማስብ መጀመሪያ አልታወቀኝም:: ቀጥሉ ግን የፍሬሕይወት የተጎረደ፣ ጠንቅቄ ያልተማርኩት ትዝታ.....ከአእምሮዬ ጀርባ ገላዎችዋ ተገንጣጥለው ለየብቻቸው መጡ......

ነጭ ጫማ ያደረጉ እግሮቿ ብቻቸውን ምንም አካል ሳይሸከሙ እየተራመዱ መጥተው ፊቴ ቆሙ:: ከሌሳ አትጣጫ......የለበሰችው ቀሚስ ከባሕር እንደወጣ ሁሉ ብቻውን ውሐ እያንጠባጠበ መጥቶ እግሮቿ ላይ ተንሳፎ ቆመ::

ጡቶቿ ሸሚዝ ለብሰው እንደባልና ሚስት እርግቦች ከሰማይ ወርደው የተንሳፈፈው ጉርድ ቀሚሷ ላይ ቆሙ:: ምስሉ ዞረና ከኋላው ረዥም ፀጉር በቀለበት......ጥቁር፣ የሚንቀጠቀጥ፣ ኮንዲሽነር የጠባ፣ ከመሃሉ በቀይ ላስቲክ የተሰበሰበ ረዥም ፀጉር::

የአይኖቼን ከዳኖች በጣም በመጨፈን በሕሊናዬ ለፍሬሕይወት የፊት ገፅ ልፈጥርላት ፈለግሁ......

ጠመም ያለ ረዣዥም አፍንጫ......ትንንሽ አይኖች፣ ስስ ከንፈሮች፣ እንቁላል ቅርፅ ፊት:: ይሔን ግምት ያኔውኑ እረሳሁት::

አጭር ደፍጠጥ ያለ አፍንጫ......፣ ሞላ ሞላ ያሉ ከንፈሮች አራት ማእዘን ቅርጽ ፊት:: ይሔንንም ቶሎ ዘነጋሁት::

ብዙ ዐይነት ፊቶች በአእምሮዬ ውስጥ እንደ ሲኒማ የትዕይንት ገመድ እየተተረተሩ አለፉ::

መብራት አብርቼ በጋቢዬ ተከናንቤ በጀርባዬ ተኛሁ:: ባዶ አየር ውስጥ አፍጥጬ ጥቂት እንደቆየሁ የአጉቴ ሥም ከመኝታ ክፍሉ በማያምረኝ ሁኔታ ተደጋግሞ ሲጠራ ሰማሁት::

የማላምጠውን ጫት አሽቀንጥሬ ተፍቼ እተከናነብኩት ጋቢዬ ውስጥ ማጉዋጨት ጀመርኩ---

*ማማዬ......ማማዬ......ሽረ ተይ ማማዬ*

ግጥሞቹ ጠፉኝ:: አዝማቹን ብቻ ለረዥም ጊዜ ቀጠልኩበት::

---- // ----

*የካቲት 1975*
*አዲስ አበባ*

@BOOKALEM

# ዘላን[2]

ተሻለ አደፍርስ በግንቡ ላይ በእጆቹም፣ በእግሮቹም እየቧጠጠ ወጣና አንድ ክንድ ያህል ወደ ጐን ስፋት ያለው ቦታ አግኝቶ ተጋደመ:: አጠገቡ የቆሙት የጽድ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸውን እያወናጨፉ ሽብሽባ ላይ ያሉ ሎጋ እንስት አድባሮች ይመስላሉ......የግንቡ ቅዝቃዜና ሽካራነት በአንድ ጐኑ አላስተኛ አለው:: በሆዱ ተምበለበለና ፊት ለፊቱ ተመለከተ:: የአጥሩ በር መግቢያ ዳርና ዳር የተተከሉት የደረቀ ሰንባ የሚመስሉ መስታወት የለበሱ አምፖሎች በዚያ ጨለማ ውስጥ በጥቁር ካባ ተሸፍኖ ብቻውን እንደሚሳብ የጋኔን አይኖች ያበራሉ......ከመፍራቱ የተነሳ ሙቅ ፈሳሽ ከልቡ ሥር ወደ ሆድቃው በቀጭኑ የሚንጠባጠብ መሠለው......አይኖቹ እንባ አፈለቁ---ከአንዳንድ የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ጋር ተሰብስቦ

[1] ይሄ ድርሰት «ጭጋግና ጠል» በተባለ የአጫጭር ታሪኮች መድብል ውስጥ በዚሁ አርዕስት በ1990 ዓም በሜጋ አሳታሚ ድርጅት ታትሞ ነበር። በዚያ መድብል ውስጥ ድርሰቱ የተሰበሰበበት እንጂ ይሄ የተጻፈበት ዓ.ም. አልሠፈረም። የተጻፈበት ጊዜ ለምን እንዳልሠፈረ ምክንያት አልተሰጠም። ድርሰቱ የተጻፈው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በሐምሌ 1977 ዓ.ም. ነበር። ማለት ሜጋ ያሳተመው ድርሰቱ በአስራሰባት ዓመታት ያህል ከአረጀ በኋላ ነው:: አሁን ሰፊ ድጎሳ አድርጌበት ተርቦአል። ነገር ልሒቃ ውስጥ ትንሽ ምናብ ወርውሬአለሁ:: ይሄ አሁን የምታነቡት ለውጥ የተሰነዘረው ሰኔ 1994 ዓ.ም. ውስጥ ነው:: እንደሚመስለኝ ከ17 ዓመታትም በኋላ የታሪኳ ሁለንተናዊ መልዕክት አልጠፋም። ሜጋ አሳታሚ የተጻፈችበትን ትክክለኛ ቀን ማለትም 1977ን ሰቶ/ሰርዞ በ1990 አካባቢ የተወለደች ካስመሰላት እኔስ ከውስጥ ለውጬ ዛሬ የተጻፈች ለምን አላስመስላትም? (ነገሩን ነው እንጂ ነገር ቀኑን ታውቃላችሁ)። ስለ ለውጡ ጥራትና መጠን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ከቀድሞው ታሪክ ጋር አመሳክራችሁ ደምሩና ቀንሱ።



@BOOKALEM

የሚያወራው የሠይጣኖች ታሪክ ትዝ አለው:: ምናልባት ከአጥር ግቢው ውስጥ ረዥም ጥቁር ፍጡር በቀስታ እየተራመደ መጥቶ በቆዳ ጅራፍ ጀርባው ላይ ቢገርፈውስ? ቁጭ አለ......

ከኋላው መጥቶስ በሰፋፊ እጆቹ ቢገፋውስ? ቆመ......

ዙሪያውን በፍርሃት እየዞረ ተመለከተ......ፀጥታ:: አልፎ አልፎ ቡናና ቃጫ ጭነው ወደ ከተማው ማዕከል የሚያልፉ ከወልቂጤ የሚመጡ የጭነት መኪናዎች ዝዝታ ብቻ ይሰማል......አንዳንዴ ውሾች ሪሊ ይጮኻሉ::

ተመልሶ ተጋደመ.....የድካም እንቅልፍ ወሰደው::

ርጥብ የጥቅምት ሌሊት ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው::

እንደማንኛውም ቀን ፀሐይ የምትወጣበት የምሥራቅ ሰማይ ነጭና ቀይ ኾኖአል......ሽሚዙና ቁምጣው በጤዛ ረጥበዋል......ዙሪያውን ቀና ብሎ አየ:: ቤቶች በየቦታው ሲከፈቱ ሲዘጉ ድምፅ ይሰማል......አንዳንድ ማድቤቶች ይጨሳሉ:: እንደራበው አወቀ:: ከተቀመጠበት ግንብ ላይ ወርዶ ብርድ ያኮማተራቸው እግሮቹ ወደመሩት መሄድ ጀመረ::

ሰፈሩ ሲደርስ ቤቱን ከሩቅ እያየ ቆመ:: የፊት ለፊቱ በር አልተከፈተም......ነጭ ጢስ ከቤቱ ጓሮ ይፈልቃል......ትኩስ ሻይና የሚበላ ነገር ማግኘት አለበት:: ወደ ቤቱ ጓሮ በቀስታ እርምጃ ሄደ:: እናቱ ምድጃ ዳር ተቀምጣ ሻይ ታፈላለች:: ትኩስ ንፁሕ ጨረቃ የመሰሉ የበሰሉ ዕንቁላሎች ተልጠውና በነጭ ሳህን ላይ ተደርድረው ጉም ያትጎለጉላሉ:: ለእናቱ ፊቱን በጨረፍታ እያሳያት ቆመ::

ከኋላዋ የከበዳት ነገር እሱ መሆኑን አውቃ ፊትዋንም ሳታዞር:

"የት አደርክ?"

ዝም::

"ሆድህን ልትሞላ ነው የመጣኸው አይደለም?"

ክርኑን አከከ.....አይኖቹ ተቅለበለቡ......የሚመልሰው ጠፋው......ሳትረበሽ ፊቷን ዞር አድርጋ አየችው......እሱም ትክ ብሎ አያት......ከንፈሮችዋን መጠጠች:: ይሄ ነገር—ከንፈር ሲመጠጥ......ሲሰማ እንጀቱ ውስጥ የተደበቀ ውርደት ሳይፈልገው ይቀሰቀሳል:: ሊሸከመው የማይችለው እርግማን ይሰማዋል:: በመደናገጡ፣ እርዳታም በማጣቱ፣ በመውደቁ የሳቀችበት መሰለው:: እየሮጠ ወጣ......

በእግሩ ወደ መርካቶ......

* * *

ዝርፍጥ ብላ ተቀምጣለች......ከእሰዋ ፊት ለፊት ነጫጭ ነጠላ የተከናነቡ ሶስት ሴቶች እግሮቻቸውን ወደ ፊት ዘርግተው የተረጨ ወፋፍራም ፊንድሻ መሰለዋል:: መነሻና መድረሻው የተሳከረ፣ በአጋጣሚ የሚቀላለፍ፣ በአጋጣሚ የሚለያይ፣ ተዋረዱ የተሰወረ ወሬ ሲደልዙ ቆይተው አንዷ ሴት በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ለመምታት (ለወሬው ትኩረት ለመስጠትና ስለ ሴትየዋ ወንድ ልጅ በማንሳት 'አንድ ልጅ ማሳደግ የከበደሽ ነሽ' ልትላት) ጉንጉንዋን እያከከች እንዲህ ጠየቀች:

"ልጅሽ የት ሄደ? አሁንም አትቆጭውም?" አለች

እናቱ ብርቱካን ተቆርጦ ተከርክሞ የተቀመጠ መልስዋን መናገር ጀመረች:

"ስንት ጊዜ ልቆጣው......ሴት ኖኜ አጥብቼ አልብሼ ምን ልበል እንደገና እንደ አባት ደብድቤ ነው ያሳደግሁት:: ይከብዳል የእኔ እናት"

"ትምህርት ቤት ለመሆኑ ይሄዳል?"

"ለወር ያህል ይሂድ አይሂድ አላውቅም"

......"እኔ የምልሽ አንድ ቀን ለቅሶ ላይ አግኝቼአቸው ጋሼ አሰፋ ያልባቱ ልንገርሽ......መቼም"

"ሰምቼዋለሁ እባክሽ ተሻለ 'ሠረቀ' ቢሉ እኔ አልከራከርም......አሁን የሚበላው አጥቶ ነው?"

"ምን አደረገ?" አሉ ሲላኛዋ ሴት ወፍራም ጣቶቻቸው መሃል ጥንግ ካከለችው ስኒ ርጥብ ፊኛ በመሰሉ ከንፈሮቻቸው የሚፋጅ ቡና እየሳቡ:: ሳሽጌ እንጂ ለበጎ ቸልተኛ ናቸው:: የእሳቸውን አትኩሮት ሐዳብ ካሁኑስ ለለውጥ ችሎታ አለው::

"የጋሼ አሰፋ ሚስት በቀሉ ከገበያ መጥታ ዘንቢሏን እግሯ ስር አስቀምጣ ቡና እስትጠጣ አለፈ ትላለች"

እናቱ ንግሯ እንዳልጣመት ለማሳየት ፊቷን ቅጭም አደረገች......

ወፍራምዋ ሴት አተኩሩና የቡናቸው ጠለል ምን ያህል ጣፍጦ እንደሆን ለማየት ወደ ስኒው የንግብረት አፈጠጡ::

የሚቀጥለውን ወሬ አቅቷ ያብራራችው ልጅ አይደለህም ብቻ 'አይደለሁም' አላት 'አይ አውቅሃለሁ ባለጌ......ምን ይዞ ሄደ አጣህ?' ብትለው 'አይደለሁም ምን አገባሽ' ብሎ ድርቅ 'አይ ዞሮ በል ደግሞ ልጅን አስከሆዶሽ ተብሎ ለሌላ ይነገር' ብላ ሌላ ሰው ለመጥራት ስትከጅል ከገዛችው ፖስታ አንዲት ሽንኩርት ይዞ ሮጠ......

"ምን ሊያደርገው?" አሉ አንዲት ሶስተኛ ሴትዮ የተሻለ ድርጊቱ ሳቅ ፊታቸው ላይ አምጥቶባቸው......

"ሆቴል ሄዶ በርካሽ ሸጦ ፖስቲ በላበት"......አለች የሚያስደንቅ ወሬ እናቱ ፊት እያዘነች ማውራት በመቻሏ ኩራት ተሰምቶአት......በተዘዋዋሪም 'ልጂ ከልጅሽ ይበልጣል' የጎሳ ባይመስልም ግን የጎሳ 'እንኳን ዐይንሽ ወለቀ የእኔ ባትሪ ይመስላል' አጀንዳ ነበረበት......ተናግራ ስትጨርስ አንገትዋን እየሰበቀች:: (ምን የሚያሰብቅ ነገር እንዳለ ነቢዩ ኢሳያስም የሚያውቅ አይመስልም)

ጆሮዎቿ ላይ ያንጠለጠለቻቸው ሎቲዎች ጉንጮቿዋን ይገርፋሉ......የቀይ እጅዋ ጀርባ ላይ ድፍን ክብ ንቅሳት ተጠቁራለች......ጉራዳ ሴት......ጫማዋን አውልቃ በባዶ እግሯ ኸንችና አንድ እግሯን ጉያዋ ከተተች:: በአቀማመጥዋ ረክታ ይሁን ወይ ተመልካች ያልገባው የአዛል ድካሟ ቀንሶላት ወይ ወሬዋ ተንከል ሳይመስል ዓላማውን ስለመታ......ከልብዋ ተነፈሰች......

"ለአስተማሪዎቹ መንገር ነው......ለመሆኑ ይማራል?" አሉ ጥያቄአቸውን በሌላ አማርኛ ደግመው---ወፍራምዋ ሴትዮ:: ከስኒው ሥር የቀረውን የስኳር ደለል አንጋጠው እየጠጡ::

"አስተማሪዎቹ ምን እንዲያደርጉ? የገዛኋት ደብተር ትሸጣለች..... በበነጋታው ያው እርሳሱ ጭቃ ቀለሙ አንድ ቀን አያድር......እብድ እኮ ነው......አንዳንዴ የት እንደሚያድር አላውቅም......አስተማሪ ይመልሰዋል እሱን? ሠራዊትም ከቡር ዘበኛም አይችል" ለራስዋ ከንፈሯን መጠጠችና: "እሱን ስነስርዐት ለማስያዝ ጀርባው ላይ ያልጨረስኩት ባህር ዛፍ የለም"

"እንደገና ደግመሽ ንገሪ፣ ለዲሬክተር ቢሆን ይሻላል" አሉ ወፍራምዋ ሴት ቡና እንዲጨመርላቸው ሲኒያቸውን ረከቦቱ ላይ መልሰው::

"ከገዛሁለት አምስት ደብተሮች ያቺ ናት የቀረችው" አለች ጠረጴዛ ላይ ከዛም ወደ ወለል ለመውደቅ ኩርማን ያህሏ አየር ውስጥ የሚንሳፈፍ፣ ልባስ የሌላትና በቁመቷ ለሁለት የታጠፈች ደብተር እያሳየቻቸው......

"እኔ የማድረው የኪራይ ገንዘብ እየለቀምኩ ነው......እንደ አባቱ እርኩስ ነው" ልቅሶ እንደሚጀምራት አይነት ንግግሯን አቁማ ራስዋን ደፋ አረገች፣

"ሁለተኛው ቡና ላይ ነን?" አሉ ወፍራሟ ሴት አርእስት ለመለወጥ---ቁጥሩ ባይጠፋቸውም......

ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ነገሠ:: የብርቱካን ሁለተኛ ሞላ ልጅ፣ የተሻለ ትንሽ ወንድም መሆኑ ነው ድክ ድክ እያለ መጥቶ እግሯ ሥር



@BOOKALEM

ተቀመጠ......ወፍራምዋ ሴት አዲስ የተላጨ ጭንቅላቱን አርእስት አርገው ለማሳቅ ፈልገው......

"ይሀቺ እናትህ ናት እንደው ዳግመኛ እንዳይበቅል አርጋ ከሥሩ የላጨችህ? ቀንጮም አታስቀር?" አሉ......

ብዙ ከአርእስት መራቁ ወሬውን የሚገለው የመሰላት ጉራዛዋ ሴት ብቻዋን አኩርፋ ነጠላዋን መዳበስ ጀመረች......

"ነገ ደግሜ እንግራለሁ ለትምህርት ቤቱ ከዚያ በኋላ ይበቃኛል:: እንደኸነው ይሁን"

"ልጅ ይሳሳታል ሰማሽ.....ልጅ ካላጠፋ ደግሞ......ያውም ወንድ ልጅ" አሉ ወፍራምዋ ሴት በተከፈተው በር ወደ ውጭ እያዩ......

"የሱ አቻ የለውም......ኧረ......ሲወለድ አስጨንቆኝ......አሁን ደግሞ ያቃጥለኛል......ይሙት አሁን ሳልታገስ ቀርቼ ነው?" አለች ጀበናውን የፈላ ውሃ እየሞላች......

እንደዚሀ እያወሩ እያሉ አንድ ጥላሞት በቀስታ እየተሳበ መቶቶ በሩ አጠገብ ቆመ:: ብርቱካን ጭኗ ላይ የተቀመጠ እስዋን የሚመስል ሁለተኛ ልጅዋን አቅፋለች:: ......ጎራዳዋ ሴት እናቷን ቀና አድርጋ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የአደፍርስን ፍቶ ግራፍ ትመለከታለች:: ከባድ ሳቅ ይስቃል......አምስት የሚደርሱ የፊት ለፊት ጥርሶቹ በሬዶ መስለዋል......የእሳት አደጋ ልብሱን እንደለበሰ ነው:: የሰውዬው መልክና ሁኔታ እንደመሰጣት ሁሉ ለረዥም ጊዜ ዐይኖችዋን ከሰውዬው ላይ አልነቀለችም:: የወሬ መቀስቀሻ የለበጣ ትኩረት እንደኾነ የገባው ያለ አይመስልም::

"የድሮ ባልሽ ቆንጆ ነበር" አለቻት! አትኩሮትዋን አጢዋ ወሬ ቆስቋሽ ሲጠፋ::

"ያንሳው እቴ......ይሔን ሰጥቶኝ ሔደ......ይሔን ክፋት......እንደ እሱ ክፋት......በማን ወጣ ቢሉ ይሔ......በአባቱ:: ፎቶውን የምሰቅለው ወድጄ መሰለሽ:: ተሻለ አባት እንዳለው እንዲያውቅ፣ እንዳልተደቀለ እንዲያውቅ ብዬ ነበር:: አልጠቀመም እንጂ" አለች ፍቶግራፉንም ለማየት ቀና ሳትል---ብርቱካን::

"አሁን የት ነው ያለው?"

"እንጃ አባቱን"

"ተጣልታችሁ ነው? ወይስ ምንድነው?"

"አንቺ ደግሞ ምንድነው ያለፈ ነገር እያነሳሽ......የምትጨቀጭቂአት......እንደው እኮ ጉድ ነው እናንተ......አሁን ምን ይባላል" ብለው ወፍራምዋ ሴትዮ አቋረጧት- ውይይታቸው ወደማያምር ጭቅጭቅ እንዳይለወጥ......



@BOOKALEM

"አንተስ የማነህ?" አለች ቀይዋ ጎራዳ ሴት አጎንብሳ ብርቱካን ወደአቀፈችው ሕፃን ልጅ ጉንጩን ለመንካት የተነቀሰ እጅዋን እየሰደደች።

"አ ሆይ!" አሉ ወፍራምዋ ሴት ቀደም ሲሉ ያቋረጧት የዳይሬክተሩ ጉዳይ ተመልሶ እንዳይመጣ በመፍራት በብስጩ አባባል ነገሩን ለመግታት ፈልገው......

ሴትዮዋ የደነገጠች ያፈረችም አልመሰለች።

ከመሃል: "እንዴ ማነህ አንተ?" አሉ ወፍራምዋ ሴት በር አጠገብ ሳይነቃነቅ ወደ ቆመው ጥላ እየተጣሩ......

ተሻለ የፊቱን ከፊል ብቻ አሳይቶ ወደ ኋላ ተመለሰ።

"ና......እንዴ ና እንጂ ምን ትፈራለህ?" አሉ ከተቀመጡበት ወለል ላይ ለመነሳት ምድርና አየር እየጧጠጡ።

"ልጅሽ ተሻለ ነው" አሉ ወፍራምዋ ሴት......አለመግባቱን ሲያዩ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ እሱ ሄዱ።

"ና ልጄ......ና......ቤትህ አይደለም ና" ራሱን እያሻሹ እጁን እየጉተቱ አስገቡት......እናቱ ደብቃው የነበረው ከአፍዋ ጀርባ፣ ከቆዳዋ ስር የሚንፎለፎል ቁጣዋ ገነፈለባት......

"አንተ ደነሞ ዞር በል!" እምቦሳ ልጇን ከሳይዋ ላይ አንስታ ወለል ላይ አስቀመጠች።

"ተይ አንቺ ደግሞ አትቆጪው" አሉ ወፍራምዋ ሴት የገጽዋን ሁኔታ አንብበው።

"የት ጠፋህ?!......የት አደርክ!? ደግሞ ዛሬ......የሚበሳም አውሬ የለም?» አለች እናቱ ብርቱካን።

"ተይ እንጂ አንቺ......እንዴ? ሕፃን ነሽ እንዴ?......ከልጅ ባስሽ......ና ልጄ፣ ምሳህን እስክትስጥህ ከዚህ ቡና ቁርስ ቅመስ" አሉት። ወንበር ላይ እንዲቀመጥ አድርገው ተደራርበው የተኙ እነሱ ሲቃመሱዋቸው ከነበሩት ደረቅ የስንዴ ቂጣዎች ቁና ላይ አድርገው አመጡለት።

"አትናገርም......የሆዱማ ነገር ይሆንልሃል......የት አደርክ?"

መብላት የጀመረውን ዳቦ የሚነጠቅ ስለመሰለው ሚስጥሩን ማውጣት ነበረበት። ......እናቱ ሚስጥሩን ስትሰማ የባሰ ከተናደደችስ? አልመለሰላትም። አፉ ውስጥ የከተተውን ጉርሻ ማላመጥ አቆመ......ጉሮሮው ደረቀበት......

"እዩኝ እንግዲህማ...ተንኮል ነው ይሄ አይደለም?" አለች ብርቱካን። ....

ጎራዳዋ ሴት ብርቱካንን የምትበልጥበት አንድ ነገር እንደሚኖር ከተሻለ ድንጉጥ ሁኔታ በመገመት በጉጉት የሚሆነውን ትጠብቃለች:: ብርቱካንም በቀላሉ የራሷን ውርደት መስማት የምትፈልግ ትመስላለች:: የተሻለ መውደቅ የእሷ መውደቅ አልመሰላትም:: በእስዋና በተሻለ መሃል ግን አድካሚ ግድግዳ አለ:: ይኼንን ግድግዳ ማንም እንዲያየው ትፈልጋለች:: የእሱ መውደቅ ለእሷ 'መገላገል' ይመስላታል::

"ተይው በቃ አንቺ......ብላልኝ ልጄ......" አሉት ወፍራሟ ሴት ሊያባብሉት አፋቸውን አሞጥሙጠው......

"የት አደርክ አትናገርም!!?"

"እ......እ......" መናገር ፈራ......ቀስ ብሎም፡ "እርስዎ ቤት" አለ ወደ ወፍራምዋ ሴት እያየ......

"እንዴት......እኔ ቤት?" አሉ በመገረም

"ማታ ኩቺናችሁን ከፍቼ ገብቼ"

እጃቸውን አገጫቸው ላይ አስደግፈው በሃዘንና በመገረም አዩት:: እናቱ በንዴት፣ በሃፍረት ፊቷ ቀላ:: ስፌቱ ላይ የቀረችውን ሁለተኛ ቂጣ ዳቦ በሌላ እጁ አንስቶ ያዘ......እናቱ አጠገቧ የነበረ አንድ ስኒ በሚያስገርም ፍጥነት አንስታ በእሱ አቅጣጫ ወረወረች......ለመሮጥ ዞር ሲል ጀርባው ላይ መታው:: የያዛት አንዷ ቂጣ በድንጋጤ ከእጁ ቊብጥ አፈተለከች:: እናቱ ከተቀመጠችበት ተነስታ ልትይዘው ወደ እሱ ተንደፋደፈች......ከእጁ ተፈናጥሮ የወደቀውን ቂጣ ከመሬት አንስቶ ከግቢው እየሮጠ ወጣ......ወፍራምዋ ሴትና ነገረኛ ጓደኛቸው (እንዲህ እንዲሆን እንዳልፈለገች ሁሉ) በድንጋጤ ያሉበት ፈዘው ቀሩ:: ብርቱካን የአባቱን የአደፍርስን ፍቶግራፍ ከተሰቀለበት ምስማር ላይ አውልቃ ተሻለን በሩጫ ተከተለችው::

"የእዚህ ሽንት አይደለህም መጀመሪያውኑስ......እ......እ ጠብቀኝማ እኔ ብርቱካን አይደለሁም አንተን ካልገደልኩ" (ምን ይባላል ካወጣጣች በኋላ ውርደቱን እንዳልፈለገች ሁሉ መራገም? ምንድነው ይኼ እርስበርሱ የተጋጨ ነገር?)

የቤቷ በረንዳ ላይ ስትደርስ ተሻለ ከግቢ ውጭ ነው...... የያዘችውን ፎቶግራፍ በእሱ አቅጣጫ አምዘግዝጋ ወረወረች......ለጭቃ መከለያ ግቢው ውስጥ የተደለደለ በድንጋይ የተሰራ እግር መንገድ ላይ ተሰባበረ......አሮጊቶቹ ተከትለዋት ወጡ:: ተሻለ አልነበረም:: ዓይኖችዋ ውስጥ የበቀለው የጥላቻ እሾህ ቤቱ ዙሪያ ተንዘረፈፈ:: የተዘበራረቀ ነጠላዋን እያስተካከለች ጣር ጣር እየተነፈሰች በድብቅም በቀረቀረቻት ልብዋ የአደፍርስን ዘመን እየረገመች ወደ ቤት ውስጥ ተመልሳ ገባች....(ያቺ ጎራዳ በነጠላ አፏን ጋርዳ ስትስቅ ወይም ፈገግ ስትል



@BOOKALEM

አሳየቻትም:: ወፍራሟ ሴት በጎሪጥ አጢነዋት ከንፈራቸውን እየመጠጡ በልባቸው 'አንቺ ጎራዳ ነግ በኔ በይ' ሳይሉ ይቀራሉ?)

* * *

ከአስር አመታት በፊት እንዲህ እንደ ዛሬ ፊቷ በኑሮ ውጣ ውረድ ታሽቶ ሳይፈዝ (አስቀያሚ እንኳን አይደለችም) ከዚህ ልጅ አባት ከአደፍርስ ጋር ወዳጅ ኸነች:: ኮልፌ፣ መሳለሚያና አጣና ተራ ለአጭር ጊዜ ያወራለት ዘልዛላ ፍቅር ነበር:: እዚህ አሁን አለችበት ሠፈር ቤቶች ሠርታ ለማከራየት ከመምጣቷ በፊት ምግብ ቤት ነበራት.....እናም እሱ ኮንትራት በወር እየከፈላት የሚመገብ ደንበኛዋ ነበር.....ምግብ ቤቷን ከከፈተች ጀምሮ ይሄ ቆይቶ ወዳጅዋ የኾነው የእሳት አደጋው አደፍርስ ሌላ ቦታ ሄዶ በልቶ አያውቅም.. እንደምትገምተውና ሲባል እንደምትሰማው:: (ይኼም በኋላ ስትገምት ለእሱ የሚያሽቃብጡ ወሬኞች ያባዙት ልብወለድ ሊሆን ይችላል::)

ከዚህ የምግብ ቤቷ ንግድ በቂ ገንዘብ አጠራቅማ ሽሮ ከማገንፈል፣ ምስር ከመከካት፣ ጠላ ከመጥመቅ፣ ውሃ ከመቅዳት ተገላግላ እጅና እግሯን አጥፋ ለመኖር ነበር አላማዋ......እያንዳንዷን ሳንቲም ወደ ሳጥን ወይም ወደ ባንክ ወረወረች:: ምግብ ቤትዋን በጭካኔ የምትቆጣጠር አምባገነን፣ ለትንሽ ጥፋት ረዳትዋን በግልምጫ ሲያል የምትገሸልጥ ፈታውራሪ፣ ደንበኛዎቿን ከመደለል የማትመለስ፣ ንፉግነትዋን በአቆላማጭ ቲያትር መጋረድ የለመደች......አይጠሏት ነገር ምግብዋ የሚጥም፣ አይተዋት ነገር ቲያትሯ የሚያደናግጥ ሞላጫ ኾነች::

እስዋ ሳታውቅ ግን እሳት አደጋ ጣቢያው ውስጥ የወሲብ ጀብደኛው አደፍርስ ብርቱካንን 'ጉድ ማድረግ' እንደሚችል ተወራርዶአል......

ብሬት ባርኔጣውን በብብቱ ይዞ:

"እንዲህች አይነት ሴት ቀላል ናት:: ራስዋን በግድ ያሰረች ናት:: በዚህ ዕድሜዋ ትደብቀዋለች እንጂ ወንድ ትፈልጋለች:: አይመስላችሁም? ፍርሐት እንጂ ፍላጎት አለ:: ግንባሯንማ ስታየው ያስፈራሃል:: ግንባሯን አትይ:: ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሂ..." አለ:: ከጓደኞቹ ጋር አፍ ለአፍ ገጥሞ ቆሞ:: የወንድ ትምክሕተኞች ፓርቲ::

መለሉ ቁመና ነበረው.......አፍንጫው ሥር ደሞ የተከረከመ ማንንም ሴት የሚያስደነግጥ ቾቦ የመሰለ መልካም ሽንጉበት:: ተላጭቶት ካደገ ሁለት ሳምንት የሚኾነው የአናት ፀጉሩ በመጥቆሩ የሚያብለጨልጭ......አይኖቹ በቅንድቡ ትልቅነት ተሸፍነው በእነሱ ፊንታ የሚታየው ጥቁር የጉን ሽንትር የኾነ......

እና ጉራውን ነስንሶ ሲስቅ በገላው ሙሉ የተሸከመው ወፍራም ስጋ ተንቀጠቀጠ::



@BOOKALEM

"ከቀናኝና ከተሳካልኝ የሚቀጥለውን ወር የእኔን እቁብ ትከፍላለህ፤ ካልተሳካልኝ ያንተን እከፍላለሁ"

የዚህችን የእቁብ ውርርድ ብርቱካን አልሰማችም......

ደ'ሞ አልሰማችም ብርቱኬ በአዲስ አባ አራዶች መፅሐፍ በሁሉም ገፆች ላይ እንደ ሕዳግ ማስታወሻ: *ቆንጆን ከረሳን፣ እግዜር ይርሳን* የሚል እንደተፃፈ::

ከዘጠኝ ዓመታት በፊት፣ የኾነ ቅዳሜ ማታ የኮልፌ የእህል በረንዳ ከቀን ትርምስዋ ስትፀዳ አደፍርስ አንድ ያልተከፈተ ጠርሙስ ጂን ይዞ እቤቷ ሔደ:: በዚያን ሰዓት በምግብ ቤቱ የሚገለገል ሰው ስላልነበር ተዘግቶ ደረሰ (እንደሚዘጋ አውቆ)......

በር አንኳኳ......

ብርቱካን ገና ሳትጋባ አልቀረም......ከጥቂት ዝምታ በኋላ ማንነቱን ጠየቀች:

"ማነው?"

"እኔ አደፍርስ ነኝ"

"እንዴ በዚህ ሰአት ምነው......እንደምዘጋ እያወቅህ?"

ተከፍቶለት ገባ......('ደንበኛዋን አታስከፉም' አሉ)

"እራቴን ልበላ ነው የመጣሁት"......በወረቀት እንኳን ሳይሸፍን ብብቱ ሥር እያሞቀ የያዘውን የጂን ጠርሙስ ተሸክሞ ዘወትር ወደሚቀመጥበት ቦታ እየሔደ::

"ቢያልቅስ ኖሮ" አለችው......

"ትንሽ ሽሮም ቢሆን አፍይልኝ:: የተገኘውን ጠኔ የሚገል ነገር ስሪልኝ......አንቺን ከሰዓት ውጭ ከማስቸግር ብዬ ሌላ ቦታ ብሄድ በስማአብ እቴ የሚበላ እኮ አይደለም......አንድ ሁለት ጉርሻ በልቼ...... ያው አንቺ ትሻይኛለሽ ብዬ እንዳለ ትቼው መጣሁ......ሰራተኛሽ ባትኖርም አንቺኑ እንደተረገምኩት ላስለፋሽ......የእኔ እህት"...... መውደድና ልመና እንዲሁም ለበጣ ቀላቅሎ......

ትዕቢቷን ስላበለፀገላት 'እሺ' ብላው ወደ ጓዳዋ ገባች......እዛው ሆና ታወራዋለች......

"ለመሆኑ አረቄውን ለምን ያዝከው?" አለች ወሬ ቢያልቅባት::

"አረቄ አይደለም ጂን ነው" አለማወቋን ሊነግራትና የባሕል የበታችነት ስሜት ልቦናዋ ውስጥ ሊተክል::

"ጂንም ይሁን አረቄ ለምን ያዝከው?" አለማወቋ ያላደናበራት ለመምሰል በሌላ ጥያቄ እየሸሸችው::

"ምን እባክሽ......"



@BOOKALEM

ዝም አለ......ላለመናገር የሚፈልገው ነገር እንዳለ ሁሉ::

"ምን አልከኝ?"

"ምን ያደርግልሻል" አላት

"እስከዚህ ከባድ የማይነገር ሚስጢር ነገር ነው?"

"መናገር አፍሬ ነው"

"ምን የሚያሳፍር ነገር አለው?»

"አንዲት ጓደኛዬ አለች......ከእስዋ ጋር ተቃጥሬ ነበር እጋብዝሻለሁ ብዬአት" ወደአቀጣጠለችው ክሰል ምድጃዋ ጋ መጥታ ኩርሲ ላይ ተቀመጠችና ቅር ያለው ፊቷን ወደ እሱ አዞረች......አላያትም::

የሥራ ውጥረት ረገብ ሲል አንዳንዴ በተለይ በራት ሰዓት እንደዚህ አግድም ታየዋለች:: ለራት ለራት ዐይኖችዋ ወንድ ይቀላውጣሉ:: በተለይ አደፍርስን:: ጎኑ ተደርድረው ምሳ ከሚበሉት ሰዎች ሁሉ የረዘመ ነው:: ትከሻው ስፋቱ የሁለት ሙሉ ሰዎች ቦታ ይይዛል:: አፈ ሰፊ የሚያምርም ሸንጎበት አለው:: ጥርስ-ትላልቅ ሳቁ ልብ የሚያስደነግጥ ነው:: ከንፈረ-ከባድ ሲከፍትና ሲገጥማቸውም እንደሚከደን የሸክላ ድስት ድምፅ የሚያወጡ ይመስላሉ:: አንዳንዴ ከፊሉ ተቀምጦ ምግብ ሲጠብቅ፣ ከፊሉ ጨርሶ ሲወጣ፣ እሱ ገና ጀምሮ ጎጆ ቤት የሚያክል ጉርሻ አንስቶ በሰፊ አፉ ሲዶል ማሕፀንዋ ትንፋሽ እንዳጠረው ሁሉ ያቃትታል:: ፊቱን ወደ ጣሪያው ሲሰቅል በእጁ አይበሉባ በከፊል የተጋረደ ወንዳወንድ ፊቱን ሰርቃ ስታየው አጢኖአል:: ብርቱካንን ልብ ብሎአት ይሆን? ስታየው የሚያያት ዕለት በልቦናው ውስጥ አድራለች ይሆን?

አደፍርስ ወዳጅዋ ባይሆንም ለወዳጅነት ይዛዋለች ብላ ሕሊናዋ ውስጥ በፈጠረቻት ሴት ቀንታለች:: ግራ የሚያጋባ ቅናት:: ያቺ ሴት ብትኖርም ባትኖርም:: ግራ የኾነ::

ብርቱካን መለሎ አይደለችም:: እጥር ምጥን ያለች ናት:: (በሃሳብዋ የፈጠረቻት ተቀናቃኝ ቀጭን ጠይም ረዥም ናት):: በትክክል እንገምግም ከተባለ ብርቱካን አንድ ፍሬ ቁመና ነው ያላት:: እነዚያ ትልልቅ እጆቹ መሃል ቢይዛት ምናልባት ትከሻው ትደርስ ይሆን? (ታስባለች አንዳንዴ እተኛችበት ዕንቅልፍ እምቢ ያላት ዕለት በሳብዋ መረቅ ተነክራ አንድ እጁ መዳፍ መሃል እንደ ሰርገኛ እንጀራ ጉርሻ ተጠቅላ፣ ወይ በግዙፍ ገላው ስር ለሁለት እስክትከፈል ሲሰብቃት):: በአእምሮዋ ከቁመቱ እየተለካካች ነበር:: ማሰቡን እየጠላች---የሚያጎል ነገር ባይኖርም:: እርፎ የመቀመጥ መሐላዋን ግን እየናደች ነበር::



@BOOKALEM

ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሠፈነ......

የሬዲዮውን የዘፈን ሳል የሚያሸንፍ የሚቁላላ ሽንኩርት ድምፅ ይሰማል......

"እንዳልተኛ አረግሽኝ" አለችው......በመሽኮርመም ሳቅ (እንዳልተኛ አረግሽኝ እንዳላንቀላፋ......)::

"መቀመጥ ከደከመሽ ትራስሽን አምጭና ምድጃሽ አጠገብ ጋደም ብለሽ ስሪው" አላት::

የምትጠቀምባቸውን እቃዎች በሙሉ ከጓዳዋ አምጥታ ምድጃው ዙሪያ ደረደረቻቸው......ለወጥ ሥራ አንዳንዴ ብቻ የምታወጣቸው ቅመሞች፣ ቁሳቁሶች ሁሉ አልቀሩም::

"ምንድነው ይሄ ሁሉ?" አለ አደፍርስ::

"ወጥ እኮ ነው የምሠራው" አለችው::

ቀሚስዋን ወደ ጉያዋ ሰብስባለች:: ቀያይ ጭኖችዋ ግራጫው ቤት ውስጥ የብርሐን ችቦዎች ይመስላሉ---አንድ ሰሞን በልጅነት ፍቅረኛ ለአፍታ ያህል ተነክተው የታለፉ......ግራና ቀኝም ኾነው ተራርቀው የከሰል ትኩሳት ይወስዳሉ:: የልጃገረድ ይመስላሉ:: በመቅጠናቸው ረኻም ይመስላሉ:: ክብ፣ ሰፋ ያለ የደስ ደስ ያለው ፊት አላት:: ዝቅ ብሉ ላያት ጭኖችዋ የትንሽ ልጃገረድ ነው:: አብራው እንዳለች ብቻ እንጂ ሊነካት እንደማይችል ልታሳየው ፈልጋለች:: 'ወዳጅ አለችው! ግን ቢያንስ ከእስዋ ጋ ሲሆን ትንሽ ተመኝቶኝ እንኳን እኔን ቢያስብ'---ሽሚያ ነገር:: ስለምን ቀሚስዋን ወደ ላይ ሰበሰበች? አደፍርስ በኀሪጥ ዐይቶ አፉ ውሃ ቢሞላ እና ቢደፍራት ስህተቱ የማን ነው? በየደቂቃውም ጉስጎሳውን እያጠለቀች ጭኖችዋም እየረዘሙ ጭኖችዋም እየቀጠኑ ጭኖችዋም እያባቡ......:: ከእንዲህ ዐይነቱ ሰው ጋር ልትኖር ፈልጋ ሳይሆን፣ እንደ ሌሎች ሴቶች በተራ ጥቅሻ የወደቀች ሳትሆን ተወዳጅ ወንድነቱ ፈልጎአት ያመለጠችው እንዲመስልላት---ቢያንስ 'እምቢ' ያለችው ምርጥ ቢጤ ለመሆን:: ቢያንስ እምቢታዋ በውድ ይሁን በግድ በአጋጣሚም ኾነ በስሌት ምርጥ ቢያደርጋት:: ቢያንስ ሲነጋ ሲነጋ ወንድ የሚሸሽ ገላዋ 'ተፈላጊ' እንደነበረ ብቻ ትዝ እንዲለው---የተፈላጊነት ትዝታ እንኳን ቢያድርበት:: ቢያንስ እየሸሸች ወደ ኋላ ዞር ስትል ስምዋን ወንድ ይጠራት እንደነበረ መረዳት፣ እና ፍሬ ባይወጣውም ከጓደኞችዋ ጋር ስትቀመጥ 'አልፈለኩም እንጂ' የሚል ግለ--ተረት እንዲኖራት::.

"እሱ ነገር ያው አረቄ ነው......አይደለም?» አለችው......

"የተለየ ነው......ይሄ ከፈረንጅ አገር የሚመጣ ነው......የአማርኛ ጽሁፍ እንኳ የለውም" አላት::

ክልቡ አያወጣውም እንጂ እሱን ጨምሮ ወገኑ አበሻ የተደበቀች ዝቅተኛነት እንዳለችበት.....ጦር ይመዛል እንጂ......በድብቅ የፈረንጅ ስልጣኔ እንደሚፈራ፣ በፈረንጅ እንደሚበለጥ እንደሚያውቅ......ቢማርም ባይማርም የፈረንጅ ነገር ከራሱ የበለጠ እንደሚያመልክ......

ቅመም መበተን ጨው መርጨት ድስቷን ማማሰል ቀጠለች::

ጠርሙሱን እያቃሰተ ከፈተው......

"ምነው?" አለችው

"ትንሽ ልጠጣለት" አላት ብርጭቆ ወደ ተደረደረባቸው ቡፌዎች እየሄደ......ትልቅ ብርጭቆ አንስቶ ሊቀዳበት ሲል......

"መለኪያው አይሻልህም?" አለችው

ብርጭቆውን ትቶ አንድ መለኪያ ይዞ ሄዶ እነበረበት ተመልሶ ተቀመጠ::

እስዋ ባትጠጣም ለስላሳ መጠጥና ጠላ ብቻ ይሸትባት የነበረችው ቤትዋ የፈረንጅ ጂን ስለገባባት ደስ አላት......

"በኋላ ስክረህ እንዳትረብሽ" አለችው በሳቅና በቀልድ::

"ይሄ!!" አላት ሙክ ብሎ "ይሔ እኮ አያስክርም፣ ያጫውታል እንጂ:: የአገራችንን ዳግም አደረግሽው እንዴ? ለምን አትሞክሪውም ብርቱካንዬ"

ቁልምጫውን እንዳልሰማች ሁሉ ድስቷን በኃይል ማማሰል ቀጠለች:: ቁልምጫ:: ቢዋሽም ምንም አልመሰላትም:: ይሄን የቁልምጫ ቃል በውሸት እንኳን ለመጥራት ትንሽ ፍላጎት መኖር አለበት:: ከወንድ ልጅ አፍ እንዲሁ በዘፈቀደ አይፈልቅም:: የዕውነትም ይሁን የውሸት ድለላ፣ ልብዋ የሚመኘውን ዋና ነገር ሰማ:: ስምዋ በወንድ ልሳን ከመጨረሻው ላይ ሲቆለፍ:: «ዬ» የተሰኘች ጀምበር ስሟን ቦግ ስታደርግላት:: በጥራቷ ከዋና ስምዋ ተላቃ እንደምሽት ፀሐይ የምትንበገበግ ሆሄ:: ለአፍታ የድስት ኢላማዋን ያሳታት ሐምስ:: ለጎረቤቶችዋ የምታወራው ትንሽ ጉዳይ አላት:: ቢያንስ መወደድዋን የሚያሳይ መረጃ አላት:: የምትጥም ስምዋን ይህቺ 'ዬ' የተሰካላትን በጆሮዋ ከባ አቅፋ ለመጠጣትና በስካር ለመዝለፍለፍ መመኘትዋን አልነገረችውም:: አደፍርስ ከተቀመጠበት ተነስቶ ሔዶ ሌላ መለኪያ ሞልቶ በትሕትና ሰጣት:: በመሽኮርመም፣ በመግደርደር በአመልካች ጣትዋ ጥፍር ከመለኪያው ጂን ጨለፈችና እስዋን መጠጠቻት:: አደፍርስ የብርቱካንን የአጠጣጥ ስልት ለመተቸትና በዚህም ሞራልዋን ለመስበር ትልቅ አፉን በርግዶ በሳቅ ተንዘፈዘፈ:: እንደ ጅል አይንዋን አቁለጨለጨች......

አሁንም በኃይል ማማሰል ቀጠለች......



@BOOKALEM

"እንዴ በደንብ ጠጪው እንጂ" አላት እየሳቀ::

መልስ አልሰጠችውም......

የራሱን መለኪያ ይዞ ወደተፈለቀቀው ከሰል ቀረበ......

"ምንም ጨርቅ ብደራርብ ብርዱ አልለቀኝ አለ" ጭኖችዋን ሳታየው እያየ፤ ወደ ምድጃው ብሎም ወደ እስዋ በመጠጋቱ ስልተኛ ይቅርታ እየጠየቀ::

ከሰሉን እያራገበች ቀና ብላ አየችው......

መለኪያውን በእጁ አንስቶ እየሰጣት፡ "ወዳጅ የተባለች ያቺ ሙጢ ትቆጣኝ እንጂ እንደ እናት ለምታበላኝ እህቴ ጂን ጠርሙሴን መክፈቴ አይቀር" አለ::

ከብዙ ወሬ በኋላ---ሁለቱም ድገሙት ቢባሉ ትዝ የማይላቸው ወሬ--በር ከፍቶ ወደ ውጭ ወጣ......ሲመለስ የካፖርቱ ቁልፍ ተከፍቶአል......ከላይ የብሉኬት ግድግዳ የመሰለ ደረቱ፣ እስከ እግሩ ድረስ ደ'ሞ ቢታይ ቢታይ የማያልቅ ዠርጋዳ ቁመና::

"የት ሔደህ ነው?" አለችው እንደማያውቅ:: የወሬ ጉጉቷ በከፊል ልትሰማው በፈለገች፣ በከፊል ብትሰማው ወደሚያስፈራት ነገረ-ሥራ በጨረፍታ እንዲወስዳት:: በሃሳብዋ ረዥም የሱሪ ዚፕ ታያት፣ ቢተረተር ቢተረተር የማያልቅ:: እጆቿ ለእስዋ ብቻ እንዲሰማት ኾነው ይርበተበታሉ::

"ሽንቴን ልሸና" አላት......ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጣትን መለኪያ ጨልጦ ሌላ እየቀዳ......

ሲቀመጥ አግዳሚ ወንበሩ---በአስራሁለት ሳንቲ ሚስማር የተያያዘው ሊፈርስ እንደ ከጀለ ሁሉ ሲንጣጣ......አይ ወንድ:: ይሄን ወንድ ፈርተው ሳይጠጉት:: ትፈልግ እንደሆነ ሳይጠይቃት ያጋመሰቻትን መለኪያ በጂን ሞላላት::

ስለምንድነው በዚህ በረፈደ ማታ በብቸኝነት የተገለለ፣ ወንድ ያላመነ፣ ከገንዘብ የተስማማ ገላዋን ከልጓሙ ለቃ ለፈተና የተቀመጠችው? ስለምንድነው 'ከረፈደ አልከፍትም' ብላ ቤትዋን ዘግታ ኀልማሳነት የሰበራቸው ጡቶችዋን በእቅፍዋ ጋርዳ ሰፊ አልጋዋ ላይ ተዘርግታ ያልላላችው? የሴትነት ሚስጥር ከራስዋ ከሴትዋ ተደብቆአት ይሆን? ለቀቅ ያለው ተንኮለኛ ልብዋ የውሽቱን 'ለደንበኛሽ ቅን መሆን ነው' ይላታል:: ልብዋ---ከእንዲህ ዐይነት መቀራረቦሽ የሚርቀው መሰብሰብ የለመደው ደ'ሞ ይህን እጅ--ስጥ ትንኮሳ እያቃተተ ይዋጋል::

ጂንዋን በለሆሳሰ ግን በጥልቀት መምጠጥ ቀጠለች:: ቀስ በቀስ እንዲህ ከምታውቃቸው ዐይኖቿ የተለዩ ሌሎች---እስከዛሬ



@BOOKALEM

የደፈነቻቸው ዐይኖች---ከውስጧ የብረት ሽፋሽፍቶቻቸውን ሲያነሱ ይሰማታል:: ሰፋፊ ዐይኖች:: ጥቋቁር ብሌን ያላቸው:: ታዲያ እነዚህ በግለት የሚንቦገቦጉ---በዚህም በዚያም የሚፍለቀለቅ ማራኪ ነገር የደረደረ ሐጢያተኛ ዓለም እያሳዩዋት:: የእጆችዋ ውስጠኛ ያልባቻቸዋል:: ስትሸሽ ደ'ሞ---'አበዛሁት እቴ' ብላ---አጥፋ እጋጥማ የምትጠብቃቸው ጭኖችዋ መሃል ጠንቃቃ ዘበኛ ልብዋን የሚያስደነግጥ የፍትወት ፍላጎቴ......

ራት ሲደርስ አብረው ከበሉ በኋላ በስካር እንደደከመ ሁሉ እንደ ምንም ተሸክሞ መኝታ ቤቷ ሲወስዳት የውሽትዋን ትንሽ ተፈራግጣ ግንብ ደረቱን በጥፊ ቸብቸብ አድርጋ ትንሽ ከማልቀስ በስተቀር ምንም አልተናገረችም......ዕንባ ከዐይኖችዋ ወደ ጆሮዎችዋ ጉድጓድ......ምላስ እንዴት ከሐዲ ነው? ያ ጎረቤቶቹን በንፍገት ተረብ ያራቀ ምላስ......ያ ገላ እንዴት ከሐዲ ነው? በስስቱ ራሱን ቀኝ ውስጥ ቆልፎ የያዘ:: አደፍርስ በታላላቅ ክንዶቹ ሲይዛት ገላዋ ባባ ኾነባት......ምድርስ እንዴት ራቀች? ትንፋሹስ ከላይ ሲመጣ በደረትዋ ገብቶ ሳንባዎችዋን አልደፈናቸውም? ልትጮህ ፈለገች፣ ግን ጉሮሮዋ የሰራው ድምፅ ለምን ከአይጥ ለቅሶ ተማሰለ? ጂን፣ ክክ፣ የበሬ ስጋ ጥብስ ቤትዋ አየር ውስጥ ነበሩ፣ የአፍንጫ ስሜትዋ የት የተማረው ክህደት ነው የተዘጋውና በእሱ ብብት ጠረን ብቻ የተሳበው? አደፍርስ አልጋዋ ላይ ከቁመ ሲጥላት ዐይኖችዋን ለምን ጋረደች? ለምንስ ረዥም ካኪ ሱሪውን ሲጎትት የሚንቦገቦግ ፍትወቷ የት ጉድጓድ ከርሞ ወጣ? ስለምንስ ቀሚስዋን ወደ ወገብዋ ከፍ እያደረገ ሲሰበስብ ከፊሉንም ፊትዋ ላይ ሲጥለው 'ኢድያ' ብላ አልመለሰችውም? ስለምንስ እግሮችዋን አጥፎ ቆዳው ቆዳዋን ሲነካው 'ማርያም ታንሳህ' አላለችውም? እምቢታ ሲፀነስበት ከኖረ የምንጭሯ ጀርባ ለምን የተመሰጠ ማለክለክ ተወለደ? ያ ሁሉ ካሬሜትር ወንድ ሲሸፍናት በስሉ የኖረ ፍርሐቷ 'ወይ እምላኬ' በተባለ ቃል ብቻ ተብራራ? 'የሰይጣን ስራ' ስትለው በኖረችው በዚህ ዓይነት ነገር እሱ እግዜር ምን አገባው? የተራበ ሥጋዋ እንዲያ እየተዘባረቀ---ትኑር አትኑር እንኳን ያላየቻትን የአደፍርስን ወዳጅ ቢያንስ 'ዛሬ በለጥኩሽ' አላለችም? በእሱ አለክላኪ ሳንባ፣ ከአፉም ዙሪያ በሚነሳ የበሬ ጥብስ ወጥ፣ የሳልሳና የድልህ ጠረን መሃል የመወደድ ፋክክርን ምን አመጣው?

አደፍርስ ሰኞ ጠዋት ሥራው ሲመለስ እቁቡን እንዲከፍል ጓደኛውን ጠየቀው::

ብርቱካንን ግን ፍቅር አዞራት:: ወንድ የረሱ ገላዋና ነፍሷ ተንገበገቡ:: ገፅዋ ፈካ:: ልብዋ ተከፋፈተ:: ከአደፍርስ ጋር አንድ ስድስት ወር ያህል አብረው ቆዩ:: አደፍርስም---የእሳት አደጋው



@BOOKALEM

ብርቱካንን ትቶ---እንደለመደው በየመንደሩ የተጸፌኑ ፍም ሴቶችን ለማቀጣጠል ተሠማራ……

ክዚያ ፀነሰች:: ወንድ ልጅ:: 'ተሻለ' ብላ የሰየመችው:: ከአባትህ ብትሻል ልትል::

አምስት አመት እዚያው ኮልፌ አካባቢ ከነገደች በኋላ የሚከራዩ ቤቶች ገዝታ ጎሩ መጣች:: ልጅዋ እያደገ ሲሄድ ከላይ እስከ ታች መልኩ አደፍርስን መሰለ:: አደፍርስ ያታለላት ትዝ እያላት የወለደችለትን ልጅ ጠላችው:: በመንገድ ሲተላለፉ እንደማያውቃት ሁሉ ፊቱን ሲያዞር በብስጭት ተቃጠለች:: ተሻለን እንዲህ እያጠባች ስታየው 'በመዳከም' አሳባ ስንቴ ነው ከሚጠባ አፉ ጡትዋን ስባ የወጣችው? ስንቴስ ነው የጡቶችዋን ጫፎች ግራዋ ጨፍጭፋ ውሃውን የቀባችው:: ስንቴ ነው ተሻለ ጨቅላ አፉን ጡት ሊጠባ ወደ ደረትዋ ሲያመጣ ለራስዋና ለእሱም: 'መስሎሻል' ያለችው? ፊቱን ከስክሶ ሲያለቅስስ ከት ብላ አልሳቀችበትም? ስለምን? የዚያች የስድስት ወሯ ደስታዋስ? ንፉግ እድሜ ቀስ በቀስ እንደጥለት ክር እየመዘዘ የሚያወጣው ልጅነትዋን ተጠግቶ የሰጣት ደስታ ለስድስት ወር ብትመነዘር ታንሳለች? 'ካላባበላችሁኝ ካላታለላችሁኝ አትንኩኝ' ስትል ኖራ ምኞቷ ሲደርስላት ኪሳራውን ለምን ልጇ ይክፈል? እንዲህ ልቀፍህ ስትለው ክንዶቿ ትከሻውን ዞረው ከማይገጥሙ በእሳት የሚቃጠል ከተማ ከሚያበርድ ወንድ ጋር ትንሽነቷን ለምን አዋዋለች? ጡቶቿ አደፍርስ አፍ ዋሻ ሲጠፉ የማርያምን ስም አልጠራችም? በጠዋት ትቶአት ሲሄድ ገላዋ በድካም ተሰብሮ የሱ ላብ ያረፈበት ትራስ ውስጥ ፊትዋን ቀብራ ቀኝ እጅዋን እግሮችዋ መሃል ደግና የሚንጠባጠብ ዘሩን አልሰበሰበችም? በራስዋስ ሳታፍር ያለመበገር ቃልኪዳንዋን ዘንግታ በጊዜ ደንበኞቿን አባርራ ቤትዋን ዘግታ አልጋዋ ላይ በጀርባዋ ወድቃ ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ በጉጉት አልጠበቀችም? አደፍርስ ገላዋን ዐይቶ አልጋ ጠርዝ ራቁቱን ሲቆም ጭኖቿን ግራና ቀኝ ከፍታ አልለመነችውም? ገና ለገና ስይታዩ አልበረደምና የወለድኩት የተረገመ ይሁን ማለት ምኑ ብልጠት ነው?

የሕይወትን ትብትብነትና በሸር መሞላት እየተረዳች ስትሔደ በዚያች ዕለት ምሽት አደፍርስ የሠራት ሥራ ሁሉ ተንኮል' ማስመሰል እንዳለበት ስታውቅ እንዳንዴ ከሰው ተደብቃ ታለቅሳለች::

ቤት እያከራየች መኖር ስትጀምር……ወንድ ሱስ ኽኖባ ነገር……አደፍርስ መርዝ ዘርቶባት እንዳለፈ ሁሉ ምሬትዋ በየደቂቃው እየረሳች የልጅዋን የተሻለን ት/ቤት ርእሰ መምህር ውሽ አድርጋ ያዘች……



@BOOKALEM

* * *

"ትናንትና ት/ቤት ዴስክ ላይ ተኝተህ ተገኘህ......ልክ እንደ ሌላ ነገር ለምሳሌ እንደ ዱርዬ እንደሚያስቆጥርህ አታውቅም?" አለው ዳይሬክተሩ(ርዕሰ መምህሩ) ተሻለን በቁጣ እያየው......

ሌሎች ሁለት አስተማሪዎች ርእሰ መምህሩ ጠረጴዛ ፊት ለፊት የብረት ወንበሮች ስበው ተቀምጠዋል......ተሻለ ከእነሱ አንድ ሁለት እርምጃ ራቅ ብሎ ጀርባው ግድግዳ እየታከከ ቆሞአል::

ርእሰ መምህሩ ሞላ ያለ ተክለ ቁመናና መሃከለኛ ዕድሜ ላይ ያለ ቀይ መላጣ ሰው ነው.....ሉጫ ፀጉሩን ከኋላ ጉትቶ በማበጠር ከግንባሩ ከፍ ብሎ ያለውን መላጣ ለመሸፈን ሞክሮአል---ከቀጭን ጠፍጣፋ የፀጉር ጣውላ ሥር የጭንቅላቱን ቆዳ አልቦታል......ሁሌ ያልበዋል::

"አትናገርም?" አለ ደገመና:: ሁለት ክንድ ርዝመት ያለው እንደ መግረፊያ የሚያገለግለውን ቀጭን ጉማ በእርጋታ ጠረጴዛ ላይ እንደ ተጋደመ በዓይኖቹ እየገረመመ:: ለተሻለ በዓይን ሽሙጥ እያሳየው::

"ማደሪያ የለኝም"

"እናትህ ከእስዋ አልፎ ለሌሎች ማደርያ ትሰጥ የለም?"

"እፈራታለሁ" አፍንጫውን እያከከ

"ምን ያስፈራሃል?" አሉ እቶ ለገሰ የተባሉ አስተማሪ (ሆም ሩም ቲቸሩ) አንድ ዐይናቸው ሸውራራ......መሬት ሲያዩ ጣሪያ የሚያዩ፣ ጣሪያ ሲያዩ መሬት የሚያዩ የሚመስሉ......ትልቅ ፍልስፍና እንደተናገሩ ሁሉ እናታቸውን አመልካች ጣታቸው ላይ አስደግፈው: "ያጠፋሽው ከሌለ ምን የሚያስፈራህ አለ?" አሉ::

መልስ አላገኘም:: ወይም መልሱ በአጭር የማይነገር፤ እንዲህ እንዲህ ተብሎ በቀላሉ የማይዘረዘር ስለኾነ፣ የተወሳሰበ ስፋት ያለው ስለኾነ::

"ይሔ የማይሠራው ተንኮል የለም......ባለፈው ጊዜ......" አለና ርዕሰ-መምህሩ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ልጁ ሄደ......

ተሻለ ዐይኖቹ እየተቅለበለቡ ......እጆቹን አንዴ እግሮቹ መሃል ያደርጋል......አንዴ ጭንቅላቱን ያከባቸዋል--ያልበላውን::

ሲጠጋው የርዕሰ-መምህሩ ረዥም ሰውነት እላዩ ላይ የወደቀበት መሠለው:: ማልቀስ ጀመረ......

"ደብተሩን መሽጡ አንደኛው ነው!" አለ ርዕሰ-መምህሩ......መግረፊያ ጎማው ወደ ተጋደመበት ጠረጴዛ እየሔደ::

"አ ል ተ ገ ዛ ል ኝ ም" አለ ተሻለ በለቅሶ መሃል::

ርዕሰ-መምህሩ ሴት ልጁን ለዚህ ዱርዬ ልጅ የመዳር ጭንቀት ሰርፆበት ሳይሆን ለሚያውቃትና ከልጁ የበለጠ ለሚቀርባት ለልጁ



@BOOKALEM

እናት ለብርቱካን ውለታ እየከፈለ እንደኾነ ያውቃል:: ማስተማር ይበልጣል ወይስ አልጋ? ግን ቢጥር ቢጥር ድርጊቱ ወደ ላይ ከፍ አልልለት አለ፣ ቁም ነገርና ግርማ አላበቅል አለ:: የግል ጉዳይ እንዳይመስልበት ቢለፋም ሁኔታዎች በሙሉ 'ታላቅ' እንዳይሆን ተብትበው ያሰሩት መሰለው:: ልጁን በቀጥታ ተንትኖ ሲያየው በፍፁም ያቺን ቆንጆ እናቱን ብርቱካንን የሚመስል ነገር የለውም:: በቁመቱ ከዕድሜ እኩያዎቹ ይተልቃል፣ ዐይኖቹ ሊከደኑ የደረሱ ናቸው:: የፀጉሩ ሉጫነት እንደ ሕንዶች ነው:: ጥቁር ጠይም የሚያምር ጋንግ ነው:: (አባቱን መምሰሉን ጠርጥሮ ባላየውና በማያውቀው ሰው ወንዳ ወንድ ውበት ሳይቀና አልቀረም፣ እና ብርቱካንን ባቀፋት ቁጥር በእንጎልዋ ግማሽ የዚህን አባት የምታስብም ይመስለዋል---ባይኾንም--- ባታስብም እንጎሉ ባይኖራትም):: ተሻለን ሲርበተበትና በዓይኖቹ ሲለማመጥ ሲያየው ኃይለኛና ትዕቢተኛ ነው ብሎ ወንጅሎ ሊቀጣው እንደማይችል ገባው:: በዚህ የበላይና የበታች ፍጥጫ መሃል ብርቱካን እንደገና ትዝ አለችው:: እንዴት ያን ከመሰለ ለስላሳ ገላና ሲነኩት ከሚቀልጥ ደረት፣ እጁን ጣል ሲያደርግባቸው ከሚሟሙ ሴትነቶች እንዲህ ዓይነት ዕርጉም ተወልዶ ጡት ይጠባል? እጅግ በመቆጣት፣ በማማረርና በመነጫነጭ ልጁን ከእናቱ የተለየ አድርጎ በመነጠል በተመልካች ፊት አስተዳደጉ ሳይሆን የልጁ የደም እርኩስነት ብቻ ተጠያቂ እንደኾነ ለማድረግ ቃጣው:: በቀስታና በፍትወት ወደ አልጋዋ የሚጎትታት ብርቱካን፣ በቂልነት፣ በቅንነትና በየዋህነት በመውደድም ዲቃላ የሰጠችውን፣ እዚህ አካባቢ ካለው ተራ የግጭት ትኩረት ሰርቃ በምቹ ምግብዋ ሞልታ (ቀይ ወጥዋ እንደ ዶሮ የሚያደርገው)......ቾክ ያበለዛቸው ወፋፍራም ጣቶቹ የፀዳ ምሩቅ ወገብዋን (በወላድነቱ የሞላ) ይዘው......ጉንጮችዋ እንደቲማቲም ቀልተው (ይሳማት ወይስ ይላሳት ወይስ ይከተፋት---እንደ ዘመዶችዋ)......ምድር ፍስሐ ብቻ ያለባት የምታስመስለው ብርቱካን ትዝ አለችው:: ከንፈሮችዋም አፉ ውስጥ ረጥበውና አብጠው ያጨበጭቡ ነበር......

"ደብተር ተሸክመህ ስትመጣ አላየሁም?" አለው ሶስተኛው በላይ የተባለ አስተማሪ፣የተጣመመ የሚመስል ፊቱንና የደፈረሰ አይኑን በጉጉትና በቁጣ እያገለባበጠ::

"የእኔ አይደለም"

"ታዲያ የማነው?"

"የልጆች፣ የጓደኞቼ ነው"

"እንዴት?" አለ ዳይሬክተሩ

"የኪራይ:: እ......የእነሱን ደብተር ስሸከምላቸው እንዳጠናበት ያውሉኛል"



@BOOKALEM

በላይ የተደነቀ አይነት አንድ ጊዜ አስተማሪውን ሌላ ጊዜ መምህሩን አይቶ:

"እናትህ ጠዋት እዚህ መጥተው የተናገሩት ሁሉን ነገር እንደሚገዙልህና በትክክል እንደሚያስተምሩህ ነው......»

ተሻለ የርእስ መምህሩንና የእናቱን ወዳጅነት ያውቃል.....ግን ሰውዬው ለንዝናዛ እናቱ ለብርቱካን ለምን እንደሚያደላ አልገባውም:: ምናልባት ሁሉ ነገር ረቆበታል:: እዚህ እንግዳ ጠልቆ ላይ የሰው አንዱ ችሎታ ላለው ሰው ማረገድ፣ ላማረው ማጎንበስ ባሕሉ እንደኾነ ሲገባው ሁሉን ይቅር ይል ይሆናል:: ወይም ዛሬ የሚማረው ፍርሐት ስሩን ሰዶበት ወደፊት የሰው ጫማ ስሞ እንኳን አፉን የማይታጠብ ሞላጫ ይሆን ይሆናል:: ወይም ሴት ጭን ማሻል የገባ ወንድ ታልቦ ሲነሳ ይሄን የፍስ ዝርገፋ ቁም ነገር አድርጎ እንኳን የወለደችው እናቱን ቀርቶ አገሩን እንደሚክድ ያኔ ሲረዳ.....አሁን ብዙ ነገር አይገባውም:: ገጹ ላይ የሚፈራረቀው መገረምና ፍርሐት ነው:: መገረሙን ጊዜ ይሰርዝለታል:: ከሚቁለጨለጬ ለማኝና ፈሪ አይኖቹ እንባ ፊቱን ሰንጥቆ ወረደ......

"ለመሆኑ ባለፈው ሴሚስተር ምን ነበረ ማርኩ......? እየው እስኪ" አለ ወደ በላይ ዞር ብሎ......

በላይ ከተቀመጠበት ተነስቶ የተማሪዎች ሪፖርት ካርድ ወደ ሚቀመጥበት ሄደና በላስቲክ ገመድ የታሠረ ጥራዝ ይዞ መጥቶ ተቀምጦ ፈታታና ስሙን መፈለግ ጀመረ::

"እምምም......ተሻለ......"

ሪፖርት ካርዱን ገልጦ ራሱ ሲያነብ ቆይቶ:

"አማርኛ፣ 65

እንግሊዝኛ፣ 78

ታሪክ፣ 82"

"ዝም በል ተወው በቃ" አለ ዳይሬክተሩ ሪፖርት ካርዱን ከአስተማሪው ነጥቆ ወደ ጠረጴዛው በመወርወር እየመለሰ.....

"ደብተር ከሌለው......አቤቱ አድሮ ካላጠና ይሔንን ማርክ የሚያገኘው ኮርጆ መሆን አለበት......ወይም አንተም ስክረህ ዞሮብህ ስትደምር ተሳስተህ ይሆናል" አፉ ዳርና ዳር ምራቁ ደርቆ የሻግ ቅራፊ መስሎአል......

ቲቸር በላይ ስለተወረፈ በእፍረት ተሻለንና ሌላውን አስተማሪ እያየ በአረቄ የተመላለጠ ከንፈሩን ነከሠ:: መልስ አልሰጠም::



@BOOKALEM

"ውጣልኝ አሁን" አለ ሙክ ብሎ--ክፍሉ ውስጥ ያሉት በሙሉ እስኪረብሹ ድረስ......"ዳግመኛ ስለ አንተ አንድ ነገር ብሰማ ከትምህርት ቤት ትባረራለህ" አለው::

ተሻለ እንገቱን በፍርሃት ሰብሮ ከክፍሉ ወጣ:: በላይ የተሻለ ነገር ከንከኖታል:: እየተከራየ ደብተር ማንበቡ፣ እናቱ ቤት እያከራዩች ልጅዋ ት/ቤት ዴስክ ላይ ተዘርሮ ማደሩ (የአባይን ልጅ ውሐ ጠማው) የተለየ አስደንጋጭነት ነበረው:: ተሻለን ተከትሎት ወጣና ለመጀመሪያ ጊዜ አተኩሮ አየው:: ሊጠራውና ሊያነጋግረው ቢፈልግም በዝምታ አካሄዱን፣ እንገት አደፋፉን፣ ክንዱን አጥፎ ያነቡ ዓይኖቹን አጠራረጉን፣ ነፋስ የሚያርገፈግፈው አቧራማ ጥቁር ፀጉሩን፣ ቀጫጫ አመዳም ባዶ እግሮቹን እያጠና በሐዘንና በመገረም በቀስታ ራሱን ነቀነቀ......

* * *

የአሥራ አንድ ሰአት ፀሐይ ፊቱ ላይ ታበራለች......እንደማንኛውም ቀን:: የኸነ ቦታ ቀትር ይሆናል......ጅማ ምናምን ወይ ሸበሌ:: አቧራማ ፊቱን ሠንጥቀው ያለፉት የዕንባ ጠብታዎች የሠሯቸው መስመሮች ጉንጮቹ ላይ ጠቆር ብለው ይታያሉ......

ወደ ኮቶኒ አካባቢ ጉዞውን ጀመረ............

"ተሻለ መጣህ?!» አሉት አንድ ሽማግሌ የግንብ መኖሪያ ቤት የሚያቆሙት የቀን ሠራተኞች 'አባት' የሚሏቸው......

"አዎ! አባት" አላቸው ድምፁን ዝቅ አርጎ

ቀና ብለው አዩትና:

"ለምን ዘገየህ?......ሰዎች ሁሉ ወደየቤታቸው ሄደዋል......ራትህን እዚያ ዘንድ አለልህ ብላ......ሂሳቡን በኋላ አብረን እናሰላለን" አሉት:: ያጋጠመውን ሊነግራቸው አልፈለገም:: በችግሩ ተገፍቶ እንደመጣ ያውቃሉ:: ዝርዝር ዕውቀት ግን የላቸውም:: ለእሱ ከውጭ ያለው ዓለም የተቀናበረ ነው:: እኝህን ሽማግሌ ለምኖ ቢጠለልም በኸነ በረቀቀ መልክ ከእናቱ ከብርቱካን ጋር የሚመሳሰሉበት ነገር ያላቸው ይመስለዋል:: ለራሱም እየገረመው ትንሽ ይፈራቸዋል:: ከእያንዳንድዋ ችግር ለማምለጥ የሚወስዳት መንገድ ስለምን መጥፎ ተብላ እንደምትሰየም አይገባውም:: ያስተረፉለትን ራቱን ለመብላት በር አጠገብ ቁጭ አለ......

"እቃዎቹን እኔ አስገባልዎታለሁ እርስዎ ይተኙ" አላቸው::

አንዳንዴ የኸነ የሚያምር ግን የሚያስፈራ ስሜት ይሰማዋል:: በዚያች አስር ዓመት ባልሞላቸው ጡንቻዎቹ ውስጥ ጥንካሬና ነፃነት



@BOOKALEM

እንዳለ ይገባዋል:: ገና ያልታጠበች፣ አላፊ አግዳሚ የምታስፈራ ሚስጥር የኾነበት የመሳደዱን ምክንያት ሲደርስበት አለመቻሉ ነው:: ማን ይነግረዋል? ማን ያብራራዋል? ይሄን የማወቅ ነፃነቱን የሚጎናፀፈው ሌላ ዘመን ውስጥ ይሆናል::

'አባት' የተባሉት እኚህ ሰው የሚቆረቆረው አዲስ ቤት የሚሠራበት እቃ እንዳይዘረፍ ቤቱ ጀርባ የቆርቆሮ መጠለያ ቆሞላቸው የሚጠብቁ ዘበኛ ናቸው:: አንድ ቀን ሲነጋጋ አካባቢ በማያርፉ እግሮቻቸው በግቢው ውስጥ ሲመላለሱ ተሻለ የሲሚንቶ የዘበኛ ክርታስ አንጥፎ ገና ያላለቀ ቤት ውስጥ ተጠልሎ ተኝቶ ያገኙታል......ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከተሻለ ጋር ይተዋወቃሉ:: ለቀን ሠራተኞች የሚሸጡትን ሻይና ዳቦ ሂሳብ እያስላላቸው 'አብረው ይኖራሉ'......

አንድ ቀን:

"ሰማህ ልጅ ተሻለ እኔ ከዚህ አካባቢ ሌላ ቦታ እንደው ማለቴ ከዚህ ትምህርት ቤት አካባቢ ርቄ ብሔድ ትመጣለህ?" ብለው ጠየቁት የጦር ሠራዊት ብርድ ልብስ ውስጥ ተጠቅለው ተቀምጠው......ነደ ፍሙ ከጠፋ ቁርጥራጭ የጣውላ ፍም ላይ አፍጠው::

ጉንጩን የሞላው ደረቅ ዳቦ አላናግር ስላለው ራሱን ብቻ በአዎንታ ነቀነቀ:: እሳቸው ተሻለን ወዳጅ ካደረጉ በኋላ የሆነ ሕዝብ መሃል ያሉ ይመስላቸዋል:: ከእሱ ጋር ብቻ ኾነው ሕዝብ መሃል ያሉ ይመስላቸዋል:: እንደ ቀድሞአቸው ብቻቸውን ጨረቃ ላይ አያፈጡም፣ ብቻቸውን የኮሽታ ምንጭ ለመፈለግ ጓሮና ሥርቻ አይገቡም፣ ብቻቸውን የሲሚንቶ ከረጢት ለቅመው ጉልትና አትቡስ ማቆሚያ ሄደው አይቸረችሩም......የሚወዱት 'አበባው ዘላኔአቸው' በባዶ አየር ውስጥ አይዘምትም......

አንድ ቀን ሲጨልም አካባቢ የንግድ ስሌታቸውን ጨርሰው በትርፋቸው ከረኩ በኋላ እንደለመዱት በር ላይ ቆመው መንገደኛ ለመመልከት መኪና ለማየት ሲወጡ ተሻለ 'እቤት' ቀረ......

ከደብተሩ መሃል ወረቀቶች ገንጥሎ እጅ የሚያካክል ስፋት ወዳላቸው ትናንሽ ወረቀቶች ሸነሸናቸው:: መማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሉትን የዴስኮች ብዛት በአእምሮው ቆጥሮ ስላነሰበት ወደ ቆሻሻ መጣያ ሄዶ የሲሚንቶ መያዣ ከረጢት ከሚሰራባቸው በርብራብ ከተጠረዙ ወረቀቶች ያልጎደፉትንና ያልተሸነተሩትን እየቀደደ አወጣ:: እነዚህንም በስርአት ከደብተሩ ቀዶ እንዳወጣቸው ወረቀቶች እያስተካከለ ከሸነሸነ በኋላ ከጎኑ ከምሮ እላያቸው ላይ መፃፍ ጀመረ......

አባት አልጋ ላይ ወገባቸውን ለማሳረፍ ሲመጡ ቁጭ ብሎ ሲጽፍ ያገኙታል......



@BOOKALEM

"እንዴ ዛሬስ አላበዛኸውም?" አሉት......ማንበብ እንደሚችሉ ሁሉ ወደሚጽፍበት ወረቀት አጐንብሰው ጭቃ ቀለሙ ያተማቸውን ፊደሎች እየተመለከቱ......

ተሻለ ከሌላ ጊዜ ቀድሞ በጠዋት ከእንቅልፉ ተነስቶ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ::. ክፍሉ ውስጥ በእያንዳንዱ መማሪያ ዴስክ ላይ አንዳንድዋን የወረቀት ቅዳጅ አስቀምጦ ወጣ......

ደወል ተደውሎ የትምህርት ጊዜ ሲጀምር፣ ተማሪዎች እነክፍላቸው መግባት ጀመሩ:: እሱ ከሁሉም መጨረሻ ግን ከአስተማሪው ቀደም ብሎ ገባ......ክፍሉ ውስጥ ትርምስና ሳቅ ጢም ብሎአል......

"ምንድነው?" አለው አጠገቡ የሚቀመጠውን ብዙ ጊዜ በሽክም ኪራይ ደብተር የሚያውሰውን ልጅ......

"እይማ ይኼን ተጽፎ አገኘን"......ከሲሚንቶ ቀረጢት የተቀደደ ወረቀት እያሳየው......

ተሻለ ቀድሞ እንዳልተመለከተው ሁሉ ይሄን ማንበብ ጀመረ:

*ማስታወቂያ:*
*1/ የዳይሬክተሩ መላጣ ያስጠላል:: የብርቱካን ውሽማ ናቸው::.*
*2/ ቲቸር በላይ ሠካራም ናቸው:: የኮታቸው ኪስ ተቀድዶአል::*
*3/ የሆም ሩም ቲቸራችን ዐይናቸው በመንሸዋረሩ ያስጠላሉ......*

ሆም ሩም ቲቸሩ አቶ ለገሰ በር በርግደው ሲገቡ የክፍሉ እርጭታ ተረብሾአል:: አንዳንድ ተማሪዎች ብጫቂ ወረቀቷን ይዘው ሳቅ ይለዋወጣሉ::

"ምን ሆናችሁ?" አሉ ወደ ጥቁር ሰሌዳው እየሄዱ፣ አንድ ዐይናቸውን ጣሪያው ላይ አንድ አይናቸውን ተማሪዎች ላይ አድርገው:: ተሻለ አጠገብ የሚቀመጠው ልጅ በወረቀቱ ላይ ባነበባቸው ነገሮች አስተማሪው ተደፍረው ግን መደፈራቸውን ሳይረዱ የሚያደርጉት ንቅናቄ ሳቁን አመጣበት:: ሰው ሁሉ እሳቸውን ሲያይ በሸውራራነታቸው የሚስቅ የሚመስላቸው አስተማሪ ፊታቸውን ቁጣ ቀብተው ወደ ልጁ ተጠጉ......

"ምን ያስቅሃል?" አሉት......

በፍርሃት አይኖቹን ከተወሸቀበት ዴስክ ወደ ላይ አንጋጠ አቀለጨለጨ:: ዝት አድርገው ሲያዩ እጆቹን ብጣሽ ወረቀት ላይ ጣል አድርጎአል! በሙሉ ያልተሸፈነውም ወረቀት ላይ በእጅ የተፃፈ ጽሁፍ ተመለከቱ:: ከልጁ አደነጋገጥ ያሳቀው ጉዳይ እዚያ ውስጥ መሆኑን ጠርጥረው እጁን አንስተው ከስር ያገኙዋትን ወረቀት በንጥቂያ ያህል ወሰዷት......ተማሪዎች ደነገጡ::



@BOOKALEM

አቶ ለገሰ ጆርባቸውን አዙረው ወረቀትዋን እያነበቧት ተማሪዎች የሆም ሩም ቲቸራቸውን ስሜት ማወቅ አልቻሉም ስለሂዱ ወረቀቱን ኪሳቸው ከተው ቁጣም ይሁን ደስታ የማይነበብበት ...ለገሰ ፊታቸውን ለተማሪዎቻቸው እያሳዩ ወንበራቸው ላይ ተረጋግተው ተቀመጡ......

"ማነው የፃፈው?" የተሻለ የዴስክ ጓደኛ ላይ አፍጠው......

"እኔ እንጃ......እ......እዚህ ጠረጴዛ ላይ ነው ያገኘሁት" አለ......

ወደ ተሻለ ቁጣቸውንና ጥያቄአቸውን አዞሩ......ተሻለ አልተረበሸም::

"እኔ እንደውም ሁሉም ልጆች እያዩ ነው የደረስኩት......አርፍጄ ነው የመጣሁት" አላቸው

"ደ'ሞ......ሁሉም ጠረጴዛ ላይ ነበር" አለ ልጁ::

ንዴታቸውን ውጠው በተመሰቃቀሉ ዐይኖቻቸው ሲያዩት ቆዩና በየዴስኩ እየዞሩ ሳቅ የፈጠረውን ፅሑፍ በሙሉ እየሰበሰቡ......

"ተውት በቃ መገኘቱ አይቀርም» አሉና ወረቀቶቹን ዴስካቸው ላይ ከምረው ቾካቸውን ይዘው ወደ ጥቁር ሰሌዳው ዞሩ::

መፃፍ ጀመሩ......

*__መልመጃ__*

*1/ የዩንቨርስቲው ዳይሬክተር ለማዳ ውሻ አላቸው*

*2/ ከሠካራም ሰው ቁም ነገር አይጠበቅም*

*3/ ሆሜር እውር ከመሆኑም በላይ ፈላስፋ ነበር*

*4/ ሚስት ያላገባ ሰው ውሽማ መያዙ አይቀርም*

*5/ የሸዋረገድ የኮት ኪስ ቀዳዳ ነው*

*6/ ሕፃናት የሚያስጠሉት ሰው ከሰው በላይ አይደለም*

*7/ የእድራችን ዳኛ ቲቸር መስፍን ናቸው*

*/ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች ባለቤትና .......ተሳቢውን ለይ/*

"ለፈተና የሚደመር ስለሚሆን አስባችሁ ሥሩ» ብለው ተቀመጡ::

# አራት አጨራረሶች

(አንደኛ አጨራረስ)

## ያለበት ተብላላበት

መማሪያ ክፍሉ ውስጥ የተፈጠረው ትርምስ ከስሞ ተማሪዎች መልመጃቸውን ለመሥራት ወደ ደብተሮቻቸው አጎነበሱ:: የመልመጃውን ጥያቄዎች ገልብጠው ጨርሰው መልስ መስጠት



@BOOKALEM

ሳይጀምሩ አስተማሪው እየዞሩ ወረቀቱን ሰብስበው ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አሉ:: ለሩብ ሰአት ያህል ተደፍተው የተማሪዎቹን ጽሁፍ ከተበተነው ወረቀት ጋር ሲያስተያዩ ቆይተው ተሻለ ላይ አፈጠጡ......

ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የጠፍር አለንጋ አውርደው በአየር ውስጥ ሾጥ እያደረጉ ወደ ተሻለ መቀመጫ ሄዱ:: ተማሪዎች ሁሉ ፊታቸውን ወደ እሱ አቅጣጫ አዞሩ......

"አንተ ነህ አይደለም የፃፍከው?"

ዝም አላቸው......ወደ ላይ እያንጋጠጠ እያየ......

"ውጣ!" እንገቱን ይዘው ክፍሉ ፊት ለፊት አቆሙት......

ለቅሶ እንደሚከጅለው ሁሉ አፉን እያንቃነቀ አስተማሪውን ማየት ጀመረ::

"አትሰማም......ደንቆሮ ነህ? አንተነህ የፃፍከው አይደለም?"

"አዎ!"

የቆዳ ጅራፍ ጀርባው ላይ እየደጋገመ አረፈ:: አላለቀሰም::

"ድንጋይ! ዱርዬ!......አንተ መቼ እኔን ሰምተህ ታውቃለህ፣ ልክ የምትገባበት ቦታ አለ......ዳይሬክተሩ ጋ እወስድሃለሁ" ብለውት እያዳፉ ከክፍል ይዘውት ወጡ...........

"ይሔ ለራሱም ለቤተሰቡም ለአገርም አይሆን" አለ ዳይሬክተሩ ለአስተማሪው......የተሰጠውን ብጣሽ ወረቀት ካነበበ በኋላ:: የጐማ አለንጋውን እየመቻቸ:: እንዲጠጋው ተሻለን በእጁ ጠራው......

'አንተስ ለማን ነው የምትሆን?' አለ በልቡ ተሻለ::

"እጅህን፣ እጅህን" አሉ አስተማሪው ለገሰ ቀድሞ ያላለቀሰው የተገረፈው ጀርባው ደንዳና ሆኖ ስላላመመው መስሉአቸው.....

"እጅህን ዘርጋ......» የጨው ውሃ ውስጥ ተዘፍዝፎ የደረቀ ጥቁር ጨርቅ እስኪመስል ገረፈው::

"ውጣ!" አለው ዳይሬክተሩ እርግጫ ሰንዝሮ......

በዚህ ድርጊት የተገረሙ የመሰሉት አስተማሪ አስተሳሰባቸው ፊታቸው ላይ እንዳይታወቅባቸው ቶሎ ብለው:

"ለእንደዚህ አይነቱ ልጅ ቤተሰቡን አልሰማ ካለ፣ እኛን አልሰማ ካለ ማታ ተማሪዎች ከመበተናቸው በፊት ተማሪው ፊት ይቅርታ እንዲጠይቅ እናደርጋለን" አሉት::

በብስጭት ማዕበል ውስጥ ኾኖ ሊያስተምርና መንፈስን ሊቀጣ የሚችለውን ይህን ዘወትር የሚጠቀምበትን ጥበብ ቀዝቀዝ ብለው ሲቆሙት ዳይሬክተሩ ተበሳጩና ለጥቂት ጊዜ ተከራከራቸው......

"ምን እንዲህ አይነቱን ሲአል ምድጃ ዳር አስቀምጠው 'ልገፋህ ነው ይቅርብህ' ቢሉት አይተውም......እሺ አንተ ሸውራራ ነህ እሺ እንትናም ያ ማነው በላይ እሱም ሰካራም ነው......የእኔ ለእናቱ ውሽማ መሆን ምን አመጣው? ከየት አየው? እናቱን እንኳን አያከብርም፣ አሁን ይሔ ለአገሩም አይጠቅም፣ ለራሱም አይሆን፣ እንደ አባቱ ነው ያረገኝ......አባት ለዚህ? ለዚህ??? አሁን እንዴት ይሁን?" ከወንበሩ ተነስቶ እየተንጉራደደ......

"አስተማሪዎችን ስለሰደበ አስተማሪዎች ይቅር እንዲሉት፣ የጓደኞቹን አስተማሪዎች በመጥፎ በመጥራቱ ተማሪዎችን ይቅር እንዲል......"

ነገሩ ጥሩ ቢመስልም አንዲት ክፍል ውስጥ የተፈፀመውን 1000 የሚሆኑ ተማሪዎች እንዲሰሙት ማድረግ ወሬውን ማስፋት መሰለው......

"ወሬው የሚዛመት መስሉዎት ፈርተው እንደኾነ መዛመቱ አይቀርም" አሉት ለገሰ፡፡

"ማን አለህ እሱን......እኔ የማስበው ሌላ ነበር.....ይህች ሀገር እንዲህ አይነቱን ንፍጣም የምታሳድግ ከኾነ የት ነው የምትደርሰው፣ ንጉሡ ነገሥቱም የሚለፉት እንዲሁ ቀረ እኮ ማለት ነው" አለና......'ልክ ነዎት!' የሚል መልስ ከአስተማሪው ጠብቆ ሲያጣ፡

"ማታ እንዳትረሳ......ተማሪዎች ቀድመው ከክፍል ይውጡ" ብሉአቸው......ወንበሩ ላይ ተቀምጦ በወፍራም እጁ መጨፍለቅ የለመደ ብዕሩን አነሳ......

ከአንድ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በሙሉ ወጥተው ሰንደቅ ዓላማ መስቀያው ፊት ለፊት ተሠልፈዋል......ርዕሰ መምህሩ ሰንደቁ ስር ግንባሩ ላይ በተሸበሸበው ቆዳ ከዳር እዳር በእንግሊዘኛና በአማርኛ ቁጣውን ዕፎ ቆሞአል......

ቲቸር ለገሰ የሠልፉ መሥመር ፊት ለፊት ተሻለን እየጉተቱ አውጥተው አቆሙት.....

ሁለት፣ ሶስቴ አጨብጭበው የተማሪዎች ጫጫታ ረጭ ሲል ንግግራቸውን ጀመሩ......

"እኛ እዚህ ትምህርት ቤት የምንመጣው ለመማር ነው......ለሌላ አይደለም......ቤተሰቦቻችንና አገራችንን ንጉሠ ነገሥታችንን ለማገልገል ነው......ነገር ግን ከስንዴ መሃል እንክርዳድ እንደማይጠፋ ሁሉ ጨዋ ተማሪዎች መሃልም ባለጌዎች አይጠፉም......(ተሻለ አንገቱን ደፋ...... ፊት ለፊቱ የቆሙት ተማሪዎች ሁሉ እሱ ላይ አተኮሩ......ለገሰ



@BOOKALEM

ከሸውራራቸው የበለጠ አተኩሮት የሚስብ ነገር እየተናገሩ እንደኙኝ ገብቶአቸዋል)......አስተማሪ ባይወልድም አባት ነው......ከእውቀት ምግብ ከእውቀት ማእድ ያበላል.....እንድ አትክልት ተኮትኩቶ እንደምታድግ ሁሉ እሱም ተማሪዎችን ይኮተኩታል፣ ውሃ ያጠጣል......ነገር ግን አንዳንድ ባለጌዎች (የአስተማሪው የመናገር ስሜት እየጋለ ሲሄድ በልጆቹ ፊት ላይ የመመሰጥ ስሜትም ይታያል) ፍርፎዎች ማለት ይሻላል ቢተሰባቸውን ማስቸገርና ትምህርታቸውን አለመከታተል ብቻ ሳይሆን አስተማሪዎቻቸውንም ይሰድባሉ......ተማሪ ተሻለ እውቀት የሚሰጡትን አስተማሪዎች አንዳንዶቻችሁ በተለይ ፋይቭ ኤ ያላችሁ ሳትሰሙ አትቀሩም ሰድቦአል......ይሔንን አስነዋሪ ሥራ እሱም ይሁን ሌሎች ይመሰክራሉ......"

(......ተማሪዎች እስኪሰላቹ ድረስ ንግግራቸውን ቀጠሉ...እንዴ አስተማሪውን እንዴ ተሻለን እያፈራረቁ የሚያዩት የተማሪዎች ጥንድ አይኖች ለመጨረሻ ጊዜ ተሻለ ላይ አረፉ)

ቲቸር ለገሰ አለንጋውን እያነሱ ተሻለ እግር ላይ፣ ጀርባ ላይ፣ አንገት ላይ ይጥሉት ጀመር......ተሻለ ማልቀስ ጀመረ.....የአስተማሪው የመገረፍ ስሜት እያደገ ሔደ......ተሻለ ግርፊያው ሲበዛበት መሬት ላይ ቁጭ አለ......የሚያቃጥለውን እጁን፣ እግሩን፣ አንገቱን ለመከላከል እየተፈተራገጠ......

"ይለምድሃል?" አለው ዳይሬክተሩ ከቆመበት የባንዲራ ምሰሶ አጠገብ:: ሲቃው 'በል' ላሉት ቃል ለመመለስ ትንፋሽ አልሰጠውም......

"ይለምድሃል?" አሉት ለገሰ አለንጋቸውን ተከትለው:: ቀረብ ብለው ከክሳዱ ላይ ይዘው በግድ ከተቀመጠበት መሬት ላይ ጉትተው አያቆሙት::

"አይለምደኝም!" አለ......ዛሬ የሚከዳው ግን እሱን የማይሸሸው የነገው ሁኔታ ትዝ ብሉት ማልተስ ጀመረ......

"ሙከ በል!"

"አይለምደኝም!! አይለምደኝም!!"......

ዳይሬክተሩ ባንዲራ ማውረጃውን መገመር በመዘመር ተማሪዎችን መምራት ጀመረ......

*ደሙን ያፈሰሰ ልቡ የነደደ*
*ባርበኝነት ታጥቆ ጠላት ያስወገደ......*

ሠለስቱ ቀለማት በሰንደቁ ላይ ቁልቁል በቀስታ ሲንሸራተቱ የተሻለ ልቅሶ ጨመረ......የተማሪዎች የዝማሬ ድምፅ ገነነ......

ለተሻለ ስቃይና እንግብግቦት ማንም ጆሮ አልነበረውም......



@BOOKALEM

(ሁለተኛ አጨራረስ)

# የለመደች ጣጣ

መማሪያ ክፍሉ ውስጥ የተፈጠረው ትርምስ ከስሞ ተማሪዎች መልመጃቸውን ለመሥራት ወደ ደብተሮቻቸው አንገበሱ:: የመልመጃውን ጥያቄዎች ገልብጠው ጨርሰው መልስ መስጠት ሳይጀምሩ አስተማሪው እየዞሩ ወረቀቱን ሰብስበው እተለመደ ቦታቸው ወንበር ስበው ቁጭ አሉ:: ቲቸር ለገሰ ለሩብ ሰአት ያህል ተደፍተው የተማሪዎቹን ጽሁፍ ከተበተነው ወረቀት ጋር ሲያስተያዩ ቆይተው ከክፍሉ ጀርባ የሚቀመጠው ከበደ ላይ አፈጠጡ......

ጭንቅላታቸውን ግራና ቀኝ በፍጥነት እየነቀነቁ ማዟናቸውን ሁሉም ልጆች እንዲያዩላቸው አደረጉ:: ተማሪው ጠቅላላ ከስድሳ በላይ ዐይኖቹን ወደ ጀርባ ዞር አደረገ:: ከበደ ግራ ተጋብቶ ያያል---ከቴስቱ ጋር የተያያዘ ነገር መስሉት::

«ቲቸር! ቲቸር! አልኮረጅኩም! አልኮረጅኩም» ብሉ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ:: ተማሪዎች እንደተማከሩ ሁሉ ተያይዘው በአንድነት በሳቅ ፈረሱ:: ከበደ ጉልበተኛው የገለፈጡበት ጥቂቶች ላይ 'ውጭ አስተማሪ ያድንሽ መስሉሻል' አይነት፣ ከዴስኩ ስር ቡጢ ጨብጠ እየዛተና ግልምጫውን እያሳየ የአስተማሪውን የቁጣ ውጤት በመበሳጨት ሲጠብቅ፣ አመልካች ጣታቸውን ወደ ላይ ቀስረው ወደ ፊትና ወደ ኋላ ዊን ዊን እያደረጉ ወደ እሳቸው እንዲመጣ ጠሩት::

ከበደ በመሰላቸት ከተቀመጠበት ተነሳ:: ጥፋት ተሰራ ሲባል የማንም ቀልማዳ ዓይኖች እሱ ላይ ማተኮራቸው ያበሳጨው ጀምሮአል:: የቬትናምን ጦርነት ማን አስጀመረ? ተብሉ ቢጠየቅ ከበደ መጠርጠሩ እንደማይቀር ይገባዋል:: አስተማሪው እተቀመጡበት እንደተጠጋ ግራ እጃቸውን ዘርግተው ተንከርፎ የቆመ ጆሮውን ያዙት:: በኃይል የሚቆነጥጥ ለመምሰል ፊታቸውን አጨማደዱና:

«ስንቴ ተመከርክ? ሌላ ቁም ነገር ጠፋ»......

«ምን አደረግሁ?» አለ ዋናው የቁንጥጫ ሕመም ከአሁን ከአሁን ይመጣብኛል እያለ ሲጠብቅ::

«ለምን ፃፍክ ይሄንን? ጠባይህ እንኳን መደባደብ ነበር:: ተማሪን በቡጢ አስተማሪን በነገር መደብደብ ፈለግህ? ጋዜጣ ማተምህ ነው?»

በአባባላቸው ከፊት ለፊት ያሉ ተማሪዎች ሳቅ ፈጥረው ተቀባበሉ::

አስተማሪው 'አያገባችሁም' ዐይነት ገላመጡዋቸው:: ከጀርባ ተሻለ በጉጉትና በፍርሀት የሚደረገውን ያያል::

«ምኑን?» አለ ከበደ ዐይኖቹ ፈጠው::

ከበደ በባህርዩ ታላላቆቹን የሚያከብር፣ ገና ሲጠጉት የሚያሸበርክ፣ አንገቱን ደፍቶ የሚሰማ የሚመስል ሸንጋይ ግን በአካል ከእሱ የሚያንሱትን ተማሪዎች በኩርኩም፣ በሾኬና በግፍተራ ያማረረ ነው:: ከበደ የዚህ ዐይነት ነገር እንደማይሰራ አስተማሪው ከተመከሮ ቢያውቁም፣ እጅ ፅሑፋቸው ከሚመሳሰል ሁለት ልጆች አንደኛው ከበደ ነው:: ሁለተኛው ደሞ ተሻለ ነው:: የተሻለ ፀባይ ከትምህርት ቤት መቅረትና መዘግየት ካልኾነ በተቀር ሰው ነካ ሲባል አልሰሙም:: ልጆች መጥተው 'ተሻለ ይሄን አደረገን' ብለዋቸው አያውቁም:: ከበደ «ምኑን?» ብሎ ሲጠይቃቸው፣ ለገስ በሐሳባቸው ተሻለ አልነበረም:: እንደ ከበደ ዐይነት ወስላቶች ነጋ ጠባ እየረበሹ እንዳያስቸግሩ ቢያንስ ለመቅጫ ነው የጠሩት:: ሰው መስደብ ጥፋት ነው:: ታዲያ ተሳዳቢው ሰው መቀጣት አለበት:: ሆኖም እጅግ የተቀራረቡና ተመሳሳይነት ያላቸውን የእጅ ፅሁፎች ብቻ አወዳድሮ ሰውን ጥፋተኛ ማድረግ ከብዶአቸዋል:: ያም ሆነ ይህ ቅጣት መኖር አለበት:: በከበደ ተሸፍኖ እውነተኛው ጥፋተኛ ካመለጠስ? እድሉ ነው:: ጥፋቱ ቢደረስበትና ቢያዝ ግን መቼም ቢሆን ያለቅጣት እንደማያመልጥ እዚያው ተደብቆ በተቀመጠበት ሊረዳ ያስፈልጋል::

«ምን ያልገባህ ትመስላለህ?» አሉት ረጋ ብለው::

«አልኮረጅኩም» አለ ከበደ

«ማን አለህ እሱን? ይሄን ወረቀት የበተንከው አንተ ነህ?»

«ኧረ እኔ ቲቸር አልወጣኹም»

«ታዲያ ማን ይመስልሃል?»

«እኔ እንጃ»

«ሎሌ አትሁን:: ያደረግኸው እንኳን አንተ ነህ:: የአንተ ስራ ትታወቃለች»

የጆሮው ሳንፋ መዞር እስኪያቆም ኮስተር አድርገው ቆነጠጡት:: ወፍራም የልጅ ልቅሶ ክፍልዋን ሞላት:: እያስለቀሳቸው የሚስቀው ከበደ እዬዬ ሲል ሲሰሙት ተማሪዎች (በተለይ የበደላቸው) ትንሽ ገላቸው ተጠቅላ ኳስ እስክትመስል ድረስ ከቤ እንዳያያቸው ኾነው ሳቁ::

ለገስ እጃቸውን ከጆሮው ላይ አነሱና [illegible] ላይ በጥፊ እየመቱ:

«ሒድ ተቀመጥ:: ወስላታ» አሉ::



@BOOKALEM

(ሉተኛ አጨራረስ)

## ይህቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም

መማሪያ ክፍሉ ውስጥ የተፈጠረው ትርምስ ከስሞ ተማሪዎች መልመጃቸውን ለመሥራት ወደ ደብተሮቻቸው አጎነበሱ:: የመል መጃውን ጥያቄዎች ገልብጠው ጨርሰው መልስ መስጠት ሳይጀምሩ አስተማሪው አቶ ለገሰ እየዞሩ ወረቀቱን ሰብስበው ወንበራቸው ላይ ቁጭ አሉ::

.....ግርማ ሰዋሰው የሚባል ነገር ይጠላል:: አቶ ለገሰን ራሳቸውን በሚስጢር ይጠላል:: እዚህ ት/ቤት ተመዝግቦ የገባው በቅርብ ስለኾነ ብቻ አይደለም:: አመት ሙሉ ከልቡ የተጠጋው ልጅ ያለ አይመስለውም:: የጭንቅላቱ ነገር ነው:: ጭንቅላቱ ሁልጊዜ የሚያብለጨልጭ መላጣ ነው:: የሚያብለጨልጭ መላጣ ብቻ የሚያብለጨልጭና ቆረቆራም ነው:: ልጆች አይደለም:: መላጣ፣ የሚያብለጨልጭና ቆረቆራም ነው:: ልጆች ሲጠጉትና ሲቀርቡት ትናንሽ ነጫጭ ቆቦች የመሰሉ የቅባት ደሴቶች የሸፈኑትን ጭንቅላቱን ሲያዩ በግልፅ ይደነግጣሉ:: ሊርቁትም ምክንያት ይደረድራሉ:: ርቀውትም ያዩታል:: እየተነጋገሩ ያዩታል:: አባቱን ባርኔጣ እንዲያደርግ ለምኖ በ'ወዲያ በል፣ አለበለዚያ መድሃኒቱ አይሰራም' ብለው ገላምጠውታል:: ስለዚህ ጠንካራ ተማሪ በመሆን የአስተማሪዎቹን አትኩሮት ሊስብ ይፈልጋል......ሁልጊዜ ታዲያ ትምሕርት ከመጀመሩ ግማሽ ሰዐት ቀደም ብሎ መጥቶ ከደወል በፊትም ትንሽ ቀደም ብሎ ይገባል:: ስነስርዐት ያከብራል እንጂ ትምህርቱ አይገባውም:: ከተማረውና ከሚማረው ነገር ይልቅ አእምሮው ውስጥ የተንሰራፋው ተማሪዎች ስለ እሱ ያላቸው አመለካከትና አመለካከታቸው የሚመስለው ነገር ነው:: እልፍ እላፍ ጊዜ ኳስ ተጊድነው ሲጫወቱ ለምንድነው እሱ ብቻ የተተወው? ስለምንድነው ወዳጅነታቸውን ለመፈተሽ 'ደብተር አውሱኝ' ሲል 'እባክህ እንሰራበታለን' ብለውት ሌላ ተማሪ ሲጠይቃቸው ግን የሚሰጡት? ለምንድነው ስሙ ግርማ ኾኖ 'ያ ቆረቆራም' የሚሉት?

ታዲያ እንደሁሉ ጊዜ በጠዋት ትምህርት ቤት መጥቶ ፀሐይ ሲሞቅ እንግዳ ነገር አየ......ትምህርት ቤቱ ትልቅ ግቢ አለው:: ግቢው ከውጭው ዓለም በመጀመሪያ በእሾሐም የሽቦ አጥር፣ ቀጥሎ በረዣዥምም ዕዶች፣ ለሶስተኛ ጊዜ ረዝመው በማይበቅሉ የቁጥቋጦ ዛፎችና መልካም አበቦች ታጥሯል:: ግርማ እንደ ለመደው ትምህርት እስከሚጀመር በአበቦቹና በቁጥቋጦቹ መሃል ቀዝቃዛ ሳር ላይ በእጅ ብቻ የመሄድ ስፖርት ይሰራል:: ሰርቶ ለማረፍ ቆም ሲል ተሻለን መማሪያ ክፍላቸው እየተገላመጠ ሲገባ አየው:: ምን አገላመጠው? እያለ ግርማ ራሱን ሲጠይቅ ቆየ:: ትንሽ ጠብቆ ሲዘገይበት ወደ ክፍሉ



@BOOKALEM

ወረቀት የፃፋችሁ ወይም የፃፈው ግለሰብ 'እኔ አደረግሁት' ብሎ በፈቃደኝነት እንዲቀርብ ነው:: ለዚህ አምስት ደቂቃ እሰጣችኋለሁ:: ከዚያ በኋላ ያደረግሁት እኔ ነኝ የሚል ልጅ ከጠፋ ሁላችሁም ከክፍል ትወጣላችሁ:: ከዚያ እንደገና ወደ ክፍል ትገባላችሁ:: ተመልሳችሁ ስትገቡ ግን እያንዳንዳችሁ እጃችሁን በዚህ አለንጋ አምስት አምስት እየተጠፈጠፋችሁ ነው:: ይህቺ አለንጋ እንዴት እንደምትጣፍጥ ብዙዎቻችሁ ሳታውቋት አትቀሩም::" አሉና አለንጋቸውን አየር ውስጥ ሾጥ እያደረጉ፣ እያመቻቹ ወደ ወንበራቸው ተመልሰው ዘርጋ ብለው ተቀመጡና የተማሪዎቹን ፊቶች እያቀያየሩ ማየት ጀመሩ::

ግርማ እጁን ለማውጣት ዳዳውና ቶሎ ብሎ ወደ ዴስኩ ስር መለሰው:: በጣም ደስ የሚል እንደ ከረሜላ የሚጥም ሃሳብ መጣለት:: እዚህ ውስጥ ካሉት ልጆች በሙሉ የስድብ ወረቀቱን ተሻለ እንደፃፈና ዴስኩቹ ላይ እንደደረደረ የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው:: ራሱን ግርማን ቢጨምር እንኳን ሁሉንም ተማሪ በዚያች አለንጋ ለማስገረፍ አቅዶ የጥፋተኛውን ስም ላለመናገር ወሰነ:: እሱን ቀንና ሌት በስድባቸው ሲገርፏት፣ ለምኖ ባላመጣው ቆረቆርና መላጣ ሲያበሽቁት መቼ 'ቀለል እናድርግለት!' ብለዋል? በሐሳቡ ሁሉም ልጆች ተደርድረው በአለንጋ ሲቸበቸቡ ማየት ነፍሱን በደስታ ሞላት:: ዞር ብሎ በስተግራ በኩል ከጀርባ በሩ አጠገብ የተቀመጠውን ተሻለን አየው:: ተሻለ ምንም እንዳላደረገ ሁሉ ተረጋግቶ ተቀምጦአል::

ተሻለ በእርሳሱ ዴስክ ላይ ጫረና (የተከለከለ ቢሆንም) በቁልጭልጭ ጥቁር ዐይኖቹ ተማሪዎቹን ቃኘ:: አቤቱታ ያቀረበ ወይም የተቃወመ አልነበረም:: መጀመሪያ ላይ አዝኖላቸው እንዳይደበደቡ በማሰብ ራሱን ለማጋለጥ ወስኖ ነበር:: ሲያያቸው በጥቂት ሰኮንዶች ሲጠነጥናቸው ግን መገረፍ ብቻ ሳይሆን መሰቀል እንደሚገባቸው አመነ:: ለምን? ምክንያቱም የአቅማቸውን ተጠቅመውበታል:: አስፋልት መሃል በድንጋጋይ ጎል ሰርተው እግር ኳስ ሲጫወቱ ያለቻቸውን ትንሽ የደብተር ሃብት አሸክመው አስጠብቀውታል:: ለምን በፍቅር አያውሱትም ነበር? የአቅሚቲ አሲረው ጎበዝ ተማሪነቱን አስጨንቀው ቀምተውታል:: መጥፎ የትምህርት ውጤቶች ሰብስቦአል:: እነዚያም ውጤቶች ለዘለዓለም እንዳይጠፉ ኾነው ተመዝግበዋል:: ሲያስበው እንደውም ይሄ ሁሉ ጨካኝ ሕፃን በአስተማሪው አለንጋ ቢጨፈጨፍ ወደደ:: ይባስ ብሎም ቢችል ወደ ፊት የዚህ ዓይነት ተንኮል እየሰራ የተማሪዎቹን ደደብነት ቀውስ ውስጥ መክተት ፈለገ::

አምስት ደቂቃው ተጠናቀቀና ለገሰ ከተቀመጡበት ሳይነሱ ያለምንም ማንገራገር: "በሉ ወስላታዎች:: መደበቃችሁ ነው? ሁላችሁም ወደ ውጭ ውጡና ተደርደሩ፤ ማንም ወደ የትም መሄድ

አይችልም:: ተግባባን? ጀምር!" አሉና ፊት ለፊት አጠገባቸው የተቀመጡትን ሁለት ልጆች የበሩን አቅጣጫ በያዙት አለንጋ አሳዩአቸው::

ተማሪዎች እየተከታተሉ በሰልፍ ወደ ውጭ ሲወጡ ግርማ ገና ያልተስተካከለው የሸሩ ቅንጅት አስደስቶት ጠቅላላ ቁመናው ተንዘረዘረ:: በልቡ ተሻለ ፊርቶ ግርፊያው ከማለቁ በፊት እንዳይናዘዝ ተመኘ:: እጅግ ተመኘ::

......ተማሪዎች በሰልፍ ቅነው በየተራ ከተገረፉ በኋላ ክፍል ገብተው በመጨረሻ የቀሩት እሱና ተሻለ ብቻ ነበሩ፣ አንተ እለፍ አንተ ቅደም ሲባባሉ:: ከመሃል አቶ ለገሰ ግርማን በቁጣ ጠሩት:: ግርማ መቅረብ የፈለገ አይመስልም::

"ና እንጂ አለበለዚያ ቅጣቱ ይጨምራል" አሉ አቶ ለገሰ::

"ያስፈራል" አለ ድምፁን ዝቅ አድርጎ::

"ለሁሉም እንደዚያ ነው"

"ያደረገውን ባውቅስ?" አለ ጠጋ ብሎ እሳቸው ብቻ እንዲሰሙት::

"ለምን አልተናገርከም ቀደም ብለህ? "

"ከተናገርኩበት ይመታኛል ብዬ"

"እና እሱ ማነው?" አሉ ለገሰ::

ፊቱን ወደ ኋላ ዞር አድርጎ ወደ ተሻለ እያየ

"ተሻለ ነው"

"ተሻለ?"

"አዎ"

ተሻለ የሁለቱን ንግግር ባይሰማም የኾነ ነገር እየተደረገ እንደኾነ ገብቶታል::

ለገሰ አላመኑትም:: ያላመኑበት አንዱ ምክንያት በዕርግጥ የተሻለ እናት የዳይሬክተሩ ውሽማ መኾንዋን ስለሚያውቁና እሱዋም የዚህ የተሻለ እናት መኾንዋን ነው:: እንዴት አንድ ሰው የእናቱን ወዳጅ ኣያከብርም?

ለገሰ ወደ ክፍል ተመልሰው ገቡና የእጅ ፅሑፍ ሲያስተያዩ ቆይተው ራሳቸውን ነቅንቀው ተመለሱ:: ራሳቸውን የነቀነቁት አሳፋሪ ስህተት በመስራታቸው ሳይሆን ዝምተኛ፣ ሰው መንካትና መቅረብ የሚፈራ አንድ ፍሬ ልጅ ይሄን ዐይነት ተንኮል ሊያስብ እንደሚችል በምናባቸው እንኳን መገመት ባለመቻላቸው ነው::



@BOOKALEM

"በል ወደ መቀመጫህ:: እሱን ወደሚወሰድበት እወስደዋለሁ" አሉና ልክ ገላ ለሚሟሟቀ፣ያ ዐይነት ግርማን እንደ በአለንጋቀ ጀርባው ላይ በቸልታ ቸብ አደረጉት......

"ይሔ ለራሱም ለቤተሰቡም ለአገርም አይሆን" አለ ዳይሬክተሩ ለአስተማሪው......የተሰጠውን ብጣሽ ወረቀት ካነበበ በኋላ:: የጉማ አለንጋውን እያመቻቸ እንዲጠጋው ተሻለን በእጁ ጠራው......

'አንተስ ለማን ነው የምትሆን?' አለ በልቡ ተሻለ::

"እጅህን፣ እጅህን" አሉ አስተማሪው ለገበ ቀድሞ የተገረፈው ያላመመው ጀርባው ደንዳና በመሆኑ መስሉአቸው......

"እጅህን ዘርጋ" የጨው ውሃ ውስጥ ተዘፍዝፎ የደረቀ ጨርቅ እስኪ መስል ገረፈው::

"ውጣ!" አለው ዳይሬክተሩ እርግጫ ሰንዝሮ......

ተሻለ ወገቡን እያከከ በሩጫ ከቢሮ እየሮጠ ወጣ::

በዚህ ድርጊት የተገረሙ የመሰሉት አስተማሪ አስተሳሰባቸው ፊታቸው ላይ እንዳይታወቅባቸው ቶሎ ብለው:

"ለእንደዚህ አይነቱ ልጅ ቤተሰቡን አልሰማ ካለ፣ እኛን አልሰማ ካለ ማታ ተማሪዎች ከመበተናቸው ቀደም ብለን ተማሪው ፊት ይቅርታ እንዲጠይቅ እናደርጋለን" አሉት:: በብስጭት ማዕበል ውስጥ ኾኖ ሊያስተምርና መንፈስን ሊቀጣ የሚችለውን ይህን ዘወትር የሚጠቀምበትን ጥበብ ለገሰ ቀዝቀዝ ብለው ሲቀሙት ተበሳጨና ለጥቂት ጊዜ ተከራከራቸው......

"ምን እንዲህ አይነቱን ሲአል ምድኝ ዳር አስቀምጠው 'ልገፋህ ነው ይቅርብህ' ቢሉት አይተውም......እሺ አንተ ሽውራራ ነህ፣ እሺ እንትናም ያ ማነው እሱም ሰካራም ነው......የእኔ ለእናቱ ውሽማ መሆን ምን አመጣው? ከየት አየው? እናቱን እንኳን አያከብርም? አሁን ይሔ ለአገሩም አይጠቅም፣ ለራሱም አይሆን፣ እንደ አባቱ ነው ያረገኝ ......አባት ለዚህ? ለዚህ??? አሁን እንዴት ይሁን?" ከወንበሩ ተነስቶ እየተንጉራደደ......

"አስተማሪዎችን ስለሰደበ አስተማሪዎች ይቅር እንዲሉት፣ የጓደኞቹን አስተማሪዎች በመጥፎ በመጥራቱ ተማሪዎችን ይቅር እንዲል......"

ነገሩ ጥሩ ቢመስልም አንዲት ክፍል ውስጥ የተፈፀመውን 1000 የሚሆኑ ተማሪዎች እንዲሰሙት ማድረግ ወሬውን ማስፋት መሰለው......

"ወሬው የሚዛመት መስሉዎት ፈርተው እንደኾነ መዛመቱ አይቀርም" አሉት......



@BOOKALEM

"ማን አለህ እሱን......እኔ የማስበው ሌላ ነበር.....ይህች ሀገር እንዲህ እይነቱን ንፍጣም የምታሳድግ ከኾነ የት ነው የምትደርሰው? ንጉሡ ነገሥቱም የሚለፉት እንዲሁ ቀረ እኮ ማለት ነው" አለና......'ልክ ነዎት!' የሚል መልስ ከአስተማሪው ጠብቆ ሲያጣ:

"ማታ እንዳትረሳ......ተማሪዎች ቀድመው ከክፍል ይውጡ" ብሎአቸው ...... ወንበሩ ላይ ተቀምጦ በወፍራም እጁ መጨፍለቅ የለመደ ብዕሩን አነሳ......

ከአንድ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በሙሉ ወጥተው ዓላማ መስቀያው ፊት ለፊት ተሠልፈዋል......ርዕሰ መምሩ ሰንደቅ ስር ቆሞ ግንባሩ ላይ በተሸበሸበው ቆዳ ከዳር እዳር በእንግሊዘኛና በአማርኛ ቁጣውን ዕሮ ቆሞአል.....

ቲቸር ለገሰ የሠልፉ መሥመር ፊት ለፊት ተሻለን እየጐተቱ አውጥተው አቆሙት......

ሁለት ሶስቴ አጨብጭበው የተማሪዎች ጫጫታ ረጭ ሲል ንግግራቸውን ጀመሩ:

"እኛ እዚህ ትምህርት ቤት የምንመጣው ለመማር ነው......ለሌላ አይደለም......ቤተሰቦቻችንና አገራችንን ንጉሡ ነገሥታችንን ለማገልገል ነው......ነገር ግን ከስንዴ መሃል እንክርዳድ እንደማይጠፋ ሁሉ ጨዋ ተማሪዎች መሃልም ባለጌዎች አይጠፉም......(ተሻለ አንገቱን ደፋ...... ፊት ለፊቱ የቆሙት ተማሪዎች ሁሉ እሱ ላይ አተኮሩ......ለገሰ ከሸውራራቸው የበለጠ አተኩሮት የሚስብ ነገር እየተናገሩ እንደኾነ ገብቶአቸዋል)......አስተማሪ ባይወልድም አባት ነው......ከእውቀት ምግብ ከእውቀት ማእድ ያበላል.....አንድ አትክልት ተኮትኩታ እንደምታድግ ሁሉ እሱም ተማሪዎችን ይኮተኩታል፣ ውሃ ያጠጣል......ነገር ግን አንዳንድ ባለጌዎች (የአስተማሪው የመናገር ስሜት እየጋለ ሲሄድ በልጆቹ ፊት ላይ የመመሰጥ ስሜትም ይታያል) በሚት እየጋለ ሲሄድ — ዱርዬዎች ማለት ይሻላል ቤተሰባቸውን ማስቸገርና ትምህርታቸውን አለመከታተል ብቻ ሳይሆን አስተማሪዎቻቸውንም ይሰድባሉ......ተማሪ ተሻለ እውቀት የሚሰጡትን አስተማሪዎች አንዳንዶቻችሁ በተለይ ፋይቭ ኤ ያላችሁ ሳትሰሙ አትቀሩም ሰድቦአል......ይሔንን አስነዋሪ ሥራ እሱም ይሁን ሌሎች ይመሰክራሉ......" (......ተማሪዎች እስኪሰላቹ ድረስ ንግግራቸውን ቀጠሉ)

(አንዴ አስተማሪውን አንዴ ተሻለን እያፈራረቁ የሚያዩት የተማሪዎች ጥንድ አይኖች ለመጨረሻ ጊዜ ተሻለ ላይ አረፉ)

ቲቸር ለገሰ አለንጋውን እያነሱ ተሻለ እግር ላይ፣ ጀርባ ላይ አንገት ላይ ይጥሉት ጀመረ......ተሻለ ያለቅሳል.....የአስተማሪው የመግረፍ ስሜት እያደገ ሔደ......ተሻለ ሕመሙ ሲበዛበት መሬት ላይ ቁጭ አለ ...... የሚያቃጥለውን እጁን፣ እግሩን፣ አንገቱን እያከከ......



@BOOKALEM

"ይለምድሃል?" አለው ዳይሬክተሩ ከቆመበት የባንዲራ ምሰሶ እጠገብ፡፡ ሲቃው መልስ ለመስጠት ትንፋሹ አልሰጠውም......ከባንዲራው ምሰሶ በፍጥነት ወረድ ብሎ፡

"ይለምድሃል?" አለው ደገመና......ከተቀመጠበት እጁን ይዞ በግድ ጉትቶ እያቆመው......

"አይለምደኝም!" አለ......ዛሬ የሚከዳው ግን እሱን የማይሸሸው የነገው ሁኔታ ትዝ ብሎት ማልቀስ ጀመረ......

"ጮክ በል!"

"አይለምደኝም!! አይለምደኝም!!"......

ዳይሬክተሩ ባንዲራ ማውረጃውን መዝሙር በመዘመር ተማሪዎችን መምራት ጀመረ......

*ደሙን ያፈሰሰ ልቡ የነደደ*
*ባርበኝነት ታጥቆ ጠላት ያስወገደ......*

ሠለስቱ ቀለማት በሰንደቁ ላይ ቁልቁል በተስታ ሲንሸራተቱ የተሻለ ልቅሶ ጨመረ......የተማሪዎች የዝማሬ ድምፅ ገነነ......ለተሻለ ሰቆቃ ማንም ጆሮ አልነበረውም......

ግርማ ብቻ የሚያንጓጥጡትን የክፍሉን ተማሪዎች በጅራፍ እስጠብጥቦ ፀጥ ያሰ፣ የፈራ፣ የራደና ጨዋ የመሰለ ፊቱ በደስታ ይንፈቀፈቃል፡፡ ገና የተወለደ መሰለው፡፡ አረንጓዴው የደመቀ የትምህርት ቤቱ ባንዲራ ተጣጥፎ ሌሎች ቀለማትን የደበቀ የተቀቀለ ቆስጣ መሰሉአል፡፡ አብሻቂና ጮሌ የሚመስሉትን እዚህ የተሰበሰቡትን ሁሉ በቀላሉ እርስ በርስ ማጣላት የሚችል፣ ሕፃኑ እንደ አዋቂ፣ አዋቂው እንደ ሕፃን በሆኑበት ት/ቤት በቀላሉ የሚፈራና የሚከበር ልጅ እንደሚሆን ገባው፡፡ የተሻለ ለቅሶ ለእሱ የአዲስ ዘመን ብስራት ነበር፡፡ እዚህ ተሰብስበው ባንዲራ በሕብረ--ዝማሬ የሚሳትቱት ጅሉች፣ አንደኛው ቢያበሽቀው በሌላኛው ሊያስገርፈው የሚችል ተራ ሆኑበት፡፡ እስከዛሬ እነዚህን የደደብ ስልፎችች መፍራቱ አበሽቀው፡፡ ......መዘመሩን አቁሞ ግራና ቀኝ አየ፡፡ መዘመሩን አቁሞ ኋላና ፊት አየ፡፡ መዘመሩን አቁሞ ወደ መሬት እያየ እስከ ዛሬ ስቆ የማያውቀውን ዐይነትና ከራሱ የወጣ ያልመሰለውን ፍልቅልቅ ሳቅ ሳቀ፡፡ ትኩስ የልጅነት ጆሮዎቹ በተሻለ ለቅሶ ረከተው፡፡ አእምሮውም ከወንጀለኛነት ስሜት ተገልሉ፡፡



@BOOKALEM

(አራተኛ አጨራረስ)

## የወንድ ልጅ

ማታ ስራውን ጨርሶ ከትምህርት ቤት ሲወጣ ቲፑር በላይ ለራሱ እየማለ ነበር:: የስራው ኋላ ኪስ ከሎተሪ ትኬት ጋር አዳብሎ ያጠፋቸውን ሁለት አስር ብሮች በፍፁም ወይን እንዳይጠጣባቸው:: ግን ፋሽኬት ሲያስብ ወይም ስለ ፋሽኬት ሲያወራ ወይም ሲያወሩ ሲሰማ አፉ በአምሮት ምራቅ ይሞላል፣ ሆዱ ውስጥ በንዎዝዝት ይነዳል:: በምሽት፣ ደንገዝገዝ ባለ ማታ……ወደ ከዋክብት በተንቀሰቡበት እኩለ ሌሊት ግርስሪ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጦ እንደ ወላንሳ የለሰለሰውን የአዲስአባን ጨለማ እያየ በስካር ዞር ሲልበት፣ ብብቱ አልቦት በእርጥበት ሲያዳልጥ፣ የየቀኑ ፍርሐቱ ዞር ብሎለት ደፋር ሲሆን የራሱን ውበት ያደንቃል:: ይሄ ከእሱ ውጭ ወዲያ ወዲህ የሚለውን ጠቅላላውን ዓለም ይጠላል:: ሲነጋ ግን በተቃራኒው ዐይኖቹ ቀልተው፣ ፊቱ አብጦ፣ አፉ ደርቆ ምራቁን መዋጥ ሲከብደው፣ አንጎሉ በዛገ ሐዲድ ላይ እንደሚሔድ ባቡር እየጮኸበት ድብርትን 'ይገፍ ከተፍ' ሲልበትና በሠራ ነፍሱ ሲሰርፅበት ከሰማይ እስከ ምድር ያለው ፍጡር ሁሉ 'ወድተሃል' ያለው ይመስለዋል:: ሳይከርም እዚያው በዚያው እኩል ብዛት ያለውን ያኑኑ የናቀውን ፍጡር 'የውድቀቱ' ተጠያቂ ያደርጋል::

ከጥቂት ዓመታት በፊት መጠጥ ሲጀምር አብረውት በአፍ ይላፉ የነበሩት ወዳጆቹና ሌሎች አቸፍቻፊዎች በሙሉ እየሸሹት ብቻውን መቅረቱን በእሱ ላይ የተደረገ የተቀናበረ ሴራ ያደርገዋል:: ይሄ ሁሉ ለእሱ ፕላን አለው:: እንደውም ሲጀመር አባቱ በሰው መጫወቻ እንዲሆን አቅደው ነው የወለዱት:: እንደውም በእሱ አመለካከት የአገራችን ግማሸቹ አባቶችና እናቶች የሚወልዷቸው ልጆች ለሌሎች መጫወቻ የሆኑ ፍጡራንን ነው:: ለእሱ ብዙው የአበሻ እናትና አባቶች የአሻንጉሊት ፋብሪካዎች ናቸው::

«ት/ቤት አልኮል አልኮል እየሸተተህ አትምጣ» ይሉታል:: ግን ያውቃሉ፣ ያውቃልም (ቢያንስ በእሱ ግምት) የሚያስተምራቸው ግማሽ ያህሉ ውጫጭ ከሰከሩ አባቶች የተፀነሰ እንደኾኑ:: ያውቃል የብዙዎችን ልጆች አባቶች ያገኙ ዕለት በተለይ ለልደታ ልጅ መውለዳቸውን ረስተው በየግሮሰሪው እናትና ልጅ አረቄ ወይም ፋሽኬት ደፍተው እንደ እንስሳ ለሐጫቸውን እያዝረበረቡ ወደየቤታቸው እንደሚሄዱ:: የቤታቸውን በር ሲያንኳኩ የምትከፍትላቸው ሴት በእንቅልፍ የለዘዘች ቢገፏት የምትወድቅ፣ ቢመትዋት የምትመታ፣ ሲሰድብዋት የምትንጠራራ እና ቀሚስዋ ሲገለብ በቦዘ ዐይኖችዋ ጣሪያ እያየች የባልዋን የወሲብ ስራይ ያለማንገራገር የምታብርድ ናት:: ያውቃል አላማው እነዚህ ልጆች አንጎል ውስጥ በእጅ አዙር ከመፀነሳቸው ጀምሮ



@BOOKALEM

የተተከለውን የጎርጊስ ቢራ፣ የመሎቲ ቢራ፣ የሳሪሱንና የጠጅን ክሮሞዞም ከደምስራቸው ሊያወጣ እንደነበር:: ታዲያ በበጣቸው ቁጥር ጫጫታ ያመጡበታል:: በስካራምነቱ ይሰድቡታል፣ ያሙታል፣ ያሽሟጥጡታል:: አንድ ሰው ገንዘብ ያባክናል ማለት ስድስትን በአራት ማካፈል የማይችል የሒሣብ መሐይም ነው ማለት ነውን?

እነዚያ መጠጣት ያለማመዱት ጓደኞቹ የት ሄዱ?

«የወንዶች ቤት እንሂድ» እያሉ ለጅማሮ ቪኖ በኮካ አጠጥተው ጨቅላ እንጥሉን በከረሜላ ደልለው መልሰው ደ`ሞ ሲለምድ:

«ቤት ነህ? እንደ ወንዶች ሞክር እንጂ፣ የወንድ ልጅ ሆኖ ደሞ» ብለው ከመራራ ኬሻ ቂጥ ስር አልቀረቀሩትም? እናቱ ዙሪያ እንደ ሻሽ ጌሽ አልጠመጠሙለትም? ዛሬ እነሱ የት ናቸው? አዎ ሁለቱ መድሐኒያለም ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ አስተማሪ ኾነው፣ አንደኛው ደሞ ልዑል መኮንን ኮምፕሪሄንሲቭ ምክትል ዳይሬክተር ኾኖ ሄደዋል:: እሱን 'ተዝናንተሽ አመሸሽ' እያሉ እየደለሉ፣ የቀኑበት ግን እንደሱ መሆን ያልቻሉበት በማስመሰል በማታ ትምህርት ራሳቸውን ሲያሻሽሉ ቆይተው ከዐይኖቹ ጠፉ:: አራተኛው ጓደኛው ደ`ሞ የራሱ ት/ቤት ርዕሰ-መምህር ኾኖ እንደማያውቀው ሰው ጌታው መሆኑን ሊያሳየው፣ ትምህርት ሚኒስቴር አሰራሩን ባይፈቅድም በቁንጮው እየጎተተ በዓለም ፊት ሊያሳፍረው ስለ ስካራምነቱ እያነሳ ያጣጥለዋል::

በላይ ዛሬ ሳምንቱ ኾነው---መጠጣትና ማጤስ ካቆመ:: ራሱን ለመፈተን፣ ለመፈታተን ሃያ ብሯን ከሎተሪ ቲኬት ጋር በኋላ ኪሱ ሰፍቶ ይዞአል:: ለሳምንት ሙሉ ግን ሲያስታውሳት ነበር:: በሕሊናው ይሸሻት እንጂ ከሱሪው የቀኝ ኋላ ኪስ፣ የኾነች ነፍስ አድን ሃያ ብር በቂጡ ስብ እየተሟሟቀች በከፊል ወደ ስሕተት በከፊል ወደ መልካም መንገድ ልትወስደው ተዘጋጅታለች::

እነዚያ የውሸት ጓደኞቹ መጥፎ ልማዱን ለማቆም መቁረጡን እንዲሰሙ ብሎ አጠገቡና አጠገባቸው ላሉ ወሬ አቀባይ ሰይጣናት ይሄን ስቅዱን እንዲያደርሱለት ነግሮአቸዋል:: ድሮ ጓደኛው ዛሬ ዳይሬክተር የኾነው ሰው የተረጨለትን ወሬ ለቅሞ:

«በዚህ ሰሞን መልክህም ሁኔታህም ተለውጦአል» አለው—ለሥራ ጉዳይ ብሎ ወደ ክፍል ሊገባ ሲል አስቁሞት::

ግን ምንም የተለወጠ ነገር የለም:: ሰባት አመታት ሳያቋርጥ ካንሰሩን የተከለ ሲጋራና አልኮል ያለበሰው ማድያት እንደ ዐይን አር በአፍታ አይፀዳም:: የጥርሱ አይበሉባ ቡናማ ከፌይ ጫማ ይመስላል:: ወይን መጠጣት የለመደ ደረቅ ሆዱ ገና ንፁሕ ውሐ ያስደነግጠዋል:: የተለወጠ ነገር የለም:: ዳይሬክተሩ ያናገረው 'ወሬውን ሰምቻለሁኝ'



@BOOKALEM

ለማለት እንዳኘነ ይገባዋል:: ግን ማን ለማን ስነስርዐት ያስተምራል:: ማን ወንድ ነው የትኛውን ወንድ እሴት ሊያስተምር እንጥሉን ጠራርጎ የጉሮሮውንም ሽረሪት በሙርይ ጎርጉሮ ዮርዳኖስ እየተንደረደረ የሚወርድ? ማነው ጨዋ? ማነው የጨዋ ደም ዕውነትን ኩርኩም ፊት፣ ዕውነትን መስደብ ፊት፣ ዕውነትን አላጋሮች ፊት፣ ዕውነትን አግላዮች ፊት ግንባሩን ሳያጥፍ የሚናገር? ስልቻውንም ከፍቶ ከውስጡ ብዙ ቀለም ያላቸውን የራሱን እከኮች እንድናይ አስቲሞ የሚጋበዘን?......

ዳይሬክተሩ ወጣት፣ ባላገር፣ ባለርስት ሐብታም ሚስቱን ትቶ ከፈቱዋ ከብርቱካን ጋር ሲዳራ የሚውል፣ ይሄንን ልማዱን ሰው አውቆበት እንኳን ያልሰማ መስሎ ያለማፈር የሚቀጥል፣ ይሉኝታ ቢስ ፈጣጣ እንዴት ብሎ ጨዋነትን ተራራ ላይ ወጥቶ ያስተምራል? እንኳን ሰው ተራራውስ እሺ ይላል? ለበላይ ልጅነት ብልግናዎችን ያላመዱት ሰዎችም በእሱ ጋባዥነት ጀርባ ማታ ማታ ተምረው አለቃው ኾነዋል:: በዚህም ከእሱ የተሻለ ብሩሕ አእምሮ እንዳላቸው ሁሉ በተፈለገው አጋጣሚ ይጠቆምለታል:: ጥሩ ሰው ለመባል ወሰኑ የት ይሰራል?

ይላሉ: «ፀጉሩን ሳይበጠር ክፍል ይገባል»---መላጦች እንዲህ ይሉታል::

«የኮቱ ኪስ ተቀዶ፣ ሱሪው ቆሽሾ ያስተምራል» ---የሚያስተምራቸው ግን የደሐ ልጆች ናቸው፣ የተጣፈ ካኪ ለብሰው የተመዘገቡ::

በላይ «ስለ ጨርቅና ስለ አለባበስ የሚያስብ ፎቃቃ ትውልድ ልፈጥር አይደለም» ብሎ ሊከራከር ይሞክራል:: አይዝለትም:: ሰካራም የቱ ቃሉ ሙጫ ይሆናል::

የወዳጅ ጠላት፣

የወዳጅ ጠላት እያደርስ ነው፣

የወዳጅ ጠላት አይዘዝ ነው::

ወደ መልካም ጎዳና መሄዱ ቅር ያሰኛቸው አልጠፉም:: በትንሽ ብሩሕነት ዓለም መለወጥ እንደምትችል ያውቃሉና::

መጀመሪያ ቅዳሜ ጠዋት ያደረገው ነገር ቢኖር (ለስምንት ዓመታት የዐይን ፍቅር አስይዛ እንዳያናግራት---በሰካራምነት ስሙ ስለጠፋ) ይህቺን ጨዋ የምትመስል ብርቱካን የተባለች ሴት እንደወደዳት በድፍረት ሊነግራት ነበር:: ይህቺ ሴት ቢያንስ በቀን ሶስቴ የሚንቦገቦግ ቅላትዋ ላይ ነጠላዋን ሽር አድርጋ እሱን

በምታከራየው ቤት ፊት ለፊት ስታልፍ ወይም በየወሩ የኪራይ ሒሳብዋን ሊሰጣት ቤቷ ሲሔድ ረጋ ብላ በከብ ቀይ ፊቷ ስታየው በእነዚያ ትላልቅ ቡናማ ዐይኖቿ ውስጥ ለሰኮንዶች ምርኮ ኾኖ ይጠፋል:: ይደመሰሳል:: ገንዘቧን ተቀብላው ስትቆም ከዕንብርቷ ዝቅ ብሎ የሚያየው የወላድ አባጣ እንደ ሕፃን ልጅ ጉንጭ ይስበዋል:: የእሱ ዕድሜ እኩያ የሆኑ ወጣቶች የሚጎተት ሸንጥ ሲያሳድዱ እሱ በብርቱካን የቦርጭ አባጣ መመሰጡ አልፎ አልፎ ያስቀዋል:: ይሄን ቦርጭ ራቁቱን ቢያገኘው ሁለት እጆቹን እላዩ ላይ ጭኖ እንደ ልብ ሲመታ ያዳምጠው ነበር፣ እንደ ዶጋን ጎብጦም ወገ ያቋረ የእምብርቷን የጉድጓድ ገደል ይስም ነበር:: በእትብቷም ረቂቅ ቀዳዳ ፍትወቱን ይደውልላት ነበር:: እሱ እንደሚያስበው ይሄ ጉብታ ለሰላሳ ነው:: ከዚህ ጉብታ ውስጥ ውጋጋን ይወጣል:: ለእሱ ይሄ ጉብታ ገና ከምጣዱ እንደወጣ ጥቢኛ ትኩስ ነው::

......ያየው አሳወራውምና......ወይ አልገባቶት......የትላልቅ ዐይኖቿን ሽፋሽፍቶች እንዴት እንዴት ነበር---ይላል ለራሱ—ተቅለስልሳ ወደ መሬት የምትጥለው? በሯን ከፍታ ፈገግ ስትል ያሪቲ ጠረን ነበር ከኩታዋ ላይ ክንፉን ዘርግቶ ፊቱን የሚመታው?

ሳምንቱን ያለ ወይንና አልኮል እንዳጠናቀቀ አንድ ቅዳሜ ጠዋት ከቁርስ በፊት የብርቱካንን ቤት በር እንኳኩቶ ሲከፍት በረንዳ ላይ በካናቴራና በውስጥ ሱሪ ማንን ያገኛል? ኅደኛው የነበረውን ዳይሬክተሩን:: ወሬውን ሰምቶአል:: ስለእሱና ስለብርቱካን ወሬውን ከሰማ ከርሞአል:: ግን እንደዚህ አፍጦ የሰማንያ ሚስቱን አገር ቤት ልኮ ከውሽማው ብርቱካን ጋር የሚንፈላሰስ አልመሰለውም:: በላይ ሊያስታውክ ቃጣው:: እስከመጨረሻው ሰክሮ እንኳን እንዲህ ሽቅብ ብሎት አያውቅም:: ምንም ሳይተነፍስ ወደ ቤቱ ተመለሰና በሩን ገርበብ አድርጎ ብርማ የእጅ መታጠቢያ ሰሐኑ ላይ እፍኝ እፍኝ የሚሞላ ሐሞት አስወጣ:: ያስታውሳል ኅደኛው ለነበረ ጊዜ በላይ የብርቱካንን ውበት አዳንቆ ነግሮት::

ያኔ(1): «ምንዋ ያምራል!» ብሎ ስቆበታል:: ከት ብሎ ስቆበታል::

ያኔ(2): «ስንት ስንት ወጣት ልጃገረድ ባል ፍለጋ እየተንከራተተች አንተ ፊትና ወላድ ጋ ትሄዳለህ» ብሎታል

ያኔ(3): «ምነው እባክህ ሴት ጠፋ» ብሎታል

ያኔ(4): «ቅላትዋ ነው ደስ ያለህ? ሌላ ምኗ ነው ደስ ያለህ?»

የገረመው ዳይሬክተሩ በውስጥ ሱሪና በካናቴራ ከተቀመጠበት ሳይነቃነቅ ቃል ሳይወጣው ስስ ዕፍረት በጋረደው ሳቅ ሲመለከተው



@BOOKALEM

ነው:: ሁሉቱም ይተዋወቃሉ:: እንኳን ሲከጅላት ዞር ብሎ የሚያያት አይመስልም ነበር---ያኔ ብርቱካንን ሲያንቋሽሽበት:: በላይ እናቱን በእጆቹ ይዞ ለረዥም ጊዜ ካለፈው ወደ አሁኑ፣ ከላይ እስከታች ሲያስብ ቆየና ሱሱን ለማቆም የበለጠ ቆረጠ:: እልፎ እልፎ ከላይ ከቡልጋርያ ሠፈር ከሚያመጣቸው አስቀያሚ ሴተኛ አዳሪዎች ሌላ ለአምስት አመታት ያህል ንፁሕ ሴት አላየም:: የመጀመሪያ ወዳጁን ለፋሽኬት ለውጦአት ትታው ስትሄድ ያኔ ቅር አላለውም::

ያኔ(5): «ሴት በሽ ነው:: ይህቺም ዝም ስትላት ቆይታ ትመጣለች» ብለውታል ጓዶቹ:: አልመጣችም::

ያኔ(6): «ተው በላይ ተው:: ከስተር በል:: ልቤን አስጨነቅሃት:: መስከርህን አቁመህ ቁም ነገር ያዝ:: እኔንም አታሰናክለኝ» ብላው ነበር አስቴር ወዳጁ::

ያኔ(7): «ያለ ጓደኛ ኑሪ ነው የምትይኝ?»

ቢስላች ሴት ተወ:: ልቡ ውስጥ የቀረው ለብርቱካን ያለው ምኞት ብቻ:: በስካር ማዕበሉ ውስጥ በሲጋራ ጢሱ ጉም ውስጥ ሲያያት የኖረው ብርቱካንን:: ግን ሲያጣጥሉበት ወዳጆቹን አመናቸው:: ከርሞ ከርሞ ዛሬ ግን እንደኛው ወሽሞአታል:: አጣጥሏት ወሽሟታል---ያውም የተከበረና የተከበረበትን ትዳሩን እየወጋ::

......በላይ ሰኞ ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ ቀለል ብሎት ነበር:: እየደጋገመ ቢያዛጋውም ሃያ ብሯን አልነካትም:: ዐይኖቹ የበሩ፣ ጡንቻዎቹም የተፍታቱ መስሉታል:: አቶ ለገሰ በሕመም ምክንያት ቀርተው ስለነበር የጠዋት ክፍላቸውን እንዲሸፍንላቸው ዳይሬክተሩ መጥተው ነገረው:: ክፍል ገብቶ ለማስተማር ሲዘጋጅ ተማሪዎች ያለ ልማዳቸው እየተንሜጩና እሱን እያዩ በሳቅ ሲንከተከቱ አየ:: ምክንያቱን ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም:: የሚያነቧትን ብጣቂ ወረቀት ከአንዱ ተማሪ ወስዶ ሲያነብ ከላይ እስከ ታች ቁጣ ወረረው:: ወንበሩ ላይ ተቀመጠና ጠረጴዛ ደበደበ:: ፀጥታ ከሰፈነ በኋላ:

«ስማችሁ ይሄን የፃፈው ሰው ህፃን ነው:: የሚሰራውን አያውቅም:: ቁም ነገር አይደለም እሺ:: የቤት ስራችሁን ያልጨረሳችሁ ካላችሁ ጨርሱ:: ይሄ ወረቀት ቁም ነገር ስላልኾነ ጨባብጬ እጥለዋለሁ» አለና ወረቀቶቹን ሰባስቦ አንድ ላይ ጨባበጠና ልጆች እያዩ ከፍሉ ጥግ ወዳለው የቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫት አቅጣጫ ወረወረው:: ባጋጣሚ የወረቀት ኳሱ ስተት ብሎ ገባ::

«ባስኬት ቦል ጎበዝ አይደለሁም? በዕረፍት ሰዐት የሚገጥመኝ እፈልጋለሁ» አለ እየሳቀ:: ልጆቹ ተከትለውት ሳቁ::

ልጆቹ ለአፍታ ጉዳዩን የረሱት መሰለ:: ለጊዜው እንደረሱ ያውቃል:: አሁን በዘዴ ቢያዘናጋቸውም ነገ ከነገ ወዲያ ወይም ሁለተ ደረጃ ሲደርሱ ወይም ኮሌጅ ገብተው ወይ ከኮሌጅ ተመርቀው እን እሱ የሲወርድ ሲዋረድ ጂን ቶኒክ እየጠጡ ሲቀልዱ ይሄ ገጠመ ተነስቶ ስካራምነቱ ይተረካል::

«ያ በላይ......ታውቀዋለህ?»

«የቱ?»

«ያ ሰካራም ነገር......»

«እም»...በትንንሽ የሠፈር ትውፊት ውስጥ አወዳደቁና ውርደ ይመዘገብና የቁም ነገራቸውን ደረት ልብ በአልኮል ጦር የወጉ ተጠናቀው ያላደጉና ወደ ፊት የሚጠፉ ኀልማሶች ልጋጋቸው ያዳርቁበታል:: ተጫዋቾችና ቀልደኛ አስታዋሾች ይፎልሉበታል:: የእሱ ያለፈ እከካም ሕይወት ጀርባ እከካም ጣቶች ያቆስሉታል:: የሚረ ይመስላል:: ማንስ ያስረሳል? እንደበለጡት ሊያሳዩት......የወደቀ ዚ ሲጠቀስ......ስላንኾነለት ሰው ሲወራ......የእሱ ስም በትልቁ ይጠራ የማይረባው ጨዋታ ሁሉ ወደሚረባ ተረትና ምሳሌ ይለወጣል::

ግን ተማሪዎቹን ያፈቅራል:: ጊዜው ደርሶ ምሳ ሊበላ እጆቹ ሲታጠብ መዳፉ ላይ የሚያገኘው የተማሪዎቹን እናት ሲዳብስ በእሱ በእነሱ ወዝ ታስረው የቀሩ ትናንሽ ፀጉሮችን ነው......ምናልባት የፎረፎር ቡናኞች:: ለእረፍት ሲወጣና ግድግዳ ተደግፎ ሲያጤ ('እዚያ ግድግዳ ጋ እታጡትም' ተብሎ ሰው ተልኮ የሚጠራበት ቦታ) ጣቶቹ ላይ ለረዥም ጊዜ ያልተለየውን ይሄን የልጆቹን ሚር ተቀብቶ ነው:: ከልቡ ውስጥ በእውን እንደሞተ የሚያውቀው ወይ መሞት እንደጀመረ የሚረዳው ማስተማር ሲሳነው ብቻ እንደኾ ይሰማዋል:: ይሄን የሚረዳ ሰው የለም:: ቢገባቸውም ያልገባቸ ይመስላሉ:: ቢሰክር የራሱ የግሉ ጉዳይ ነው:: ሴሰኛነትም ቢኖርበ የራሱ ጉዳይ ነው:: ግብዝም አይደለም:: የማስተማሩ ሐላፊነት ግ ሁሌም ትከሻው ላይ እንደተጫነ ይገባዋል:: ከትንንሽ ልጆቹ ጋ በቁስል ቡጢ የመሰለች ጉበቱን አዝሎ እስከመጨረሻው ሳይከዳቸ ሊዘልቅ ይፈልጋል:: አድገው፤ ሸንጎበታቸውን እየተላጩ እሱ ባያስታውሱት እንኳን ወደየስራቸው ቸኮል ቸኮል እያሉ ሲሄ ይታየዋል:: በተለይ ማታ ገንዘብ አንሶት ተጠናቆ ሳይሰክር ይቀር በጠራ ጨረቃ ከቤቱ ፊት ለፊት ያለች ኩርባ አስፋልት የሚያልፍባ ለስላሳ ሳርማ ዳገት ላይ ኾኖ ሲጋራ ለኩሶ ተማሪዎቹን ይዞ ወደገደ እንደማይወርድ ይምላል፤ጠመኔ ጥይቱ እንደኾነ ወታደር:: ረጭ ባለ የአምስት ሰዓት ጭለማ የሰፈሩን ከፊል እየቃኘ መብራቱ ያልጠ ቤት ያያል......በየቤቱ ጠረጴዛዎች ላይ በምናቡ ከተማሪዎ



@BOOKALEM

እንዳንዶቹን በሐሳቡ ይስላል......የ'ሳይንስና ሕይወት' መፅሐፋቸውን ዘርግተው፣ ጥቂቶቹ እንቅልፍ ጥሎአቸው:: ከፊሉቹ እንደመከራቸው መፅሐፋቸው ላይ በእርሳስ እያሰመሩ—ስካራም መሆኑ ትዝ አይላቸውም:: ብሏቸው አያውቅም:: ወደ ጓሮ ተሸሽጎ ሲጋራውን የሚያጤሰው እሱን በማየት ሱስ እንዳይማሩ አክብሯቸው ነበር:: ይሄም ይገባቸዋል:: እንደሚገባቸው ያምን ነበር::

ታዲያ ከፍል ውስጥ የተበተነውን ወረቀት እንዳነበበ የተረዳው ነገር ቢኖር ይሄ ቄንጠኛ የአስዳደብ ስልት የልጅ ሳይሆን የአዋቂ ስራ እንደኾነ ነው:: ማን ይሆን?......ከሰባት ዓመታት በፊት ወይን መጠጣት አላምደው ከከዱት ጓደኞቹ ሌላ ማን ይሆናል? ያውቃል፤ እነሱም ያውቃሉ ራሱን ካሰባሰበ ሊያልፉቸው እንደሚችል:: ቅስሙ ግን ገና እንደተንበረከከ ነው:: በስካር ጉዞ ላይ ባልታወቀ ጊዜ እንዴት እንደኾነ መረዳት በማይቻልበት ሁኔታ ቅስም ትጓጉላለች:: ድንገት ሲነቁ ነው መድከሟ ትዝ የሚለው:: ነቅተው ራስን ሲያዩ ፊት ተለውጦአል:: ጥርስ ዝጎአል:: አብራክ ደክሞአል:: ጡንቻ ላልቶአል:: ልብና ምኞት ብቻ ያለ አጃቢዎቻቸው ይውተረተራሉ:: ያልተሰራባት ልጅነት ከተጎዱ ዐይኖች ጀርባ ትለፋለች:: 'በላነው' 'ጠጣነው' 'አጤስነው' 'በዳነው' ከማለት ሌላ ምን ሊል ይችላል? እሱስ ምን ማለት ነው?

ወረቀቱን ካነበበ በኋላ በአእምሮው የመጣው ዳይሬክተሩ ነው:: ንፁሕ ልብሱ:: ንፁሕ! የተላጨ፤ በሚስትና በውሽማ በፈረቃ የሚወለወል ፊቱ:: አስቀምጦ ሲመክረው......'እኔን እየኝ' እያለ ሲመክረው:: ምን ዓይነት መካሪ ነው? ምን ዓይነት ጓደኛ ነው? ዱሮ ክራቫት ሲዋሰው ነበረ:: ትንሽም ቢሆን በዱሮ በሬ ይታረሳል እንጂ.......የድሮ ዘመን ካመረተው ነገር የበላንለት ቫይታሚኑ የስራቸው ሕዋሳት እንዲህ ፈጥነው ባንዴ ይጠፋሉ እንዴ? በሳንባዎቻችን ውስጥ ተገንብተው እንድንተነፍስ ይረዱን የለ? በአጥንቶቻችን መሐል ጅማት ኾነው ትንሽ ያቆሙን የለ? ትናንት የቆረፈዱ ዛሬ የተመቻቸው የሚነሳ ታሪክ የላቸውምና፡ 'በዱሮ በሬ......' እያሉ በክብት ቢተርቱ ማን ይሰማቸዋል? አንዳንዴ ሊሰረዝና ሊጠፋ የማይችል ቀለም አለ:: ቢሉት ቢሉት፣ ቢፍቁት ቢያጥቡት:: ቲቸር በላይ ግን ያለፈ ታሪኩን አያነሳውም፣ ለመተረት ምላሱ አትቀብጥም:: 'ክራቫቴን ያኔ ስትዋስ' ብሎ በጫወታ ጋርዶ ዳይሬክተሩን ከእሱ የሚያንስ እንደነበረ ሊጠቁመው አይፈልግም:: እንደውም ዳይሬክተሩ ያለፈ ዘመኑን እስማምሮ ሲያወራ እየሰማው ላለማሳፈር ብሎ አያርመውም:: ሺህ ከርፋፋ ሳይጠይቅ አፉን ከፍቶ ካመነ እሱ ምን ጉዳዩ ነው? አለቃ ነኝ በሚል ሰበብ 'በአወቅሁሽ ናቅሁሽ' ደደብ መመሪያ ቢያወጣ እንኳን ሰዎች መሐል በንቀት አያጣጥልበትም:: ቢሳሳትም አይንቅበትም::



@BOOKALEM

እንዳንዴ ፈርቶም ነው። 'ቀንተህበት ነው?' እንዳይባል። ግን ቀንቶም አያውቅ። እንዲህ ዓይነት ትችቶችን ማቆሚያ መንገድ የተፈለሰፈው የት ይሆን?......ከክፍሉ ወጥቶ ውጭ ቆመ። እወዲያ የዳይሬክተሩ ቢሮ ይታያል። ቢሮው በር ላይ አብሮት ያደገውን የዳይሬክተሩን ጉረኛ ቁመና ያያል። ስፋቱን ያያል። በመሃላቸው በአበባና በሳር የተዋጋ የሁለት መቶ ሜትር ያህል ርቀት አለ። ለሰከንድ ይሄ አለቃው እንደሚፈራው ገባው። '*ዘግይቶ በቀተኛ ልቡ ከዳተኛ*' አለ በሃሳቡ።

ዳይሬክተሩ ክራቫቱን አስተካከለና የኮቱንም ፊት ለፊት አመቻችቶ ወደ ቢሮው ሊገባ ሲል በላይን ቆሞ አየው።

«በላይ ምነው?» አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ዳይሬክተሩ።

«ምንም......የሚሰራ መልመጃ ሰጥቼአቸው ነው»

ዳይሬክተሩ ተመልሶ ገባ። ቢሮው ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲል ይታያል።

በላይ ለሰከንድ ብልጭ አለለት......

......ይሄን ወረቀት አንድ ወይም ሁለት ወይም ሶስት ተማሪዎች ከበተኑትስ?......እንዲህ መልካም እየሰራላቸው፣ እያስበላቸው ተማሪዎቹ ከከዱት መልፋቱ ምን ፋይዳ አለው? ምንስ ቢሆን ማንስ ቢሆን 'በትኑልኝ' ሲላቸው ለእነሱ ሲል የሚለፋውን ልፋት አይተው 'አስተማሪያችን ላይ አናደርግም' አይሉም? ሸለቆውን ወርደው ዳገቱን የሚወጡት አብረው እኮ ነው። ለጠላቶቹና ለጠላታቸው ካገለገሉ አብሯቸው መባዙ ምን ጥቅም አለው። ለማያልቅ ችኩና ለማያልቅ ወይን መስዋዕት ለመሆን?

በላይ ዙሪያ ገባውን አየ። ከግቢው በታች ወዲያ የባሕር ዛፍ ደንና ቀለሙ የማይታይ ቢታም ሲምህ ነው። ለአፍታና ለመጀመሪያ ጊዜ ምድር ላይ ብቻውን እንደኾነ ተሰማው። ከጀርባው ካለው መማሪያ ክፍል ውስጥ ምስጋና ቢስና የሚጠቅመውን የማያውቅ ኡሩ፣ በቀረው ዙሪያውን ደ'ሞ የግል ሕይወቱን ለማሸነፍ የሚውተረተር ያኀበሰ ሕዝብ። ብዙው ጅል። ብዙው በተራ ቁም ነገር የሚደሰል። በግብዞች የሚነዳ ከብት። እና ብቸኛ መሆኑን ማወቁ ታላቅና ከባድ ዕውቀት ኾነበት። ሰውነቱ እቆመበት ከላይ እስከ ታች ተንዘረዘረ። ከሸሚዝ ኪሱ ሲጋራ ፈለገ። የለም። ጣቶቹ ይንቀጠቀጣሉ። አፉ ደርቆአል። ዙሪያውን የከበበው ገዋ ሊውጠው ሲንደረደር ይሰማዋል። እንደ ነፋስ ማዕበል ነው። ነፍሱም ውስጥ ዕርጥበት አለ። ልክ ምሬት ሲተፋበት ያለውን ዐይነት ብትንትን ዕርጥበት። ይሄንን ሁሉ የሚኀትተው አዙዋሪት ደንዳኔው መሃል ነው። ጭንቅላቱ ይዞራል። ቀኝ እጁን ወደ ታች ሰዶ ሊቀመጥ ሞከረ.............ወደ ክፍሉ መግቢያ ላይ ያለውን የጡብ ግንብ ለመያዝ ገላውን ሲወረውር ሳተው። በአፍጢሙ መሬት ላይ ወደቀ። ......'*ደረጃውን እንዴት ሳትኩት?*' *ሽክሳውም እንደለው*

*ይሸውዳል?'* .......ከላይ እስከታች ተዳክሞ እወደቀበት መንጋጋውን እየነከሰ ስለ ነገሮች ቀላልነት ያስባል......ነገሮቹ በትክክል ምን እንደሆኑ አያውቅም......ግራ ዐይኑ በሚሞቅ ነገር ሲጨልም ተሰማው......እንደተጋደመ ደም መሆኑ ገብቶት ጠረገው......*ጠረገው?* ሲያነሳው የራሱን እጅ ያየው መሰለው:: ከተጋደመበት መነሳት አልፈለገም:: የሚጣፍጥ ነገር አለው:: ሳሩ ቀዝቃዛ ነው:: ልቡ እንደምትፈላ ነገር ስትንተከተክ ይሰማታል:: ይሄ እንዳስገረመው ሁሉ ፈገግ አለ......ከሩቅ እግሮች ወደወደቀበት እየሮጡ ሲመጡ ይታየዋል:: አራት፣ ስድስት፣ ስምንት:: የሰው ፊት እንጂ እግር ለይቶ አያውቅም:: አሁንም ፈገግ እንዳለ ነው:: *ማነው ያ ከሩቅ ነጭ በነጭ ለብሶ የሚመጣው?*

እንድ ሰው: «አትጠጣ ሲሉት፣ አትጠጣ ሲሉት አይሰማም» እያለ ሲናገር ሰማው:: *ማነው ይሄ? ከእናንተ ወዲጅ ከመሰላችሁ ውሸታሞች የጉበት በሽታ፣ ደም ማነስ፣ ቂጥኝ ይሻለኛል*......አይኖቹን ሲጨፍን ባሕር ውስጥ የወደቀ መሰለው......ዐይኖቹን ሲገልጣቸው ሰማይና መሬት ቀልቶአል:: አንዲት ትንሽ ልጅ ከክፍል ወጥታ ፊቱን ተጠግታ ዐይታ እየጮኸች ተመለሰች::......ዙሪያውን እግሮች ከበቡት::

ብዙ ሰዎች ወገባቸውን ይዘው ዙሪያውን ቆመዋል::

ተማሪዎች ደንግጠዋል::

እሱን ያጣጥሉት የነበሩ አስተማሪዎች እንደደከሙ ሁሉ ግድግዳ ተደግፈው መሬት መሬት ያያሉ:: ኢምንት የሆኑ መስሏቸዋል:: የሚያለቅሱ ወጣት ልጃገረዶች አሉ::

*ከአፈ የወጣው ደም እንዴት የሚያምር ቀይ ነው?*

*ተሻለ የታለ?*

*የታለ ተሻለ?*

ተሻለ በሩጫ ወደሚሄድበት ይሄዳል:: ጉልበቱ አገጩ እስኪደርስ እግሩን እያነሳ ይሮጣል:: *ስለምንድነው ገልመጥ ብሎ አይቶኝ የሳቀው? እ? እናቱን እንደምወዳት አያውቅም? ከፍትወተ-ፍቅር ይልቅ ፍትወተ-ሥጋ ለምን ይደነቃል? ለምንድነው ተሻለ የሁለት እግሮቹን ውስጥ ፅሩይ ቀለም የተቀባው?*

ሳሩ ላይ ከተጋደመው እጁ መሐል ያሉት ሁለቱ ቀይ ብሮች እተጨበጡበት ሲንፈራፈሩ ይሰማቸዋል:: *መቼ ለወጣኋቸው?* የጣቶቹን ቡጢ ሲፈታ ብሮቹ ተዘረጋግተው ጨምዳዳዎቻቸውን አስተካክለው ከመዳፉ መሐል እንደ ሁለት ሶረኔዎች እራሳቸውን እንደ ክንፍ እያማቱ ወደ ላይ ተነሱ:: የሚበሩበት አቅጣጫ ጨረር ስለተቀላቀለው ሊያተኩርባቸው አልቻለም......ብሮቹ መዳፉ መሐል ምን ሲሰሩ እንደተቀመጡ ራሱን ይጠይቃል......ኪሱን ሲፈትሽ

ይሞከራል......እጁ አየር ላይ ይቀዝፋል-መስመጥ እንደጀመረ ፈረሰኛ ወንዝ አቋራጭ......

ታላት ልጅ።

የተሻለ ማደግ እየገረመው ያያል። ዛሬ ጡጦ ይጠቡና ነገ ይሸብታሉ......

ዙሪያውን የመከራ መድፍ ተጠምዶበት እንደገናም ፈርተውት።

አንድ ትንሽ ልጅ ግን ነፋስ የመሰለ......እግሮቹ በኩራት ይሸሻሉ። እግሮቹ ከአንጎላችን ይፈጥናሉ።

ከበላይ በስተቀር ተሻለን ያየው አልነበረም።

*ሶረኔዎቹስ?* ከንፋቸውን እያማቱ ሳንቼር ወደመሰለው ሰማይ ይጋልባሉ......

በላይ አናት ላይ አስተማሪዎች ውሐ አፍስሰውበት መሬት ላይ ያደገ ርጥብ ሳር መሃል ተቀመጧል። በመገረም ተሻለ በሮጠበት አቅጣጫ አየ። እስከ ዛሬ ይሄ ልጅ ለምን ትዝ እንዳላለው በራሱ ተገረመ። የትምህርት ጊዜ እንዳለቀ ወደማታ አካባቢ በቀጥታ ወደ መርካቶ ይወጣል። ለዚህ ልጅ መሬት የሚያነጥፈው የጥጥ ፍራሽ ይገዛል። ወደ ራሱ ቤት ይጠራዋል። የሚበላውንም ያበላዋል። ...... በነገሩ እንግዳነት ለራሱ ሳቅ አለ።

ወደ ማሕፀኗ መግባት ከተከለከለ ምናለበት ከማሕፀንዋ የወጣውን ቢንከባከብ።

ከት አለ በሳቅ። ከት።

እሱ ዙሪያ የከብ ግማሽ የሰሩት አስታማሚዎቹ በመገረም ተያዩ።

ዝቅ ባለ ድምፅ፡

«በላይ ደህና ነህ?» አለ ዳይሬክተሩ።

«በጣም» አለው።

እፉ እንዲህ ተሳቆለት አያውቅም።

— // —

*ሐምሌ 1977 ዓ.ም*

*አዲስ አበባ*



@BOOKALEM

# አብዲ

ቤቱ አጠገብ ብቻውን ቆሞ ድምፁን ዝቅ ያደርግና ለራሱ ጥቂት ያወራል......አንዳንዴ ያመልጠዋል---የራሱ አፍ ያንባርቅበትና:

"ከፈቺ!......አንቺን ነው ከፈቺ!.....አትሰሚኝም.....ይገፈልሽ የመጣሁልሽን አታውቂም......ሙቺ......ፍቅሬ ሙቺ......አልማዝ ሙቺ ወይኔ እንዴት አታምኚኝም......"---ለገዋ---እቤቱ ውስጥ ላለ ባዶ......

"ጀመረው ይሄ ያበደ ሰካራም" ይሉታል፣ ሰዎች---ጐረቤቶቹ......

ቤቱን ከፍቶ ገብቶ መብራት ሲያበራ፣ ደጃፍ ላይ ቆሞ ብቻውን ሲያወራ ሰምተው የፈሩትና የተረበሹት የጨለማ ውስጥ ፊቶች በሳቅ ሽንተረር ይፈነካከታሉ......

ሃ!ሃ!ሃ!

"ምን አሳቃችሁ?!" ይላል አንዱ ከጨለማ ያልሰከረ ድምፅ......

"ይሔ አብዲ ነው እባክህ"---ሳቂዎች::

* * *

ፀጉሩ ላይ የተረጨውን ዱቄት ሳያራግፍ እህል እህል እየሸተተ ከሕዝብ ጋር ይቀላቀላል......ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰአት እስከ አምስት ሰአት ማታ በስራና በዙረት የሰባተኛን ከተማ ያበጥራል......:: መርካቶ የጨለማ ብርድልብስ ተከናንባ......በመሸታ ቤት በሮቿ ወደ ጎዳናዎች ስታፈጥ እንደ ታዛቢ እየተንገዳገደ፣ ጉድፍ የተረጨባቸው ቀን ቀን መኪና የሚያሻቸው አስፋልት መንገዶች



@BOOKALEM

መሃል ይገተርና የሱሪውን ፊት ለፊት ከፍቶ ረዥም ነጭ የባለቲ ገመድ በሚመስል የሽንት ውሃው ያጥባቸዋል---ደንበ::

በሚከላተፍ ምላሱ ተሰምቶ የማይታወቅ በካሴት በሬድዮ በአዝማሪ ያልተመዘገበ ዘፈን እያንጉራጉረ መስቀለኛ መንገዶች በበታተኗቸው የአዲስ ከተማ ያደፉ ዘማማ ቤቶች መሃል እንደ ንፋስ እየተጥመለመለ ቤቱ ይገባል::

አብዲ መንዲስ ነው:: ከጉን ሲያዩት ግንባሩ ወደ ውጭ የተፈነጠረ አይነት ነው......አፉ ወደ ውስጥ ገብቶ አገጩ ጡጠ መስላ ወደ እዳሪ የሾለች ናት......ፀጉሩ ቁጥርጥር ነው......አይበጠርም......ቢያበጥረውም ስለማይዋጣለት ብዙ ጊዜ ጭንቅላቱ የተንጋደደ ይመስልበታል::

ጠጥ ሲል......

የመርካቶ የቀን ሳት ጭም ሲል......

የመርካቶ ደደብ የሚያደርግ ጩኸት፣ ለሸቀላ ሲንኳኳ የዋለ እዳራሽና ሳቅ......በምሽት ሆድ ሲዋጥ፣ ቅዳሜ ማታ......ስራ የሌለ ዕለት ማታ፣ ከተዋጣለት ተጣጥቦ፣ ካልተዋጣለት ከእንቱታው፣ እንደ ታላቅ ሐረግ ከቤቱ እየተጥመለመለ ወጥቶ......በመንገዶች ዳር ዳር ሲተበተብ ያመሻል---አብዲ የሰባተኛው ጉልማሳ::

ከየት እንደመጣ አይታወቅም......የአባቱን ስም እንዲህ ነው ብሉ የሚጠቁም አልተገኘም......ድርጊቱ እንደ ወላጅ አባት ተቆጥሮለት ስሙ 'አብዲ ሠካራሙ' ኾኖአል::

"ሠካራም ነኝ......ምን ይጠበስ!" ይላል ባንኮኒ ተደግፎ ማንም ሳያናግረው፣ ሳይጠይቀው......ቅዕል ስሙ አልኮል የሚሰግርበት እናቱ ውስጥ ሲያቃጭልበት:: ከጉድጓዱ አፉ ጆርባ አውጥቶ......ተፍቀው የማያውቁ ጥርሶቹን ሸልቀቆ እኝ......እኝ......ኝ......ኝ እያደረገ......

"ሠካራም ነኝ እሺ ምን ትሆኑ......እናንተስ እዚህ ምን ታደርጋላችሁ?" ይላል......

የሚያዘወትራት መጠጥ ቤት አለችው:: ቢሆንም እሱ መጥቶ ሲቀመጥ ደንበኞነቱ እንዳይጠፉ ከሩቅ ያንጋግሩታል እንጂ የሚቀርበው ማንም ሰው የለም---ዘንባባ ብቻ:: ያውም ይሄን ከእሷ ጋር ያለውን የሩቅ ቃል ቅብብል እንደ 'ማስደሰቻ ምራቂ' ሊያዩለት የሚሞክሩ አይጠፉም::

ዘንባባ የዐይን ወዳጁ ናት:: ገና ከወለንኮሚ አዲስ ከተመ መምጣቷ ስለነበር አሮጊት አዛዥዋ /ቦስ/ ወይዘሮ አልማዝ እንድትለማመድበት የጠቆመቻት የመጀመሪያው 'ጤይባ' ሰው አብዲ ነው......



@BOOKALEM

"ያ ጅልሽ መጣ ያኘው" ይሏታል ዘንባባን መለኮ ጓደኞቿ—ሁለቱን በማፋተራቸው ራሳቸውን ከፍ ያደረጉ ስለሚመስላቸው ተቻኩለው ሳይቀደሙ......

ከመጠጥ መደርደሪያው ከፍ ብሎ ግሪያው ላይ ከበራው አጭር የፍሎረሰንት ብርሃን ሥር በቀጭን እግራቸው ውጥርጥር ያለች ሆዳቸውንና ሁሉ ደረታቸውን ተሸክመው ወዲያና ወዲህ እየተሯሯጡ እጥፍ ሴቶቻቸውን ያስግራሉ—አልግዝ:: እስከ መቶ የተብረገደ ቴኝም ዘመም ባለችው በር እየሾለከ ወጥቶ መንገደኛ ወደ ቤቲቱ እንዲገባ የድምፅ መረቡን ይወረውራል......

"አንቺ ደህና ነሽ.....እኔ ደህና ነኝ" ይላታል ዘንባባን አብዲ.....

በአይንዋ ጥግ እመቤቷን ትመለከትና ለሳቅ ያሞጠመጠ አፍዋን በስፋት ሳትከፍት:

"ደህና ነኝ" ብላ ትመልሳለች......

"አትጠጪም" ይላታል ወደ ፋሽኮው እያሳያት::

ልትጉዳው አትፈልግም......ያሳዝናታል—ውሽማዋ እንዲባልም አትፈልግም......'ጓደኛ' ከሚባል 'ውሽማ' ወደሚባል እንዳይሸጋገር ከባልንጀሮቿ ጋር ቀንና ሌት ታላቅ የንገር/የሥነ-ልቡና/ ውጊያ ታደርጋለች......

"ጠጣ" ትላለች

"እየጠጣሁ ነው......አንቺ ጠጪ" እነኚህን አረፍተ ነገሮች ብቻ ያወራል......

"ስማሽ ዘንባባ! አብዲ 'እንሂድ' ብሎሽ አያውቅም?" አለቻት አንድ ቀጫጫ ትዕቢተኛ ጓደኛዋ፣ የሆድዋ ቦርጭ ከእርግዝና የሚያምታታ......ካንጋሩ የምትመስል......

"እንዲም ብሎኝ አያውቅ"

"ምነው እባክሽ?"

"እና?"

"በቃ እስኪ አብረን እንደር በይው"

"እሺ የሚልም አይመስለኝም እባክሽ......እንዲህ ዓይነት ነገር ያውቃል?"

"ብቻ ጠይቂው......ምን ቸገረሽ......እወድዋለሁ አላልሽኝም"

"እይ እቴ......ያኘ ይሔ አፍሽን......ምስኪን ነው ያሳዝነኛል አልኩሽ እንጂ......አንቺ ትወጂው እንደሆነ ንገሪኝ"—ትላለች::

ዘንባባ በቁጣዋ ደኄን ደብቃለች: በሚያሳዝኑ የኑግ ኳስ በመሰሉ 'ቱሉግ' አይኖቹ ካቀረቀረበት ቀና ብሎ ሲያያት ገላዋ አንዳንዴ እንግዳ ንዝረት የሚሰማውን......

* * *

መንገዱ ፀጥ ብሎአል......

የአውራ ጉዳናው መብራቶች ጨለማውን ያቅማቸውን ያህል በብርሃን ከፋፍተውታል......አዲስ ከተማ አልኮል ከአብከነከነው ንቁ ደንባራ በስተቀር......ባልያን ትቶላት የሔደውን የነቃ ነውሿን ተያይዛዋለች......ዘንባባ ለእርዳታ የላከችለትን እጅዋን በእምቢታ ወደ ታች ገፍቶ ሽቅብ፣ ቁልቁል አያት......

"እኔ እኮ ላንተ ነው" አለችው ዘንባባ::

"ምን ሆንኩ?" አላት በጉን እያያት::

"የሆንከውንማ ታውቀዋለህ......እንዴ ምን ቸገረኝ"

"አልሰከርኩም......ለአንቺና ለመሰሎቻችሁ መሰልኩ እንጂ"

ምን ማለቱ ነው 'መሰሎችሽ?':: ዘነጋችለት የጡንቻማ ምላስ ዳጡን::

"እየው እየተንገዳገድክ?" አለችው ዘንባባ......

እሷም እሱም የነበሩበትን መንገድ ትቶ ወደ ሌላኛው የመንገድ ጠርዝ ተሻጋገረ......ወደመጣችበት ለመመለስ ፈለገች:: `እንዴ!!ምን አስጨነቀኝ?` ነገር የደከመ ፊትዋ ላይ እየተብከነከነ:: ወደ ኋላዋ አየች.....ማንም የለም......የሚዘጉ በሮች ድምፅ አልፎ አልፎ ይሰማል......ከአዲስ ከተማ በስተደቡብ የሚተላለፉ መኪናዎች የሚያጉተመትም ድምፃቸው ቀርቦ ይጠፋል......ከሩቅ የምትታየው ነጭናጫ ፒያሳ ውጋጋኗ የሽግናም ሳቅ ይመስላል......ፊት ለፊቷ አየች--ማንም......

ወደ ሰማይ አየች......ከዋክብት ፈዘው ተገትረዋል......

ወደ መጣችበት አቅጣጫ ተመለከተች......የሚያስፈራት ያህል ርቃለች......የሰከረም ወንድ ቢሆን......ብቻን ከመሔድ እንዲህ አብሮ መሆኑ ሳይሻል አይቀርም......ማስፈራሪያ ይሆናል......እሱን የመተው ሃሳብ ትንሽ ብልጭ ሲልላት ራስዋን ታዘበችው......መምጣቷንም ጠላችው......

በስካሩ ምክንያት አቅም ያጠረው አብዲ ግግር ያለዉን እንደ እርጥብ ነገር የሚካበድ ቀዝቃዛ ጨለማ በሚወናጨፍ እጁ እየቀዘፈ ለእርምጃ ሲያጣጥር አየችው......ቆሞ ትንሽ ትንሽ እየተወዛወዘ 'ምንም አልሆንኩ' ለማለት አይነት እጆቹን ቱታ ኪሱ ከተተ......

"አትመጪም?" አላት

ተከተለችው......

"ዝም ከምንል ተረት ሳውራልሽ" አለ ሳያያት መድረሻ የሌለው ትኩረት ፊት ለፊቱ ወርውሮ::

መገረምና ሳቅ ያዛት......ግን በዕድሜ የሚልቃት አንድ ሰው ትንሽ መጃጃሉን ስታይ የመብለጥ ስሜት ተሰማት......

"ንገረኝ" አለች ጠጋ ብላ ነጠላዋን እያስተካከለች......የሚንተባተብ እግሩን እየጐተተ ተረቱን ጀመረላት......

*"በድሮ ጊዜ......"*

ድምፁን ሳይሰሙት የመጣ ባዶውን የሚንገጫገጭ ቺኳንታ በአጠገባቸው ሲያልፍ አቋረጠው......ሁለቱም ማሺኑን በአይኖቻቸው ተከተሉት......

*"አንዲት ክፉ ሴትና አንዲት ደግ ሴት ተጉራብተው ይኖሩ ነበር......"*

ነፋስ በቀስታ መንፈስ ጀመረ......ፊት ለፊታቸው መሬት ላይ የተበታተኑ የጫት ገራባዎች፣ የክባ ቅዳጆች፣ የሲጋራ ፓኮ ብጥስጣሾች፣ የጋዜጣ ቅዳጆች......አቧራና ሣር ምድር የተንቀጠቀጠች አይነት እኩል ተላውሰው ፀጥ አሉ......

*"ሁለቱም አጋጣሚ ኾኖ ሁለት ሕፃናት በአንድ ሰሞን ይወልዳሉ......እራሶች ኾነው እንደተኙ......ክፏ ሴት የወለደቻትን ሕፃን ይዛት ተኝታ እያለ ድንገት ስትገላበጥ ልጅዋን ትገላታለች......"*

የነጠላውን ከንብንበሽ አልፎ ሰውነትዋን ሁሉ ብርድ አርገፈገፈው ......በሚነዝር የድቤ ሙዚቃ ምት ውስጥ በተረጋገጠ የሽቀላ ወሲብ እየታሸ......የሚሟሟ የጓደኞችዋ ገላ ትዝ ብሉአት በሁለመናዋ በተዘረጉት የቆዳ ቀዳዳዎች ላብ ችፍ አለ......አዲስአባ ከመጣች ስድስት ወር ተኩል ነው:: ባልገባት ምክንያት የአንድ ቀን ወዳጅ አልወጣላትም:: ደንበኛ ለማግኘት 'ዘንጠሽ መልበስ አለብሽ' ይሉአታል ልምዱ ያላቸው:: ግን ዘንጦ ለመልበስ ገንዘብ ያስፈልግ የለ:: ገንዘቡንስ ለማግኘት ከወንድ ጋር ወጣ ማለት ያስፈልግ የለ:: የኾነ ልትወጣው ያልቻለችው አዙዋሪት ነው:: ሞፈር በትከሻው ላይ እንደ እርሳስ ቁጭ የሚያደርገው ባልዋ ትዝ አላት ቅዳሜ ቅዳሜ የሚያደርጋት፤ ሁሌ ሊነጋ ሊነጋ ሲል ሴትነትዋን እንዴት አብጠልጥሎት እርሻ ደርሶ እስኪመጣ በትዝታ ወንድነቱን ስታብሰለስለው:: ከዚያ 'ሰነፍ ሴት አልወድም' ይላል:: ያልገባው:: ከወንድነቱ አይቀንስም? እሱስ አርፎ አያርስም፣ እስዋስ አርፋ አታርምም? የቤት ማሕበን እንደ መሬት ቢመስልም መሬት ነው



@BOOKALEM

ያለው ማነው? ቢነገረው ግን አልሰማም......ቢመከር ቢዘከር በየት አገር ነው ወንድ የሰበረው የቆንጆ ወገብ በአንዲት ሲኒ የተልባ ብጥብጥ ቀና ይላል የተባለው?......በዚህ ላይ 'የት ስትዞሪ ነው ወጥ ያልሰራሽ?' ......ትታው አዲስ አባ:: የሁሉ አገር አዲስ አባ:: እናት አዲስ አባ::

*"..........ከዚያ በኋላ መልካምዋ ሴት የሞተ ልጅዋን እንዲመልስላት እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደ አልታወቀ ቦታ ጉዞ ትጀምራለች......"*

"ቶሎ ቶሎ እንሂድ እባክህ" አለችው አሁንም የወንድ ነገር ያልቀናት መስሎአት::

ቤት ንብረቷን ደፍታ እዚህ ስትመጣ የበለጠ ሰላም ልታገኝ ነበር:: ነጋ ጠባ ወሲብ ካለበት ባርነት፣ ወሲብ ባይኖርበትም ነጻነት የበዛበት:: አሁን ግን ወሲቡም የለ ነጻነቱም የለ:: ይሄ ኪሳራ ሁልጊዜ አንጀቷን ይበላዋል:: የምትተክዘው በዚህ ነው:: አንዳንዴ ያ ባሏ እየደበደበ ቢያበላት ስጋ ፍላጎትዋን ቢያረካት ትመኛለች:: 'ይሄ ኑሮ አይባልም' ብላ ሴትኛ አዳሪነትዋን ስታማርር 'ያጣ ወሬ ነው' የሚልዋት ጥቂት አይደሉም:: ታዲያ ቢቸግራት አንገራግራ አንገራግራ ሽፍታ ሽፍታ ከመራብና ከመጠማት ከመታረዝና ከመሰደብ ያገኘሁትን ላግኝ ብላ አብዲን ራስዋ ገፋፍታ ይዛው ወጣች:: አሁን ትንሽ ይቆጫታል:: ታዲያ ከቆሻሻነቱ ሌላ የማይረባ ተረት አውሪ ሰብድ::

አብዲ የዘንባባን መቆናጠር አልሰማም:: አልሰማትምና ቀጠለ:

*"በሞተ ልጇ ፈንታ ያቺ ተንኮለኛ ሴት የደግዋን ወይዘሮ ሕፃን ዘርፋ የሞተውን ተክታ ነው ለካስ......ልጅዋ በሽር መሰወሩ አበሳጭቶአት ፈጣሪን ለመለመን ከመንደሯ......ከቀዬዋ ተሰደደች......እየሽ!!"*

"እዎ" አለችው ቶሎ::

'አትጨማለቅ' ለማለት ፈለገች:: ይሄን እንድትል የገፋፋት......ተራ ንዴት ቢጤ፣ ተራ ቁጣ ቢጤ መልሶ ራስዋን ተሰማት......ማሰብዋን ሊያውቀው ባይችልም እንደማባበል አድርጋ ተጠግታ አቀፈችው......ሀሳቧ ወደ ነበረው ሕይወቷ እንደገና ሸሸ..........

*"......ድም ድም የሚለው የሰይጣን ቤት ነው፣ ኪል ኪል የሚለው የእግዚአብሔር ቤት ነው......ድም ድም የሚለውን ትተሽ፣ ኪል ኪል የሚለው ውስጥ ግቢ አልዋት—ደግዋን ሴት—እንያ ኩበት ይለቅሙ የነበሩት አሮጊት......»*

ፊቷን ትከሻው ላይ ጣል አደረገች:: አንገቱ ጋ አትደርስበትም እንጂ ቀብራ ዓይኖቿንም ጨፍና በራሷ ሁኔታ ማዘን ፈለገች......ተራቱን ረስቶ.....እጁን ወደ ወገቧ ሰዶ አቀፋት......ሃሳቡ



@BOOKALEM

ነው:: ከንዱ የሚሞቅ ግንድ ነው......ስፌ የሰራተኛ እጆቹ ትንፋሽ አጥሮአት የምትንፈራፈር የመሰለች ስራ የፈታች ቂጧ ላይ አረፈ:: ከንዱ በፍርሃት ይዳዳል:: ይንዘረዘራልም:: 'ከዚህ ቀሚስ ስር ሲመሽ ሲመሽ በጨዋ ደንብ ተቀምጬ የማየው ቂጥ ይሄን ነበርን' እያለ ያስባል:: ሲቀርበው ያልተሳመደውና የማያውቀው ኾነበት:: የማየትና የመንካት ስሜቶች እንዲህ ያህል የሚራራቁ አልመሰለውም::

"ሚስትህን ፈተህ ብቻህን የምትኖር ይመስለኛል" አለች:: ተረቱን መስማት አልፈለገችም::

"ሚስት አልነበረኝም" አሳት የድምፁን ቅላጼ ከተረት መንገሪያው ዝቅ አድርጉ:: ዞር ብላ አየችው......ጭንቅላቱን እያወዛወዘ መሬት መሬት ይመለከታል......

"እንዴት?"

ገላው የዱቄት ብናኝ ይሸታል......በስካር ከሚያመነጨው ላብ ጋር ወፍጮ ቤት ያቀፈች መሰላት......

ትንሽ የሳቅ ድምፅ ጉሮሮው ውስጥ አሰማ......አልመለሰላትም......

የጉዳችው፣ ያሳዘነችው መሰላት::

"አቤትህ አልቀረብንም?" አርእስት መለወጡ የሚያዋጣ መሰሏት::

"ያውና!" ፊት ለፊቷ አመለከታት......

በስተቀኝ በኩል ተጠመዘዙ......ግራ እጁን ያዘችው......እንደ ድንጋይ ጠንካሮች ናቸው......

"ክንድህ እንዴት ጠንካራ ነው"

አሁንም ትንሽ የሳቅ ድምፅ ጉሮሮው አሰማ......አልመለሰላትም......

'ወንድ ነህ' ለማለትና ትምክህቱን ከፍ ለማድረግ የሰነዘረችው ነበር......

'ገባው ወይስ አልገባውም' አለች ለራሷ

'ጠንካራ ወንድ ነህ ሳይሆን የቀን ሠራተኛ ኩሊ ነህ ለዚህ ነው የጠነከርከው! ያልኩት መስሎት ይሆን' ---ተጸነጋገራት::

"ከዚያች የአምፑል መብራት ይርቃል ቤትህ?" አለችው......ቆም አለና መሬት መሬት ከሚያይበት ቀና ብሎ ፊት ለፊቱ ተመለከተ......

"እሱ ዘንድ ነው"............

ተረቱን መጨረስ ረስቶአል:: እቤቱ ደርሰው ከኪሱ ቁልፍ ለማውጣት ሲታገል ከአምፖሉ የሚሰራጨው የብርሃን ኳስ ፊቱ ላይ ነጠረ......ግንባሩ ላይ ያሉት መስመሮች ጨምረዋል.....ምናልባት ሁለት



@BOOKALEM

ያህል......ትንንሽ ከንፈሮቹ ወደ ውስጥ ገብተዋል.....ጊዜ እየጠበቀ የሚነቃነቅ አገሬጩን ሲያዩት ከንፈሮቹን የሚያሳምጣቸው ይመስላል.....በሩ የተዘጋበትን ቁልፍ ከፍቶ ወደ ውስጥ ሲገባ የተናጋው ደጃፍ እውስጥ ድረስ ተነቃንቆ የብረት እቃዎች አቅጨለጨሉ...

......ሲል ሲል የሚለው......

ከውጭ የገባችው ትንሽ ብርሃን የቤቷን ከፊል አበራች......ዘንባባ አንገትዋን መዝዛ ወደ ውስጥ ተመለከተች......ምንም ነገር አልታያትም .....በሩ ሥር መለያያቸው በአፈር የተሞላ ሰፋፊ የጣውላ ማስመሪያዎች (ስጐች) ወለል አየች......

ከቆመችበት ግራና ቀኝ ወደ ውጭ ተመለከተች......የሚራገጥ ጨለማ ነው......የማይታዩ እጆች አንገት ለማነቅ ለብቻቸው የሚንሳፈፉበት አይነት ጨለማ---ቢኖር:: የመብራት ማብሪያ ድምፅ ሰማች......ከውስጥ ብርሃን ወጣ:: ቤቱን እንደ ድመት በአይኖቿና በእግሮቿ እየፈተሸች ገባች......አብዲ ከኋላዋ፣ ከጀርባዋ እያየት በቀስታ በሩን ዘጋ......ቤቱን ከጣሪያው እስከ ወለሉ ጭንቅላቷን እያዞረች ተመለከተች:: አንድ ክፍል ናት......ካኪ የመሰለ ጆንያ እንደኮርኒስ ተወጥሮበታል......አንድ ሽቦ አልጋ አንዱ ጥግ ተተክሎአል......ብርድ ልብስና አንሶላው አንድ ጐን ተቆልለዋል----ከአልጋው የሰፋ ያረጀ የጥጥ ፍራሽ አጋልጠው::

አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጦ ቀና ብሎ አያት......ከጐን በሚበራው ብርሃን ፊቱ የበለጠ የሻከረ......ሰፊ ግራ እጁ በትንሹ ሲንቀጠቀጥ ያየችው መሰላት......

"አልጋውን ሳንጥፈው" አለችው......

ለማነጠፍ እንዲመቻት ከተቀመጠበት ተነስቶላት በሩ ሥር ቆመ......

ጀርባዋን ወደ እሱ አዙራ ስታነጥፍ የራሱን አቋም ዝቅ ብሎ አየ......

ጭኑ ላይ የተለደፈ የሚመስል ነጭ ነገር ተመልክቶ ለመፋቅ ሲሞክር ዘንባባ ወደ እሱ ሳትዞር:

"አልጋህን ሁልጊዜ እንደዚህ ነው የምትተወው?" አለችው......

እጁን ሰብስቦ ቶሎ ኪሱ ከተተ......"እ......እ......እ" አላት......ካጐነበሰችበት ቀና ብላ አየችው......ፊቱን በማፈር ቶሎ አዙሮ ግድግዳ ላይ ወደተሰቀሉት ጨርቆች አፈጠጠ......

"ወንበሩን ወስደህ እዚያ ተቀመጥ" አለችው......

እንዳለችው ቶሎ ተሸክሞ ከአልጋው ዞር ብሎ ተቀመጠ......



@BOOKALEM

አንዳንዴ ብቻ ወደ ጉን ዞር እያለ በጉሪጥ በማጉንበስ ሽቅብ በተነሳው ቀሚሷ ሥር እንደ ሕፃን ልጅ ጭኖች የተከተፉ የመሰሉ ወፋፍራም ጭኖችዋን እያየ እጁን ወደ ኪሱ ውስጥ የበለጠ ይቀብራል......

ከሚነጠፍ አልጋና......ሰገነቱን ለመሥራት በዙሪያው ስትሽከረከር እግሮችዋ ከሚያሰሙት ድምፅ በስተቀር ጭርታ ቤቷን አፈናት...... አብዲ ፈራ......

"ና በል ተኛ" አለችው......

ጀርባውን አዙሮ ያለ ጥድፊያ ልብሱን እያወለቀ ዞር ብሎ አያት......

"እዚህ የምትኖረው ብቻህን ነው?" ብላ ጠየቀችውና አልጋው ላይ ተራምዳ ወጣች......

"ምን ይደረጋል......ብቻዬን መኖር ይሻለኛል" አላት

"ለምን ታዲያ እኔን ይዘህ መጣህ?»

አልመለሰላትም::

ሙታንታ ያልሸፈነው ብልቱን በሠፊ ቀኝ እጁ አቅፎ ብርድ ልብሱን በግራው ገፎ አልጋ ላይ ወጣ......

አንሶላዎች መሃል ገብታ ልብስዋን እያወለቀች፣ በከለላት ቀሚስ ድምፅዋ እየታፈነ......

"ሰው ትፈራለህ መሰለኝ"

"ኧረ ይፈሩኛል"

"ይፈሩሃል......እኛ መጠጥ ቤት ያሉ ሴቶች በሙሉ ይፈሩሃል" 'ይንቁሃል' ልትለው አልፈለገችም::

"እኔ ደግሞ ሁሉንም እፈራቸዋለሁ"

በቤቱ አጠገብ የብዙ ሰዎች የሩጫ ድምፅ ኮቴ ቀርቦ እየራቀ አልፎ ሄደ......

"እዚህ አካባቢ ሌባ ይበዛል አሉ" አለችው

"ለምን ሰው ሰርቆ እንደማይበላ አይገባኝም......አንድ ቀን ሰው ሠረቀ ተብሎ የተያዘው አንድ ሌባ......የሚደንቅ ነው......ምንትስ የሚያክል ነው......ይሔ ራሱ የእኔን ሁለት ያክላል"

ታሪክ ለማናገር ያለ እቅድ የሚያነቃንቀው እግሩ ጭኗ መሃል ገባ:: የሚያሳያትን የከንዱን ጡንቻ በጀርባው ተጋድሞ ወደ ላይ እንደሰቀለ ዞር ብሎ አያት......



@BOOKALEM

እጅዋን ወደ እግሮቹ መሃል ሰደደች......ፊቱን ወደ እሱዋ አዙሮ ሰረሰሯን እስኪያማት ድረስ በግዙፍ ክንዶቹ አቀፋት......ብዙም ሳይቆይ የሚያቃትት ትኩስ ትንፋሻቸው ክፍልዋን እንደ እጣን ጢስ ሞላት......

"ባል አግብተሻል?......በፊት" አላት በሆዱ ተኝቶ ፊቷን እያየ።

"አግብቼአለሁ......ትዳር ካቆምኩ አስር ወር ሊሆነኝ ነው"

"ትዳር ጥሩ ነው......አይደለም?"

ትንሽ ቆየች.....ያላሰበችው ነገር ነው......አብሮአት ይኖር የነበረው ወንድ 'ባል' ይባል ነበር። እንዲህ ነገሩ ከተበለሻሸ በኋላ ትንሽ ገባት እንጂ......ጥሩና መጥፎነቱን መለኪያውን አታውቅም ነበር......አሁን አሁን ከባልዋ የተለያዩበት ምክንያት ግልጽም ሆኖ አይታያትም......ከተፋታች ግን አሥር ወር ብቻ ቢሆናት ነው......የአምስት አመት ትዳሯ ለሁለት ደቂቃ ወሬ ማድመቂያ መሆን አለመቻልዋ......

ማሰብ አልፈለገችም። ማን ይወዳል ውድቀቱን ሳጋጠመው ባይተዋር መለፈፍ......

«እንደ ሁኔታው ነው» አለች።

የለመደችው ነው። ከትክክለኛ መልስ ይልቅ ታጥበው የተቀመጡ መሸወጃ ሙልጭልጭ አባባሎች ምላስዋ ላይ ደርድራለች። ሞቅ ያለ ጥያቄ ሲመጣ አጫጭር የሚያበርዱ መልሶች አዘጋጅታለች። የሚያድናት መልስ መሰላት። ከእሱ ጥያቄዎች ማምለጫ ቢሆናትም ልብዋ ውስጥ ግን ያልተሟላች መኾንዋን ታውቃለች። የምትሰራበት ሆቴል ቤርጎ ብዙ ጊዜ ችኩል ብለው የሚገቡ፣ ችኩል ብለው የሚጓዙ ችኩል ብለው የሚወጡ ተገላማጭ ባለትዳር ሴቶች ይመጣሉ። ንጹህ ወሲብ ለውሽማቸው ይሰጡ ይሆናል። እስኪለምዱትም ድረስ በሂያጅነታቸው ለጥቂት ጊዜ አፍረው ባላቸውን ቀና ብለው ማየት ይቀፋቸዋል። ቀስ በቀስ ስርቆት ሲለምዱ ለባላቸው ብቻ ሊሰጡት የገቡትን ቃል ይረሱታል። ቀን የት ውለው እንደነበር ይረሱታል። እነዚህ ባለትዳር የተባሉ እህቶችዋ ግን በጋራ ስም እንደሚጋሯት ትረሳለች 'ሽርሙጣ' ......

"ባልሽ ምን ይሠራ ነበር?"

"ክረምት ክረምት ያርሳል፣ የእርሻው ስራ ሲያቆም እንጨት ይቆርጣል......ረዣዥም ዛፎች በገመድ እየወጣ የሚቆርጥ፣ በዶፍ.....ማዕበል በሚመስል ዝናብ ውስጥ የሚወዛወዙ ዛፎች ላይ ተጣብቆ እያነጣጠረ ግንድ ሲቆርጥ ድፍረቱና ጥንካሬው ማረከኝ......ጠላ ሊጠጣ እናቴ ቤት ሲመጣ ተዋወቅን......በ15 ቀን ውስጥ እንድንጋባ ጠየቀኝ......ተጋባን ......በቃ......"



@BOOKALEM

"መጠጥ እንደ እኔ ይጠጣል?"

«አይቀምስም......እናቴ ቤት አንዳንዴ......ለእኔ ሲል ጠላ ይሞክራል"

"አልወለድሽም?"

"አንድ ወለድኩ......ሞተ...... ያልጨነቀህን ነው የምትጠይቀው"

"ሌላ ምን አለ......መቼም......"

"ስለ ትዳር ሲነሳ እጠላለሁ......የሚቀጥለው ሳምንት ጓደኛዬ ታገባለች.....አንድ መንደር አብረን ነበርን......አንድ ነጋዴ አዲስ አበባ የሚኖር ያገሯ ልጅ እዚህ አምጥቶአታል......ሚዜ ሁኚኝ ብላኛለች ልብስ ደ'ሞ የለኝም ምን እንደምላት አፈርሁ" አፍዋን ያዘች......

"ልብስ የለኝም አትያትም?"

የአብዲን ቤት አልፎ ሄዶ የነበረው የኮቴዎች ስልፍ ቀድሞ ወደመጣበት አቅጣጫ ተመለሰ......

ሲያዳምጡ ከቆዩ በኋላ......

"በሌሊት ሰው ይረብሻሉ" አለች

"ይሔ ሌባው እኮ ሠላም አሳጣው ሰውን......ለምን ልብስ የለኝም አትያትም"

ጓደኛዋ በእስዋ ቦታ ብትሆን እንደማታረገው ታምናለች......አስቀድማ የነገረቻት፣ ከነጋዴው ሳይተጫጩ የመንግሥት ሥራ እንደምትሠራና ጥሩ ብር እንደምታገኝ ነበር......'ሴተኛ አዳሪ ነኝ......መቼም ገንዘብ እንደፈለጉት አይመጣም' ብትላት......ታርቃታለች......ጓደኛዬም አትላት።

......ብዙ ገንዘብ ያላትን የአገሯን ልጅ ጓደኛ ማድረግ በእሷ ዘንድ የሚፈለግ ዋና ጉዳይ ነው......ጉራ ኾኖ ጠላቶቿን ያደናግራል......ከእለታት አንድ ቀን ግን መታወቁ አይቀርም......የ የፈረደበት 'ዕለታት አንድ ቀን' እስኪመጣ ዋሽቶ መጠበቅ ይሻላል......

* * *

......እንዲት መስታወት ግድግዳ ላይ በምስማር ከተመታ ዘንቢል ውስጥ አወጣና የጠዋት ቀዝቃዛ አየር ወደሚያስገባው በር ዙሮ ማበጠር ጀመረ......

ከጭንቅላት ፀጉሩ ላይ የተሰደዱ አባራዎች እንደ ደቃቅ ቢራቢሮዎች እየተንሳፈፉ ቻፍግፍግ ያለው ርጥብ ጢሙ ላይ አረፉ......ግጥም ያሉ ከንፈሮቹን ፈልቅቆ ጥርሶቹን ፈተሸ......ገላቸው ቢጫ ኾኖ ጫፋቸው በግራጫ የቀለም ብሩሽ የተነካካ ይመስላል......



@BOOKALEM

በጣቱ ፋቀ::

የቱታውን ኮሌታ ጉትቶ በውስጠኛው ጨርቅ ጥርሱን እየፈተገ አልጋ ላይ ወደተጋደመችው ዘንባባ ዞረ......አይኗ ቀልቶአል......ጉጽዋ ተለዋወጠበት::

"ምነው?" አላት

* * *

ወፍጮ ቤቱን ከወለል እስከጣራ የደፈነው እንደ ጉም የሚያደርገው የእህል ዱቄት አንዳንዴ በአብዲ በተለኩሰ የሲጋራ ፍም ቅላት ይገሰሳል.....

"አብዲ!"

"አቤት!"

"ለአደም መልእክት ትነግርልኛለህ ......ና!"

ያናገረው (ያዘዘው) ሰው ከበሩ ላይ ከጫፍ እስከ ጫፍ የተቆለፈ የካፖርት ኪሱ ውስጥ ሁለት እጆቹን ከቶ ወደ ወፍጮ ቤቱ በሚገባው የብርሃን መደብ ሲያዩት ረዥም ዝንብ ይመስላል......

የመርካቶ ጠዋት ትርምስ እየከጀላት ነው......አብዲ የሰውዬውን ንግግር አጣርቶ ሊሰማው ስላልቻለ ሲጋራውን እየሳበ ግራ እጁን ወደ ኋላ አጣምሮ ጥላሞቱን ተጠጋው......

"ምን አሉኝ ጌታዬ?"

"አደምን......ምነው? ባርኔጣህን አውልቅ እንጂ ስርዓትም የለ?......የሚሰጥህ እቃ አለ......ተጠንቅቀህ ይዘኸው ና......እንዳይበላሽ"

እንገቱን ሰብሮ ሳይነቃንቅ......የሚያብረቀርቅ ጥቁር ጫማቸው ላይ ዓይኖቹን ተክሎ ጠበቃቸው......

"አብዲ!!......አትቸኩል......ቀስ በል:: ትእግስተኛ አልነበርክ? ቀውስኛ ሆንክ:: ፈጭታችሁ ጨርሱ......መጀመሪያ ለደመወዝህ አታስብ......መጀመሪያ ለስራ ነው የሚታሰበው......ልጅ የለህ አንተ......እነሱ እንኳን......"

ሰውዬውን ትተአቸው ወጣ......ራሱን ነቅነቅ አደረገና (ዱቄት ሊያራግፍ ይሆን ወይ ትዕዛዛብት) በጣቶቹ መሃል ያስራትን ሲጋራ ለመጨረሻ ጊዜ ሳባት......መሬት ላይ ጥሎ በእግሩ ረገጣትና ወደ ጌታው ዞሮ:

"ጫማዎ በአቧራ ቆሽሾአል" አላቸው......

ሰውዬው በድንጋጤ......አንድ ጊዜ ጫማቸውን አንድ ጊዜ ከደረጃው ላይ ሽቅብ የወረወረላቸውን ሽሙጥ ቀልበው ውጠው አፍጠው አዩት......ወደ ኋላቸው ወደ ወፍጮ ቤቱ ውስጥ ሲገላመጡ



@BOOKALEM

በዱቄት ጉም ውስጥ እንደ መናፍስት የሚንሳፈፉ የሚመስሉ የሶስት ሰዎች ፊቶች---ይስቁባቸዋል......

* * *

ያዲሱ ገበያ ግርግር ያው ነው......አብዲ ረዥም ቁመቱን እየጐተተ አደም ሱቅ በር ሥር ቆመ......ባንኮኒውን የተደገፈች አረብ የምትመስል ቀይ ሴት ያልተለኰሰ ሲጋራ ይዛ አቧራማ ተራራ መስሎ ፊቷ የተገተረውን ሰው ስታይ በረዣዥም ጣቶቿ ታቆላምጠው የነበረው ፊቷ ተደናገጠ......

"አደም የለም?" አላት

መንፈሷ ተረጋጋ።

"እዚህ ጐን ያለው ሱቅ ነው ያለው......ይመጣል" አለችው

ነጋዴዎች የማይወዳጁት ሰው እንደሌለ ብታውቅም ከዚህ አይነት የአመድ ክረብታ ጋር ባሏ ምን ጉዳይ እንደሚኖረው ለመገመት ሞከረች......ጥራት ያላት ሱቃቸውን ያጐደፋት መሰላት......እቆመበት እየተሽከረረከረ የተደረደሩትን እቃዎች ይመለከታል......

"ሰው ልከህ ነው?"

"አዎ" አላት እሷን ሳያይ

"ማን ላከህ? "

"ጌታዬ ናቸው" አለ ለመሳቅ እየሞከረ።

"ማን ጌታዬ?" ነገር የሚያወራም......ሽሙጥ የሚደረድርም መሰላት። አባባሉን ለመመርመር ጥቂት አሰበችና፡

"ከአቶ......ዘሪሁን ነው?" እየፈራች እንደምትናገር አይነት ቃላቶቹን እየቆጠረች......

"እንዴት አወቅሽ?" አላት ቶሎ ዞሮ......

ለወሲበኛ አስተያየት የምትጠቀምባቸው የተገረበቡ አይኖቿን በመጠኑ በልቅጣ መላ ሰውነቱን ከፍ ዝቅ አርጋ አየችው......ባርኔጣውን አውልቆ......ከእጆቹ ላይ ዱቄቱን አራገፈና ጉሬዛ ሲጋራውን አቀጣጠለ......

ሱቋን የአቧራ ፋብሪካ ከማስመሰሉ በፊት ለመገላገል፡

"አደምን......ልጥራልህ" አለችውና ከሱቋ ወጣች......

* * *

"እዚህ ነበር"

"ታዲያ የት ሔደ?"

ጠረጴዛውን በአይኗ በረበረች......



@BOOKALEM

"እዚህ ላይ ዘርግቼው የነበረው ቀሚስ የለም"

በባንኩኒው ላይ ተንጠራርታ ድንገት ተንሸራቶ ወደ ታች ወድቆ እንደኾነ ብላ ኮመዲናው ሥር አየች:: እየሮጠች ወጥታ ሰው የሚመላለስበትን መንገድ ተመለከተች......የአብዲ ባርኔጣ ሰዎች መሃል ውልብ አለባት......አንገቷ ላይ ተንጠልጥሎ የነበረ ሻርፒን ወርውራ በሩጫ ተከተለችው......

ከአባቷ አይን እንደተሰወረች "ሌባ!ሌባ!ሌባ" እያለች መጮህ ጀመረች::

ኩርማን መርካቶ ተከተላት......

* * *

"ለኪው......ለኪው"

"ይሔ የመኳንንቶች እኩ ነው......የወይዛዝርት"

"ምን ያንስሻል?"

"አትቀልድ......"

እየተሽከረመመች ቀሚሱን እያገላበጠች አየች......

ስለ ጨርቆች አሠራር እንደሚያውቅ እየጐተተች የክሮችን ሰልፍ የቀለሞችን አሰበጣጠርና ሕብር እያየች......

"ሌላ ነው......በስንት ገዛኸው?"

"ምን ያረግልሻል......ብቻ አንቺ ሞክሪው"

ራቁቷን ተነስታ ቆመች......ትናንሽ ጡቶችዋ በአልጋው ንቅናቄ እየደነሱ ቀሚሷን አጠለቀች......

"የጓደኛሽ ሠርግ መቼ ነው?"

"ለእሱ ነው የገዛህልኝ?" አለችው

ቃላት ለማውጣት ስሜቱ እምቢ ስላለው ራሱን ብቻ በአወንታ ነቀነቀ......

"ና!! ቅረብ እስኪ" አለችው እጆችዋን ዘርግታ......

ሌብነት ሐጢያት እንደኾነ ታውቃለች:: አ! ታውቃለች:: ሌብነትና ፍቅር ሲታገሉ ፍቅር ከረታ......ደ'ሞ አዲስአባ ግድ አላትን በረሃብ ተመተህ ብትወድቅ? እቅፍ ሙሉ ልጆችህ በረሃብ መቀስ ቢሸነሽኑ......በዚህች በተወለደችባት ምድር ደስታዋ ከሌላው ለምን ያነሰ ይሁን......ካላበው ፊቷ የሚነሳው ጠረን ከአዲሱ ቀሚስ የተጋባባት የሽቶ ጠረንና የአብዲ ጹቂት ነው:: ከእነ ልፍስፍስ የጨርቅ ባርኔጣው ጭኗ መሃል ፊቱን ሲሸጉጥ ተያይዘው ወደቁ......በሳቅ መፍነክነክ ሲጀምሩ ሌሊት የተቀሰቀሰባት፣ ጠዋት አልጋ ላይ አስተኝቶ ያስቀራት ራስ ምታትዋ......

ጣውላ አጥር ላይ ቆመው የሚዘምሩ ወፎች......በፍጥነት የሚንከራከሩ ሙዚቃዎች......ደስ የሚል አካባቢውን በየአቅጣጫው የሚሸነሽን የሴት ሳቅ፣ እና ከውስጥ......ከጥልቅ ከአንጀቱ በላዩ ላይ ሳይዘልቅ አብዲ በፈገግታ ፍርፍር አለ......

* * *

ሃምሳ አለቃው ባርኔጣውን ፋይሎች ክምር ላይ ጥሎታል......አደም፣ እህቱና አቶ ዘሪሁን ተቀምጠዋል......

"ሠርቀሃል"

"እዎ ሠርቄአለሁ"

"እቃው የታለ?"

"የያዙኝ በታች መንገድ የነበሩት ሰዎች ጨርቁን ቀሙኝ"

ሃምሳ አለቃው ትክ ብለው አየው::

"ታውቃቸዋለህ ሰዎቹን?" አለ ሃምሳ አለቃው

"እንዴት ብዬ ጌታዬ"

"ቀሚሱ ውድ ነው እህት?" አሳት ሃምሳ አለቃው ወደ አደም እህት ዞሮ::

"ሰባ አምስት ብር ነው ብዬ ነገርኩዎት"

"ሥራህን ከምታቋርጥና ከምትጉዳ ቀሚሱን ብታመጣ አይሻልም?"

"ቢኖረኝ ለምን አላመጣም ጌታዬ......መታሰርና ሥራ መፍታት እኔ እወዳለሁ ይመስልዎታል?"

"የት አካባቢ ነው የተቀማሽው?"

"ሰባተኛ"

ሃምሳ አለቃው ከሚጽፍበት መዝገብ ላይ ቀና ብሎ ለመጠየቅ ሲሞክር አቶ ዘሪሁን ተቻኩለው:

"ለምን ሰረቅህ? ምን ጎደለብህ፣ ደህናው ሰው ትበላሽ?......አሰዳቢ" አሉት

"ገብጋባ ነዎት:: የሚሰጡኝ አልበቃኝም"

"ተርፎህ ትጠጣበት የለም......ሃምሳ አለቃ! ከነስሙ 'አብዲ ሠካራሙ' ነው የሚባለው" አሉ አቶ ዘሪሁን::

ሃምሳ አለቃው አብዲን ዞር ብለው አየውና:

"ስማህ አብዲ ይሔ ጉዳይ ፍርድ ቤት ቢቀርብ ቀሚሱን መልሰህ ......ቢያንስ ከአንድ ወር እስራት ጋር፤ ካልኸነ፣ ማለት ቀሚሱን ካልመለስክ ሁለት ወርህን ትጠጣለህ"

"ምን አደርጋለሁ:: ሁለት ወሬን እጠጣለሁ"

ሃምሳ አለቃው ዙሪያው ያሉትን ሰዎች በሙሉ ገላምጦ አብዲ ላይ አተኩረ......ንግግር ለመጀመር የእጅ እንቅስቃሴ ሲያሳይ......አንድ



@BOOKALEM

ፖሊስ እየሮጠ ገብቶ ሙሉ ሥርአት ያልጠበቀ የችኩላ ሠላምታ አቀረበና እንደሚፈለግ ነገረው......

ከተቀመጠበት በፍጥነት ተነሳ......ለእንግዶቹና ለአብዲ ባርኔጣ በያዘበት እጁ የመሰናበቻ አይነት ሠላምታ እየሠጠ:

"አብዲ ሌባው ሁለት ወርህን ጠጣ» አለ።

* * *

አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ በር ላይ ቆማ በሩት እጇን አወዛውዛ ጠራችው......

"ማንን ነው የምትፈልጊው?" አላት ከአፍንጫው ሥር በጣም ጥቁር ጢም እንደ ቀበቶ የዘረጋ ተራ ፖሊስ......

"አብዲን" አለችው

"አብዲ ማን"

የአባቱን ስም አታውቀውም......ስህተቷ ትንሽ ቢያስደነግጣትም ሆዷ ድረስ አልዋጠችውም......

"ያው እዚያ" አለችው

አብዲ እምብርቱ ድረስ ተጋልጠ ፀሐይ ይሞቃል.....አጠገቡ ያሉ ሰዎች ክብ መስመር ሰርተው ያደሩ የጨርቆች ክምር መሃል እንደተባይ ተወትፈው ያወራሉ......

"የቱ? ዘመድሽ አይደለም እንዴ?"

"ነው......ያው ጥራልኝ" አለችው ደግማ......

አይኖችዋ እንባ ሰብስበዋል (እሱን በማየቷና ስሙን ከነአባቱ ባለማወቋ)......ፖሊሱ አንዴ እሷን አንዴ አብዲን አቀያይሮ ተመልክቶ ተጣራ......አብዲ ካጉነበሰበት ቀና አለ......እፊቷ የተጋረጡትን ሰዎች ጥሳና ቁመታቸውን ዘልቃ ለመታየት እጅዋን ወደ ላይ ስቀለችለት......በሐሳብ ተመስጦ የነበረው የአብዲ ፊት ቀስ በቀስ በርቶ አፍንጫው ተቀልብሳ ወደ ጉድጓዳ አፉ እስከትመለከት ድረስ ሳቀ......የእጅዋ ጣቶች ከአጥር በላይ ብቅ ጥልቅ ይላሉ......መዳፋቸው ጥቁር እንሶስላ የተነከረ......በሃሳቡም መለመላ ወጣትነቷ የሰርግ ቀሚስ ለብሶ ሲዘል ታየው......እና ስታቅፈው ጡቶቿ ለምን እንዲያ ለሰሉ? ድምፅዋን ከፍ አርጋ ሠላምታ መለዋወጥ አልቻለችም......ያንገዋብብ የነበረ እንባዋ ጉንጩዋን እያጠበ ወረደ......

......የላከችለትን በትንሽ ሰሐን የተቋጠረ እንጀራ ሲበላ ስስ ከንፈሮቹ ላይ ያንጠለጠላት ፈገግታ ፈንድታ ሳቅ ሳትሆን፣ በርጃም ሳትከስም ብዙ ቆየች......

— // —

ሐምሌ 1976

አዲስ አበባ



@BOOKALEM

# ጋለሞቶች

"እላበዛችውም እንዴ በእናትሽ?" አለች ሳባ

"ልማድዋ ነው እባክሽ:: መምጣትዋ አይቀር" አለች አሰገደች

"እኔ እንደዚህ አይነት ነገር እንደማልወድ አታውቂም? ሙች ወይ መምጣት ወይ መቅረት...ይኼ አንጉል ነገር ምንድነው? እኔ ስትጠራኝ አንድ ሰአት ተኩል ላይ ነይ ስትለኝ......በዚያው ሰአት እሄድላት የለ......እንድትማር ብዬ 'ሰአትሽን እይ እላታለሁ' ......ያን ቢጫ ጥርሷን ሽንት እንደሸተተው በግ 'እኝ' ታደርጋለች"

"አንቺ ደግሞ ነገር ከያዝሽ አትረሺም"

"ደስ አይልማ!......አንቺ እንደዚያ ታደርጊያለሽ?"

"ምን ታድርግ አሷ ቀጠሮ አልለመደባት" አለች አሰገደች ሳቅ ሊያስታውክ የመሰለ አፍዋን በግራ እጅዋ አፍና፣ የዋጠችው ሳቅ ሆድዋ ውስጥ እየዘለለ......በቀኝ እጅዋ የያዘችው ኮኛክ የሞላበት ብርጭቆ ሚዛን ስቶ ትንንሽ ጠብታዎች በከንፈሮቹ በኩል እጅዋ ላይ እያፈሰሰ......

"አንቺ ሙች! ሳይሆን አይቀርም......ልምድ እኮ ያስፈልጋል" በተረቧ እንዳታፍር እጆቿን መስቀልያ ዘርግታ በአፈ ሰፊ ሳቅ እየደገፈቻት......ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሂሂሂሂሂሃሃሃሃሃሃሃሃ......

"አንድ ቀን ገብርኤልዬ አንዱን አዞላት......ስትሯሯጥ አይቼአት አይ አንተ......ምን ሊያደርገን ይሆን" ፊቷን ወደ ኮርኒሱ ቀና አድርጋ እጆችዋን እያርገበገበች—ለማይታይ ባለሥልጣን......

"እንዴት?......አንቺ ደግሞ ጨዋታ መደበቅ ትወጂያለሽ"



@BOOKALEM

"እባክሽ እንዳትመጣብን......" ወደ ሺሳዋ ወደ ሳሎኑ በር ፊቷን ዞር አደረገች......

"ተዘግቷል.....ስለምታገኚኚ ብትመጣ እንሰማታለን....."

"ከልጁ ጋር አብረው ነው የሚሠሩት መጣ፤ መጣ በነው ነው.....እንዴ እስዋን ልጠይቃት ሄጄ.....የሚሠራ ነገር አለ ብላ እሱን እንዳደላት ከሌላ ከፍል አሳስጠራችሁም መሰለኝ.....ትንሽ ተነጋገሩና ሄደ.....ጉዳዩ ስለገባው ሊናገረችም የሚፈልግ ይመስላል፤ እኔን እንደ እንግዳ ወስዶኝ ፊቱ መሰለኝ.....ከዚያ ከዚያ በኋላ 'እኔንና ይኼንን ልጅ ሰው በወሬ ሊገለን ነው.....በቃ ተውቀያለሽ ተሰዋዬ ብዬ ስለጠይሁት ነው.....መጥፎ ነው?.....አንድ ቀን ትልማ ከሰአት በኋላ ራስ ሆቴል ቡና ልንጠጣ ገብተን እንደ እዚህ ያ የምትቀመጥ ወሬኛ አለች.....እሷ አይታን አታስወራ መሰለሽ.....ወይ ሙች እኛ ሴቶችን ደህ እግዚአብሔር ምን ቢያደርገን ይሻላል' አትለኝ መሰለሽ።"

"ምን? ቦይ ፍሬንዱ ነው ልትለኝ ፈልጋ ነው?"

"መቼ ጨረሰከልኝ.....ያን ጊዜማ ቦይ ፍሬንዴ ነው ብዬ አለ አይደለ እንዲገባኝ ነው.....ከንፈሮቹ ብቻ ቢመነዘሩ እናቴ የእሷ ሰውነት ተጠቃለ አይሆን፤ በኋላልሽ ይሄን ልጅ ከማን ጋር አገኘዋለሁ መሰለሽ? ከዘውዲቱ ጋር"

"ዘውዲቱ?!"

"ዘውዲቱ—አሁን ስትሬት የሆነችው"

«ሆናለች እንዴ?»

«ያንቺ ጆሮ፡፡ ያንቺ ጆሮ ያለ ሜራ አርምዴ አይሰማም፡፡ ያ ያየሽው ልብስ የዓረብ ገንዘብ እኮ ነው፡፡ ይሞቤ ትንሽ ናት ብላ ነው እሉ»

«ጉድ»

«ጉድ ትያለሽ ጉድ፡፡ ለጨርሰልሽ የዚችን ጉድ.....ናይል እንግባ አሉኝና የምሄድበት አልነበረኝም 'እሺ' አልኩና ገባን.....በጨዋታ በጨዋታ ስለ ከቤው እነሳሁላት.....ከከቤው ጋር ሽርክ ነበሩ"

"ምናለችሽ በእናትሽ?"

"ምን አስቸኮለሽ?......'አንድ ቀን እንዲሁ ሰው ቦይ ፍሬንዴ ብሎ እንዲያምንላት ያልኸን ነገር ስታወራ በጥፊ.....በጥፊ መታኋት' አትለኝ መሰለሽ፡፡ 'ኑ ብላ ብትለምን አይቀርባትም' አለችኝ፡ 'አንዳንዴ እኔን ሊያወጡኝ ሲፈልጉ የእሷንም መውጣት ግዴታ አደርገዋለሁ፡፡ ምን አለፋሽ እኔን የሚያወጣ ወንድ አብሮት ሌላ ወንደ ካለ ከቤን እንዲያወጣ በቴክኒክ እጠይቀዋለሁ' አለችኝ»

"እሷ ምን እንዲህ ያሬጋታል?"

"እንጀራት አርፋ አትቀመጥም......ለወንድ መታደልም ያስፈልጋል......እንደ ገንዘብ፣ እንደ ሀብት ማንባር ያስፈልገዋል፡፡ እስዋ እማዜር......"

"እኔ እኮ አንዳንዴ መልኳን ሳየው......ወንዶች 'ውሻ በጩው አይነካትም' የሚሏት አይነት......እንዱን በግድ ጠልፋ ቤቷ ካላስገባችው......"

"አሁን ታዲያ ወንድ መድፈር እንደጀመረች ይሉ ያልኩሽ የመስሪያ ቤቷ ልጅ አጋጠማት......አሁን መልሳ ተስፋ ቆርጣለች......በጣም ዝቅተኛነት፣ ኮምፕሌክስ ምናምን አለባት......አይመስልሽም?......ከዚያ ወዲህ ተሸማቃለች......ወንድ ፊት ለፊት ሲያዋራት አይኗ ይስባበራል......እንኪ ቅጅልኝ"

"ከራት በፊት እንዲህ ከጠጣሽ......ገና ሳትበይ ስከርሽ ማለት እኮ ነው፡፡ ጥሩ አይደለም"

"ምንም አልሆን......ቆየች ታውቂያለሽ......ለምን ራቱን አናዘጋጅም......ከደረሰች ትድረስ......ካልደረሰችም በኋላ ለብቻዋ ትብላ......ስላሳ ደቂቃ ጠበቅናት......ሙች ኮኛኩ ነው መሰለኝ......ራበኝ......ምነው ሙዚቃ በእናትሽ......ደስታን ያለ ሙዚቃ መፍጠር የሚቻል አይመስለኝም......ታውቂያለሽ? ጆሮ ስጥተውት ባያዳምጡትም......እንዲሁ ዘፋኝ ሲጮህ መስማቱ ብቻ ያረካኛል፡፡ የመጀመሪያ ቦይ ፍሬንዴ ታውቂያለሽ......አልረሳውም......ስለምንን አይደለም......ያ ባምቢስ አጠገብ ይኖር የነበረው፡፡ አንዳንዴ ሃምሳ አመት ከኖርሽው ባል የአንድ ወር ቦይ ፍሬንድሽ ትዝ ይልሻል፡፡ አቤቱ እንደወሰደኝ ገና ቦርሳዬን ከትከሻዬ ሳላወርድ ቴፑን ከፍቶ አብሬው እንድደንስ እጄን ይዞኝ......ሙቺ አሁን ሳስታውስ......ሙቺ......እንቺ ልስከር ነው እንዴ......እባክሽ ራት እንብላ"

እስኪያዞራት የጠጣችበትን ብርጭቆ አላስቀመጠችውም......ሳባ ትታት ወደ ጓዳዋ ስትገባ ከተቀመጠችበት ተነስታ በቀስታ እየተራመደች እራት መብያ ጠረጴዛው ዘንድ ሄደች......ሙዚቃውን ተከትሎ የፕላስቲኩን ሞዛይክ ወለል የሚመታው ታኮ ቆዳ ጫማዋ አልፎ አልፎ ይጮሃል......ስለወበቃት የደረበችውን ሹራብ አውልቃ ወደ ሶፋው አቅጣጫ ወረወረችው......ፊቷ እንደ ቅባት የሚፈልቅ ወዝ ነው፡፡ ሹራቡ አላማውን ስቶ ወለል ላይ ወደቀ......እዚያው አለበት ተወችው......ሞቅታው እላይዋ ላይ የነሰነሰችውን ሽቶ እያተነነ ባለችበት አካባቢ የአምስትና የአሥር ጫማ ክፈፍ ስፋት ይሰነፍጣል...... ከተቀመጠችበት ወደ ጉን ገልመጥ ስትል የልብ ቅርጽ ባለው የትንሽ ቢፌ መስታወት ውስጥ ምስሏ ታያት---መርዘም

ያቆመው ፀጉሯ ከማጅራቷ ላይ 'ፊኒር' ብሎ-እል--ጀርባዋን ላለመንካት እንዳሴረ። ይሄ ከርፋፋነቱ ሁሉ እንዳበሽቃት ነው:: ያላበው ፊቷ ላይ ሶስት አራት ቦታ ትናንሽ ኳስ መሰል ነፀብራቆች ይታያሉ......ነጣ ያለ---ከፍሉ መሐል እንደሚንቦገቦገው ፍሉ-ረሰንት:: ሁለቱም ጉንጮቿ ላይ ብስጭት የሳለባት የማድያት ካርታዎች ላይ ትንሽ ጌጤ አፈጠጠች......የከንፈሯ ቀለም በምትጠጣበት የብርጭቆ ጠርዝ ስለተዘረፈ ትላቱ በርዶአል......እጆቿ ወፍረዋል......ባሏን ከመፍታቷ በፊት ስንት ወንዶች ይሔን ከንድ እንደተንተራሱ ለመቁጠር ገና ስትጀምር......የዘንድሮ ነገር ከመሃል እየገባ ያቋርጣትና ተነጫነጪ ይላታል......

'አሉ' ና 'የሉም' የተባሉ ያዲስ አባ ወንዶችን አውጥታለች:: የዚታዎ በባይ ካለው የጭማድ የክፍለሐገር ሾፌር እስከ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ አሶሺዬት ፕሮፌሰር፣ በእድሜዋ እጥፍ ከምትበልጠው ብላቴና! እጥፍ እስከሚበልጣት አዛውንት:: አሁን ግን ነገሮች ተለዋውጠዋል:: ተወርቶባት ተንቃለች:: 'ይተኙሻል፣ ያወሩብሻል፣ ይርቁሻል'---የፈጠረችው ተረትና ምሳሌ:: በሕይወቷ በዚህ አመትና ካች አምና የትንሳኤን በዓል ያለወንድ አሳለፈች......ፀሐይ እየጠለቀች ነው:: ከሳምንት በኋላ ለሥራ ጓደኞቿ የምታወራው የላትም......ረኸም ፈቃድ የጠየቀችውም በዓሉ ሲረሳ ወደ መሥሪያ ቤቷ ለመመለስ ነው......(ይገርማታል በወንድ ስትፈለግ የተሻማቻቸው ሴቶችም ይሁኑ ተሻምተው የወሰዷት ወንዶች 'ሹሺ' ይሏት ነበር፣ አሁን ወንድ ሲጠፋ ደ`ሞ ብቸኝነቷን ማብሽቂያ ሊያደርጉት ይፈልጋሉ:: ከዚህ የበለጠ የዞረበት ሕዝብ አለ? ሳይዘነጋ በድሮ በሬ የሚያርስ):: የላሲካ በዓልዋን እንዴት እንዳሳለፈች ያኔ የሚጠይቃት የለም.....ምናልባት የሚወራ ነገር ከጠፋ በጨዋታ መሃል በውድቀቷ ሊያሾፉ ያነሱባታል.....ቢያምኑም ባያምኑም ከዱሮ ጀብዱዋ እንዱን ማውራት ነው......

......የሚከብድ ዘመን ነው......ባሏ ቤቷን ትቶላት ቢሄድም ሌላም ሰጥቷት ነው......የተቀዳደደ ውበቷን......ማድያቷን......በሲጋራ የዛገ ጥርሷን......ማደግ በቅቶት እንደ ጥፍር የኾነው ፀጉሯን......የቀጠነ ጡንቻ መኾን የጀመረ ባቷን......በጀርባዋ ስትንጋለል ወደ ብብቶቿ የሚንሸራተቱ ጡቶቿን......እነኚህን ሁሉ 'ራስሽ ያኽያቸው' ብሏት ነው የሄደው......በደረቷ በኩል ከቀሚሷ የወጣው የወርቅ መስቀልም እንደእሷ ብርሃን መፈንጠቅ አቁሞአል......ከማግባቷ ሁለት አመት በፊት ስለሞን የሰጣት ማስታወሻ ነበር......ከካች አምና እስከ ዘንድሮ ግን የስከረብቶ ከዳን የሰጣት የለም......ከእርሳስ አቅም እንኳን ከአንዳንድ ወንዶች ቀላልዷ በግድ ማስታወሻ እርጋ ለማስቀረት



@BOOKALEM

ስትፈልግ......አላማዋን የተረዱ ይመስል አሳደው ይቀሚያታል (መልዕክቱ ቢገባትም 'አሁን ለእርሳስ ይሄ ሁሉ' ትላለች::)

ከኩኖኩ ትንሽ ትንሽ እየዋጠች......ዞር ዞር እያለች በመስታወት ራስዋን ታያለች......አስጠላት......በመቀባባት ራሷን ለማን እንደምታዘጋጅ ግራ ገብቷት መሠረተቢስነቱ እስደነገጣት......ግን ዞር እያለች ወደ መስታወቱ መመልከት አላቆመችም......

......ሳባ ከሠራተኛዋ ጋር ስሀኑንም......ምኑንም ይዛ መጣች......ክትፎ፣ ቁርጥ፣ ዱለት፣ የድልህ ስሀን፣ የዶሮ ድስት፣ ወዘተ......'መቼም ቤት ያፈራውን' አለች ሳባ ወደ ጓዳ እየተመለሰች::ጠረጴዛው ላይ በስልፍና በክብ ተደርድረው እንደፍቅር ያምራሉ::

"ብራንዲውን እዚህ አቅርቢው" አለች አስገደች---ለሠራተኛዋ::

ሠራተኛዋ እምጥታ አጠገብዋ አስቀመጠችላት......ዳር ዳራቸው ዘርፍ ያላቸውን የሸሚዢን እጅታዎች ሰብስባ የምትፈልገውን ዐይነት ቀናንሳ መብላት ጀመረች......ሳባ እጓዳዋ አንዳንድ ነገር እዘጋጅታ መጣች......ብራንዲ ጠርሙሱን ካየች በኋላ:

"በእናትሽ አስገድዬ ይበቃናል ብዬ አንድ ጠርሙስ ብቻ ነበር የገዛሁት......እሷ ሳትመጣ እንዳያልቅ......ጠላ ደ'ሞ ማን ይጠጣል ......ሌላ እንዳንገዛ ደግሞ ግሮሰሪው ሩቅ ነው......"

አስገደች እንደማትሰማት ሁሉ ዝም ብላ ትበላለች......

"ስጠራሽ ትመጪያለሽ" አለቻትና ሰራተኛዋን፣ ሳባ ተረጋግታ ተቀምጣ መብላት ጀመረች......በሩን እየች፣ ራስዋን ነቀነቀች......

"ሰዓቱ ሁለት ከሩብ ኾነ እኮ......አይገርምሽም የዚህች ልጅ ነገር? ......ምን ይባላል......እኛንም ወንድ አደረገችን"

"ከእኛ ብትርቅ የሚረጥብላት፣ የወንድ ዝናብ የሚወርድላት መሰላት?"

"አሁሁ......አስገደች ሙቺ......ይሄን ብትሰማሽ አንቺን አያርገኝ"

በር ተንኳኳ......

"መጣችልሽ" አለች......ለሠራተኛዋ በሩን እንድትከፍት ጠረጴዛውን በብርጭቆ በመምታት እየጠራቻት::

ወ/ት ከበደች በር ተከፍቶላት ገባች......ኮት ደርባለች......አጭር ፀጉሯን መቆም እስከሚችሉበት ከፍታ ድረስ እንደ ትናንሽ ቀጫጭንና ጥቋቁር ሚሳይሎች ሰብስባ አቁማቻቸዋለች......እግዜርን እጉር በመፈልሰፉ የሚያሳፍረው......ጓደኞቿን ስታይ ጉርብጥብጥ ካለው ፊቷ አደይ አበባ የመሰለ ሳቅ አወጣች......ታኩ ጫማ እንዳታደርግ

ያደመባት ቀጭን ጠማማ እግሯን እንደምንም ገርታ የሥጋ ወዝና ሚጥሚጣ የተለቀለቁ የወዳጆቿን እሮች ተራ በተራ ሳመችላቸው......እዳፍኔ ማስገባት የሚችል ቦርሳዋን ሶፋው ላይ ጥላ የተዘጋጀው ማእድ አካባቢ መልኳን ተሳስታ እንኳን እንዳታይ ከመስታወቱ ፈቀቅ ብላ ተቀመጠች......

"ምን መኾንሽ ነው ከቤ......ጠብቀን፣ ጠብቀን......"

"......ደግ አደረጋችሁ" ቅር ቢላትም ቀጭኗን በሚንቦጫረቅ ሳቅ እየሸፈነች።

ሳባ፣ አስገደች የነገረቻት ነገር ትዝ ብሎአት የከቤ ስፊ ወንዳወንድ ፊት ላይ የጥፊ ምልክቱ እስካሁን እንደሚቆይ ሁሉ ሰምበር እየፈለገች፡ "ምን ኾነሽ ነው እስካሁን?" አለች......

"አሥራ አንድ ሰአት ላይ ጋደም እንዳልኩ እንቅልፍ አይወስደኝ መሰላችሁ......ጥሩ ተኛሁ፣ ግን......" ከአልጋዋ እንደተነሳች ሁሉ ያኔውኑ ፊትዋን እንደ ድመት እየጠራረገች። ቆዳዋ ላይ የተዘራው ሽፍታ ወይ አይከስም ወይ አይፋፋ......እሸዋ መስሎ ምናልባት ከልጅነትዋ ጊዜ ጀምሮ......

"እንቺ ከበደችን እጇዋን አስታጥቢያት» አለች ሳባ።

ሠራተኛዋ ከመቅጸበት መታጠቢያ ውሃና ማስታጠቢያ ሳህን ይዛ መጣችና አስታጠበቻት። እንዳንድ ነገር እየተጨዋወቱ መብላት ቀጠሉ ......ከቴፑ የሚወጣው ሙዚቃ ድምፁ ከፍ እንዲል ተደረገ......አስገደች እየበላችም እግሯንና ጭንቅላቷን ማንቃነቅ አላቆመችም......ቀድማ እንደመጀመሯ ቀድማ ጨረሰች......

እየኮረኮራት የነበረው ስካር በክትፎና በዶሮ ወጥ ሲዋጥ ይታወቃታል......እንድትሰክር ስለፈለገች ጓደኞቿ በልተው ከማጠናቀቃቸው በፊት አንድ መለኪያ ብራንዲ በችኮላ ጨልጣ ከተቀመጠችበት ተነሳች......

"የት ትሔጂ?" አለቻት ሳባ።

"ቆይ እባክሽ ይሄ ብራንዲ አይበቃንም......ደ'ሞ ብራንዲ ብቻ ይሰለቻል። አንድ ነገር ይገቤ መጣሁ......እንቺ ልጅ ምነው ስምሽ አልያዝ አለኝ ......ቦርሳዬን አቀብይኝ"

"ምን ልትሆኚ?"

"ምን ቸገረሽ"

"ሌላ ልገዛ ነው እንዳትይኝ"

"ብልስ?"



@BOOKALEM

"አይ አትሟዘዥ:: እኔ ነኝ ጋባዥ......እኔ ነኝ የምገዛው:: እንዳታመጭላት" አለች ሳባ::

አስገደች ኮትዋን ከተቀመጠበት አንስታ እየደረበች ወደ በሩ መሄድ ጀመረች:: ሳባ አልተከራከረቻትም......

"ለመሆኑ ብቻሽን ልትሄጅ ነው?"

"ታዲያ የክብር ዘበኛ ያስፈልጋል......ወይስ ሰለሞንን ልትጠሪልኝ ነው"

ከበደችና ሳባ ተያዩ......

"ታዲያ ብቻሽን? ተሟዘዝሽ......ሙዚ"

"ምን ይሆናል? መኖርያ ሠፈሬ እኮ ነው......መጣሁ ጠብቂኝ" ብላ በሳቅ እየተንከተከተች ከቤት ወጣች......

ሳባ ሠራተኛዋን ጠርታ አስገደችን ተከትላት እንድትሄድ ነገረቻት......

"እባክሽ ይህቺን እብድ ሰው እንዳይተናኮላት" አለቻት ሳቅ እያለች::

......ሠራተኛዋ ነጠላዋን ደርባ ወጣች......ከበደችና ሳባ በዝምታ ሲበሉ ትንሽ ቆዩና ሳባ ዝምታውን አፈረሰችው......

"አስገደች እኮ ትንሽ ከጠጣች አይሆንላትም" አለች፣ አፍዋን በክትፎ ሞልታ......ሳቅዋ ትን እንዳያስኛት የፈራች አይነት አፏን ይዛ--ሣቅዋም አልመጣ፣ ትንም አይላት......

"እንዴት?" አለች ከበደች......በሙሉ ልቦናዋ የምትሰማ አይመስልም:: ገና በጣት ሲነኩት እንደ በሃ የሚፈራርሰው እንቁላል የመሰጣት ትመስላለች::

"አንቺ ደግሞ አይገባሽም......ቅድም እኮ ሞቅ ሲላት 'ሳባ......ሳቢና እኔ እኮ ሞት ካለኝ......ይቆጥርብኛል......ሙቺ......የምሠራውን ነው የሚያሳጣኝ' አትለኝ መሰለሽ......"

ከበደች አሁንም ካጐነበሰችበት እንኳን ቀና አላለችም......አንድ ድፍን የእንቁላል አስኳል በአውራ ጣቷና በአመልካች ጣቷ ቆንጥጣ ሰበቃ ያሞቀው አፏ ውስጥ ቁጭ አደረገችው......በላንቃዋ ተጭና ከደረመሰችው በኋላ ወሬዋን እንድትቀጥልላት ወደ ሳባ ዞር ብላ ራስዋን ነቀነቀች......

"ተይ እባክሽ......አንቺ ጆሮሽ ላይ ተቀምጠሽ እንደኾነ እኔ ሳወራ ልውል ነው?" አለች ሳባ በሹካዋ ትንንሽ የስጋ ክትፎዎች እየለቀመች......



@BOOKALEM

"ሰምቻለሁ እኮ"

ዝም አለች ሳባ---ብድር የመመለስ አይነት......

"እንኳን ጠጥታ......ሌላም ቀን አያስችላት......ባሏ የፈታት ሳቢያ ሳይሆን አይቀርም......" አለች ሳባ ከዝምታዋ በሁዋላ::

ከበደች የእንቁላሉ አስኳል ጉሮሮዋ ላይ እንደ ሞራ ተጣበቀባት መሰል እሱን ለማስወረድ ሁለት ጉንጭ ብራንዲ ዋጠች......

"ቅድም አንድ ነገር አምልጦአት ስታጫውተኝ......ናይል አግኝቻት እና የጠራችልኝ ዘውዲቱ የተባለች ልጅ......ስትሪት ናት?......አልመሰለኝም ነበር"

"እባክሽ ራስዋም ነበረች ከአረብ---ከነገደ ሴም ጋር መሯሯጥ ከመጀመሯ በፊት ከነገደ-ካምና ከነገደ ቅማንት ጋር ሠልጥና ነበር .....ተያይዛው ነበር......ባሏ ልጇን የወሰደባት ለዚህ አይደለም? ግ ለማን ስም ይሰጣል 'አንቺን ብሎ አሳዳጊ ገና ያልበሰልሽ' ብሎ......» አለች ከበደች

"አሁን የወጣችው ወንድ ካጋጠመኝ ብላ እንዳይሆን......ሠራተኛዬ እቃ ማጠብ ትረዳኛለች......እሷንም እንዳታስጠቃት ሙቺ...... ሀ!ሀ!ሀ!"

"ልክ አልነበርሽም......ከእስዋ ጋር መሳከሽ:: ነጻ እንዳትሆን ነው ያደረግሻት......ስጠጣ...... 'አለ አይደለ......ነገር' ......ካለችሽ፣ ገረድሽን ማስቀረት ነበረብሽ......መብቷን እንደተገፈፈች ገብቷት ብልጭ ካለባት እናቷን በጠርሙስ ነው የምትመታው......"

"እሷ እኮ አንቺ ሃይለኛ ናት......ደረቅ ናት:: ራሷ ባልጋ ራሷው አስፈራርታ:: ባሏን አንገቱን ይዛ ነበር አሉ መግቢያ መውጫ የምታሳጣው......ልጅህንም ውሰድ ብላ አስፈራርታ ያስወሰደችውም እሷ ናት"

"የእሷ ጌታ ሰለሞን ነው......ያናፍጣት ነበር......ሰው አለ፣ የለም አይልም......በጥፊ ይወለውላታል......እርግጫው፣ ቦክሱ......ይሔ አሁን ማዲያት የለበሰው ፊቷ የቦክሱ ጠባሳ ሳይሆን አይቀርም......ለምን ይወዳት እንደ ነበረ እንጃ......ሸርሙጣን እንኳን ጥፊ ናጋሳኪ ላይ የወደቀው ቦምብ አይመልሳትም"

"አልጋ ላይ ሌላ ናት ይሏታል"

"የረኸርም ጊዜ ልምድ አላት! አይደለም እንዴ?......የድሮ ስሟ 'ዊ' ነበር አሉ......እኔ ለምን ፈረንሳይ ትምህርት ቤት ሊሴ መማር እንደማልወድ ታውቂያለሽ? ድንገት ለምዶብኝ 'ዊ' ካልኩ በድሮ የዱርዬ ስሜ ጠራችኝ እንዳትለኝ......እ......እንዳትቀየሚኝ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሁ ሂ ሂ ሃ ሃ ሃ ሃ ሄ ሄ ሀ ሆ»



@BOOKALEM

"እ……አይ አንቺ ግፈኛ ነሽ……እንደውም ቆየች……በኋላ ሠራተኛዬን ታታ አስደርጋት ባለቤቴን እንዳታስጠረጥረው"

"ሁለቱንም አብረሽ ማሳደግ ነዋ……ለምን እንትን አታዘጋጂም፣ የወሊብ ጆርናል……"

"እንዴት?"

"ማለቴ ከባልሽ ጋር የተኛሽበትንና……ያረገዝሽበትን ጊዜ "ባላንስ ሺት" ስሪ……"

"አይ ከቤ ደስ የማይል ነገር አትናገሪ" አለቻት……

ሳባ ከተቀመጠችበት ተነስታ ገጽዋ ተለዋውጦ ወደ ጓዳ ገብታ፡ "ከበደች……አይብ ልጨምር?" አለች፡፡

ከበደች መብላት ብትጠግብም……አይቡ (ያውም ደረቅ ዐይብ) ቢስለቻትም፣ አሁን ላጋጠማት የምላስ ዳጥ ይቅርታ መጠየቂያ ለመጠቀም የጓደኛዋን ፍላጐት ተቀብላ……

"በእናትሽ አምጭልኝ……እንዴት ወደድኩት መሰለሽ" አለቻት……

ፊቷ ውሸት አይታይበትም……ጥሩ የመቅጠፍ ልምድ ያላት ትመስላለች፡፡ ሳባ ግን የረሳች አትመስልም……ፊቷን ኩርፊያ እንደለወጠው ነው፡፡ አይቡን በትንሽ ጥቁር ሽክላ ድስት ይዛ ከበደች ፊት እንዳስቀመጠች በር ተበረገደ……

"አይገርማችሁም?" አለች አስገደች የተከፈተ የማርቲኒ ጠርሙስ ይዛ በቀጥታ ወደ ጠረጴዛው እየሄደች……ሠራተኛዋ አፍዋን በነጠላ ጋርዳ በሳቅ እየተንፈቀፈቀች ተሽሎኩሉካ ወደ ጓዳ ጠፋች……

"ምኑ?" አለች ከበደች

"አላስችል ብሎኝ ከመንገድ ከፍቼ ጠጣሁት……ልጅሽ ሳባ ሙቺ ዝርዋእት በሳቅ አትሞት መሰለሽ……ደ'ሞ እኝህ የጉረቤትሽ ሰውዬ ሽማግሌው አውላላ ሜዳ ላይ እንጋጥጨ ስነፋ አይተው……ተናደው ከዘራቸውን ሶስት ጊዜ አሽከረከሩት……ጠጅ ጠጅ ይሸታሉ"

ከበደች የጓደኛዋን ቀልድ ጠምዝዛ ነገር ለማድረግ፡ "ጠጅ ጠጅ እንደሚሸቱ እንዴት አወቅሽ?" ከምትበላበት በትንሹ ቀና ብላ እያየቻት……

ነገሩ የገባት ይመስል፡ "ሳምኳቸው……ጆሊ ሽማግሌ ናቸው……ሙቺ ከትብተብተ፣ ሲያስኙቸው ከሚማቱ ቀኑ ጉረምሳዎች ይሻላሉ……እኔ ልሙት……" አለች አስገደች

"የትኛው ሰውዬ ናቸው?" አለች ሳባ



@BOOKALEM

አስገደች የከበደች ራጋ ማለት አስደንቆአት ጠርሙሱን ጣሬጴዛ ላይ አስቀምጣ ለራስዋ በመለኪያ ሙሉ ቀዳች......ወደ ላይ አንስታ፡

"ለጤናችን" ብላ አንድ ጉንጭ ዋጠችና "ምን ያደርግልሻል ማን እንደኾኑ?" አለች

"አስቀንተሽኝ ላወርድብሽ" አለች ሳባ

"ኧረ እባክሽ......በላይ አጥር በኩል ያሉት ሰውዬ"

"በቅርብ ሰፈር የገቡ እስላሙ ሰውዬ ናቸዋ" አለች ከበደች በፍጥነት......

ሳባ ማንኪያዋን በሰለቾ ጥጋብ አንድ ነጭ ሸክላ ሳህን ላይ ጣለች......ነገሩ ስላላማማራት እቃውን ለመሰብሰብ እንደፈለገች ሁሉ ሠራተኛዋን ጠራች......

"ታውቂያለሽ አስጊ ስትደንሺ ሳይሽ ማን ትዝ እንደሚለኝ......" አለች ሳባ።

"በእናትሽ አስጊ የአሁኑን 'ስቴፕ[3]' ድገሚው"

"ከበደች ለምን የሰው ወሬ ታቋርጫለሽ?» አለች አስገደች ኮስተር ብላ።

"መቼ አቋረጥኩሽ......ቀጥይ"

አስገደች ማስፈራራት መቻሏን ካረጋገጠች በኋላ ከሳባ ጋር ለመደነስ ወደ ሳሎን መሐል ሄደች......ፊት ለፊት እየተያዩ መወጥወጥ ጀመሩ......አስገደች ታኮ ጫማዋ ስላልተመቻት አውልቃ ጥላ እየሳቀች መደነስ ጀመረች......ሳባ ከበስተኋላ የበላችው መረቅ ትን ስላላት የጀመረችውንም ወሬ ሳትጨርስ ዳንሱንም አቋርጣ ሶፋው ላይ ተቀመጠችና......የዘነጋችውንና ጀምራ የተወችውን በብርጭቆ የተሰፈረ መሉጊ ቢራ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠች። አእምሮዋ ውስጥ እንድትደሰት ከሚገፋፋት ስሜት ሌላ ብቻውን ተጉልቶ ተዝቃዛ ንፋስ የሚረጭባት ነገር እንዳለ ይታወቃታል......ባልዋ ከቤት ከሄደ ስስት ወሩ ነው......ሃያ አራት አመቷ ነው......እርግዛለች......በፋሲካ ዕለት እንኳን አብሯት ለማሳለፍ አይችልም። ማግባት ምን ይረባል......ስትወልድ ይመጣል......ማርገዝ። የማፍቀር ሳይሆን የማርገዝ ውደት። አመት ሲገባ፣ አመት ሲወጣ.....ጭኗ መሃል ያለው አውሬ ነጋ ጠባ ያዛጋል......ዘውዱን ጭኖ ይመነኩሳል......ከእነዚህ አስቀያሚዎችና አሮጊቶች ጋር ጉረቤትነት አጠጋጋቸው......ከከሠረ አራዳ ምን ይጠበቃል? እነሱን ረስታ ወደራሷ አለም ለመግባት ዳንስ

---

[3] የእግር አረጋገጥ (እንግሊዝኛ)



@BOOKALEM

ጀመረች......ያው እንደለመደችው "አላረጀሁም" የምትለው አሰገደችም በስሜት የሚያወራጫት ዳንሷን ቀጥላለች......

ከበደች እንደኾነ ሆዷን ባትወድም ከሊላ ግንኙነት ስለሚከለክላት መብላት አታቆምም......

"ድሮ ምግብ እንቅ ነበር......እንዲ ካመመኝ በኋላ ገባኝ" ትላለች ......ብዙ መብላትዋ በቀጥታ ወይ በእግቦ ሲጠቆማት......

ግን ምግብ ንቃ አታውቅም:: በምግብ ምክንያት ታመምኽ የተባለችበት ጊዜ የለም:: አሁን ገና ሊገባትም አይችልም......በጣም ማክሲ የኾነ ቀሚስ ካልለበሰች መደነስ አትችልም......እግሯ......ከለበሰችም ደግሞ መደነስ አትችልም:: ምክንያቱም ማክሲ ቀሚስ ስለሌላት......ከሰው ጋር ለመደነስ ድፍረቱ አልነበራትም:: በገዳዳ እግሯ እያፈረች፣ ስለዚህ መደነስ አትለማመድም ---አትችልም......

አሰገደች ግን ከድሮም ቢሆን 'ቢት'[*] መጠበቅ ስለምትችል ዳንስ ትሞክራለች......ከበደች አንድ ሁለት ጉንጭ ማርቲኒ (በደንብ ያበጡ ጉንጮች) ከጨለጠች በኋላ እጆቿን ተጣጥባ ከተቀመጠችበት ተነስታ ተቀላቀለቻቸው......ክፍሉ ውስጥ ትርምስ በመብዛቱ ምን እንደሚደረግ ለማየት ሠራተኛዋ መጣች......አፍራ ልትመለስ ስትል አሰገደች ጠራቻት......ሰክራም ሳትሰክርም ማሕበራዊ አሰገደች ናት:: 'የትም ሄዳ ታድራለች' ይሏታል::

"አትደንሺም አንቺ?" አለች አሰገደች ልጅቷን:: ልጅቷ አልመለሰችላትም፣ ሳቅ የወጠረው አፏን በእጇ ይዛ ወደ ጓዳ ጠፋች......

....ሙዚቃው አለቀ......አሰገደች ደክሟት ወደ ሶፋው ሄዳ ተቀመጠች......ከበደች የማርቲኒውን ጠርሙስ ከምግብ ጠረጴዛው ላይ አምጥታ ለሶስቱም ቀዳች......ከአምቦ ውሃው ለራሷ የሚበቃትን ከወሰደች በኋላ ተወችላቸው......ቤቱ ርካታ የገባበት ይመስላል......አንዳንዱ እቃ ሁነኛ ቀለሙን ሳይደብቅ ያበራል......መስታወቱም በውስጡ ምስሉችን ማንጸባረቁ አልቀረም......

"ፋሲካ ማለት ይሄ ነው......አይደለም?" አለች አሰገደች::

"ታዲያ ምን ትፈልጊያለሽ?" ራስዋን ለማስከር የምታደርገው ጥረት እየሠመረላት ይመስላል......

"ሳባ እንዳያምሽ ብዙ አትጠጪ"

"ምን እሆናለሁ" አለች ሳባ

---

[*] ምት (እንግሊዘኛ)



@BOOKALEM

ጀመረች……ያው እንደለመደችው "አላረጀሁም" የምትለው አስገደችም በስሜት የሚያወራጯት ዳንሷን ቀጥላለች……

ከበደች እንደኾነ ሆዷን ባትወድም ከሊላ ግንኙነት ስለሚከለክላት መብላት አታቆምም……

"ድሮ ምግብ እንቅ ነበር……እንዴ ካመመኝ በኋላ ገባኝ" ትላለች ……ብዙ መብላትዋ በቀጥታ ወይ በአግቦ ሲጠቆማት……

ግን ምግብ ንቃ አታውቅም:: በምግብ ምክንያት ታመምሽ የተባለችበት ጊዜ የለም:: አሁን ገና ሊገባትም አይችልም……በጣም ማክሲ የኾነ ቀሚስ ካልለበሰች መደነስ አትችልም……እግሯ……ከለበሰችም ደግሞ መደነስ አትችልም:: ምክንያቱም ማክሲ ቀሚስ ስለሌላት……ከሰው ጋር ለመደነስ ድፍረቱ አልነበራትም:: በገዳዳ እግሯ እያፈረች፣ ስለዚህ መደነስ አትለማመድም ---አትችልም……

አስገደች ግን ከድሮም ቢሆን 'ቢት'[4] መጠበቅ ስለምትችል ዳንስ ትሞክራለች……ከበደች አንድ ሁለት ጉንጭ ማርቲኒ (በደንብ ያበጡ ጉንጮች) ከጨለጠች በኋላ እጆቿን ተጣጥባ ከተቀመጠችበት ተነስታ ተቀላቀለቻቸው……ክፍሉ ውስጥ ትርምስ በመብዛቱ ምን እንደሚደረግ ለማየት ሠራተኛዋ መጣች……አፍራ ልትመለስ ስትል አስገደች ጠራቻት……ስክራም ሳትሰክርም ማሕበራዊ አስገደች ናት:: 'የትም ሂዳ ታድራለች' ይሏታል::

"አትደንሽም አንቺ?" አለች አስገደች ልጅቷን:: ልጅቷ አልመለሰችላትም፣ ሳቅ የወጠረው አፏን በእጇ ይዛ ወደ ጓዳ ጠፋች……

….ሙዚቃው አለቀ……አስገደች ደክሟት ወደ ሶፋው ሂዳ ተቀመጠች……ከበደች የማርቲኒውን ጠርሙስ ከምግብ ጠረጴዛው ላይ አምጥታ ለሶስቱም ቀዳች……ከአምቦ ውሃው ለራሷ የሚበቃትን ከወሰደች በኋላ ተወችላቸው……ቤቱ ርካታ የገባበት ይመስላል……አንዳንዱ እቃ ሁነኛ ቀለሙን ሳይደብቅ ያበራል……መስታወቱም በውስጡ ምስሉችን ማንጸባረቁ አልቀረም……

"ፋሲካ ማለት ይሄ ነው……አይደለም?" አለች አስገደች::

"ታዲያ ምን ትፈልጊያለሽ?" ራስዋን ለማስከር የምታደርገው ጥረት እየሠመረላት ይመስላል……

"ሳባ እንዳያምሽ ብዙ አትጠጪ"

"ምን እሆናለሁ" አለች ሳባ

---

[4] ምት (እንግሊዝኛ)



@BOOKALEM

"እንዲሁ ነገሩን ነው......አንቺ ደግሞ ሰለሞንን ያረግሻል......ሰለሞን ታውቃላችሁ? አድርግ ያሉትን አያደርግም:: 'ሰለሞን በእናትህ ስሞትልህ የፀሐይ መነጽርህ ያምርብሃል እርገው፥ ስለው ትቶት ይመጣል......ለምን ሶስት የቀትር ፀሐዮች ሰማይ ላይ አይወጡም......'አፍሮህ እንዲያድግ ትንሽ ቅባት ግዛለት' ካልኩት የባስ በመቀስ አሳጥሮት ይመጣል......'አካሄድህ ያምራል' ብለው እግሩን ቆርጦ ሳይመጣ አይቀርም......አሁንም አንቺ......"

ሳባ የምትሰማት አይመስልም......ጭንቅላቷን ሶፋው መደገፊያ ላይ እንዳንተራሰች አይኖቿ ገርበብ አሉ......የያዘችው ብርጭቆ ከእጇ ሸርተት ብሎ ወደቀ......

"ሰማሽ አንቺ መድኃኒቱን አምጭላት!" አለች አስገደች በድንጋጤ::

ሠራተኛዋ ነጠላዋን ወርውራ ወደ ሌላ ክፍል ገባች......አስገደች ዋናውን በርና ከኋላዋ ያለውን የሳሎን መስኮት ከፈተች:: የሳባን ካናቴራ የጉርድ ቀሚሷ ላስቲክ ጨምድዶ ከያዘበት ወገቧ አላቃ ወደ እንገቷ ጉትታ ወተት መጠራቀም የጀመረባቸውን ጡቶቿን ነፋስ እንዲገባባቸው ከፈተችላት......ከኋላና ከጐን የሚመጣው ነፋስ ገላዋን ማቀዝቀዝ ጀመረ......ከበደች በመሐረብ ውሃ ነክራ አመጣች......ግንባሯ ላይ፣ አንገቷና ጡቷ ላይ እያርከፈከፉና እየዳበሱ አረጠቧት......አስገደች በሳባ ጡት ውበት የተደነቀች አይነት ማራገቧን ትታ እንደ ወንድ ታያታለች......

ሳባ ከልብ ድካሟ ወንዝ ተንቦጫርቃ ከወጣች በኋላ ደጋግፈው መኝታ ቤት አስገቧት......

አስገደች ሰአቷን አየችና ራስዋን ነቀነቀች......ከበደች በግንባሯ ጠየቀቻት......የእጅዋን ዘጠኝ ጣቶች አየር ላይ ሰቀለች......ሳባን ከድካም እንቅልፍ ላለመቀስቀስ በቀስታ እየተራመዱ ወጡ......

በመታመሟ በርግጐ የጠፋ ስካራቸውን በቀረችው ውስኪ እሚሙቀው ሶፋ ላይ ተጋድመው ማውራት ጀመሩ......

የሁለቱም አፋቸው መንተባተብ ጀምሯል......

"ሰማሽ......ይሄ......ልብ......ድካም.....መጥፎ ነው"

"ያውም ገና ሺ ኢዝ ቬሪ ያንግ[5]"

"አንቺ ደግሞ.....'ያንግ' ማለት ትወጂያለሽ......ምን ይሠራል እሱ"

"እሱስ ምን ያደርጋል......ሳቢን እንኳን ከልብ ድካም አላዳናት"

"የልብ.....ድካምዋ ምክንያት.....ባልዋ እንደኾነ አታውቂም"

[5] በጣም ወጣት ናት (እንግሊዘኛ: She is very young)



@BOOKALEM

"ይገባኛል»

ፈጣን ሙዚቃው ቀርቶ ለስላሳ ሙዚቃ ስለሚሰማ በየዜማው መሐል ብቅ የሚለው የቤቱ ፀጥታ ሐዘን በመገመድ ላይ ያለ የሚያስመስል ስሜት ይፈጥራል......

"ከክፍለ ሐገር የመጡ ጓደኞቹ እያስወሩበት......እሷንም በአሽሙር ሰላም አሳጧት"

"ኧረ እኔም ሌላ ነገር ሰምቼአለሁ:: ይሄ ያረገዘችው ከሌላ ሰው ነው ይባላል"

"የእኛ ነገር......'ድሬዳዋ ከዚራ ባልሽ በአንዱ አብዷል' ብለዋት......እኔ ራሴ ነበርኩ...... ለእሱ ሠላምታ አድርሽልኝ ተብላ ብለዋት......እኔ ራሴ ነበርኩ...... ከድሬዳዋ የተላከችው ሴትዮ እቤቱ መጥታ ሳባ ባለችበት 'ድሬዳዋ እንዴት ናት?' ብሎ በጅምላ ሲጠይቃት......ምናለ ዝም ብትል፣ ሌላ ሌላ ነገር ዘበራረቀች:: ሳቢቲ አብድ:: የሰውስ ነገር አይገርምም? ሰው ለማቀያየም የማይሰራው ነገር የለ"

"እንዴት ዝም ይባላል:: ጨዋታ የማታውቅ ሆና ይሆናል:: የእሱን መወሽም የት ታውቃለች"

"ሳትጠረጥር ትቀራለች፣ እሱስ እዎ......በኋላ......'ምን ድሬዳዋ ጥሩ ናት በተለይ......ከዚራ ቆንጆ ቆንጆ አለ......የሚያሳብዱ' አለችና የኸነች ጎራዳ ቢጤ ናት እኮ፣ በድሬዳዋ ስም የምትነግድ፣ 'ሃቦሾች እኮ ቆንጆዎች ነን' የሚሉ አጎዶ አበሾች አያበሽቁም? ሂሂ......አልኩሽ በነገር እንደ ተግባቡ ሁሉ እሷን በሽሙጥ ፈገግታ ጉረድ አደረገቻት......እኔ የት ልግባ!!?......እንደ ምንም ብዬ ሌላ ጨዋታ አመጣሁ......"

"ማርገዟዋን መስማት ደስ ቢያሰኘውም፣ ተጠራጥሮአል ብሎኛል አንድ የመስሪያ ቤቷ ሰው......አንቺ ሚስጥር ነው......ምን አገባን......ከቤ በጣም ጠጣን አይደለም?"

"ይሄኔ ሰለሞንን ብታገኚውስ?"

"ተይ በእናትሽ ጠጥቼ እሱን ካስታወስኩ መተኛት አልችልም......ያስፈልገኛል......እንርሳው" አይኗን በቀስታ ጨፍና በዘረጋቻቸው እግሮቿ መሃል እጅዋን አስቀመጠች......

የአስገደች ሁኔታ ያሳቃት ከበደች ሶፋው ላይ ተኝታ ስትንተከተክ ጭንቅላቷን የደገፈችበት ክርኗ የሶፋውን መደገፍያ ስቶ ወለል ላይ ወደቀች......ሁለቱም ሳቃቸውን ማቆም አልቻሉም......ከበደች ከወደቀችበት በቀስታ ተነስታ እየተንገዳገደች ወደ ሽንት ቤት ሄደች......የጉሮሮዋ የድምፅ ሳጥን በሚመለስ እህል ሲታፈን ይሰማል......የኸነ ፈጣን ቋቂታ::

"ሻፕሌ......" አለች አሰገደች የጀመረችውን አረፍተነገር መቋጨል እያቃታት፣

"እ እ እ እ እ " እያለች ከበደች ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደች።

አሰገደች እየሳቀች ከተቀመጠችበት ተነስታ ጓደኛዋን መደገፍ አልቻለችም......ከበደች እያዞራት፣ እየተንገዳገደች ጨርሳ ተጣጥፋ ወደ ሳሎን ስትመለስ አሰገደች በጀርባዋ አንድ እግሯ መሬት፣ አንድ እግሯ ሶፋ ላይ ፍርክስክስ ብላ ተኝታለች......አፍዋ ቡጢ የሚያስገባ ያህል ተከፍቶአል......

ከበደች ጃኬቷን ከወንበር ላይ አንስታ እላይዋ ላይ ጣል አደረገችላትና ወደ ሶፋው ሄደች......ቴፑ ተረስቷል......የሚገለብጠው አላገኘም......ከበደችን የቤቱ ፀጥታ አስፈራራት......ጉልበቶቿን ወደ ደረቷ ሰብስባ ኩምትርትር ብላ ሶፋው ላይ ተኛች......በእንቅልፍ ልብ የምትንጠራራው አሰገደች መሬት አርፎ የነበረ አንድ እግሯን ስታነሳ የጠረጴዛውን ጠርዝ ነካችውና ማርቲኒ የያዘ መለኪያ ጠረጴዛው ላይ ተከነበለ......ከበደች ጠርሙሱ ከመውደቁ በፊት እንደ ምንም ብላ በአንድ እጇ ያዘችውና ወለል ላይ ወድቆ ከመሰበር አዳነችው......ከጠረጴዛው የላስቲክ ልብስ ላይ እንደ ባዜቃ ድቡልቡል የሆኑ ቀይ የውሃ ጠጠሮች ወለሉ ላይ እየተንጠባጠቡ ወደቁ......እሱ ላይ ስታፈጥ ቆይታ አስቀያሚ ፊቷን እየገመደች፣ እየቋጠረች በቀስታ ማልቀስ ጀመረች።

......ክፍሉ ቀዝቃዛ ባዶ ነበር......የአሰገደች ትንፋሽ ለስላሳና ረጋ ያለ ነው፣ የቴፑ ዘፈን እንደ ቆመ ነው......በልብ ድካም፣ ስመመን የገባችው ሳባ የሕመም ሕልሟን እየጨረሰች ነው......ምድር ልትነጋ ትቅበጠበጣለች......

ከበደች ለቅሶዋን አቁማ እንቅልፍ እንዲወስዳት እይደን በግድ......ጭፍን አደረገች......

---- // ----

አዲስ አበባ

ግንቦት 1977



@BOOKALEM

# የብሩክታዊት ጠጠር

ድፍን ጨረቃ በዛፎች መሃል አንዳንዴ ወደ ወንዙ ሠርቃ ታያለች......ሽሮ የመሰለው ድፍርሱ የወንዙ ውኃ እንደ መዳብ ያንፀባርቃል......ከሩቅ ሰዎች ሲጠራሩ ይሰማል......የትምህርት ቤቱ ዘበኛ የጥበቃ መጠለያቸው ውስጥ ሆነው ያልተገራ የቀርከሃ ዋሽንት ይነፋሉ......ከዳገቶች ነፋስ በለዘብታ ይነፍሳል......ተከዘው የቆዩ የወንዙ ዳር ቅጠሎች እርስ በርሳቸው ይተሻሻሉ......አበቦች በቀስታ ዘውድ የመሰለ ራሳቸውን ያነቃንቃሉ......

ዘበኛው ዋሽንታቸውን መንፋት አቁመው ለጥቂት ጊዜ አዳመጡና ቀና ብለው ዙሪያ ገባቸውን አይተው፡ "ማነው?" አሉ......

ከወንዙ አንድ ሪባዳ፣ ከላይ ማንጠልጠያ ከሥር መደገፊያ የሌላት እንዲት ኩከብ የመሰለች የብርሃን ነጥብ በአየር ላይ እየዋኘች ወደ ወንዙ እየቀረበች መጣች......ለጥቂት ጊዜ......ነፋስ እንደሚያንገላታት ሁሉ ከፍ፣ ዝቅ......ከፍ፣ ዝቅ ብላ ቆይታ ቆመች......ይፈስ የነበረው ወንዝ ረጋ......

ዘበኛው ዋሽንታቸውን መንፋት እንደጀመሩ የት/ቤቱ ጣሪያ ትልቅ ድንጋይ እንደወደቀበት ሁሉ ጮኸ......የዋሽንቱ ድምፅ ቆመ......

"ማነው?" አሉ ዘበኛው



@BOOKALEM

ወደ ትምህርት ቤቱ ጀርባ እየሮጡ ሄዱ......ወንዙ መፍሰስ ማቆሙን አላዩም......መንቦጫባጭ፣ መንቦጫረቅ ከወንዙ አይሰማም......

የብርሃንዋ ነቁጥ እየጐላች......እየጐላች ወደ አንድ ትልቅ የብርሃን ኳስ ተለውጣ ወደ መሬት ተጠጋች......ጥቂት ቆይታ የአንዲት ቢት ውብ ቁመና ኾነች.....ስስ፣ ነጭ የሐር ቀሚስ ለብሳለች......የሰውነትዋ ቅርጽና ተፈጥሮዋ ይታያል......ከጡቶቿ ጫፎች ወተት የመሰሉ የብርሃን ነቁጦች ወደ ወንዙ ጠለል ይንጠባጠባሉ......ብዙ አደይ አበባዎች ፀጉርዋ ላይ ተሰክተው አናቷን ደብዛዛ ፀሐይ አስመስለውታል......ከወንዙ ዳርቻ በአበቦች የተከበበ አንድ ዕንቁላሌ ቢጋር ያለው ትልቅ ጥቁር ድንጋይ ላይ ተቀመጠች......

"ሒድ!" አለች......

ወንዙ መፍሰስ ጀመረ......በሳይዋ ላይ የደረበችው ነጭ የሐር ነጠላ ከትከሻዋ ሳይወርድ እየተሳበ ለብዙ ሜትሮች ያህል በወንዙ ውሐ እየተጐተተ ሄደ......የወንዙ ድምፅ......ሽካራነቱ እየለሰለሰ በዝምታ መውረድ ጀመረ......ፊቷን ወደ ሰማይ አንስታ የበሰለ እንኮይ የመሰሉ ከንፈሮችዋን ማንቃንቅ ጀመረች......

ዘበኛው የሚረብሻቸውን ነገር ለማወቅ ባለመቻላቸው ቀድሞ ወደ ነበሩበት መጠለያቸው ተመልሰው ዋሽንታቸውን መጫወት ጀመሩ......ለብዙ ዘመን እንደሰለጠኑበት ሁሉ ከዋሽንቱ የሚያምር ድምፅ ተንቆረቆረ......በሁኔታው ተገርመው ዋሽንቱን ከለጎሙበት አፋቸው አላቀቁና አገላብጠው አዩት......ፊት ለፊታቸው ሙሉ በሙሉ ከአድማስ ያልተላቀቀች የማር ቲባ የመሰለች ጨረቃ ጥምዝ አፍንጫቸውን የሳመችላቸው መሰላቸው......

አፈሩ......

ልባቸው ደፈረሰ......

የዋሽንቱ ድምፅ......

አዋይቷ ፊቷን በትምህርት ቤቱ አቅጣጫ አዙራ እተቀመጠችበት አይኖቿን ከድና አንገቷን በቀስታ ትሰብቃለች፤ ከንዷን ወደ ላይና ወደ ታች እያነሳች ትደንሳለች፤ በአካሏ ንቅናቄ ሰበብ አንዳንድ አደዮች ከፀጉሯ ከብባት ላይ ወደ ወንዙ በለሆሳስ ይወድቃሉ......ከአፏም እንደ ዋሽንት ድምፅ ......

ዘበኛው ችሎታቸውን ስለሚያውቁት......ዋሽንቱን በእጃቸው አገላብጠው አዩት......ዋሽንቱ ድምፅ ማውጣቱን አላቆመም......በፍርሐት ወደ መሬት ባሉት.....ድምፁ ቆመ......

አዋይቷ አይኖቿን ከድና የአንገቷን ሰበቃ፣ የጣቶቿን እስከስታ አቁማ በሐዘን ፊቷን ወደ መሬት ደፋች......አንዳንድ አደዮች ከፀጉሯ ላይ ወደ ወንዙ ተንጠባጠቡ......በእጇ የወንዙን ወለል ስትዳብስ ቆይታ አንዲት የምታብለጨልጭ ነጭ ጠጠር አወጣች......ወደ አፏ ውስጥም አስገባቻት......

ዘበኛው ዋሽንቱን መሬት ላይ ጥለውት በመደመም አዩት......ስህተቱ ከራሳቸው ሕሊና የመጣ ስለመሰላቸው እያመነቱ ዋሽንቱን ከወደቀበት አንስተው ካፖርት ኪሳቸው ውስጥ ከተቱት......

አዋይቷ ጠጠሯን ከአፍዋ አወጣችና አየቻት......እንደ እንቁ ታበራለች...... ፈገግ አለች......እጇን ፊት ለፊት ዘርግታ ጠጠሯን መሃል መዳፏ ላይ አስቀመጠቻት......ከጠጠሯ ላይ ደብዘዝ ያለ የብርሃን ውጋጋን ይወጣል......የአዋይቷ አፍ መንቃነቅ ጀመረ......የሚያምር ዘፈንና ዜማ ወንዙን ተከትሎ ወረደ......

"ለዋሽንቱ ዜማ ብሸለመው---
ድምፄን ፈራኝ፣
እድሉን ላሳምርለት ዜማ ባድለው---
ሸሸው፣
እጣውን ሲንቅ ሰው---
ሲያስቅ።
ነፋስ ሲነፍስ ቢያሳዝነኝ፣
ካፖርቱ ከብርድ ስለማይጋርደው፣
ዋሽንቱን በልብስ እንዲለውጠው፣
ስጦታ ብሰጠው---
ሸሸው።
መቼም የእናቴን መልእክት ሳላደርስ፣
ጥቂት ስጦታ ለሰው ልጅ
እንገቱ ዙሪያ ሳልጥል---
አልመለስ"

ጠጠሯን በሁለት ጣቶቿ ይዛ ወደ ላይ እነሳቻት......ከጠጠሯ የሚወጣው ብርሃን በቀስታ ወደ መሃል ሰማይ የምትጓዘውን ጨረቃ መሰለ......መዘመር አላቆመችም......

*"ምድር ከነበረች ጀምሮ*
*ምኞታችሁ ያልሰመረ......*
*ከከፋት ነፋስ*
*ከመከፋት ሐሩር ለመጋረድ ያልቻላችሁ*
*ደህችን ጠጠር የሚያነሳ*
*ተመኝቶ ይጣልላችሁ......"*

ዘበኛው ቡና መጠጣት እስኪጓጉ ከካፖርታቸው ኪስ እጃቸውን አውጥተው ወለል ላይ የቆመውን ቡናማ ቀለም ያለውን ፔርሙሳቸውን ሊያነሱ ሲያጉነብሱ ዋሽንቱ ተንሸራቶ ወርዶ የትምህርት ቤቱ አስፋልት ላይ ወደቀ......ያኔውኑ ከሸክላ እንደተሠራ ሁሉ ለሁለት ተሰበረ......ዘበኛው ቆም ብለው አይተው በመደመም ራሳቸውን ነቀነቁ......የዋሽንቱን ስብርባሪ ሊያነሱት ወይ ‹ምን ኾነ› ብለው ለመፈተሽ እጃቸውን ሰደው ሲነኩት፣ ምሽቱን ተቆልሎ እንዳደረ የረጋ የዘመሚት ኩይሳ ጣቶቻቸው መሃል ተናደ......በድንጋጤ ራቅ አሉ......ከግቢው ውስጥ የተነሳ የመሰለ ነፋስ እያፏጨ ወደ ነበሩበት መጥቶ የዋሽንቱን ስብርባሪ ጠራርጎ አንስቶት ሄደ......በብርዱ ይሁን በአፂራው ምክንያት ዘበኛው ትን ብሏቸው ሣል ሳሉ.....ቡናቸውንም ረስተው የእንጨት ማረፊያቸው ላይ ጋደም አሉ.....ጣመን የተሰማቸው መሰላቸው......አይኖቻቸውን ጨፈኑ......

......ወንዙን በትልቅ ሞተር የተሰራ የመሰለ ሳቅ በኃይለኛ ነፋስ እየታጀበ ሞላው......ግቢው የበረዶ ውኃ ያለማቋረጥ እንደሚወርድበት ሁሉ ይቀዘቅዛል......አዋይዋ ጠጠሯን እንደጨበጠች ሳቁ ወደመጣበት በድንጋጤ ዞረች......

ከትልልቅ ጥምዝምዝ የብሳና ዛፎች መሃል......ፀጉሮቿ እንደ ጭራሮ የቆሙ፣ እግሮቿ እንደ ዝግባ እንጨት የተጠመዘዙ፣ የአፍንጫዋ ጉባጣ ወደ ሰፊው አፍዋ በቀዳዳዎቹ የሚያተኩር፣ ስትስቅ በአፍዋ ምትክ ቀጭን ጥቁር አግድም መስመር የሚታይ አሮጊት አዋይ ከወንዙ ሌላው ዳርቻ ብቅ አለች::

"ቃልኪዳኔን ልጨርስ አትጠጊኝ" አለቻት ወጣቷ አዋይ በቁጣ

"እኔስ ቃልኪዳን አይኖረኝም እንዴ?" አለች አሮጊቷ::

"አታቋርጪኝ......ድግምትሽን ከአየር ላይ አንሺ"

"ወንዙ እኮ የእኔም ነው.....እምላካችን ለሁለታችንም ነው የሰጠችን......"

አሮጊቷ እንደመቆሚያ የምትጠቀምበትን ረዥም ቅልጥም አሸዋ ውስጥ ተክላው ወንዙ ውስጥ ዘላ ገባች......በእድፍ የጠቆረ የሚመስል የጥጥ መከናነቢያዋ በውኃ ረጥቦ በቀስታ ወደ ታች መስመጥ ጀመረ::

"ምርቃትሽን ጨርሺ" አለቻት አሮጊቷ......

ሁለቱም የጉሪጥ ተያዩ......

"ገና ሳትመጪ ነው......ወንዙ ውኃ ውስጥ ተደብቀሽ የምርቃት ዘፈኑን በእርግማን ዘፈንሽ ለማጥፋት የለፋሽው" አለችና ወጣቷ አዋይ በእጇ መሃል የያዘቻትን ነጭ ጠጠር እየቻትና እንዲህ ብላ ወደ ወንዙ ውስጥ ጣለቻት......

*«በይ ሒጂ!*
*የሚይዝሽን ሰውረው*
*የምትይዥውን ሰውረው*
*ምኞትሽን ከቶ እንዳይሰልበው*
*መሰውርንትሽ ይኼው»*

አሮጊቷ አዋይ ሳቅ እየዳዳት አየቻት:: ከአፍዋ ውስጥ አንዲት ጥቁር ጠጠር በቀስታ አውጥታ ወደ ውሃው ውስጥ ተፋችና......

*«ነጯን ሟርት ተከተያት*
*በሔደችበት ሒጂ*
*በገባችበት ግቢ*
*የምትገኝውን ሁኚ*
*ወደማይጨምራት ከሄደች*
*አንቺም ወደሚጨምርሽ ሒጂ*
*በምታልፍበት እለፊ*
*የምትቋጥረውን ፍቺ*

አለቻት::

ወጣቷ አዋይ ተበሳጭታ ከቆመችበት ድንጋይ ወደ አየር ተመንጥቃ ለጥቂት ጊዜ ስትንሳፈፍ ቆየች:: ቀሚሷ ከውሃው አልወጣም:: ወደ ብዙ፣ የሚያብለጨልጩ ከዋክብት ተሰባብራ ወደ ሰማይ ውስጥ ተወርውራ ጠፋች......ዐይነ-ርግብ ቀሚሷ ወንዙ ላይ እየተንሳፈፈ ቀረ:: አሮጊቷ አዋይ አይኗን ወጣቷ አዋይ ከተሰወረችበት ቦታ ሳታነሳ በሳቅ እየተንከተከተች ወደ ኋላዋ በአየር ውስጥ በፍጥነት እየዋኘች ወደ ድቅድቅ ጨለማ ገባች......ዛፎች አውሎ ነፋስ እንደገባባቸው ሁሉ ክፉኛ ተወዛውዘው ፀጥ አሉ::

ዘበኛው ከእንቅልፋቸው ወይም እንቅልፍ ከመሰላቸው ነገር ባነኑ:: የትምህርት ቤቱን ዙሪያ ገባ አይተው ያሆራቸው ዓይነት በእጆቻቸው መሃል እናታቸውን ደግፈው ቁጭ ካሉ በኋላ ተመልሰው ተኙ::

* * *

ነጯና ጥቁሯ ጠጠሮች በወንዙ ላይ ጉዞአቸውን አላቆሙም......ሆኖም ነጯ ስትሮጥ......ጥቁሯ ስትከተል:: ከአጭር ጉዞ በኋላ ሁለቱም ደክመው ጐን ለጐን ተኙ.....

አንደኛ ቀን......ሁለተኛ ቀን......ሶስተኛ ቀን......

አንደኛ ሳምንት......

ዝናብ ዘንቦ ወንዝ ሲሞላ ጉዞ ጀመሩ......ነጯ ጠጠር ከጥቁሯ የማምለጥ ጥረቷ አልሰምር አላት::

ሁለተኛ ሳምንት......

ድንገት ትልቅ ኮረት ሲያቆማት መንገዱ ቅን የኾነላት ጥቁሯ ጠጠር ከፊት ቀድማ ስትጠብቃት ታያለች:: ተስፋ ቆርጣ ትተኛለች::

ሶስተኛ ሳምንት......

አንደኛ ወር......

* * *

ብሩክታዊት በውስጥ ልብስዋ አልጋው አጠገብ ቆማ አይኖችዋን እያሸች ታያቸዋለች:: የሂሳብ አስተማሪዋ የሆኑት አጐትዋ በጠዋት ተነስተው ይሮሁባታል::

"ከገጠር አውጥቼ እዚህ ታላቅ ከተማ ለምን እንዳመጣሁሽ ታውቂያለሽ? ለአንቺ በየወሩ የምከፍለው ገንዘብ እያሳስብሽም? አንቺ ልጅ አትባይም:: ብሩክታዊት ሙች:: አሁንስ በዛ:: በየቀኑ፣ እርሳስሽን ደብተርሽን ለማንም እየሰጠሽ ትመጪያለሽ"

"በጣም ስለቸገራቸው ነው:: መግዣ የላቸውም እኮ ጋሼ» አለች በልምምጥና በማቆላመጥ::

እንደምትቀልድባቸው ቆጥረውት ሊመቷት እጃቸውን አነሱ:: እንደገና መለሱት::

"አሳዛኝ:: ሰማሽ ዋንዛ......ይህቺ ብልጥ ልጅ ትንሽ በተቆጣኋት ቁጥር 'ጋሼ' እያለች ታቆላምጠኛለች:: አንቺ ነሽ ያስተማርሻት? " ......ያልጋ ልብስ ተከናንበው በረንዳ ላይ ፀሐይ የሚሞቁ ሚስታቸውን ጠየቁ::

"እኔን ለቀቅ፣እዚያው እናንተ ማስመሰልና ቲያትር በደማችሁ ያለባችሁ ታደርጉት ይሆናል:: እኔም ሆንኩ የእኔም ልጆች የለበጣ ማቆላመጥ አናውቅም:: ያውም ለማታለል አሁ! ሁ!......ይህቺ ሌብነቷም ጅልነቷም በደማችሁ እናንተ"

አስመሮም ወደ ብሩክታዊት ቀርበው:



@BOOKALEM

"ዋንዛ የምትለውን ትሰሚያለሽ? እሷ ብቻ ሳትሆን የሠፈሩ ሰው በጠቅላላው ስለ አንቺ ሞኝነትና ቂልነት ነው የሚያውቀው:: እቃሽን የምትሰጪቸው ልጆች እንኳን እቤታቸው ገብተው ይስቁብሻል:: አንዳንዶቹ ምን እንደሚያደርጉ ታውቂያለሽ? አይገርምሽም እንጂ አይቆጭሽም እንጂ ከአንቺ ወስደው ይሸጡታል"

"አይደለም ጋሼ:: እየጠፋባቸው ወይም ትላልቆች ልጆች እየነጠቋቸው ነው"

"አትከራከሪ አሁን!......የመጨረሻ ትእዛዝ ነው:: ዋንዛ! ለዚህች ልጅ የስፖርት ጫማ ገዝተሸላት ነበር አይደለም?"

"አዎ" አሉ ወይዘሮ ዋንዛ ከተቀመጡበትም ሳይነቃነቁ ፊታቸው ላይ ዝንቦች እንዳያርፉባቸው በእጆቻቸው እያራገቡ::

"ትናንት ምን እንዳደረገች ታውቂያለሽ? ጫማዋን ለሌላ ሰጥታ ነበር"

"እ......የምታሳዝን ልጅ......ብሩክቷ! ለሌላ ሰጠሽው እንዴ?"

ብሩክታዊት መልስ ሳትሰጥ ራስዋን እያከከች በወይዘሮ ዋንዛ አቅጣጫ ተመለከተች::

"ትምህርት ቤት እለከፋለሁ......እዚህ መጥቼ ደግሞ ይህቺ ትነጅሰኛለች......'ቂል ይኑር እንዲያስቅ' ነው የሚሉት......እኔ አልስቅም"

የቁጣ ንግግራቸውን ባለቤታቸው አቋረጧቸው::

"ትምህርት ቤት ደግሞ ምን ብለው ለከፉህ?"

"ተይኝ እባክሽ:: አንቺ ምን አለብሽ እቴ የመጣውን ተኝተሽ መብላት ነው"

"አይ እንግዲህ ንጀሳህን ተወት አድርገህ የጀመርከውን፣ የሚረባውን ወሬ ጨርሰው"

አስመሮም ወዲያና ወዲህ ሲመላለሱ ቆዩና.....

"ሮዛን ታውቂያታለሽ አይደለም"

ዋንዛ የፌዝ አይነት ሳቅ አሉና፡

"እንዴ አንዴ እዚህ ቤት ጠርተሃት 'ጠላ አልወድም' ብላ ዘንጣብኝ የሄደች ግራ የገባት ዘመናይ?"

"ማርያምን ነው የምመስለው ልትል ትንሽ የሚቀራት......ሙቺ"

"ምን አገጣጠማችሁ?"

"ትምህርት ቤቱ ሊታደስ ስለኾነ እደሳውን የሚመራ ኮሚቴ ይመረጥ ተባለ......እና የሸዋዬ ባል ዮሐንስ እኔን ጠቆመኝ......ብዙ ጊዜ



@BOOKALEM

ኮሚቴዎች ውስጥ ሰርቻለሁ......ይሔ ሁሉ ሳያሳፍራት ማንም ተቀምጦ እንዳለ: 'እኔ በአስመሮም አልተማመንም፣ አትል መሰለኝ እሱ አስመሮም እንደ ሮዛ ወገባቸውን ይዘው እየተወናወኑና የማይታዩ የበጉር ጭረቶች አይኖቻቸውና ግንባራቸው ላይ እንደወደቁ ሁሉ በጣቶቻቸው እያነሱ......

"ምን አገባት?"

"እሱን እኮ ነው የምልሽ......የኛ ሰው አያበላ፣ አያስበላ"

"ያዳመጣት አገኘች?"

"እሱ እኮ ነው ያበሳጨኝ......ያሳፍረኛል ብዬ ስጠብቅ ማንም ቅማላም እየተነሳ......" ራሳቸውን ነቅንቀው ብሩክታዊት ፊት ቁጭ አሉ......

"አልጨረስክልኝም እኮ......ምን ኾነ?"

"ትምህርት ቤቱ እኮ መሠራቱ አይቀርም......ለምን ኮሚሽን ያገኝ ነው......እሷን አላውቃትም?......አንድ ቀን ክፍል ውስጥ እኮ ነው በእናትሽ ዋንዛ ቦታ ጠፉ እንዴ? ዋንዛ ሙቺ ዴስክ ተደግፎ ሴት ልጅ ከወንድ ልጅ ጋር ይገናኛል?"

"ተው አንተ ደግሞ......የማታውቀውን፣ ያላየኸውን" ፊታቸውን ኮምጨጭ አድርገው......

"ከእኔ ጋር ሌላ ሁነኛ ሰው አይቷል......አንቺ ደግሞ የት ታውቂያታለሽ......ጠላሽን ብትጠጣልሽ ኖሮ አብረሻት ሳትመቀኚኝ አትቀሪም ነበር"......

ብሩክታዊት ከተቀመጠችበት ተነስታ ለመሄድ ስትሞክር አስመሮም: "ቆዪ......ብሩክታዊት ቆዪ......ገና ከአንቺ ጋር አልጨረስኩም......ፔሬዱ አላለቀም" ወደ ሚስታቸው ወደ ዋንዛ ዞር አሉና: "እናልሽ እኔ አስመሮም ተበላሁኛ......'የማልታመን መኾኔን አረጋግጪ' ብዬ ብላት ማረጋገጫው በሙሉ በአሉባልታ የተፈጠረ ሲሆንባት ወደማይሆን ወደማይሆን ገባች"

"ምን አለች?"

"የትምህርት ቤቱን ካፌቴርያ የማስተዳድረው እኔ ነኝ......በየአመቱ እንደከሰረ ነው......የሚረባ ትርፍ የለውም.....ታውቂያለሽ".....ብለው ሚስታቸውን በልምምጥ አዩዋቸው......

ዋንዛ ሳቅ ብለው: "አዎ" አሉ......

"እናልሽ ለእኔ የላከችው ነገር ዮሐንስን አይጨምረው መሰለሽ......እሱ ደግሞ እንደ ሚስቱ ነው......እንኳን ነክተውት ያልነካውን አርፎ የተቀመጠውን ሰው በሽሙጥ፣ በአግቦ የሚዘረክት



@BOOKALEM

ነው......እሳት ነው......ሙቺ ወንድ ነው......እርገበገባታ......ምላስ አለች......"

"እህህ......" አሉ ዋንዛ በሳቅ......ባሳቸው በሰው እያመሃኙ ራሳቸውን ሲያመሰጋግኑ ሲሰሙ::

"ምን ያስቅሻል?"

"የሸዋዬ ባል ነገር"

"ምን የሚያስቅ አለው?"

"እሱን ስታነሳው......የዚያን ቀን እዚህ ቤት ያጫወቱን ነገር ትዝ ብሎኝ ገርሞኝ ነው......"

"እ......ከዚያ አቶ ደስታ ተነሱና ሀይ፣ ሀይ ብለው ነገሩን አብርደው ምርጫው ይለይ ብለው ሃሳብ አቀረቡ......እሺ አልን......በኋላ ሲመረጥ እሷ ሊቀመንበር እኔ አባል......ይሔንን ነዋ የፈለገችው"

"ሰው እንዴት በአንዴ ተቀበላት?"

"ስታስወራ ከርማለቻ! እንዲህ እኮ ነው የሚደረገው:: ወሬውን ማስቀደም......ሰው ካመነ አመነ፣ ካላመነ ጥርጣሬ ከፈጠርሽበት ይበቃል......ከዚያ የስብሰባው ዕለት በድፍረት ሰው ፊት እዚያው አጠገቡ ስሙን ያጠፋሽውን ሰው መልከፍ፣ እየሽ ያማሽበትን ነገር እንደ እውነት አድርገሽ ሰውዬው ፊት ዘክዝክሽ ማውራት......ሰዎች 'የሰማነው ወይም የተነገረን ነገር ለካስ እውነት ነው' ይሉና......ከዚያ በኋላ......"

"ምን አስጨነቀህ? ከኮሚቴ አልወጣህ" አሉ ዋንዛ

"ነገርኩሽ......ቦታዋ ትንሽ ገንዘብ ነበራት......አሁን እሷ እያለች......ጠንቋይ"

"በቃ ይቅር......ካፌቴሪያው ይበቃሃል"

"እ......ቀልቢ መሄድ አትፈልጊም?......የድሬዳዋ የሚያምር የኮንትሮባንድ ልብስስ?፣ ዕቃ መግዛት"

"ምን አገናኘው?"

"ይገናኛል እንጂ......ገንዘብ ስለማይኖር እዛ አንሔድም"

"አሁሁ......ቂቂ......ሁሁ:: በል እሺ አንተ ዝም ቢሉህ ብዙ ትናገራለህ......በእውነት:: መሄድ አልፈልግም፣ አረመኔ ነኝ አትልም እንደኛውን"

እስመሮም የሚስታቸውን ተረብ ሳይመልሱ ወደ ብሩክታዊት ዞሩና......ጥቂት ጊዜ በመገረም ከአይዋት በኋላ ተነስተው ሌላ ክፍል ገቡ:: በእጃቸው አንድ እግር ጫማ ይዘው ተመልሰው መጡ......

"ይሔ ጫማ የማነው?"

"የእኔ ነው......"

"የት አስቀምጠሽው ነበር?"

የአስመሮምን የተቆጡ ዓይኖች ስታይ ብሩክታዊት ዝም አለች......

"አትናገሪም! ምን ይዘጋሻል! የት ጥለሽው ነበር?"

"አልጣልኩትም"

"እህህ......ታዲያ የት ነበር?"

"አንድ ልጅ ጋ ነበር...... "

"ልጁ ዘንድ ምን ያደርጋል? ልጁን የት ታውቂዋለሽ? ወንድምሽ ነው እህትሽ?"

"ኳስ ሊጫወትበት ነበር......እና ጫማ አልነበረውም ሰጠሁት"

"አንቺ ጫማ አዳይ ነሽ.....ወይስ ስፖርት ኮሚሽነር ነሽ?"

ብሩክታዊት ዝም አለች......

"የምትለኝን ትሰሚያለሽ አይደለም ዋንዛ?! የደሳት ሐብታም ልጅሽ እርጥባን ጀምራለች ማለት ነው" አሉ በተቆጣ ሽሙጥ::

ወይዘሮ ዋንዛ አልመለሱላቸውም......

"አንቺስ በምን ልትጫወቺ ነው?"

"እኔ አልጫወትም"

"መስጠትሽም ልክ አይደለም፣ ግን እንደገና መቀበል አይገባሽም?"

"ነገም፣ ከዚያም፣ ከዚያም መጫወት ይፈልጋላ!"

"ኧረ ይህቺ ልጅሽ ዋንዛ!......ከእንቺ ጋር ማውራት ምክርም መምከር አያስፈልግም:: እንኪ ጫማሽን" እግሯ ሥር ወረወሩላት......

"ከየት አገኘሽው ግን ጋሼ?"

ጥያቄዋን ስምተው በቁጣ ዝም ብለው አይዋት......በጣቶቿ የፒጃማዋን ኮሌታ እያፍተለተለች......እየቻቻው......

"የእንግሊዝኛ አስተማሪሽ ማርታ ነገረችኝ:: ሞኝነትሽ የማይደንቀው ሰው የለም፣ የአገሩ ሰው በሙሉ ነው የሚደንቀው:: ልጁን ነጠቅሁት"

"ለምን?"

"ዝም በይ!......አንቺ ልጅሽን አንድ ነገር በያት......" እየተቆናጠሩ ወደ ዋንዛ ሒዱ......

"እኔን ልቀቀኝ እስኪ እዚያው......እዚያው እርስ በእርሳችሁ" አሉ ዋንዛ::

ወ/ሮ ዋንዛ እንጀራ እናቷ ናቸው:: ኸረ እዛም አይደርስም:: አስመሮም ለብሩክታዊት አጎቷ፣ ለዋንዛ ባል ከሆኑ በየት በየት እንጀራ እናት ይሆናሉ?

"አንቺም ያልተበሳጨሽ አትምሰይ"

"አዎ ያበሳጫል......ግን ታዲያ ምን ማድረግ ይቻላል?......ልብ ካልገዛች" አሉ ዋንዛ ከተቀመጡበትም ሳይነቃነቁ ፊታቸው ላይ ዝንቦች እንዳያርፉ በእጃቸው እያራገቡ::

ቀጠሉ: "ዘመድህ ምን ሊልዋት ነው? አንተና ብሩክታዊት ምን የሚያዛምድ ጠባይ አላችሁና ነው:: እሱም ይገርመኛል?"

"እኔን ለቀቅ......ደ'ሞ እኔን ነጣቂ፣ ዘራፊ ለማስመሰል ነው? ከእኔ ዝርፊያ ያልተጠቀመች ትመስላለች:: ያላበረታታች"

የአስመሮምን አባባል እንዳላስተዋሉት ሁሉ ዋንዛ ገሽሽ ብለው:

"እኔ እንደዚች አይነት አላየሁም......ብታድግም የሚለቃት አትመስልም......ያልቀመስነውን ዶሮ ወጥ እንዳለ ለለማኝ አውጥታ የሰጠች እኮ ናት—አምና......ለፋሲካ ትዝ ይልሃል? ይኼማ ጫማው ምን ቀላል አይደል......" አሉ ዋንዛ......

አስመሮም ሚስታቸውን እንዳስደነገጡና መስመር እንዳስያዙ ከገባቸው በኋላ ወደ ብሩክታዊት ዞር ብለው:

"ስሚ ብሩክታዊት ዛሬ የሰራሽው ነገር የመጨረሻ ነው:: የመጨረሻ ነው:: እኔ የገዛኋት ሰቃ ያለቀችም እርሳስ ብትሆን ሰው እጅ ባገኛት እንደ ሌላው ጊዜ ተገርሜ አላይሽም"

ብሩክታዊት የሚያሳዝን አይኗን ቦግ አድርጋ እየቻቸው......ለጥቂት ጊዜ ተፋጠጡ.....ያለማፈር ዓይኖቿን ሳትሰበር እንዲህ ስታተኩርባቸው ሲያዩ አጎትዋ ትእግስታቸው ተሟጦ ጉንጭዋን ለቁንጥጫ ያዝዋት.....ቀጥ ብላ ቆመች......አልተነቃነቀችም:: ......ቁንጥጫቸውን እያጠበቁ፣ እያጠበቁ፣ እየጎተቱ እየጎተቱ በመጨረሻ ሲለቁት አፍዋ 'ቦጭ' የሚል ድምፅ አሰማ::

እያለቀሰች ከቤትዋ ወጣች......

በትምህርት ሰዓት አስመሮም ሲያገኟት ውስጥ ልብሷን ብቻ እንደለበሰች ነበር:: የት/ቤት ልብሷን (ዩኒፎርሟን) አቅፋ ክፍሏ በር ፊት ለፊት ቆማለች:: አስመሮም ተበሳጭተው ጠሯት......ብሩክታዊት ቁጣቸውን ስትሰማ ለመጠጋት ፈራች......



@BOOKALEM

"ለምን ራቁትሽን አትመጪም ነበር?" አሏት::

እቆመችበት በችኮላ ቀሚሷን ለበሰች

"ጤነኛ አትመስይኝም አንቺ......እንዲህ የቆሸሸና......የገለማ ቀሚስ ለብሰሽ እኔ የማስተምርበት ክፍል አትገቢም:: አሰዳቢ"

ብሩክታዊት ቅር አላት......የአስመሮም ማስተማርያ ክፍለጊዜ ሲደርስ ሹልክ ብላ......ማንም ሰው እሊለበት መስክ ላይ ብቻዋን ለመጫወት ወጣች::

ትምህርት ቤቱ ከተሠራ አምስት አመታት ብቻ ቢያልፈውም አስራ አምስት የክረምት ወራት ዝናቦች የተቀባውን የውጩን የግድግዳ ቀለም በዝናባቸው አጥበውታል......በተጨማሪም 'ትንግርታዊ ማገርጀት' ተብሎ በሚመዘገብ ፍጥነት የውታ ልኩ ሲሚንቶ ተንዳድሎአል:: የአንዳንድ ክፍሎች ብሎኬት ግድግዳ ከጣሪያ እስከ ወለል ተሰንጥቆ ነፋስ እያፏጨ ሲያስገባ ይሰማል:: የልማት ኮሚቴው በአለፈው አመት ትምህርት ባልነበረባቸው የዝናብ ወሮች ሙሉ ሲሰበሰብ ቆይቶ መጠገኛ በጀት ስለፈቀደ ለሥራ የሚሆኑ እቃዎች ተገዝተው ግቢው ውስጥና ከግቢው ፊት ለፊት እየተከማቹ ነው:: የኳስ ሜዳውን ከፊል ጣውላዎች፣ ቆርቆሮዎች፣ የድንጋይ ክምርና ሲላም ሸፍነውታል:: ወጪ ለመቀነስ ሲባል አሸዋ ትምህርት ቤቱን ከበ ከሚገኘው ወንዝ ተዘግኖ እንዲመጣ ተደረገ......

ብሩክታዊት ክፍል እንዳትገቢ ከተባለች በኋላ ሜዳው ላይ ተቀምጣ ስትጫወት ቆይታ ስለሰለቻት አሸዋ ወደሚገለብጥ አንድ የጭነት መኪና ተጠግታ ትእይንቱን ለመከታተል ፈለገች......

የጭነት መኪናው ሹፌር አጉቷን አስመሮምን ስለሚያውቀው ሰላምታ ሰጣት......

"አንቺ ቆንጆ የአስመሮም ልጅ ነሽ አይደል?"

ፀሐይ አድክሟት ስለነበር ባትናገርም ጭንቅላቷን ብቻ በአዎንታ ነቀነቀች......

"ደህና ነው?"

ራስዋን በአወንታ ነቀነቀች......

"አትናገሪም ዱዳ ነሽ?"

በዝምታ አየችውና:

"አስመሮም አጎቴ ነው" አለች:: ሰውዬው ከት ብሎ ሳቀ::

አሸዋ ተዘርግፎ ያለቀ መሆኑን አውታንቲው ለሾፌሩ ስለነገረው መግልበጫውን ሳያጥፍ ወደፊት እየነዳ አለፈ......አውታንቲው ከጀርባው ተፈናጠጠ:: መኪናው ሁለቱን ሰዎች ይዞ ሜዳውን አቋርጦ ከአይን

ሲሰወር ቦታው ላይ ቀድሞ ያልነበረ፣ ሜዳው ለምዶት የማያውቅ ዓይነት ፀጥታ ሰፈነ:: ብሩክታዊት ከተከመረው አሸዋ በእጅዋ እየዘገነች ስትበትን፣ ሲገለበጥም ወደተሰራው ትንሽ የአሸዋ ኮረብታ እየተንባቸች ስትወጣ፣ በጫማዎቿ አፈር እየሞላችና እያፈሰሰች ስትጫወት ነጭና ጥቁር ቀለም ያላቸው ሁለት ክብ ጠጠሮች ከክምሩ ውስጥ ተንከባለው ወጡ......የጠጠሮቹ መልካቸውና ልስላሴአቸው ስላማራት ከሁለቱ በመጠኗ የምትበልጥ የመሰላትን ነጭዋን ጠጠር በከፊል ከስመጠችበት አሸዋ መሃል ለቀመቻት......ያኔውኑ ገላዋን ከላይ እስከ ታች ቀለላት ......ወንፊት እንደ ኾነች ሁሉ በደረቷና በጭንቅላቷ ውስጥ ነፋስ የሚያልፍ ጨረር ዘልቆ የሚሄድ መሰላት......ትንሽ የድንጋጤ ድምፅ አሰማች......ጠጠሯ እጇ መዳፍ መሃል እንደ ሙጫ ተጣበቀች ......ነጭዋን ጠጠር ከለቀመች በኋላ ጥቁሯን የማንሳት አቅዷን በዚህ ባጋጠማት አስደንጋጭ አጋጣሚ ምክንያት ረሳች......ተሰወረች......

"እንዴ! እንዴ!" አሉ አስመሮም......ለተማሪዎች መልመጃ ሰጥተው በቀስታ እርምጃ በረንዳ ላይ ወዲያና ወዲህ ሲሉ የብሩክታዊትን እንዲህ እያዩአት በድንገት ከአይን መሰወር አይተው::

አሸዋው ወደ ተከመረበት ቦታ እየሮጡ ሄዱ......እዛ አካባቢ ሲደርሱ ቦታውን በጣም ቀርበው ለማየት፣ ለመዳበስና ለመፈተሽ ልባቸው ፈራ......የብሩክታዊት ሁለቱ ነጫጭ ጫማዎች በከፊል ድቡሽት ተሞልተው ተራርቀው ቁጭ ብለዋል......ከመጫሚያዎቹ መሃል በጣም ውብ የኾነች እንደ አልማዝ የምታበራ ጥቁር ጠጠር ትታያለች......

ወደ አሸዋው እየጮሁ ሲሮጡ ያያቸው አንድ ዮሐንስ የተባለ አስተማሪ: «አስመሮም ምንድነው? ምንድነው?" አላቸው::

አልሰሙትም:: አልመለሱለትም:: ......አንድ ከባድ ነገር እንደሚፈልጉ ሁሉ ሲገለማመጡ ሲያይ ለመረዳት ብሎ እየሮጠ ወደ እሳቸው መጣ......

"ምን ሆንክ አስመሮም?" አለ

"የሚገርም ነው......የሚገርም ነው......አይኔን ማመን አልቻልኩም" አሉ......ሲመልሱለትም መሬት መሬት እንጂ እሱን አያዩትም......

"ምንድነው?" አላቸው እንደገና......

"ብሩክታዊት እዚህ ነበረች......ተሰወረች......ጠፋች" አሉት ቀና ብለው......

"እዚህ ነበረች......እዚያ ቆሜ ነበር......በስመአብ" አሉ ቀጠሉና

እንዲህ ብለውት......ልባቸው በእሷ መጥፋት ተደንቆ በፍርሃት ስሜት ጫማዎቿን ለመሰብሰብ ጠጋ ሲሉ ከነጭዋ ጋር የነበረችው



@BOOKALEM

ጥቁር ጠጠር ማርካቸው ከጫማው ውስጥ አነሷት......ወዲያውም ገላቸውን ከላይ እስከ ታች ቀለላቸው፣ በደረታቸውና፣ በጭንቅላታቸው ውስጥ ለስላሳ በዓይኖች ለማየት የሚከብድ ጨረር ወይም ለስ ያለ ነፋስ የሚያልፍ መሰላቸው......ትንሽ የድንጋጤ ድምፅ አሰሙ......ጠጠሯ እጃቸው መዳፍ መሃል እንደሙጫ ተጣበቀች......ተሰወሩ......

የአስመሮም መሰወር ዮሐንስን በድንጋጤ አፈዘዘው......አፉን በረገደ:: በራሪ ወፎች ወደ ውስጥ እንዋሉ ድረስ ገብተው እንቁላል ጥለው ቢወጡ እንኳ የሚሰማም አይመስልም......ግራና ቀኝ ሰማይና መሬት እየገላመጠ እየጮኸ ተጣራ......

"አስመሮም! አስመሮም!"

ወደ ርእሰ መምህሩ ቢሮ እየሮጠ ሔደ......ያየውን የሰማውን ሊናገር::

* * *

በታባው ዓለም አስመሮምና ብሩክታዊት ይነጋገራሉ......

"ጋሼ ምንድነው?" አለችው አጉትዋን

"ሌሎች ሰዎች አያዩንም ማለት ነው መሰለኝ"

"ሊዳብሱንም አይችሉም"

"እንጃ"

"ጠጠሯን ከያዝክ በኋላ ነው የተሰወርከው አይደለም?"

"አዎ! የእኔ አይነት ነው? እስኪ አሳይኝ"

"ተጣብቆአል እጄን መክፈት አልችልም" አለቻቸው......

"የእኔም እንደዚያ ነው" አሏት

"ወደ የት እንሂድ?"

ሁለቱም ትንሽ ቆመው ምርጫ ላይ እንዳሉ ሁሉ አሰቡ......

"እቤት እንሒድ" አሏት

"ወደ ወንዝ ይሻላል......ወንዝ ሂጂ ሂጂ ይለኛል" አለቻቸው ብሩክታዊት::

"አይ ወደ ቤት እንሔዳለን......ዋንዛን እንያት" አሏት

ብሩክታዊት ስታቅማማ ጠጠር ያልጨበጠ እጇን ነጠቅ አድርገው ይዘው በቤታቸው አቅጣጫ እየጎተቷት መሄድ ጀመሩ......

እቤት ደርሰው በር ሳያንኳኩ ገቡ......አቶ አስመሮም ሚስታቸው ወደ ተቀመጡበት ክፍል ገብተው ጠሩአቸው......የሰማቸው አልነበረም......

"ጋሼ……እማማን ስትጠራት አትሰማም ማለት ነው?"

"አትሰማንም መሰለኝ"

"ደግመህ ጮህ ብለህ ጥራት"

"አንቺ ዋንዛ! ዋንዛ!"

ዋንዛ ድምፅ የሰሙ አይነት እተቀመጡበት ኾነው ወዲያና ወዲህ አዩ……

"የመጨረሻው አቅምህን ጨኽ ጋሼ……ኸ»

አስመሮም እስከሚችሉት፣ ደም ስራቸው እስኪገታተር ድረስ ጮኹ……ዋንዛ ከተቀመጡበት ተነስተው ክፍሉ ውስጥ እየተንጐራደዱ……

"ማነው? ማነው?" አሉ……

"ሰምታለች፣ ሰምታለች" አለች ብሩክታዊት

"ጆሮዋ አጠገብ ሔጄ ብጮህ ምን ትላለች?" አሉና አስመሮም ወደ ሚስታቸው ተጠግተው "ዋንዛ!" ብለው ጮሁ……

ዋንዛ የሰሙበትን አንዱን ጆሮአቸውን ትንኝ እንዳረፈበት አራገፈው:

"እንዴት የሚያስፈራ ድምፅ ነው……አንተ የቂልቢው እንዴት የሚያስፈራ ድምፅ ነው" እያሉ ወደ ጓዳ እየሮጡ ገቡና በፍርሃት ጆሮአቸውን ይዘው አልጋቸው ላይ ተቀመጡ……

አስመሮም ግራ ገብቶአቸው:

"ብሩክታዊት ድምፄ ተለውጧል እንዴ? እኔ መኾኔን እንኳን እንዴት ማወቅ ተሳናት?"

ብሩክታዊት ለጥያቄያቸው መልስ አልሰጠችም::

"ምናልባት ድምፁ ከማታየው ነገር ስለመጣ ፈርታ ይሆናል……ቢሆንም አንቺ እስኪ ጥሪአት" አሉ አስመሮም……

ብሩክታዊት ዋንዛ ወደሮጡበት ተከትላቸው ገባችና……ጐናቸው ቆመች……ዋንዛ ሁለቱንም ጆሮአቸውን በሁለት እጃቸው ይከድኑትና ይለቁታል፣ ይከድኑትና ይለቁታል……ያዳምጡና ፍርሃት ሲጀምራቸው ወይ ድምፅ የሰሙ ሲመስላቸው ተንቦቅቡቀው ይከድኑታል……

ብሩክታዊት ጆሮአቸውን ሲለቁት ጠበቀችና ጮኸች……

"እማማ! ብሩክታዊት ነኝ"

"ምን? ምን?" አሉ ዋንዛ ሁለቱንም እጃቸውን ከጆሮ ግንዳቸው አንስተው……

"ብሩክታዊት ነኝ"



@BOOKALEM

"ብሩክታዊት......የት ነሽ? የት ነሽ?"

"እዚህ አጠገብሽ ነኝ እማማ"

"እንዴ......በስመአብ......መልአኩ ገብርኤል......ዮሐንስ አሁን ስልክ ደውሎ የነገረኝ እውነት ነው?"

ወ/ሮ ዋንዛ ሊዳብሷት፣ ሊይዝዋት እጃቸውን ዘረጉ......

"እዚህ ነኝ እማማ......ዮሐንስ ምን ነገረሽ? ከጋሼ ጋር መሰወራችንን?"

"አዎ! እውነቱን ነው ማለት ነው?......ማበዱ መስሎኝ ነበር......እንዲህ ያለ ነገር አለ? ምን አመጣብኝ? የት ነሽ? የት ነሽ?" ወደ ቆመችበት ተመልሰው መጡ፣ ድምፅዋን የሰሙበት አካባቢ ሔደው ቆሙ......

"እዚህ ነኝ......እሰማሻለሁ"

"አዎ ትሰሚኛለሽ? ብሩክቴ ነሽ ግን?"

"አዎ......በድምፄ አላወቅሽኝም?"

"ያንቺን ድምፅ በጥቂቱ ይመስላል......ኸረ ይመስላል:: በጣም ደስ የሚል ድምፅ ነው:: አስመሮም ደህና ነው? ምን ኾኖአል:: ከአንቺ ቀድሞ አንድ ድምፅ ሰምቼ እንደው ድምፁ የሚያስፈራ ነገር አለው ልጄ ......ምንድነው?" አሉና ተረጋግተው አጠገባቸው ያገኙት ሶፋ ላይ ራሳቸውን በሁለት እጆቻቸው ይዘው አረፍ አሉ::

ይሔንን ይሰሙ የነበሩት አስመሮም ተናደው ብሩክታዊትን ከዋንዛ ሊያሸሹዋት ይጐትቷት ጀመር......

"ተው እንጂ ጋሼ ተው እንጂ"

"ምን ሆንሽ ብሩክቴ?" አሉ ዋንዛ

"ጋሼ ከአንቺ ጋር እንዳልሆን ይጐትተኛል"

"ቀድሞ የሰማሁት የእሱን......"

"አዎን የእሱን ድምፅ ነው የሰማሽው:: ልቀቀኝ!"

የብሩክታዊት ድምፅ እየጠፋ፣ እየራቀባቸው ሲሔድ ዋንዛ ያጋጠማቸው ነገር ሁሉ ለአእምሮአቸው፣ ለሥጋቸው ከብዶአቸው አንዳች ነገር ጥንካሬያቸውን እንደነጠቃቸው ሁሉ እተቀመጡበት ጥልቅ እንቅልፍ ባላቸውና ማንኮራፋት ጀመሩ......

ዋንዛ ከተኙበት ሲነቁ ያጋጠማቸው ነገር ሁሉ ሕልም፣ ራእይ መሰላቸው......ነጠላቸውን አጣፍተው ከቤታቸው ወጡ......ስለ ሁሉ ነገር ያልነገሩት ጐረቤት አልነበረም......



@BOOKALEM

* * *

ከጥቂት ቀናት በፊት የብሩክታዊትን ጫማ ተውሶ የነበረው ልጅ ለመተኛት ልብሱን እያወለቀ እያለ በር በቀስታ ተከፍቶ አንድ የሚያውቀው ጥንድ ጫማ በአየር ላይ እየተንሳፈፈ ሲገባ አየ...... ተደናግጦ በፍርሃት ፊቱን አልጋ ላይ ሲደፋ:

"እኔ ብሩክታዊት ነኝ" የሚል ድምፅ ሰማ......

"እ......እ"

በጉሪጥ ለማየት እየሞከረ ደግሞ ፈራ እያለ......

"እኔ ብሩክታዊት ነኝ......እንደ ተሰወርኩ ሰምተህ የለም?" አለችው......

ፊቱንም ሳያዞር: "እ......እ......አዎ" አለ......

"እጉቴ አስመሮም የነጠቀህን ጫማ ነው ያመጣሁልህ:: ውሰደው"

የሚንሳፈፈውን ጫማ በጉሪጥ አይቶት እሱ መሆኑን ቢለይም ስለፈራ ብቻ ከተኛበት አልተነሳም......በሆዱ እንደተንበለበለ ፊቱን በብርድ ልብስ ሸፍኖ እጁን ብቻ ዘረጋ......ብሩክታዊት የምትሰጠው ጫማ ገና ጣቶቹን ሲነካው በድንጋጤ ሁለመናውን ሰበሰበ......

"ያዘው......ያዘው አትፍራ......እኔን ትፈራኛለህ?" አለችው......

ልጁ በቀኝ እጁ ጫማውን ይዞ ፊቱን እንደደፋ ጥቂት ቆይቶ:

"ብሩክታዊት......የት ጠፋሽ?" አላት

"እዚሁ ነኝ......ብዙ ጊዜ ትምህርት ቤት ጀርባ ያለው ወንዝ ነው የማድረው፣ ደ'ሞ እዛ ጋ ነው ሁል ጊዜ የምጫወተው"

"እ......አትፈሪም?"

"ማታ ማታ ያስፈራል......ግን ሳላውቀው ወደዚያ እሔዳለሁ......"

"የማይመች ከሆነ ለምን እኛ ቤት አታድሪም......ለመጫወትም ከፈለግሽ ትምህርት ቤት ነይ እዚያ ገራዡ ጀርባ ሁልጊዜ አለን...... እንናገርብሽም"

"እሺ......ለምን ወደ እኔ አታይም?"

"ፈራሁ......"

"ብሩክታዊት እኮ ነኝ"

ልጁ በቀስታ ፊቱን አዞረ......የሚታይ ነገር የለም......

"ቲቸር ዮሐንስ ትምህርት ቤት፣ ሠፈር ያወሩት እውነት ነው?"

"አዎ! የምትፈልገው ነገር ካለ ጥራኝ ለልጆችም ንገራቸው"

"ከእጉትሽ ጋር ትገናኛላችሁ?"

"አዎ አብረን ነው ወንዙ ዳር የምናድረው"



@BOOKALEM

"አንቺ አትቀየሚኝም......አጉትሽ እኮ ክፉ ናቸው......"

"አዎ......"

"ጫማሽን የሰጠሽኝ ጊዜ ሲነጥቁኝ፣ በእናትሽ......መቱኝ......ደግሞ ማርታ የእንግሊዝኛ አስተማሪያችን ናት የተናገረችብን......ከአጉትሽ ጋር ሸርክ ናት......አንቺ ማርታ አንድ ቀን የቲቸር ሮዛን አይነት የወርቅ ሐብል አድርጋ አልመጣች መሰለሽ"

"አ......"

"ቲቸር ሮዛ ታመሙ እኮ......አንድ ቀን መንገድ ላይ የጋኔን በሽታ የሚባለው ጣላቸው......ሲያሳዝኑ"

"የጋኔን በሽታ አይደለም......" አለች ብሩክታዊት

"ታዲያ ምንድነው?"

"ጋሼ ይሆናል......ስለማይታይ ሐብልዋን የበጠሰባት፣ ልብስዋን ሁሉ የቀደደባት"

"ኸረ? ክፉ ናቸው አንቺ......አጉትሽ......ምን አደረገቻቸው፣ ደግ አስተማሪ ናት አይደለም? እኔ በጣም ነው የምወዳት......ግን ሰዎች አመማት ነው ያሉት......"

ልጁ ፍርሃት እየለቀቀው አልጋው ላይ ተቀምጦ ድምፁን ከፍ አድርጐ ከብሩክታዊት ጋር መነጋገር ስለ ጀመረ......የክፍሉ በር ተንኳኳና ጐርነን ያለ ድምፅ ያላቸው ሴትዮ---እናቱ:

"ምን ሆንክ ብቻህን የምታወራው......ማን አለ እዚያ?" ብለው ጠየቁ::

ብሩክታዊት ጫማውን ለልጁ ስጥታ ያኔውኑ ወደ ማርታ ቤት ሔደች.....የማርታ ግቢ የአጥር በር ተዘግቶ ስለነበር በግንቡ ላይ ተንጠልጥላ ገባች......ከሽታ የሰሙና የተረበሹ የጒረቤት ውሾች ጮኹ......ዋናውን ቤት ዞረችና በሽርቪስ ቤት በኩል ያለው የጀርባ በር ክፍት መሆኑን ስታይ በዚያ ወደ ዋናው ቤት ገባች......

"ሽዋዬ በሩን ዘጋሽው?" አለ አንድ ድምፅ ከውስጥ......

አንዲት ቀጭን ሴት /ወይዘሮ ሽዋዬ/ ፀጉሯን በሻሽ ጥፍር አድርጋ ያሰረች ከአንድ ክፍል በነጠላ ጫማ ወጥታ በሩን ዘግታ ተመለሰች......ሴትዮዋ የተረጨችው ሽቶ ለብሩክታዊት አፍንጫ ይሰማታል:: የወንዱን ድምፅ ወደሰማችበት ክፍል ሽዋዬን ተከትላ ገባች......የአስመሮም ጓደኛ ዮሐንስና ባለቤታቸው ሽዋዬ አልጋው ላይ ቁጭ ብለው የመኝታ ክፍሉንም በር ሳይዘጉ ይሳሳማሉ:: ብሩክታዊት በማፈር ከክፍሉ በቀስታ ወጣችና ሌላ መኝታ ክፍል ፈለገች፣ በስተቀኝዋ አንድ ክፍል አየች:: ከክፍሉ በር ስር ነጭ ብርሃን ይወጣል.....በሩ ድምፅ እንዳያሰማ ቀስ አድርጋ ከፈተች.....ማርታ

አለተኛችም......ፒጃማዋን እንደ ለበሰች አልጋው ጐን ካለ መቀመጫ ላይ እግሯን ዘርግታ ለእሷ የማይታዩ ለብሩክታዊት ግን የሚታዩትን አስመሮምን አቅፋለች......

አይኖቿ ተከድነዋል......በቀስታ ከሚነቃነቁት ከንፈሮቿ ድምፅ አይወጣም፤ አንዲት ረዥም የስፓጌቲ ዘለላ ሳታቋርጥ የምትውጥ ትመስላለች......ፒጃማዋ እስከ ደረቷ ድረስ ተከፍቶ አስመሮም አጎንብሰው ትናንሽ ጡቶቿን ይስማሉ......

ብሩክታዊት የምታየው ነገር አስደንግጦአት አዲስም ስለኾነባት አካልዋ የተከሰተ አይነት ደንግጣ ወለል ላይ ተቀመጠች።

በጉጉት ግፊት ክፍሉ ዙሪያ ስትመለከት አልጋው ራስጌ ካለች አንዲት አጭር ኮመዲኖ ላይ አይኖቿ አረፉ። ባለፈው ጊዜ አጉቷ ከሮዛ የገፈፉት ሐብልና ሎቲዎች እጅብ ብለው ተቀምጠዋል። አስመሮም እንዳያይዋት ወደ ጠረጴዛው እየዳኸች ሔደችና ጌጦቹን ከተቀመጡበት አነሳቻቸው። እንደ አገባብዋ ልትወጣ ሹክክ ስትል በትከሻዋ በሩን ስለነካችው ድምፅ አሰማ......አስመሮም አይዋት......

"አንቺ አንቺ አትመጪም......ምን ታደርጊያለሽ እ......"

አስመሮም ማርታን ማሻሸት አቁመው እየሮጡ መጡባት......ማምለጥ እንደማትችል አውቃ የያዘችውን ሀብል ከጀርባዋ ሸሽጋ ቆማ ጠበቀቻቸው......

"አምጪአት ሀብልዋን......አምጪአት ብዬአለሁ" አሉ አስመሮም

"እምቢ!" አለች ብሩክታዊት

ብሩክታዊት ለማምለጥ ወደ በሩ ስትሄድ አስመሮም ቀድመው መንገድ ዘጉባት......ማርታ 'እምቢ!' የሚል ድምፅ ወደመጣበት አቅጣጫ ዞር ስትል እንደተጨበጠ ሁሉ ሰብስብ ያለ፣ የወርቅ ኳስ አየር ላይ ሲንሳፈፍ አየች። ወርቁ ይንሳፈፋል......ባዶ አየር ውስጥ ማንም የያዘው ሳይመስል ከፍ፣ ዝቅ ይላል......ማርታ ከአስመሮም ጋር ሆነው ወርቁን ሊነጥቋት ብሩክታዊትን ማሯሯጥ ጀመሩ......ትርምሱን የሰሙ ዮሐንስና ሚስታቸው ሸዋዬ ከመኝታ ክፍላቸው ወጡ......ክፍሎችን የሚለያየው ኮሪደር ላይ እህታቸው ማርታ እንደ እብድ ትሮጣለች ትነጫነጫለች......የሚሰማው የሶስቱ ሰዎች ድምፅ ጆሮ ያደነቁራል......

"ምንድነው አንቺ?" አሉ ሸዋዬ ራቁቷን ለመኾን ትንሽ የቀራትን ማርታ በፒጃማዋ ይዘው እየጐተቱ፡

"ብሩክታዊት ናት......ትረብሸኛለች"

ወይዘሮ ሸዋዬ ባላቸው ያወሯቸውንና በመንደር የተነዛውን ወሬ በአይናቸው ለመመስከር መቻላቸው ደስታ ሰጥቶአቸው የተመለሱ ግን ሲንጫነጩ የሚሰሙ ሰዎችን በጆሮአቸው መከታተል ጀመሩ......

"ምን ኾነው መጡ እዚህ?" አሉ ዮሐንስ

"ብሩክታዊት ሐብሌን ወስዳብኝ......አስመሮም ሊያስመልሳት ነው"

"ምን አገባት በሰው ሐብል?"

"ድርቅና ነዋ!"

ብሩክታዊት ጮኽ ብላ:

"የሮዛ ሐብል ነው......የአንቺ አይደለም......" አለች

የአጥሩ በር ኃይል ባለበት ቡጢ ተንኳኳ......ተደጋግሞ ተመታ:

"ጉረቤት ረበሻችሁ......ውጡልኝ ከዚህ" አሉ ዮሐንስ......

የሳሎኑ በር እንደተከፈተ ብሩክታዊት እየሮጠች ወጣች......አስመሮም ተከተሏት......ሁለቱም በጫጫታቸው ግቢውን ሞሉት......አቶ ዮሐንስ ነገሩ አስመርሮአቸው ለመሳደብ እየፈለጉ ግን ፍርሃት አስሮአቸው ወደ ሚስታቸው ጆሮ ጠጋ አሉና:

"ይሔ ሰው ተሰውሮም፣ ሳይሰወርም አይለወጥም?" አሏቸው......

ሸዋዬ ባላቸው የተናገሩትን እንዳልሰሙ ሁሉ ትተዋቸው ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ......ዮሐንስ የአጥሩን በር ሔደው ከፈቱ......ጉረቤቶቹ ጋቢ ተከናንበው፣ ካፖርት ደርበው፣ ባትሪ ይዘው:

"ምንድነው ረብሻው ምንድነው?" አሉ......

በተከፈተው የውጭው በር ብሩክታዊትና አስመሮም እየተጯጯሁ ወጡ ......ዮሐንስ የአስመሮም ድምፅ ወደሚመጣበት አቅጣጫ እያሳዩ:

"አስመሮም ከልጁ ጋር ይረብሸናል" አሉ......ሰዎች ባትሪያቸውን ፊት ለፊት የሚታይ ነገር እየፈለጉበት የአጥሩን ግድግዳ ሙጥኝ ብለው ቆሙ......

"ምን ኾነው ነው?"

"እኔ ምን አውቃለሁ......ደህና እደሩ......"

በሩን ዘጉት......

ጉረቤቶች ሊያዩዋቸው ያልቻሏቸው ሰዎች የሚያውቋቸው በመሆናቸው ድፍረት ቢሰማቸውም፣ የማይከሰቱ በመሆናቸው ደግሞ ተምታቶባቸውና ፍርሃት ጨብጦአቸው እየተያዩ ከተለጠፉበት ግድግዳ ሳይላቀቁ ጠበቁ:: የሚያለከልኩ ድምፆች ይሰሟቸዋል......ድምፁና ልፊያው ሣር ያልለበሰ መሬት አካባቢ ሲደርስ አቧራ ይነሳል.....ተቷት



@BOOKALEM

እንደጠበቀ የጥሬ ድምፅ ሰሙ......ቀጥሎም የሴት ሕፃን ልጅ ልቅሶ ከከንብንብ ውስጥ እንደሚወጣ ኹኖ አዳመጡት......

"የት ጣልሽው? " አሉ አስመሮም::

"ሀብሉ እኮ የሮዛ ነው......ትናንት አንተ አይደለህም የነጠቅሃት?"

"ስለእሱ ምንም የሚያገባሽ ነገር የለም:: የምጠላውን፣ የምቀጣውን እቀጣለሁ......ይልቁን የት ነው የጣልሽው?"

"አልነግርም"

የጥሬ ድምፅ ድጋሚ ተሰማ......የተሰበሰቡት ሰዎች እየፈሩ፣ እየተገረሙ፣ እየደነገጡ፣ እያሰቡ እነበሩበት ሲቆሙ አስመሮምና ብሩክታዊት እየተንቃረኩ ወደ ወንዝ ወረዱ......

* * *

የከተማው ሰው ቀስ በቀስ ለሁለት ተከፈለ......ችግር ሲያጋጥማቸው ለእርዳታ አስመሮምን የሚጠሩና ብሩክታዊትን የሚጠሩ::

የአስመሮም ሰዎች አስመሮምን ሲፈልጓቸው ተደብቀው ስለኾነ ምን እንደሚሉ የሰማ ባይኖርም ብሩክታዊትን የሚጠሯት ግን እንዲህ ይሏታል:

*"ብሩክታዊት ብሩክቴ*

*ነይልኝ በሞቴ......*

(የሚፈልጉትን ወይም የሚወዱትን ነገር እንድትሰጣቸው ይጠይቋታል፣ በአስመሮም እስከሚነጠቁ ድረስ)

እንደውም ማንቦት ልደታ ከገባ ጀምሮ እስኪጠናቀቅ ያለ አባት፣ ያለ እናት ያለ ዶግ አጉት በየወንዙ ዳር ለምትንከራተተው ብሩክታዊት እንዳይርባት እያሉ በግ ያርዱላት......ንፍሮ ይቀቅሉላት ጀመር......አስመሮምን ፈላጊዎች ደ'ሞ ከቶዎች ናቸው ላለመባል ያንኑ ወር ከሌሎቹ ከብሩክታዊት ተከታዮች ጋር ተያይዘው ወንዝ ይወርዳሉ......ሕፃናትም እንደ ሕዝብ መዝሙር መኾን የጀመረውን የብሩክታዊትን መጥሪያ ዜማቸውን ወንዝ ዳር ኾነው ይዘፍናሉ......

*"ብሩክታዊት ብሩክቴ*

*ነይልኝ በሞቴ......"*

* * *

ከወንዙ በወዲያ ጉን ከሥር መደገፊያ ከላይ ማንጠልጠያ የሌላት አንዲት ኮከብ የመሰለች የብርሃን ነጥብ በአየር ውስጥ እየዋኘች ወደ ወንዙ እየቀረበች መጣች......ለጥቂት ጊዜ......ነፋስ እንደሚያንገላታት ሁሉ ከፍ ዝቅ፣ ከፍ ዝቅ ብላ ቆም አለች......

ይፈስ የነበረው ወንዝ ረጋ......



@BOOKALEM

መንበጫረቅ ከወንዙ አይሰማም......የብርሃኗም ነቁጥ እየጉላች እየጉላች ወደ አንድ ትልቅ የጨረር ኳስ ተለውጣ ወደ መሬት ተጠጋች......ጥቂት ቆይታ የወጣቷ የወንዝ አዋይ ውብ ቁመና ኾነች:: አዋይዋ ስስ ነጭ የሐር ቀሚስ ለብሳለች......ከጠጉሯ ጫፎች የብርሃን ነቁጦች ሳያቋርጡ ወደ ወንዙ ይንጠባጠባሉ......ወንዙ ዳርቻ በአበቦች የተከበበ አንድ ድንጋይ ላይ ሔዳ ተቀመጠች......

ከወንዙ ሌላኛው ዳርቻ በኩል ከትልልቅ ጥምዝምዝ የብሳና ዛፎች መሃል......ፀጉሮቿ እንደ ቁልቋል እሾህ የቆሙ፣ እግሮቿ እንደ ዝግባ እንጨት የተጠመዘዙ፣ አፍንጫዋ ጉብጦ በሁለቱ ቀዳዳዎቿ ወደ ሠፊ አፏ የሚያተኩር፣ ስትስቅ በጥርሶቿ ምትክ ቀጭን ጥቁር ስንጥቅ የሚታይ አሮጊት የወንዝ አዋይ ብቅ ብላ ወጣቷን አዋይ......

"ምርቃትሽ ሰመረልሽ?" አለቻት በማሾፍ::

የጉሪጥ ተያዩ......

አሮጊትዋም መልስ ሳትጠብቅ......ይሄን አለች:

"ጠጠርሽን በጠጠራ ስከዳት
ይህቺ ልብሽን ከፋት፣
አንቺ የምትለግሺውን ጉዳይ
ባላዳረጎቱም እንደሁ አየይ"

ወጣቷም አዋይ ከተቀመጠችበት አለት ድንጋይ ወደ ላይ ዘላ ለጥቂት ጊዜ ስትንሳፈፍ ቆየች፣ ቀሚሷ ከውሃው አልወጣም:: ወደ ብዙ የሚያብለጨለጩ ረቂቅ ከዋክብት በመሰባበር ወደ ሰማይ ውስጥ ተወርውራ እየተሰወረች እንዲህ አለች......

"አምላካችን የሰጠችን አንዳንዲት ጠጠር
ከዚህ ወዲያ ምን ሊፈጠር::
የእኔ እጣ ከልጅቱ
የአንቺ እጣ ከሽበቱ
ልጅት ስትንዘረፈፍ ሽበቱ ይረገፍ"

ሐር ቀሚሷ እወንዙ ላይ እየተንሳፈፈ ቀረ......አሮጊቷ አዋይ በብስጭት እየጮኸች የተደገፈችበትን ምርኩዝ ወደ ወንዝ ውስጥ ወርውራ በፍጥነት በአየር ላይ እየዋኘች ወደ ጨለማ ውስጥ ገባች::

......ዛፎች አውሎ ነፋስ እንደገባቸው ሁሉ ክፉኛ ተወዛውዘው ፀጥ አሉ......

ረግቶ የነበረው ወንዝ መፍሰስ ጀመረ......

---- // ----

ነሐሴ 1977
አዲስ አበባ



@BOOKALEM

# እንጀራዬን

እንደቸኮለ ሲንደፋደፍ የነበረው መንገደኛ ሁሉ እየቆመ ተሰብስቦ ክብ ሠራ......ቀለበቱን ሰንጥቀው የጫማ መወልወያ መሳሪያቸውን በየሳጥኖቻቸው አንጠልጥለው የያዙ ብዙ ሊስትሮዎች በተለያዩ አቅጣጫዎች እየሮጡ ተበታተኑ......

"እዚህ ቤት ፊት ለፊት እንዳላይህ አላልኩህም ነበር?" አሉ አንድ አዛውንት የአንዱን ጉብል ሁለቱንም ጆሮዎቹን በእጆቻቸው ይዘው በቁንጥጫ እየመዘለጉ......ለመከላከል እጁን ሲያነሳ በግራ እጃቸው ቀኝ ፊቱ ላይ በጥፊ አጮሉት......ሰሞሊኖ የተረጨበት መሰለ...... የተመታበትን ቦታ በትከሻውና ዕቃ ባልያዘበት እጁ አሸ......

"ከዚህች ግንብ ሥር......" የሹራቡን ኮሌታ ያዙት......እግራቸውን ወደ ሆዱ ሰንዝረው አብራኩ አጠገብ መቱት......አልተናገረም......በውጋቱ ካጐነበሰበት ሳይቀና በአይኑ ትክ ብሎ አያቸው......ጢማቸው ከቅንጣቸው እስከ ደረታቸው እንደ ጭቃ ወንዝ ይፈሳል......ትናንሽ አይኖቻቸው ቀልተዋል......አንደኛው አይናቸው ሽውራራ ይሁን በስካር ተጨማዶ ሊከደን ደርሶአል......ገንቦ ጭንቅላታቸው ላይ ጭቅቅታም የሰሌን ባርኔጣቸው ሊበታተን እስኪ መስል ድረስ ቀርቅረውታል......ለንቦጫቸው ተላልጦአል......ሁለቱ የፊት ጥርሶቻቸው የሉም......ጥቁር ወፍራም ምላሳቸው ይገባል፣



@BOOKALEM

ይወጣል....ግራና ቀኝ ጉንጮቻቸው ላይ ሁለት ረገዣዥም መስመሮች ቁልቁል በትክክል ወጥተውባቸዋል......ጭንቀትና የእድሜ ባንጠለጠሉ አይኖቹ ሲያያቸው አሳዘኑለትም......

'አንተ ሽማግሌ......እንዴልበላበት ነው......እዚህች ዘንድ ጠርጌ ......የሰው እግር አተረማምሼ ሰስት ዱዲ ብበላ ይጉልብሃል? እንደ እኔ አልለፋሀም? አያሳፍርህም? ዙሪያችንን የከበበን ሰው አያሳፍርህም?' የሚላቸው መስላቸው......

እና ፈሩት......

"ምን ታየኛለህ ደነሞ! እ? ምን ለመፍጠር ነው? እዚህች አካባቢ እንዳላይህ"......በቅጡ ያልተጨበጠ ቡጢ አምዘግዝገው ወደ እናቱ ላኩ ......ስላጉነበስ ሳቱት......እየሸወደ የሚያላግጥባቸው መሠላቸው...... የሚመለከታቸውን ሰው አፈሩ......ራሳቸውን ልጁ ላይ በእልህ ጣሉ...... ውርንጭላ እንደሚጋልብ ሠፈሩበት......የቡኛዎቹ ብዛት ትግ አይላቸውም—እንጭጭ ሰውነቱ ላይ ያሳረፉአቸው......እልፊቸው ቁና ቁና እየተነፈሱ ድብደባቸውን አክትመው ተነሱ......ከቦ የሚያያቸውን ሰው አፍረው ቀና ብለው አልተመለከቱም......

ልጁ እንደ ምድር ትል እየተልፈሰፈሰ አስፋልቱ ላይ ተጋደመ......ያቃስታል......አይኖቹ ላይ ግን እንባ አይታይም......

"እንጀራ ከባድ ነው ልጄ......!" ብላው ነበር እናቱ በአምስት ብር የሊስትሮ እቃ ገዝታ ወደ ፒያሳ መሐል ስትወነጭፈው......"እንጀራ ከባድ ነው ልጄ—ጫማ መጥረግ ምን መሰለህ—የመጨረሻ ቆሻሻ ስራ ነው—በእጅህ የያዝከው ብሩሽ የውሸት ነው—ግን እንጀራ፣ ልጄ—መከራ ነው......ለፍተህ፣ ጥረህ፣ ግረህ፣ ወጥተህ፣ ወርደህ......እንዲያ ነው እንጀራ......እግዜር ካላጣው ብልት እንገታችን ስር ሆድ አስቀምጦ እኔን የመንገድ ዳር ጉልት፣ አንተን የሰው እግር ስር አስፈነደደን—መከራ ነው፣ እንጀራ ነው......»

እግሩ ተጫጭሮአል—ከባቱ ጀምሮ ቁምጣው እስካጋለጠው ጭኑ ድረስ......የመሬቱ አቧራና ሣሮች ሰውነቱና ካኪ ቁምጣው ላይ ተለጥፈዋል...... የሱሪአቸውን ቱቦዎች ከፍ አድርገው "በል በደንብ ጥረግ" ብለው እግራቸው ሥር እንዳለ ረስተውት ደመና ደመና እያዩ፣ የሚያልፍ የሚያገድም የቤት ባት ላይ የሚያፈጡ የወርቅ ውሐ ውስጥ የተነከረ የሚመስል ወፍራም ለበሳ ባቶች ያላቸው ወንዶች ታወሱት......እግሩ እንደ እነሱ ለስላሳ ቢሆን ይመኝ ነበር......የጭኑን ቆዳ ውፍረት የባቱን ቆዳ ክረት በአመልካች ጣቱና በአውራ ጣቱ እየቆነጠጠ ወፍራምነቱንና ሸካራነቱን ይፈትሽ ነበር—ወፍራምም ሸካራም ነበር......ዛሬ አንድ ጠንካራ ሽማግሌ እላዩ



@BOOKALEM

ላይ ተቀምጠው እንደዚያ ሲነርቱት ሲነርቱት፣ ሲያንከባልሉት ደም ሥሩን ጋረደለት......

ከተጋደመበት ከበውት የቆሙትን ሰዎች ...... ቀና ብሎ አየ......የመሸማቀቅ መልክ በሰውነታቸው ንቅናቄ፣ የመገረም ቅርጽ ከአፋቸው አከፋፈት አነበበ......

ሰውዬው ጆርባቸውን ለእሱ ሰጥተው ቆመዋል......አንገታቸውን ቀስ ብለው ጠምዘው ወደ ኋላ አዩ---በትከሻቸው ላይ......ጥቋቁር አይኖቻቸው ከልጁ አይኖች ጋር ተገጣጠሙ......ፊቱ አስጠላቸው......ከዚህ ሁሉ መፈተግ በኋላ ሳይደማና ሳይጫር ቆሞ ሲያዩት ያራገፉት የመሰላቸው ንዴት ተሰባስቦ በጡንቻዎቻቸው ሰረፀ......

በጥቂቱ ጠመም ካለችው አፉ መጨረሻ ያለችው የከንፈሮቹ መገናኛ ጎድጓዳ የሚስቅ አስመሰለችው...... ('የልጁ ውበት አፉ እኮ ነው' ይሉ ነበር እናቱ:: ለሰው ሳይሆን ለራሳቸው---ለሰው ካሉትማ 'ጥጋበኛ ደሐ የምትበላውን አታስብም:: ስለ ልጁ አፍ ውበት ታወራናለች' ሊሉአቸው ይችላሉ---ትቀምሰው የላት የምትበላው አማራት)

አዛውንቱ አይናቸውን በፍጥነት ወደ ግራ ወርውረው ከጉኑ ወደ ወደቀው የሊስትሮ ሳጥን ተንደረደሩ......ልጁ ሁኔታቸው ስላላማረው ወደ ሥራ እቃው ዘንድ ቀድሞ ለመድረስ ተንደፋደፈ......

ሳጥኑ ጋ ከመድረሱ ቀድመው በቀኝ እግራቸው ትከሻው ላይ ረገጡትና ከብ ስርተው ወደ ቆሙት ሰዎች ሥር ጣሉት......ከወደቀበት እንደ ኳስ ነጥሮ ተነሳ......እንዳይቀርባቸው ሳጥኑን ከመሬት አነሱና ባላቸው ጉልበት በአየር ላይ እያሽከረከሩ ጥቂት ቆዩ......

"እባክዎ አበባ ስጡኝ---ስጡኝ" አላቸው......አይኖቹ እንባ አቀረሩ......

አዛውንቱ ማሸነፋቸውን ለማረጋገጥ ሣጥኑን በሁለት እጃቸው ከአናታቸው በላይ አንስተው ከሚጠብቁት ቤት ግቢ እንደ ምላስ ተመዞ የወጣ የሲሚንቶ ደረጃ ላይ ከሰከሱት......

ሕፃኑ ከቆሙ ዘጭ ብሎ በቂጡ አስፋልቱ ላይ ወደቀ---መንጋጋዎቹ እስኪንገጫገጩ......ሳጥኑ ወደ ብዙ ትናንሽ የጣውላ ፍንክትካቶች ተለወጠ......የቀለም ቆርቆሮዎች በየቦታው ቀለማቸው እየተሰባበረ ተበታተኑ......ቡርሾች በየሰው እግሮች መሀል እየተንከባለሉ እየነጠሩ ገቡ......ፊቱ ለሁለት የሚከፈል እስኪመስል ድረስ አፉን ከፍቶ አቀረቀረ......ጉንጮቹን ሳይነካ እንባው ቶሎ ቶሎ ወረደ......እግሩ ስር የተኛው አመድ ከመሰለው አስፋልት ላይ ጥቋቁር ነጥቦች እንደ እንጉዳይ ፈሉበት......ያቃትትበት ከነበረው አፉ

የሚያሰትቅ ድምፅ እየጉላ ወጣ---ዋይታ ኾነ......የለቅሶ ትንፋሽ እንዳጠረው ሲረዳ አቤቱታውን ጀመረ......

"ሳጥኔን......ሳጥኔን......"

ፀጥ ብሎ ይመለከት የነበረው የሰው አጥር እየተንቃነቀ መበታተን ጀመረ

"ሳጥኔን !......ሣጥኔን!"

ሰው ሁሉ ተበታተነ......

"እንጀራዬን!"

---- // ----

ነሐሴ 1975

አዲስ አበባ

# ከሰማያዊ ወደ ቦቢ

ከምንጩ ጉን የሚያልፈው አስፋልት መንገድ ተፈርፍሮ አልቆ አቧራ ኾኖአል......አልፎ አልፎ ነፋስ አመድ ተሸክሞ ይጉርፋል......እናቶችና ሕፃናት ስኳር እንደሚመጥ ቁጫጭ የጉድጓዱ ዙሪያ ተሰብስበዋል......ፊታቸው የቆሸሸ ፎጣ የሚመስሉ፣ ባሊና ምንጭ ላስቲክ የተሸከሙ ሴቶች በአመዳሙ መንገድ ላይ የሚያናውዝ አይነት እየተራመዱ፣ ልፍስፍስ ሳቅ እየሳቁ ወደ የቤታቸው ያዘግማሉ ......ለሶስት ወር ሳያወላውል ከተመደበለት ቀናት ውጭ የቀጠለው በጋና ነፋስ ሰውን ቡሳ አድርጎታል፣ የሕፃናት ገጽ እንደ ከረሜላ ልባስ ተጨማዶአል፣ ጫጫታቸው ግን የሞቀ የዋህነት ነው......

ስድስት የሚሆኑ ሕፃናት መንገዱ ዳር ተሰብስበው ይጫወታሉ......ትርምሳቸውና የሚለዋወጡት ንግግር የሳበው አንድ ጎልማሳ ጉዞውን አቋርጦ ቀረብ አላቸው......

ነጭ ቀለም ያላት ወፍራም ቡችላ ከበው ቆመዋል......እድሜዋ ወር የሚሞላ አይመስልም......ረዥም ጆሮዋ እንደ ኮሌታ አንገትዋ ዙርያ አርፎአል......አይኖቿ ወርቅማ፣ ክብና ንፁህ ናቸው......ፀጉሯ ረዥም ነው.....እፏ የሕፃን ልጅ፣ ትክ ብለው ሲያዩዋት ደግሞ በትንሹ---በጣም በትንሹ ፈገግ የምትል ትመስላለች......

"አንተ በእግርህ አትንካት" አለ አሥራ አንድ አመት የሚኾነው አንድ ልጅ:: ፊቱ በጭርት ነጠብጣቦች ተሸፍኖአል......ቢጫ ወፍራም

የንፍጥ ዘንግ ከግራ አፍንጫው ቀዳዳ ጀምሮ ምንጭሩ ላይ ሲደርስ ደርቆ ቆሞአል......ያደፈ ቡናማ ባለ ጉርድ እጅጌ ሸሚዝ ለብሶአል......በሸሚዙ ሰፊ ቀዳዳ እምብርቱ ትታያለች......በጥብጣቦቹ ያልገባ የቀበቶው ጫፍ እግሮቹ መሃል ድረስ ተንጠልጥሏል......ወደ ውሻዋ ቀርቦ ጀርባዋን ዳበሳት......ከተቀመጠችበት ተነስታ እግሩ መሃል ቆመች......የልጁን አንድ እግር አነፈነፈችና በሰውዬው አቅጣጫ ቀና ብላ ተመለከተች.....ሰውዬው በፍቅሯ ወደቀ....

"የማን ቡችላ ናት?" አለ ሰውዬው::

ሕፃናቱ የአይናቸውን ትኩረት በመውደድ ከሚመለከቷት ውሻ ላይ ነቅለው ዞር ብለው መሃላቸው የቆመውን ንፍጣሙን ልጅ አዩት......እሱም ሊነጠቅ እንደ ፈራ አይነት ወደ ቡችላዋ አጐንብሶ በእጆቹ ይዳብሳት ጀመር......

ሰውዬው መልስ ስላልተሰጠው ጥያቄውን ደገመ:

"የማናት?"

ሁሉም ሕፃናት መሃል ወደ ቆመው ልጅ ተመለከቱ......ሰውዬውና ልጁ ጥቂት ተያዩ....

"የአንተ ናት?" አለው......

መልስ ሳይሰጠው ልጁ የዳቦ ፍርፋሪ ከሱሪው ኪስ አውጥቶ ቡችላዋ አፍ ሥር በእጁ ያዘላት......መብላት ጀመረች......

ሰውዬው ይህቺ ስታድግ ጠንካራ ውሻ መኾን እንደምትችል ገምቶ የሕፃናቱን ከብ ጥሶ ወደ ልጁ ቀረበ......

"የኔ ናት" አለው በድንገት---ልጁ......

ፍርሃቱ ገብቶት:

"አይዞህ አልወስድብህም" አለው......

ዝምታ......

"እስኪ ልያት" አለው እጁን ዘርግቶ......

ልጁ ወደ ኋላ ሸሸ......

ዝምታ......

ልጁ ከቡን ሰብሮ ወጥቶ ቡችላዋን አቅፎ ወደ ምንጩ ወረደ......ሕፃናቱ ስድስት የጠጠር ናዳዎች---ተከተሉት......

* * *

የቤቱ የውጭ ግድግዳው ደማቅ አረንጓዴ የተቀባ ነው......ከኘላኑ ይሁን ካለማስተዋል የቤቱ ዋና መግቢያ ከጀርባው ነው......መናድ በጀመረ የድንጋይ ምሰሶ የተደገፈው የግቢው አጥር ዘሞአል......ከፊል

ጉኑ ቆመው የነበሩ እንጨቶቹ በባዕዳን ለማገዶ እየተጉተቱ አልቀዋል......

እቤቱ ገባ......

"ሰማሽ ሰላማዊት፣ እዚህ ጉረቤታችን ያለው ጭርታም ልጅ ስሙ ማነው?" አላት ሚስቱን......ገና የእንጨት ወንበር ስቦ እንደተቀመጠ::

ፀጥታ......

"አንቺ፣ አትሰሚኝም?!" ድምፁን ከቀድሞው ከፍ አድርጎ......

"ከእነሱ ጋር መላፋት ፈለግህ?" አለችው......

ከጉንጉኑ የተላቀቀው ፀጉሯ እንደ ብዙ ቀንድ ቆሞአል......ከጠይም ገጽዋ ላይ ጉልተው የሚታዩት ረገግሽም ነጭ ጥርሶችዋ ሽኮኮ ያስመስሉአታል::

"ውሻ እንደምንፈልግ ታውቂያለሽ:: እሱ ልጅ በምታሳዝን ቡችላ ይጫወታል......እንዴት ያንገላቷታል መሰለሽ!"

ከተቀመጠበት ተነስቶ በሳሉን መስኮት በኩል ወደ ውጭ አየ......

"ብርሃኔን ነው?" አለችው ሰላማዊት......

"እርግጠኛ ነሽ ስሙን?"

"ቡናና ዘይት እንዲገዛልኝ የምልከው እሱን አይደል?" አለችው......

ፊቱን እንዳዞረ ጥርሱን ነከሰ......'አይዞሽ' ብሎ አዝኖ እንዲያቅፋት፣ ወይም ዛሬም እንሞክር ብሎ አልጋ ላይ ደጋግሞ እንዲጥላት በተመቻቸና ባልተመቻቸ ጊዜ ሁሉ ልጅ አለመውለዳቸውን ታስታውሰዋለች......እንዳላወቀው ሁሉ......

"አሁን ልትጠሪው ትችያለሽ?" አላት

"ለምን?"

"ቡችላዋን እንዲሰጠን"

ዝምታ......

"በረሃብ ነው የሚገላት......ይልቁን ቢሰጠን በእሱ ስም እንሰይምለታለን" ለራሱ ሳቀ......

"ደግ የዋህ ልጅ ነው ይሰጠናል" ወደቆመበት መጥታ ትከሻውን እያቀፈችው....

"ይልቁን ቶሎ ጥሪልኝ......እቀፊኝ አላልኩሽም......ቡችላዋን ብታያት በፍቅር ትሞቺያለሽ"

"ሂ---ሂ---ሂ---ሃ---አሁይ---!" በውሸት ሳቅ ተተረተረች......ዕንባ ያቀረሩ ዐይኖችዋን ወደ እሱ ሰቅላ አፍዋን ያዘች......



@BOOKALEM

ባልዋ ፍቅሩን ከእሷ ወደ ውሻዋ ማዞሩ እንዳስቀናት እንዳይታወቅባትና ማሾፍ እንዲመስልላት፡ "ብለህ ብለህ ውሻ ወደድህ? እጠራልሀለሁ" አለችው......ትታው ስትሄድ ግን እርምጃዋ እንደድሮው ሳይሆን በቁጣ ትንሽ ተመናቅሮ......

ለምን እንዳገባት ይጠይቃል፤ በልቡ ሲጀመር ከብ ቅርፁ ያምር የነበረው ቂጥዋ በዝግመተ ለውጥ እሱም ይሁን ዳርዊን ሊገባው በማይችለው መንገድ ሞላሌ ኾኖአል......በእሱና በእሷ ፍካቢ ስጋ መሃል ቆሞ የሚያየው ይሄ ደባሪ ቂጧን ነው......ወይስ የሴት ቁመና እየጠላ ሄደ?

"ይሔ ግቢ መጠበቅ አለበት......ስንት ጊዜ ሌባ እንዳስቸገረን ታውቂያለሽ?......ስንት ጊዜ ከእንቅልፋችን እንደባነንን፣ ይልቁን ሳይመሽ ጥሪልኝ......"

ፀጥታ......

በምሽቱ ውስጥ የሚስቱ ነጭ ቅርጽ ከግቢው እየተንሳፈፈ ወጣ......

"ብርሃኔ! ብርሃኔ!"

ትንሽ ቆይቶ፡

"እመት!" ከርቀት የሚሰማ የልጅ ድምፅ......

"ይዞኻት ና......ይዞኻት ና አልኩህ!" አለች......

ባልዋ መስኮቱን በቡጢ መታ......

"የዚህ ዘመን ህፃናት ከማሕፀን ውስጥ ነው ቀበሮ ኾነው የሚወጡት"

ሚስቱ የተገረመ ፊቷን አስቀድማ እየተጉተተች ገባች......

አካሄዷ ውስጥ የረቀቀ ተስፋ መቁረጥ አለ---አተኩረው ካዩአት:: ከመነሻ ወደ መድረሻዋ በግዴታ የምትመላለስ ይመስላል:: ለብዙ አመታት ከባልዋ ጋር ተኝተው ያደሩ ዕለት ለብቻዋ ተቀምጣ ሆድዋን እየዳበሰች እውስጥዋ የተጠራቀመው የባሏ ፍስ ልጅ እንዲሆን ትፀልይ ነበር:: የወር አበባዋ አንድ ቀን እንኳን ሲዘገይ እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ አምላክን ታመሰግናለች፤ ቁምሳጥኗ የምታስቀምጣትን የእመ ብርሃንን ፎቶ አውጥታ እስኪረጥብ በምራቋ ትስመዋለች......አሁን የቀራት ሞቶ እንደተነሳ፣ እንደፈዘዘ መራመድ ነው......ከቀልቃላ ሴትነቷ ሁሉ ነገር ተመጦ ወጥቶ የቀረችው 'ድንገት ቢቀናኝ' የምትል ሴት ናት፣ ያውም ያለ ማርያም......

ዝምታ......

"እምቢ አለኝ......አልመጣም አለ፣ እንኳን ውሻዋን ሊያመጣ...... ጠይቀኸው ነበር እንዴ?"



@BOOKALEM

አልመለሰላትም......ኒያላ ሲጋራውን አቀጣጥሎ የሃሳብ ሐይቅ ውስጥ ሰመጠ::

* * *

በሚቀጥለው ቀን ልጆቹን እዚያው ቦታ ተሰብስበው አገኛቸው......ብርሃኔ ሰውዬውን ገና ከሩቅ ሲያየው ውሻውን ይዞ ሌሎችንም ልጆች አስከትሎ ከመንገድ ራቅ ብሎ ቆመ......እልፍ እልፍ ቀና እያለ ያያል፣ የሰውዬውን እርምጃ አቅጣጫ እያጤነ.....ከተጠጋው ለመርጥ የተዘጋጀ ይመስላል::

ከብርሃኔ ጓደኞች አንዱ የእድሜው ከሌሎቹ መብለጡ ድፍረት ሰጥቶት ይሁን ወይ ቸልተኛነት ተጠናውቶት አይታወቅም፣ ጠባብ ደረቱን እስከ መጨረሻው ወጥሮ ሰውዬውን እስኪቀርበው ጠበቀው......እሱን ቢያየውም ያለመፍራቱን በሰውነቱ ንቅናቄ ለመግለጽ እጆቹን ወገቡ ላይ አድርጐ ለማንም የማይሰማ ለራሱ ብቻ ከሚያዳምጠው ዘፈን ጋር ያለ ይመስል እግሮቹን በስልት ያነቃንቃል......

ሰውዬው ሲጠጋው ብቻ የተምታታበት መሰለ......

"የብርሃኔ ጓደኛ ነህ?" አለው......

ልጁ ከብዙ መልሶች የተሻለውን እንደሚመርጥ ሁሉ ትንሽ ቆየና፣

"አዎ" አለ......

ስለ ውሻዋ ጉዳይ ቶሎ ማንሳት ልጁን የሚያስፈራው መስሎት የሚናገረውን ለማሰብ ወደ ሰማይ ሲያንጋጥጥ:

"ሰማያዊን ይፈልጓታል እንዴ?" አለው ልጁ......

"ማን ናት ሰማያዊ?" አለ ሰውዬው በመገረም፣ የጥያቄውም ልዩ መኾንና ድንገተኛነት አስደንግጦት......

"የብርሃኔ ቡችላ ናታ!" የእውቀቱ ትልቅነት አስደስቶት የእግሩን ንቅናቄ ጉራ ጨምሮባት ወደ ዳንስ እያስጠጋት......

"ሰማያዊ! ምን አይነት ስም ነው እባክህ?" አለው በመደነቅ......

"ያለፈው አሥራ አምስት ቀን ሞቢል ቤንዚን ማደያ ስናገኛት ቤት እየታደሰ ስለነበር ሰማያዊ የግድግዳ ቀለም ፈስባት ነበር"

"ለዚህ ነዋ 'ሰማያዊ' ያላችኋት! እኔ እንኳ አልፈልጋትም"

"ትናንት እትዬ ሲጠሩት እምቢ ያለው የሚወስዱበት መስሎት ነው»

እግሩን ማነቃነቅ አቁሞ ሰውዬውን ትክ ብሎ ተመለከተና ቀጠለ፣

"ታዲያ ለምንድነው ጋሼ?"

"እኔ እንኳን ደስ ስላለችኝ አንገቷ ላይ ይሄን ጨርቅ ሳስርላት ነበር" ብሎ ከኮቱ ግራ ኪስ የገና ስጦታ ማሰሪያ ረዥም ርካሽ የቦብሊን ጥብጣብ አውጥቶ አሳየው......

ልጁ ጨርቋን ለመያዝ የዘረጋው እጁን በሃፍረት ቶሎ መለሰ......

"ግድ የለም፣ ግድ የለም......ውሰድና ስጠው" አለው ሰውዬው......

ልጁ ጨርቋን ይዞ፣ አሠራሯን በማድነቅ ሲመለከት ቆየና:

"ይህቺ ነገር ውድ ሳትሆን አትቀርም" አለ......

"ስማ ማሙሽ፣ ብርሃኔ ሰማያዊን አይሸጣትም? ጨርቋን ሳንተ ውሰድ.....ቡችላዋ ያለጥብጣቡ መኖር ትችላለች"

"እሬ---እንጃ---ብቻ---" እግሮቹን ማነቃነት አቁሞ ሰውዬውን ትክ ብሎ ተመለከተው......

"እውነቴን ነው እንዲህ ከምታንገላቷት ሊያሳድጋት ለሚችል ሰው ለምን አትሰጧትም......ትንሽ ካደገች ደግሞ ሆዷ ያድጋል፣ ይሰፋል፣ማሳደግ ይከብዳችኋል......መጠለያ መስራት ያስፈልጋል......ብዙ ነገር አለ......ቀላል ይመስላል እንጂ......እንትን---የብርሃኔ ቤተሰቦች ሃብታም ናቸው?"

ልጁ ነገሩ ሁሉ ከብዶት ዝም አለ......

"ስምህ ማነው?"

"ዲ---ዳምጠው" አለው......

"ስማ ዳምጠው፣ ዲ ብልህ ይሻላል? ከልጆቹ ሁሉ ትልቅ አንተ ነህ......ሳይገባህ አይቀርም ብዙ ነገር......ደግሞ አራዳ ትመስለኛለህ......ብርሃኔን ለምን እንዲሸጣት አትነግረውም......የማደርግልህን አታውቅም......ሲኒማ ትወዳለህ? አሃ ሃ! ከረሜላ የምትወድም ትመስላለህ......ጥርስህን ያበላሸብህ እሱ ነው?" ኮቱ ቀኝ ኪስ ያገኘውን ሳንቲም ዘግኖ ለዳምጠው ዘረጋለት......

"ስንት ነው? ስድሳ ሳንቲም? ለዛሬ ይበቃሃል......መልሱን ማታ ቤቴ መጥተህ ንገረኝ.....ቻው!"

"ቻው!" አለ ልጁ በመገረም......ሣንቲሞቹን ወደ ሱሪው ኪስ እያስገባ....

ሰውዬው ብዙም ሳይርቅ እነ ብርሃኔ እየሮጡ መጡ......

"ምን አለህ?" አለ ብርሃኔ፣ ሰማያዊን በሁለት እጆቹ አቅፎ ይዞ......

"ምንም......ምንም!" ግራ ገባው......አንገቱ ላይ እንደ ክራቫት ያንጠለጠላትን ጥብጣብ እንኳን ረሳት......

"ታዲያ ምን ነበር የምታወሩት? ይኼን እሱ አይደለም የሰጠህ?"



@BOOKALEM

"ይሔን ጨርቅ ለሰማያዊ ስጣት አለኝ" አለው::

ጓደኞቹ ሊላም ጥያቂ አልጠየቁት......ለአስር ደቂቃ ያህል ሰማያዊ አንገት ላይ ሰውዬው ለዳምጠው የሰጠውን ጥብጣብ እንዴት ማሰር እንደሚችሉ ሲመካከሩ ሲከራከሩ ቆዩ......

ብዙም ሳይቆይ ዳምጠው ትቶአቸው ሄደ......ስልሳ ሳንቲም ያስቀመጠበትን ኪሱን ዳብሶ እዚያው ሠፈር አንድ ሻይ ቤት ገባ......

ደስ ብሎት ከሻይ ቤት ወጣ......በወላለቁ ጥርሶቹ መሃል የተወታተፈ የስንዴ ሊጥ በጥፍሮቹ እያነገለ ማታ ምን ማድረግ እንዳለበት ማውጣት ማውረድ ጀመረ......

ብርሃኔ ውሻዋን እንደማይሸጣት የተረጋገጠ ነው......ማታ እንኳን አብሮአት ነው የሚተኛው......አደናቅፎአት እንኳን ስትወድቅ አንስቷት ጆሮዋን ይስማታል......አፍዋንም!......ልጅነት ነው እንኳን ባይባል ሞኝነት ነው......

በሠላም እሺ ካላለ---መንጠቅ ግዴታ ሊሆን ነው......ብርሃኔ ውሻዋን እሸጣለሁ ቢል ገንዘቡ የሚሄደው ለብርሃኔ ነው---ዳምጠው ብሩን መውሰድ አለበት---ውሻዋ ደግሞ ከባለቤቷ ሌላ ማንንም አትወድም......

* * *

ዲ በሚቀጥለው ቀን ከረሜላ ገዝቶ እየመጠጠ አቶቡስ ጣቢያ በረንዳ ላይ ከፀሐይ ተከልሎ ቆሞአል......ምንም የውሳኔ ሃሳብ አልመጣለትም......ጥሩ ብልጠት ማሰብ አለመቻሉ አሳፍሮት ለሰውዬው ቃል መግባቱን ጠላ......ከረሜላውን ጨርሶ እጁን በልብሱ ሲጠርግ አንድ ሃሳብ ብልጭ አለለት......ብርሃኔን ከነውሻው ከሠፈር አርቆ መውሰድ እና መምታት......ቢጮህ እርዳታ አይመጣለትም:: ሮጦ የሚያሳብቅበት የእናቱ ቤት አይኖርም......ዳምጠው የበላው እንዳይታወቅበት አፉን ጠራርጐ፣ ዘይታም እጁን በአቧራ አሻሽቶ ወደ ጓደኞቹ ሄደ......

"አላማረባትም?" አለ ብርሃኔ፣ ሰማያዊን ፊቷን ወደ ዳምጠው እንድታዞር አድርጐአት......ቡችላዋ እንደ አማረባት ያወቀች አይነት በቀስታ እየዞረች ጌጥዋን ለ ዲ ም ለሌሎችም አሳየች......

"ለምን እና ተስፋ ሠፈር አንወስዳትም? ሰማያዊን ቢያዩዋት ይወዱአታል" አለ ዳምጠው......

"ሩቅ አይሆንም? ይደክመናል» አለ ብርሃኔ፣ ቡችላዋን በአንገቱና በጉንጩ መሃል አስገብቶ እያቀፋት......

"ምን ይደክማል? ሰማያዊን መሸከም እንደኸነ እኔ አግዝሃለሁ" አለው፣ የቡችላዋን ኮሌታ በጣቶቹ እየነካካ---ዳምጤ......

አብረዋቸው ያሉ ሕፃናት ሁሉ ቆንጆ ቡችላ አለን ብለው ሊላ ሠፈር ልጆች ላይ ጉራ ለመንፋት በጫጫታ ተስማሙ......

የተስፋ መንደር ልጆች ተሰብስበው የሚጫወቱበት እተለመደው ሜዳቸው ላይ በአጋጣሚ አልነበሩም......የሰፈራቸው ትላልቅ ልጆች የእግር ኳስ ግጥሚያ ሊያደርጉ ማዘጋጃ ቤት ሜዳ ወጥተዋል ተባሉ...... ከዚያ አድካሚ የሰላሳ ደቂቃ መንገድ በኋላ ማንንም ባለማግኘታቸው ሕፃናቱ ተበሳጩ......እንሂድ ያሉት ሁሉ፣

"ምን፣ ይሔ ዳምጤ እኮ ነው፣ እንሂድ፣ እንሂድ ብሎ......" እሉና አጉረመረሙ......

ሰማያዊ ቅልልቦሹና መተሻሸቱ አድክሞአት ባገኘችው የሕፃን እቅፍ ውስጥ ተልፈስፍሳ ታናውዛለች......ዳምጤ እንዳልተሳሳተ ለማሳየት ጨዋታዎችና ወሬዎች ለማምጣት ሞከረ......ጓኑቶ የሚያዳምጠው አላገኘም......

"መሃረቦሽ እንጫወት" አለ ዲ......

ሁሉም ቀና ቀና እያሉ በትናንሽ ስለታም ዐይኖቻቸው ተመለከቱት::

"አሌ ቡም እንጫወት እሺ---ምን እዚህ እንደው!?"

"ማን ይችልሃል አንተን? እኛ የማንችለውን እንጫወት እንጫወት ይላል" አለውና ብርሃኔ......እጁን ስለደከመው ውሻዋን ከእቅፉ አውጥቶ መሬት ላይ አቆማት.....ገላዋን እራግፋ የምታምር ትንሽ አፍዋን በድካምና በስልቹነት በለቀጠችና የማያስፈራ የአፍዋን ቅላት ለሁሉም አሳየቻቸው......ከት ከት ብለው ሳቁ......

"እኔ ልያዛት አይደል ብርሃኔ......ነይ ሰማያዊ! ነይ! ነይ"

ቆማ ወደ «ዲ» ቀና ብላ አይታ ወደ ብርሃኔ እግሮች መሃል ልትጠጋ ስትል......ዳምጤ ከመሃል ያዛት......

"አንተ እንዳትጥላት! ቀስ በል!" አለው ብርሃኔ......

"ተስፋን ለምን ቤቱ ሄጄ አልጠራውም? እዚህ ከምንጠብቀው" አለ ዳምጤ::

ከልጆቹ አዎንታ እንኳን ሳይጠብቅ ሰማያዊን እንዳቀፈ ወደ ተስፋ ቤት አቅጣጫ ሮጠ:: ሁሉም ደክሞአቸው ስለነበር አልተከተሉትም......ዳምጤ ትንሽ ከሮጠ በኋላ ከአንዲት ቤት ጀርባ ቆሞ እነ ብርሃኔ ከተቀመጡበት እንዳልተነሱ አረጋግጦ መንገድ አሳብሮ ወደ ሰፈሩ ተመለሰ......

......ሰማያዊን ይዞ ሰውዬው ቤት እንደደረሰ......በር ሲያንኳኳ የሰማው አልነበረም......በቀስታ እየተራመደ ወደ ግቢው ገብቶ ቤቱን ቀርቦ ተጣራ......



@BOOKALEM

"ጋሼ ! ጋሼ !"

የሰውዬው ሚስት ዛሬም በጉሯ እንደቆመ ወጣች......መጀመሪያ ልጁን፣ ከዚያ ውሻውን፣ ከዚያ ልጁን፣ ከዚያ ውሻውን አይታ ኮስተር አለች......

"ጋሼ ና ብለውኝ ነበር"

"ማን ጋሼ?" ፊቷን ወደ ቤት ውስጥ አዙራ ባሏን:

"ፈልገኸው ነበር?" አለች.....

ሰውዬው ወደ ውጭ ወጣ......ገና ቡችላዋን ሲያይ:

"ግባ ዳምጤ......ግባ......መጣህ?" አለ ውሻዋንም ዞር ብሎ ሳያይ......ልጁ ትንሽ ተቃለለ......

ገና እቤት ገብቶ ሳይቀመጥ ሰውዬው ቡችላዋን ከዳምጠው ተቀብሎ እንደተወዳጀት ሁሉ ያሻሻት ጀመር......

"እስኪ ዳቦ ሻይ በይው" አላት ሚስቱን በለበሰው ጋቢ ላይ እንኳን የሚታይ ሞላላ ስፋት ያለው ቂጥዋን እየሳበች ወደ ጓዳ ገባች:: ብዙ ቆየች......

ሰውዬው ከሱሪው ኪስ ሁለት ብሮች አውጥቶ የዳምጠው አይን ላይ አተኩሮ ቆይቶ አይኖቹ ውስጥ ሊፈነዳ የደረሰ ገብጋባነት ሲያይ እንዲወስድ ሰነዘረለት ......

"አምስት ብር አሳሉኝም?" አለው

"ሁለት ብር አይበቃህም? ብርሃኔ የት አለ?" አለ ሰውዬው

ዳምጤ አልመለሰም......

የሰውዬው ሚስት ዳቦ ያለሻይ አምጥታ ዳምጠው ጭኑ ላይ አስቀመጠችለት::

......የጀመረውን ጥያቄ ሳይቀጥል ቂጣውን መብላት ጀመረ......

"ሚስት! ሠራተኛ ፈልጊ እስኪ......ይህቺን ውሻ ጉድጓድ ውስጥ ስለማሳድጋት በዚያ በላይ በኩል መሬት የሚቆፍር......"

ሚስት ቡችላዋን መጀመሪያ ስታያት አልወደደቻትም ነበር......ኋላ ግን በውሻ ጩኸት ባሏ ከሚያንኮራፋበት እንቅልፉ መቀስቀሱ ለእሷ ጥቅም እንዳለው አሰላስላ በመረዳቷ:

"እሺ! የኔ ጌታ" አለችው......የልብ ሃሳብ እዛው ራስ ልብ ተቀብሮ መኖሩ ደግ አለች:: የባልና ሚስቱ ውይይት ለዳምጤ ደንታ ሳይሰጠው ዳቦውን በልቶ ጨርሶ ተነሳ......

"ስሟን ማን ልበላት?" አለ አፉን ወደ ሚጠራርገው ዳምጤ ዞር ብሎ......



@BOOKALEM

ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ......

"የእኛ ውሻ ስም ቦቢ ነው......አሁን አርጅቶ እንኳን የሚሞት አይመስልም......አንድ የሚችለው ውሻ የለም---በጥል" አለ ዳምጤ በስሜት......

"በቃ እንዳንተ ውሻ 'ቦቢ' ይባላል" አለ ሰውዬው

......በሚቀጥለው ቀን ዳምጠው ሲኒማ ቤት ገብቶ ዋለ......

* * *

እነ ብርሃኔ ዳምጠውን ጠብቀው ጠብቀው ከነውሻው በመጥፋቱ ተደነጋግረው ወደ እነ ተስፋ ቤት ሄዱ......ተስፋ ገና የጥሪ ድምፃቸውን ሲሰማ የጨርቅ ኮፍያውን አይኑ ድረስ ወደታች ጎትቶ ከቤት ......ጉንፋን ይዞታል......ንፍጡን ከመጥረግ ይልቅ አንዱን ቀዳዳ በጣቱ ተጭኖ ሌላውን በትንፋሹ ንፋስ ይናፈጣል---ያፈናጥራል......በዚህ ችሎታው ይኮራል......

"ዲ አልመጣችም?" አለ ብርሃኔ......

"ዲ? አላየሁትም ዛሬ" ከአንድ የአፍንጫው ቀዳዳ ንፍጥ ወረወረ......ብርሃኔ ደነገጠ:: ዳምጤን ፍለጋ ዙሪያውን ተገላመጠ:: የሚሄድበት ተምታታበት......ግራ የገባቸው ጓደኞቹ የሰማያዊን ባለቤት አፍጠው አዩት......

ዘጭ ብሎ ወደቀ ከቁሙ----ቁቁታ ጀመረ......

ተስፋ ደንግጦ እየውና:

«ምን ይጠበስ ነው?» አለ በንቀት......

"ዳምጤ ውሻውን ወስዶበት ነው" አለ ከብርሃኔ ጋር የነበረ አንደኛው ልጅ......

"ለውሻ እንዲህ ያለቅሳል? እዚያ ቆሻሻ መጣያ ኑ ላሳያችሁ፣ ብዙ አሉ»

የተስፋን አስተያየት በኡኡታው ውስጥ ያዳመጠው ብርሃኔ ተስፋን ለማሳዘን አንገቱን ሰበረ......በሆዱ ግን ጠላው......ሌሎች ልጆች እንደ ብርሃኔ የቡችላ ባለቤት መሆን ስለፈለጉ ብርሃኔን እያለቀሰ ጥለውት ከተስፋ ጋር ወደ ቆሻሻው መጣያ ሄዱ......

ብርሃኔ በእንባ የረጠበ ጉንጩን በሸሚዙ ኮሌታ እየጠረገ ከኋላቸው ቀስ እያለ ተከተላቸው......

ብዙ ቡችሎች አሉ የተባለበት ቦታ ሲደርስ ተስፋ እየተናፈጠ ቆመ......

"እኛውላችሁ!"



@BOOKALEM

ልጆቹ ችብ ብለው አቧራና ወረቀት ውስጥ ወደሚርመጠመጡት ጥቋቁር ቡችሎች ተጠጉ......የቡችሎቹ እናት የአራስነት ክልሏ መደፈሩን ስታይ ጥርሶቿን በንዴት ሸለቀቀች......

ሕፃናቱ በፍርሃት እየሮጡ ተመለሱ......

ብርሃኔ ቡችሎቹን እያየ ቆመ......ጠላቸው......ቀስ እያለ......ብቻውን ወደ ቤቱ ማዝገም ጀመረ......ለአንድ ሳምንት ያህል ከዳምጤ ጋር አልተገናኙም......

* * *

ሲገናኙ......

"የት አደረካት ሰማያዊን?" አለው ብርሃኔ በፍርሃት ራሱን እያከከ......

"አምልጣኝ ሮጠች......ልይዛት አልቻልኩም......» አለ ዳምጤ

ዳምጤ የቆጨው ይመስላል......ሲናገር ድምፁን ዝቅ አድርጐ ነው......ውሻዋን ሸጠ ያገኛት ሁለት ብር ብዙ የምትቆይና የምታዝናናው መስሎት ነበር......ሲኒማ ገብቶ ያየውንም እንኳን ለሌሎች ማውራት አልቻለም--ገንዘቡን ያመጣበት ቦታ የሚጠየቅና የሚታወቅበት ስለመሠለው......

"ወዴት ሮጠች ታዲያ? አትነግረኝም ነበር?"

"አፍህን ያዝ!" አለው በቁጣ......ከንፈሮቹም እየተንቀጠቀጡ......

ዝምታ......

ብርሃኔ አንገቱን ደፍቶ ዞሮ ለመሄድ መራመድ ሲጀምር፣

"ብርሃኔ!" ብሎ ጠራው......

ብርሃኔ ተስፋ በቆረጠ ስሜት ፊቱን ብቻ ዞር አደረገ......

"እዚህ ቤት ያለው ሰውዬ ወስዷታል" አለውና፣ ሌላ ወሬም ሳይቀጥል ጥሎት እየሮጠ ሄደ......

* * *

ብርሃኔ ብዙ ጊዜ ሰውዬው ቤት አካባቢ እየተልከሰከሰ ሰማያዊን ለማየት ሞክሮ አልቻለም......ከአእምሮው ተጨልጣ የማየት ዕድል አልጠፋችም......ትዝታዋ አልለቀቀውም......ግን የምትለው አጋጥሞት አያውቅም:: ስኳርና ሻይ ቅጠል ግዛልኝ የሰውዬው ሚስት ውሻውን ከሰረቁት በኋላ ዳናዋም የለ:: የተሴረበት ይመስለዋል:: ሰዎቹ ብቸኞች ስለሆኑ ቡና ሊጠጣ የሚመጣ ጎረቤት እንኳን የለም......ከሰው እንዳልተፈጠሩ ሁሉ ዘመድ ሊጠይቃቸው አይመጣም......ወይም ሲመጣ አላጋጠመውም......



@BOOKALEM

እንድ ዕለት የእንቁጣጣሽ በዓል ባለፈ በሁለተኛው ቀን እቤቱ ፊት ለፊት ቆሞ በቅጠል ኳስ ጢብ ጢብ ሲጫወት ከዘራቸው ላይ ሊወድቁ ትንሽ የቀራቻው ሽማግሌ ቀረቡትና እናገሩት:

"ልጄ፣ አቶ በለውን ታውቃቸዋለህ?"

ሰውዬው እናታቸው ላይ የፀጉር ዘር የለም......ተጨማደ የተንጠለጠለ ፊታቸው እርጥብ ጀንዲ ይመስላል......ሁለመናቸውን እየ......ዝም ቢል ደስ ይለው ነበር......ሆኖም ሰማያዊን ለማየት ዕድል ያገኘ ስለመሰለው ሊረዳቸው መረጠ......

"እዚህ ጋ ነው......ኑ ላሳይዎት" አላቸው

"ጉሽ ልጄ፣ ጉሽ፣ ጉሽ!"

የሰውዬውን የውጭ በር አንኳኳ......

ትንሽ ቆይቶ ተከፈተ......

እንግዳ ሰዎች መምጣታቸውን ያየው 'ቦቢ' መጮህ ጀመረ......ትልቅ ነጭ ውሻ ከታሰረበት ቦታ ጥርሱን ገሽልጦ ወደ ብርሃኔና ሽማግሌው አቅጣጫ...

......ብርሃኔ ሰማያዊን በመደነቅ ሲመለከት ቆይቶ፣ እቆመበት በልቅሶ መንዘፍዘፍ ጀመረ......

---- // ----

*ሚያዚያ 1976*

*አዲስ አበባ*



@BOOKALEM

# ከልጅቷ

"በብቻኝነት ክር ላይ---
ሁሉ ያንጣጥራል......
ተኰስኩ ቢል እንኳን ጉበዝ ነኝ ባይ
እስከ ሕልፈተ - ዓለም ይስታል::
ክሩ እንኳን ቢኖርም
ለተመልካች አይታይም"

/ከልጅቷ/



@BOOKALEM

## ማታ ሶስት ሰአት ተኩል፡

የፎቶግራፍ አልበሚ ቦርሳዬ ውስጥ ይነጥራል:: ቦርሳዬ ብብቴ ሥር ይነጥራል:: ነፋሱ ቀዝቃዛ ነው:: ወደ እኔ የሚነፍሰው ብቻ ይሆን? ቆዳ ጫማዬ እንደ ፈረፋንጉ ይጮኻል:: ይሄም የማላውቀውን የማያውቀኝን ይቀሰቅሳል:: የእንግዳ ሰው ጆሮዎች ወደ እኔ አቅጣጫ ቆመው ያዳምጣሉ......

ስለምን ቤቴ በቶሎ እደርሳለሁ? ተኝቼ ለማለም? ሁልጊዜም አልማለሁ:: ለማንም ያልኾነ ቦታ ያውም የሰው ታክሲ ውስጥ እንኳን ሆኜ ዐይኖቼን ከድኜ አልማለሁ:: የምወዳቸው ሁሉ ትተውኛል:: እኔ የምሻር ነኝ? የተሰነጠቀች ልቤን የትኛውም ሲሚንቶ፣ የትኛውም ሙጫ፣ የትኛውም ፈገግታ፣ የትኛውም ማቀፍ ወደ ነበረችበት ጠገና አይመልሳትም:: የተደፋ ውሃ ራሱ ተመልሶ ይዘገናል? ስሌት አበላሽቼአለሁ? ወይስ ስሌቴን አበላሽተዋል? በሕልሜ እንኳን ታሳድዱኛላችሁ::

በነበረችኝ አንዲት ልብ እስከሚበቃኝ ወድጄባታለሁ......

እንደዕድ ዛፍ ቅርንጫፎች ጭንቅላቴ በነፋስ የሚነቃነቅ ይመስለኛል......እዚህ ብቻዬን እንዛለሁ:: የለመድኩትን መንገድ እንደ እንግዳ ሰው እረግጣለሁ:: ልጅነቴን አልጨረስኩ ይሆን? ያልገባኝ ነገር አለ? ይሔ ሁሌም መንገዴ ነው:: የመንገዴን ርዝመት በልቦናዬ፣ የጠጠሮችንም ብዛት አውቃለሁ:: እግሬ ግን እንደ እንግዳ ይረግጣል......

ጨለማው አቅፎ ያባብለኛል:: ወደምጠላው ተሸሽጌያለሁ:: እምጠላው ውስጥም እሸሸጋለሁ:: በቆሸሸ የትዝታዬ ድሪቶ ይህቺ ትንሽ ዕድሜዬን ተጠቅልዬአለሁ:: እንደተጠረገ የሸረሪት ድር ተጣብቄ ከነበርኩባቸው ጥጉቼ ተፈልቅቄ ወጥቼአለሁ:: እግሮቼ ጥላሸት ተቀብተዋል:: ምሁርነቴ በቀዳዳዎቼ እንደላብ ይወጣል:: ከጥርሶቼ የማይማርክ ሳቅ ይፈልቃል:: ፊቴ እንደ ቆሻሻ ምንጭ ደፍርሶአል:: የመነሻ ዕዳቴን ተጠራጥሬአለሁ......

ከዋክብቶች ዐይን አላቸው? ካላቸው ዕንባ ያወጣሉ:: እኔን ሲያዩኝ ያለቅሱታል:: ጠብታዎችን ነፋስ ወደ ውቅያኖስ ይወስዳቸዋል:: ማንም አያያቸውም......

ይህቺ ምንድናት? የሞተች ድመት? ሶስተኛ ቀንዋ? አራተኛ ቀንዋ? ቂጫጮች እንኳን ትተዋት አልሄዱ ይሆናል:: ዝንጉዎች ፀጉሯ ውስጥ ይርገፈገፋሉ:: አንዱም ይተኛል፣ አንዱም ያገጠጠ ጥርሷን ይልሳል፣ አንዱም......

የኤሌክትሪክ ሽቦዎች ላይ አሻንጉሊት ፖራሹቶች ይወዛወዛሉ:: እኔን ሲያዩ ያኩበኩባሉ:: እንደ ቆለጥ ባንጠለጠሉት ድንጋዮቻቸው



@BOOKALEM

ወደ እኔ ይንሳፈፋሉም:: በመንገዱ መብራት እሳትራቶች በክንፋቸው ይንተባተባሉ:: እኔን አያዩኝም:: ካዩኝ ክንፋቸውን ሰለው እንደ ግልገል አንሳ፣ እንደ ሞልፊት ይወርዱብኛል......

የአቶ አታላይ ሉካንዳ ቤት እንዴት ያበራል? ሆዶች ይጋብዛል:: ከባድ ካፖርት የደረቡ ሰው የጭን ሥጋ ያስመዝናሉ......

ሣንቲም እንደገባበት የእንጨት ባንክ ጡቴ ይጮሃል:: ማህፀኔ ቅርፊት ኾኖአል:: እንደገሞራ የሚያቃጥሉ ወንዶች አድርቀውታል:: ጨለማ ውስጥ በጥቁረቱ የደመቀው ተራራ በብብቱ እንደ ሽንት የሚፈስ እንደ ሽንት የሚጭረቀረት ቀዝቃዛ ወንዝ ደብቆአል......

እነዚያ ከጨለማው የበለጠ ጠቁረው እያወሩ የሚመጡት ሰዎች እነማን ናቸው?

ከጨለማ ወደ ጨለማ እሔዳለሁ......

ከጠቆረ የእናቴ ማሕፀን ወደ ጠቆረ ዓለም:: ለእኔ መዓልት የለም:: ረዥም የጨለማ ቱቦ ነው:: ዓይኖቼ ከበቀሉባቸው ኪሶቻቸው ወጥተዋል:: በድስቶቹም እፈጣለሁ......

እነዚህ ሰዎች ማን ናቸው?

*(ሶስት ሰዎች ቀረቧትና አንዱ አፍዋን ያዛት፣ ሁለተኛው ፀጉሯን ወደ ኋላ ጐተታት:: ሶስተኛው ረዥም የሚያብለጨልጭ ቢላ ዓይኖቿ ፊት ለፊት አወጣባት:: ወደ አንድ ከጨለማዎች የጨለመ ጥግ እየሳቡ ወሰድዋት:: አንዱ እንዲህም አላት: "አንዲት ጩኸት የለችም......እሱ የያዘውን ቢላ ታያለሽ?"፤ ጥርሱን ነክሶ ድምፁን ዝቅ አድርጐ በማስፈራራት:: መሬት ላይ ከጣሏት በኋላ ቢላኛው ቀሚሷን ገልቦ ፊቷን አለበሰው)*

እነዚህ ሰዎች ማን ናቸው?

አንደኛው ቢላ፣ ሁለተኛው አፈን፣ ሶስተኛው እኔ ላይ......እልበሜ ቦርሳዬ ውስጥ ይደንሳል......ቦርሳዬ መሬቱ ላይ ስልት ይዞ ይፈራገጣል.....ይወዱኛል? ወይስ ሱስ ነው?

በፊት ጨለማ የሆነ ግን ብርሃንማ የመሰለኝ አንድ ጊዜ ነበር:: ያኔ ሁለት ሰዎች ወድጄ ነበር---ባሌና ወዳጄ:: ሁለቱም ሰዎች ጠሉኝ:: ሁለት ሰዎች መውደድ መጥፎ ነው? መውደድን በአንድ ሰው መወሰን ይቻላል? ልቤ ወደ ሁለቱም ይበር ነበር:: ዛሬ ክንፎቼን አጥፎ መንገድ ዳር ወድቆአል:: አለት ኾኖአል:: እንደ አሁኑ ያሉ አላፊና አግዳሚዎች ያነሱታል:: ወዳጄ የሚጠላ አልነበረም:: ባሌም የሚጠላ አልነበረም:: ባሌ ወዳጄን አልወደደውም:: ወዳጄ ባሌን አልወደደውም......



@BOOKALEM

እነዚህ ሰዎች ማን ናቸው?

ወዳጄን እንዳልተወው እወደዋለሁ:: ባሌንም እንዳልተወው እወደዋለሁ:: የደስ ደስ ያለኝ ኾኜ መወለዴ ከፋ? የወንድ ዐይን ውስጥ ቀድሞ መግባት እኔ የፈጠርኩት ክፋት ኾነ? ሠላም እጣሁ:: መምረጥ ነበረብኝ:: ከሳንባሽ ወይም ከልብሽ:: ከአንድ በላይ መውደድ ሕገ-ወጥ ነበር:: ሕግም አሳዶኝ ወደ ወዳጄ ሄድኩ::

እሱም ተወኝ::

«ምነው 'ከአንቺ ጋር አብሮ መኖር በሕይወቴ የምመኘው ዋና ነገር ነው' አላልከኝም ነበር?» ብለው

«ሥጋሽ እንዳይርቀኝ የወደድኩሽ መስሎሽ እንድትቀርቢኝ ነው» አለኝ:: አውጥቶ ይህቺን አቅጭ እንኳን አላለኝም---ስሜቱ ወደዚህ የሚሔድ ነገር አወራኝ......

ወደ ባሌ ሔድኩ:: ሳቀብኝ......

"አንቺን ወንድ በተመለከተ ቀጥር ነፍሴን ቅናት ይበላት ነበር:: ሌላ ሚስት አገባሁ" ብሎኝ አዲስ ሚስቱን ሰፋ ላይ እንደተደረደረች አሳየኝ:: ጥዬ ወጣሁ---ወደ ራሴ ድንኳን:: ሳያፈቅሩኝ ይተኙኝ ነበርን? አልኩ......

በሥጋዬ፣ በጉድጓዴ የተመዘዝኩ ነኝ አልኩ......

እኔ ሳልወድ አልችልበትም:: ሳልወድ መሥራት ይከብደኛል:: እንዴት ሳልወድ እንግዳ ምንተፍረት ወደ ገላዬ እጋብዛለሁ? አሁን እየተጠራጠሩ ይተኙኝ የነበሩትን ባልና ወዳጄን ሳስብ---አዳም ከሥጋ ብቻ ነው የተሠራው እንዴ? እላለሁ:: ሔዋንስ ቴራ ብቻ ነበረችን? እላለሁ......በሳቅ፣ በጫወታ፣ በወዳጄነሽ፣ በባለቤቴ ነሽ ከለለው ደፈሩኝ:: የምኞቴን አልኖሩኝም:: እንሰሳዬ እንሰሳቸው፣ ብርድልብሴ ብርድልብሳቸው አልነበረም:: በሁለት እግር እልጋ ላይ ነበር የተኛሁት:: በአንድ ጡታቸው ነበር ያቀፉኝ:: በአንድ ዐይናቸው ነበር የሚያዩኝ:: የሚያታልል ሳቅ፣ የሚያታልል ፍቅር ቢላ ነው......

እነዚህስ? በቢላ ተከልለው ሱሪያቸውን ይፈታሉ፣ ዚፖቻቸውን ይተረትራሉ:: እቆሙበት በጥጋብ ያቃስታሉ:: ቆላ አቋርጠ እንደመጣ በቲ ያለከልካሉ......ስጋዬን እንደ ባስኮ ዳጋማ ይፈትሹታል......እኔ ግን ባዶ ነኝ:: ማሕጸኔ ውስጥ ፍቅር፣ የሚሞቅ ሥርቻ የለም......መልካም የሥጋ አግዳሚ ወንበሮች ተደርድረውበታል:: ማንም ዕንግዳ መጥቶ ያርፋል:: የሚያስተናግደው ግን የለም......

አልበሜ ውስጥ የሁለቱም ፍቅረኞቼ ፎቶግራፎች አሉ:: ባሌ እኔንም ልጄንም አቅፎ:: እናቴን 'እወድሻለሁ' ያልኳት እውነት ይሆን? ልጄን አባቱ ስብኩት ነው መሰለኝ በመንገድ ስንተላለፍ ይገላምጠኛል:: ወይስ አባቱን ፈርቶ በአካል እየሸሸኝ በልቡ እየወደደኝ

ነው? አልበሜ ውስጥ ባሌ ልጄንም እኔንም አቅፎአል:: ወዳጄ እኔን አቅፎአል:: ብዙ ፎቶ ግራፎች:: ግን ራሴንስ ተሸክሜ እሄድ የለ? ቀልድ፣ ፌዝ፣ ቧልት መሃል ብቅ የምል የቢንጐ ዕጣ ነኝ:: ዘፈኔ ራሴ ውስጥ ሞቶአል......

አ!! አ!! እንዴት ያማል! ጡቶቼን ገንጥለው ሊወስዷቸው ነው? የቤት ልጅ ባንዲራ---የምርኩኛ......

ሁለተኛው እኔ ላይ፣ ሶስተኛው ቢላ፣ አንደኛው አፌን

እነዚህ ሰዎች ማን ናቸው?

የአቮካዶ እግሮች የቤቴን በር ይደበድባሉ:: ቤቴ ውስጥ ገብተው ትፋታቸውን ጥለው ይወጣሉ:: ብርድ ልብሴን ቀድጄ እፀዳዳለሁ:: አሠሪዬ ፀጉሬን ይጐትታል:: ለነገ ጤፍ እንጀራዬ ሥጋዬን አሰቦካለሁ፣ የቤቴን በር እከፍታለሁ:: ሁሉ ሴት እንዲሁ ነው? እንዲህስ እንደ እኔ ጠልቶታል?

ቦርሳዬ አሸዋ ላይ ይዘባል:: በሚቀረቀረኝ ጀርባዬ እንደ ሰዓሊው እንደ ማቲሲ ልጃገረዶች ተኝቼአለሁ:: ደረቅ ሣር ይወጋኛል:: ጀርባዬን እንዴት አመመኝ?

ለምን ትተውኝ አይሔዱም:: መቀመጫዬ አቧራ ላይ የማይነበቡ ፊደላት ይፅፋል:: መጨረሻው አንድ ነው:: ወደ መጨረሻው የሚወስዱት መንገዶች ሕልቁ ናቸው:: መጨረሻው አንድ ከኾነ ልዩነቱ ምንድነው? በፊት ተቃልያለሁ:: አሁን አልቃለልም:: ጥላቻን ከነአከታዋ እቅፋታለሁ:: እግሮቼ አየር ላይ ፊደላት ይጽፋሉ:: ሆሄያቱን ነፋስ፣ አየር ይወስዳቸዋል:: ማንም ዕጣዬን አያነብም:: ለአጭር ጉዞ ረጅም መንገድ እሔዳለሁ:: ቱቦ ውስጥ እርመሃለሁ:: በወዲያኛው በኩል ጆሮ የለም:: ጉሮሮዬ አቅም አጥሮት ያልበዋል......

ተረት:--ምን ብታፈገፍጊ ከግድግዳ አታልፊ? ተስፋ ለማይሰጥ ዘፈን ዳንኪራ እመታለሁ......

ማን ናቸው?

የማውቃቸው ይመስለኛል......

ቀሚሴ ከአይኖቼ ላይ ተንሸራቶ ወረደ:: ዓይኖቼን አልገለጥኩም......

ጭንቅላቴ ውስጥ መጨረሻ የሌለው የወንዶች መስመር አያለሁ:: ሰማይ ላይ የቆመችው ጨረቃ ኩርማን ትሆን ይሆናል---ሠይጣን ገምጠላት የሔደ:: እኔ እንደ ጨረቃ ነበርኩ......

የተበላሸ ሥጋዬን አበላሹ......

አልበሜ ቦርሳዬ ውስጥ ተኝቶአል:: አልበሜ ውስጥ ፎቶግራፎች አሉ:: ይሔን ሁሉ ስሆን አልበሜ ውስጥ ያለው የባሌ ምስል ይስቃል---አዲስ ነገር እንዳየ:: አልበሜ ውስጥ ፍቅረኛዬ ሲስም በሚነክስበት



@BOOKALEM

ጥርሶቼ ይስቃል፣ በጣቶቼ አንገቴን ይጎጉጣል:: እኔም እስቃለሁ:: እዚሁ ያሉት ሶስቱም ሰዎች ይስቃሉ......በጆርባዬ እዚህ ያለሁበት እቆያለሁ::

(ሶስቱ ሰዎች እየተንሾካሾኩ ሔዱ......

"እኔ የምትጮሀ መሰሉኝ ነበር"

"እኔም"

"ፈልጋለቾ"

"ፈልጋለቾ"

እዚህ በጆርባዬ ተኝቼ አዝናለሁ:: በተገለበ ቀሚስ ወደ ጉያዬ ንፋስ ይዘምታል:: ሶስቱ ጥላዎች እየሮጡ ሔዱ:: 'ቀስ በሉ' ልላቸው ፈለግሁ:: በአካባቢዬ ያለው ነፍስ ሁሉ የሞተ መሰለኝ:: እኔም ወደ መቃብሬ ለመጨረሻ ጊዜ የምዘምት---ጭኔ ላይ የተጣበቁት አሸዋዎች ትሎች መሰሉኝ......

ወደታች ልቁጠር?

......10፣ 9፣ 8፣ 7፣ 6፣ 5፣ 4፣ 3፣ 2፣ 1፣ 0::

ማታ አራት ሰአት::

---- // ----

ግንቦት 1979 ዓም

አዲስ አበባ

# የድንች መዋስዕት

**እንደ መግቢያ:**

*ከድንቾች ቅዱስ መጽሐፍ ከትንቢተ መዋስዕት የተወሰደ ጥቅስ*
*ምዕራፍ 26*

*10. "እንዴት ያምርብናል?*
*በሚሞቅ ለስላሳ አፈር ውስጥ ተኝቶ የሰው ልጆችን*
*መጠበቅ!*
*12. ከፈጠረን አምላክ ትዕዛዝ አለመውጣት ምንኛ ውብ ነው!*
*ከመጀመሪያው የከቱዎችን ጎዳና ዘግቶልናል::*
*13. በጠዋት ከሰማይ የወፎች መዝሙር ወደ ጆሮአችን*
*በምሽትም ጓጉንቸሮች ሲሞቁን*
*በምድር ውስጥ ይጠጉናል::*
*14. ሁላችንም በተጠንቀቅ ቅዱስ ሞትን*
*ተጣጥበን*
*ድምፃችንን ከፍ አድርገን*
*በመዘመር*
*እንጠብቃታለን::*
*15. ዓለም በዚህ ዕድላችን ይቅና*
*ለስጋት የተፈጠሩ ያልቅሱ*
*16. እኛ በአምላካችን ፈቃድ*
*ስጋታችንን ጨርሰናል::*
*ለሚጋውን እንጠብቃለን*
*ይጣፍጠናልም*



@BOOKALEM

* * *

የነሐሴው ወር አረም ከመሃላቸው ተነቅሎ ጉሮሮአቸው ስለፀዳ መዘመር ይችላሉ……በጠዋት ቀላል ካፊያ ምላሶቻቸውና ዕንጥሎቻቸው ከደረቀ አፈር ትለቃልቀዋል……ስለዚህ እንደደንባቸው ማዜም ጀመሩ በሕብረት……

"ጉሮሮአችን የፀዳው ትናንት ነበር
ብዙዎቻችን እንወፍራለን
እናም ብዙዎቻችን ደስ ይለናል
ቀጫጮቹ ይነቀላሉ
ደካሞች ግን ይወረወራሉ
ምስኪኖች ግን ይታረማሉ
ሞታቸው አይጣፍጥም
ፈልገው አላደረጉትም
ጥፋ ሞት የላቸውም"

እንደ ብዙ ክረምት ጠዋቶች ፀሐይ አልወጣችም፣ ቀላል ነፋስ የሚገፋው ብን የሚል ዝናብ መንደሯን ሸፍኖአታል:: ከየጎጆዎች ጎር ላይ ቡላና ነጭ ጢስ ይንፎለፎላል:: አንዳንድ ገበሬዎች መስከ ላይ ጉንበስ ቀና ሲሉ ይታያሉ---አረም ጉልጎላ ያቆረፈዳቸው እጆቻቸው ስር፣ የበረዳቸው ባዶ እግሮቻቸው ሥር ሕብረዜማ እንደ ጥጥ ይነደፋል……

*ከፊሉ ድንች (1)"አንዳንድ ዘመዶቻችንን ወሰዱአቸው*
*ምን ሊያደርጓቸው እንደሆነ ሳይነግሩአቸው"*
*ከፊሉ ድንች (2) "ምናልባት ሊበሏቸው"*
*ከፊሉ ድንች (1) "ሊሞቱ?"*
*ከፊሉ ድንች (3) "አዎ"*
*ከፊሉ ድንች (1) "ታድለው"*
*ሕብረ ዜማ(1) "አንዳንድ ዘመዶቻችንን ወሰዱአቸው፣*
*ሊበሏቸው……ክኛ ይልቅ ታድለው"*
*ሌላ ሕብረ ዜማ(2) "ታድለው……ታድለው"*

ከብዙዎቹ ድንቾች አንዱ ብቻ ገና በቅጡ ያልበሰለ፣ ከፊል ጉኑ አረንጓዴ የኾነ፣ በትንንሽ የአፈር ኳሶች ላይ እየተንኳለለ የሚመጣው ውሃ ውስጥ ዓይኖቹን ሳያርገበግብ በዘፈኑም ሳይሳተፍ እንደተደበረ ሁሉ ተጎልቶአል……ሌሎች እየዘመሩና በየመሃሉ ዝማሬአቸውን ቆም እያደረጉ በግልምጫ ያዩታል……መልስ አይሰጥም……አይናገር፣ አይጋገር:: ሌሎች ድንቾች ሃሳባቸውን ተከትሎ የሚያደርጉትን አላደርግ ስላላቸው እየረበሹ ትዕግስት ሊያስጨርሱት ጆሮው አጠገብ መጥተው ይጮኹበታል:: ግን አይነቃነቅም:: አፉን ለመልስ

አይከፍትም......ግልምጫቸውና ጩኸታቸው፣ ግሬአቸውና ተራ ስድባቸው አልቀሰቅሰው ቢል ዜማ ድርዳሬአቸውን ቀጠሉ......

*ሕብረዜማ(1) "የማይዘምሩትን ምን ብላችሁ ትጠሯቸዋላችሁ?"*
*ሕብረ ዜማ(2) - "አውሬ"*

ለሁለት ሳምንቶች ያህል ሳያቋርጡ ሲዘምሩ ቆዩ......በሳምንቶቹ መጨረሻ ላይ ገበሬዎች እዚህም እዚያም ድንች መሰብሰቢያ የሚጠራ ዕቃዎችና ዶማዎች ይዘው ወደ ጓሮዎቻቸው ገቡ......

*ሕብረ ዜማ(1):"የዘሩን እየመጡ ናቸው*
*በዶማና በእጆቻቸው*
*ተልእኮአችንን ሊቸሩን"*
*ሕብረ ዜማ(2):ይሔን በዳንኪራ፣*
*ይሔን በከበሮ፣*
*ይሔንን በክራር፣*
*ይሔንን በሞሸንት፣*
*በዕልልታና በሳቅ ካልተቀባበልነው፣*
*ዓላማችን ሁሉ እንደተረሳ ነው::*
*ሕብረ ዜማ(1):ይሔን ደስታ በመለከት፣ በእሽታ የማይቀበል፣*
*ወደ ፈራት ሞት እንዲደርስ፣*
*አሁኑኑ ይሰቀል......"*

አተኩረው በጠንጋራ አይኖቻቸው አዩት:: ገልመጥ ብሎ ያለፍርሃት አያቸው......ያኔውኑ ከላያቸው ያለው መሬት መናድ ጀመረ......ሁሉ ድንች በዶማ ተቆፍሮ ከአፈር ውስጥ ለመውጣት ሽሚያ ጀመረ......ገበሬዎች ከመሬቱ ላይ የበቀሉትን ቅጠሎች እየበጣጠሱ በጭቃ የተለወሱ ድንቾች ከመሬት ውስጥ እየፎገሉ፣ እየማሱ፣ እየቆፈሩ ወደ ሳጠራቸው ውስጥ ይወረውራሉ፣ ያጠራቅማሉ......የተሰበሰቡትም ድንቾች በሕብረት ዜማ......

*"ተሰብስበናል ዛሬ ወደ ዓላማችን ለማለፍ*
*በሞት ሠረገላ ለመክነፍ*
*ከነቢያችን ቅዱስ ቃል*
*ኪዳን ገብተናል*
*እንዝሎዎን አድርገነው*
*ገና የምናልመው ሞታችን ተሞናል"*

በሕብረ ዜማ (ከመሬት ገና ተቆፍረው ካልወጡት ድንቾች):

*"ምነው ዶማው ቀረብን*
*ምነው ጊዜው ሸሸን*
*ምነው ሳተናው ሞት ራቀን"*



@BOOKALEM

አንድ ገበሬ የፈለገውን ያህል ቆፍሮ ከወሰደ በኋላ የለቀማቸውን ድንቾች ሲያገላብጥ ለዐይን እንኳን ደስ የማይል ኮስማና አረንጓዴነቱ ገና ያልለቀቀው ጨቅላ አገኘና ስህተቱን በማረም ከቅርጫቱ አውጥቶ መሬት ላይ ወረወረው::

ከቅርጫቱ ሕብረ ዜማ:

"ትጠልያ የገኘነው አውቆ ነው፣
ከሞት ሲሸሽ ነው::
ለዘር ዘራችን ስድብ ነው፣
የሚጣፍጥ ምትን የሚሸሽው::
ይሄ የአሸባሪ ዘር አሸባሪ፣
የቀልባጣ ዘር ቀልባጣ፣
ነገር ያልገባው ለሚመስለው፣
ወደ ማድ ቤት አስገብተህ በቢላ በበይፍ ስትመትረው
'ግብህ ይዘገያል እንጂ ይሄው አደርሰንሃል' በለው"

አረንጓዴው ድንች እንደተወረወረ ውሐ የቋጠረ ጉድጓዳ መሬት ውስጥ እየተቻከለ ተንከባሎ ገባ......የድንቾቹ ተቺ ድምፅ ቢሰማውም ራቀው......ደስታ እንደሰረፀበት ሁሉ ዐይኑን እንደጨፈነ ለራሱ ትንሽ ሳቅ አለ::

አንዳንድ ገበሬዎች እርሻውን እየለቀቁ መውጣት ጀምረዋል:: ከቦዩ ግራና ቀኝ ከስሩም ድንቾች እየተገፉ ቀሉ ለመውጣትና እንዳሉት 'ለመሞት' ይሻማሉ:: ዶማ ወደተሰማበት፣ የገበሬ ኮቴ ወደተደመጠበት አካባቢ ጫጫታው ይሞቃል::

......ከጥቂት ጊዜ በኋላ በቀላሉ ይወርድ የነበረው ካፊያ ትንሽ በረታ፣ አረንጉዋዴው ድንች ስምጦ መለቀሚያውን ይጠብቅበት የነበረው የጥቁር መሬት ጭቃ ናፈቀው---የሚዘንበው ዝናብ በልዩ መልክ እንዳከረሰሰው ሁሉ እየተንዘፈዘፈ አጠገቡ ወደነበረ የአቋሪ ውሃ ተንሸራቶ ገባ:: ከሥሩ የሚያዳልጥ ለስላሳ የበካ መሬት አጋጠመው ......የደፈረሰው ውሐ ባልጠበቀው መልክ ለምላሱ ጣፈጠው (ለራሱ 'ይሄ መረሬ ነው' አለ):: ደቃቅ አፈሩ ቆዳውን እንደወዳጅ ኮረኮረው......ልቡ በደስታ ዘለለ፣ ጤዛ የመሰሉ የውሐ ጠብታዎች ከዐይኖቹ ተንጠባጠቡ......መዘመር አማረው...... ዘመረ......

"ለመጥፋት ከኾነ ለምን መጣሁ?
ከመሞት ትሰዛዛቸው አምልጬ
ነፍሴን እወስዳለሁ::
እስካረጅ ራሴን ጠብቄ
ሰማይና ምድርን አይቼ እልፋለሁ::
ለድጓቸው አልታዘዝም::
ለምኞታቸው አልቀቀልም::"

ድምፁ እምብዛም ከፍ ስላላለ፣ ከመሬት ውስጥ ወላልቀው በየቦታው የወደቁ ወይም ቅርጫት ውስጥ የገቡት ድንቾች አልሰሙትም......ትንሽ ከተረጋጋ በኋላ እዚህ አካባቢ መኸን የማያዋጣ፣ ሞትን ሊጠራ የሚችል ቦታ ስለመሰለው ከነበረበት ጎድጓዳ ቦታ ለአመል ብቻ ብቅ ብሎ ዓይኖቹን ገልጦ ዙሪያውን አየ......ግራና ቀኝ አድማስ ጉም ውስጥ የሚጠፋ ቀጭን የረጠበ የእግር መንገድ አየ--መሬት ላይ የወደቀ የተወጠረ ትልቅ ቆሻሻ ገመድ የመሰለ......

በጀርባዋ ሰቃ ያዘለች አንዲት መሃከለኛ ዕድሜ ያላት ሴት እያዘገመች እሱ አሾክኮ ወደሚሰለልበት ትመጣለች:: የቀኝ እግሯን አውራ ጣት በጨርቅ ተጠቅላለች (እንቅፋት ያንግላት ወይ ባሏ ይርገጣት አይታወቅም):: የጨርቋ ቆብ ላይ የደም ጠብታ ይታያል:: ድንቹ ጋ ልትደርስ ስትል አውራ ጣቷ የታሰረበት ፋሻ ስለተፈታ ቅርጫቷን ወደ ጎን አስቀምጣ ስትንበረከክ ድንቹን አየችው.....ከወደቀበት አነሳችውና `ይሔ መደብ ይሞላልኛል` ብላ ዘንቢሏ ውስጥ ጣለችው......ድንቹ ገና ዘንቢሏ ውስጥ ሳያርፍ አየር ላይ እያለ ቀድሞ ትቷቸው የመጡት ድንቾች በሁካታ ተቀበሉት......በጫጫታ፣ በትርምስ......በሕብረ ዜማ:

*"ቅር ብሎት ወንድማችን*
*አለመሞቱ አሳዝኖት*
*ብቸኝነቱ አስከፍቶት*
*ወደ ዘመዶቹ የኸው መጣት"*

መልስ የሚሰጥበት ጊዜ ሳይሰጡት እየተቀባበሉ ወደ ዘንቢሉ ሥር አስገቡት......ገላቸው በውሃ ታጥቦ ስለፀዳ ይረጥባሉ፣ ይበርዳሉ......

ሕብረ ዜማ:

*"ቆሽሸአል ብለው እንዳይጥሉት*
*ጭቃውን ከላዩ ላይ ተሉ ብላችሁ እጠቡት"*

እስከ ዘንቢሉ ቂጥ ድረስ እየተቀባበሉ ያወርዱትና እንደገና ወደ ላይ ያወጡታል:: ጭቃው ከመልቀቅ ይልቅ በሁላቸውም ላይ እየተሠራጨ ቀባባቸውና ድርጊታቸው ቀስ በቀስ ራሳቸውን እንደጎዳቸው ስላዩ ወደ ጥግ ገፋ አደረጉት *(መፅሐፈ ቁልቁሉ ምዕራፍ አስራ ሰባት ላይ ይሄን ይላል: `የባሪያዎቹ የመጀመሪያ ምልክት የቆዳ ንፅሕና ነው`)*--ወደ ዳርቻ አገለሉት--ጨለማ ወደበዛበት የሸምበቆ አድማስ......

ሴትዮዋ ቅርጫቷን እንዳዘለች ምንም አዲስ ነገር እንዳላጋጠማት ሁሉ ወደ ገበያ ጉዞዋን ቀጠለች:: ከጀርባዋ ላይ የሚደረገው የድንቾች ትርምስና ጫጫታ አይሰማትም:: ሁለት ሶስቴ እንደ መተከዝና እንደ



@BOOKALEM

ማስብ ብላ ለራስዋ `ለምንድነው አንዳንዱ ድንቹ እንደ ደረቅ ቅጠል የሚንሻሻው?` ትላለች:: ገበያ ስትደርስ ቅርጫትዋን ከጀርባዋ አውርዳ ድንቾቹን መንገድ ዳር አገሩ በለመደው የነጋዴ ስልት ደረደረቻቸው፡ በስሙኒ በስሙኒ መደብ:: የሚያማምሩትን ዐይን የሚስቡትንም ከላይ እንዲታይ ደርድራ ከመንገድ የለቀመችውን ብቸኛ አረንጓዴ ድንች ግን ጭቃውን በጨርቅ አፀዳድታ ከሌሎች ሥር እንደ መደበቅ አድርጋ አስቀመጠችው......(`መወሸቅ` የሚለው ቃል ሳይሻል አይቀርም)

የአርፋጃው ፀሐይ እንደ ደከመች ሁሉ ውልብ እያለች ትጠፋለች......የበዮች ጉልበት አልደከመም......ከድንቾቹ መደብ ፊት ለፊት ሰዎች ያልፋሉ ባለጫማ እግር፣ ባዶ እግር፣ የሚሸት እግር፣ የሴት እግር፣ የወንድ እግር......ድንቹ በአንድ ጎኑ ከዘመዶቹ ስር ተሰንቅሮ ሁሉን ያያል: የኸነ ሰው /የኸነች ሴት/ ያጉነብስና/ታጎነብስና የመደቡን ዋጋ ይጠይቃል......እግር ያልፋል፣ ጫማ ያልፋል......

"በጣም ከበዳችሁኝ" አላቸው አረንጓዴው ድንች ከላዩ ወደ ተጫኑት መሰሉቹ እንጋጠ......

"ዝጋ እቦ......ታዲያ መስዋዕትነት በድሪያ ይገኛል?"

"በጣም ነው......በጣም ነው የከበዳችሁኝ"

ከመሃል አንድ ድንች ከልጅነቱ ጀምሮ የተማረውን ዜማ አነሳ:

*"መቼ ያለምጥ ልጅን*
*መቼ ሳያርሱ እሸቱን"*

ሌሎች:

*"መቼ ሳይሞቱ ቃሉን"*

"ለመሆኑ መሞት ለምን ይጠቅመናል?" አለ በድፍረት:: ይሄ አይነት ጥያቄ መጠየቅ ከባህል ውጭ ነው:: ለምን ድንች ሆንኩ አይባልም:: ራስን መጥላት ነው:: ግልምጫቸውን ለማየት ያለበት አቀማመጥ ባይፈቅድለትም የሚነዝር ዜማቸው ግን ታች ድረስ ወርዶ በሁለመናው ይሰርጋል:

*"የሚመጣው ትውልድ እንዲከተለን"*

እሱ:

*"በመሞት?"*

እነሱ:

*"መቼ ያለምጥ ልጅን*
*መቼ ሳያርሱ እሸቱን*
*መቼ ሳይሞቱ ቃሉን"*

ከመደቡ ጫፍ ላይ ተጎልቶ ፀሐይ የሚሞቅ ከድንቾች ሁሉ አሪፍ የተባለው አንዱ በወፍራም ድምፅ ጠየቀው......



@BOOKALEM

"ቃሉን ብታፈርስ ምን ይጠቅምሀል! ኖረህስ?"

"መኖር ጥሩ ይመስለኛል"

"ለምን?"

"አሊታየማ"

"እኛን ቃል ኪዳኑ ይመራናል.....ሞት በራሱ ይጣፍጣል......መስዋዕትነት በራሱ ያስቀናል:: ምን እንደምትል አይገባህም"

"መሞት አልፈልግም"

"ለምን መጣህ?"

"ሴትዮዋ ከመንገድ ለቀመችኝ"

ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ሰፈነ::

ከዚያ በዜማ:

*"ያጥፋልን ከሀዲውን*
*ሞት ያልማፈጠውን".*

ይሔን አስቀያሚ ነገር እየሰማ አብሮአቸው መቆየት አስጠላው......ለትንሽ ጊዜ ራሱን ሲያነቃንቅ ቆየ......ብዙ ሳይቆይ ያልጠበቀው ነገር ኾነ:: መደቡ ተናደ:: እራሱን ከክምሩ አላቆ በፍጥነት እየተንከባለለ ፊት ለፊቱ ያገኘው ቦይ ውስጥ ገባ:: ነጋዴዋ ከተቀመጠችበት ተነስታ እጅዋን ሰዳ ልትይዘው ስትል ከራስዋ ጋር `ይሄ ገና ያልበሰለ ምን ያደርግልኛል` ብላ ተከራከራ ተወችው:: ቦዩ ውስጥ እንደገባ መካከለኛ ጉልበት (ብዙ ቦዮች ጉልበታቸው ድንች ለማንከባለል አይችልም) ያለው ጎርፍ ከድንጋይና ከቆሻሻ ጋር እያላተመ ይዞት ወረደ:: ለጥቂት ደቂቃዎች እንደ ተንከባለለ እንጨት ቢጤ ቆልፎት ይዞት ሲቆም ከዘመዶቹ ዝማሬ ሰማ......

*"ከፃሳማ ቢስ ከባንዳ*
*ከከሃዲ ከይሁዳ*
*ከጥርጣቡሌ ደፊ......"*

ድንቹ እየተንከባለለ ወረደ: እዚህ ሲቆም፣ እዚያ ሲቆም---በውሃው እየታጠበ---ከጣር እየታከከ---ቡናማ ቀለም ያለው አረሩ እየተነፈሰና እያፈነዳ---እዚህ እየተደገፈ እዚህ እየተያዘ---እዚያ እየተለቀቀ---ቁልቁለቱን---ትንንሽ ፏፏቴዎችን እመር እያለ---በአንቀራራት አፍንጫ ሥር--በጉደፉ የአረሩ ኩይሳዎች ስር---ደግሞ ከሌላ መሰል ቦይ ጋር ተቀላቅሎ---በሰፋ ውሐ ላይ---በልስላሴው ውስጥ እየዋኘ---የሕፃናት የወረቀት ጀልባ ዐይኑ ላይ እንዳያንፀባርቅበት ተከልሎ---እወዲህ ከአለት ታኮ---ወዲያ በደለል ላይ እየተንሸራተተ---በደቀቀ አሸዋ ላይ

እየተንከባለለ---ዳርና ዳሩ የሰፋ ሜዳ ቦታ ላይ ከመድረሱ ያደረገው ጉዞ ትልቅ ደስታ ሰጥቶት---ለብቻው አንጎራጎረ......

*ከዚህች መንገድ ተሳስቼ*
*ይሄኔ ነበር ሞቼ*
*ምን ሊገኝ ከሞቱ*
*እንዲያው በከንቱ*

ድንቹን ተሸክሞት ይጓዝ የነበረው ውሐ ጨፌያማ ቦታ ሲደርስ ተዘርግፎ ቆመ......ከሩቅ የሞላ ሐይቅ ይታያል......ድንቹ እዚያ ሐይቅ ሳይደርስ ችግችግ ያሉ ቀጤማዎች መሃል እስከ እናቱ በደለል አፈር በከፊል ተጋርዶ እዚያ አረንጓዴ ስፋት ላይ፣ እዚያ ነፋሻ ቀዬ ላይ እዛ እዛ በሁሉ እዛ የሚያማምሩ ወፎች ባሉበት እዛጋ ጭቃ ውስጥ ተሰንቅሮ ቀረ......

ነሐሴ አለፈ......ራሱን እንደሳተ ሁሉ ተኛ......በደን ሽታ ታጥኖ በቄጤማ ዳንቴል ተሸፍኖ ከጠዋት እስከ ማታ እየሞቀው......

አንድ ቀን ቀድሞ ተሰምቶት የማያውቅ ስሜት ሆድቃው ውስጥ-ጠቅ፣ ጠቅ እያደረገ ወጋጋው......ግራ ተጋብቶ ቀኑን እንቅልፍ ሳይወስደው ዋለ......ሌሊትም ዕንቅልፍ በዐይኑ ሳይዞር......ሲነጋ ግን ደክሞት አሸለበ......ጠቅ፣ ጠቅ የሚያደርገው ውጋት በቀስታ፣ በጣም በቀስታ እየተለወጠ እንደሚጣፍጥ ቁንጠጣ ይሰማው ጀመር......ከውስጥ እያበጠ ቆዳውን የሚያነዝር ነገር እውስጡ እንዳለ ተሰማው......

አንድ ጠዋት ከእንቅልፉ ድንገት ባነነ:: አንድ ነጣ ያለ ፀጉር ነገር እንደመተኮስ ብሎ ከስጋው ውስጥ መጥቆርና መጨማደድ የጀመረ ቆዳውን በጥሶ የወጣ መሰለው......በአንድ ዐይኑ ዝቅ ብሎ አየ---ንፁህ ነጭ ቀጫጫ ሥር የመሬት አፈር ለመያዝ ትዳብሳለች:: ሳያውቀው የኾነ ያልለመደው ጥልቅ ሃላፊነት ተሰማው፣ ያቺን እንደ እውር እጅ የምትቀዝፈውን ሳር አፈር ማስያዝ እንዳለበት......አድርጎት አያውቅም......ግን ድርጊቱን ትክክል መሆኑን ማን ነገረው? ተመቻችቶ ተቀመጠ:: ገላው በሙሉ በዚህ ዓይነት ስሜት ተሞላ፡ ቆዳው ይቀደዳል ሥር ይወጣል፣ ቆዳው ይበሳል......በትሎች የተወረረ መሰለው.....ትርጉሙን መግለፅ አቃተው.....ሞትን ባያውቀውም ጨክኖ የመጣበት መሰለው:: እንደገናም ከተለያየ አቅጣጫ የሚዘነትሩት ነገሮች የኾነ ሊገልፀው የሚከብድ ደስታ ሰጡት:: አወጣጣቸው በስስት ያያል......ሞት የመጣበት ቢመስለውም......እውስጥ ያለው ስጋው ልስላሴው......ሲበጣጠስ......ሲጎራረድ......መረቁ ሲመጠጥ ይሰማዋል:: ሰመመን ተጫነው:: ከእናቱ በኩል አፍጦ እያየ አረንጓዴ ቅጠል በድሶ ወጣ......



@BOOKALEM

ወዲያ ቦታ ከዚህ ጨፌ ጉያ ብዙም ሳይርቅ......እዚያ መንደር......እንዲት ትልቅ ቢላ በግራ እጅዋ የያዘች ወፍራም ሴት ትልቅ የታጠበ ድንች መክተፊያ ላይ አስቀምጣ በአንድ ውንጨፉ ለሁለት ቆረጠችው:: ጩኸት ወጣ::

መቆም ያቃተው እዬዬ......እዬዬ ዬ......ዬ......ዬ......ዬ......

ይሄኛው ድንች ከውስጡ ፈንድቶ የወጣውን አረንጓዴ ዕንቡጥ አንጋጦ ከበስተላይ ባለው ገና ስር ባልበቀለበት ዐይኑ ያያል......የተቆራረጠ......ገና እንኩርኩር እያለ ጀምሮ የሚጠባው አመልማሎ ደመና ሰማያዊ አንሶላ ላይ የፈሰሰ ወተት መስሎ......የእንግጫውን አረንጓዴ ጣቶች ነፋስ ያማስላቸዋል፣ እንደው የሠከሩ ይመስላሉ:: ይሄን ከፊል የሚያምር ሰማይ ጥቁርና ነጭ ፀጉር የለበሰ የሚያነፈንፍ እንስሳ ጋረደው:: እንደ ጥቁር ፀሐይ ግራና ቀኝ ያጨረረ:: ትንፋሹ......

ያስባል: `ትንፋሹ እንዴት ይሞቃል? እንዴት ይመቻል?'

ከእንስሳው አፍ የሚወጣው ወላፈን ያጉጠጉጡ ዐይኖቹን እንደማሳወር ያህል ተነፈሱበት:: አጥበረበረው::

`ስለ ምንድነው ታዲያ የሰላም ከኾነ፣ እሾህ ለብሶ እሾህ ተከናንቦ ጥርሶቹን በምላሱ የሚያጥበው?'

የተከፈተው አፍ እንደ ቀይ ጥላሞት ድንቹ ላይ ወደቀ:: ስለታም ጥርሶች ግማሽ ገላውን ጠርበው ወሰዱት::

ገና ባልተበላ ጆሮው የሌላ ወገኑን ጩኸት ባሕሩ ዳር ካለ ሠፈር እየተንከለከለ ሲመጣ አዳመጠው:: ጎረቤቱ ሳይሆንም አይቀር ምድር ውስጥ ለነበረ ጊዜ......`ወይስ የራሴው ጩኸት ነው?'

እንደገና ትኩሳት የሚተነፍስ የሚፋጅ ለሐጭ የሚያዝረበርብ፣ በጉምዥት የሚያለከልክ ጥርሳም አፍ ተከፍቶ ከበቀለበት አፈር ላይ ቦጭቆ ሲጎርሰው ዓለም ሁሉ እንዲሰማው ዓይነት ጮኸ......

ጃርቱ እሾሁን እያንኳኳ ረግረጉን አቋርጦ ኼደ:: ሆዱ ውስጥ ሳያቋርጥ በሚጮኸው የድንች ፀባይ ተገርሞ::

የሚጮህ ድንች በልቶ አያውቅም::

---- // ----

ሰኔ 1978

አዲስ አበባ



@BOOKALEM

# ጭጉላ፡ ወደፊት ወደኋላ

ሳሎኑ በሚያምር መልክ ተሰናድቶአል......የሚያብለጨልጩ ባለቀለም የወረቀት ገመዶች በየኮርኒሱ ላይ ተጠላልፈዋል......ከየኮርኒሱ ተንጠል ጥለዋል......የሚያንፀባርቁ የተለያዩ ቀለም ያላቸው የፕላስቲክ ጥብጣቦች ቀስተ ደመና ይመስል አራቱም ግድግዳዎች ላይ ተዘርግተዋል:: ሙሽሮችና ሁነኞች የሚቀመጡበት ጠረጴዛ በደብዛዛ ቢጫ ጨርቅ ተሸፍኖአል......ወደ አራት የሚደርሱ መልክ ያላቸው ጠርሙሶች ጽጌረዳ፣ ማርጋሬታ አበቦችና ሰንበሌጥ ተሞልቶባቸው ጠረጴዛውን መሃል ለመሃል በሚያቋርጥ የማይታይ መስመር ላይ ተደርድረዋል...... ሙሽራውንና አጀቡን ለማስተናገድ የሚጠብቁ የመመገቢያ ሳህኖች በአቧራ ከመቆሸሽ እንዲያመልጡ ፊታቸው ተደፍቷል......ንፁሕ ቂጦቻቸው ይፈልቃሉ......ወገባቸው ዙሪያ አበባ የተሳለባቸው ብርጭቆዎች ነጫጭ ወረቀቶች ጎርሰው ይጠብቃሉ......

ከላይ እስከ ታች ነጭ ለብሳለች: ነጭ ቀሚስ፣ ነጭ ጫማ፣ የዝሆን ጥርስ አምባር፣ የብር ሀብል፣ የብር ሎቲ፣ ቀይ ፊቷ መሃል አፍዋ ይከፈትና ከመስታወት ላይ እንደሚነጥር ብርሃን ነጭ ሳቅዋ ይፍለቀለቃል......

የሠርግ ዘፈን ከአንድ ስቲርዮ ፕሌየር በቀስታ እንደ ላስቲክ ኳስ እየነጠረ ይወጣል......ረገዳዋም እግሮችዋን በቀስታ እያነቃነቀች ሙዚቃውን የምታዳምጥ ብትመስልም በሃሳብ ሌላ አለም ውስጥ እንደገባች ከገፅዋ ስሜት የለሽ ልሙጥነት ይነበባል......



@BOOKALEM

ሁኔታዋን የተመለከተችው አንዷት ባልንጀራዋ የሠርግ ዕለት ምን እንደሚያስተክዛት ገርሞአት......

"ሰማሽ መሰበወርቅ....ምን ሆንሽ?" አለቻት

"እ......ምንም" ወደ ውስጥ የሳበችውን የጭንቀት አየር ሳታወጣ በደረቷ ነክሳ ይዛ......

"ተይው በቃ"

"ሰማሽ የሚጠጣ አምጭልኝ"

"እንዴ መሰብ ምን መሆንሽ ነው......ሰው እንዲህ ጊዜ አጥሮት ሲራወጥ አንቺ ተኳኩለሽ ቁጭ ብለሽ የሚጠጣ ምናምን አምጪ ትይኛለሽ?"

"እባክሽ አሞኝ ነው"

"እውነትም ትመስያለሽ"

«አይ በቃ እቴ አሳመጣም አይሻልም»...... ከተቀመጠችበት ተነስታ የሴት ድምፅ የሚንቻቹባቸውን ክፍሎች ትታ ሰው የሌለበት አንዱ ውስጥ ገባች......ተጠጥቶም ይሁን ተደፍቶ የጐደለ ብራንዲ ጠርሙስ አገኘችና በብርጭቆ ቀድታ ጠርሙሱ አጠገብ ወንበር ስባ ቁጭ አለች......የሠርጉ ዘፈን አሁንም ጆሮዋን አልሳተም......

*"ሙሽራዬ ሆ! ሙሽራዬ ሆ! የወይን አበባዬ"*
*"ሙሽራማ ሆ! ሙሽራማ ሆ! የእኔ ውብ አይናማ"*

በራሷ አለም ውስጥ ሊያፍናት አቅም ያነሰውን አንዴ የተጐነጨችለትን ብራንዲ ገላምጣ ተነስታ ያለችበትን ክፍል በር ዘጋች......አከታትላ የጨለጠችው አልኮል ቁልቁል እንደሚገፋ ቆልማማ አስፒል እየጧጠጣት ወረደ......ሆዷ ውስጥ ቋያ ተቃጠለ......

የስካር ሕልም ቀስ በቀስ ጭንቅላቷን በጣቶቹ ይዳስሳት ጀመር......አሽኮርማሚ ደስታ እየተሰማት ዐይኖችዋን በቀስታ ጨፈነች......በስከረ የሐሳብ ጋሪ ወደ ኋላ መፍለስ ጀመረች......አንድ አመት......ሁለት አመት......ሶስት አመት......

* * *

......አጉቷን ለማስደሰት የኮርሶችዋን ፈተናዎች ማለፍ ነበረባት......ልፋት ያልተቋጠረበት ምኞት ደግሞ የትም አይደርስ....አስተማሪዋ በጣም ኮስተር ያለ ገጽ ነበረው......ጠባብ አፉ ችፍርግ በመሰለች ክብ ጺም የተከለለች......ቅንድቡ መሃል ያሉት ሁለት ሽጦች ከቆዳውና ከግንባሩ አጥንት ተፈልፍለው የተሰሩ የሚመስሉ......በጉሩ ከመሃል አናቱ የሚጀምር......

እሷ 20 አመቷ ነበር......



@BOOKALEM

የወደፊት ሕይወቷን በቀላሉ ለመግዛት የአንቷን ፈገግታ ለማትረፍ ትኩስ ስጋዋን ሰጠችው......ለአስተማሪዋ ስለ አለም ብዙ የማታውቀው መሶብ ከሰማይ የወረደች ስጦታው ነበረች......እንደገሠሳት ባየ ጊዜ ተድላ አንቆት......የተዝለፈለፈ በላብ የተዘፈቀ ሰውነቷ ላይ ተኝቶ......በደስታ ልቅሶ ተንፈቀፈቀ......

እንዲያ ሲሆን በተስለመለሙ አይኖቿ ሴትነትን 'ኖር' ስትል አለም ሁሉ ያያት፣ አለም ሁሉ ያወቀ መሰላት: የኮሌጁ ዲን፣ ጓደኞቿ ፣ አጉቷ ያወቁ መሰላት......የወሲብ ሕመም ግን ይጣፍጣል......ሁለተኛ ቀን፣ ሶስተኛ ቀን---አረገዘች......

ይሔ ሌዋታን አለም ሰፊ አፉን ከፍቶ የመንጋጋ ቁልፉን በላይዋ ላይ «ቀጭ» ያደረገባት መሰላት---ድምፁ፣ ጓጓታው---ጭንቅላቷ ውስጥ አሁንም እንደ በረዶ ይዘንባል......

---እናም ተጋቡ......ታዲያ የት ይደረሳል......አንድ ሽል---ምናልባት እንደ አባቱ የተመለጠ በደም ጋንዋ ይዛ?

"እንዴት እሱን ታገቢዋለሽ?" አላት አጉቷ አንድ ቀን......

"እወደዋለሁ"

"ግን ምን አገናኛችሁ?"

መልስ አልሰጠችውም......እንዳወቀባት ሁሉ ሰው ሰራሽ ጥርሱን በክብሪት እንጨት እየፋቀ ለረዥምም ጊዜ ትኩር ብሎ አያት...... በጩኸት ፈንድታ ፊቱን ብትበጫጭረው ደስ ይላት ነበር......ሳይነጋገሩ ከሁኔታዋ፣ የግል ሚስጥሯን መደበቅ ካልቻለ የልጅነት ፊቷ ተነስቶ ልብዋን ማንበብ ቻለ......

ከዚያ ወለደች......

በእርግጥ አስተማሪዋ ይወዳታል......ማንም 'ባል ሚስቱን እንደሱ መውደድ አይችልም' ብሎ መወራረድ ይችላል......የፈለገችውን ያደርግላታል፣ የሚለበስ ይገዛላታል፣ ሽርሽር ይወስዳታል፣ ጥራት ባለው አልሚ ምግብ ቀን ከሌት ይንከባከባታል.....ቢሆንም ስህተቷ በየቀኑ ጭንቅላቷ ውስጥ የቋጭት ገመድ ይፈትላል......በየቀኑም ይከራል......

ልብ ሳለ፣ ሳወቃት፣ ውበቷን ከቀድሞዋ መሶበወርቅ ጋር ሳወዳደረ ከሚያበራው የቀይ ዳማ ቅላትዋ ስር ፈልፍለው እንዲያዩት የሚጠብቅ የፈራ ግራጫነት አለ......ለጥቂት ማርኮች ብላ የሰጠችው ሰውነቷን ልጅ ከወለደች በኋላ ነፈገችው......

*መጀመሪያ ምሽት:*

"እንዳትነካኝ"

"መሶበወርቅዬ ምነው?"

"እንዳትነካኝ ብዬሃለሁ"

"እንዴ? ተይው በቃ"

"እንዳትቀርበኝ!!"

*ሁለተኛ ቀን ከምሳ በኋላ:*

"ሰውዬ አበድክ?......እንዳትነካኝ"

"ምን ማለትሽ ነው?"

"እኔ ወንድ አልፈልግም"

"ምን ሆንሽ?"

"ምንም......የመኛል:: ልቀቀኝ"

አይኖቿ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚንፀባረቅ ጥላቻና ንቀት አነበበ......አፈራትም ፈራትም......ላብ ግንባሩ መስመሮች ውስጥ ጎምዛዛ ወለላ ሾኖ ይፈልቃል......

"ምን አደረግሁሽ?" አለ በሰለለ ድምፅ ጨምድዶ የያዛቸውን ቀጫጭን እጆቿን እየለቀቀ---ከተከፈተ አፉ ትንፋሹ በፍርሃት እንፃ እያወጣ......

"ምንም አላደረግሽኝ......ደ`ሞ ምን አደረግሽኝ?......ብቻ ተወኝ"

"ካልነገርሽኝ አልለቅሽም" መልሶ ያዛት......

"ል-ቀ-ቀ-ቀ-ኝ!!" እጅዋን ከእጁ መንጭቃ ሙኸች......

በድንጋጤ አፉን ከፍቶ ቆመ......

የእሱ ስሜት መሰበሩን የእሷም ልብ ተቀዳ የተስፋ መቁረጥ ቀዝቃዛ አየር......ልትመልሰው በማትችል ጥድፊያ እያስገባች መሆኑን ስታውቅ---`እንዲህ ነው` ብላ ልትነግረው እንደሚያቅታት ስታውቅ......ግራ በመጋባት እሱም አፉን እንደ ጅል ከፍቶ ከቆመበት ፊሆ ሲያያት አለመጣጣማቸው አሳዝኖአት ከሶፋው ወደ ወለሉ ምንጣፍ (ለመሶበወርቅ እግሮች ተብሎ የተገዛው) ወርዳ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች......እዛው በተቀመጠችበት ማናወዝ ስትጀምር ተሸክሞ ወስዶ በስርአቱ አስተኛት......

*ከወር በኋላ:*

ዝኒ ከማሁ......

*ከወር በኋላ፣ የወሩ የመጀመሪያው ቀን:*

ስሜቷን የሚጉዳ ስለመሰለው አልጠየቃትም......

*ከሁለት ወር በኋላ፣ የወሩ አስረኛው ቀን:*

አውጥ መስላ የጨለማ እቅፍ ለመግባት ወደ ምዕራብ አድማስ በመውደቅ ላይ ያለችውን ፀሐይ እበረንዳዋ ሸራ ወንበር ላይ ተቀምጣ



@BOOKALEM

ትመለከታለች......የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር የለበሰችውን የጀርሲ ሹራብ አልፎ ጭንዋ ቆዳ ላይ ይሰማታል......የምትጠጣው ውስኪ ልዩ ጣእም አለው......እጆቿን እየለዋወጠች የምትደገፈው ፊቷ ይሞቃል......ራስዋን በመስታወት ለማየት ጓጉታ ወደ ቤት ውስጥ ገባች......በዚህ የምቾት ወጥመድ ውስጥ ተንሰራፍታ ስትጋደምም ሆነ.....በለስላሳ ድንጋይ ወለሉቹ ላይ ቂጧን እየሰበቀች ስትራመድ ከብዙ ወንዶች የተገለለውን መልከ መልካምነቷን ማየት ትፈልጋለች::

ግድግዳውን ሊሞላ ትንሽ የቀረው መስተዋት ተሰቅሎአል......አልፎ አልፎ መስመሮች ክፍሏ ውስጥ እሻራዎች በተመሰጣጠረ አቅጣጫ በጉልህ የሚታዩ የጣት ለማሳየት የሚበቃትን ያህል መስታወት ታትመውባቸዋል......መልኳን ወረቀት ከጠረገች በኋላ ወደውስጡ ማፍጠጥ ጀመረች......በሽንት ቤት መገልገያ

ጉንጮቿ ፍም እንደተቀቡ (ቀለም ቢሆን) አይነት ሆነዋል፤ ከንፈሮቿም እንደተሳሙ አብጠው ቀልተዋል......አይኖቿ እንባ አቁረው የሚስ ለመለሙ ይመስላሉ......አንገቷን ወደ አንድ ጎን አዘንብላ የደረቷን ቆዳና ተበታትኖ የወረደ የፀጉሯን ልስላሴ አይታ ሳቅ አለች ......ሹሪዋን አውርዳ ከፊት ለፊት ሸሚዟዋን ወደ ላይ ለአመል ሰብሰባ ነጣ ያለ ቅላት ያላቸው ጭኖችዋን ውስጥ ሱሪዋ መዳረሻ ድረስ እየች......ማንኛውንም ወንድ ማለም ጀመረች......

የባልዋን ኮቴ ከውጭ የሰማች መሰላት......ፍርሃት ፍርሃት አላት......ማን እንደኾነ ለማረጋገጥ የመኝታ ቤቷን በር በትንሹ ከፍታ ተጣራች......እጆቿን አልቦአቸዋል......ጥያቄዋ ውስጥ ፍርሃት ነበር......

"ማን ነው?!"

የሚገባው ሰው ኮቴ እያደፈጠ የሚመጣ መሰላት......ምናልባት ባኋ በማድባት ሊይዛት......

"ማነሽ ስንቅነሽ!"......ሠራተኛዋ እንደሊለች ታውቃለች......

በድንገት ከሳሉን መግቢያ በር ላይ አንድ ሰው ገና በአይን ከመታየቱ:

"እኔ ነኝ" አለ......

ሌላ ወንድ እንደኾነ ስታውቅ በፍርሃት ካደባችበት ክፍል ወጣች......

ወደ ላይ ከተጠቀለለው የጂንስ ሸሚዝ እጀታው ትላልቅ ደምስሮች እንደ አውራ ጎዳና የተጋደሙበት ምሰሶ የሚያክል ክንድ ከነወፍራም ጣቶቹ ተጉልጉሎ ወጥቷል......ከተጋለጠው ደረቱ ላይ እስከ አንገቱ መለያያ የሚነጭ ያህል ፀጉር አድጉአል......ቆዳው እስኪታይ ድረስ የጭንቅላት ፀጉሩ ተስተካክሏል......

ጉረቤቷ ነው......ሕልሟም ነው......

ጀርባውን ለእሷ ሰጥቶ በረንዳ ላይ ቆሞአል......ያረጀ አዳፋ ልብስ ለብሶአል......አንድ እጁ ላይ ያለችው ትንሽ ጣቱ በጎዝ ታስራለች......

"ጤና ይስጥልኝ" አለችው......በውስኪ የሚሞቀው ሰውነቷ ከእሷ አምልጦ የሚበር መስሎአት የእርምጃዋን ፍጥነት እየቀነሰች......

ቶሎ ወደ እስዋ ዞሮ የሰላምታ እጁን ዘረጋላት......

"ወይዘሮ መሰበወርቅ እባክሽ ቤት ውስጥ መብራት ተበላሽቶብኝ ልሠራ ፈልጌ ስክሩው ድራይቨሬ ስለጠፋብኝ እንዳላችሁ እንድታውሺኝ ነበር"—ሳቅ እያለ......

"እ......እም......ቁጭ በል......ልፈልግልህ እስኪ......እሱ እቃውን የት እንደሚያስቀምጥም አይታወቅ"

እስዋ ከነበረችበት ፊት ለፊት ወንበር ስቦ ተቀመጠ......

"ለምን ትንሽ አትጠጣም?"

"አአ......ኤሌክትሪክ ነው የምሠራው......እጄን ከሽቦ ጋር ልታያይዥኝ ነው መሰል" አለና ሳቅ አለ

"ለምን ይይዝሃል......ግድ የለም......አንድ ብቻ......እኔ መጣሁ" ወደ ሩጫ በሚጠጋ ፍጥነት ወደ ሌላ ክፍል ገባች......

ውስጥ ብዙ አልቆየችም......የባሏን ቁምሳጥን ከፍታ ለተበላሸ መኪና መጠገኛ የሚጠቀምባቸውን ብዙ ስክሩው ድራይቨሮች እንደተደረደሩ ከነቦርሳው ይዛለት መጣች......

"የትኛውን እንደምትፈልግ አላወቅሁም......አንተ ራስህ ምረጥና ውሰድ" አለችው......የቀዳችለት ውስኪ እንዳይደፋ አድርጋ እፊት ለፊቱ የሣጠራ ጠረጴዛው ላይ እያስቀመጠች......

"ፐ!! በጣም ጉበዝ ነው ባለቤትሽ"

"አንድ ጨምር" የሄጉን ጠርሙስ ድጋሚ ልትቀዳለት እያነሳች......ሥራ የፈታ እጁን አንስቶ አገዳት......

ቅር ተሰኘች......አነስተኛ መፍቻ አነሳና መለያ ቁጥሩን አንብቦ እንድታስታውስ ለማድረግ ቁጥሩን ሲነግራት ትክ ብሎ አያት...... የቀረችውን መለኪያ ውስጥ የምትዋልለውን የውስኪ እንጥፍጣፊ ጨለጠና ትንሽ ሳል ስሎ አፉን ጠርጉ ተነሳ......ከእስዋ ራቅ ብሎ ሰላምታ ምስጋና ለማቅረብ ቆም ሲል ከሌላው አለም ጋርዶ እቤቷ ውስጥ ያፈናት መሰላት...........

መለኪያዋን በእጅዋ እያሸች በተስለመለሙ አይኖቿ አተኩራ እያየችው መልስ ሳትሰጠው ቀረች......ተቀምጦበት የነበረበትን የቃጫ መቀመጫ አየች......ከጉደጉደበት አልተመለሰም......እሱን እንደሚያይ




@BOOKALEM

ሁሉ ባዶ አየር ውስጥ አተኩራ ቆየችና ጠጥታለት ትንሽ የቀራትን መለኪያ ፊት ለፊትዋ ወደ ላይ አነሳች......መለኪያውን የገጨላት ሰው አልነበረም......ሆድ ብሶአት ሲፈነዳ የሚቃጣ ልቅሶዋን አምቃ መኝታ ክፍልዋ ገባች......

ከአንድ ሰአት በኋላ ስትመለስ ለሰውዬው ያዋሰችው መፍቻ ቦርሳው ላይ ተቀምጣለች:: አናደዳት::

"ከረፈፍ ወንድ" ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ......

በተለያዩ ቀኖች የተጠናከሩ የመፈለግ ምልክቶች ብታሳየውም ቦታ አልሰጣትም......የራስዋን ውበት ተጠራጠረች......በየቀኑ በየሰአቱ መልኳ ዝናብ ውስጥ እንደቆየ ሳሙና......እየሞቀሞቀ በመሟሸሽ ላይ ያለ መሰላት......ጠዋት ጠዋት ሰአቶች ያህል ለመኳኳል ጊዜዋን ታጠፋለች......ድሮ ችላ የምትላቸውን ልብሶች፣ መጊያጊያጫ የቤት እቃዎች የመታጠቢያ ቤትዋ ከመዲና ሞልቶ የላስቲክና የጠርሙስ ፉፎቴ እስኪመስል ደረደረች......ባልዋ ዋልጌነት እንዳመጣች ቆጥሮት በተለያየ ጊዜ ከሕሊናው እየተሟገተ ቢከታተላትም ምንም ስህተት አላገኘም......

ሥራዋ ትገባለች፣ ወደ ሥራዋ፣ ወደ ቤትዋ......አብራው እያለች እንኳን ወንድ ቀና ብላ አታይም......

በምሁርነቱ ወደመተንተኑ ስለሚያደላ የኾነ ግምት ወስዶ ነበር---አንዳንድ ሴቶች ልጅነታቸውን ሳይጨርሱ ቀድመው የሚያረጁ ይኖራሉ......ምናልባትም ከእሱ ጋር አብራ መተኛት የተወችው ከእሱም ያረጀች መስሎአት ሊሆን ይችላል---እርጅናን እየፈራች ይሆናል......ለዚህ መላ ምት ማረጋገጫ ተጨባጭ ነገር ግን አላገኘም......

በልቦናዋ፣ በምኞቷ የወደደችው ወጣት እሙኛ እንዳለው ሰምታለች......ወሬው ላይታመን ይችላል......መንደር ይታመናል? ለሰው ማማከር አትችልም......የቅርብ የስፈር ጓደኛ እንኳን የላትም......ጓደኛ ምን ይሠራል? ከዚህ አስተማሪ (ሌክቸረር) ጓደኞቿ አይደሉም እንዴ፡ "አንድ ቀን ተቸገረለት" ያልዋት......ጓደኝነት ሽፋን ኾና ካላሰበችው ካልጠበቀችው የተቋለፈችው......ገላዋ የራስዋ ነው---ስለዚህ የራስዋ ጉዳይ ነው......ወይ ባልዋን መፍታት.....ዝም ብሎ ይፈታል? ዝም ብሎስ ወንድ ዘረፋ ይወጣል? ከሀደት እምነቷም አይደለ......በሽርሙጥና ከመጠርጠር የበለጠ ለእሷ አስቀያሚ ነገር ተሰርቶ አያውቅም......እንግዳም ነገር ነው ለእሷ......አሁን ባለችበት ትብትብ ሁኔታ ውስጥ የምትችለው ማለም ነው......

ከወር በፊት:



@BOOKALEM

ባልዋ አንድ ቀን ማታ መላጣውን እየዳበሰ እያሻሸ ፊት ለፊትዋ ተቀምጦ......

"መሰበወርቅ ይሔ ጉረቤታችን መላኩ የዛሬ አስራ አምስት ቀን ሠርግ አለብኝ ብሎአል" አላት::

"መኪና ነው የሚፈልገው? አታጅበውም?"

"ቆይ አልጨረስኩልሽም"

ግልፍተኛነትዋን ሊለምደው አልቻለም......

በቅርብ የደም ግንኙነት ምልጥና የለበትም......የራሱ የግሉ ባሻ ይመስለዋል......በልጅነት ኮስታራነቱ፣ በጉርምስና ዘመን ስቀቀኑ የተባጠጠ ስለሚመስለው ብዙ ነገሮችን ችላ ማለት ከጀመረ ቆይቷል ......ብስጩነቷ ቢያሳዝነውም---መልሶ አያበሳጨውም......

"እም ሰሐን ብርጭቆ---ሙሽሮች ብቻ የሚጠቀሙበት እቃ ይፈልጋል......ሠራተኛዋን እንድታፀዳዳ ንገሪያት"

"እሀ......"

ተነስታ ሔደች......እሱ ዞር ብሎም ሳያያት ጭኑ ላይ ያስቀመጠውን መጽሔት ለማንበብ አነሳ::

......መጥፎ ነው---በራሷ እቃ፣ እራሷ ባጠበቻቸው እቃዎች ላይ ያቺ...... ሰው ንቃ አታውቅም......

ፊቷ ላይ ያሉት ድሮ ያላየቻቸው ጎድጓዳዎች፣ የአይኖቿ ነጭ ላይ የሚፈሱ ቀያይ መስመሮች---የአስቀያሚነት ምልክቶች መሰሏት...... ሜካኘዋን ለሶስተኛ ጊዜ ለመስራት መስተዋቷ ፊት ለፊት ቁጭ አለች ......ከጨረሰች በኋላ---መኝታዋ ላይ በጀርባዋ ተጋድማ ሕልምዋን ጀመረች......

## ሕልም 1

ጠንካራ ላባ ገና እንዳልለወጠች ባለ ለስላሳ ላበ ጫጩት አይንዋን እያስለመለመች......እቅፉ ውስጥ ስትገባ፣ ሰንበሌጥ ወገብዋን ጨምቆ አቅፎ ፊቱን ደረቷ ላይ ሲያስተኛ ታላቅ ክንዱ ከቀሚስዋ ስር እንደ ዘንዶ አርፎ ያን ጊዜ......

እጮኛው በር ከፍታ ትገባና:

"እንዴ? ይኸቺን ይወዳል!!" ስትል

"ዝም በይ......ውጪ!" ይላታል፤ እጮኛው ደንግጣ ፊቷን ስታዞር ከንፈሮቿን በእጆቹ ይዳብስና--- ዋኔ መሰብ---መሰብ" ይላታል......

ከዚያ---ባልዋ ዶ/ር አስግድ የልጁን እጮኛ ተከትሎአት ይገባል......



@BOOKALEM

"ዝም በል……ውጣ……አንተስ ባጋጣሚ ያገባኸኝ ነህ" ትለዋለች……

"ሞሰብ ለአንቺ ያለኝ ፍቅር እንዲህ……"

"ይሔ ሽማግሌ አይገባውም?"

ወደ ምናብዋ ቀና ትልና፡

"ለምን አንተኛም?" ትለዋለች……

ሕልም 2

ማታ እሱን ፍለጋ ወደ ቤቱ ስትሔድ……በውስጥ ልብስ የቆመች እንደ ዝንጅብል ጠመዝማዛ ቅርጽ ያላት ሚስቱ በእርካታ ስታናውዝ ሁለት ወዳጆች እንዲግባቡ ባበጁት ምልክት……ምልክቱ በጠጠር ቆርቆሮ መምታት ነው……ሶስት ጊዜ አምስት ሴኮንድ ያህል እያራራቁ መምታት……አንድ ቀን ማታ ጠጠሮች ቆርቆር ላይ ትወረውራለች ……አትክልት ስፍራው አበቦች መሃል ተደብቃ ትጠብቅዋለች……በእሱ ምትክ ሚስቱ ትሰማና……ወደ ተሸሸገችበት ትመጣለች……

"አንቺ! ልጅ መኾንሽ ነው?……አትጠፊም! ሳትዋረጂ……"

ምናልባት! ወይም---እንትልፍ ወስዶአት ሚስቱን ሆና ታልማለች……ከነአሳበው የተላጨ አናቱ (አናቱን ለምን ሁልጊዜ ያልበዋል?) እሷም እግዜር እንደሰራት አረቋን፣ እንደ ባልና ሚስት ተቆላልፈው ……

* * *

እየተከታተሉ አለችበት ክፍል ውስጥ ሰዎች ይገቡና ደረቷን ቀጥ አድርጋ ስስ ረዥም ቀሚሷን ለብሳ ብርጭቆዋን ወደ ደረትዋ አስጠግታ ፊት ለፊት አፍጣ ሲያይዋት፣ እነሱም በፊናቸው ለጥቂት ጊዜ አተኩረውባት የሚፈልጉትን እቃ በእጆቻቸው ይይዙና ጥፋት እንዳዩ ሁሉ ደግመው ያተኩሩባትና ከንፈሮቻቸውን አሳውሰው (በእርግማን ይሁን በምርቃት እነሱም አያውቁ) ይወጣሉ……እየተከታተሉ ይወጣሉ፣ እየተከታተሉ ይገባሉ፣ ይወጣሉ፣ ይገባሉ::

ሌላ ሰው ቤት ውስጥ ያለች፤ በስካር እየዞረባት እንዳለ፡ በአማሃይ ከተመደበላት በላይ እየጠጣች መኾንዋ ቢገባትም ግድ አልሰጣትም……ልጅነቷን በእጣ የተዘረፈች መኾንዋ የሚገባው የለም……ወይም ባልተረዳችው የሕይወት ረቂቅነት……አቀማመጧ--- ትምህክታዊ አቀማመጧ እሳት እንደተለኮሰ የቀላው ከንፈሯ……እንደ ኑርፍ በደረቷና በጀርባዋ የሚወርደው ጥቁር ፀጉሯ፣ ማር የመሰለ የፊቷ ቀለም፣ በእንባ የተሸፈኑ የሚስለመለሙ ዐይኖቿ



@BOOKALEM

......የምትጠጣው `ዘመናዊ ልሁን ብላ ነው` ሊያሰኝ ይችላል---ማይም ለኾነ ምላስና ዕድሜ---

......እንደ ሕልም ይሰማታል ሠርገኛ ከሄደበት ተመልሶ ሲዘፈን......

የአጠጣጥ ፍጥነቷን እንደቀድሞው መቀጠል አልቻለችም: እጅዋ ላልቶ መጠጡ ከነብርጭቆው ከእጅዋ ሲወድቅ ይታያታል---ሲሰበር ግን ድምፁ አልተሰማትም......

ሠርገኛ እየገባ ነው......

እንደ እንትልፍ ነገር ተጫጫናት......

......ስትባንን በአካባቢዋ ፀጥታ በመጠኑ ሰፍኖአል......እግሯ ሥር ወድቆ የነበረው ስብርባሪ ተነስቶአል......

"ሰክሬ አይተውኛል......ብርጭቆውን ስጥለው?" አለች ለራስዋ ትንሽ በሚኮላተፍ ድምፅ......ጉኗ ወዳለው ጠረጴዛ ላይ አየች......በወረቀት የተጠቀለሉ ሁለት የውስኪ ጠርሙሶች ግድግዳ ተደግፈው ቆመዋል......አንዱን ወሰደችና እላዩ ላይ የተፃፈውን አነበበች......

"ለብሩክ ከዶ/ር አሰግድ" ይላል......

ሳቅ አለች......ባሏ እዚህ ክፍል ገብቶ ቢያስቀምጥና የኾነችውን አይቶአት ቢሆን ደስ ይላት ነበር......ጠርሙሱን ከፍታ ያለ ብርጭቆ እተቀመጠችበት እንድ እምስት ጉንጭ ዋጠችና......መልሳ ከድና እንደነበረ በወረቀት ጠቀለለችው......

"ያቺ ጉራዳ ከዚህ ስትጠጣ ምናለ ቢያንቃት" ለራስዋ ተናገረች ትንሽ በሚኮላተፍ ድምፅ......

ለመሔድ ከተቀመጠችበት ስትነሳ መቆም አልቻለችም......የወንበሩን መደገፊያ ተመርኩዛ ሰአት አየች......አራት ሰአት......ድንገት በሩ ተከፈተና ያገር ባህል ቀሚስ ያለ ነጠላ የለበሱ ሴት ገቡ......የሠርግ ዘፈን እየተኾሩጉደጉደ ተከተላቸው......የቴፑም የሰውም......

*"ሙሽራዬ! ሆ! ሙሽራዬ! ሆ!*
*የወይን አበባዬ"*

ራቅ ብሎ ከድንኳን ውስጥ የሚመጣው የዲስኮ ዜማ ውልብ ብሎ ገባ......ሴትዮዋ አቋቋሟን አይተው ወደ ተጠቀለሉት ውስኪዎች አይናቸውን ወርወር አደረጉና እንዳልተከፈቱ አጢነው ጤንነቷን ተማምነው:



@BOOKALEM

"ተቀሳቅሰሽ አትጫወቺም......ሙሽሮች ሚጉላ ቤት ገብተዋል---እስኪ እናያለን" አሉና በራሳቸው አባባል በሳቅ ሊያጨበጭቡ ሞከሩ......

መሰበወርቅ ዝም አለች......

የተሰማቸውን እፍረት ሊያባብሉ: "ለምን የኾነ ነገር አትጠጪም ልጄ?" አልዋት ቀድሞ አይተውት ወደ ነበረው ውስኪ ተገላምጠው......

ማፍጠጥ እንጂ መልስ አለመስጠቷን ደግመው ሲያዩ ከበሽታዋ ለመራቅ እንዳሰቡ ሁሉ "መጠጫ ላምጣልሽ" ብለው በሩን ዘግተው ሄዱ---አልተመለሱም......

ግንባሯን ቋጠረች......አሁን እዚህ ቆማ ለባላንጣዋ:

"ሚጉላሽ አብቧል ዛሬ
......እቴ ሽንኩሬ......"

ማለቱን አልወደደችም......እጅዋ ክትክሻዋ ተነቅሎ የሚወድቅ እስኪመስል ተመናጨቀች......

ሚጉላ ቤት መቼ እንደገቡ ለመገመት አልቻለችም......የጊዜ ስሌቷ ውሐ ላይ እንደተደፋ ዘይት ቅርፁን ይለዋውጣል ይረዝምና ያጥራል......ይሠፋና ይጠባል......በሩን ቀስ አድርጋ ከፍታ ፊቷን ብቻ አውጥታ ወደሌላ ክፍል አቅጣጫ አየች......የሙዚቃው ምት አልቀነሰም......ወደ አዲስ ኘላኔት፣ እንግዳ ሕዋ ተወርውራ የገባች መሰላት---ከአንድ ጊዜ ወደ ሌላ ጊዜ......

የቀድሞዋ አሮጊት እያደቡ ጠጋ አልዋትና፤

"ልጄ ረሳሁብሽ---ላምጣልሽ ቆይ" አልዋት---አውቀው የረሱትን ብርጭቆ የውሸታቸውን እያስታወሱ......

ተወርውረው ሊሔዱ ሲሉ ትከሻቸውን ነካ አደረገቻቸውና ጥያቄ ልትጠይቃቸው ሞከረች......ለረዥም ሰአት ያልተናገረችበት አፏ በብሉን የታሰረ ወይ የዛገ መሰላት......እንደ ምንም ፊደላትን እየጐተተች......

"ሚ......ጉላ ቤት ከገቡ ቆዩ?"

"እረ አሁን ቅድም እንደነገርኩሽ"

*"አምስት?---አሥር? አሥራ አምስት ደቂቃ?"* በሐሳቧ::

"ስሙ አትዬ ዶ/ር አሰግድ እዚሀ አካባቢ አሉ?"

"እኚህ እዚህ ቤት ጉን ያሉት---ለሰርግ እቃ ሰጡ የተባሉት ሰውዬ?"

"እፉ!......አሉ?......ስለ ሠርግ እቃ መቼ......"

"ሣሎን ይኖራሉ......እኔ እንጃ"

ወይዘሮይቱ የሚያደንቋቸውን ሰው መሰበወርቅ ስላላደነቀችላቸው ቱጭት እያፈናጠራቸው ወደ ኩሽና በሚያወጣው የቤት ውስጥ መንገድ የሚነጥር ቂጣቸውን እስከትለው ጠፉ......

መሰበወርቅ ወደ ሳሎን ሄደች......በሰው ተሞልቶአል......ጉረምሳው፣ ኮረዳው፣ አዛውንቱ፣ ወይዘሮዎቹ......ቆም ብላ ከሚጫወቱት ሰዎች በአይኗ እየቃኘች ባሏን ፈለገች......እንደሱ ጠና ካሉ ስድስት ከሚደርሱ ሰዎች ጋር አጠር ያለ ጠረጴዛ ከበው ሁለት የውስኪ ጠርሙስ አቁመው ይጨዋወታሉ......አሰግድ መነጽሩን አውልቋል (ሞቅ ሲለው--አይኑ እስከ አውስትራሊያ ድረስ የሚያይ ይመስለዋል) መላጣው ላይ ላቡ ጤዛ ይመስላል......ራሱ እስኪያያት ድረስ መተላለፊያ ላይ ቆመች......

ዶ/ር አሰግድ ሊላ ቀን የሚያሳየው ለዘብ ያለ ቄንጥ የለም......እጆቹ ስለሚሮጥ ባቡር፣ ስለሚቃጠል አውሮፕላን፣ ስለሚፈነዳ ገሞራ እንደሚገልፁ ሁሉ ይወናጨፋሉ፣ ከደረቱ ወደ ሰዎቹ ከሰዎቹ ወደ ሰማይ ወዘተ......

ከትናንሽ ኮረዳዎች ጋር ተቀምጠው የነበሩ ጉረምሶች ያቀፉአቸውን እየረሱ በመሰበወርቅ አስማታዊ ቁመና ፈዘው በአይኗ እገላለጥ ደንዘው:

"የማናት......ማናት?"

ባሏን አብረው የሚያጣጡት ሰዎች ትክሻውን ነካክተው ወደ እሷ ጠቆሙት......ዶ/ር አሰግድና መሰበወርቅ ለሰከንዶች ያህል ተያዩና እንደ ሌሎች ሰዎች ሁኔታዋ ግራ እያጋባው ከተቀመጠበት ተነሳ......አጠገቧ ደርሶ ትክሻዋን እንደያዛት 'የት ጠፋሽ?' ብሎም ሳይጠይቅ:

"ምነው መሰብ?" አላት

"እፈልግሃለሁ"

"ምንድነው የምትፈልጊው?"

"እዚህ አይደለም......እቤት ነው......"

የረሳው......ግን በሞቃት ጭንቅላቱ ወደምንም ሊመድበው ያቃተው መልእክት ንግግሯን ያጀበው ስሜቷ ውስጥ እንደ ንዝረት ይሰማዋል......

ከሰርጉ ቤት ወጡ......

"ቆዩ ጫጉላ ቤት ከገቡ?"

"አላየሁም"

ከማን ጋርና የት እንደነበረች መጠየቅ አልፈለገም……

"እነግርሃለሁ ያልሽኝን ነገር አሁን ልትነግሪኝ አትጀምሪም?"

ውጭው የመስከረም ወር መጨረሻ አስማታዊ ማታ ነው……ሰዎች ፊት ላይ ቅዝቃዜ እንደ ኩርኩራ ይወድቃል……በእንባ ብቻ የሚደነቅ የአዲስአባ የውበት ሽፍጥ…

"እቤት ገብተን ይሻላል……አታቅፈኝም?"……አቀፋት……ትንሽ ተደናግሮት (ስንት ጊዜ ሆነው ከራራ ክንዱ እንዲህ ወገቧ ዙሪያ ያረፈው?) (ስንት ጊዜ ሆናቸው ቀዶ ጠጋኝ ጣቶቹ ነፍስ ያለው ዳሌዋ ላይ አርፈው የነዘራቸው?)……

"የገቡበትን ጊዜ አልነገርኩሽም መሰለኝ……አራት ተኩል አካባቢ ነው……"

"ቶሎ እንሂድ……"

ወገቧን አጥብቆ አቀፈው……በቀሚሱ ውስጥ ሰውነቷ ቆዳው እንደጠበበው እባብ ይወራጫል……በጠገበ የመስከረም ምሽት ውስጥ በሙቀት ቀልጣ እንደምታልቅ ነገር ሰውነቷ በላብ ያሚልጫል……

"ሙሽሮቹ ገና ቁጭ ብለው ይጫወቱ ይሆናል……የተነካች አትመስለኝም" አለችው……

"ይሆናል" አለ……የሰጣት መልስ አውቶማቲክ ነበር……

ቸልታውን አልወደደችውም……እቤት ከገቡ በኋላ ስለተፈለገበት ነገር ለመወያየት ወደ ሳሎን ሲያቀና እጁን ጎተተችው……

"የት ነው?" አለ……

"መኝታ ቤት ነው የምነግርህ" ሠራተኞቸው ትእዛዝ ለመቀበል መሃል ሳሎን ላይ እጇን አጣምራ ቆማ ነበር……

መሰበወርቅ፡ *'ሙሽሮቹ ልብሳቸውን እያወለቁ ይሆናል'* ብላ አሰበች……እንደገቡ የክፍሉን በር ከዘጋች በኋላ በሙሽሮቹ ቤት አቅጣጫ የሚከፈተውን መስኮት ግራና ቀኝ እንደ ግቢ በራፍ ሚገፋ ሁሉ አልፎ አልፎ በረቂቁ ይላወሳል……(ወተት የመሰለው መጋረጃው ግን በሰው ትንፋሽ እንደ በረገደችው……

"ልብስህን አታወልቅም?" አለችው ባሏን……መስኮቱን በቀኝ አይኑ የጎሪጥ አየ……ማንም መስሳል ካልተጠቀመ ወደ ውስጥ ማየት እንደማይችል ቢያውቅም ሁሉ ነገር ውስጥ እቅድ ያለ መሰለው……

"ለምን?" አላት

ተጠጋችውና መነጽሩን ከአይኖቹ ላይ አንስታ በቀስታ አንገቱን አቀፈችው……ትስመው ጀመር……



@BOOKALEM

'ሙሽሮቹ አሁንም እየተሳሳሙ ናቸው......ምክንያቱም ሙሽሮች ስለሆኑ ስለሚዋደዱ......አሁንም አሁንም ይሳሳማሉ' ብላ አሰበች......

አሊጋ ላይ ራቁቷን ወደቀች......ዶክተር ከነረኸም ሙታንታው ተከተላት......

'መሶብ You are the sweetest—you the most beautiful—you are mine[6]' ሺክስፒርኛ ቋንቋውን አላቆመም......

'እንደ ሙሽራው' አለች በህሳብዋ......

ሁሉን ወደደችው.....የጋለ አረቄ ሲጠጋት በአለም ላይ ካሉ ደስተኛ ሴቶች እንድዋ የኾነች መሰላት......እያቀፈች እየሳመችው......

'ፍቅረኞች ይተኛሉ......እሱም ለእሷ---እሷም ለእሱ የጠበቁትን ውድ እቃቸውን ይሸላለማሉ......' ለራሷ በኃሳቧ......

እላይዋ ላይ እንደተኛ፣ ጨዋታ መሆኑ ሳይገባው ጡቶችዋን እያቀያየረ ምራቁን ሲቀባቸው፣ መሳጣው መሀል ጉች ያሉት ጥቂት ፀጉሮቹ እንደየአቅማቸው ሳብ አርሶአቸው ራስ ቅሉ ላይ ተለጥፈው ሲፈልቁ፣ ደስታውን እንደሚነጠቅ ሁሉ በችኮላ ሲንደፋደፍ ስታየው...(ሰው በአገሩ ሰው በወንዙ ቢጠጣ ክህደት ቢበላ ሸፍጥ) አዘነች......በዝምታ እያየችው ጥቂት ከቆየች በኋላ ምሽት የታፈነችበት ቡሽ ወልቃ ከሠርጉ ቤት ዜማ ይሰማቸው ጀመር......የሚያተኩስ ድምፅ ኾኖ በተከፈተው መስኮት......

*ብር አምባር ሰበረልዎ*
*ብር አምባር ሰበረልዎ*
*አሆሆ!!ሽጋው ልጅዎ*
*ሰብርብር አረጋት እንጅ እንክትክት አረጋት እንጅ*
*አሆሆ---የኛማ ልጅ*
*ሰብርብር---ሰብርብር---ብር......*

በስከረ ገላዋ ተንጠራርታ ትንፋሽ እስኪያጥረው ድረስ መላኩን አቀፈችው የእሱን ወገብ ያቀፉ እግሮችዋ ከፍ ዝቅ እያሉ......

እጅ አዙር ጫጉላ......

እጅ አዙር ፍቅር......

እጅ አዙር ከንፈር

እጅ አዙር......

ዜማው ከነከበሮው በጥጋብ ሲነጥር ይሰማል---ለዘለአለም የማያቆም መስሎ፡

[6] ከሁሉ የምትጣፍጪ፣ ከሁሉ የምታምሪ የእኔ ነሽ



@BOOKALEM

*እሰቲ አምጡት የደሙን ሸማ*
*እሰቲ አምጡት የደሙን ሸማ*
*አሆሆ!! እንድንሰማማ......*

......እጆችዋ ግራና ቀኝ ባልዋን ለቀው መሬት ለመንካት ደርሰው...... ዳሌዋ ቀልጦ እንደ ቀሳሳ ወንዝ ግቢዋን አቋርጦ......ጎረቤትዋ ቤት ደጃፍ እንደ ኩሬ ፈሶ......እግሮቿ ግራና ቀኝ-ጉዞ እንዳደከመው መንገደኛ፣ ውሃ ጥም እንደጣለው......ከሚቀጣጠል አፏ ምጥ የመሰለ ድምፅ እየወጣ......

ያማረበት፣ የተኳለ ገላዋ ተዝለፍልፎ......እንባ ከአይኖቿ ወደ ጆሮዎቿ ኩለል ብሎ ወረደ።

---- // ----

*ግንቦት 1979*
*አዲስ አበባ*

# አለንጋና ምስር

## ማዙካ

ከሁለተኛ ባልዋ ነው የወለደችኝ:: ታዲያ አባቴን ልታበሽቀው አስባ ይሁን ወይ ከልብዋ---እኔ አላውቅም «ከአንተ የመጀመሪያው ባሌ ይሻለኝ ነበር» ትለዋለች:: ታዲያ የአባቴ ጠባይ ግልፕ ስላልኾነ ብቻ ወይ ቅናቱን ሊያኪያኪስ አፉን---ያ ቡሃቃ አፉን (እስዋ እንደምትለው) እስከመጨረሻ ከፍቶ ባ ባ ባ ባ እያለ ይስቃል:: ጥጥ የመሰለ ፀጉር አላት:: ገና በወጣትነትዋ ጠቅላላ ፀጉሯ ሽበት የኾነ እናት ያለኝ ልጅ እኔ ብቻ ነበርኩ:: ከባልዋ ጋር ተቀምጣ የምትደባብስ እናት ያለኝ እኔ ብቻ ነበርኩ:: ጠይምነትዋ የበግ ጥብስ የመሰለ፣ በመንገድ ላይ ጎረምሳ ገላምጦ የሚያያት («የፍሬው እናት ደስ ይላሉ አይደለ?») የምትባል የእኔ እናት ብቻ ናት:: «ገና በሰላሳ አመቴ ሽብቼ!» የምትል እናት ያለኝ:: ስምዋ «ሉል» የተባለ---አፍ መሃልና ምላስ ላይ እንደረጠበ ከረሜላ የሚልወሰወሱ፣ የሚያዳልጡ ፊደላት ያሉት ስም ያላት እናት ባለቤት እኔ ብቻ ነኝ (ያንዳንዶች ልጆች እናቶች ስማቸው 'አስካለ' 'አልማዝ' 'አሰለፉ' 'በግዬ' ምናምን ነው):: ደግነትን እንደመስከ ዓለም ፊት ዘርግታ የምታሳይ......ከትምህርት ቤት ስመጣ ቤትዋ በር ላይ የምትጠብቀኝ......ከመግባቴም በፊት እግሯ ዙርያ ተጠምጥሜ ሳትፋት፡ ቀሚስዋን ሳሽት:: ደ`ሞ እንዴት እንደዋለች ልጠረጥር:: ጠቅላላ ፊቴን በቀሚስዋ ጠቅልዬ ምን ዓይነት ምሳ እንደሰራችልኝ ልጠረጥር---እናም ይሄ ቴክኒክ የማይገባት እናት ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ:: እሷም አንዳንድ ቀን ቅቤያማ ጠረን አላት ቀሚስዋን የላም የላም የሚያደርግ:: አልወደውም:: እንዲህ ሲሆን ለአባቴ የተዳላበት ቀን ነው......ከባድ ቅባታም ወጥ የተሰራለት::

……ሳር ሲሸተኝ፣ እናም ለስለስ ያለ የዘይት ዱካ ያቺ እናት ያቺ ማዙካ አውቃለሁ ያን እኩያ የለሽ የፈረንእኖችን ምስር ወጥ እንደሰራች::

## ሚኒስትሪ

እናቴ የተነገረለት ታላቅ ቀሚስ አላት እዛው በሰፈራችን እንድ የዶርዜ ሸማኔ የተሰራ:: ቀይ ጢማም ሰውዬ:: አንድ ነጠላ ሰርቶ በጨረሰ ቁጥር ከጉድጓዱ ወጥቶ ድር የሚዘረጋበት አካባቢ ብቻውን ዶርዚኛ ይደንሳል:: ቀሚስ ሰርቶ ሲጨርስ እንደዚሁ:: ሸምኖ ሲጨርስ ነው ሲባል ልጆች ተጠራርተን ከበነው እንቆማለን:: የጨረሰውን ነገር ሰባስቦ ሳጠራው ውስጥ ይከትና ዳንሱን ይለቀዋል:: እሱና አንዳንድ የነበሩ እንደሚናገሩት ከኹሉ ትልቅ የሰረፍት ዳንሱን የደነሰው የእናቴን ቀሚስ መገንቢያ ሰርቶ የጨረሰ ዕለት ነው:: ከሶስት መቶ እጥፋት በላይ ያለው ቀሚስ የተሰራበት ሸማ:: ነጠላውም ሳይረሳ::

«ታዲያስ ወይዘሮ ሉል እንዴት አደረጉህ?» ሲሉት

«የእሳቸውን መስራት ስምንተኛ ሚኒስትሪ እንደመፈተን በለው:: መከራ ነው»

«እስከ ዛሬ ኢ ኤስ ኤል ሲ አልወሰድክም?» ሲሉት በማሾፍ!

«ዝም በል ደንባራ:: ወሬኛ:: እንጀራና ቀልድ ለይቶ የማይገባው ወመኔ» ይላል::

ለዚህ ሳይሆን ይቀራል ብዙ ልጆች በእናቶቻቸው ላይ ሸፍተው እንዳፈለጋቸው ሲሆኑ እኔ በእናቴ ስሜት የምገዛው? ማለቴ የቀሚስዋ ሸብሸብ በመብዛቱ እሱን ፈልፍዬ ወደ ውጭ ፀሐይና ብርሃንን ጨረቃና ከዋክብትን የመሳሰሉ ነገሮችን በራሴ ዓይኖች ለማየት ያዳገተኝ?……እና የዚያ የምስር ወጥ ጠረን:: እንደ ምስር ፍሬ የሚስበኝ የጥሬ እህል አልነበረም:: እነማን ነበሩ? አለ ዘፋኝ:: ምስር ወጥ የበሉ? በእንጀራ ዓይኖች ውስጥ በጥናት እንደተሰሩ ብሉኖች ልክክ ብለው ተሰንቅረው ወይ ተቃቅፈው? (`እንዴ?! ዐይኔ ጠፋ እኮ· --እስኪል እንጀራ) በተቀቀሉበት መረቅ ረስርሶ እሱን በትናንሽ እጆቼ ተነሀነሂ ሰባስቤ ሰለሂ መለሂ ጉሮሮ ማይነሂ ገብተህ ጃና ሳደርገው……ጣቶቼም ላይ (ብታጠባቸውም ባልታጠባቸውም) የመሰለ የኑግ ዘይት::

በዚያ ዕድሜዬ ሁልቀን የምሰራው ነገር ቢኖር ወይ ለሚኒስትሪ ማጥናት ወይ ኳስ መጫወት፣ በዚህ መሃል ምስር ወጥ ማደን ነበር:: ቢቻልና ቢፈቀድልኝ ሁልጊዜ ኳስ ብጫወት:: ግን አባቴ ኳስ ጨዋታን `ፈኛ ማባረር` ነው የሚለው:: ትምህርቴን በመጥፎ ማርክ ካበላሸሁ፡ `ትበላለህ («ያው ምስርህን ትነፋለህ» ማለቱ ነው)



@BOOKALEM

ትዘላለህ (ያው «ፊኛህን ስታለፋ» ማለቱ ነው)

እና እንዴት አምስት ከአስር ታገኛለህ?

አባቴ ቁጡ ነው:: ከስሩ አቁሞኝ ጥፋቴና ጥፋቴ ያልኾነውን የገባኝና ያልገባኝን ነገር እየደባለቀ፣ ምራቁ እየተፈናጠረ ሲሎህብኝ ቀዝቃዛ ሲሚንቶ የሚዘንብበት ክረምት ይታየኛል:: እንዲህም ስለሚል:

«ትዕዛዜ ሲሚንቶ ናት»

ምን ማለት እንደኾነ ባይገባኝም፣ አንድ ሁለት ቀን ከጠቀሰልኝ ስነስርዓቶች አፈንግጬ ከምን ጋር እንደተላተምኩ በአስመራሪ መልኩ ተረድቼአለሁ:: እኔ ላይ ብቻ ሳይሆን በሰፈሩ 70 ከመቶ ሕፃናት ላይ በሕገ መንግስት ያልተረቀቀና ያልፀደቀ ስልጣን ነበረው:: ብዙ ጊዜ ግን አይናገርም::

«እኔ ስቀጣ ታግሼ ነው:: አንድ ጊዜ እንዲህ አደረገ:: ታገስኩት:: ደ`ሞ አንድ ቀን በዚያ በኩል ሲያልፍ እንዲህ አድርጎ እንዲያ ሲያደርግ አየሁት:: ዝም አልኩት:: አንድ ቀን በወዲያ ሳልፍ ከማን ጋር ነው እባካችሁ እንዲህ አድርጎ እንዲህ ሲናገር......ሰማህ በቀደም ዕለት ከሰዓት በኋላ እንዲህ አድርጎ.......» ታሪክ ይዘረዝርና በእርግጥም ዕውነቱን ነው.......ብሎ ይልና ቁጣውን ሲከፍተው.......የኾን ስለሚኒስትሪ ሳጠና ነው::)

ላለመናገር እንዲመቸው ነው መሰለኝ ወይ አካባቢውን እንደ አውራ ዶሮ መቆጣጠር እንዲያስችለው ሲቀመጥ እንጨት እንደዋጠ ሁሉ ቀጥ ብሎ ነው («ምነው እንደ ኮንጎ ዘማች በተጠንቀቅ ተቀመጠ?» ይሉታል የማያውቁት) እናቴም ትለዋለች---ስታሾፍ::

«እርፎ ስቀመጥ ነዋ» ይላል::

«ውይ እቴ ታረፈ»

«አይ እንግዲህ ካላረፌሽ እንደ ልጅሽ ነው የማቀምስሽ»

ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ

ሁለቱም በሳቅ ተያይዘው ይፈርሳሉ:: ፈገግ እላለሁ:: ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ እንዳልስቅ አባቴ ሲያቀምስ ምን ምን እንደሚል ስለማውቅ ነው::

ልጅ እያለን ግን ብዙ እንረሳለን መቅመሱንም ምኑንም:: ሁላችንም ነን:: ከፈሪዎቹ ጥቂቶች በስተቀር:: ታዲያ ይሄ ልጅነት የሚነብኝን ልበ--ቢስነት ምን ሳድርገው?

አንድ ቀን ቀጥ ብሎ እንደተቀመጠ ሳይነቃነቅ ወደ ታች እያየ:



@BOOKALEM

«ስማህ አንተ ወደላ (ቀጫጫ ብሆንም) ሚኒስትሪ ደርሶአል ይባላል:: አንተ ግን ሳይህ እንኳን ሚኒስትሪ የደረስበት ጥምጥሙ የጠፋበት ቂስ አትመስልም» (ምን ማለቱ እንደኾነ አይገባኝም)::

ሚኒስትሪ ተፈታኝ እንደኾንኩ ያወቅሁት መስከረም ላይ ነበር:: በኋላ ወራት ሲያልፉ ግን ረሳሁት:: ምክንያቱ: ኳስ ጨዋታ:: መስከረም ላይ ት/ቤት ጥቂት ልጆች ተሰባስበን «የረር» የተባለ የእግር ኳስ ቡድን አቋቁመን እሱን ማደራጀት ስራ በዝቶብኝ:: ስም ሲወጣ አንዱ ቀልባጣ ታሪክ በስም መመዝገብ ይወዳል መሰለኝ የቡድናችን ስም «አለንጋ» ካልኾነ ሲል ነበር:: ስንት ዓይነት ጨጨ አለ በእግዜር::

«ከነገ ጀምሮ እዚያች ኳስ ሜዳ እንዳላይህ:: ቅዳሜና እሁድ ከብሩ ጋ ሂድ» አባቴ ይሄን ሲናገር ገጹ ላይ ፈገግታ አልነበረም:: ሲያመር ትዕዛዙ ኮስታራ ነው:: ለስላሳነት ቀርቶ የለስላሳነት ሩሕ የለበትም:: ቀይ ፊቱ ላይ የበቀሉት ጠጉሮች እሾህ ይመስላሉ:: የቡናማ ዓይኖቹ ክቦች የሰፉ ይመስለኛል:: በሳሙና የተተኮሰው የካኪ ሱሪው ስለት የሚፈልጥ ይመስላል:: ብዙ የወንፊት ጌጥ ያለበት ጫማው መሬት በስልት እየመታ ይመለሳል:: በጫማው አፍንጫ መሬት ገጭ፣ ከዚያ ብድግ ገጭ፣ ብድግ ገጭ፣ ብድግ::

«ሰማኸኝ?»

«እዎ»

## የኔታ

አባቴና እናቴ የሚተኙበት ትልቅ ፋሚሊ አልጋ አለ:: ታዲያ ብዙ ጊዜ ደብዘዝ ያለ ቦታ ነው የሚዘረጋው:: (እስከ ዛሬ ከዚህ ልምድ ተነስቼ ነው መሰለኝ አልጋዎች በተቻለ መጠን ጨለም ያለ ቦታ መዘርጋት ያለባቸው ይመስለኛል):: አባቴና እናቴ `አቀማመጡ ሰለቸን` እያሉ አልጋው የተዘረጋበትን ቦታ ሲለዋውጡ ሁልጊዜም የሚያስፍሩት ደብዘዝ ያለ ጥግ ነው:: መኝታ ቤታቸው የጨለማ ሐብት ስላላት ይሁን አላውቅም:: የዚህ ፋሚሊ አልጋ ሁለት ልባሶች በየሳምንቱ የሚለዋወጡ ሽምብራ ስራ ዳንቴሎች ናቸው:: ቀለማቸው አንድ ነው---ደማቅ ቀይ:: ትራሶቹ በሙሉ አበባ በተጠለፈባቸው ቀረጢቶች ውስጥ የተከተቱ ናቸው:: እነዚህ ሁሉ አይስቡኝም:: የምትስበኝ ሁልጊዜ እንደ ሙሴ ዕላት ቀና እያልኩ በፍርሃትና በመገረም የማያት `የኔታ` ናት:: ሁል ጊዜ የአልጋውን የቦታ መለዋወጥ እየተከተለች፣ ጨለማውን እየተጋራች ሳትረሳ እንደ ሌላው የአልጋው ብልቶች በየግድግዳዎች የምትዞር ጉድ ናት:: ሌላም ነገር አይደለች:: አለንጋ ናት:: እንደ ሌሎች የአልጋው አጃቢ ብልቶች ግን

ታጥባ የማትሰጣ:: ከትራስጌው ከፍ ብሎ አንድ የትልቅ ሰው ክንድ ዕርቀት ላይ አስራሁለት ሳንቲም ምስማር ጭቃ ግድግዳው ውስጥ ያለምህረት ተቀብቅቦአል:: እዚህ ምስማር ላይ አባቴ «ኳስ ሜዳ እንዳላይህ» ካለኝ ቀን ጀምሮ የኔታን ሰቅሎአል:: `ወንጀለኛ መቅጫ` እንደማለት ነው:: የኔታን ካየሁ በኋላ አባቴ እንዳመረረ ገባኝ::

እሷን የኔታ ብዬ የሰየምኩበት ምክንያት እንዲህ ነው......

አባቴ ቄስ ትምህርት ቤት ስማር እኚህ ወዳጁ አስተማሪዬን እንዲህ ይላቸዋል፡

«እንግዲህ ስሙ......ሰሙኝ? ልጁ መንግስት ት/ቤት ሊገባ ነውና ያቺ ያስለመዱት አለንጋ ልትናፍቀው ስለምትችል፣ እስዋን ካላየ ስለማይማር የአለንጋዎን ኮር እንዲሰጡኝ»

እኚህ ቄስ ደ'ሞ ከማስተማር ይልቅ መግረፍ የሚመስጣቸው፣ በመደሰት፣ ልክ ልዩ የቴክኖሎጂ ዕውቀት እንደሚያስተላለፉ ሁሉ፡

«እንዴ እሱማ ያስፈልጋል!! እዚያ ስነስርዓት የጎደለበት ቦታ ነው:: በየቀኑ ያቺ መድኃኒት ታስፈልጋቸዋለች:: እስዋ እኮ ራስምታት ለኾነ ልጅ ጥሩ ካፌኖል ናት:: ፌውስ ናት:: እሱ ደ'ሞ ያውቃታል:: ብዙ ባያጠፋም፣ ጥፋት እንዳያስብ አንድ ሁለቴ አቅምሼዋለሁ:: ግን የሚኾነው አይታወቅም:: ለሰውዬዬ አንድ ጨምሮ እንዲሰራልኝ እነግረዋለሁ»

ይህቺ አለንጋ እጀታዋ ስድስት የተገመዱ ሽቦዎች ናቸው:: ከአናትዋ በኩል እንደመድፌ ትልቅ ቀዳዳ አላት:: በዚህ ቀዳዳ ሰፋቷ ሁለት ሳንቲሜትር ዕርዝመቷ አንድ ሜትር ተኩል የሚሆን ቆዳ አጥልቃለች:: ደብዛዛ ወይ የቆሸሸ ቢጫ ቱባ ክር የገባባት መድፌ ትመስላለች::

«የፍየል ቆዳ ናት የፍየል ቆዳ ናት» ሲሉ ሰማሁ::

*«በፍየል ቆዳ የተሸጠ ልጅ*
*ይለፈልፋል 'አልደግምም' ብሎ»*
*(እንተ እራም ግጥም)*

ሲሉ ሰምቼአለሁ::

ፍየልና ለፍላፊ ሰው የምጠላው በዚህ ምክንያት ይሆናል::

ታዲያ ይህቺ የኔታ ስነስርዓት ያጎደልኩ ዕለት፣ የታዘዝኩትን ካልሰራሁ በእኔና በስነ ምግባሬ መሃል እየተወሰወሰች የተፈጠረው ክፍተት የሚጠገንባት ናት::

ዝነኛ ሆናለች ደ'ሞ::

ጓደኞቼ፣ ከብሩ ሳይቀር ትንሽ ሰላም የሚነሳቸው ኩሸት ካበዛሁ፡



@BOOKALEM

«ካላረፍክ ለአባትህ እንነግርና ያቺን የኔታ ትቀምሳለህ» ይሉኛል::

አባቴ ልምዱ አለው:: በአለንጋ ሳይሆን በዱላ ጥቂት ሰዎች አቅምሶአል:: ሲባል በኋላ ስሰማ አባቴ ኮንጎ ዘምቶ የመጣ ነው:: ልጅ እያለሁ 'መዝመት' ሲባል ስንቅ ምናምን በጨርቅ ቋጥሮ ሩቅ ቦታ ሄዶ መመለስ ይመስለኝ ነበር:: ዘመድ ሊጠይቅ ሰበታ ወይም ጉደር ሄዶ የመጣ ሁሉ የዘመተ ይመስለኝ ነበር:: ብቻ 'እከሌ ሰነቀ' ምናምንማ ካሉኝ ከባድ ዘማች ይመስለኛል::

ከዘመቻ እንደመጣ አባቴን ስታየው እናቴ ያኔ ባለትዳር ናት ጎምላላነቱ ማርኮአት ትዳሯን ትታ ቤቱ ትገባለች:: አንዳንዴ እናቴ ፌሚኒዝምን[7] የጀመረች ይመስለኛል:: ደ'ሞ ሴቶች ጎምላላ ይወዱ ይመስለኛል:: ለምሳሌ አንዲት አሜሪካ ኖራ የመጣች ዘፋኝ ስሟ አይያዝልኝም 'ጎምላሌ' ብላ ትዘፍን የለ:: የሚጎማለል ፈረንጅ አይታ ይሆናል:: ለምሳሌ ጆን ዌይን ሲራመድ ይጎማለል የለ::

እናቴ በአባቴ ተጠልፋ ከሄደች በኋላ ለድሮ ባሏ በሰው እንደማትመጣ መልዕክት ላከችበት: 'ቅር እንዳይለው ብዬ' ትላለች:: ታዲያ ጎረቤታችን የነበረ አንድ መልከ መልካም ጎልማሳ ባለ ትዳርና የሶስት ልጆች አባት ጠጋ ጠጋ እያለ እናቴን 'ያሻክራል':: አባቴ እዚያው አጠገቡ እያለ ሁሉ በሽሙጥ እንደሚፈልጋት ይናገራል:: ሰው ሁሉ ባለበት:: ያለ እፍረት:: እናቴ ደ'ሞ አባቴን ለማስቀናት ሳይሆን አይቀርም ለሰውዬው ፊት ታሳየዋለች:: ሰውዬውም ልብ ያገኛል:: አባቴ ቢያይ ቢያይ ሰውዬው አላበርድ አለ:: አንድ ቀን 'የንቀቱ ንቀት' (አባቴ ሲል እንደ ሰማሁት) አባቴን ለሰላምታ አስቁሞ:

«ያቺ ቆንጆ የማትጠገብ ሚስትህ ደህና ናት?» ይለዋል::

«ደህና ናት እሷስ፤ ያንተ ነገር ሲገርማት ይኖራል» ይልና ከአጥር ላይ ጨፈቃ ዘንጥሎ ሰውዬውን ይዠልጠው ጀመረ:: ሰውዬው እየተመታ ግራ ገባው:: ይመታል ግን ያልተመታ ይመስለዋል:: ቢለማመጥ ቢለማመጥ ዥለጣው አላቆመም:: ራሱን መከላከልም አልቻለም:: ሰውዬው እየጮኸ ሲሮጥ አባቴ እየተከተለ ሲዠልጥ ተያይዘው ቀበና ይወርዳሉ:: ሠፈር ሊያገላግል ሲመጣ «እንዴ እሱ በነገር ሲያበራየኝ እናንተ የት ነበራችሁ?» ይልና በድምሩ አራት የሚደርሱ ሰዎችን እየደበደበ ሲበታትኑ ያንን ሰውዬ ግን እየተከተለ ቀበና ድረስ አወረደው:: ሰውዬው ቢመረው ዘሎ ወንዝ ገባ:: ሊለቀው ነው! ከላይ እስከ ታች በወንዙ ዳር ዳር ሰው ተኮልኩሎ እያየ አብሮት ወንዝ ገባ:: ከዚያ የሚገርም ነገር ተፈጠረ:: ሰውዬው ጠፋ:: ማለቴ ወንዙ መሃል ከቁሙ ጠብ አለና ቁርጭምጭምት የማይደርስ ውሐ

---

[7] እንስታዊነት



@BOOKALEM

ውስጥ ጠፉ:: ሲቀልዱ «ሰውዬው 'እንዲህ ከምደበደብ' ብሎ ወደ አሳ ተለወጠ» ይላሉ የሰፈራችን ወሬኞች---ይሄ ወሬ አባቴን ሳይጥመውም አይቀርም:: ሰውዬው ሶስት ልጆች ነበሩት:: ሉሺ፣ ቶሺና ሞሺ የሚባሉ:: ከዚያን ቀን ጀምሮ የሰውዬው ሚስት ልጆቿን ሰብስባ ወንዝ ዳር ወርዳ ሰፍራ ባልዋን አጥምዳ ለማውጣት መረብ ትጥል ነበር:: (ይሄ እንኳን ብዙው ቀልድ ይመስለኛል)::

አባቴ ስለተደባደበላት ግን እናቴ ተደሰተች:: እንደምትለው:

«ወንድ አልዶመዶመ እንደሆነ ስለቱ በየዓመቱ መፈተሽ ያለበት ቢላ ነው:: እንደው ይሄን የሚያክል ቁመና ይዘህ አንዳንድ ቁም ነገር ስራበት እንጂ»

እሱ ደ'ሞ:

«ለአገሬ ስል ምንም ያላደረገኝን ኮንጎ የወጋሁ ነኝ:: ለሚስቴ ፍቅር ወስላታ አልምታ እንዴ?» ይላል:: (አይገርሙም?)

ይሄን ሁሉ ያነሳሁት መደብደብ አባቴ የሚያምንበት መሆኑን ነው:: አንድ ወዳጄ ይሄንን ዓይነት ጠባይ «ልብነ ድንግላዊ» ነው ያለው? 'የሚወጋ ሰው ቢያጡ፣ በጥጋብ መሬት ይወጋሉ' ዓይነት::

## የኔታና ዕቃ ዕቃ ጨዋታ

ሰፈራችን በአንድ አስፋልት መንገድ ለሁለት የተከፈለች ናት:: የመዝናኛ በታዎቻችን ደ'ሞ ሶስት ደረጃዎች አላቸው:: ደረጃቸው የወጣው በመፈቀድና ባለመፈቀድ ውሳኔዎች ውጥረት ውስጥ ነው:: ከዚህ መንገድ ወዲያ፣ ከቤቶቹ ጀርባ በስተምዕራብ ግማሽ አቧራ ግማሽ አከርማ የኾነ ሜዳ አለ:: የማያሳዝነን፣ ሳናቋርጥ የምንመልጠው:: ብዙ ጊዜም የሚፈቀድልን መጫወቻ ይሄ ብቻ ነው:: ለማንም ዐይን እንታያለን:: እናቴ ከፈለገችኝ ሰፈሩን አቋርጣ መጥታ ሜዳው ደርዝ ብቅ ካለች ሁሉ ወገግ ብሎ ይታያታል::

«አንተ ደንቆሮ ጆሮህን ውሻ በልቶታል ስጠራህ አትሰማም!»

ከዛ ልጆች በሳቅ ይሞታሉ:: ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ

«ዶግ በላብሽ እንዴ ጆሮሽን» ይሉኛል በአምስተኛ ክፍል እንግሊዘኛ ተርጉመው ሊያበሽቁኝ::

«ፋሊሽ ሁሉ» እላለሁ በስድስተኛ ክፍል እንግሊሽ::

የመጀመሪያው መዝናኛችን ይሄ በታ ነበር::

ሁለተኛው መዝናኛ የአስፋልት መንገዱ ራሱ ነው::

አባቴና እናቴ አንዳንዴ በትልቅ ጓንንቸር ቁልፍ የተዘጉ መጻሕፍት ይመስሉኛል:: ጠረጴዛ ላይ ዝም ባለ ቆዳ ተጠርዘው



@BOOKALEM

የማይገባኝ ነገር በልባቸው የቋጠሩ፣ ቄስ ሽውዶው ቤተክርስቲያን ማስጢር ቤት አፂሬ ኀርሰው የቀኑ ድጓዎች፡፡ እነሱን ከፍቶ ማንበቢያ ብልሃቱ አልነበረኝም፡፡ አንዳንዴ የምሰራው ቢጠፋኝም እነሱን ለማስደሰት ብዬ የሚወዷቸውን የታወቁ የባህል ዘፈን እዘፍናለሁ፡፡ ግን እኔ ስሜወታቸው ያዩና ወይ ያዳምጡና፣

«እንደዚያ አይደለም፣ አይ......አይ......አይ......» ይሉኛል፡፡ ስህተት ኸና ይተረጎሙብኛል፡፡

«ምነው?» ስል፡፡

«ድምጡ መረሩ ነህ ለዘፈን አትሆንም» ይሉኛል፡፡ ማነው በተቁ የቀመሰኝ? ዘፋኝ በደም ነው በድምፅ የሚገመት? ጉድ እኮ ነው፡፡

በዚህ ሁሉ እንካ ሰላንታ ተዳክሜ ከቤቴ ስወጣ መጀመሪያ የማርፈው መንገዱ ላይ ነው፡፡ ታዲያ እዚህ መንገድ ላይ ከየሰው ጋ በማይየለሽነት ይሁን በዕውቀት የሚባሉ ስድቦችን እየለቃቀመን የምንለማመድበት ቦታ ነው፡፡ ከትልልቆቻችን ሳንተች ሳይገባን ቁንቁ የምንቀሰምበት ጊዜ ነው፡፡ እጆቻችንን ኪሳችን ውስጥ ከተን ምላሳችንን አጥፈን ረቂቅ ቶጬት እንሰራለን፡፡ ዕድሜአችን በጠኝ ኸኖ መንገድ ዳር ተዋህደው በችቦ የታሰሩ ልፍስፍስ የቅጠል ካሶች እያንጠባጠብን ኮረዳዎች ሲለከፉ ሰምተን እኛም እንደ ነገሩት ወስደነው እንዳደግን ሁሉ ለክፈናል፡፡ እነዛ ሁሉ ባዶ እግሮች አይረሱኝም፡፡ ጭቃ ከለበሱት ያልታጠቡ ጫማ የለሾች ጀምሮ ጠቢጠቡን ለመጫወት እንዲያመቸው ጫማውን አውልቆ የአስፋልት ጠርዝ በአንድ እግሩ ነክቶ፡ «ላ አንድ ላ ሁለት ላ ሶስት ላ አራት ላ አምስት ላ ስድስት......» በመሳሰሉ ምሕግሮች የሚያቀላጽሰው ሁሉ፡፡ ዛሬ የእነዚያ ልጆች እግሮቻቸው ብቻ ፎቶግራፍ ተነስተው ቢመጡ የእነማን እንደሆኑ ያለችግር ለይቼ አውቃለሁ፡፡

አንዳንዴ ያመለጠ ካስ ተከትለን አስፋልት መሃል ስንርተ የሚጮህብን ሰው ብዛት፡፡ ስንሰድባቸው የናቁንን ያልሰሙን የመሰለንን ልጃገረዶች እንዲሰሙን ጠጠር ወርውረን ጀርባቸውን መተን በፍርሃት ደጋ ሮጠናል፡፡ በተለይ ቤቶች ቀላል ኢላማዎች ነበሩ፡፡ ስለ ሽፋፋ ሳናውቅ ሲባል ሰምተን «እንቺ ሽፋፋ!» ብለናል—እግር እንዳለን እንኳን ትዝ ብሎን ሳያውቅ፡፡ ያከረከሩ ጎረምሶች «ይህቺን ማድረግ ነበር» ብለው ሲሉ፣ በበጣራቸው፣ በአፍሮአቸውና በቆሸሸ ሸኪታቸው ተጠልለን እንደነሱ ለሐሜችንን ለማዝረብረብ ሞክረናል፡፡ ለሴጭም ወጣተናል—ገና ልጅ ስለሆንን ይሁን ወይ ጎርምሰን አላፊ አግዳሚ ተመልካች የማፈርደው ነው፡፡

መንገዱ መንግስት ያላወቀው ት/ቤታችን ነው፡፡ ለመልከሙም ለክፋም፡፡ የማናውቀውን መንገደኛ በኋላ ደርቦ «እኔ አይደለሁም ጂ እሱ ነው» ማለት፡፡ አስፋልት ላይ በቾክ ክብና ቀስት ቢጋር ስርተን



@BOOKALEM

ብዶና ኮርኪ የምናንካካበት፡፡ መስታወት ወስደን የምትንቀል ትንሽ የፊት መስታወት......ከወገር ብሩሽ ላይ አድርገን.......እስኪ ሴቶች ቀሚስ ስር

«ሲኒማ አየን» የምንልበት፡፡ ባይታየንም፡፡

«ምን አያችሁ?» ብንባል

«ሲኒማ»

«መስታወቱ ውስጥ ምን ነበር?» ሲሉን ያየነው ጨለማ እያሳፈረን ልፋታችን ሜዳ አልቀረም ለማለት ድርቅ ብለን፡

«ሲኒማ»

ሰስተኛው መዝናኛችን ግን የተከለከለ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከብትና ገበሬ ከእንጦጦ እያንጋጋ የሚያመጣው ለሰፈራችን ፍርሃት የለገሰው ጠንጋራው ቀበና፡፡ ክረምት ይሁን በጋ ወርዶ እል ከተባለ እናቴም አባቴም እኔን ፍለጋ ይመጣሉ፡፡ ደፋር ነው ሲባል ቢሰማም አባቴ በወንዝ ነገር አያምነኝም

«ለእኔ መሰለህ? ለአንተ ነው፡፡ ውሃ አይከራከርም፡፡ እያዝንም፡፡ ጅብ ቢያገኝህ አንድ እግር ካገኘ ይለቅሃል፡፡ ይፈራል፡፡ ወይ ይጠግባል፡፡ አንበሳ ቢያገኝህ ልጅ ከሆንክ አይበላህም፡፡ ይኮራል፡፡ ውሃ ልብ የለውም፡፡ ይዞህ እብስ ነው፡፡ ነርቭ የለውም የሞላ ውሃ» (ለምን እንደኛውን የጅብና የአንበሳ የአበላል ማኒፌስቶ እያወጣም ነበር?)

ደ'ሞ ፈሪ ሰው ሲያጋጥመው—አባቴ «እይ! እይ! የዚህ ሰው ነገሩ ሁሉ የቀበና ነው፡፡ ደካማ የሚያጠቃ» ይላል፡፡

እረፍ ኮሚኪ ፍልስፍና ነበረች፡፡

ፋቴ በክረምት ብርድና በኳስ ጨዋታ ጨው ከመሰለ ገና ለገና ወንዝ ሳትወርድ አልቀረህም ተብዬ ሾጥ የምደረግበት ጊዜ አለ፡፡ በዚህ መነሾ ክረምት ክረምት የማይመታ ልጅ የለም፡፡ እንናገረውም እንጂ፡፡ የተለመደ ነው፡፡ እንደመተንፈስ በሉት (ሰማህ ዛሬ ስተነፍስ አደርኩ አይባል)፡፡

የኸን የሐምሌ ቀን ነበር፡፡ ዝናብ ያልነበረበት ጊዜ፡፡ 'ዝናብ ጠፋ ዝናብ ጠፋ' እያለ ሰው ያማረረበት ጊዜ፡፡ ወላጆቻችን ከፈለጉ በአለንጋና በአዋጅ ይግረፉን ብለን ከብዙ የሠፈር ልጆች ጋር ወደ ወንዙ አካባቢ እጋም ለቀማ ሄደናል፡፡ አስር የሠፈር ልጆች ነበርን፡፡ ሁሉ በፍርሃት እንዳንድ ኪስ እጋም ለቅሞ ወደ የቤቱ ሲመለስ እኔና አንድ መንበሬ የምትባል ጓደኛዬ ልብ ሳንለው ብቻችንን መቅረታችንን አየን፡፡ በፀባዬ እጋም በላተኛ አይደለሁም፡፡ እጋም ስበላ እማዞን ደን ውስጥ የምኖር! ሕብረ ትምህርት ላይ የተማርኳቸውን ቦጋናና ዋናን



@BOOKALEM

የተባሉትን ልጆች የሆንኩ ይመስለኛል:: እኔ ደ'ሞ ከስማቸው ጀምሮ ስለ እነሱ ያስተማረኝንም አልወድ:: ለእኔ አጋም ለተማ ጨዋታ ነው ከልጆች ጋር ለመኾን ነበር ወደ ወንዙ የምሄደው:: ወሬና መጣፋት እወዳለሁ:: ሱስ ነገር ነው:: ታዲያ ከመንበረ ጋር ምን እንበራ? ለስላሳ፣ ወንዝ ያለፈበት ደረት ያለ ደለል የተኛበት ቦታ ላይ ገባ ቆፍረን እንጫወት ተባባልን::

«ቀር» ስንል «ጂም» ስንል ቆየንና ተሰላቸን:: ከዚያ እኔና እሰዋም ማታለልና ማፈር ጀመርን:: ማታለሉንም ማፈሩንም አልቻልኳትም:: እና ተናድጄ ልመታት ስል ተነሲታ መሮጥ ጀመረች፣ በንሯሯጥ ባር አዳልጦአት ይሁን ጠልፎአት ወደቀች:: እንደደረስኩባት ሳትነሳ እላይዋ ላይ ወደቅሁ:: መንበረ ዕድሜዋ ብዛቱን አላውቅም እንጂ ከእኔ ይበልጣል:: እኔ ታድያ እላይዋ ላይ ስወድቅ ለእሷ የስጣት ትርጉም ልፊያ ብቻ አልነበረም:: እኔ የማውቀው በመንገድ ላይ ጎረምሶች ስለሚያወሩት `መደራረግ` ነው:: እንጉቱን ግን አያውቅም:: ለእኔ በመልካም አመታት በእግር ከተጠለዘች ኋስ የበለጠ የሚያምር ነገር አልነበረም:: እሰዋም እኔም መሳሳም እናውቅም:: እሰዋ `የመደራረግ` ጉጉት አላት:: ሁለታችንም ግን መሃይምናን ነን:: ሰዎች ሲደራረጉ ልብስ ያወልቃሉ ሲባል እንሰማለን:: ስማያዊ ቀምጣ ሱሪዬን 'አውልቅ' አለችኝ:: ያለ ውስጥ ሱሪ ቀበና ዳር ቂጤን የለምል ውርጭ እየለበለበኝ:: ሴቶችስ? ሴቶች ደ'ሞ ይገልባሉ:: እና በጀርባዋ ሳር ላይ—ገና እርጥበቱ ያልጠፋ ሳር ላይ ተንጋለለች:: እዚህ ሁኔታ ላይ ለመድረስ ግማሽ ሰዓት ሳይወስድብን አልቀረም:: ጎናችን እንደ የተረገመች ላም ጥላው የሄደች ገና ትኩስ የሚጤስ እበት አለ—እሱ እዛ ጋ ነው:: ዛሬ ትዝ ይለኛል:: ለመደራረግ እየለፋን ነበር:: ገላችን ተነካክቶ ሙቀትና ልስላሴ ይሰማኛል:: እሰዋ ደ'ሞ ምን ልፍጠር ብላ እንደኾነ አላውቅም ዓይኖችዋን ጨፍናለች:: ደንብ ይመስለኝ ነበር፣ ታዲያ እሰዋ አይኖችዋን ጨፍና አላየችም እንጂ እኔ ሬሻም ግላ እላያችን ላይ ሲወድቅ ልብ ብዬአለሁ:: ከእሰዋ ጭንቅላት አልፎ ዞር ስል ኮንጎ ዘማቹ አባቴ:: መንበረን ቀሚስዋን በስነስርዓት አለብሼ (የተሳሳትኩት የመገለብ ነገር ብቻ እንደኾነ ሁሉ፣ `እዚያ መኖሬ ቦታ አልነበርኩም` ለማለት ይሁን አላውቅም)—ልንባ ስል ያቺ መራራ የኔታ ጀርባዬ ላይ እንደ ጅራፍ ሙኸች:: በመሬት ላይ እየተንፈራፈርኩ እየተንፏቀቅሁ ቀምጣዬን ከመሬት አነሳሁ:: (በጣም የምታምር ገጠሬ የምታስመስለኝ ቁምጣ:: ከሰፈ ደ'ሞ በተለይ ወልይ ሲነካት የሚፈልቅ ስማያዊ) ምን አስነሳኝ? ሁለተኛው ግረፎት በዶ ቂጤ ላይ አረፈ:: መንበረስ? መንበረ በብርሃን ፍጥነት ከአባቴ እግሮች ስር ሾልካ አመለጠች:: (ከዚህ ቅልጥፍናዋ በመነሳት ምናልባት ሴቶች

ተሚስ የሚለብሱት ሲባልጉ እያለ ባሉቻቸው ሲደርሱባቸው ፈጥነው ለማምለጥ እንዲያመቻቸው ይሆናል ስል ነበር)

ታዲያ በኋላ ስጠየቅ፡

«አልባለግሁም ባልና ሚስት ስንጫወት ነበር» አልኳት እናቴን።

«እእእእእእ ከቴም። ገና ገና ጡት ሳትጥሉ»

በባሕሉ ባልና ሚስት ጨዋታ ይፈቀዳል።

ወንዝ መጫወት አይፈቀድም።

የተመታሁት ወንዝ ስለወረድኩ ይሁን ባልና ሚስት ስለተጫወትኩ ሳይገባኝ ብዙ ቆየ።

## የሚያበላ እጅ

ከተቀማሁ ቤቴ ቶሎ አልገባም ነበር። ከተመታሁ ጀምሮ ከቤት የተሰደድኩ ጥላቻ ሆዴ ውስጥ እየተንተከተከ እስኪመሽ ቤቴ አልገባም። ጠዋት በዱኔታ ብመታ ቤቴ የምገባው ከምሽቱ አንድ ሰዓት ነው፣ ያውም ተጣደፍኩ ስል። ያውም ጅብ ፈርቼ።

«ትዕቢቱ እኮ ነው»

«ጥጋብ»

ግን እርቦኝ ጠኔ ጥሉኝ እውላለሁ እንጂ ቤቴ በቶሎ አልገባትም። ግን አንድ ስልት ያለው ነገር አደርጋለሁ። ቀስ በቀስ ወደ ቤቴ ያለኝን ዕርቀት አሳጥራለሁ። ምናልባት ጅብ ከመጣብኝ ሮጬ የምገባበት ርቀት እንዳይረዝምብኝና እንዳልበላ ይሆናል።

መጀመሪያ ሜዳ ላይ ነኝ። ማንም ባይኖር ግድ የለኝም። እዚያ ቡላግና አረንጓዴ ፀጥታ መሃል እንከራተታለሁ። ሲመሽ አካባቢ ሜዳው ጎን ያለውን ሠፈር አቋርጥና ወደ አስፋልቱ እጠጋለሁ። መስል ሰዎችን ማናገር ያስጠላኛል። የሚግርኩኝ ነገሮች ሁሉ ቀለማቸው ይረግፋል። የምሰማው የልጆች ድምፅና የኳስ ቡምታ የክረምቱ ቅሀቃዜ የስራቸው ሳሉች ይመስሉኛል። ብዙው ለምን ጠባዬ በአንድ አፍታ እንደተቀየረ ያውቃል።

«አጅሬ የኔታን ቀምሳለች» ይባላል

እሳደባለሁ።

«ምናባትክንሰና»

«ጥናግም»

«ብስብስ»

«እከካም»



@BOOKALEM

የመሳሰለ::

ባለጌ ነገር አልሳደብም (ወሲብ የሚጠቁሙ ነገሮች ብቻ ባለጌ ይመስሉኝ ነበር) እንጂ. እንዲህ ዓይነቶቹን ከመሰሉቹ ጋር እንዳፈለገን ነበር የምንጠቀመው (ስድብ የሚባሉት እነሱ ብቻ ናቸው መስሉን)::

ምሽቱ ለዐይን ሲይዝ ቤታችን ፊት ለፊት በሩን ራቅ ብዬ እያየሁ ወዲያ ወዲህ እሳለሁ:: የሰፈሩ ልጆች ሁሉ በየቤታቸው ገብተው እኔ በዛ ቀዝቃዛ ምሽት አስፋልት ዳር ቀጠሮ እንዳለው ሰው ወዲያ ወዲህ እላለሁ:: ቤቴ አልገባም:: ታዲያ ወሳጆቼ እኔን መጠበቅ ይሰላቹና......እናቴ ኩታዋን ተከናንባ ከቤት ትወጣለች:: ባያትም እንዳላየኋት ሁሉ ፊቴን አዙሬ—ከቤቴ ለመራቅ እንደሻትኩ ሁሉ መንገዱን በቀስታ እጀምራለሁ:: ትደርስብኝና ፊት ለፊቴ መጥታ ከውሽት ጉዞዬ ታቆመኛለች:: በብስጭት አስፋልቱ ላይ ስቀመጥ እስዋም ተከትላኝ ቁጢጥ ትልና ዓይኖቼን በዝምታ ታያቸዋለች:: ፊቴን ወደ መሬት እደፋለሁ:: ልታባብለኝ ሞቅ ያለ እጅዋ ራሴ ላይ በቀስታና በዝምታ ያርፋል:: ወደእስዋ ሳብ አድርጋ የተሳጨ እናቴ መሃል—ትስመኛለች:: ቤት ከአባቴ ጋ ሆና እንግዲህ፡ «የእሱ ጥጋብ አቅም ቢኖረው ይማታል» ስትል እንዳልነበረ::

ምንም ጩጨ ብንሆን ይገባናል::

በጨለማው ውስጥ ስትስቅ እያታለሁ:: ትከሻዬን ትይዘኛለች::

«የእኔ ሰንደል ና እስኪ» ትለኛለች::

መሬት በእግሬ እየመታሁ ቀርባ እንዳታቅፈኝ ልርቅ እዳዳለሁ:: እንባዬን እውጣለሁ:: ትጎትተኝና ጉያዋ ውስጥ ትከተኛለች:: ለማልቀስ እንደፈለግሁ ታውቃለች:: በጋቢዋ ተከናንቤ ትኩስ ምስር ወጥ እሸታለሁ:: ሆዴ ይሞሃል:: ትጠብቀኛለች በዚያ ብዙ ነፍስ በሌለበትና በማልሰለልበት ጊዜ እንደ ወንድ ሳልታይ ሽፍንፍንዋ ውስጥ ተደብቄ እንዳለቅስ:: የምትሸፋፍነኝ ሳላፍር እንዳለቅስ ነበር::

ጩጨ ብንሆንም ይገባናል::

እንዲህ እንደጋረደችኝ ብዙ እንቆያለን:: ሁለቱንም እጆቼን አንስቼ ለይቅርታ ሳቅፋት፣ መሃል እናቴን ጎንበስ ብላ ትስመኛለች:: ሳቅፋት እንደታረቅኋት ይገባታል:: ሳንነጋገረው የተግባባንበት ድርጊት ነው:: አንድ እጄን ይዛኝ እየጎተተችኝ እቤት ትገባለች:: ከአባቴ ጋር አንተያይም:: የመምጣታችንን ዱካ ሲሰማ መኝታ ቤት ይገባል:: ከነጋ በኋላ እንኳን አላየውም:: አንዳንድ ጊዜ እስከ ሁለት ቀናት ድረስ አላየውም::

'ከእናት እጅ መብላት' የሚሉት አባባል ልቤ አይገባም ዛሬ ድረስ:: ማብላትማ ዩኒሴፍም ያበላል:: እናታችሁንና ያቅፋል በሉ::

ጩጨ ብንሆንም ይገባን ነበር::

## ክብሩ ሀብታም ነው

'ክብሩ ጋ ሄደህ አጥና' ተብዬ ታዝዤ ቤቱ ስሄድ እንደሊላው ጊዜ አላብዛው እንጂ የጥናት ፕሮግራሚ በጨዋታ የታጨቀ ነበር። ግን በእቅድ የተያዘ ነው። ለጥናት የምንገናኘው አራት አምስት ልጆች ነበርን። ክብሩ ከሌሎቻችን የተሻለ ፕሮግራም ማውጣት ይችላል። ብይችልም በአባቱ ይረዳል። አባቱ አስራ ሁለተኛ የጨረሱ ስለነበሩ 'ማጥናት ስልት ያውቃሉ' ይባላል። እና እሳቸው እንዳሳዩት አድርጎ የራሱን ትንሽ ይጨማምርና ሁሉ ነገር የተዶለበት 'ምንም አይቅርብን' ፕሮግራም ያወጣል። እናጠናና ያጠናነውን እንጠያየቅና የዕውነትም ይሁን የውሸት ያጠናቀቅን ከመሰለን አንዱ ልጅ ከደበቀበት ቦታ ኳሱን ያወጣል። ኳስ ወደ ሰማይ ይጠለዛል። ሜዳ እንገባለን።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ—አንዳንዴም ከተመደበው በላይ ከተጫወትን—ክብሩ በቁጣ፣ «ምናባታችሁንና ይበቃናል ኑ! ኑ!!» ይለንና ለጥናት እንሰበሰባለን። እንደገና አንድ ሰዓት ሁለት ሰዓት እናጠናለን። ከሳምንት ሳምንት ጊዜው እየረዘመ ትምህርታችንን እያወቅንና እየተረዳን ስንሄድ የምንጫወትበት ጊዜ እየረዘመ ፈተናው ሊደርስ አካባቢ እንደውም ጨዋታው እያስከረን ሄደ። ከመሃል አንዳንዴ ጥናቱም ኳሱም ሲያማርረን ክብሩ አራት ኪሉ ድረስ በእግር እየነዳ ወስዶ ሐምበርገር ያበላናል። 'ሐምበርገር' የሚባል ነገር መጀመሪያ ያስቀመሰኝ እሱ ነው። ክብሩ ሁልጊዜ ኪሱ ውስጥ ገንዘብ አይጠፋም። ከሁላችንም በላሌ የሚለብሰው እሱ ብቻ ነው። በኪሱ ቢያንስ አምስት ብር* አያጣም። ክብሩ ሐብታም ነው። ታዲያ ቢያንስ በየአስራምስት ቀኑ ወይም በየሳምንቱ፣ ብዙ ገንዘብ ካለው ካፌ አስገብቶ ሐምበርገር፣ ከሌለው ሻይ ቤት አስገብቶ ብስኩት ይገዛልናል። በዚሁ በአንዱ የጋብዣ ዕለት ነው እበላው የነበረው ፓስቲ ውስጥ የደረቀች፣ ግማሽ ገመድዋ በዘይት ተጠብሶ የጠቆረ ትል ያገኘሁት። ፓስቲ ከዚያን ጊዜ በኋላ ጠላሁ። ግን ይሄ ጥላቻዬ ለጥናቴ ስኬት ያበረከተው ነገር አልነበረም።

ታዲያ ፓስቲን ስጠላው የሚሸጥበት ቤት ውስጥ ገብቶ መቀመጥም ነው የጠላሁት። ሌሎች ልጆች ግን ትሉን እንኳን ቢያዩ አላቆሙም።

የጣፈጠኝና የወደድኩትን ቅሽር ሻይ እንኳን ፈራሁት።

ታዲያ እሱ ቤት ስሄድ ሁሉን እናደርጋለን—እንጫወታለን፣ እንበላለን፣ እንጫወታለን፣ እናጠናለን። አንዱ ድርጊት በአንዱ ድርጊት ላይ ሲረባረብ ቅዳሜና እሁዳችን ሐምበርገር ይመስላሉ።

---

*ሳንቲም ብር በሙሉ ብዙ ፊት ላይ ባለው ኢራሽ ዝብሬ ስለል ምክንያት የተፈጠረ ነው።



@BOOKALEM

ጠፍጣፋ ስጋ የተቆረሰ ዳቦ መሃል ማስቀመጥ ምኑ ቁም ነገር ሆኖ እንደሚያንሰፈስፈን ስናገር ሰምቶ ክብሩ ምን አለኝ:

«አይገባሽም»

## ቦላሌ

እኔ፣ ወልዴ፣ አሰፋ፣ እንግዳ በሙሉ የምንለብሰው ቁምጣ ነው:: ክብሩ የሚለብሰው ደ'ሞ ቦላሌ ነው:: መሃል ከተማ መውጣት የማልደፍረው በዚህ አፍሬ ይሆናል:: አባቴ ታዲያ የቦላሌ ነገር ሲነሳ:

«ገና ልጅ ነህ:: ለቦላሌ አልደረስክም» ይለኛል:: ከሚክ ዘመን ነበር ወይስ አባቴ ነው?

ክብሩ የትም ባያቸው የማውቃቸው ሁለት የራንግለር ሱሪዎችና አንድ ኪሶቹ በካምሱር የተለበጡ ካኪ ሱሪዎች አሉት:: ታዲያ እሱን ለባብሶ ሲመጣ በመንፈሳዊ ቅናት ዓመዳም ጭንቅላቴ ትቦናለች:: ማንኛውንም ዓይነት ቦላሌ ስለምወድ አንዳንድ ሰሞን ምን በመሰለ ሰዎች ስለገንትና ስለሶሻሊዝም በሚያስቡበት ዕለት እኔ ቦላሌ ስመኝ እውላለሁ:: እስከ ዛሬ ልረሳው በማልችለው አንድ ትንግርተኛ ሌሊት እንደውም ከተኛሁ እስከነቃ ስለቦላሌ ሳልም ነበር:: በሕልሜ የማየው ሰው ሁሉ ቦላሌ የለበሰ ነበር:: መሪጌታ ገብረወልድ ወልደ ኢፍራታ— እኛ የሰፈሩ አዋቂ ቄስ---ጂንስ ሱሪ ለብሰው እንደ ሊ ቫን ክሊፍ ሲራመዱ አየኋቸው:: ቆመው ነበር ሜዳ መሃል:: እንግዳ ሜዳ ነው የጎል እንጨቶች እንኳን ያልቆሙበት:: ታዲያ ጋቢያቸውን ወደ ትከሻቸው ሲሰበስቡት ጂንስ መልበሳቸውን አየሁ:: በድንጋጤ ሸሽቼአቸው ሮጥኩ:: ከሁዋላዬ በከተሜ አማርኛ ሲጮሁ ሰማኋቸው:

«ወሳ አቦ ያየኸውን ለሌላ ሰው እንዳትነግር:: ከነገርክ እራውጥሃለሁ»

ስሮጥ ስሮጥ ፶ አለቃ ቱሉን አገኘኋቸው---የእንግዳን አባት---አንድ ጂፕ መኪና ጋቢና ውስጥ ቆመው መኪና ሲነዱ አየሁ:: መኪና ነድተው የሚያውቁ አይደሉም:: በዚህ ተገርሜ ቆሜ ሳያቸው ታዲያ እየነዱ ሲያልፉኝ ጂንስ መልበሳቸውን አየሁ:: ቆመው ከመንዳታቸው የበለጠ የገረመኝ ራንግለር ሱሪያቸው ነበር:: ከዚያ ስደነግጥ ሲያዩኝ:

«ለማንም እንዳትነግር በተለይ ለጄኔራል ከበደ ገብሬ:: መንገርህን ብሰማ ኢምዋኔን ትቀምሳለህ» አሉኝ:: ኸረው ብለው ደረታቸውን ነፍተው አለፉኝ::

ከ፶ አለቃ ለማምለጥ ስሮጥ አባቴን አገኘሁት:: ሙጥኝ ልለው ስንደፋደፍ አስቆመኝና: «የት ትሄዳለህ? ቀስ በል» አለኝ:: በትኩረት ሳየው የለበሰው ካቦርታ በስዕል ተሸፍኖአል:: ስዕሎቹ የተለያየ መጠን ያላቸው ጂንስ ቦላሌ ሱሪዎች ናቸው:: ሊይዘኝ ወይም ሊያቅፈኝ ሲጠጋ



@BOOKALEM

አንድ ሶስት የሚሆኑት ጂንስ ስዕሎች ከትከሻው ላይ ሙጫቸው እንደደከመ ወይም በስርዓት እንዳልተጣበቁ የወረቀት ስዕሎች ወደ መሬት እያዘገሙ ወደቁ (በሕልሜ ነፋስ አልነበረም)፡፡ በድንጋጤ መሮጥ ቀጠልኩ፡፡

«ሱሪዬ! ሱሪዬ!» ሲል ሰማሁት አባቴን፡፡ የአባቴ ድምፅ አስቃቂ ነበር፡፡

አስገራሚ ሕልም ነበር፡፡

ዛሬ ድረስ ይመጣብኛል፡፡

አንድ ቀን ክብሩ እና መንበረ ሲያወሩ ደረስኩባቸውና እስዋ አፍራ ሸሸች፡፡ ቀናሁ፡፡ ከክብሩ ጋር እንደዚህ ሚስጢር የምታወራው በላሌ ስለሚለብስ ነው አልኩ፡፡ በላሌ ያላቸው የሚወደዱ ይመስለኛል፡፡ 'ዘበናይ ማርዬ' የተባለው ዘፈን በላሌ ለሚለብሱ ዘመናዊ ሰዎች የተዘፈነ ነው፡፡ ቦለለ ማለት ዘመን ይመስለኛል፡፡ እሱ ዘመናዊ ነው ከሚሉ እሱ ቦለሌ ነው ቢሉ ይቀናኛል፡፡ ታዲያ መንበረ ክብሩን ስታዋራው እንደወደደችው ሁሉ ነው፡፡ ለምን ተጠግታ ታወራዋለች? ለዚህ ይሆናል አባቴ በላሌ የማይገዛልኝ እል ነበር---መንበረ እንድትጠላኝ፡፡

አባቴ ከእናቴ ጋር ወር በገባ ቁጥር ይጨቃጨቃል፡፡

«ተማሪ የወታደር በባይ ያስፈልገዋል፡፡ በላሌ ከለመደ አገሩን ለበላሌ ይሸጣል» አላት፡፡

«ለቁምጣስ አይሸጥም?» አለችው እሷ፡፡

አይ አንቺ ነገረኛ አለና የጫማዎቹ ማሰሪያዎች እስኪላሉ ድረስ ሳቀ፡፡

ኋ ኋ ኋ፡፡

## ጭንቅ ቀን

አባቴ የፈተናውን ቀን `የጭንቅ ቀን` ብሎ ሰይሞታል፡፡ ለምን የጭንቅ ቀን እንዳለው ባይገባኝም ያስፈራኛል፡፡ ፈተናው ሳያስፈራኝ የምፈራው ቃሉን ነው፡፡ `ጭንቅ`፡፡ ቃል አይመስልም፡፡ የኾነ ወታደር የኾነ ብሔራዊ ጦር፡፡ ታዲያ ትንሽ ዕውቀቱን ማስፈራሪያ ለማድረግ፡

«እስኪ የምታጠናውን አምጣ፣ ጥያቄ ልጠይቅህ» ይለኛል፡፡

ውረቀቶቹን ሰብስቤ እቀርባለሁ፡፡

«እስኪ እስኪ እስኪ ተንከሉኛ ነገር እጠይቅሃለሁ፡፡ መቼም የዛሬ ልጆች ዞር አድርገው ከጠየቋችሁ አትችሉባትም......ስልጣኔ የተጀመረው የት ነው?»

ስልጣኔ ምን እንደኾነ አይገባኝም።

«ኤፍራጥስና ጤግሮስ ወንዝ ዳርቻ»

«አሃ ስልጣኔ የት እንደተጀመረ ማወቅ አይከብድም። የት እንደሚያልቅ ነው የማናውቀው። የቡዲሂዝም ሐይማኖት መሪ ማነው? ስለ ሐይማኖት እንኳን አታውቁም። አሕዛብ ዘመን»

«ጉተማ ቡድሃ»

«ሃሃሀ። የግብፅ ዋና ከተማ ማን ነው?»

«ካይሮ»

ጥያቄው ቀጠለ።

«በአውሮፓና በአፍሪካ መሃል ያለው ባሕር ስሙ ማን ይባላል?»

«ሚዲትራንያን ባሕር»

ጥያቄው ቀጠለ።

«ጥሩ አጥንተሃል ጃን። እጅ ፅፈትህ ግን ተወው አይነሳ። ስክረሀ የፃፍከው ነው የሚመስለው»

«ፈተናው እኮ የምርጫ ነው»

«ቆይ ልጠይቅህ። የኮንጎ ዋና ከተማ ማነው?»

ጠፋኝ።

«ዳሬ ሰላም? ናሚቢያ? አአአ ገና እሱን ማጥናት አለብኝ»

«እንዴት ይሄ ያቅትሃል? እኔ የዘመትኩበት። ይሄ የምታየውን ሃብት የገዛልህ ኮንጎ እኮ ነው። አሁን እስተማርን ይላሉ። ቆይ ሌላ እጠይቅሃለሁ። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴር ማን ናቸው?»

«የት አውቃለሁ?»

«አየሀ ሚኒስትሪ ጭንቅ ነው»

«አልተማርንማ እሱን»

«ፈታኞቹ እኮ ተንኮለኞች ናቸው»

«ያልተማርነውን ያመጣሉ?»

«ፈታኝ ስራው ይሄ አይደለ!»

ወረቀቱን መለሰልኝ።

ከዛ፡ «ምን እየሰራችሁ ነው ከክብሩ ጋር?»

በግድ ቀውጢ ቀን የሚፈጥሩ ሰዎች ያሉ አይመስለኝም ነበር።



@BOOKALEM

መንበሬ

ክብሩ ታሞአል አሉኝ--አባቴ:: በሽታው ተስቦ ሊሆን እንደሚችልና በዚህም ሰበብ ቤት እንዳትመጣ ብለውኝ ከማን ጋር እንደማጠና ግራ ገብቶኝ ነበር:: ለሁለተኛ ቀን እሱ ቤት የሄድኩት እናቴ የአቦ ጠበል በጠርሙስ አስይዛ ውሰድለት ስላለችኝ ነው:: እናቱ ጠበሉን ከደጃፍ ላይ ተቀብለውኝ ያለእኔ አስገቡት:: ሊደፉት ያቀዱም ይመስላል:: የክብሩ እናት ከእናቴ የበለጡ ዘመናዊ ናቸው:: አንገታቸው ላይ ያለው ሐብል በመስቀል ፋንታ የልብ ቅርጽ ነው ያለው:: ይሄ ዓይነት ጌጥ የተጀመረው ኤፍሬጦስና ጤግሮስ ወንዝ ዳርቻ ይሆናል:: ምናልባት ቡድሃ ይሄ ዓይነት ሐብል ይኖረው ይሆናል እያልኩ ሳስብ ነበር:: ታዲያ ከክብሩ ቀጥዬ በጣም የምግባባት መንበሬ ስለሆነች እስዋ ጋ ሄጄ ላጥና አልኩ:: ቂም አላውቅም:: መንበሬን እወዳታለሁ::

«እሱ እኮ ይሳሳላታል» ይላሉ እናቷ እንኳን::

አባቴ ግን አይኖቹ ይቀሉና፣ «አየን ሲሳሳላት» ይላል:: ነገሩን ግን አይጨርሰውም::

እነ መንበሬ ሰፊ ግቢ አላቸው ልክ የእኛን የሚያክል ግን ብዙ ዛፍ ያለው::

ዛፉ ስር እንንበለበልና እሷ ታጠናና ሸምደዳችን ተሳክቶልን እንደሆነ ለመፈተሽ እጠይቃታለሁ:: እኔ አጠናና ደ'ሞ እሷ ትጠይቀኛለች:: ዛፎቹ ስር ደስ ይላል:: መንበሬ ደ'ሞ እንደታጠበ ልብስ ደስ የሚል ሽታ አላት:: አጥንተን ሲሰለቸን ዳማ እንጫወታለን:: የዳማ ጠጠሮቹ ከፊሎቹ ስለጠፉ በቆርኪ ተተክተዋል:: እናቷ ደ'ሞ አንዳንዴ ይታያሉ እንጂ አይነጨንጩንም:: ደጋግሜ ጉልበቷ ጀርባ ላይ ስላለው ጠባሳ እጠይቃታለሁ:: እግሮቿ እንደዚያ ለስላሳ ሆነው ለምን ለምን እዚያ ቦታ ላይ ጠባሳ እንደኖነ ግራ ይገባኛል::

«በልጅነቴ ቢላ ላይ ወድቄ ነው» ትለኛለች::

«ቢላ ያስጠላል» እላታለሁ::

«ቢላ ከጠላህ ዳቦና ስጋ በምን ልትቆርስ ነው?» ትለኛለች::

«ድንች ቀቅዬ እልበላም እንዴ» እላታለሁ::

ከዛ እንስቃለን::

አንድ ቀን ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ አባቴ ከስራ ሲመጣ እዚህ ፖስታ ቤት ያለው መከላከያ ሚኒስቴር ነው የሚሰራው፡

«የት ሄደ?» ብሎ እናቴን ይጠይቃል

«መንበሬ ጋ ሊያጠና ሄደ» ትለዋለች እናቴ::



@BOOKALEM

ምንም ሳይናገር ከቤት ይወጣና በቀጥታ መንበረ ቤት ይመጣል። የመንበረን ቤት አጥር ገፍቶ ይገባና እናቷን እንጨት ሲፈልጡ ያገኛቸዋል። ፈለጣ እንኳን 'ልርዳዎት' ሳይል ስለእኔ መናር ይጠይቃል። ጓሮ መሆናችንን ይነግሩታል።

ወደአለንበት ሲመጣ ስናየው የሚጠረጥረውን ስለምናውቅ ከችኝ አልን በድንጋጤ።

ምን ይናገር? ምን ብሎ ይውሰደኝ?

«ና ምሳህን በልተህ ትመጣለህ»

«እሺ»

ያንን ዕለት አልተመለስኩም። ግን በደንብ የተመለስኩበት ጊዜ ይመጣል። (የመጨረሻውን ምዕራፍ እጢን)

(ትዝ የሚለኝ የማልናገረው ዛሬ ድረስ በሆዴ የማብሰለስለው የዚያ ጓሮ ትዝታ አለ። ትዝታም ሳንሱር ይደረጋል እኮ። በፀሐይ የተዝጎረጎረ የወይን ዛፍ ጥላ ስር እኔና መንበረ ተንበልብለን። የደብተራችን ነጭ እንደ ግስላ ቆዳ ተዝጎርጉሮ። እሷ በሆዷ ክርናቿን ተደግፋ ሳለች ገና ተሰርተው ያላለቁ ያኮረኮሩ ጡቶቿን በላላ የቀሚሷ አንገትጌ በኩል እጨለማ ውስጥ አጮልቄ አሞጥሙጠው እያየኋቸው። ጨርቋ ተሰብስቦ የጭኗ ግማሽ ተራቁቶ። እግሮቿ በፀሐይና በጥላ ተዝጎርጉረው። የማይታዩ መዓት ንቦች የወይን ሐረግ ውስጥ ሲንዛዙም እሰማቸዋለሁ። ይኼ ሁልጊዜ መንበረን ሳስብ የሚመጣልኝ ምስል ነው። መንበረ፣ ንብ፣ የወይንዛፍ ጥላና የቅጠሎች ጠረን፣ በከፊል የተራቆቱ ቀይ ዳማ ጭኖች። ብዙ ነገሮች አይደሉም ግን ስምዋ ሲነሳ ወይ ከአራቱ ነገሮች አንዱ ሲጠራ ስሰማ ወይ ሳይ ትዝ ትለኛለች)

*ዎዎዎ*

ከመንበረ ጋር መለያየት ቢያቅተን ወደ እኛ ቤት እንድትመጣና እንድናጠና ተነጋግረን መጣች። ታዲያ ከመሃል 'ተለከፉ' ሲለን ዘፈን መዝፈን ጀመርን። መልካም ድምፅ ነበረኝ። የምዘፍነውን ዘፈን ትርጉም ግን አላውቅም። ከመንበረ ጋር በሕብረት በቶክክር ዓይነት የቶም ጆንስን እንግሊዘኛ ዘፈን «ሺ ኢዝ ኤ ሌ ዲ»[*] የሚለውን ስንዘፍን ዳንስ ቢጤ ስንውረገረግ አባቴ በር በርግዶ ይገባል። ክብሩ ቤት ነው ዘፈኑን የሰማሁት። ክብሩ የማያውቀው የፈረንጅ ዘፋኝ የለም።

«ሺ ኢዝ ኤ ሌ ዲ *ዎዎዎዎዎ*» ስንል ስድስተኛዋ 'ዎ' ላይ ያዘን።

---

[*] she is a lady

«ጉድ! ጉድ! ምን ቢያደርጓችሁ ይሻላል? ፈተና ሲደርስ እናንተ አዝማሪ ትሆናላችሁ:: ፍየል ከቀዘነ ተማሪ ከዘፈነ ብላሽ ነው»

«አይ ለማረፍ ነው» ስንለው:

«ኳሱን ማን ገደለው?» ብሎን እርፍ::

እናቴ ስንዘፍን እየሰማችን ዝም ማለቷ አብሽቆት ምናልባት ለግማሽ ሰዓት ያህል አዝማሪነትና ሚኒስተሪ ፈተና እንደማይገናኙና አዝማሪው አዝማሪ የኾነው ሚኒስትሪ ማለፍ ስላቃተውና ከዕውቀት ይልቅ መሸታ ቤት የሚወድ በመሆኑ እንደኾነ ሲያብራራላት ቆየ:: ‹ዘፈኔን የዘፈኑትን ልጆች ትንሽ እንኳን ልርዳ› ብሎ ከፈረንጅ አገር ሳትታይ ፊቷን እያዞረች ትስቅ ነበር:: እንደማይመጣ አሁኑኑ ማወቅ ያስፈልጋል እያለም አሸፈ:: መንበረ

«ቢችሉ ምን አለበት የባህል ቢዘፍኑ:: ጉራጊኛ መልካም ነው:: ዶርዚኛው ምን አለ? እንቺስ ጋልኛ አታሳዪውም:: አገርሽ ሆሲታ ብዙ የባህል ዘፈን አለ:: እስክስታውስ ምን አጠፋ» አለ::

«የሚያውቁት ይሄ ነው:: እንግዲህ አፋቸውን በማሰሪያ ነገር አላሰረው:: ሲያጠኑ አይቻቸዋለሁ» አለች እናቴ::

ዛሬ የምጠላው ዘፋኝ ቶም ጆንስ ነው:: ቶማስ ሀርዲ የሚባለውንም ደራሲ እጠላዋለሁ:: ቶማስ ኤድሰን የሚባለውንም ፈልሳፊ እጠላዋለሁ:: ቶማስ የሚባለውን የክርስቶስ ተከታይ እጠራጠረዋለሁ:: ያን ዕለት የቀመስኩት ኩርኩም ሃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ ከጭንቅላቴ መብራት ሳይወጣ አይቀርም:: ዛሬ ድረስ እሱን ቦታ ስንነካው ‹ይፋጃል› የሚሉ ሰዎች አጋጥመውኛል::

## አብደላ

መርካቶ አብደላ ሱቅ ቢያንስ በወር አንዴ እንሄዳለን ከእናቴ ጋር:: የኾነች ሞላላ የምታስቅ ዘንቢል አለቻት:: እስዋን አንጠልጥልና ከሁዋላዋ ኩስ ኩስ እያልኩ መርካቶ አብሬአት እዞርና ሲደክመኝ አብደላ ሱቅ ወስዳ ታስቀምጠኛለች:: አብደላ ሱቅ የስኳር ጆንያ ላይ እቀመጥና ዕቃ የተሞላችው ዘንቢል እንዳትሰረቅ እግሬ ስር አድርጌ እናቴ ከሔደችበት እስክትመጣ እጠብቃለሁ::

ብዙ ጊዜ ሊትሮ ዘይት፣ መዓት ድንች፣ በድርብርብ ቅጠል የተጠቀለለ (ቅጠሉ በኋላ ‹የጉሎ ነው› ተባልኩ) ፓሎኒ ኳስ የሚያክል ቅቤ፣ የተዘረገፈ ቀይ ሽንኩርት (ተከትፎ በጥሬ ዘይት የተለወሰ ቀይ ሽንኩርት በደረቅ እንጀራ መብላት እወድ ነበር) በካኪ ወረቀት ቦርሳ ውስጥ ኪሎ የሚሆን ፓስታ (አባቴ ይወዳል)፣ 777 የተባሉ



@BOOKALEM

ሳሙናዎች፣ በንጭ ሎጋ ጠርሙስ የበጉር ቅባት፣ ምላጮች......በትንንሽ ላስቲኮች የታሰሩ ቅመማት (የሁሉንም ስም አላውቅም ከአንዱ በስተቀር:: የሌሎቹን ጥቅም አላውቅም---አንደኛውን ግን ምንም ሳይለወጥ ዳቦ ውስጥ አገኘዋለሁ)::

አብደላ እየደጋገመ ተምር ይሰጠኛል:: የበላሁትን ሳልጨርስ::

እናቴ ትታኝ ስትሄድ ውስጥ ልብስና የአንገት ልብስ ልግዛ ብላ ነበር:: ስትመለስ ግን አንድ ውስጥ ልብስና ብርማ ቀለም ያለው የምላ መያዣ ቆርቆሮ ይዛ መጣች::

«ሰው ሲታመም ለመጠየቅ ያመቻል» አለችኝ ምላ ሰሃኑን አገላብጣ እያየች:: ምላ መያዣው የራሱ ቁልፍ አለው:: እንደዚያ ዓይነት ዓይቼ አላውቅም::

«በመንገድ ይብላ» ብሎ በጋዜጣ የተጠቀለሉ ተምሮች አብደላ ሰጠኝ::

«አለው ይበቃዋል:: ጥርሱን ያበላሻል» ብላ አስመለሰችው::

ዞር ብዬ አብደላን በፍቅር ዐይን አየሁት:: እኔን እያየ ጣቶቹን ሳመ:: እናቴ ምቀኛ አልኾነችም?

ዘንቢልዋን `ይከብድሃል` ብላ አነሳችና ራሴን ደባበሰችኝ:: ሕዝብ መሃል ሲደባብሱኝ አልወድም:: ልጅ የሆንኩ ይመስለኛል:: ከምትደባብሰኝ ተምሩን እንድበላ ብትፈቅድልኝ ይሻለኝ ነበር:: የምላ ሰሃንዋን አንጠልጥዬ እያንኳኳሁ ራቅ ብዬ ከኋላዋ እየተከተልኩ አቶቡስ ተሳፈርኩ:: በአቶቡስ መሄድ ደስ ይለኝ ነበር:: በተለይ በመስኮት በኩል ተቀምጬ አንዳንዴ ጭንቅላቴን ብቅ እያደረግሁ የሚጋፋ ጥቁር አየር እየለጠጥኩ:: ግንባሬ ላይ የተሰበሰበው ፀጉር እየተውለበለበ:: እንደውም ብዙ ጊዜ ወደ አቶቡሱ ውስጥ አላይም::

የአብደላ ልጅ ዛሬ መርካቶ አለ:: ግን ቴምር ለልጆች አይሰጥም:: ደንበኞች 'ልጅ ጠብቅልኝ' ሲሉት አይጠብቅም:: ሱቁ ውስጥ የሚነግዱት የሚያስፈራ ውበት የተጎናፀፉ ደስ የሚሉ ቆንጆ ልጃገረዶች ናቸው:: ሚኒስትሪ የሚባል ነገር እንዳልተፈተነ ሰምቼአለሁ:: ሱቁ ፊት ለፊት የሚቆመው መኪና ግን ውሃ የፈሰሰበት መስታወት ይመስላል:: አብደላ የመንበረ እናትም ደንበኛ ነበር::

## የምሳ ሳንቲም

አባቴ ወንበር ደገፍ ብሎ ተቀምጦአል:: ጡንቻማ ክንዱን ጠረጴዛ ላይ አጋድሞአል::

(«አንተ አባትህ ትንሽ ክብደት ቢያነሱ ግርማ ቸሩን ነበር የሚያክሉት:: ምነው ቀጫጫ ሆንሽ?» ይሉኝ ነበር ጓደኞቼ)

ፊቱ ጠማቦ የበሳ ይመስላል:: ጠረጴዛ ላይ ፊት ለፊቱ በቅቤ ያበደ ቂጣ ፍርፍር የበላበትን ጎድጓዳ ሰሃን ጉዳይ እንዳለው ሰው በትኩረት ያየዋል:: ለምን ያየዋል? ስል ነበር:: የበላበትን ዕቃ ሁልጊዜ እንደ መፅሐፍ ወይም ስዕል ያየው ነበር::

«ነገ ፈተና ስለኾነ እርሳስና ላፒስ ብቻ ትወስዳለህ:: እና ለምሳ የሚሆን ሳንቲም እንካ» አለና ጠረጴዛ ላይ ሁለት ስሙኒዎች አስቀመጠ::

ከዛ ቀጠለና:

«ለክብሩም ይበቃል ይሄ:: ተካፈሉ»

«የት ነው የምበላው?» አልኩ

«ምን የማታውቅ ትመስላለህ:: ከክብሩ ጋር ሻይ ቤት አይደለም የምትውሉት? ሻይ ቤት ነዋ»

«አልፈልግም ሻይ ቤት» አልኩ

«አ አ ታዲያ ገነት ሆቴል ትፈልጋለህ? ምንድነህ አንተ? ልዑል መኮንን?»

«አልፈልግም:: አልወድም»

«ኩራት ነው ምንድን ነው?»

«ስለማልወድ ነው»

«ሻይ ቤት የማትወድ ኡሪ አንተን አየሁ:: ታዲያ ምሳህን ውሰዳ»

«አልሸከምም» ምሳ መሸከም ይደብረኛል::

«ፈተናና ረሃብ አብሮ አይሄድም»

«እቤት እመለሳለሁ»

«ጊዜ አለህ?»

ዝም አልኩ::

«እኔ ምሳህን አመጣልሃለሁ» አለች እናቴ::

«የዕረፍታቸውን ሰዓት ታውቂያለሽ? እሷንም አስለፍተህ ደ'ግሞ ፈተናም እንዳትወድቅ»

«የት አውቃለሁ ሰዓቱን»

«ስንት ሰዓት ላይ ነው ለምሳ የምትወጡት?» አለ አባቴ::

«ስድስት ሰዓት ላይ»

«ሰው ታስቸግራለህ:: እንደሌሎች ልጆች ሁን እንጂ»

«አታስጨንቀው»



@BOOKALEM

## ሳጥ

ለፈተናው ዕለት ጠዋት ላይ ክብሩ ቤት ሄድኩ:: የምንፈተንበት ትምህርት ቤት ያው አንድ ስለነበር አብረን ለመጓዝ:: የክብሩ አባት ገና በፒጃማ ነበሩ:: በረንዳ ላይ ቆመው ሲጋራ እያጨሱ ነበር:: ግቢው ውስጥ ስገባ:

«ታዲያስ ጎረምሳው:: ዓመት ሙሉ የለፋችሁበትን ዛሬ እናያለን:: ሁለታችሁም ሳጥ አድርጋችኋት እንደምትመጡ ተስፋ አደርጋለሁ» አሉ:: ደስ አለኝ::

እናቴ ከቤት ስትሸኘኝ:

«መኪና ተጠንቀቅ እንደለመድከው ስትንቀለቀል እንዳትገጭ»

የክብሩ አባት በግራ እጃቸው ሲጋራቸውን ይዘው በቀኝ እጃቸው ጆሮዬን ሳብ ሳብ አደረጉት:: እያምም:: ክብሩ ከቤቱ እየሮጠ መጣና ከግቢው እየጎተተኝ ወጣን:: ብርድ ነበር:: በቦርሳችን ውስጥ ሁለታችንም የያዝነው እርሳስና መቅረጫ ብቻ ነው::

ፈተና የምንሰጥበት ትምህርት ቤት ስንደርስ አንድም ተማሪ አልነበረም::

«ለምሳ ገንዘብ አምጥተሃል እንዴ?» አለኝ ክብሩ

«አላመጣሁም:: ሻይ ቤት ሄጄ ትል አልበላም» አልኩት

«አትረባም» አለኝ

ተማሪዎች መፈተኛ ግቢውን እየሞሉት የሚያበሽቅ ነገር መስራት ጀመሩ:: እኔና ክብሩ እንሸሻለን::

ዕውቀታቸውን ይፈታተሻሉ::

---የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሤ ስም ማነው?

---ተፈሪ መኮንን

---የተወለዱበት ቦታ ማን ይባላል?

---አይያዝልኝም

እኔና ክብሩ እየተያየን እየሸሸናቸው እንሳሳቃለን::

## የሚያበራ ምሳ

ፈተናው በሁለት ክፍለ ጊዜ የተሸነሸነ ነው:: ጠዋትና ከሰዓት በኋላ:: ጠዋት መሃል ፈተና ላይ ራበኝ:: ምናልባት አምስት ሰዓት ቢሆን:: ምሳዬን አለማምጣቴ ቆጨኝ:: እናቴ ስራ በዝቶባት ሳትመጣ ትችላለች:: ፈተናው ያልጠበቅሁት ዓይነት ቀላል ነበር:: ጥያቄዎቹን



@BOOKALEM

እየመለስኩ 'ሚኒስትሪ የሚባለው ይሄ ነው እንዴ? ለምን 'የጣዕር ቀን መጣ' ይላል እላለሁ ለራሴ:: እላለሁ:: አባቴ

የጠዋቱን ፈተና ጨርሰን ስንወጣ ክብሩና እኔ በደስታ ስለ ፈተናው ቀላል መኾን ስናወራ ዓይኖቼ ላይ......ከኾነ ዛፍ ስር ቆርቆሮ ፈለቀባቸው:: እዚያ ብርሃን አጠገብ እናቴ ቆማለች:: ክብሩን ትቼ ወደ እሷ መሄድ ጀመርኩ:: እናቴ የክብሩን አብሮኝ አለመምጣት አይታ እየተበሳጨች ትጠራዋለች::

«ክብሩ!! ክብሩ!!»

እሱ ሻይ ቤት መብላት ነው የሚፈልገው::

«ከሰዓት እንገናኝ» ብሎኝ ስትጠራው እንዳልሰማ ሁሉ ለእናቴም ሳይመልስ ወደ ውጭ ወጣ::

«ይሄ ጥጋበኛ:: ጥጋባቸው እኮ:: የቤት ሽሮ አይሻልም ከማይረባ ሆቴል:: አባቶቻችሁ እየመሩአችሁ ምን ታድርጉ እናንተ» እያለች ስታማርር እሷ ጋ ደረስኩ::

ምሳዬ የመጣው ያ ከመርካቶ በገዛነው ቆርቆሮ ነው::

እዚያ ቦታ የነበረችው ወላጅ---እናቴ ሉል ብቻ ነበረች:: የተዘባረቀ ስሜት ተሰማኝ:: ሜዳውን ከከበቡት ዛፎች ሰፊ ጥላ ያለውን መርጣ ከእሷ ጋር እዚያ ስር ሄድን:: ብዙ ተማሪዎች ተከተሉን:: ስለ ፈተናው ያወራሉ:: አስጠልቶኝ ጆሮዬን መድፈን እፈልጋለሁ:: እናቴ ስለፈተናው አንዲት ቃል አልወጣትም:: እኔም ገና ከሰዓት በኋላ ስለምፈተን በትምክህት ልነግራት አልፈለግሁም:: ያመጣችልኝ በቅባት የነደደ ምስር ወጥ ነበር:: በቅባት የነደደ:: ከምስሩ ፍሬ ደሞ የማፈቅረው መረቅ የጠጣውን እንጀራ:: ደስ አለኝ:: እሱን እንደ አሳማ ዋጥኩ:: እናቴ አበላሌን እያየች ፈገግ ትላለች::

ምሳዬን ጨርሼ ለመታጠብ ቧንቧ ፍለጋ ሄድኩ:: ተመልሼ ስመጣ እናቴ ኒኬሉን ገጣጥማ ወደ ቤት ለመመለስ ቆማ አገኘኋት::

«በል ስራ አለብኝ:: በርታ» አለችና ራሴን ዳበሰችኝ:: ተናደድኩ:: የበለጠ የተናደድኩት አጠገባችን ያሉ ምሳቸውን የሚበሉ ሌሎች ልጆች ስትደባብሰኝ ሲያዩ ነው::

## እንደ ሁንዴ ጡሬ

ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ከፈተናው ስንወጣ ክብሩ ዘሎ አንገቴን አቀፈኝ::

«ደፈንሽ አይደለም»

«አንተ ነህ የምትደፍነው»



@BOOKALEM

ከፈተናው ቦታ ተያይዘን ስንሮጥ ሌላ ጊዜ ግማሽ ሰዓት የሚወስድብንን መንገድ በአምስት ደቂቃ ጨረስናት:: እቤት ያገኘሁት እናቴን ነበር:: ስለፈተናው ቀላልነት ነገርኳት::

«እሰይ የእኔ ልጅ» አለች አስር ጊዜ:: ክብሩ ቤት ተመልሶ መጣና እናቱ ሻይ እንደሚያፈሉልን ነገረኝ:: ሳሉን ተቀምጠን ምን የመሰለ ዳቦ በሻይ በላን:: እሱን ጨርሼ ለአባቴ ስለፈተናው ልነግረው ወደቤት ሄድኩ:: ገና ገብቶ ኮቱን ሲያወልቅ ደረስኩበት:: ስለ ፈተናው ቀላልነት በደስታ ነገርኩት::

«አትቸኩል:: መስከረም ሲደርስ እናውቃለን:: ስትዘሉና ስትጨፍሩ ነበር አሉ ከክብሩ ጋር»

ዝም አልኩ:: ሚኒስትሪ ቀውጢ ቀን እንዳልኸነ ለመንገር ያሳየሁት ጥረቴን ያበላሸው መሰለኝ::

«እናንተ ቤት ገብታችሁ ሻይ ጠጥታችሁ ስትጨርሱ ከእናንተ ጋር የተፈተነው ተማሪ ገና ሠፈር አልደረሰም:: ምን ትቸኩላላችሁ? ደ'ሞ እንዴት ብትሮጡ ነው እንዲህ በፍጥነት እዚህ የመጣችሁ:: እንደ ሁንዴ ጡሬ ሮጣችሁ መኾን አለበት:: አንደኛውን ኦሎምፒክ አትገቡም?»

ከአባቴና ከንግግሩ አምልጬ ወደ ሰፈሬ መንደሮች ገባሁ:: ክብሩንና ሌሎችን ሜዳ አገኘኋቸው:: አሪፍ ቀን ነበር:: እንዲህ ዓይነት የሚያምር ግንቦት እስከ ዛሬ አላየሁም::

## ልጥፍ ኪስ

ፈተና በተፈተንን በሳምንቱ እናቴ ሜዳ ድረስ መጥታ ጠራችኝ::

ቤት ገብቼ ሳልቀመጥ አባቴ ጠረጴዛ ላይ በወረቀት ተጠቅልሎ የተቀመጠ ነገር እያሳየኝ:

«እስኪ ይሄን ሞክረው» አለኝ::

በቀስታ ወረቀቱን ስተረትር ልብስና ቆዳ ጫማ ወጣ::

«ከክብሩ አባት ጋር ተነጋግረን ፈተና ጥሩ ሰርታችኋል አለኝ:: ክብሩ ግን ሳይበልጥህ አልቀረም:: እሱ የተማረ አባት አለው:: ስለዚህ ይሄ ሳያስፈልግህ አይቀርም»

ጂንስ ጃኬትና ቦላሌ ሱሪ እና ጫፉ ሹል የኾነ ቺፖሊኒ ቆዳ ጫማ::

ሱሪው የመጀመሪያ ቦላሌዬ ነው:: ግን የበለጠ የተደሰትኩት የሱሪው ኪሶች በሙሉ ልጥፍ በመሆናቸው ነው:: ጃኬቷ ገላዬ ላይ ልክክ ያለች ናት::

«ሲያድግ እኮ ሸንጣም ነው የሚኾነው ልጄ» አለች እናቴ::

ጫማው ትንሽ አፍኖኛል፤ ልክ ሳንባዬ አውራጣቶቼ ውስጥ እንዳለ ሁሉ::

«ሱሪው ትንሽ ረዝሞአል:: ፋላስ ያሳጥርልሃል» አለ አባቴ:: (ፋላስ የሰፈራችን ልብስ ሰፊ ነው:: 'ሰው ሲታመም ወደ ቀኃሥ፣ ጨርቅ ሲቀደድ ወደ ፋላስ' ይባላል በሰፈር ተረብ)

## ጨቅጫቃ

ብዙ ጊዜ በተለይ ማታ ማታ እንዲህ አስብ ነበር:: ስለምንድነው አባቴ ጨቅጫቃ የኾነው?

* * *

## ለመሆኑ የኔታና ልጅት መንበረስ?

አንድ ጠባብ ግቢ አለ:: የቆጠባ ቤት የሚባል:: ወፌ-ገንት የሕብረት ሥራ ማሕበር ያሰራው:: እዚህ ጠባብ ግቢ ውስጥ አንድ ጋዜጠኛ ከሚስቱና ከአምስት ልጆቹ ጋር ይኖራል:: ግቢውን ደ'ሞ ገና ለጋ ለማደግ የሚቅበጠበጡ ፅዶች አጥረውታል (ምን አስቸከላቸው? ማነው እሱ አንድ ወዳጄ ተረት ነበረው «የጽድ ችኩል ማዕዘን ይሆናል» ያለኝ፣ መሞቱን ፈጥኖ ይደርስበታል ሊል):: በወዲያ በኩል ያለው ጎረቤት ከሰኞ እስከ እሁድ ጌሾ ጌሾ የሚሸት ስካራም ወይም ቆጠባ ቤት መስራት የማይገባው ቆጣቢ ያልኾነ ሰው የሚኖርበት:: በግራ በኩል ግቢው ሰው ያልሠፈረበት በረሐ የሚያስመስለው ጭርታና የዱባ እርሻ አለ:: እመ—ወራዋ ያለ ዱባ አትበላም («ምን በመሰለ የኑግ ዘይት የተሰራ በስሉም ግን ያልፈረሰ ዱባ በለምለም እንጀራ ከመብላት የተሻለ ምን አለ? ያንተን ምስር ወዲያ በልልኝ» ትላለች ዶክተር መንበረ):: በቀኝ በኩል ጋዜጣ ቆጭ ብሎ የሚያነብ ሰው አለ:: ሰውዬው ከመዳብ የተሰራ ሐውልት ነው:: የአባ ወራው የመጀመሪያ ልጅ ከሥነጥበብ ት/ቤት ትምህርቱን ሲጨርስ ለመመረቂያ የሰራው:: በቤቱ ጠፈጠፍ ዙሪያ ሳያቋርጥ እያለከለከ የሚሮጥ በከፊል እንደ ውሻ በከፊል እንደ ሰው የሚሰራው ፀጉረ-ቢጫ ከለውቱ እንስሳ አለ:: የብረት አጥሩ መሃል ላይ «እዚህ ቤት ተናካሽ ውሻ አለ ይጠንቀቁ!!!!» የሚል ማሳሰቢያ ተለጥፏል (አራት የቃለ አጋኖ ምልክት ለምን አስፈለገ?):: ይሄ ማስጠንቀቂያ በትክክል ምን ማለት እንደኾነ ባለቤቱ ራሱ አይገባውም:: ምክንያቱም ውሻው ሰው ላይ ከመጮህ ይልቅ ሳያቋርጥና ሳያርፍ ቤቱን መዞር ነው የሚወደው:: ይሄን ባለቤቶቹም ጎረቤትም ያውቃል:: ቤቱ ማሪያ ላይ በስተግራ በኩል ጭስ መውጫ የተደገፈ ዘመም ያለ የቴሌቭዥን አንቴና አለ::

ቢያቃኑት ሁልጊዜ የሚዘም:: እንዲህ የሚኾነው ነፋስ እያጋደመ ይሁን ወይ ተቀብሎ የሚያቀብለው እያስመረረው ገና ማረጋገጫ አልተገኘም:: የቤቱ ግድግዳ ጠርዞቹ ሸክላ ሲሆኑ የቀረው ብሎኬት ሲሚንቶ ነው:: የአጥሩን በር አልፈን ስንገባ ሁልጊዜ የሚሰማ ምንም ነው:: ፀጥታ:: በረንዳው ላይ የቀርከሃ ወንበሮች አሉ:: ማ ማታ አባወራውና እመወራዋ ጋቢ ተከናንበው ይቀመጡበታል:: እዚ ከተቀመጡ ለማንም የሚታየው የወጨጫ ተራራ ደብዛዛ ጉብታ ነው::

ያቺ የምታምረው ፀሐይ ማታ አስራሁለት ሰዓት ላይ ማር መሰ ብቅ ስትል ብዙ ጊዜ ከጋቢ ጭንቀት የሚላቀቀው የአባወራው እጅ ወደ እማወራዋ ይሳብና ተስቦም ታላቅ የወላድ ጭኗን ጨብጦ ጨብ ያደርጋል:: እማ ወራ ደ`ሞ «አንተ......እይ ያንተ ነገር......እ ዩ[10]......እ ዩ[11]» ትልና ያ ስካራሙ ጎረቤት በቀኝ በኩል በግራ ደ`ሞ እነዚ ለቃሚያቸው የዘገየባቸው ዱባዎች ሁሉ እስኪሰሙ በሳቅ ትንከለከላለች:: አባ ወራውም እጇን ስቦ ምዐምዐምዐምዐ እያደረገ እየሳመ:

«ገባ እንበል እንጂ......ገባ እንበል እንጂ—የእኔ ምስር» ይላል::

ከልጅነቱም በምሽት ፀሐይ ልቡ ይንቃቃል:: ከቤቱ ጀርባ አጭር ሰርቪስ ቤትና ቆሻሻ መድፊያ ስፍራ አለ:: ቆሻሻው የሸንኩርት ልጣጭ ይበዛዋል:: አባወራው አንዳንዴ ቆሻሻው የሸንኩርት ልጣጭ እንደ በዛው ያይና ይገረምና ራሱን ይጠይቃል:

«ስለምንድነው ቆሻሻዬ የሸንኩርት ልጣጭ የሚበዛው?»

ቤቱ አምስት ክፍሎች አሉት:: በጣም ንፁሕ ነው:: በዋናው በር ሲገ በስተግራ መኝታ ቤታቸው ነው—የወራዎቹ:: ቀዝቀዝ ያለ ነው:: እዚ የሚሰማው ድምፅ በውስጡ ሲረማመዱ የራስ ጫማ ኮቴ ብቻ ነው:: ፊት ለፊት አንድ ፋሚሊ አልጋ የክፍሉን ግማሽ ሞልቶታል:: በስተቀኝ ባለመስታወት ቁምሳጥን ነው:: በስተግራ ቢፊ አለ—ዶክተር መንበሬ ብ ትራትንቦ የምታስቀምጥበት::

አምስት ልጆች አሏቸው:: ትምህርት ቆመ አልቆመ ቤቱ በጫጫታ ይሞላል:: ብዙ ጊዜ ከእነዚህ ዓይነት አደንቋሪ «ደመኅለት» ለመራት እናትና አባት ዱካቸውን አጥፍተው ወደ መኝታ ክፍላቸው ይገቡና አልጋቸው ላይ ይጋደማሉ:: እርጅናቸውን እየተሻሹ:: «ተወ እንጂ ተው እንጂ» እየተባባሉ:: በልጅነቷ ጊዜ ሳይሆን ሚስቱ ሆና ሲያውቃት ጀምሮ «ተው እንጂ......ተው እንጂ» እንዳለች:: ግን አትተወው:: ደጓሳ ገላዋን......ከውስጡ አምስት የከፈለውን......አል ላይ ስትጥል:

[10] እይ አንተ (እንግሊዝኛ)

[11] ዝኒ ከማሁ

«ምንው መንበረ ወለል ላይ ልትገለብጭኝ አቅደሽ ነው?» ሲላት እንደ ተናደደ ሁሉ በሚያስቅ ደካማ ቦክስ/ ቡጢ «ቴክ ዚስ[11]፣ ቴክ ዚስ፣ ቴክ ዚስ» እያለች ጀርባውን ደቀስ ደቀስ ደቀስ ታደርገውና ከነተሚሷ ብርድልብስ ስር ትገባለች::

ፊት ለፊታቸው ደ`ሞ ቁምሳጥን ተከልላ የተንጣለጠለች ተአምረኛዋ የኔታ አለች:: መንበረን እንደሚያገባ ሲናገርና ሲታወቅ አባቱ በኮንጎ ጦር የቆሰሉትን ከንፈሮቹን ወደ ጎን አጣሞ «የጀመርኩትን ልጨርስ ብሎ ነው» አለ አሉ:: ነፍሱን ይማረው:: ግን መንበረን ብቻ ከልጅነቱ አልወሰደም:: መንበረን ሚስቱ እንድትሆን እንደተመኛት፣ የኔታን ደሞ---ሁሉ ለምን ደረሳል?---ግድግዳ ላይ:: እምስቱንም ልጆቹን ይወዳቸዋል:: ትልልቅ ነገሮች ተምረው ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ስለ የኔታ ታሪክ ይነግራቸዋል::

«ይህቺ አለንጋ ቀላል ትመስላችኋለች:: ከላሊበላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም የተገኘች ናት:: ያሬድ አልማርም ብሎ ከትምህርት ቤት ሲሸሽ በአስተማሪው የተገረፈባት:: እመኑኝ:: ከናፖሊዮን ቦናፓርት ትበልጣለች:: ምክንያቱም ናፖሊዮን ያመ ድንን አልሻፈም»

«እ እ እ ጀመረው:: ጀመረው ዳዲ:: ድን ድን ይላል:: ስለ ድን ታውቃለህ ራስህ??»

---- // ----

*ታሕሳስ 1987*
*አዲስ አበባ/ሆላንድ*

[11] ይሄን ወሰድ/እንካ ቅመስ(እንግሊዝኛ)

@BOOKALEM

# ደብዳቤዎች

*03/07/79*

*ለፅጌሬዳ ሐብታሙ*

*ፖ.ሣ.ቁ 0000*

*አዲስ አበባ*

*ሰላሜናሽ እንደምን ከርመሻል? ሦስት ሳምንቶች ያህል ከጠፋሁብሽ በኋላ በዐይን ሲጋ ሣይሆን—እንዲህ በወረቀት፣ በቀለምና በሆሄያት፣ በፖስታ ላናግርሽ መኾኔ ግራ ሳይሆንብሽ አይቀርም:: ግን አሉ በዐይን-ሥጋም ተገናኝ፣ በዐይን-ሕሊናም ተገናኝ እተብቀው በማይተዋወቁ ሰዎች መሃል የሚተም መግባባት ሊኖር አይችልም:: እንደ በሰል ቀለም ፈደላትን ማዘዝ ባልችልም......ላዋይሽ የምፈልገው ጉዳይ ዕንብርቱ ላይ ማነጣጠር ባልችልም......ሽታው እንዲደርስሽ ለማድረግ እሞክራለሁ::*

*ስለእንቺ ያለኝን ርዕዮት የፈጠርኩበት መንገድ የከረመና ረዥም ነው:: እንቺን ያወቅሁሽ ከእንቺ ጋር መገናኘት ከመጀመሬ በፊት ነው:: ልጅ እያለሁ፣ ጎረምሳ እያለሁ::*

*አባቴ አናጢ ነበር:: (ይህ አይነት አጀማመር እንኩዋን ጥሩ አልነበረም፣ ይሁን ግን)*

*ሰድሜዬ አሥር አካባቢ ሲሆን ረዥም ሕንፃ ከሚጠግንበት ርብራብ ላይ ወድቆ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: በዚህች አንዲት ገጠመኝ የተነሳ ሁለት ሀይነት አባቶች አወቅሁ:- በሕይወት ያለ— እንጨት የሚልግ፣ ድንጋይ የሚቀጠቅጥ እና ሞቶ የፈተ ቆዳ የደረቀ፣ የዕድ ሳጥን ውስጥ የተሰነቀረ......*



@BOOKALEM

ከባድ ስሙቀት ነው:: ልጅ ከሆኑ ደግሞ ሕሊና ውስጥ ተጠብሶ ይታተማል::

ሳይዘገይ እንጀራ አባት መጣ—አሥረኛ አመቴን አልፌ::

አንቺ ባለአንድ አባት ነሽ:: እኔ ሁለት አባት ነበረኝ……ሁለት እናትም:: ሁለት እናት ለምን አልኩሽ? ምክንያቱም እናቴ ተለወጠች:: እናት ይለወጣል:: በባልዋ ላይ የተደገፈች ስለነበረች (ከገንዘብ እስከ ወሲብ) የባልዋን አስተያየት መያዝ ነበረባት:: ተቃወመች:: መደሰቴን ተቃወመችኝ::

አሥራ አንድ አመቴ ነበር……

የአባቴ ወንድም አጐቴ መሰቃየቴ አሳዝኖት ይሁን በኋላ በሰማይ ለሚወርሰው ቦታ አስቦ ወደ ቤቱ ወሰደኝ:: አሁን ሲያወራ `ሰው ያደረኩት እኔ ነኝ' ይላል፣ የኑሮ ነገር ትንሽ እንደቀናኝ ሲያውቅ:: በየመሃሉ ትንሽ `ተሳስቼ' ሳበሳጨው `አንተን ለማምጣት ሞላሌ የወረድኩበትን እግሬን ጉሳ ሚካኤል በሰበረው' ይለኝ እንዳልነበር::

አዲስአባ ለትምህርት ስመጣ አጐቴ በፖስታ ያሌታሸገ የአደራ ደብዳቤ ፅፎ ወደ ዘመድ መራኝ:: እነዚህ ዘመዶቼ መልካቸው እንጂ ነጠላ ፀባያቸው ከአባቴ፣ ከእንጀራ አባቴ፣ ከአጐቴ ጋር የሚተራረብ ነበር::

---ሁሉም ተመሳሳይ ለኸኑ ነገር ይሥቃሉ (የሚለዩበት ነገር ቢኖር አንዱ ገጣጣ ወይ አንዱ ድዳም ይሆናል)

---ሁሉም ምላስ አላቸው (ቡና ይጠራሩበታል፣ ይሙቡታል፣ ይሸሚጥቡበታል፣ ይሳደቡበታል)

ላውቃቸው ግን ተበፋ አልቆረጥኩም::

ዕድሜዬ 16 ደረሰ

ፍቅር ጀመርኩ (እንዲህ ስል አትቀኚም? ያለፈው ታሪኬን እንኳን ለመቀማት የምትገደቢ አይመስለኝም:: ቅኚ)

ፍቅር ጀመርኩ:: ደብሪቱ ትባላለች (ረካሽ? ስሟ የባላገር ስለኾነ፣ እንቺን ስላልበለጠችሽ? ራሴን አጠቃሁ መሰለኝ:: ነጥብ ልቀጠርልሽ:: አንድ)

ደብሪቱ ገረድ ናት:: የዘመዶቼ ገረድ (ደስ አለሽ አሁንም? ወደ ገረድ ስለወረድኩ? ሁለት:: ለአንቺ ነጥብ)

ደብሪቱን የወደድኩበት ምክንያት ነበረኝ:: ዘመዶቼ በትዕቢታቸው እንገልለዋት፣ ያልተገራ ትንደሬ እንደበትዋን እየሸሚጠጡ፣ እንዲታውቃቸው ከፋት ሲያባርሯት፣ በገረድነትዋ እንገሸሸዋት፣ ግድግዳ ተለጥፋ የሚያምሩ ዐይኖችዋን ስታንከባልል ሳይ ለእስዋ በማዘን፣ በእነሱ ፀባይ ወይም ጉራ በመናደድና እልህ በመግባት ደብሪቱን ልወቃት አልኩ::



@BOOKALEM

አንድ ቀን ማታ ወደምትተኛበት ክፍል በቀስታ እየተራመድኩ ገባሁ......አስተኛኘትዋ: ድርና ማጉ ብቻ የቀረ ባለአንገላ የምትለብሰው ብርድልብስ ከላይዋ ተንሸራቶ ወርዶአል:: የተኛችው በጀርባዋ ነው:: አፍዋ በትንሹ ተከፍቶአል:: አንድ እጅዋ ወደ መሬት ተንጠልጥሎአል:: ጡቶችዋ ወደ ላይ ቆመዋል:: ትንፋሽዋ አይሰማም......

...ለጌሬዳ.......

ውበትዋን መቋቋም ባልቻልም......

ነፍሴ ለሁለት ተከፈለች:

አንደኛዋ እንዲህ አለችኝ:.....ተኛት፣ ተኛት፣ ተኛት::

ሁለተኛዋ እንዲህ አለችኝ:.....ከዚህች ጋር አቤት ውርደት ......ትሉት፣ ልክስክስ ጣባ ጣሳውን ይለቅማል፣ ምንዋም ከማይታወቅ፣

አንደኛዋ አሁንም እንዲህ አለችኝ: ሰው ናት፣ ውብ ናት፣ ተኛት

በዚህ ፍጥጊያ መሐል አንድ የዘመዴ ልጅ ገባች::

የየችኝ አስተያየት......ሁሉም ሴት በሚያይበት (አንቺም)......

የኛ አለንልሀ አይደለም:: ሁልቀን የምንታጠብ፣ ምን ዓይነት ሽቶ ትፈልጋለህ? ይሔን ቁመና ይዘህ......ይሔን ጥርስ፣ ይሔን ዐይን ይዘህ የትኛዋንም ሴት የሚያማልል (አትቅኚ አይዞሽ:: ምንም ነገር አላደረግኋትም)::

የዚያን ቀን ሰራተኛዋን ትቼአት ወጣሁ::

በሌላ ቀን ስገባ ልክ እንደ መጀመሪያው ቀን ተኝታ አገኘኋት::

ላውቃት ፈለግሁ:: (እዚህ ላይ መቼም አይምራትም በሚል ትንፋሽሽ ከእሁኑ ቀርጥ ቀርጥ ማለት ሳይጀምር አይቀርም)

መጀመሪያ መንካት ፈራሁ:: እግሮችዋን ስታንቃንቅ ብርድ ልብሱን በሙሉ ከላይዋ ላይ ገፍታ ጣለችው:: እንበርከኬ የሚያፀልይ ውበት አላት: ከግላ የተቀዳ ጠይምነት:: የወደቀው ልብሰዋን ላለብሳት ስሞክር ተንቀሳቅሳ አንድ ዐይንዋን ገለጣ ፊትዋን ወደ እኔ አዞረች:: ዳበስኳት:: ወደ ጀርባዋ ገለበጥኳት:: እንዳደረኳት ኾነች:: ዳበስኳት:: እስኪበቃኝ ዳበስኳት:: ዕንባ ዐይኖቼ ሽፋሽፍቶች ላይ ሲንጠለጠል ተሰማኝ---ሊወድቅ::

ገላዋ እንደ ነብር ጅራት መወራጨት ጀመረ:: ልቅሶ በጀመረው ድምፅ ወደ ደረትዋ አየስጠጋችኝ ትስመኝ ጀመር::

በዚያች ቀን ብቻ አረገዘች:: (አትቅኚ)

ያ ቤት ተናወጠ፣ ከኩርኒሱ እስከ ውሐ ልኩ:: ሊተቀብኝ ምንም አላቀሩችው:: ከዚህች ልጅ ጋር አድንቂአት ተኛኋት እንጂ ለሌ እሷ ብዙ የማውቀው ስለእኔ ብዙ ያወቀችው ነገር አልነበረም:: ከፊርም ግን በሰው ቤት እንደ ሚስት ሊያደርጋት ከጀላት::



@BOOKALEM

እሷን ማስረገዜን ያዩ የቤት ውስጥ ልጃገረዶች...... ጥቅሻቸውን ቢገቱም ነገር መዘምዘማቸውን አላቆሙም፡ `ልክስክስ` `ወራዳ` `አትሙን አያውቅ` `ደደብ` `አህያ` `ከብት` `ጅል` `ማሳ` (ከጀርባዬ ደግሞ በትንሹ እንድሰማ ግን ሳልሰማቸው የተናገሩ እንዲመስል አድርገው፡- `ከአናጢ ልጅ ምን ሊጠበቅ`) እነዚህን ሁሉ ቃላት በተለያየ አገባብ እንድደነብርባቸው አድርገው በዐረፍተ ነገሮቻቸው ውስጥ በተለያዩ መልክ እየዋቀሩ አመጧቸው::

ጥርሴን ነከስኩ:: አወቅሁ::

ዕድሜዬ 18 ነው......

ገረድዋ በወሊድ ሞተች፡ ልጁም አልተረፈም::

አሁንም ራሴ ውስጥ የዘነጋሁት ትግል መጣ......

አንደኛው፡ እሰይ ተገላገልኩ......ከገረድ የተገኘ ልጅ መሰደቢያ ነበር::

ሁለተኛው፡ ለአንተ ክብር ብለህ (አለመከበርም ሊኖር ይችላል) የሰው ነፍስ እንኳን አለፈ ትላለህ? እሷን ባታውቃትም......ምክንያት ሆናህ እሷንም ሌላውንም ሰው አሳይታሣለች (ይሔን ክርክር ግን ሲዘገይ ረሳሁት)

እሰዋ ከሞተች በኋላ እዚያው ቤት ትከጅለኝ የነበረችውን ደብሪቱ መኝታ ቤት እጅ ከፍንጅ የያዘችኝን (እላይ ሳልጠቅሰው ስላለፍኩ ይቅርታ እጠይቃለሁ) ያገኘችኝን ልጅ ተኛኋት:: ያው ናት:: ሦስት ነበሩ:: ሦስቱንም ተኛኋቸው:: ያው ናቸው:: ሥጋ ናቸው:: አሠራራቸው በመጠኑ ቢለያይም::

ሃያ ዓመቴ ነኝ::

እዚህ እንነርኩሽ ቤት ውስጥ ያሉ ሴቶች በሙሉ እንዲትዋም ሳትቀር ከሌላ ሴት ጋር የማደርገውን ግንኙነት ይከታተሉኝ ነበር:: መኝታ ቤቴ ገብተው ፎቶግራፍ፣ ወይ ደብዳቤ ግን ይሔ ለሴት የፃፍኩት የመጀመሪያዬ ደብዳቤዬ ነው:: ለአንቺ አፅፋቸው የነበሩትን ማስታወሻዎች (Memos) ትተሽ::

እንደ አንቺ አንድ ቦታ የበቀልኩ ባሕር ዛፍ ሳልሆን እንደ ኮባ ውላጅ የተሽከረከርኩ ነኝ::

ከእነዚህ ሴቶች ምንሽ ይለያል? እስቢ! መልካችሁ፣ አወላለዳችሁ ባይመሳሰል ይችላል:: እነኚህን ሴቶች ያወቅኋቸው ገና በ18 ዓመቴ ነበር:: አሁን በሣሳ ሰባተኛዬ ውስጥ ነኝ:: ባገኘሁና ባጋንና):: ዲግሪሽን፣ ዲፕሎማሽን (የትኛው እንደሆነ ሳልረሳው አልተረርም) መኩራሪያ ብታደርጊው እንኳን የተለየሽ ትልቅ ወይዘሮ ወይም ወይዘሪት አያደርግሽም (አንዱን ምረጪ):: አንድ እሁድ እንገናኝ ስልሽ ከጓደኞቼ ጋር በየወሩ የገብርኤል ማህበር አለብኝ



@BOOKALEM

አላለሽም፣ ይሆን ዘመናዊ ሰንበቴሽን 'Get together' ነው ያልሽው? በአንቺ ቤት አውሮፓዊ (በልጡን) ያደረግሽው መሰለሽ:: በሙሉ የሌተደላችሁ፣ ያልምላላችሁ ያልተጻፉችሁ የቤት እመቤቶች ናችሁ::

የሥስል ስራዬን ከልብሽ ትወጂልኛለሽ? እኔ እንዳልርትሽ ብለሽ ለምናቤ ውጤቶች የለበጣ ከመስገድና ኢግዚአቢሽን ላይ ከማጅብ በስተቀር......በአለባበስ ተለቃልቀሽ፣ በውሽት ዘመናዊነት::

ባለወሬው ደስ ይለኛል:: የጭንቀቴን ፎቅ ጫፉን ከሾሽው ይበቃል:: ብዙ ጊዜ በሥርአት ባይሆንም አስር ጊዜ ያዘ...... አሰሬም ባይሆን አለፍ አለፍ እያልኩ እንካልሻለሁ:: ሁላችሁም መረራችሁኝ:: ለእኔ እንድትማፍጨኝ እራስሽን አዘጋጅተሽ አታውቂም:: ወይ ሽቶ ታበዥያለሽ ወይም......የማልዋሸሽ ስጋሽን እወድቃለሁ:: የሌሎችንም ብዙ ቤቶች ወድጃለሁ (እትትኚ) እንቺ ከጊደኛዬ ጋር አላተኛሽም? ምን አልኩሽ? ከአንቺ አፍ እንዲወጣ ግለ እንዲሆን ብጠይቅሽ በአንቺ ቤት 'አራዳ' መኾንሽ ነው: 'አሁያ ነገር ዝ......መጠራጠር ትወዳለህ፣ አርቲስቶች ቆዳችሁ ስስ ነው ይለል የለ......ትንሽ ነገር ይቀዳችኋል' አልሽኝ:: ያን ጊዜ አብሬሽ ብዙ ጊዜ መቆየት ውሰባው ላይሆን ውሽትሽ:: አስጠላሽኝ:: ከሐዲው ሥጋዬ እስከአሁን እንደማልችል ሆዴ ውስጥ ታወቀኝ:: ከአንቺ ጭን አስር ያዘገየኝ ይመስለኛል::

ጠዋት፣ ጠዋት ከአልጋዬ ተነስቼ እንደለመድኩት ባዶ ሆዴን ሻይ ስጠጣ ይሰማኝ የነበረው ደስታ ዛሬ ዛሬ አይሰማኝም:: ተድሞ......እንደኒጋላት ወፍ እበርቅ ነበር....እንደኒጋላት ወፍ እዘምር ነበር......በዓለም ላይ ካሉ ነገሮች ጋር የተዋሃድኩ ይመስለኝ ነበር:: ሰው አብሮኝ እንዳለ መስሎኝ አያውቅም:: ብቻዬን የሆንኩ......ከለበስኩት ሸሚዝ......ካደረኩት ቤቴናር......ከተቀመጥኩበት ወንበር......ከማጤሰው ሲጋራ ጋር አንድ የሆንኩ መንበር......ከሚንፍሰው ንፋስ......ብቻ ሳይሆን ብፋሼ የሚገባበት ቀለም ውስጥ ሽርጤ ይመስለኝ ነበር:: ይህቺ አለም ምንኛ ከምንኛ ነፍስ የተነከረች ይመስለኝ ነበር:: ከሁሉ ቤት መገናኘቴ ለአንቺ ይከጠላል? ምንኛ ከምንኛ ይለያል? አስጠላሽ? አስቀናሽ፣ አበሳጨሽ፣ ከቶ አናገረሽ::

ማነን?

እኔ ማንኝ?

አንቺስ ማንሽ?

ነፍስ አንስቶ ወደሚፈልገው ከሚነዳው ቁሳቁስ የምንለየው በምንድን ነው?

ፀጌሬዳ:: እስከዛሬ ድረስ ከትትልሽን አቱሚ እያልኩ ወለሆሳስ ነገሬሽ አልለበማ አልሽኝ:: አንቺን እንድወድሽ ነው የምትፈልገው? እወድሻለሁ:: ግን ሌላ ነፃነቴን እንድትጋፈኝ አልፈልግም:: ሥጋዬ በልብ ድካም ሕመም እየተጨነቀች መንፈሴ

ደግሞ ቅናትሽ በምትረጪው መርዝ እንድትቃጠል አልፈልግም:: ለእኔ ፍፁም ክፉ ነገር የለም:: ክፉ ብለን ጅምላ ስም በሰጠነው በእያንዳንዱ ነገር ውስጥ መልካም አለ:: በእያንዳንዷ የሴት ጭኖች መሐል አበባና እሾህ አገኛለሁ:: ባለፈው ጊዜ ትዝ ይልሻል ውብ ስዕል ተብላ የተደነቀችውን ብጥስጣሽ ጨርቆች የተባለችውን የሰራኋት፣ ሴተኛ አዳሪ በነበረች ሴት ዕርዳታ ነበር:: ያኔ እየመሸሁ ስለምሰራ ትበሳጪ ነበር:: ስቱዲዮዬን ለጊዜው ወደ ጊደኛዬ ቤት በመቀየሬ የተጣላሁሽ ከሴላ ሴት ጋር ልዩ ግንኙነት ያደረግሁ ወይም ማድረጉ አይቀርም ብለሽ ጠርጥረሽ ባገኘሽኝ ጊዜ ሁሉ በሚያነክሱ ምክንያቶች ነገር እየሰራሽ ሕሊናዬን ትፍቂኝ ነበር::

ለብዙ ጊዜ ደጋግመሽ አስኮረፍሽኝ:: ከላይ እስከታች ሴትን ማወቅ ምን ክፋት አለው? የትኛው ነው መልከስከስ? የትኛው ነው ዝሙትነት? ታችኞቹ ከሌሉ ላይኞቹ እኩ አይኖሩም:: የአክሱም ሐውልት የዐሐይና የጨረቃ ቆቦቹ ያለ መሰረቱ ይከፈላሉ? ይመስልሻል? የትኛው ምልቃቃ ጉልተኛ ያለገበሬው ይፈጠራል? ላይኛውም ከሌለ ታችኛውም አይኖርም:: በማንም ደም ሥር ውስጥ መመላለስ እወዳለሁ::

ከእንግዲህ አንገናኝም:: የስዕል ስራዬን እንደድሮው በስሜት ባልተተልም አንዳንዴ እሞክራለሁ ብያለሁ:: በሦስት ዓመት በአራት ዓመት ኤግዚብሽን ካዘጋጀሁ ይበቃኛል:: ከላይ እስከታች ያላችሁ ሴቶች የሚለያችሁን ነገር አጣሁ:: ብቻዬን መኖር እፈልጋለሁ:: ሃያ አመት ሙሉ እናንተን ባሰስ ያገኘሁት ተመሳሳይ ነገር ነው:: ከጀመርኩ እስከ ዛሬ አስከጨረስኩ::

ዐጌሬዳ

ዐጌ

ዐጊ

ዐ

(እየሰባበርኩሽ ነው)

ደህና ሁኚ

እስጢፋኖስ ሴማዊው

* * *

በመኪናው መስኩት የአላፊ አግዳሚ ሳቅ እየነፈሰ ይገባል:: ማርጀት የጀመረችው የአዲስአባ ፀሐይ እንደ እንጥል ቀልታለች......ወደ ምሽት ጉሮሮ ትንቀረፈፋለች:: ሜክሲኮ አደባባይ ቀይ ስስ ጨርቅ የተጣለባት ትመስላለች:: ሠንጋ ተራ ታክሲ ማቢያ ሰው እንደከብት ተደርድሮአል:: ብዙ ታክሲዎች ወደ ቄራ ይወርዳሉ:: ተ-ካሬ (ቲ ስኩዌር) የያዙ የተግባ ረዕድ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሊወቁት ይዥራገዳሉ፣ የቆመበት ስራ የፈታ ጎረምሳ ግንብና የኪዮስክ ግድግዳ ተደግፎ ድዱን እንደ ጭላዳ ይገሽልጣል፣ ምራቁን ይውጣል::

ባለቀጠሮ ሰአቱን ይገላምጣል—ለማታ የቦኖያ ዳንስ፡፡ ሹል ጫማና ሱሪ ቀሚስ እንደ ሳንቡሳ የሚደገቡበት የለም፡፡ መንገዶች በሚስቲን ልብስ ተሸፍነዋል፡፡ የፈረጠ ብርቱካንና የብርቱካን ልጣጭ በየአስፋልቱ ወድቋል፡፡ የሚታከክ ወይበር የእውቀብስ ማቆሚያው የብረት ዘንግ የተቀባውን ቀለም በጥፍራቸው ይፍቃሉ፡፡ ተቀምጠው ያናውዙ የነበሩ ሴት ያመለጣቸውን አቶቡስ ተከትለው ይሮጣሉ......ግድ ያልሰጠው ነጠላቸው ከጓላቸው ይቀራል፡፡ ሰርግግን ይተፋሉ፡፡

እስጢፋኖስ ከተቀመጠበት አሮጌ ፔጆ ታክሲ ወደ ውጭ ያያል፡፡ ሲጋራ ካጠቆራቸው ከንፈሮቹ ጀርባ ጥርሶቹን ገጥሞአል፡፡ አጥብቆ የከሰው ነገር ያለ ይመስል የመንጋጋው ቅርፅ መለሃጫው ቆዳ ላይ ተለጥፎ ይታያል፡፡ መብራት ሲያቆማቸው አንድ ሎተሪ ሻጭ እግረ መንገዱን ትኬቶቹን አደኖቹ ስር አውለብልቦለት ሔደ......እስጢፋኖስ ፊት ላይ የተቀረፀው ቁጣ ያሳደደው ይመስላል፡፡

አረንጓዴ መብራት እስኪታይ ድረስ የማያስፈልግ ረዥም ጊዜ ያለ የጠበቀ መሰለው፡፡ እስጢፋኖስን ትንሽ ከፋው፡፡

የታክሲዋ ሾፌር ወደ እሱ ዞረ አለና፡

«ይሔን መብራት እወደዋለሁ»

እውስጥ ከሚናቸው ሰሰት ተሳፋሪዎቹ፡

መልስ የሰጠው አልነበረም/1/

ስለጉዳዩ የጠየቀው አልነበረም/2/

የደገፈውም የነቀፈውም አልነበረም/3/

«ያሳርፈኛል፣ መብራት ሲበራ እርፋለሁ»

/1/ /2/ /3/

ግራ የተጋባም ሳይመስል ቀጠለ፡

«እዚሁ እስከነገ ብቆም ግድ የለኝም»

/1/ /2/ /3/

ከጥቂት ዝምታ በኋላ፡

«ለምን?» አለው እስጢፋኖስ በራሱ አጠያየቅ የተገረመ ዐይነት በድንጋጤ፡፡

«ያው ነው፡፡ መኪናዬን ስነዳት አንዳንዴ ተኝቼ ነው፡፡ ስተኛትም ተኝቼ ነው......በመሔድና በመቆም መሃል አንዳንዴ ልዩነት አላይም»

«እርሳው» አለው እስጢፋኖስ መንጋጋውን ደጋግሞ እየነከሰ፡፡

«ምኑን?......እየኖርኩትን?»

«አንድ መሆኑንም የተለያየ መሆኑንም»

-ሲንዲሬት ይጋባል ወንድሞም፣
-ሲንዲሬት ይጣባል ወንድሞ ምቀ ኢትዮጵያዊነቱ፣
-ሲንጣበው እኔ። ሃሊን እንጂ ምቀ እድሜ አልነገራቸውም።
-ሰው እንጂ እድሜ እዚያ ድረስ አልነገሩኝም።
-ሰው እንጂ እድሜ እዚያ ድረስ አልነገራቸውም። መልሳት ለቀቃቸውና ናፍቆ
እስጢፋኖስ መልስ አልሰጠውም።
ቀጠለችና።
ፓሬቱ አልፎ አልፎ እስጢፋኖስን የጉራቴ ያየዋል። ትንሽዬ
እንደሞገድ ያሰበው አልመጣለትም። የሆረሸት መሰለው።
ሰዎች ነው እመርጣለሁ ያለችኝ፦ ያለውቅ ዓይነት። እስጢፋኖስ ዞር
ብሎ አየው። ለመስማት በጓሮ ፈቱን መለሰ።
ዛሬ እንደ ልጅ ሰውዬው በእናቴ የምመርጣቸውን ቢታ.... ትዝታ መንገዱ
-እንዲህ አሉን
አድራሻውም አለው እስጢፋኖስ
-ውን አለኝ እኔ....የሚወርዱበትን መጠየቅ የአንድ ታክሲ
ሹፌር ሥራው ነው.... ትርጉም የሌለው ነው.... ብቻ......
ዋዜ ሸበል ሆቴል ሲደርስ አቆመለት። እስጢፋኖስ ሹፌሩን
የበኋቱን መስሉት እየተሳተፈ ወጣ......እየተዝናና ከፈለ......
ፊኛው በፈሳሽ እንደተወጠረ አሁን ትዝ አለው። ዋዜ ሸበል
ሆቴል ገባ። የመፀዳጃ ቤቱ መጀኒያ ተጠግቶ ትንፋሹን ዋጠ። የሽንት
ቤት ጠረን ያሞቃል። ጉት ካለው ክፍል ሰው ያሞቃል። ሱሪውን
ቤት ጠረን ያሞቃል። ሽፋኑ የተገለፈፈለት ተቀማጭ
ከፍቶ ጭንቅላቱን ወደ ላይ አነሳ። እንግዲህም ወደ ታች ሳይለብር በእጁ
እምቧል ወደናቹን ወጋው። እንግዲህ ሲደፋ ታላቅ ጭንቅ ያራገፈ
ፈትኝ ትንፋሹን አወጣ። ሽንቱን ሲደፋ ታላቅ ጭንቅ ያራገፈ
መሰለው......ወደ ውጭ በኃይል ተንፈሰ።

ፖስታው ደረቱ ኪስ እየተፈራገጠ እንዳስቸገረው ሁሉ በአንድ
እጁ ሱሪውን እየሰተካከለ በሌላ እጁ አወጣና አየው። አድራሻዎቹ
በትላልቅ ፊደሎች ተሰፍሯል። ያለፈ ሕይወቱ በእጭሩ በስስ ነጭ
ወረቀት ላይ ሰፍርአል። የመበበበት መሰለው። ውሳኔ ሰባት ክረምቶች
በዘመኝ ትናንሽ ገጾች። ያመለጠ ነገር ይኖራል። ርካሽ! ቅሪሬ ሕይወት
መሰለው። ተጨምቆለት! ተጨምቆለት ግን የበረደ አልቦ። ሆቴሉ
በረንዳ ላይ ቆሞ የሚመላለሰውን ሰው ሲያይ ቀጣሪ ትዕይንት
መሰለው። ዝምን! ተንቻል! አሊ! ሚዳቅዋ! አዞ! ጂሬ ጨርቅ
ለባሰው ወደ ቀዳቸው! ወደ ነጃአቸው—ሳይግባቡ።

በምላሱ እርጥቦ የገጠመውን ፖስታ በእጁ እያገላበጠ እንደገና
ለረጅም ጊዜ አየው። እጣጥፎ የከተታቸው ወረቀቶች የህብረት ቅርፅ
ከውጭ ይታያል። በሌላ እጁ ተጫነው። ከመዳፉ ሥር እየር ግራና ቀኝ
ወደ ፖስታው ጥጉች ሲሰደድ ተሰማው። ነጭ በንብ በእንክብካቤ የያዘ
መሰለው።

ቴምብር ለማስለጠፍ ፖስታ ቤት ገባ:: እንዲመዘንለት በመስታወት ቀዳዳ አሾልኮ ለፖስተኛው ሰጠው:: ሰውዬው አድራሻውን ዐይቶ ፖስታውን በእጁ መዝኖ ዋጋውን ነገረው:: እስጢፋኖስ ፖስተኛው ዐይኖች ውስጥ አንድ ነገር ያነበበ መሰለው: የጻፈውን ነገር ያወቀበት:

'አንተ ትልቅ የነበርክ፣ ሁለንተናዊ የነበርክ ሰው……ለመጨረሻ ጊዜ የቀረችህን ቤት……ልትለያት፣ ልታስቀይማት?'

ቴምብር ለመግዛት የተሰለፉትን በሙሉ እየገላመጠ አያቸው:: ያቀረቀሩት በውሳኔው ያዘኑ……የሚስቁት ጅልነቱን ተረድተው……ግን ሁሉም አውቀው—ዝም:: በሩ እንኳን በጣም ተበርግዶ: 'በል ቶሎ ሂድልኝ ልዘጋበት' የሚል ዐይነት እየመሰለው::

ከፖስታ ቤቱ ሲወጣ በረንዳው ላይ ባልጠበቀው ሃይል ይነፍሳል፣ ይበርዳል:: የሚተሳለፉ አንድ የቤት መኪናና ታክሲ መንገድ መሃል ሊጋጩ ሲሉ……እውዬ ያለው ሰው ግን ግድ የሰጠው አይመስልም:: ጩኸት ይበዛል:: ተሟጦ እረፍት የለም:: ትኩሳ ነው:: የአልባሌ ብልጦች ቀን ይመስላል:: ፖስታ ቤቱ ውስጥ የተሰማው ውጥረት እየበረደ ሳብ ችፍ ብሎበት የነበረው ሰውነቱ ነፋስ ሲነካው በረዶ የገጨው ያህል ከረሰሰው::

ፖስታ ወደመከተቻው ሣጥን ተጠግቶ የሣጥኑን ከዳን ከፍቶ ፖስታዋን ግማሽ ድረስ አስገባትና ቆመ:: ልቡ ዘለለበት:: ሰውነቱን የኤሌክትሪክ ንዝረት እንደወረረው ሁሉ ቆዳው ስር የሚጠቀጥቁ ነገሮች ተረጩበት:: ዐይኖቹ ዕንባ አቀረሩ:: የዕጌሬዳ ገፅ እንዳለ መጣበት:: ቀጭን አንገትዋን ሰብራ……ቡናማ የፀጉር ገመድ ጠይም ግንባሯ ላይ ወድቆ በአንገትዋ ሐብል እየተጫወተች……በጠቋቁር አይኖችዋ ወግታ ይዛው: 'ብቸኝነት እንዴት እንደኾነ ታውቃለህ? እ……ከአንተ ጋር ስቀመጥ ከዓለም ጋር የተቀመጥኩ ይመስለኛል……መዝፈን ይቃጣኛል:: ሞኝ ነሽ አትለኝም? የሚሰማኝ ደስታ በምን ቃላት ይገለጣል? ትይዘኛለህ?……እ?……እስጢፋኖስ ያዘኝ……'

ወደ ሳጥኑ አፍ ሲያይ ፖስታው የለም:: ጣቶቹ እንደጠፉበት ሁሉ ደንግጦ እጁን አየ:: በቀዳዳው ውስጥ ወደ ሳጥኑ ጉድጓድ አፈጠጠ:: ጨለማ ነው……የተከመሩ ነጫጭ ፖስታዎችና ሰማያዊ ኤሮግራሞች ጫፋቸው ይታያል:: ከአለም ጋር ያያያዘውን አንድ ገመድ የጎመደ መሰለው:: ከዕጌሬዳ ጋር ያጣመደው እትብት ከዕንብርቱ ተነስቶ በፎቆች ጣሪያ፣ በጐዳናዎች የትራፊክ መብራት ሳያቆመው፣ ብርድ ሳያደርቀው……ሙቀት ሳያኰማትረው:: እልቅስ እልቅስ አሰኘው:: ፖስታውን ቀድሞ ዕጌሬዳ ዘንድ ለመድረስ ተመኘ:: እዚያው እቆመበት እንደ በረዶ ቀልጦ ወደ ቦይ ውስጥ ቢፈስ



@BOOKALEM

ወደደ......ከከተማው ቆሻሻ ጋር ቢቀላቀል......ከአረንጓዴ ቆሻሻ፣ ደፍጥጦት ካለፈው ሙዝ ጋር፣ ከብርቱካን ልጣጭ ጋር......ከሆቴል ቤት ፍርፋሪ ጋር፣ ከከሰረ የሎተሪ ቲኬት ጋር፣ ካለፈው ዓመት የጋዜጣ ቅዳጅ ጋር......ከተሸራረፈ የሸሚዝ ቁልፍ ጋር ......

ራሱን በሁለት እጆቹ ያዘ::

ወደ ቤቱ ለመሔድ የመኪናውን መንገድ ሮጦ ተሻገረ:: በአየር ላይ የሚዋኝ መሰለው:: እግሮቹ ብቻቸውን የሚርገበገቡ ጥንድ ክንፎች...... መላጣ አናቱም ከዳመና በላይ ዘልቆ......ባልለመዳቸው በማያውቃቸው የነፋስ መንገደኞች በእርጥበታቸው እንደታጀበ......ጫማው፣ እግሩ አዳልጦት ወድቆ......ወደ ታች ሲወርድ......የአስፋልቱ ቁርቁራ ጉልበቱ ድረስ እየተሰማው......ደረቱ ድረስ......ሆዱ ድረስ......አንገቱ ድረስ:: አቅለሸለሸው::

ምራቁን ተፋ:: ነጭ ጠጠር......

ልብ ድካሙ መንገድ ላይ እንዳይነሳበት ፈራ:: ቅርብም ቢሆን ቶሎ ቤቱ ለመድረስ ታክሲ ጠየቀ......በመኪናው መስኮት ወደ ውጭ፣ ወደ ሰማይ አየ:: ብቸኛ አሞራ እየቀዘፈ ያልፋል:: እስጢፋኖስ ማልቀስ ዳዳው:: የጽጌሬዳን ድምፅ የሰማ መሰለው......ስታለቅስ:: ስታለቅስ ሰምቶአት አያውቅም......ታክሲ ውስጥ ለብቻው እጁን ያወዛውዛል ......እንደ ዕብድ አድርጎታል:: ራሱን ለማበረታታት በልቡ የውሸት ኩስታራነት ለመፍጠር ሞከረ:: የኽን የኽን ዐይነት::

ሌላ ነጭ ጠጠር—በመስኮት:: ጠጠሯን ነፋስ ጉያው ከቶ ሰባበራት......

ዝናብ ከሰማይ ሊወድቅ......

* * *

*ለፍቅረኛዬ ለፅጌሬዳ*

*በ03/07/79 ቀን የፃፍኩልሽ ደብዳቤ ከዚህኛው ቀድሞ እንደሚደርስሽ አልጠራጠርም......*

ምንስ አስቀድሞ ምንስ እንደሚቀጥል......ግራ ገባው:: ትንሽ እህቱን ጠርቶ ከጎረቤታቸው ግሮሰሪ ቢራ እንድታመጣለት አዘዛት:: እሷም ሁኔታው እንዳልገባት አፍጣ ስታየው ቆይታ እየሮጠች ወጣች:: ረዥም ነጭ ሲጋራ ከጠረጴዛው መሳቢያ አውጥቶ አቀጣጠለ:: ብዕሩ እጁ መሐል ጣቶቹን ሳይነካ የቆመ መሰለው:: እንዳለ ረሳው::

*......የልኩሽን ሁሉ የፃፍኩትን ሁሉ ዘንጊው:: እሷን ደብዳቤ ከፃፍኳትና ፖስታ መሰብሰቢያ ሳጥን ውስጥ ካስገባኋት በኋላ የእኔ ውሳኔ ውሸት ነው አልኩ:: ደብዳቤውን አስገብቼ ቀና ስል በዓለም ላይ ለብቻዬ ያለሁ መሰለኝ:: በአጠገቤ ከሚርመሰመሰው ሕዝብ መሐል......ያንቺ ምስል ብቻ ነፋስ ሊነዳው እንደ ከበደው ጢስ ወደ*



@BOOKALEM

ላይ ወጣ......አይኖቼንና ነፍሴን ሞላቻው:: ቀጨኝ:: የመፃፊያ ጠረጴዛዬ ላይ ደገፍ ብዬ......

ልቡ በኃይል ሲመታ ተሰማው:: ብዕሩ ከእጁ ተንሸራቶ ወረቀቱ ላይ ወደቀ:: በግራ እጁ ለመደገፍ አሰበ:: ያልቻለ አይነት ወደ ጐን ዘንበል አለ......ወለላ የመሰለ የሚሳብ ምራቅ ከአፉ ግራ ጥግ እየተንተተ ወረደ......ያገደው ነገር ስላልነበር እየተቆራረጠ ወለሉ ላይ ተንጠባጠበ......ገላው ትንሽ ተንቀጠቀጠና ፀጥ አለ:: ወጥሮት የቆየው የሲቃ ሲባጐ እንደላላ ሁሉ ዘና:: ቤቱ መብራት ቢበዛውም እንደ በራደ ኾነ:: እህቱ ከፍታ በተወችው በር ከባድ ነፋስ ገብቶ ይፅፍበት የነበረውን ወረቀት ያራግበው ጀመር::

እህቱ እንድትገዛ የላካትን ቢራ ይዛ አጠገቡ ደርሳ ስታየው ልብ ድካሙ እንደተነሳበት አወቀች:: አቀማመጡም ስላላማራት ዕቃ ባልያዘ እጅዋ ነካችው......

ነፋሱ ሲያቆም የእህቱ ለቅሶና በለቅሶዋ የተጠራው ጎረቤት ቤቱን ሞላው......ከመፃፊያው ጠረጴዛ ላይ ለዕጊሬዳ ደብዳቤ መጻፍ የጀመረባት ወረቀት ወደ ወለሉ ወደቀች......ሰዎች በጭቃማ ጫማቸው እየረገጡ በመቀባበል ወደ ውጭ አወጡዋት::

የቺኑ ወረቀት አንድ ሰው ከአጥር ግቢው ፊት ለፊት ቦይ ዳር ባለ ሣር ላይ ከጫማው ሊያላቅቃት ይለፋል......ቢነጋ ወረቀቷን የቀፈው የጭቃ ጊል በነፋስና በፀሐይ ሲደርቅ ተንከባሉ ቦይ ውስጥ ይገባል......ከሰዐት በኋላ የጣለው ዝናብ ይዞአት......በከተማው ሆድቃ ውስጥ ለውስጥ ከሚያልፈው ቆሻሻ ጋር ይደባልቃታል......በአዲስአባ ታላቅ የሕቡዕ አንጀት ተውጣ ፈሮ ቧጭሯአት......ቆንጥጦአት ለረዥም ጊዜ ታንቀሳፋለች:: አንዳንድ ፊደላት፣ ሐረጐች......ሥርዐተ ነጥቦች ታጥበው ይጠፋሉ......የጥያቄ ምልክቶች የአረም ስር በመንጠቆአቸው ሷጠው ይዘው በየቦታው ከሐረጎቻቸው ተነጥለው በብቸኝነት ተንጠልጥለው ይቀራሉ......የቆሸሹ እርጥብ ዐይጦች ከአሳቻ ጉድጓድ ያፀዋታል......'ምሁሩ' አይጥ ሊያነብ ይሞክራል:: ከቱቦው ወጥታ......ወደ ወንዝ ስትወረወር ዓሦች የጉሪጥ ያዩአታል......እንቁራሪቶች ይዳሩባታል......ቆቃ ከደረሰች ብቻዋን ናት: ስስ ወረቀት፣ ቀለምዋ የለቀቀ......መልዕክት የሌላት......ማንኛውም ዐይነት ተራ ወረቀት የምትመስል......ዳር ይዛ እያሰበች......የምትጠብቅ መሰላ: የኾነ ነገር......የኾነ ሰው......የኾነ ጉዳይ......

* * *

ዕጊሬዳ ወዳጇ እስጢፋኖስ ሴማዊው መሞቱን ስትሰማ በእሱ ምትክ ራሷ ብትሞት ተመኘች:: የእሱ ዘመዶች ጥሩ አድርገው ግልቀስ ስላልቻሉ እስኪናቁ......መቃብሩ አብሬ ካልገባሁ አለች......

«የእኔ ጌታ!»



@BOOKALEM

«የእኔ ፍቅር!»

«የት ልትተወኝ ነው!»

«ብቻዬን አልችልበትም!»

«ማን አለኝ?!»

«እ እ እ!»

«ሌሊት ሌሊት ልባንን ነው!»

«ሌሊት ሌሊት ልባንን ነው!» ብዛት ራስዋን ሳተች።

በማልቀሷ ብዛት ራስዋን ሳተች።

በማልቀሷ ብዛት ራስዋን ሳተች።

ዘመዶችዋ በሽቁ። ዘመዶቹ በሽቁ።

ዘመዶችዋ በሽቁ። ዘመዶቹ በሽቁ፡ «እኛን በልጣ የምታለቅስ ሽረ ማናት?»

ዘመዶቹ፡ «እኛን በልጣ የምታለቅስ ሽረ ማናት?»

ዘመዶቹ፡ «እኛን በልጣ የምታለቅስ ነው እንዲህ የሚሰራት? ሂጭ!

ዘመዶችዋ፡ «ምን ቢያደርጋት ነው እንዲህ የሚሰራት? ሂጭ! ወንድ አለቀ አልዋት እንዴ?......ቀላል። አስዳቢ»

ለሳምንት ያህል ሰው ማየት አስጠልቶአት ክፍሏን ዘግታ ቤቷ ተኛች። የእስጢፋኖስ የመጀመሪያው ደብዳቤ የደረሳት ከእዚህ ድንጋጤና ሃዘን እያገገመች ነበር። ደብዳቤውን ስታነብ በእሱ መሞት የተዳከመ የመሰላት ገላዋ እየነደደ የተለየ ስሜት ያጤስ ጀመር። ከመላ የቆዳዋ ቀዳዶች ላይ ላብ እንደ ከፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ። ከመላ የቆዳዋ ቀዳዶች ላይ ላብ እንደ ደረቅ ቀጫጭን ጭራሮ እንጨቶች እየተገተተ የበቀለ መሰላት ......የሰውነቷ ሥጋ በዐይን እስከሚታይ ድረስ ነዘረ። አርገፈገፋት።

ዳግማዊ አነበበችው።

እንደ ሕልምም መሰላት......ሆዷ ተገለባበጠባት......ተነስታ ለመሔድ እግሯ ስለዛለ......እተቀመጠችበት ጠረጴዛ ላይ......በቅርብ የበላችው ሻይ በዳቦ አስመለሳትና የለበሰችው ሸሚዝ እጅታ ተበላሸ......የግንባሯን ላብ ጠረገች......ትንሽ መለስ ሲልላት እተቀመጠችበት ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ማቆም አልቻለችም......

በማልቀስ ላይ እንደሆነች ስታውቅ......ልብዋ በሐዘን እየተሰባበረ እንደሆነ ስትረዳ......እንዲህ ሲከዳት......እፍረቷን አደባባይ ወርውራ እንዳነባችለት ስታስታውስ ለቅሶዋ ተባዛ። የምታደርገው ጠፍቶአት ራሷን ይዛ ቆመች። ወደ አልጋዋ በቀስታ እየተራመደች ሔደች። በሆዷ ወደቀች......

ስትባንን ጠዋት ኾኖአል። የክፍሏ መስኮት አልተዘጋም። ነፋስ መጋረጃውን እየገለበ ይገባል። አልጋዋ ላይ እንደተኛች ፊትዋን እጅዋ ላይ አስደግፋ ስታስብ ቆየች። ከረዥም ጊዜ በኋላ ከተጋደመችበት ተነስታ ገላዋን ታጠበችና ሽቶ ተረጨች። እንዳልተረበሸች ሁሉ

የሚሆን የወዳጆዋን ደብዳቤ ደግሞ አንብባ መልስ ለመፃፍ ተቀመጠች......

11/07/79

በሕይወት ለሌለኸው እስጢፋኖስ

እንዲህ ነበር የምታስበኝ? እንዲህ ነበር? እንዲህ? ብዙ ነገር አሳጣኸኝ:: ጠላሁህ:: እስጢፋኖስ......የባለግሁባቸው ጊዜዎች ነበሩ ግን ቀምተኸኛል ይሄንንም ታውቃለህ ግን እንዲህ ነበር የምታስበኝ? ምን አደረግሁ የእኔ ጌታ ያልሰራኸውን አልሰራሁ እ? ......

አልጋዋ ላይ እንደተኛች ሌሊት የተሞላችው ድፍረት ሲተን ታወቃት:: ዕንባ ከጀላት:: መበቀል እንደማትችል ስትረዳ ቁጣዋ ገነፈለ:: የእስጢፋኖስን ፖስታ ከነደብዳቤው ለሁለት፣ ለአራት፣ ለስምንት ቀዳደደችና......በር ስር የቆመ አሮጌ የቀርከሃ ቅርጫት ውስጥ ወረወረችው::

ጭንቅላቷን ጠረጴዛ ላይ ደፋች:: የቤት ሰራተኛዋ ገብታ ዕቃ ስታዘገጃጅ በመገረም ታያታለች......የመስኮቱ መጋረጃ መገለጥ ይገባው እንደሆነ ልትጠይቃት እንኳን ፈርታ የቅርጫቱን ቆሻሻ ይዛ ወጣች:: ከቤት ጀርባ ደፋችው......

የማያርፈው የአዲስአበባ የክረምት ሰማይ ከባድ ዝናብ ጥሎ ቆሻሻውን ጎርፍ ጠርጎ ወሰደው:: ከባድ ዝናብ ነበር......ፖስታው ውስጥ የነበሩት ወረቀቶች አዲስአበባ ሕቡዕ አንጀት ለመቀላቀል በየቦዩ እየተሯሯጡ ......ተጠባብቀው የነበሩት እየተለያዩ......እየተበታተኑ......እያንዳንዱ የራሱን መንገድ ይዞ ወደ ራሱ መጥፋት እያሸተተ......ዐረፍተነገሮች ማንም ወደማይገባው መልዕክት ተቆማምጠው......አንዳንዶቹ ወደ ቆቃ እጥፍ ዘርጋ እያሉ እየተልመጠመጡ:: በየቦዩ ሌላ ደብዳቤ የተፃፈበት ወረቀት ለማንበብ እየተጠጋጉ፣ ከየት ነህ? ከየት ነሽ?

ቢተዋወቁ እንኳን በጠረናቸው፣ አንዱ የአንዱን አንብቦ አይገባውም ......ቆሻሻ ላይ ተለጥፈው እንደ ዱዳ ይተያያሉ......

---- // ----

መጋቢት 1979

አዲስ አበባ



@BOOKALEM

@BOOKALEM

# ኢዮሄ ጊዜ

የሚኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አቀማመጥ የሚገርም ነበር:: በስተደቡብ የአራት ኪሎ የሳይንስ ኮሌጅ ግቢ አለ:: ይኼ የአጋጣሚ አስፋፈር ተምሳሌትነት አለው:: ተምሳሌትነቱ የተሰፋ ነው:: እንግዲህ ሚኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ደርሰህ ከለፋህ ወይም ከቀናህ እዚህ ኮሌጅ ትገባለህ ማለት ነው:: ካልሆነ እያሸተትከው ይቀራል ዐይነት (ደግሞ አፍንጫችን ሥር ነው......ፍዝ ሸንጉበታችንን እያከከ):: በስተፀሐይ መውጪያ ደሐና ሐብታም ተደበላልቆ የሚኖርበት ሠፈር ነው:: ከጭቃ ቤት እስከ ግንብ ቤት:: ከቀናው እስከ ከፋው:: እዚህም ችላ የማይባል ተምሳሌትነት አለ:: ተምሳሌትነቱ እንግዲህ የሚኒሊክን ግቢ አሸንፈህም ሆነ ተሸንፈህ ቤት መስራትህ አይቀርም:: ቤት መስራትህ ካልቀረ በሐብታምነትህ የድንጋይ ቤት (ድንጋይ ያድርግህና)፣ በደሐነትህ የጭቃ ቤት (እንደ ጭቃ ይጨቅጭቅህና) ትወርሳለህ ዐይነት ነው:: (ለምን ተደበላልቀው ተሰሩ? እንደ እንቁልልጭ መሆኑ ነው? 'እስኪ የኔን ግንብ እይ አንተ ጭካ አቡኪ'......የመሰለ? ደ'ሞ የሚገረመኝ ከነዚህ ሁሉ ቤቶች የሚወጣው ጢስ አንድ አይነት መሆኑ ነው፤ የስጋና የቆሎ ጥብስ):: ከት/ቤቱ በስተሰሜን ትናንሽ ግሮሰሪዎች አሉ:: ተምሳሌትነታቸው እንግዲህ መጠጣት፣ መዝናናት፣ መዳራት፣ መልማት ወይም መጥፋት ነው:: የምሥራቁ ተምሳሌት ከፈረሰ የምትሠፍረው እዚህ ነው፣ ወይም ቀድመህ እዚህ ከሠፈርክ ቤት አትሰራም ማለት ነው::

ከሚኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በስተምዕራብ ትልቅ አውራጎዳና ነው......ከእንጦጦ ኮረብታ ሥር እስከ ቦሌ እንደ ጥቁር የዘንዶ ሠረሠር የተዘረጋ:: በዚህ ሰረሰር ዳር ዳር የመንግስት መስሪያቤቶች፣ ዘናጭ ካፌቴሪያዎች እና ፈረንጅ ፈረንጅ የሚሸቱ የተማሩ አበሾች የሚኖሩባቸው አፓርትመንቶች አሉ:: እዚህ ሚኒሊክን



@BOOKALEM

አጠናቀህ ከሆነልህ ሰራተኛ ትሆናለህ፣ ሥራህን አጠናቀህ (ባይጠናቀቅ ኬሬዳሽ) ወጣ ብለህ እዚህ በ'ናህን ትጠጣለህ፣ ካልሆነልህም ባእድ አገር ሔደህ ትመለስና እነዚህ አፓርትመንቶች ላይ ትሰቀላለህ...... አፓርትመንቶቹም ባለደረጃ ስለሆኑ ሚኒ–ስከርት የለበሱ ወይዛዝርቶችን ሳትደናገጥ የኤልቭስን ዘፈን እያዳመጥህ ብሽሽታቸው ድረስ ማየት ትችላለህ ማለት ነው:: (ሞዴርን ለሞዴርን ነዋ!)::

እዚያ ስንማር በተምሣሌት ነው የተከበብነው:: ጫና ነው:: የተምሳሌት ጫና ነው:: እነዚህ የተምኔት ተምሳሌቶች ደ`ሞ እንደ ትልቅ ማሕፀን ሆነው ሊላ ትንንሽ የምኞት ተምሣሌቶች ከላይ እስከታች (ከጕን እስከ ጕን?) እንደ ፅንስ አቅፈው ይይዛሉ:: እነዚህን ተምሳሌቶች ግን አስተሳስረን የምናስባቸው ጥቂት ነን:: ለምሳሌ እንማራለን:: መማራችንን ለብቻው እናየዋለን:: ኬክና አይስክሬም እንበላለን....እሱንም ከሌላው ሕይወታችን ነጥለን እንኖረዋለን:: ከዩኒቨርስቲ ተማሪ ጏደኛ እንሆንና እሱንም የአጭር ጊዜ ጉራ መንፈያ እናደርገዋለን (ቂልነት የሚባለው ይኼ ይሆን እንዴ?)::

ሚኒሊክ ት/ቤት ሳስበው ትርምስ ይመስለኛል:: ትርምስ ስል መራበሹ ማለቴ አይደለም (በጣም እንደተማሰለ የድንች ወጥ መደፍረሱ ማለቴ አይደለም)፤ አይገባኝም ማለቴ ነው:: ብዙ ጊዜ የሐሳብ መለዋወጥ ወይም መወያየት ስለሌለ አስተማሪ ስለ ተማሪ፣ ተማሪ ስለ አስተማሪ፣ አገር ስለ ተማሪ፣ ተማሪ ስለ አገር፣ ወንዶች ስለሴቶች፣ ሴቶች ስለወንዶች ወዘተ......ምን እንደሚያስቡ `ይኼ ነው' ብሎ ወስኖ መናገር አይቻልም:: በየግል የሚያስቡት ይቅርና ተማሪው በአጠቃላይ ስለ ሕይወት ምን አመለካከት እንዳለው አይታወቅም:: አንድ ሰሞን ስለ አንድ ጉዳይ ወሬ ይነፍሳል......ብዙ ጊዜ ፖለቲካ:: ከረር ያለ ጨዋታ የሚመስል ነገር:: ስለፖለቲካ ግን ተነጋግረን፣ ተወያይተን፣ ሐሳብ ለሐሳብ ተለዋውጠን አናውቅም:: አንድ ሰሞን ግቢው ውስጥ ወረቀት ይበተንና፣ ወረቀቶቹ ላይ በደንብ የማይገቡኝ ጥያቄዎች ይደረደሩና እነሱ ካልተፈፀሙ አንማርም ይባላል:: በዚህ ጉዳይ ተማሪው ይከፋፈላል:: ብዙ ጊዜ ለሦስት:: አንደኛው ክፍል *`አገሪቷ ውስጥ የሰፈነው ጭቆና ካልጠፋ ትምህርት ቤት ደጃፍ ዝር አልልም'* የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው *`ትምህርት በማቆም ሥርዓት መለወጥ አይቻልም ስለዚህ እንማራለን'* የሚለው ነው:: ሁለቱ ይተማማሉ:: የመጀመሪያው ቡድን ሁለተኛውን *`የኢትዮጵያ ደሐ ሕዝብ በሚከፍለው ግብር እየተማራችሁ ችግሩን የማትሰሙት ወደፊት ዩንቨርሲቲ ገብታችሁ ዲግሪ ስታገኙ (አስረባሾቹም ዩንቨርሲቲ ገብተው እንደማይጠብቋቸው ሁሉ) ያሰባችሁትና ያለማችሁት ስራና የግል ምቾት እንዳያመልጣችሁ ነው:: በዚህ ታሪክ ይፋረዳችኋል'* ብሎ ሲያማ፣ ሁለተኛው ክፍል ደ`ሞ የመጀመሪያውን፣ *`እናንተ የደላችሁ የከበርቴ ልጆች ናችሁ:: ወይ በባእዳን የተገዛችሁ ግለሰቦች::*

ትምህርት በማቆም ሳይሆን በመማር ነው አገር የሚገነባው:: ይኸቺ አገር ያላት ዕድል እሱ ብቻ ነው` ይሉዋቸዋል:: እነዚህ ሁለቱ ከላይ የጠቀስኳቸውን ተምሳሌቶች ወደ እሻቸው እየተረጐሙ ይጣሉባቸዋል::

ሦስተኛው ክፍል/ቡድን ግን የእኔ ነው:: የእኔ ብቻ:: ትምህርት ቤት እንዲዘጋ አልፈልግም:: ሚኒሊክ ት/ቤት ዙሪያ ያሉ ተምሳሌቶችም መከራከሪያዬ አይደሉም:: አልፈራቸውም፣ አላደንቃቸውም:: አንድ ቀን እንኳን ተሳስቼ `ወደ ፊት ትልቅ ስሆን የዚህ ዐይነት ሕንፃ ይኖረኛል` ብዬ ተመኝቼ አላውቅም:: ወይም የዶሐ ጉጆ አይቼ ፊት ለፊቱ የተሰጣውን አሮጌ አንሶላና የተቀደደ ሹራብ አጥንቼ አስጠልቶኝም `ወደ ፊት እንደዚህ ዐይነት ልብስ እንዳልለብስ አሁን ትምህርቴን በደንብ መማር አለብኝ` ብዬ አላውቅም::

በዚያን ጊዜ የምጨነቀው ለአንድ ሰው ብቻ ነበር:: ለቆንጆዋ ለኢሌኒ:: ምን አለበት? እንዲህ ብጨነቅ?

ማታ የቤት ሥራዬን ሠርቼ ደብተሮቼን ቦርሳዬ ስከት የማስበው ቢኖር ኢሌኒ ቀን የጠየቀችውን የሆነ ጥያቄ ነው:: ጥያቄዋ መነሻ ሆኖኝ......ቀያይ ከነፈሮቿን:: ማታ ቅዳሚ ቅዳሚ የእንግሊዝ ክለቦችን ኳስ ጨዋታ እነ ቦብ ቻርልተንንና ጆርጅ ቤስትን በቴሌቭዥን ሳይ ትዝ የሚለኝ ቀልጣፋና ውብ እግር ነው......የኢሌኒ:: በየሳምንቱ ገላዬን ለመታጠብ ሻወር ስገባና ለስ ያለ ውሐ በላዬ ላይ ሲወርድ ትዝ የምትለኝ እሌኒ ናት......ለስላሳ ድምፅዋ:: ከቤቴ ወጥቼ አራት ኪሎ ድኩማን አስፋልቶች መሐል ስገባ ትዝ የሚለኝ የእሌኒ ፀጉር ነው......በተለይ የአስፋልቱ ሬንጅ ግሉ ቀልጦ ሲያብረቀርቅ:: ፀሐይ በሚያምር መልክ ወጥታ ጨረሯ ሠፈራችን ላይ ሲዘንብ ትዝ የሚለኝ የኢሌኒ ሳቋ ነው:: ክፍሌ ስገባ ዐይኖቼ በመጀመሪያ የሚፈልጉት ኢሌኒ የምትቀመጥበትን ዴስክ ነው:: ዴስኩ ባዶ ሲሆን እወዳለሁ:: ባዶ ካልሆነ ላያት የምችለው ተቀምጣ ነው:: ከተቀመጠች ደ`ሞ እግሮቿ ዴስክ ሥር ይደበቃሉ......ቂጧ ወደ ግድግዳ ይዞራል......የአካሔዷ ኪነት ይሠረዛል:: ከሌለች ግን ደስ ብሎኝ በር በሩን እያየሁ እቀመጣለሁ:: ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ ሳልገላመጥ በሩ ላይ አፍጥጬ እቀመጣለሁ:: አይቀርም ትገባለች:: ያኔ አያታለሁ:: ያኔ ሁሉ ያያታል:: የክፍላችን ግራጫነትና ቀዝቃዛነት ይጠፋል:: እንደ እሷ አይነት አንገት......ባት......ደረት......የጡት አቀማመጥ ያለው የለም:: እሷም ይገባታል:: ሁሉ እንደሚያያት ይገባታል:: ቅናት እንጀቴን ይበላኛል::

እንዲህ ሆኜላት ግን አብረን አንድ ዓመት አንድ ክፍል ተቀምጠን አነጋግሬአት አላውቅም:: ፊት ለፊት ደፍሬ ዐይኖቿን አይቼአቸው አላውቅም:: የእኔ ዋና ተምኔት ይሄ ነው: አንድ ቀን ላናግራት፣ ሌላ ቀን እንድጨብጣትና፣ ከምጨብጠው እጇ ወደ እጇ

ምን አይነት ስሜት እንደሚተላለፍ ማዳመጥና በሚተላለፈው ነገር መደሰት::

ሸፋች ተማሪዎች......የሸፈቱበትን ጉዳይ ጠልቀው ያልሸፈቱትን ‵ቀለሜዋ‵፣ ‵ሳቦተር‵ እያሉ ይሳደባሉ:: እኔ ግን ባይረዱም የምመች አልነበርኩም:: ቢሆንም ይኼ አያኮራኝም:: ምክንያቱም ለስድብ እሌኒን ለማየት ብቻ ትምህርት ቤት አመቱን ሙሉ ይከፈት ግልፅ ሆኖ አደባባይ የዋለ መከራከሪያ ሐሳብ ሆኖ አያውቅም:: ግለቴ የሚያሾረኝ ጉዳይ ቢሆንም ከእኔ በተቀር ሌላ ሰው እንዲያውቀው እራሴን አልፈልግም:: ግን ኢሌኒን ወደ ክፍል ስትገባ የሚሰራውን ሥራ አቁሞ የማያያት፣ ምክንያት ፈጥሮ ሊያዋራት የማይፈልግ፣ እንድትሰማው አድርጎ የማያሞግሳት ተማሪ አለ? የልብ እንነጋገር ተብሎ ያኔ በድብቅ ድምፅ ቢሰበሰብና ከኢሌኒና ከመሬት ላራሹ መፈክር ምረጡ ቢባል አብዛኛው ተማሪ ኢሌኒ ሳይል ይቀራል?

የሒሳብ አስተማሪያችንን ሲሳይ ወልደሥላሴን ከዘጠነኛ ጀምሮ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ድረስ ካሉት ተማሪዎች የማያውቀው የለም:: ዝምተኛነቱና ጥሩ አስተማሪነቱ ብቻ ሳይሆን ታዋቂ ያደረጉት ዝግተኛነቱና ድምፀ--ለስላሳነቱም ናቸው:: በተለይ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትን ጣጣ መጋተር ሲጀምሩ ቀለል ባለ እንግሊዘኛ......አልሆን ሲል ደ`ሞ አማርኛ እየደባለቀ በችግራቸው ተማሪዎች ዴስክ እየዞረ አጋጠመው ቦታ እየተቀበለ ስለሚረዳ ይወደዳል:: የተፈለገ ከባድ ጥያቄ ቢጠየቅ ተማሪዎች እንዲገባቸው አድርጎ በማብራራት የታወቀ ነው:: ግዙፍ ጭንቅላቱ፣ ትንንሽ ዐይኖቹ፣ የሚያማምሩ ከንፈሮቹ፣ አጭር ቁመቱ፣ ቀጭን ሰውነቱ፣ ሉጫ ፀጉሩ ቻይናዊ ያስመስለዋል ይላሉ:: ታዲያ `ሲሳይ ቻይናው` ይሉታል:: ግን በመውደድ ነው:: የሌላ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እንኳን ስለ `ሲሳይ ቻይናው` ያውቃሉ:: የተሰጠውን ቅፅል ስም ሰምቶ ያወቅ ይሁን አይሁን አላውቅም:: ለእኔ የሲሳይ ጉብዝ አስተማሪነቱ ሳይሆን የድምፁ ዝግተኛና ደካማ መሆን ከኋላ የሚቀመጡ ተማሪዎችን ፊት ለፊት ጥቁር ሰሌዳው አጠገብ መጥተው እንዲቀመጡ ስለሚያደርግልኝ በሚስጢር ሸርኬ ሆኖአል:: የሲሳይ ድምፅ ሸርኬ ሆኖአል:: ከኋላ መቀመጫ እኔ ወደተቀመጥኩበት ፊት ለፊት መስመር ከሚጉርፉት ተማሪዎች መሐል አንደኛዋ እሌኒ ናት:: ፊት ለፊት ባሉት ዴስኮች ላይ ሁለት ሁለት ተማሪዎች እንቀመጣለን:: ሲሳይ ሲመጣ ድምፁ ስለማይሰማ ሦስት ሦስት እንሆናለን:: ነገር ግን የእድል ጉዳይ ይሁን ወይም አስተይሜአት ኢሌኒ የምትቀመጠው ሰለሞንና ምንተስኖት ዴስክ ጋ ነው:: ምንም ሳያደርገኝ ሰለሞንን የምጠላው ለዚህ ነው:: በአንድ በኩል ግን ከእኔ ጋር ባለመቀመጥዋ ደግ ነው እላለሁ:: እንግዲህ የኔና የሰለሞን ዴስኮች ግራና ቀኝ ናቸው:: ኢሌኒ መጥታ ስትቀመጥ ብዙ ጊዜ በእኔ በኩል



@BOOKALEM

ነው:: ይኼም በጠቅላላ አንድ ጉንዋን ማንም ታዛቢ አደጋ ሳያደርስብኝ ላያት እችላለሁ:: ቀጥ ያለ አፍንጫዋን......ከንፈሮቿ የሲሳይን የሒሳብ ስራ እያዩ ሲያተኩሩ፣ የግራ እግሯን የሚያምር አጥንት-የለሽ ጉልበት (ከፊለ-ክብ ቅርፅ ያለው)......አንዳንዴም በጥንቃቄ ያልተዘረጋው መካከለኛ እርዝመት ያለው ቀሚሷ በትንሹ ወደ ላይ ተሰብስቦ......ከገፅዋ በመጠኑ ቀላ ያለ ጭኗን ሳይ በዚህም የሐሳብ መከፋፈል ይሆናል......የሲሳይ ቁጥር አስተማሪነት ከፍቶ ሳይሆን የሚያስተምረው አስደስቶኝ የማያውቀው:: ፀጥ ብሎ ካተኩረ በሰው ከሞላ ክፍል ውስጥ ነፍሲና ሀይኖቼ ተረብሸው ትምህርቴን የማልከታተለው እኔ ብቻ ሳልሆን እቀራለሁ?

ሰለሞን ቁልፍ ተማሪ ነው:: ቁልፍ ማለት ደፋር፣ ተናጋሪ፣ አሳማኝ፣ ደፍሮ ተናግሮ ማሳመን ብቻ ሳይሆን `ትምህርት እናቁም` ብሎ ተናግሮ ማስቆም የሚችል ነው:: ማውራት ከጀመረ አያባራም:: በከፊል እቀናበታለሁ:: አንዳንዴ በጣም እቀናበታለሁ:: የፈለግሁትን፣ ሰው የፈለገውን ማንኛውንም ጉዳይ ሳላቋርጥ፣ ሳላባራ ባወራ ደስ ይለኛል:: ሲሳይ ከሔደ በኋላ ኢሌኒን ከሌሎች ልጆች ጋር ደርቦ በወሬ ጠምዶ ዴስኩ ላይ አምስትና አስር ደቂቃ የሚያስቀያት እሱ ነው......መሐል ዳሽን ካፍቴሪያ ስለተዋወቀው የዩኒቨርስቲ አራተኛ ዓመት ተማሪ ያወራታል፣ ኰሌጅ ግቢ ካለው ምግብ ቤት ወይም ካፊቴርያ ምን ምን ዐይነት ምግብ እንደበላ ያወራታል:: በጊደኞቹ ክብርና ክብደት እኛ እንድንፈራው ይፈልጋል:: ብዙዎቹ ያከብሩታል፣ ይፈሩታል:: እኔ ግን ያበሳጨኛል:: አልፈራውም፣ አላከብረውም:: ምክንያቱም በኢሌኒ ምክንያት ብቻ ሳይሆን የጥርሱ አበቃቀል:: የጥርሱ ሽግን ማለቴ አይደለም:: የጥርስ ሽግን ይጠረጋል፣ የጥርስ ሽግን በመፋቂያ ይፀዳል:: የሚያናድደኝ የድዱ እርዝመትና የጥርሶቹ ማነስ ናቸው:: አንዳንድ ጊዜ የእግዚያብሔር ሴራ የተጠናቀቀ ይሆናል:: ሲፈጥር ያበላሸና ማበላሸቱን አከራሪ ሳድርገው ብሎ ነው መሰል ሽግናም ያደርጋል:: ሽግናምም ነው:: ሲስቅ አልወደውም:: እንደዚያ የምታምር ኢሌኒ ፊት ያለ እፍረት ቢጫ ጥርሱንና ቀይ 'ፐላስቴር' የመሰለ ድዱን ሲያሳይ አለማፈሩ ይገርመኛል::

አንድ ቀን ጎኔ ከሚቀመጠው አንድ ተማሪ ጋር እያወራን ስንመጣ ሰለሞን ከሌሎች ሦስት ሰዎች ጋር በረንዳ ላይ ቆሞ ጉራ ሲቀጭ ደረስን:: የሰለሞን ችሎታ በተፈለገው አርዕስት ላይ ማውራት መቻሉ ነው:: እነዚህንም የወሬ አርስቶች በምሳሌ፣ በሚያውቀው ታሪክ አቀናበሮ፣ ቅጥፈት ቀባብቶ ያቀርባል:: አንዳንዴ የችሎታው ስፋት የሚያስተማምን መሆኑን እጠራጠራለሁ:: ስለመኪና ወሬ ሲነሳ...... ስለመኪና ብዙ አውርቶ የሚያውቀውን ሰው ጠቅሶ......ታሪኩን የሚገርም፣ የሚያስቅ አድርጐ ያቀርበዋል:: ስለተማሪ ረብሻ ሲነሳ



@BOOKALEM

ተማሪ ሁሉ ያደረገውን አንስቶ፣ ዩኒቨርስቲዎች ባደረጉት አድርጉ፣ የእሱን አስተዋፅኦ ይጠቅስና አስቂኝ ነገር ከመሐል በኩል ተማሪውን በሳቅ ያፈርሰዋል:: አርፌ መስማት እንጂ የቱን ስከቱ የቱን እንደምጥል ግራ ይገባኛል:: አምኒ

ታዲያ በዚህ ቀን ሲያወራ አገኘነውና ተቀላቀልን:: እንደአጋጣሚ ወሬው የዩንቨርሲቲ ሴቶች ስለመጥበስ ነበር:: ወሬው ከዚያ ከምጣላው የሰለሞን አፍ ይወጣል......

«ወይ አቦ ገርዳሜ ነው የምትመስለው:: ታቂያለሽ አለ አይደለ......ጠጋ አልኩና እህት ቡና እንጠጣም? አልኳት......የገላመጠችኝ መገላመጥ......በኋላ አጠገቤ ያ ማነው ቆሞአል:: `አቦ ይኸቺ ዶና ልትገለኝ ነበር......እና ልጋብዝሽ ብላት......ምንድነው? አጠፋሁ?` ስለው፣ `እንዴ ይኸቺ የኬሚስትሪ ዲስትንኪሽን ተማሪ ናት:: ወንድ አታናግርም` ምናምን አይለኝ መሰለህ:: ወላ ቀልቤ ወደቀ:: እንዲሁ አንድ ቀን ትምህርት ሚኒስቴር ወረድ ብዬ......ወላ አቦ ደብሮኛል አንድ `በርድ`[13] ይዘሽ ጁውስ ምናምን የምትገጪበት ዐይነት ቀን ነው......አንዷን ጠጋ አልኩና `ወዴት ነው?` አልኳት:: `ምነው አንተ የእንትና ጓደኛ አይደለህም? ጥሩ አይደለም` አትለኝ መሰላችሁ? እኔ አላውቃትም:: እሷ ታውቀኛለች:: አየህ ሴት በጣም ሲቀራረብ ማን ምን እንደሆነ ማወቅ ብቻ ሳይሆን መንቃነቅ አትችልም አቦ......ለመጥበስ ብዬ እስኪ በእናትህ ሽመልስ ሐብቴ ልውረድ እንዴ?» ብዙዎቻችን ሳቅን:: በንግግሩ መሐል ያጋጠመውን ሰው ትክክሻ ይመታል:: አፉን ወደ ላይ ከፍቶ ይስቃል:: ጥርሱን እግዜር ይመስገን ያኔ አላየውም::

«ታዲያ እዚህስ እንዴት ነው?» ይለዋል አንዱ ለጫወታ::

«በቃ እዚህ ያቺ ጓደኛዬ አለች......በቃ መቅዲን ታውቂያታለሽ አይደለ?......መታሰር እኮ ነው አቦ......»

«ከኢሌኒ ጋር ጉዳይ የለሽም?......እስኪ በእናትሽ......»

«እይ......»

«ኩስተር ትልብሻለች......ቀለሜዋ አትወጂም መሰለኝ?»

«የሴት ቀለሜዋ የለውም:: እንዲህ የሚኩሳተሩት ውሽታቸውን ነው:: እንዲሁ አንድ ጊዜ ለሙከራ አለ አይደለም you know[14] ሲሳይ ሲመጣ ጉኔ ትቀመጣለች አይደል......እንዴቀልድ አድርጌ ጭኗን ዳበስኳት አለ አይደለ ሳታስበዪ ምናምን......»

---

[13] ወፍ(እንግሊዘኛ) ሴት/ልጃገረድ ማለት ነው በከተማ ቀበሌኛ

[14] ታውቃለህ



@BOOKALEM

«ሊድ?» አለ አንዱ::

እኔ የሰለሞንን እጁን አየሁት:: እጆቹን እስከዛሬ አይቼአቸው አላውቅም:: በእሱ በስተግራ ስለምቀመጥ ሊነካት የሚችለው በግራው ነው:: ጣቶቹ ረዣዥም ናቸው:: እጆቹን ሲናገር ስለሚያነቃንቅ የጥፍሮቹን ቀለም፣ መጠንና ቅርፅ ለማየት ዕድል አላጋጠመኝም::

«......ካላመንክ እሱን ጠይቀው» አለ በአገጩ ወደ ዴስክ አጋሩ እየጠቆመ::

የዴስክ አጋሩ ምንተስኖት እንደ ሰለሞን መሆን የሚጥር ከመሐል ግን ኩፍ ብሎ የቀረ ነው:: ቀልድ እየሞከረ የሚወድቅበት፣ ወሬ ጀምሮ የሚፈርስበት ነው:: ታዲያ ሰለሞን አብሮት ካለ ለዕርዳታ ይቀላውጠዋል:: ሰለሞን በቅልጥፍናው መሞት የጀመረውን ወሬ ነፍስ ሰጥቶ፣ የሚያስለቅሰውን መሳቂያ አድርጎ፣ ምሳሌ ያጠረውን በምሳሌ አዳብሮ ያነሳለታል::

«አዎ» አለ ምንተስኖት

«እንዴት እባክህ? እሷ እኮ የዚህ ዐይነት......» አለ ሌላው

«ሴት ድፍረት ነው የምትወደው:: ሙት:: ያኔ ስነካት የተናደደች መስላለች ግን ደስ ብሎአታል:: ይሞቃል ጭኗ:: ሙት»

«ከዚያስ? በቃ ተውሽ?»

«ሴት ድፍረት ብቻ ሳይሆን ወሬ ጥዝጠዛ ትወዳለች:: ኢሌኒም እንደዚያው ናት:: ልበልህ ያደረኩትን ለጓደኛዬ ብትነግራትስ?»

«አትናገርም:: የት ይተዋወቃሉ?»

«በል በል! የመጨረሻ ወሬኞች ናቸው እኮ:: ሴት ሲባል ወሬኛ ነው አቦ......በትውውቅ በትውውቅ ምላሳቸው የማይደርስበት የለም......ተው እባክህ ዝም ብዬ ባያት ይሻላል:: የምልህ አጉል ስህተት ከምሰራ:: አጠገቢ መጥታ ብትቀመጥ አይሻልም?»

ሳቅን:: 'አዎ ይሻላል' አልኩ በልቤ:: ኢሌኒን ቻላ የማለት ሐሳቡን ወድጄአለሁ:: ለምሳሌ በሰለሞን ፍላጎት ተደናግጣ ድንገት ቦታ ብትለውጥና ከኋላዬ ያለው ዴስክ ላይ ወይም ዕርቃ ወዲያኛው ጋ ብትቀመጥስ?

«ግን ምን መሰላችሁ:: ቀላል ነው:: ከጓደኛዬ ከመቅዲ ጋር ብጣላ ያኔውኑ ነው የማወርዳት:: ቆንጆ ደና ናት:: እስከዚያ ድረስ ግን እየተስማማህ ትጠብቃለህ:: በዚህ ላይ ትምህርቷን በደንብ ትሰራለች:: ትዝ ይልሐል ሳይመልቲኔስ ኢኩዌሽን ራሳችንን ያዞርንበት? ወላ እሱን በሰከንድ ሰራችው:: አስተማሪውን ሳትበልጠው አትቀርም»

ሁላችን ደገፍን:: የምጠላው ነገር ስለ ትምህርት ሲነሳ ነው:: ሆኖልኝ አያውቅም:: ዕድሜ ልኬን ሆኖልኝ አያውቅም:: ከአንደኛ



@BOOKALEM

ክፍል እስከ 11ኛ ክፍል ያገኘኋቸው ደረጃዎች ተካፍለው አማካኝ ብወጣ 24ኛ ይሆናል:: አጠናለሁ፣ አጠናለሁ መያዣ ልብ የለኝም:: ከዳር እስከዳር ደብተሬን እንብቤው በበነጋታው ምኑ ከምኑ እንደሚያያዝ ይጠፋኛል:: የቱ የት እንዳለ ይሰወረኛል:: አንዱ ከአንዱ ይምታታብኛል:: ሳላውቀው ከሥር ሕሊናዬ ከኢሌኒ የሚያርቀኝ የአእምሮ ደካማነቴን መቀበሌ ይሆናል:: ምናልባት የእሷ ዐይኖች አድንቀው ያርፉብኝ እንደሆነ ብዬ ሌት ተቀን እሰራለሁ፣ ሌት ተቀን አጠናለሁ:: እኔ የችሎታ ደካማነቴን በዝምታ ሳልፈው ሰለሞን ያወራዋል:: ሰለሞን ፈተና ወድቆ አውርቶት ዝቅ አድርጎ የሚያየው የለም:: ተስቆ ይታለፋል:: እኔ ግን ጉኔ ከሚቀመጠው ልጅ ጀምሮ ግድግዳ ላይ እስከ ተሰቀለው የንጉሰነገስት ሐይለስላሴ ፎቶ ድረስ 'ምን ሆንክ?' የሚለኝ ይሰለፋል::

ኢሌኒን በዐይን ብወዳትም ስለ እሷ የማውቃቸው ነገሮች እጅግ ጥቂት ናቸው:: ለምሳሌ ጉበዝ ተማሪ የሆነችው በጣም ስለምታጠና ነው ወይስ አእምሮዋ ብሩህ ሆኖ ነው? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ አልችልም:: ብጠይቅም መመለስ አልችልም:: ስለዚህ አልጠይቅም:: ከአባቷ ስም በስተቀር የእናቷን አላውቀውም:: ሠፈሯን እንኳን አላውቀውም:: ይሄን በሚመለከት የማውቀው ትንሽ ነገር ቢኖር የትምህርት ጊዜ ሲያልቅ በስድስት ኪሎ አቅጣጫ ወደ ላይ ወጥታ ቅድስት ማርያም ስትደርስ ወደ ግራ መታጠፏን ነው:: እሷን መውደዴ የሚታወቅብኝ ስለሚመስለኝ የት እንደምትገባ ለማየት ተከትዬአት አላውቅም:: ይሔ ይሔ ድ`ሞ የራሷ ጉዳይ ይመስለኛል:: የራስዋ ጉዳይም ነው:: ሁልጊዜ በላይዋ ላይ የተሰፋ የሚመስል ነጫጭ የቁም ሰንበሮች ያሉት ጥቁር ቀሚስ እንደምትለብስ አውቃለሁ:: ይሔን የመሰሉ ሦስት፣ አራት ቀሚሶች ይኑሯት አላውቅም:: ነገሩን ነው እንጂ የሚያገባኝ ነገር የለም:: ግን ነጭ ሰንበሮች ያሉበት ጥቁር ቀሚስ የምትለብስ ተይ ዳግ ቀጭን ልጃገረድ እንዴት እንደምታምር የሚያውቅ አለ? በተለይ ስትስቅ በመሸኮርመም አፏን በጣቶቿ ጋርዳ እንገቷን ሰበር የምታደርግ? በችከላ ስትራመድ ሳንቲሜትር ያህል ወደ ላይ የሚሰበሰብ ቀሚሷ የሚያጋልጠው የጠበደል ጭኖቿን ቅላት አይቶ ያልተከዘ ይኖራል? አፏን እዚያ ላይ እንደ አልቂት ለጉሞ ከውስጧ ማርና ወተት ሊመጥ? እናቷንም አልወቅ፣ መኖሪያዋንም አልወቅ የቀሚሷንም ሆነ የሻሸዋን ብዛት አልወቅ ለእኔ ኢሌኒ ተወዳዳሪ የሌላት ውብ ናት::

«እስኪ መቅረጫ አለህ?» ብላ አንድ ቀን በጉሉ ዐይኖቿ ትኩር ብላ ስታየኝ......መቅረጫው ፊቴ አለ፣ እሷ `መቅረጫ` ስለ ተባለ ቀላል ጉዳይ ነው የምታወራው፣ ሰለሞን በቀኝ ጉኗ ሆኖ የማያልቅ ተረቱን ይነግሩናል (አፍ የሚሸጥበት አገር ቢሄድ ይከብር ነበር):: እኔ ግን ጥያቄዋን መመለስ አልቻልኩም:: በእነዚያ ከንፈሮቿ አማርኛ



@BOOKALEM

የምትናገር አይመስልም:: ሌላ መለኮታዊ ቋንቋ ይመስላል:: ፊደላቱ ምናምን የሚጥም ነገር ተቀብተው እየተንሸራተቱ የሚወጡ ነው የሚመስሉት:: ድምፅዋ እንደ ጣዝማ ነገር ነው:: ቃላቶቿም እንደወለላ የሚጉተቱ:: የጥርሶቿ ንጣት የሚያርፍበትን ብርሐን ጠቅላላ መልሶ ይሰጣል:: የጆሮዎቿ ትንንሽ ጌጦች እንደ ትንንሽ ኩኩቦች ያበራሉ (መንታ አስታርቶዎች):: ጡቶቿ መሐል የተኛው የሐብሏ ስቅለ–ወርቅ ትንፋሽ እንዳለው እንደ አናሳ ፍጡር ይንቃነቃል:: በዚህ ላይ አንገቷን የሆነ ነገር አድርጋ ዘንበል ታደርገዋለች......ቅጥንቱ እንዲታይ ሁሉ:: እኔም ጤነኛ ሰው የሚያደርገውን ነገር አደረግሁ:: መቅረጫውን ረሳሁ:: እሷ ግን ያሰሁ አልመሰላትም:: በብርሐን ፍጥነት እኔን ከተቀመጥኩበት አንስተው በቦታዬ ፍልፈል፣ ቆርኪ፣ ወይም ሲጋራ የምታጤስ ሰጎን ቢያስቀምጡ......ሁኔታዋንም ሳትለውጥ: «እስኪ መቅረጫ አለህ?» ማለቷ አይቀርም::

ታዲያ እየቆየ ሁለት ስሜቶች እየተፈጠሩብኝ ሔደ:: እኔ እሷን እንዳየሗት ሁሉ እሷ እኔን አለማየቷ ያበሸቀኝ ጀመር:: (አምባገነኖች የሚወለዱት በዚህ ዐይነት የሥነልቦና ግጭት መሐል ይሆን እንዴ?) ባትወደኝ እንኳን ክፍል ውስጥ እንዳለሁ አለመገንዘቧ ያናድደኛል:: ዙሪያዋን ባሉ ወንዶች መደነቋ፣ ተፈላጊ መሆኗ፣ የምትታይ እንጂ እሷ የማየት ሥራ እንደሌለባት እየጠቆማት ይሆናል:: ግን ያስታውቃል እኩ ወንድ ልጅ መቅረጫ ተጠይቆ ልቡን ነስቶት አፉን ከከፈተ......(ያ መቅረጫ አያስጠላም?) ጥቋቁር ዐይኖቹም ተጉልጉለው ጉንጮቹ ላይ እንደ ቃጭል ቆለጥ ከተንዠዋዠው.....

አንድ ቀን ማታ የቴሊቪዥን ኳስ ጨዋታ ካየሁ በኋላ የቤት ስራዬን ለመስራት መኝታ ቤት ስገባ ኢሌኒን ለማነጋገር ቁርጥ ሐሳብ አደረግሁ (እንደ ትልቅ ዓላማ):: ይሔ ሐሳብ በየት ቀዳዳ ጭንቅላቴ ውስጥ ገብቶ እንደሰፈረ ትዝ አይለኝም:: አንዲት ሴት ላይ ተደብቆ በማፍጠጥ ምንም ሊገኝ እንደማይችል ስለተረዳሁ ይሆናል:: የማንቸስተር ዩናይትድ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ከመከላከል ይልቅ በማጥቃት ማሸነፋቸው ትምህርት ሰጥቶኝም ይሆናል:: እሷን ከማዋራቴ በፊት ግን አንዳንድ ነገሮች መለማመድ ነበረብኝ:: እንዴት እንደምናገር፣ ምን እንደምናገር፣ የት ቦታ እንደማናግራት......እነዚህን ሁሉ መለማመድ ነበረብኝ:: በተለይ ቴንጥ አስፈላጊ ነው:: ሺህ ልብስ ለዋውጬ አላየችኝም:: ፋሽን ቀያይሬ አላየችኝም:: ስህተቴ በአፍ አለመቅረቤ ይሆናል:: በአፍ:: የሚያጥረኝ እሱ ነው:: አፍ::

ልምምዴ ግን የማልፈራቸው ሴቶች ላይ መሆን አለበት:: ለምሣሌ በመንገድ ሳልፍ ታክሲና አውቶብስ የሚጠብቁ ልጃገረዶች:: ካፌቴሪያ ገብቼ ጁስ ስጠጣ ተያይዘው የሚገቡ ልጃገረዶች ካሉ እነሱን በመጥቀስ የሚያወርዱትን የስድብ ሆነ የትችት ናዳ መቀበል:: ወይም በመልሱ



@BOOKALEM

ቁና ሙሉ ጥቅሻ፣ ባጣ ሙሉ መሽኮርመም መቀበል:: ከእነዚህም ትንንሽ ልምዶች ለኢሌኒ የሚሆነኝን ማቀነባበር:: ታዲያ ቤቴ ውዱ ሳጠና፣ ሳነብ፣ ልብስ ሳጥብ ሬዲዮ ስሰማ የምውለው ሰው ከሰኞ እስከ አርብ ሲመሽ ወይም ቅዳሜና እሁድ ቀን ከተማ ውስጥ መዋል ጀመርኩ:: ሲኒማ ኢትዮጵያ ሲኒማ አድዋ ሲኒማ አምፒር ቤቶቼ ሆኑ:: አብሬ የምውላቸው ልጆች ፈጣን ፒያሳንና አራት ኪሎን ያቃጠሉ ሆኑ:: ሺህ ሴቶች ጠቀስኩ:: 250ዎቹ ዘጉኝ:: 250ዎቹ ተሽኮረመሙ:: 250ዎቹ መልሰው ጠቀሱኝ:: 250ዎቹ ሰላም ይሉኝ ጀመር:: ሰላምታ ከሚሰጡኝ ሁለት መቶ ሃምሳዎቹ መቶው ከአራዳ ልጆች ጋር በመዋሌ፣ መቶው መልኬ ደስ ስላላቸው፣ የቀሩት ደግሞ ደጋግመው ስላዩኝ ነው:: መልኬ ደስ ካላቸው መቶዎቹ ሃምሳው አብረውኝ መሆን ሲፈልጉ ሃምሳው አድንቀውኝ ያለፉ ናቸው:: አብረውኝ ከሚሆኑ ሃምሳዎቹ ሃያ አምስቱ እየተጫወቱ ሊያዩኝ የሚፈልጉ ሲሆኑ የቀሩት ልባቸው የከጀለ ናቸው:: ከቀሩት ሃያአምስቱ 12 ተኩሉን ስስማቸው 12ቱን ስተኛቸው የቀረቿ ግማሽ ሴት ግን ጀርባዬ ላይ እንደ ቡግር ተተክላ ፊቴ ላይ እንደ ዒም በቅላ ሚስቴ ሆነች......ስድስት ዓመት ሳትለየኝ::

ከመሐል ኢሌኒን ባልረሳትም ጠፋች::

የቀረው ጊዜ የሕይወቴ ክፍል ያለፈው በስለላ ነው:: አገሩ ስለተበጠበጠ የድሮ የሚኒሊክ ተማሪዎችን ማግኘት ከባድ ሆነ:: ያጋጠሙኝን አንድ ሁለቱን አዋርቼ በጠመዝማዛና በቀጥታ መንገድ ብጠይቅ ኢሌኒ የሔደችበትን የሚያውቅ ጠፋ:: ታዲያ በጉዳና ስሔድ በወዲያ በኩል ቀይ የምታምር ሴት ሳይ ኢሌኒ እየመሰለችኝ እደነግጣለሁ:: ምሽት ከሆነና በደንብ ማጤን ካዳገተኝ የአስፋልት መንገድ መሐል ከዕብድ ታክሲ፣ ከጉረኛ ባለመኪና ታግዬ እሻገርና ሴቷ ዙሪያ እንዣብባለሁ:: ኢሌኒ አትሆንም:: ጊዜ ካለኝና ከተመቸኝ ያቺው ያጋጠመችኝን አናግራለሁ:: የኢሌኒ ልክፍት ሆኜ ነው መሰል......ቀይ ዳማ (ትንሽ ቀላ ያሉ) ፀጉረ ሉጫ፣ ቀጠን ያሉ ሴቶች ዐይኖቼ ውስጥ የሚነድ ሾተል ሰክተው ይሔዳሉ:: (የሀበሻ ሴት ቀለም ብዛት......የጠይሞቹ፣ የጥቁር ጠይሞቹ፣ የቀዮቹ፣ የቀይ ዳማዎቹ፣ የፍኮቹ፣ የብልጭልጮቹ......ታዲያ ዐይኖቼ ውስጥ የሾተል ደን አለ) ሚስቴም ቀይ ናት ግን ወፍራም፣ ረዥም......እ! ረዥም ሴት::

ሁልጊዜ ታዲያ ሚስቴን እንደሸሸኋት ነው:: ከሥራ ስመጣ ካልመሸ በረንዳ ላይ እቀመጣለሁ:: ከእኔ ጋር በተገኘው ሰበብ ሁሉ መዳራት ስለምትፈልግ በረንዳ ላይ አንድ አሮጌ ሶፋ አለ እዛ ሄጄ እቀመጣለሁ:: የግቢያችን በረንዳ ከውጭ ከመንገድ ስለሚታይ ስድ ነገር ለመስራት አትደፍርም:: (አፈ-ደፋር፣ ድርጊተ በቅሏቃ ናት) መኝታ ቤት ስገባ ቶሎ ራሴን እቆጣጠራለሁ:: ለምሳሌ የበላሁትን



@BOOKALEM

ምግብ በማማት ሆዴን ረቂቅ ቁርጠት እንደመታው ሁሉ አልጋ ውስጥ እገባለሁ:: አንዳንዴም ቆንጥንጥ ያደረጋት ከመሰለኝ መኝታ ቤት ገብቼ በመተከዝ እቀመጣለሁ……ሥራ አበሳጨኝ ብዬ (`ይኼ ደርግ የሚባል ነገር የሌለ ነገር ያሰራናል!`……የመሰለ……ግን ኪሬዳሽ ነኝ) አንዳንዴም ፊቷ ላይ የወንድ አምሮት ሲንቀለቀል ላይ ቴሌቭዥን ፊት ለፊት አለምን የሚያስገርም ድብርት ተደብሬ እቀመጣለሁ:: (ግን ምንም አላይም):: ሚስቴ ታዲያ ቅጡ ይጠፋታል:: ትዳብሰኛለች፣ መድሐኒት ታመጣለች:: (የውሸቴን እውጣለሁ፡ አልሞት መቼም) ሰራተኞችን ትረግማለች (ሰራተኞችን እንከን የሌላት ናት)……ከዚያ ሠራተኞችን መግለጫ አንሰራም:: እኔ……በየሚዳው (ባሕሊ ያላመደኝን ፍቅር ገበናዬን) ወደ ኢሌኒ የሚጠጋ ቀይ ዳማ እየፈለግሁ ጥንጌን የወሲብ ብከት የልቤ አልደርስ አለ:: ሚስቴ አጠገቤ ቁጭ ብላ ብከት ብከት ትቃጠላለች (አለበለዚያ ውስጥ ልብስዋ ለምን ሐምራዊ በፍላጉት እንዳንድ ጊዜ ለምን እንዳገባኋት ራሴን ስጠይቅ መልስ መሰለ?):: እኔን የሚወደኝ (የሚያምነኝ ብል ይሻላል፣ መስጠት ይከብደኛል:: ስለሌለና እሷ ብቻ ስለምትወደኝና ሽርሙጣን ማን ያምናል) ይሆናል:: ከእነዚያ ሁሉ ሴቶች እሷ ብቻ ፍቅር:: ስለምታምነኝ(?) የእሷ ደንቃራ:: እሷ የእኔ ደንቃራ:: ግን ሚስቴ ከኢሌኒ አላለያየችኝም::

ይመስላል እንጂ::

የሆነው ምንድነው……አንድ ጊዜ ት/ቤት ቆመ……ኢሌኒ ጠፋች:: ኮሌጅ ጥፍ:: ስለ እሷ ባጠያይቅም የሚያውቅ አልነበረም……ጠፋች:: ኮሌጅ ገባሁ:: ላይ፣ ታች ኮሌጅ ብፈልጋት ጠፋች:: ጥፍ:: እንደመተብተብ ነገር ሆንኩ:: ከላይ እስከታች ከእግር እስከአንገት:: ስለማዕድናት ስማር 'በኢትዮጵያ ወርቅ፣ አልማዝ፣ ዩራንየም፣ ናቹራል ጋዝ፣ ታንታለም፣ ፎስፌት አለ' እያሉ ካርታ እየጠቆሙ ሲያወሩ……`እንዴ? እንዴ? ……ኢሌኒስ?` ማለት ይቃጣኝ ነበር……

ፕሮፌሰር!……ፕሮፌሰር!……

እዚህ ሚሾቴ ለመቅጠን `ዳይት`[15] ስትጀምር (በልቤ `ያበሻ ዳይት` እያልኩ) አጨበጨብኩ:: ቢያንስ በቅጥነቷ ኢሌኒን እንድትመስል:: ቢባል ቢባል……ከጡቶቿ ሥር ተነስቶ ታች እፍረትዋ ድረስ ያለው የሆድዋ ቅንፍ እንደ ደጋን ከመስፋት አልተገታም……አልጠፋ አለ:: ጡቶቿ ከርዝመታቸው ከአወዳደቃቸው አልመለስ አሉ:: ብልሐቷ ግን ለእኔ ሳትነግረኝ……በዘመዶቼ ተወዳ፣ ዘመዶቼን ከዘመዶቿ አስተዋውቃ……ቆይታ ቆይታ `አረገዝኩ` አለችኝ:: `እትዬ (እትዬ ነው ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለእናቴም……እናቴን አቅፋ የምትላት) አረገዝኩ……ፀነስኩ`::

---

[15] ለመክሳት የሚደረግ አራብን ከምግብ የሚገለልና መርጦ የመብላት ባሕል

ታዲያ በተለያየ አቅጣጫ ተወረደብኝ......

«ይኸቺን የመሰለች ልጅ......»

«ምን ፈለግህ ከእሷ ሌላ......»

«ውበት ትፈልጋለህ......ውበት አላት:: ሙያ ትፈልጋለህ......ሙያ አላት:: ፍቅር ትፈልጋለህ--ታፈቅርሃለች፣ የተማረ ትፈልጋለህ. ተምራለች:: ሌላውን አናውቅም»

እኔስ? እኔስ? እኔ ተረሳሁ:: እኔና እሌኒ ተረሳን:: (ለብቻዬ ራሴን እየጠየቅሁ)::

ልጁ ተወለደ:: ወንድ:: ጉበኚ ሁሉ `የወርቅ ፍልቅቅ የመሰለ' የሚለው:: ግድ አልሰጠኝም:: ተፈለቀቀ:: አልተፈለቀቀ:: የመጀመሪያውን ልጅ በጣቴ እንኳን ነክቼው አላውቅም:: ሲያለቅስ......በተገኘበት ሚጢጢ ትራስ አምጥቼ በተበለቀጠው አፉ ባስገባ እወዳለሁ:: ወይ ትልቅ ወንጭፍ ላይ አስቀምጬ......ልክ እንደ ጠጠር ወደ ሆሊታ ብተኩሰው......በጉዲፈቻ ማደጉ አይቀር:: የሚያበሽቀኝ እኔን መምሰሉ:: ለመካድ እንኳን አያመች::

ባለቤቴ የሆነችዋ ሴት በሌሎች ሰዎች ግምትና አባባል `ቆንጆ ነች' ብትባልም ለእኔ ሆና ታይታኝ አታውቅም:: ከእሷ ጋር የተሳሰርንበት ነገር እንደሚመስለኝ እሷ በመፈለጒ እኔ ባለመፈለጌ ነው:: ከሰው የመግባባት ትልቅ ችሎታ አላት:: እናቴ ከእኔ የበለጠ ብትወዳት......አባቴ ሲያገኛት ጉንጯን ቢስማት የሚገርም ትእይንት አይደለም:: ለአስር ደቂቃ የተገናኘችውን ሰው አቆላምጣ ትጠራለች:: በዚህም አታፍርም:: በእኔ ቸልተኛነትና ገለልተኝኛነት መሃል አሟቲ፣ አያያዥ ሆና ትገባለች:: ሴት መሆኗ ነው እንጂ ከሰለሞን የሚመሳሰል ነገር አላት:: የከፋኝ ዕለት፣ የራቅኋት የመሰላት ዕለት ሰው መሃል ሳታፍር ታለቅሳለች:: ምክንያት ፈጥሬ ክፍሌን ዘግቼ ስቀመጥ ከቴዎድሮስ አደባባይ ቤቷ የታክሲ ካገኘች በታክሲ፣ የታክሲ ካላገኘች በእግር ደብተሯን ተሸክማ ትመጣለች:: አንዳንዴ እግሮቼ ላይ ክንፍ ተክዬ ወደ ሌላ አገር፣ ብራዚል ኮሎምቢያ ምናምን መሔድ እፈልጋለሁ......መጥፋት:: የእሷ ስህተት እኔን መውደዷ አልነበረም:: ስህተቱ በእኔና በኢሌኒ መሐል መሰንቀሯ ነው:: ስስማት እየተማረኩባት ነበር:: እስዋ ግን ራስዋን ስታ አፌን ትታ ክንዴ ላይ ግማሽ ሰዐት ትተኛለች:: የደከመ፣ የሚያናውዝ፣ ሰመመን የገባ ቅድመ—ሚስት ሴቴን በገዕዋ ስሜወትና ከንፈሮችዋን ስስም ትዝ የምትለኝ ኢሌኒ ናት::

«ኢሌኒን እንዲህ ስስማት ትተኛለች?»

«የትናንቱ አሳሳም ይሻላል የዛሬ?»



@BOOKALEM

«ከንፈሮቿ የደረቁ የሚመስሉት ለምንድነው?»

እስክትባንን ድረስ ሲኒማ ላይ ካየኋቸው የአሳሳም ዐይነቶች አንዳንዶቹን እሞክራለሁ……ተራ በተራ (እንደ ክሊንት ኢስት ውድ፣ እንደ ሾን ኮነሪ፣ እንደ ጀምስ ኮበርን……ምናምን):: ከመሃል ከባንነች እሷን ፈልጌ በፍቅር ብዛት ሰክሬ ፋታ ልሰጣት ያልፈለኩ ይመስላታል:: ለዚህ ድርጊቴ ራሴን ይቅርታ ጠይቄ አላውቅም:: የምሰራው ስህተት አይመስለኝም::

በመንፈሴ ግማሽ ከእሷ፣ ግማሽ ከኢሌኒ ጋር ነኝ:: ግማሽ ሚስቴ::

የእኛ ባች የነበረው የሚኒሊክ ተማሪ ለአብዮትና ለእንጀራ ተበታትኖ ከፊሉ ኰሌጅ፣ ከፊሉ ወደ ሞት፣ ከፊሉ ወደ እሥር ቤት፣ ከፊሉ ወደ ውጭ አገር፣ ከፊሉ ወደ ሥራ አለም፣ ከፊሉ በየቤቱ ሲቀር እኔም በራሴ ተራ ኰሌጅ ተመርቄ ወጣሁ:: በማዕድን ልማት ሚኒስቴር የሐይል ምንጮች ጥናት ግብረ-ሐይል ውስጥ ጠቢብ ተብዬ ተመደብኩ:: እንግዲህ ይሔ ሁሉ ጊዜ አለፈ:: ከመሐልም ግማሽ ሚስቴን አገባሁ:: በዚሁም ሁለት ልጆች ወለድኩ:: የበሸቅሁ ዕለት እነዚህን ልጆቼን መዝሩጥና ማንሾለላ[16] ብዬ እጠራቸዋለሁ::

ታዲያ ኢሌኒን ለመጥበስ ብዬ ያደረግሁት ልምምድ ፀባዬ ሆኖ በቅሉብኝ ብዙ ጊዜ ቤቴ አልውልም:: ይሔ ደግሞ የሚስቴና የገንዘቤ ጠር እንደሆን ይገባኛል:: ምናልባት ሚስቴ ሰራተኛ ባትሆንና፣ የወሩን እስከ ወር እያባቃች የማታልፍ ቢሆን ኖሮ መዝሩጥና ማንሾለላ በረሐብ ያልቁ ነበር:: ቢያልቁም ግድ የሚሰጠኝ አይመስለኝም:: የኢሌኒ ልጆች ቢሆኑ ኖሮ ግን ራቁቴን ሆኜ እነሱን ሐር አለብስ ነበር:: ሚስቴ በእስዋ እንዳልተደሰትኩ ሁልጊዜ ይገባታል:: ሁልጊዜ ታመራለች:: ሁልጊዜ እግዜር ልቤን እንዲመልሰው ቅድስት ማርያም ወጥታ ትፀልያለች::

የሚገርመኝ ግን በዚህ በፈራረሰ የስሜት ወጣ ገባ ውስጥ ለሰዎች አማራኝ አታውቅም:: እኔን አምታኝ አታውቅም:: ነገሩ ያስጠላቸው ወዳጆቿ: 'ምነው አንቺ አንድ ነገር አርጊ እንጂ' ሲሏት::

'ያደገበት ነው:: እውነቱን አይደለም እኮ' ትላለች::

አንዳንድ ጊዜ ጎን ለጎን ተኝተን ጎኗ ባልተኛ እወዳለሁ:: በተለይ ፀጉሯን እንዳይበላሸባት አልጋው ጠርዝ ተቀምጣ በቢጉዲን እየጠቀለለች በሻሽ እያሰረችው ሁለት ያጠቡ ጡቶቿ ሆዷ ድረስ

[16] አንዳንድ ሰዎች መርዋጥ ይሉታል(ደስታ ተክለወልድን እይ) መርዋጥ መሮጥን ያሳያል:: በተረት ውስጥ የሚገኙ ሁለት ወንድማማች የጅብ ቡችሎች ('እንቅልፍ ለምኔ' የተባለውን የተረት መፅሐፍ እይ)



@BOOKALEM

ተንዘላዝለው እንግሊዘኛ እየደባለቀች ወሬ ስታወራልኝ ምታት ይለኛል:: ፊት ለፊቴ ሦፋ ላይ ተቀምጣ ጣቶቿን ቀለም ስትቀባና......'አያምርም?' ስትለኝ የጣቶቿን ጥፍሮች በገጀራ ቆራርጬ መጣል እፈልጋለሁ:: ሰውነቷ ላይ አምሮ አላርፍ ያላትን ጨርቅ እያራገፈች እያስተካከለች......ቁም መስታወት ተጠግታ ስትሽከረከር ጨርቋን እላይዋ ላይ ቅደደው ቅደደው ያሰኘኛል:: ለእሷም ሳይሆን ለእኔም ሳይሆን በእኔና በኢሌኒ መሐል የጥቁር ዶሮ ደንቃራ እንደሆነች ይሰማኛል:: ይሔ ሁሉ ሆኖ መሳቅ መጫወት አታቆምም::

ስሟን እስከአሁን አልተናገርኩትም......ሶስና ትባላለች:: ሁለት የ'ሰ' ዘር ያለበት ስም......እንደ እስስት::

የአንዱ ዐባይዋ ደንቃራ መሆን ነው ሌላው ያበሳጨኝ ጣጣ:: የማታውቀው ሰው የለም:: አዲስአባን ወደ መንደር የለወጠች ናት:: `እዚህ መስሪያቤት እንትናን እንትናን አውቃለሁ:: ያ ቤት እንትና......እንዴ እሱ እኮ የእከሌ ወንድም ነው:: ያ! ያ ኩሎኔል አንደኛ ደረጃ አብረን አስፋወሰን ተምረን የለ እንዴ! እንዴ እሱ እንዴ አፈወርቅ ማናት ያቺ ቱሪዝም የምትሰራው ዘለቃ አፈወርቅ? ወንድም አይደለ እንዴ......የአጐቱ ልጅ እኮ አብሮኝ ነው የሚሰራው......የእሷ

ታዲያ እኔ አዲስአባ መኖር አልቻልኩም:: ቤት ልተኛ አስብና፣ ወይ እላከፍና የት እንደምሠራ ስናገር......`እንዴ! እንዴት እዚያ የሚሰራ ባል አላት` እባልና......`ሶስናዬ` ተብሎ ሥሟ ጊደኛዬ ያውም ተቆላምጦ:: ምን እንደምታበላቸው አላውቅም:: ይነሳል:: ያቀመሰቻቸው ለእኔ አለመስራቱ ይገርመኛል:: ሚስቴም ለእነሱ ለተንኩል የምታውቃቸውን ሰዎች በመዘርዘር የወንዶችን አንዳንዴ በማድረግ አንዳንዴም ወንዶቹን እያቆላመጠች......እንድቀና በዛ ትፈልጋለች:: ቀንቼ አላውቅም:: አራት ኪሎና ፒያሳ አልጋ አንጥፋ የአዲስአባን ወንድ በሠልፍ ብትጠራ አልቀናም:: ግን አድርጋው አታውቅም:: ይገርማል:: የመለከፍ ነው፡ እሷ በእኔ፣ እኔ የት እንዳለች በማላውቃት ኢሌኒ::

አንድ ቀን ሶስና አድርጋ የማታውቀውን ከሁለት ሣምንት በኋላ ሠርግ እንዳለባትና እሠርጉ አብሬአት እንድሔድ ነገረችኝ:: ሌላ ጊዜም ትጠይቀኛለች:: 'እምቢ አልሄድም' ካልኩ ትረሳዋለች:: ባትረሳውም እያማረረች ትተወኛለች:: አሁን ግን ኮስተር ብላ ነው:: ነገሩ የማይቀር ቀጠሮ እንደተያዘበት ለማመልከት ነው መሰለኝ ሳሎን የሚቀመጠውን ካሌንደር ፊት መታጠቢያችን ክፍል ውስጥ አምጥታ ሰቅላ የሰርጉ ቀን ላይ በቀይ ስክሪፕቶ ምልክት አደረገችበት:: 'አልሔድም' ብዬ እንደለመድኩት በጠና ባልከራከርም፣ የበለጠ እንድታምነኝ ከሠርጉ ዕለት ሁለት ቀኖች ቀደም ብዬ የውሽቴን በጠና



@BOOKALEM

ለመታመም ወሰንኩ:: ይኼ ሽፍጠኛነቴን ጠርጥራ ሳይሆን አይቀርም በየቀኑ ማታ ማታ ስለ ሰርጉ ልዩ መሆን ታወራኛለች:: ሙሽራው እድሜው ሃምሳ ልጅቷ ዕድሜዋ ሃያስምንት እንደሆነና......ሰውዬው ሶስት ልጆች ሴትዮዋ አንድ ልጅ እንዳላት ታብራራልኛለች:: ሰርጉ የመሄዱ ፍላጐቴ የተነሳሳው ግን ሙሽራዋ ስሟ ኢሌኒ እንደሚባልና የድሮ የሚኒሊክ ተማሪ እንደነበረች ስትነግረኝ ነው::

ልቤ 'እ!እ!' እያለ ተንበልብሎ ከተኛበት እየተሳበ ቀጥ ብሎ ቆመ......

መቼም ልቤ ቆሞ አይቀር የሠርጉ ቀን ደርሶ ከሶስና ጋር የስጦታ እቃችንን ይዘን ሔድን:: እንደተወራልኝ ሰውዬው እጅግ ሐብታም ነጋዴ ነው:: ከድሮም ነጋዴ፣ አሁንም ነጋዴ:: በመጀመሪያ ቤቱ ሔድን:: ሕንፃ ነው:: ያጀበው የመኪና ሰልፍ እንደ ጨሌ ተያይዞ...... የጉዳና ጠመዝማዛ ተከትሎ የሚነጉድ ዐይን የሚያደክም:: እዚህ ሙሽሮቹን የማየት እድል አላጋጠመኝም:: የራት ግብዣው ገነት ሆቴል ሆኖ ተበልቶ አልቆ የዳንሱ ወለል በሙሽሮች ይከፈት ተብሎ 'እስክስ' ሲባል ኢሌኒን አየኋት:: በዚያን ወቅት በአዲስአባ ሐብታምን ባል የማድረግና ካለው ወንድ ጋር መውጣት ችሎታና አራድነት ፋሽን ቢሆንም እንዲህ የተለወጠች ኢሌኒ የሚሳካላት መስሎ አልታየኝም:: ሙሽራ በመሆንዋ የተደረገላትን እንክብካቤ ተንኼ ሳያት ዐይን የማትገባ የማታስደነግጥ ሆና አገኘኋት:: እንድታየኝ ፈለግሁ:: እንዲህ አምሮብኝ......ቸልተኛና ግድየለሽ ሕይወቴ ኳኩሎኝ፣ እንደ እሷ ደንግጬ እንዳላገባሁ እንድታየኝ ፈለግሁ:: ግን ሊገባት አይችልም:: ድሮ አታውቀኝም:: ግን የራሴን ስሜት ለማርካት ዳንሱን ጨርሳ ስትቀመጥ ሙሽራውን ይቅርታ ጠይቄ አነጋገርኳት......

«ጤና ይስጥልኝ ሙሽሪት......መልካም ጋብቻ»

«አመሰግናለሁ»

«ድሮ እኮ ሚኒሊክ ት/ቤት አብረን እንማር ነበር»

«እንዴ? አዎ ትዝ አልከኝ......አልተለወጥክም»

«ማነኝ?»

«ሰለሞን ጉን የምትቀመጠው አልነበርክም?» (ያ ሰለሞን፣ ጉዴ ፈላ)

«ትዝ ብሎሻል»

«ለማንኛውም ለድሮ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ሠርግሽን አሟሙቅልሻለሁ»

«እንዴ ታዲያስ......» ትቼአት ሔድኩ:: ምኗም አልሳበኝ:: ጠይም ሆናለች:: እዚያ ጠይም ገፅዋ ላይ ጥቁር ጠይም ማድያት



@BOOKALEM

አለ......በፓውደር ልትቀብረው የለፋች:: ጣቶቿን የሸፈነው ቆዳ የተሸበሸበ ይመስላል:: ጥፍሮቿ ሰፋፊና እረጃጅሞች ናቸው:: አፍዋ ግራና ቀኝ ተጎትቶ የሰፋ ይመስላል:: ስትናገር የድምፅዋ ቅላፄ እንደፈቲ ሴት ነው......ፈረንጆች 'ቢች'[17] እንደሚሏት ዐይነት:: በከፊል ደንግጬአለሁ:: ሕልሜ ከ100ኛ ፎቅ ላይ እየጮኸ ወደ መሬት ሲወርድ ዐይነት ነው:: አወዳደቁን ላቆመው እፈልጋለሁ:: ኢሌኒ እንዲህ እንዳትሆን እፈልጋለሁ::

እሷን ሰላም ብዬ ወደ ሶስና ስመለስ ድንጋጤዬ አልለቀቀኝም:: ከሶስና ጋር ለመደነስ ስንነሳ ግብግቡው ላይ ከወዲያ ወዲህ የሰበሰበችውን ወሬ ልትነግረኝ ጀመረች......

«ምን መሰልኩት በእናትህ?»

«ምነው?»

«የሰውዬው ትልቅ ልጅ ሊለክፈኝ አልፈለገም እንዴ?»

«ምናለበት?»

«ሒድ ምነው እስከዚህ»

«ልጆቹ እዚህ ምን ይሰራሉ?»

«አባታቸውን አይድሩም እንዴ?»

«አይደለም......የምልሽ......የእሷ ልጅ እዚህ አለ?»

«ምነው? በጣም ትተዋወቁ ነበር እንዴ?»

«ኧረ አይደለም......ዲቃላ የሠራሁ መሰሉሽ ነው?»

«ማን ያውቃል?»

«አይደለም:: ለማየት ጓጓሁ»

«ቅድም ሲያሳዩኝ ነበር:: ትልቅ ልጅ ነው እኮ» ተያይዘን እየደነስን ሶስና ዙሪያዋን ማየት ጀመረች::

«ያውልህ እዚያ» አለችኝ፤ ብቻውን ግድግዳ ጥግ ወንበር ላይ ተቀምጦ ፋንታ የጨበጠ አስር ዓመት የሚሆነው ልጅ እያሳየችኝ::

ዳንሱን ስንጨርስ እሷን ትቼአት ወደ ልጁ ሔድኩ:: ስጠጋው በዐይኖቹ ጠፍሮ ያዘኝና ቀልድ እንደነገርኩት ሁሉ ፊቱ ለሁለት እስኪከፈል ሳቀ:: ከላይ እስከታች በድንጋጤ ተመተርኩ:: የድዱን እርዝመትና የጥርሱን ትንሽነት ላይ:: እጁን ለመጨበጥ እጄን በንሲብ ዘረጋሁና እንደሰላምታ አድርጌ:

«የሰለሞን ልጅ ነህ? አይደለም?» አልኩት::

---

17 (bitch) በቀጥታ ትርጉሙ 'ሴት ውሻ' ማለት ሲሆን በእንግሊዝኛ የዘወግ ቀበሮ ትርቡት/ሎሙና ሴት ማለት ነው::

ትንሽ እጁን በየዋህነት እጄ ውስጥ አስገብቶ ያን የምጠላውን ጥርስና ድድ እያሳየኝ:

«አዎ» አለኝ......

የበለጠ የደነገጥኩት አንድ እሁድ ዕለት ኢሌኒ አምባሳደር ቲያትር ፊት ለፊት መኪና አቁማ ልጇን እየጐተተች ስትገባ ሳያት ነው:: ማለት ሰው እንደዚህ በአካሉ ይከዳል? ማለት ዐይን ከየቦታው ትስብ የነበረች ሴት ዛሬ ቲያትሩ መግቢያ በር ፊት ለፊት የካሼር መስታወት ላይ ሥራ አጥቶ የተንጠላጠለ ወንዴ ሸረሪት እንኳን ተገላምጦ የማያያት ስትሆን:: ወደ ቲያትር ቤቱ አገባቧ ራሱ ፍጥነት አለበት:: ከዐይን ለማምለጥ:: የሚያይ ዐይን ግን ያለ አይመስለኝም::

ሲኒማው ከመጀመሩ በፊት ለልጇ ከካከላ ለመግዛት ከአዳራሹ ስትወጣ ፊት ለፊት ስለተገናኘን ሰላም ተባባልን:: ጨዋ ለመሆን እንዳማረባት ነገርኳት:: `እሱስ ተመው` አለችኝ:: ሁለታችን የጣችውን እናውቃለን:: ቡና ጋብዥአት አንድ ጥግ ተግባብተናል:: ስለ ድሮው ሚኒሊክ ማውራት ጀመርን:: የተጋራነው ቤግ ቆመን ስለ ድሮው ... አንዳንድ ነገር አነሳሰተን ወሬው ሞተ:: ሆን ብዬ ስለ ሰለሞን ሳላነሳ ... ስለሲኒማው ጥቂት ካወራን በኋላ የት እንደምትሰራ ጠየቅኋት:: ፒያሳ በአይን የማውቀው ልብስ ቤት እንደምትሰራ ነገረችኝ:: ይሄን ስራ እንዴት እንደ ጀመረች ማብራሪያ ስትፈልግ ወደ ኋላ መመለስ ነበረባትና (እኔ ባልፈልግም) ብዙ አወራችኝ:: የምትወደው አይነት ሕይወት ያሳለፈች አትመስልም......ከአንዳንድ አወራሯ......ምክንያቱም ጨዋታዋ ሁሉ ስለ ልጇ ብቻ ነው......ስለ ዮናስ ነው......

«ዮናስ ተወለደ......በቃ»

«ለዮናስ ብዬ......»

«ዮናስ እንዳይከፋው......»

ስለሞንን አላነሳችም:: ስለሞንን አላነሳሁም:: በወሬ ምን እንደሰማሁ ልትገምት ትችላለች.....የሶስና ባል አይደለሁ:: ሲኒማ መጀመሩን የሚነግር ደወል ስንሰማ ተያይዘን ገባን:: ለብቻዬ ቦታ መምረጥ ጨዋነት ስላልመሰለኝ እሷና ዮናስ አጠገብ ሔጄ ተቀመጥሁ:: የሕይወት ዙር የሚገርም ነው:: አሁን በሕሊናዬ ሁለት ኢሌኒዎች ተፈጠሩ: ድሮ የማውቃት ኢሌኒና አሁን ዛሬ ጐኔ የተቀመጠችው ኢሌኒ:: እኔ ከእሷ በስተግራ ነኝ:: ልጅዋ በስተቀኝዋ ነው:: እንግዲህ ኢሌኒ ከመሐል ናት:: ከማየው በምናብ ከተቀመረ ጊዜ ያዛጋት ሲኒማው ይልቅ እዚህ በዐይኖቼ በጆሮዎቼ የምመሰክረው ነገር ገረመኝ:: በለጠብኝ:: ከሲኒማው ሸራ ላይ በሚነጥረው ብርሃን ገፅዋን አልፎ አልፎ እየዋለሁ:: እሷም ታየኛለች:: የዘመኑ......ዘመን

ያመጣውን ለውጥ ለመፈተሽ ብዬ ነው መሰለኝ ቀኝ እጄን ወስጄ ጭኗ ላይ አስቀመጥኩ......በሁለት እጆቿ ይዛው ማሸት ጀመረች:: ዘመን ገረመኝ:: እጄ እጇ ውስጥ ሆኖ እያሳበው፣ እያሸችው፣ እየፈተገችው:: አ! ዘመን ገረመኝ:: እንዲህ ደረቷ ላይ የቆመው ትዕቢቷ......እንዲህ ኮርታ የምትሔደው ልጅቷ......ሙሽርነቷ ሳይበርድ......ይኸው እራሷን ልትሰጠኝ አሰፍስፋለች:: ተንኩል ሆንኩ:: እጄ ተንኩል ሆነ:: ቀሚሷን ቀስ ብዬ አንስቼ ጭኖቿ መሐል እጄን አስቀመጥኩ:: ዞር ብላ አየችኝ:: ልጄን ዞር ብላ አየችው:: እጄን አላወጣሁም:: ተመቻችታ እንደምትቀመጥ ሁሉ ትንሽ ጋለል ብላ በጭኖቿ መሃል እጄን ቆልፋ ያዘችኝ:: እንዲህ ሆነን ምናልባት ግማሽ ሰዐት ያህል ቆየን (ማሪያምን ክርኔን አመመኝ:: ለማላቀቅ ከሞከርኩ የምትሰድበኝ፣ የምትገላምጠኝ ቶሎ የምታወጣው ከሆነ መጀመሪያውኑ ለምን እጅህን ሳክኸው የምትለኝ መሰሎኝ ፈራሁ)::

ማታ ላይ ከሲኒማው አዳራሽ ስንወጣ የምትሰራበትን ቦታ ስልክ ቁጥር ሰጠችኝ (ጨዋ ለመሆን ራሴ ጠይቄ):: ሁሉ ነገር አስጠላኝ::

የዚያን ዕለት ማታ (ከሠርጉ መልስ) ቤቴ ስገባ ያደረኩት ነገር ቢኖር ሶስናን፡ የልጆቼን እናት......(ጠማማነቴን ችላ የኖረችውን......የእኔን ባጠኛ......ኩንስንስ ወላዴን......የእኔን ወሬኛ......) ዘልዛላ ጡቶቿን በሁለት እጆቼ ይዤ (የታጠበ እንሰላ እንደሚጨምቅ ሰው ክንዶቼ ላይ ጠምጥሜ ልበል?) ድብልቅልቅ አድርጌ መሳም ነበር (በልቤ ከባቡር የረዘመ ይቅርታ እየጐተትኩ)፤ የእጅ አሰጣጤ አባብቶአት እስክታለቅስ::

.....ከዚያ እያለቀሰች፣ እየተናፈጠች ስርቅታ በሚቆራርጠው ለስላሳ ድምፅ፡

«ኢሌኒ ናት አይደለም?» አለችኝ::

አንገቷ ስር ያስገባሁት ፊቴ በድንጋጤ ሲጨማደድ ይታወቀኛል......

ምን ይሿታል ሶስናን? መልአክ?

የሚኒሊክ ት/ቤት አንድ ተምሳሌት ያጥረዋል......

ሄዶ ወይም ደርሶ ስለመመለስ የሚነግር::

---- // ----

*1987 ሆላንድ*

# አቸሎኒ

1

ብርዱ ብርድ አይደለም:: ሌላ ቃል መፈልሰፍ ሳያስፈልግ አይቀርም:: «ቡጥቢ ግዙላሉ ግኝቃቀጥጭጭጭ» ያደርጋል ብለው ይሻላል:: ከአልጋዬ ተነስቼ ፊቴን ለመታጠብ መፀዳጃ ቤት ስገባ ገላዬን እንደ ፈራ እንስሳ ሰብስቤ ነበር:: ብርዱ የማይኼድበት፣ የማይወፍርበት፣ የማይሰርግበት ቦታ የለም:: የወለሉ ሸክላ እንደተነጠፈ በረዶ ይቀዘቅዛል:: የእግሮቼ ተረከዞች ድምፃቸውን አውጥተው ሳያለቅሱ አይቀርም:: የግድግዳው ቅዝቃዜ ፊቴን እየገፋ ሲያጠበው ይታወቀኛል:: ቧንቧውን ስከፍት ለግማሽ ደቂቃ ያህል የወረደው እንደ ጮቄ የቀዘቀዘ ውሐ ነው:: ቀና ብዬ ፊቴን በመስታወቱ ውስጥ አየሁት:: በሶስት ድርብ የብርድልብስ ትንፋግና በቤት ማሞቂያ የውሐ ወላፈን እብጦ በማይፈልገው መልክ የተመቸው ወፍራም ሰው መስዬአለሁ:: አይኖቼ ስር ትንንሽ ቅንፍ የሥጋ ቦርሳዎች አሉ:: ቁጭራው ፀጉሬ በየቦታው ወደ ትናንሽ ኳሶች ተቆጣጥሮአል......በቀኝ እፊ ጥግ የደረቀ የለሐጭ ኖራ አለ:: ጥርሶቼን አየሁ:: ቤዥ ቀለም አላቸው:: ድዴ ያደፈ ጋቢ ቀለም አለው:: የሞቀ ውሐ መፍሰስ ሲጀምር ሽንቴን መሽናት ትዝ አለኝ:: የቧንቧውን ውሐው ሳልዘጋ ትቼው ሙታንታዬን ዝቅ እያደረኩ ወደ መሽኛው ሰሐን ተጠጋሁ:: ሽንቴን ከፉቅ ወረወርኩ:: የእንቅልፍ ክብደት ዐይኖቼ ዙሪያ ይሰማኛል:: ሽንቴ ቢጫ ነው:: የጠዋቱ ሽንቴ ቢጫ ነው ሁልጊዜ:: ለምን እንደሆነ አላውቅም:: በብርድ ተመታ ሙርጤ የከበባት ጥቁር ፀጉር ውስጥ እንደ ጃርት ጭንቅላት ጠፍታለች:: ትትቼ ነቀንቀኋትና ቆቧ ላይ የሠፈረውን ውሐ አራግፌ ከፍቼ ወደ ተውኩት የቧንቧ ውሃ ሔድኩ:: አፈሳሰሱ ያባብላል:: አወራረዱ ቀጥሮ የሚያቃጥል ሆኖአል:: በቀዝቃዛ ውሐ በረዝኩትና መታጠብ ጀመርኩ::



@BOOKALEM

ከጨረስኩ በኋላ ለማዳረቅ ፎጣ ከግድግዳ ላይ ስጎትት ፖስታ ቤቴ ውስጥ ሲወረወር ሰማሁ:: በብርድ ውስጥ እንደ ዞረበት ወደ የበረደ አየር እየተዘፍኩ ወደ ሳሎን ሔድኩ:: ከዋናው በር ግን የኢትዮጵያ ባንዲራ ያለበት ቴምብር የተለጠፈበት አንድ ሥር ኤንቬሎፕ ወለል ላይ ወድቋል...... ብቸኛ

2

ሐምሌ መሰለኝ ጊዜው ወይም ሰኔ መግቢያ......ሰኔ መግቢያ መሆን አለበት:: ወሩ ሳይሆን በትክክል ትዝ የሚለኝ ዝናቡ ነው:: ግን ዝናቡ የጥሩ ክረምት አይነት ዝናብ አልነበረም:: ሐምሌ ሊሆን ይችላል ግን በሐምሌ በሐምሌ ጥሩ ሆኖ በሐይ በወጣበትና የደረቀ መሬት ባለበት ቀን ነጐድጓዳማ ዝናብ አይጥልም:: ነጐድጓዳማ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የጣለው ቀኑን ሙሉ በሐይ ውሎ ሊመሽ ሲል አንድ ሰዐት አካባቢ መሆኑ ነው:: መምሸቱ ብቻ ሳይሆን ዝናቡ ለአጭር ጊዜ በወፍራም፣ በሐይል የወረደ የአዲስአባን መንገዶች በጉርፍ ያጥለቀለቀ ነበር:: ሐምሌ ሊሆን አይችልም:: ሰኔም ሊሆን አይችልም:: ምናልባት በዚያን ወቅት ከወረዱት የበልግ ዝናቦች አንደኛው ይሆን ይሆናል:: በደንብ የማስታውሰው ግን እኔና እስዋን ነው:: ምሽቱን ነው:: ዝናብ ሲጥል ቆመንበት የነበረውን የሜክሲኮ አደባባይ ሞቢል ቤንዚን ማደያን ነው:: ትዝ የሚለኝ ከዚያ ቀደም ብሉ በካዛንቺስ አንድ አልቤርጐ ውስጥ ያሳለፍናቸው የሚጥሙ ሁለት ሰዐቶች ናቸው:: የማስታውሰው ስስ ቀሚሷን፣ ዕጌረዳ የመሰሉ ከንፈሮቿንና ትላልቅ ጥቋቁር ዐይኖቿን ነው:: የማስታውሰው አንገቷን፣ የማስታውሰው የሚያማምሩ ክብ ጡቶቿንና እነዛን በማግባባት አዝሉ የያዘ ሳንቃ ደረቷን፣ የማስታውሰው ቢሾፍ ገላዋን አልጋ ላይ ጥላው ቆሚ ሳያት ነው:: ወሩ እዚህ የሚገባ ጉዳይ አይደለም::

በዚያን ጊዜ ወጣትነት ሳይሆን አይቀርም ቁመናዬ ቀጥ ያለ፣ ጥሩና ዘንጬ የምለብስና የምታይ ነበርኩ:: ለማየት ደስ የምል ነበርኩ:: አውቀዋለሁ:: ማወቄ ግን እንደ በቀል ይመስለኛል::

በቀልነቱ የሥር ታሪክ አለው::

እነሆ............

3

ዕድሜዬ አሥራ አራት እስኪደርስ በመልኬ እሰደብ ነበር(በኋላም ቀረልኝ ማለት ሳይሆን):: እኔም ተጨባጭ መረጃ ይገፍ ከመከራከር ይልቅ የተባልኩትን በመስማት፣ ሰምቼም በማመን ዝቅተኛነት የወረረኝ፣ `አስቀያሚ` የተባለ ፊቴን ሰው ፊት በኩራትና በራስ መተማመን ማሳየት የሚከብደኝ ነበርኩ:: የስነልቡና በሽታ በሉት



@BOOKALEM

ብትፈልጉ---'አስቀያሚ' ተብዬ መሰየሜ የፈጠረብኝን አጥንቴ ድረስ የተጠለለውን የውርደት ስሜት:: ይኼን ፕሮፓጋንዳ የትኛው ጉረቤቴ ወይም የቤተሰቤ አባል አውጥቶልኝ አምኜ ተከትዬው እኔን የወጣትነት ጨለማ ውስጥ እንደከተተኝ አላውቅም:: እኔን ማፈሬን ነው:: አጨራረሱን ነው:: ትዝ የሚለኝ ማፈሬ ነው:: የማውቀው ከፍ እያለ እንኳን ሲሔድ......በዚህም ወጣት ሴቶች ዐይን ሲያተኩሩብኝ..... አስቀያሚነቴ የሚያስገርማቸው......አስገርሞአቸው የሚያፈጡብኝ ይመስ ለኝ ነበር::

ይኼ የተሸነፈው......ይኼ ማለቴ......ዝቅተኛነቴ......በሲኒማ ነው:: ቅዳሜና እሁድ ኳስ ጨዋታ ልይ እያልኩ ሰው የተሰበሰበበት አካባቢ አስቀያሚነቴን ከማሳየት በብርና በሃምሳ ሳንቲም ከሠፈሬ ከ70 ደረጃ ፒያሳ ወርጄ ሲኒማ ቤት ተዘግቶብኝ ብውል የተሻለ መሆኑ ገባኝ:: እንደማምለጥ ነበር:: 'አስቀያሚ' ተብዬ መሰደቤ ሁልጊዜ ደምስሬ ውስጥ ጠዋት ማታ የሚያቀጣጥለኝ ቂጣ እንደ ጫረ ይታወቀኛል::

ጊዜውን አልረሳውም ቅዳሜ ቀን:: ፒያሳ:: እኔና ሁለት ጓደኞቼ ሲኒማ ኢትዮጵያ ለመግባት እየተጋፋን ሰልፍ ውስጥ ቆመናል:: ከሆስታችን ሁዋላ ሁለት ዐይን-አፋር የመሰሉ ሴቶች ቆመዋል:: ቀትሩ ከብዶ ነበር:: በወዲያ በኩል ራስ መኩንን ኬክ ቤት ረብሻ አለ:: ምን እንደሆነ አላውቅም:: ሊስትሮዎች ይንጫጫሉ:: ይነፍሳል:: በሸሚዝ ነበርኩ:: ጂንስ ሸሚዝ ያለ ካኔትራ:: እና ጥቁር ባጊ ሱሪ:: እና አንድ የወንድሜን አሮጌ አዲዳስ:: ባለሥራ ብሆንም ልብስ ገዝቼ አላውቅም:: ከታላቅ ወንድሜ እየተዋስኩ ነው የምለብሰው:: ታናሹ ብሆንም የሰውነቴ መጠን እሱን ስለሚያክል ጠይቄም ሳልጠይቅም ደስ ያለኝን ለብሼ እወጣለሁ:: ደሞዜን ግማሹን እሱ፣ የቀረውን ወላጆቼ ናቸው የሚወስዱት:: የተቂያቂያልኩም አይመስለኝ:: መልክ፣ ቁመና ቀላል ነገር ተብሎ ይሰየማል እንጂ የሰው ሕሊና ላይ......ተስፈኛ መሆኑንና ተስፋ-አልባ መሆኑን እንደሚመጥን በእኔ በደረሰበት ሰው አውቀዋለሁ::

ግብዞች ግን ይላሉ:

'መልክ ታጥቦ አይጠጣ'

እኔም እመልሳለሁ:

'ይጨለጥ፣ እልም አድርጎ ይጨለጥ'

ግብዞች እንዲህ ይላሉ:

'ቁናው ቁም ነገር ነው'

እኔም እመልሳለሁ:



@BOOKALEM

አገር ነበርኩ......ያልታደለ ዜጋ ሆኜ' እላለሁ::

'ተባለ እንዴ? እዛ አገር ነበርኩ......ያልታደለ ዜጋ ሆኜ' እላለሁ:: የጉደለብኝ ሌላ ነገር አልነበረም:: የጉደለኝ......' የጉደለህ......' ተብዬ ያመንኩት......እምኜም በደም ሥሬ ያስገባሁት መልኩ-ጥፉ መባሌ ያሳደረብኝ ገማባ ስሜት ብቻ ነበረ::

እና እዚህ እንደተሰለፍን ሁለቱ ሴቶቹ ተያይዘው ሳቁ:: እየተንሳሰሙ፣ እየተያዩ:: ሳቃቸው ቆዳ በስቶ የሚገባ ነው:: ይኼን ሳቃቸውን ሰዎች በጆሮአቸው ሲሰሙት እኔ በቆዳዬ፣ በጡንቻዬና በልቤ ነው የምሰማው:: እኔን ከጀርባዬ አይተው የሳቁብኝ መሰለኝ:: በፀጉሬ ከርዳዳነት፣ በአፌ ሰፋት፣ ምንም ባላጠፋው ሱሪዬ፣ በእሮጌው ጫማዬ፣ መንጣት በጀመረው ጅንሴ......ብቻ እኔን መሰለኝ:: ዛሬ ይገርመኛል:: ዛሬ ባሰበው በሽታ ውስጥ ወድቄ ነበር እላለሁ:: ተመልሼ እንደዚህ ያጥላሉኝን ሰዎች ብጠይቃቸው እወዳለሁ:: ለምን የማይታመን ቅጥል እንደለጠፉብኝ ብከራከራቸው ደስ ይለኝ ነበር:: ማንን ለማደን ግን ልውጣ? ማናቸው? የትስ ነው ያሉት?

እና ልጃገረዶቹ (ሴቶቹ) በሳቅ ሲፈርሱ ትኬቴን ቶሎ ቆርጬ ሲኒማ አዳራሹ መቀመጥ ፈለግሁ:: ጓደኞቼ ወሬ ጀመሯቸው:: እኔ እንዳላየ፣ እንዳልሰማ ፊቴንም ወደ እነሱ ሳላዞር ቆምኩ:: እንደኛው ወዳጅ በራሴ ግምት ተራ፣ አይን የማይገባ ኩሳሳ፣ ኩሳሳ ብቻ ሳይሆን የሚታይና የሚያስጎመጅ ወንድነት እንኩዋን የሌለው ከወደ ጀርባዬ መጣና:

«ለወፎቹ ትኬት ግዢ» አለኝ:: እሱን ዞር ብዬ አየሁት:: በዐይኔ ቂጥ ......ሴቶቹን:: ሴቶቹን ሙሉ በሙሉ ደፍሬ ማየት አልቻልኩም::

«የአምስት ሰው ቁረጪ» አለኝ::

«ጥሩ»አልኩት::

ከመሐል አንዷ:

«ፋዘራችሁ[18] ነው እንዴ?» አለች:: እንዳልሰማ ሆንኩ:: አባባልዋ የበለጠ ወጋኝ:: ከጓደኞቼ በእድሜ እንደምበልጥ አውቃለሁ:: አባት ለመሆን ባልደርስም......ትንሸዋን ዕድሜ በማጉላት 'አሮጌ' ያሉኝ መሰለኝ:: ሴቶች አይታመኑም ብዬ::

«ጓደኞችን ነው......ደግ ነገር ናት......ትከፍላለች» አለና ከኋላዬ ጉሰመኝ:: ሌላኛው ጓደኛዬ ቀልዱን (ስድቡን) ለማጀብ ይስቃል:: በተባለው ላይሆን ይችላል:: ሁለቱንም ሴቶች እንደተከፋፈሉዋቸው

---

[18] (father) አባታችሁ(እንግሊዝኛ)

አይነት ነበር:: ይሻለኛል:: ሦስት ቢሆኑ ኖሮ የቀረችዋ እንድዋ እኔ እንድጠብሳት የተዘጋጀች መሆንዋ በተለያየ ሽሙጥ እንደሚነገረኝ መጠርጠሩ ብቻ ሳይገለኝ፣ ትንፋሼን ሳይቆርጠው አይቀርም ነበር:: እንዲትን ቤት ፊት ለፊትዋ ቆሚ ዐይን ለዐይን እየተያየኋት...... አስቀያሚ ፊቴን ሳልሸፍን ማውራት የማልፈው ፈተና አይደለም:: ካራማራን ለብቻዬ ከሲያድ ባሬ ወታደሮች ነፃ እንዳወጣ ወደ ጅጅጋ ቢልኩኝ ይሻለኛል::

ረዥሙ ሰልፍ እየተጨማደደ ትኬት መቁረጫው ስንተርያ (እንዲህ ይባላል እንዴ?) ደረስንና የአምስት ሰው መግቢያ ገዛሁ:: ዞር ብዬ ለእያንዳንዳቸው ከማደል ይልቅ ኋላዬ ለቆመው ጊደኛዬ ሰጠሁትና ብቻዬን ወደ ታች ወረድኩ:: አንደኛ ማዕረግ ገብተን አናውቅም:: ለመረበሽ፣ ለመጮህ፣ ለማፏጨት እንዲያመቸን:: የምወደው አንዱ ነገር በጨለማ መሸፈት ነው:: አስቀያሚ ፊቴን ሳያዩ መሸፈት ነው:: የዘመኑን ፖለቲካ አልወደውም:: ፕሬዝዳንታችን መንግስቱ አስቀያሚ ....'ጡሩሩ ባርያ' ስለሚባል ብቻ ወሬ እንድ የመልከ ጥፉዎች ጉሳ ስለሚመድበን እወደዋለሁ:: አንዳንድ ጊዜ መረር ሲለኝ......የምታምር ሴት በዐይኖቿ ዳብሳኝ ስታልፍና አስቀያሚነቴ ተሰምቶኝ ሐሳብና ብስጭት ሲወረኝ በቀጥታ የመንግስቱ ኃ/ማርያም ካድሬ መሆን እመኛለሁ:: የመንግስቱ ኃ/ማርያምን ፎቶ ግራፍ መኝታ ቤቱ የሚያስቀምጥ ፖለቲከኛ ያልሆነ ወጣት እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም:: ጊደኞቼ ያውቃሉ:: ቤተሰቦቼ ይተርቡኛል፣ ይስቁብኛል:: ሲያማርሩኝ ('አንተ ገምጭ ምን ልሁን ብለህ ነው ለበርጫ ያልመጣኸው?' ብለው ሲናገሩ) አንዳንዴ በልቤ፣ አንዳንዴ ድምፄን ከፍ ለቀልድ እንኳዋን አድርጌ 'አስቀያሚ እያልሽ የምትጮኺበት መንጌ ያስተካክልሻል'......እላለሁ::

......እና ታች ሁለተኛ ማዕረግ ወረድንና ቦታ መርጠን ሰው መሐል ገባን:: ጊደኞቼ ሴቶቹን አስከትለው በሰልፍ ተቀመጡ:: ከፊት ለፊታችን ሁለት ጎረምሶች አጎንብሰው ሲጋራ ያጤሳሉ:: ከወዲያ 'ማጤስ የተከለከለ ነው' እያለ የሚጮህ......ቢጤስ ግድ የማይሰጠው ድምፅ አለ:: አቀማመጣችንን ቆይቶ ነው ያየሁት:: እኔ፣ ከዚያ ቀጫጫው ጊደኛዬ፣ ከዚያ አንዲት ልጅ......ከዚያ ሌላው ጊደኛዬ...... ከዚያ ሌላዋ ልጅ::

«ጊደኞቻችሁን አታስተዋውቁንም እንዴ?» አለች አንዷ ወደ እኔ ቀረብ ያለችው:: ድምፅዋ የሆነ ሕይወት ያለው ነገር ይመስላል:: የሚረሳ አይነት አይደለም:: እነዚህ ሶስት ቃላቶች በፈለጋቸው አይነት አገባብ ተነግረው እንደዚያ ያማሩበት ጊዜ ትዝ አይለኝም::

«ሚስት አለችው እሱ» አለ ቀጫጫው እየሳቀ::



@BOOKALEM

«እኔ አላገባው ታዲያ» አለች……ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ:: ጆሮዬን ቆም አደረኩ:: ዕውነቷን እንደምትናገር ሁሉ እየተከታተልኩ:: መብራት መጥፋት ጀመረ……

«ስሚ……ጂሚ……ተዋወቁ» አለኝ ጊደኛዬ……ትከሻዬን በትከሻው እየገፋ:: ዞር አልኩ ወደ ቀኝ:: ብልጥጥ ብላ ትስቃለች:: ጨለመ:: እጄን ሰደድኩ:: የእስዋን እጅ መሐል መንገድ አገኘሁት:: ጨበጥ አድርጌአት ከመመለሴ በፊት መዳፌ መሐል በአንድ ጣቷ ነካ ነካ፣ ቆርቆር ቆርቆር አደረገችኝ:: ኤሌክትሪክ እንደነካሁ ነዘረኝ:: በክንዴ ላይ አድርጎ……በትከሻዬ……በደረቴ……እና ልቤን:: ግራ እግሬ ላይ የደረብኩት ቀኝ እግሬ ራሱ የደነዘዘ መሰለኝ:: ሲኒማው ተጀመረ:: የደስታ ይሁን የረብሻ ሁሳቸውን ሊያሳዩ ብዙ ፉጨቶች ከፊት ለፊታችን ለአጭር ጊዜ ተፍለቀለቁና ጠፉ::

የሲኒማው ግማሽ አልቆ ለእረፍት ለስላሳ ለመጠጣት ስንነሳ ከግማሽ ሰዐት በፊት የተዋወቅኋት……ስምዋን ግን ያኔውኑ የረሳኋት (ስለ ተደናበርኩ) ሴትና ቀጫጫው ጊደኛዬ እየተከራከሩ ነበር:: በምኔ ተወዳጅተው በምኔ መከራከር እንደ ጀመሩ ግራ ገብቶኛል:: ምን እንደሚያከራክራቸው አላውቅም::

ቀድሞ የሲኒማ ከከፈልኩ……ለስላሳውን የሚገዛው……ሳንዱዊቹን የሚገዙት እነሱ ነበሩ:: ዛሬ ግን ወደ እነሱ ተገላምጬ ለማየት ስለፈራሁ……ሳንድዊችና ለስላሳ ለመግዛት ቀደም ቀደም ብዬ ወጣሁ:: ማምለጥ ግን አልቻልኩም:: አምስት ሳንድዊችና አምስት ለስላሳ በአንድ ጊዜ መሸከም አልችልም:: ከአምስት ሳንድዊችና ከአምስት ለስላሳ ሁለት ሁለቱን እንኳን መሸከም አልችልም:: ከመሐል የተዋወቅኋት መዳፌን የኮረኮረችው ልጅ (የዚህ ዐይነት አለካከፍ የሆነ ጤይባነት አለው አይደለ? ግን ያኔ መስጦኝ ነበር) ከኋላዬ ተከትላ መጥታ:

«ለምን አልረዳህም» አለች::

ቀይ ዳማ ፊቷን በቅርብ የታጠበች የምትመስል ንፁሕ ልጅ ናት:: ቀና ብዬ ጊደኞቼን አየሁ:: በዝምታ ያዩኛል:: ትዕዛብትና ቁጥጥር (ሁለቱም ጓደኞቼ መንግስት ያቋቋቁመውን የቁጥጥር ኮሚቴ የሚጠሉ ናቸው) ይመስላል……

«እዚህ ነን……ካስቸገራችሁ ጥሩን……ስልክ ምናምን አድርግ» አለ ቀጫጫው……እጁን እንደስልክ ወደ ጆሮው እየወሰደ:: ለስላሳውን ለመግዛት ተራ ለመጠበቅ ጎን ለጎን ቆምን:: ዝም አልኩ:: አልናገርም::

«ስምህን ቅድም በደንብ አልሰማሁትም:: ማነው?» አለችኝ:: ጉኔ ናት:: ስስ የስንቡል ጠረን አፍንጫዬ ድረስ ይሰማኛል:: ሽቶ እወዳለሁ:: በጣም እወዳለሁ:: ለታላቅ እህቴ ያለኝ አድናቆት በሽቶዋ



@BOOKALEM

ብዛትና ዐይነት ነው:: እቤት ሙሉቀን ወይ......የጨርቅ፣ የግድግዳ፣ የጠርሙስ፣ የአርጌ ቴሌቭዥን፣ የጋቢ ጠረን ባሸት እውልና እስዋ ስትገባ የረቀቀ የአበባ ወንዝ ቤታችንን ያጥለቀለቀው ይመስላል......የምትከርምበት ክርማ ስትመጣ (እጮኛዋ ነው ይባላል) ናፍቀኸኝ ብላ ስትስመኝ ሰውነቴ በጠረንዋ ማማር ይንዘፈዘፋል:: እጅግ ሐብታም ስሆን......ገላዬን ከምታጠብበት ሻወር የሚወርደው ጥሩ ሽቶ ይሆናል' እያልኩ እጎርራለሁ አንዳንዴ ለእህቴ......

እና ይኸቺ ልጅ አውቃም ይሁን ሳታውቅ በቀስታ ስትከታተለኝ ሸተዋ የብዙዎችን ተመልካቾች ጩኸት፣ ሳንድዊችና ለስላሳ ለመግዛት የሚያደርጉትን ሽሚያ፣ ሙቀትና ግለቱን ድል አድርጉ ሲሰማኝ ሠራ-ብሕር የሚያክል ሕልም መሐል የወደቅሁ መሰለኝ:: ልይዛት......እጅዋን ልይዛት ሁሉ ተመኘሁ:: መስመጥ ማን አይፈራም? ስሟን ነገርኳት:: ስምዋን ደግማ ነገረችኝ......

«ምናልባት አልሰማኸኝ እንደሆን» አለችና::

«ሰምቻለሁ» አልኳት ውሸቴን:: አዎ ሰምቼአለሁ ግን ረስቼዋለሁ:: እንዲህ ስላት የፊቷን ሁኔታ በደንብ ሳላጤን ነው:: ጉኔ ቆማ ማዋራት ባፈራም ግን አንድ ጊዜ ያየኋት መልካም ፊቷን አእምሮዬ መስከ ውስጥ ጉርድ ፎቶግራፍ አድርጌ አዞረዋለሁ:: እውጭ ቆመን ሳለን የሣቀችውን አስታውሳለሁ:: ትኬት ስንቆርጥ......ታስብ የነበረውን በግምት ሳስታውስ እሞክራለሁ:: ሲኒማ ስናይ......ስንተዋወቅ......በጣቷ የኮረኮረችኝን......ነገር አስታውሳለሁ:: የፋቀችን፣ የነካችን አንዱ ጣትዋን አሁን ላየው ፈለግሁ::

«ለእኔ ሚሪንዳ ቢሆን ደስ ይለኛል» አለች::

«እሺ»

ዝም ተባባልን:: ትንሽ ቢቀረን......ምናልባት ፊት መግቢያው ቦታ ልንደርስ ለፊታችን ሦስት ወይም ሁለት ሰዎች ቢኖሩ ነው......

«ታውቃለህ......አሁን ያየነው ሲኒማ ውስጥ አንድ አክተር አለ......እሱን ትመስላለህ» አለችኝ::

ደንግጬ ዞር ብዬ አየኋት:: ፊቴ ላይ አለማመን ተገነዘበች መሰለኝ......

«እውነት......እንደ ብቻ......አለ አይደለ......አፍህ ጋ ምናምን......ሂ ሂ» ብላ......አፍዋን እንደመዳበስ ነካክታ ልትታከከኝ ተጠጋችኝ ልበል? እንደ መደገፍ? እንደ በትክክሻዋ ነካ አድርጋ እንደመመለስ? እንደዛ የመሰለ?



@BOOKALEM

መልስ አልሰጠሁም:: ልተባበራት ለመሳቅ ሞከርኩ:: ሳንቆይ ለስላሳና ኮካ ተሸክመን ወደሚጠብቁን ጓደኞቻችን ሄድን:: ብዙም ቀለል አለኝ:: ምክንያቱን አላውቅም:: 'አክተር ትመስላለህ' ስለተባልኩ አይመስለኝም:: በየጊዜው የሚያጋጥሙኝ፣ ያጋጠሙኝ ሰዎች ብዙዎቹ ስለብዙ ነገር የሚያውቁ መስለው የሚናገሩ ናቸው:: ትክክል መሆኑን ባላረጋግጥም ይቺ ልጅ እነዚያን ብዙ ሰዎች ብዙ እንደማያውቁ የአንድ ብር ሲኒማ አይታ የመለሰችላቸው መሰለኝ:: ዋናው ብዙ ጊዜ መርታቱ አይደለም፣ ማሸነፉ አይደለም:: መጥቀሱ አቅጣጫው ነው:: ይቺ ልጅ ሕይወቴ ሜዳ ላይ በዚህች ቀላል ዐነገር ከሺህ ሰዎች ጋር ጦርነት የከፈተች መሰለኝ:: የሚገርመው እኔ የእስዋ ወገን አይደለሁም:: ቢብስ ደንግጦ፣ ፈዞ፣ አፉን ከፍቶ የሚያደርገው የጠፋው የተምታታበት መሃል ሠፋሪ......ወይም ድርጊት ውስጥ ተጉትቶ መግባት የሚጠራጠር ቦቅቧቃ አይነት ሰው::

እና እየጠጣን እየበላን ከሌላዋ ሴት ጋር አስተዋወቁኝ:: የመጀመሪያዋ እንደገና ቀድሞ ለእኔ የነገረችኝን አወራቻቸው:: ቀጫጫው ተከራከረ......`የአገሬ ልጅ አበሻው ሰቀሩት ያንኪ ይመስላል` እያለ:: ጓደኛዋ 'ዝም በይ......ምን ያልሆነ እንዴት ታወራለች በእናታችሁ' አለቻት:: ይቺ የልጅትዋ ትንሽ ሃሳብ ነገር እንዳጣላቸው......እንዳከራከራቸው አላውቅም:: ምናልባት ሌላዋ ለምን ከቀጫጫው ጓደኛዬ ጋር ጓደኛዋ የጀመረችው ሴት በላለ......እንድትጨርሰው ማስጠንቀቂያ ይሆናል:: አለ ነገር ......`መጀመሪያ ከተዋወቅሽው ሰው ጋር ለምን አትቀጥይም አይደለ-ትዘላብጃለሽ ወዴት ወዴት ነው?` አይነት ትዕዛዝ:: ይቺኛዋ የሰማች ምን አትመስልም:

«ሀበሻ መሆኑ አይደለም:: መች ጠፋኝ:: የምልህ አንዳንድ ነገሮች ቀናንሰህ»

«ከፈረንጅ ስታስተካክይው አይወድም»

«ምናለበት......ፊልማቸውን ታይ የለም እንዴ?» አለች ወደ እኔ ዞራ:: አልመለስኩም::

«ቤቱ ውስጥ......መኝታ ክፍሉ የማንን ፎቶ ግራፍ እንደሰቀለ ታውቂያለሽ?» አላት እየሳቀ::

«የማንን......የዚህን አክተር?»

«የባሪያውን» ደስ አላለኝም:: ሌላኛው ጓደኛዬ ይስቃል:: ይገለፍጣል::

«ማነው ባሪያው?» አለችው::

«ፕሬዝዳንትሽ ነዋ» አላት ግራ ቀኝ እያየ::



@BOOKALEM

ለምን እንደሆነ አላውቅም ፊቷ ላይ ቅሬታ አየሁ:: ቅሬታ ግን አይቼ ወደ ሌሎች ጊደኞቼ የምትሳብ መሆንዋን ስጠብቅ ሐምበርገሯን እየበላች ተጠጋችኝ.......ከዚያ:

«ከሲኒማ በኋላ የት ነሽ?» አለቻት ጊደኛዋን:: ጊደኛዋ የደነገጠች፣ የተገረመች መሰለኝ::

«የው ነዋ፣ ተነጋግረናል እኮ» አለች ጊደኛዋ::

«የው ማለት ምን ማለት ነው?» አለ ቀጣጣው ጊደኛዬ:: ገቡ ላይ መደበር አያለሁ:: የሆነ ስምምነት እየፈረሰ ያለ ይመስላል::

«ሚስጢር ነው» አለች ይኸቺኛዋ::

«ምን ሚስጢር ነው......ቡና ጠጥተን ትሔዳላችሁ......» አለ ቀጣጣው:: አጫጭር ወሬ ተለዋወጡና ውሳኔም ሳይደረስ የእረፍት ደወል ተደዉሎ ሲኒማው አዳራሽ ተመልሰን ገባን:: ሲኒማው ተጀምሮ ደረስን...... በጨለማ እየተደናበርን ወንበሮቻችንን አገኘንና ተቀመጥን......ገና ቂጣችን ከማረፉ:

«ይኼን ነው ያልኳችሁ» አለችና ልጅትዋ ስሜትና ድል በተከናነበ ድምፅ ተናገረች:: ቢኒማ ላይ አንድ ተዋናይ ብቅ አለ:: አተኩሬ አየሁት:: ከዚያ ጀርባው ታየ:: በጉን:: ካሜራው ከሩቅ ወሰደውና...... ለሰከንዶች ፊቱን አሳየን:: ደነገጥኩ:: ልጅቷን ዞር ብዬ አየኋት:: በጨለማ ውስጥ እየሳቀች ታየኛለች:: መመለስ አልፈለኩም:: ሲኒማው እስኪያልቅ ድረስ በደንብ ያልገባኝን ታሪክ ትቼ ሰውዬውን በሚያደርገው ድርጊት ሁሉ ተከታተልኩት:: ሰውነቴ ሲረጋጋ ሲመቸው ይሰማኛል::

እና ሺህ የሀገሬ ልጆች ያጠፉትን በራሴ የመተማመን ስንልቦናዬን አንዲት ልጅ በባዕድ ሲኒማ ተረድታ አሳየችኝ:: አነሳችኝ:: ያኔውኑ ከሲኒማ ቤት ወጥቼ የሆነ መዓት ሕዝብ በሚመላለስበት ቡና ቤት መዓት ሕዝብ ባለበት......ሴትና ወንድ......ማንም ፊት ለፊት እንድታይ ሆኜ መቀመጥ ፈለግሁ:: በአስጠላችኝ በጠላችኝ የከተማዬ መንገዶች መሄዝ ፈለግሁ:: እያፏጨሁ፣ እየዘፈንኩ:: ያቺ ልጅ እህቴ ነበረች:: እሷን ነፃ አውጣ ብባል......ጋሻዬን አውርጄ ለጦርነት በረሐ አወርዳለሁ:: ስለ ኢትዮጵያ፣ ስለ ነፃነት ሲነሳ ስለ አድዋ ጦርነት ሲነሳ ትዝ የምትለኝ ይኸቺ ትንሽ ቀይ ዳማ ልጅ ናት:: በተለያየ ቴክኒክ፣ ስላገባኝ ብልጠትም የማላውቃቸውና የማያውቁኝ ሰዎች የሰሩኝ ቅኝ ግዛት ነበርኩ::

እና ከሲኒማው በኋላ ከፊልም ቤት እንደ ወጣን ቡና ለመጠጣት ከፊመሪ ካፌቴሪያ ገባን:: ጨዋታችን ሞቅ ባይልም::

'አክተር ትመስላለህ' (ማን ይጠላል መምሰል? የሚጠላ እጁን ያውጣ) መባሌ አግሉኝ ኬክ መሰዬ መሐላቸው ተቀምጫለሁ:: ግን

ብዙ አልቆየም:: የተሰማኝ ግለት እየበረደ እየበረደ ሲጨልም የለመደኝ የለመድኩት ፍርሃት ከተኛበት ተቀሰቀሰ፣ ቡካት ገባኝ:: ከሴቶቹ ጋር ጓደኞቼና ሴቶቹ በኬክና በቡና በወተት ተሞልተው እያሽካኩ ከክሬመሪ ሲወጡ ተከትዬአቸው ወጣሁ......አድራሻ ተለዋውጠው ሲለያዩ......በየቤታቸውም ሲበታተኑ ቀን ያየሁትን ፊልም ደግሜ በምሽት ለማየት ሲኒማ ኢትዮጵያ ገባሁ::

የዚያን ዕለት ማታ ከሲኒማ ኢትዮጵያ ስወጣ ነው ያገኘኋት:: አክተር መምሰሌ እንዳሞቀኝ:: ኤልፓ ሕንፃ ሥር ታክሲ ትጠብቃለች:: ወይም አውቶብስ:: ወይም ሰው:: ‘ታዲያስ’ ብዬ አለፍኳት......እንደሚያናግር:: ተሽኮርምማ ፊቷን አዞረች:: የፈላጊ መሽኮርመም:: የመሽኮርመምን ድርጊት መፍታት ራሱ ከባድ ጉዳይ ነው:: ምናልባት ለአጭር ጊዜ በራስ መተማመን ስለተሰማኝ ለመሽኮርመሟ ቀናሽ ትርጉም አልሰጠሁት ይሆናል:: ግን ይታወቃል:: የሚሰማ ነገር አለው:: መሽኮርመሟን ካየሁ በሁዋላ ልቤ ከውስጥ እኔ እንደተፈለግሁ ገባው:: አምስት ስድስት እርምጃ እርቀት ከራቅኋት በኋላ ወደ እሰዋ ተመለስኩ:: ወሬ ጀመርኩ:: ምን እንዳወራሁ ዛሬ ትዝ አይለኝም::

‘ወደ የት ነው?’ የሚለው የመጀመሪያው ጥያቄዬ ግን ትዝ ይለኛል:: ከዚያ በኋላ ያለው ምንም......ብቻ ከወዲያ ከሊስትሮዎች በኩል ሆኖ ሳየን ተጠጋግተው የቆሙ ሁለት የሚያማምሩ ወጣቶች......አንዱ ‘አክተር’ የመሰለ፣ ሌላዋም እንደዚሁ ሳትመስል የማትቀር:: ዛሬ የሚታዩኝም እንደሱ ነው:: ራሴ እንደ ሶስተኛ ሰው ሆኜ ከሁኔታው ተነጥዬ......ባይተዋር ሆኜ ሳይ የደበዘዘ ሰማያዊ ጅንስ ሸሚዝ ያደረገ ......ጥቁር ባጊ ሱሪ ያደረገ......ሁለቱንም እጆቹን ኪሱ ከቶ......አጠገቡ ቀይ ዳማ ቀጭን ልጅ ፀጉሯን አጭር ጉፈሬ የተሰራች......ከንፈሮቿ ቢራቢሮ የሚመስሉ......ባቶቿ ጠብደል ያሉ......(ለሙሉቀን መለሰ ዘፈን) ሽንጣም ልጅ ጋር ቆሞ ሲያወራ:: ከጀርባው ትልቅ ባለብረት በር ሕንፃ ......ዙሪያቸውን ወዲያ ወዲህ የሚሉ ሰዎችና የቆሙ ሰዎች...... የአየሩ ጠረን......እም (ወደ ውስጥ ስተነፍስ)......የትኩስ ኬክ......የትኩስ ዳቦ......የመጣኝ ባህል ጠረን፣ የጉንጉን (ዝልዝል) ጥብስ ጠረን ......

## 4

እና የመጀመሪያ ልጃገረዴ ነበረች:: የመጀመሪያም የመጨረሻዬም:: ድንግል ማለቴ አይደለም:: የሴት ሰውነት ሊያምር ይችላል......ግን ለስላሳና በቀላሉ ወንድ የሚያቀባጥል መስሎኝ



@BOOKALEM

አይታወቀኝም ነበር:: መጀመሪያ የቀጠርኳት ዕለት አቾሉኒ እየበላሁ ነበር:: ሁለተኛ ቀን ስቀጥራት አቾሉኒ እየበላሁ ነበር:: አቾሉኒ ጋብዤአት ነበር:: ዛሬ አቾሉኒ ሲነሳ......ሳይ......ስበላ ትዝ የምትለኝ እስዋ ናት:: የተረጋገጠ ተቀባይነት ያገኘ ወጣትነቴም::

እና ከእስዋ ጋር ስሆን......የጠፋው፣ የተደመሰሰው፣ እንዲሰደድ የተሴረበት ራሴን ያገኘሁ መስሎኝ ነበር......

የራሴን ልብስ ሁሉ መግዛት ጀምሬ ታላቅ ወንድሜ ደሙ ፈላ:: በጉዳናዎች፣ በከተማው የሚታይ ሎጋ ሆኜ ወጣሁ:: ታዲያ በኪሴ ......በቀኝ ኪሴ (የኮትም ይሁን የሱሪ) አቾሉኒ አላጣም:: ሲኒማ ስገባ፣ ከዚህች ጓደኛዬ ጋር ተቀምጬ ወተት ስጠጣ......ወደ ሥራ ስሄድ ......ከስራ ወጥቼ ጉዳና መሐል ስገባ......

እና ለመጀመሪያ ቀን አልጋ ውስጥ ገብተን ገላችን ሲነካካ በሲኒማ እንዳየሁት አሜሪካንኛ ስስማት የሸተተኝ አቾሉኒ ነው:: ከአፍዋ ከሆድዋ ጥልቀት የለውዝ ጠረን ነው:: ለውዝ ወላይታ ነው......ጎሙጉፋ ነው:: እነዚህ ሐመልማል የሚበዛባቸው......ሰው ያልነካቸው......ቢነካቸውም ቶሎ ያላበላሻቸው......ቢያበላሻቸውም እያሸነፉት በሕይወት መኖር የሚጥሩ መልክአ ምድሮች ያሉበት ቦታ ነው:: አቾሉኒ ሕይወት ይመስለኛል......ስስማት ከአፍዋ ጎድጓዳ ስፍራ ሕይወት......በትንፋሽዋ የምትሰጠኝ ይመስለኛል:: በትልቅ ሰውነቴ ትንሽ ቀይ ዳማነትዋን ጠቅልዬ ስይዛት ተያይዘንም የሚያምር ሕልም ወዳለበት፣ ሚሊዮን የሻማ ብርሃኖች ወደ ተለኮሱበት የሞቀ ባሕር ተያይዘን የገባን ይመስለኛል:: በእጅዋ ጀርባዬን ስትዳብሰኝ......ትናንሽ ከንፈሮቿ ቆዳዬን ሲነኩኝ......ዐይኖቿን ከድና እንደተረበሸ እባብ ስትንጠራራ......ገላዋ በግማሽ ከአልጋ ወርዶ......የምትጠራው ስሜ እንደማር ከአፍዋ እየፈሰሰ ቤቱን ሲሞላው......ግዙፍ የሆንኩ መሰለኝ፣ ከተፈቀደልኝ በላይ ግዙፍ ሆንኩ......

እና ግን እየቆየ በራስ መተማመኔ እያደገ ሴላ ሴት እንደሚፈልገኝ፣ እንደሚያየኝ ስረዳ ትሰለቸኝ ጀመር:: በቀን በቀን ካላገኘሁሽ የምላት በመጀመሪያ ሁለት ቀን፣ በሚቀጥለው ጊዜ ሦስት ቀን እያለ ለሳምንትና ለወር የቀጠሮአችን ጊዜ መስፋት ጀመረ:: የገባትም መሰለኝ:: እኔ በተገኘው ክፍት ቦታ ሌሎች ሴቶችን ማማገለል ወጣሁ:: ብዙ ቀላቀልኩ:: ቀድሞ ችላ የሚሉኝ የሚመስለኝን ደፈርኩ:: አንድ ነገር ግን ይጉላቸዋል:: ሁሉ አንድ ነገር ይጉላቸዋል:: ከእኔ እኩል አቾሉኒ አይበሉም:: አንዳንዶቹ አቾሉኒ ለመግዛት ሱቅ በደረቴ ጠርቼ በዛገች ሚጢጢ ቆርቆሮ እየተሰፈረልኝ በኪሴ ስከት የተዋረዱ የሚመስላቸው አሉ:: አንዳንዶቹ ከገዛሁ በኋላ እንዲበሉ ስጋብዛቸው እንፈልግም ይሉኛል:: እሺ ብለው ከበሉት ጋር ስተኛ ከአፋቸው



@BOOKALEM

የሚወጣው ጠረን ኦቾሎኒ ሳይሆን የጠጡት ኮካ......የሊፕስቲክና የቡና በወተት ጠረን ነው::

ኦቾሎኒ የነካው አፍ ይርበኛል:: እንደዛ የሚሸት አፍ ይርበኝና...... እስዋን እጠራታለሁ:: ጠርቼአት ስንገናኝ እፈራታለሁ:: አፍራለሁ:: እንደማፍር ይገባታል:: ከእኔ ጋር እያይዞ ያስቀራት ግሬሯ መሰለኝ:: ስህተቴን እንደተረዳሁ ታውቃለች:: ከስህተቴ እስክላቀቅ ነበር የምትጠብቀው:: እቤቴ ስልክ ደውላ እንዳወጣት ስትጠይቀኝ ሺህ ምክንያት እደረድራለሁ:: ወይም ማን እንደሆነች ጠይቁ ብዬ አንስተው እሷ መሆንዋ ሲነግሩኝ 'የለም በሉ' እላለሁ......

እህቴ ንዝንዛዋን እየቀላቀለች ትረግመኛለች:: እህቴ ከእኔ ተነስታ የእኛን ወንዶች ትረግማለች:: 'ሰልጥኑ' ትላለች:: የእሷ 'እጮኛ ከተዋት ወዲህ......ወይም ከተወችው በኋላ–የትኛው እንደሆነ አላውቅም ......'አሰልቺዎች' 'ከሹመትና ከስልጣን በስተቀር የማታወሩ' ናችሁ ትለኛለች:: እንዲህ ስትል አይገባኝም ነበር:: ዕውነት አይገባኝም ነበር:: ሹመት፣ ስልጣን ስትል የከፍተኛ ሲቀመንበር፣ የኮርፖሬሽን ሐላፊ ማለቷ ብቻ ይመስለኝ ነበር:: አሁን ግን ሳወጣና ሳወርደው የእኛ የሀበሻ ወንዶች ትልቁ ጨዋታችን ስልጣን ነው:: የበላይነትን በተገኘው ትንሽ ቀዳዳ ሁሉ መፍጠርና ማስተዋወቅ ነው:: እኔ ከእስር ያወጣችኝን ልጅ እሥር ቤት ስከታት የተሰማኝ ድብርት አልነበረም:: ያሠረኝ ሌላው ......ፊቱ ያልታየኝ......እኔ የበቀል ጥፊዬን የምወረውረው ያልነካኝ ሊላው ላይ:: ይገባኛል:: ዝርዝሩን መፍታታቱ ነበር የከበደኝ:: ምናልባት ያን ጊዜ እህቴን 'አብራሪልኝ' ብላት ሳይሻል አይቀርም ነበር:: ማለቴ ስለ ሽቶዋ ዐይነት ብዙ እናወራለን......ይኼን ይኼን ለምን አብራርተን እንዳላወራን ይገርመኛል::

እና የምቀርባት ሴት ሁሉ ኦቾሎኒ የላትም:: ተግደርድረው እንኩዋን ከቀመሱት አፍ ላይ የኦቾሎኒው መአዛ ትንሽ ተላልሰን ይጠፋል:: ያቺ ልጅ ግን ሆድዋ ውስጥ:–ሆድዋ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከጎሮሮዋ እስከ ሆድዋ ድረስ የኦቾሎኒ እርሻ ያለ ይመስለኝ ነበር:: የሆነ የሚያምር፣ ዕጌሬዳ የመሰለ፣ ወላይታ የሆነ፣ ድንግልናው የሚያሳብድ የእርባ ምንጭ ኦቾሎኒ:: እሱም የታመሰ......

እዚያው እጠገብዋ ውለታ-ቢስ ነው የሆንኩት:: ብዙ አልተጊዝኩም:: ጉንዋ ቆሜ እየዳበስኳት ነው የከዳኋት:: ከተ አልተናገረችኝም:: አልተናገረችኝም ማለት አልገባትም ማለት አይደለም:: እኔ ግን የገመትኩት እንደዚያ ነበር:: ምን እንደነካኝ አላውቅም:: ሲያጋጥመው አፌ ድ'ሞ ሊያታልላት ይፈልጋል......

«ትወደኛለህ?» ስትለኝ::

«ኦቾሎኒዬ እይደለሽ» እላታለሁ::



@BOOKALEM

እህቴ ባል አግብታ አሜሪካ ስትሔድ መሸኛ ፓርቲ ተደርጐ አለጠራኋትም:: ያን ማታ የመጣችው ሌላ ከእስዋ የተሻለች የምትመስል `አራዳ` ቢጤ ናት:: (`አንቺ ሰውዬ ትለዋውጪያለሽ ሲሉኝ እኮራ ነበር ሀሀሀሀ!!!) ያን ዕለት እህቴ ደምዋ ፈልቶ አደረ:: የእህቴን ቁጣ የአሮጊት ቁጣ አደረኩት:: በጭፍኑ ከምትቆጣ ለምን አታብራራም ነበር? አለ አይደለ ማብራራት:: ስለፍቅር፣ ስለግኑኙነት:: እኋም የምታፍርበት ነገር ይኖራል:: ማለቴ ስታብራራ ምሳሌ መስጠት ሊኖርባት ነው......ምሳሌው ደ`ሞ የራስዋ ልምድ ሊሆን ነው......ስለራሱ አወዳደቅ ማውራት ማን ይወዳል? ማለቴ ሌላው አታሎ ሌላው ክፉ ሆኖ የሰራብንን ስራ ማስተማሪያ አድርጐ ማቅረብ የሚያስቅ፣ `ጤይባ` የሚያሰኝ ነገር የለውም:: ተንኰለኛው ነው ቂል:: ተንኰለኛው ዛሬ አሸንፎ......ነገ ሲወድቅ ትናንት የሠራው `ብልጥ` የተሰኘው ድርጊት አላፊ ብራቅ መሆኑን ሲረዳ መክሰሩ ያጐብጠዋል:: በራሳቸው ተንኰል የሚወድቁ እራሳቸውን ይጠላሉ:: በሌላው ተንኰል......ምን ያደርጋል መፈላሰፍ?

5

እና ዛሬ እህቴን ከነባልዋና ከነልጆችዋ ኰሎራዶ ሸኝቼ ቤቱን ለብቻዬ ይዤ ከተቀመጥኩ ሁለት ሣምንቴ ነው:: እስዋ ከባልዋ ጋር ኮንቨርተብል መኪናቸውን ይዘው የወጡት ሌሊት ነው:: ደ`ሞ ሁለተኛ እርጉዝ ናት:: ሲሔዱ ደስታውን አልችለውም:: ከቤት ሲጠፉ ደስታውን አልችለውም:: ከባልዋ ጋር አንድ ቤት ከሆኑ ሲመሽ መከራከር የጀመሩ እስኪተኙ ያው ናቸው:: በቴሌቪዥን ቻነል ይጣላሉ--ይኼ ይሻላል፣ ያ ይሻላል......ቡና እንጠጣ፣ ወይስ ሻይ...... ይኼን ኩኪ አልፈልግም ስኳር ይበዛዋል......ያኛው ይሻላል......ብቻ የሚያስመርር ክርክር ያካሂዳሉ:: የፈረንጅ ጣዕም የተጋባባቸው ናቸው:: የሚገርመው ግን አራት ዐመቶች እዚህ አሜሪካ አሳልፌ......የጎደለብኝ ነገር እንዳለ ይታወቀኛል:: የቀረ ነገር አለ......ምን እንደቀረብኝ፣ እንደጐደለብኝ አላውቅም:: ደህና ገቢ ያለው ስራ እየሰራሁ፣ ሰውነቴ ወፍሮ፣ ቆዳዬ ቀልቶ፣ ፀጉሬ ሳስቶ በየቀኑ ከምታምረው ጊደኛዬ እዚሁ ፎቅ ላይ ከምትኖር በዕድሜ ጥቂት ከምትበልጠኝ ቆንጆ ፀጉረ ቀይ የጥቁር አሜሪካዊ እና የአይሬሽ ዲቃላ ሴት ጋር እወጣለሁ......

እና ገና በጠዋቱ ከአልጋዬ ተነስቼ የፊቴ እርጥበት ሳይደርቅ በር ሥር የወደቀውን ደብዳቤው ሳነሳና የላከውን ሰው ሳይ በሰውነቴ የሚሞቅ ደም ሲተላለፍ ተሰማኝ:: ማጅራቴ፣ ዐይኖቼ፣ ጭንቅላቴ፣ ሶፋ እግሮቼ ከሆን የማይታይ ነገር ጋር የተያያዙ መሰለኝ (ትዝታ?)::

@BOOKALEM

ላይ ቀስ ብዬ ተቀመጥሁና ፖስታውን ከፈተኩት:: እውስጥም እውጭም የፃፈችው 'ስምዋ' አለ::

From Ocholoni[19]
እና ዐይኖቼ በስስ የዕንባ ፊልሞች ሲሸፈኑ ይሰማኛል......

*ደኽና ነህ ለመሆኑ? አድራሻህን ትልቁ ወንድምህ ነው የሰጠኝ:: ምነው እግዚያብሔር ምን ይለናል ብዙ እንተዋወቃለን አይደል......በደንብ ሳትሰናበትከኝ የሔድከው:: ፊት ለፊት ባገኝህ ልነግርህ የማልደፍረውን ልበልህ:: በጣም ዕወድሃለሁ:: በጣም ዕወድህ ነበር:: እስከዛሬ ሳልነግርህ በመቅረቴ የሚቆጨኝ በሃይል ነው:: እስከዛሬ ለምን እንደተለየኸኝ ባስብ ምክንያቱን ማወቅ አልቻልኩም:: ከባድ ነው አይደል:: እንዲህ የምፅፍልህ ሚስት አድርገህ አሜሪካ እንድትወስደኝ አይደለም:: እንድታውቀው ነው:: ካልወደድከኝ አታስብ:: እኔ እንድታውቀው ነው:: ብዙ ልፅፍልህ አላማ የለኝም:: ካልተመቸህ አትፃፍ:: ትዝ ካላልኩህም እርሳኝ:: በቅርብ ትዳር ሳልይዝ አልቀርም:: አንድ ጥሩ ሰው አግኝቼአለሁ:: እንደ አንተ ባላፈቅረውም ጥሩ ሰው ነው:: ልልክልህ የምትፈልገው የባሕል ነገር ካለ ፃፍልኝ:: ቻው::*

ደብዳቤዋ አንድ የሉክ ወረቀት ግማሽ ናት:: ደጋግሜ ደጋግሜ አነበብኳት:: ታዲያ የድሮ ቂልነቴ ጥልቀትና ድምቀት እያገኘ ማታ፣ ከሰዐት፣ ጠዋት በተመቸኝ ጊዜ ስድስት ቅፅ ሰፋት እንዳላት የታላቅ ደራሲ ፅሁፍ ማንበቤን ተያያዝኩት:: ከእስዋ ጋር ያሳለፍኩት የመጀመሪያና...... የመጨረሻ ጊዜያት......(መጨረሻ አልነበረውም ግን) ......እንዲህ አጥረው በሰከንድ ዕርቀት እየተደጋገሙ ነፍሴ ውስጥ ልዩነታቸው ለውድድር ዐይነት ቀረበ......ተፃራሪ ገናናነታቸው......አሃዱ ያልን ጊዜ ስንወራጭ ፒያሳ አቧራ አስነስተን አዲስ አባን እስግ እንዳላስያዝን፣ በራሴ ግፊት ስጨርሰው......ከጎንዋ ተንሸራትቼ ......ለክህደት ሰወጣ ብርድ ልብሱ ለአመል አልተገለበም......

አዲስአባን ስለቅ መሃል አየር ላይ አይሮፕላኑ ጉማውን ሲያጥፍ ከሀበሻ መሬት......ከዚያች ልጅ የሚያያይዘኝን እትብት በጉያው

[19] ከኡቾሉኒ(እንግሊዘኛ)



@BOOKALEM

ሰብስቦ የያዘው ነበር......የደበቀው ነበር የመሰለኝ:: በስፋት ረዥምም ጊዜ ያልወሰደ ......ጥልቅ የሰከንድ ስብርባሪ ስሜት ነበረች:: ከአይሮፕላኑ መስኮት ወዲያ......ገብቶኝ ነበር ያኔ ለሰከንድ......ገና የአዲስ አባን ሰማይ ሳለቅ የአርባ ምንጭ ኦቾሎኒ ታሥሮ እንደቀረ......

ስስ ቀያይ ቅርፊቶቻቸው ያሳበኝ እጂ ላይ የሚጣበቁት......

የሚገመስ ፍሬአቸው ግራና ቀኝ ሳይና ታች የሚበለቀጥ ውተት......

አልያዝ ብለው የሚያመልጡት እንደ አንጎሌ የሃሳብ ኳስ......

ግን የጣልኳት......ከአፍዋ ውሃ እንዳልሰበሰብኩ......

ጣዝማዋ አዳልጦኝ እንዳልቃተትኩ......

የዞረበት ሕብረተሰብ አንገቴ ላይ ያስገባውን የወፍጮ ድንጋይ ያወለቀችውን......

እንድንሰነባበት እንኳን ያልጠራኋት......

ምናልባት ያን ዕለት ዕንቅልፍ እምቢ ብሎአት በጀርባዋ ተኝታ...... መስኮቷን ከፍታ ሰማይ እያየች ታስበኝ ነበር......

ትዕዝብት (ሳትረሳኝ) እስከዛሬ አንጀቱዋን እየበላው......

፮

እና አንድ ቀን ይኸቺን ደብዳቤ እህቴ አልጋዬን ስታነጥፍ ታገኝታለች:: ስለደረሰች እስከትወልድ ቤት ነው የምትውለው:: ቤት ስትውል አታርፍም:: አልጋዬን ታነጥፋለች:: የማያገባትን:: ታዲያ ግታ ባልዋ ባለበት:: (እሷም ከፉ ሆናለች) የማን ደብዳቤ እንደሆነ ትጠይቀኝና ወሬው ይደራል:: ባልዋም ታዝቦኝ እሷም ተችታኝ ተኙ:: ኑሮአቸውን ጠንቅቄ ስለማውቅ እንደዚያ የማድረግ መብት አልነበራቸውም::

እና ባልዋም እህቴም ወደዚህ እንዳመጣት ነገሩኝ:: አልፈለኩም:: ማሰቡ አስፈራኝ:: እሷን የማምጣቱ ሳይሆን (መምጣት እንኳን ብትፈልግ) አይኖቿን በድፍረት ማየቱ:: እንኳን ላመጣት ደብዳቤ ምን ብዬ እንደምፅፍላት አላውቅም:: ምን ይባላል? ምን ተብሎ ይፃፋል? እስከዛሬ ግድ

`እንደምን አለሽ?` ብዬ ስጀምር:: እስከዛሬ ያልተሰናበትኩ ሳይሰጠኝ......ከአገር ስወጣ እንኳን በስነሥርዐቱ ያልተሰናበትኩ እንዲያ......እንዲያ ያደረኩ ሰው......

`ትናፍቂኛለሽ?`

ይኼን አልሞከርም:: ትናፍቀኛለች:: ልቤ ግን የአዕምሮዬን ተራ ጮሌነት አላሸነፈም:: ታዲያ የሰራኋት ሥራ ሁሉ የናፋቂ አይደለም......



@BOOKALEM

`ላኪልኝ` ብላት ምን ላኪልኝ እላታለሁ? ነፍስዋን ሳስቸግራት ኖሬ እንደገና እንደገና ቦርሳዋን ላስቸግር? ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ሆነ:: `ማጠፊያው ያጠረ' የሚሉት ይኼን ጊዜ ነው እንዴ?

ስለ እሷ ለእኔ ደብዳቤ መፃፍ ቤታችን ለሚመጡ የተለያዩ ሀበሾች በእህቴና በባለቤቷ እየተነገራቸው......ወሬው ከፋፈላቸው:: `አምጣት` የሚለው ይበዛል:: `አምጣ` ከሚሉት ብዙዎቹ ፍቅር ያጡ ናቸው:: ወንዱም ሴቱም:: ፍቅር ከወሲብ ተምታቶባቸው......በቪዲዮ ቢሉት በምን ቢሉት ያልወጣላቸው:: ወይ ምናልባትም እዚህ በመደበራቸውና አገር ቤት ይሻላቸው እንደነበር አስላስለው እዚያ ያለውም ሃበሻ እዚህ መጥቶ አብሮአቸው ደይኑን እንዲያይ ፈልገው ይሆናል:: ቀላል ይመስላል......ግን ሁሉን በክርክር ወጠረው:: ፈረንጅ መጥበስ ጉራ አድርጐ የሚያየው ሁሉ በየቀኑ የሚኖረውን ህይወት እየካደ የላይ የላዩን ጣዕም ሲያሳየኝ በፍቅር እጦት የተቃጠልን መሆኑ ይታወቀኛል:: ጊዜ እስኪያወጣው እየጠበቅን እንጂ:: የሚስቴ ባል ወንድም*****ብሎ የቅፅል ስም የሰጣትን ሜክሲካዊ ጉኑ አስቀምጦ በአማርኛ `የአገርህን ልጅ አምጣ` እያለ ይሮሁብኛል......የመጣሁ ሰሞን እሱ ቀድሞ እዚህ ስለነበረ ሜክሲካዊ ገርል ፍሬንድ እንዳለችው እንደጉራ እያደረገ ይነግረኝ ነበር:: ሳልቀናበትም አልቀረሁ:: ታዲያ እየቆየ ከጉያው ጀርባ*****እንዳለ ብቻ ሲናገር ስሰማው የትናንቱ ራሴ......ምን ነገር ውስጥ ወድቆ እንደነበር በትንሹ ገባኝ::

እና ደብዳቤ መፃፍ አልፈለኩም:: አልቻልኩም ይሻላል:: ፈልጌአለሁ ግን አልቻልኩም:: ከመሐል አንዳንዱ ነገረኛ እንደ ክርክር እውስጤ መርዝ ሊተክል የሚፈልግ አለ:: `ቆይታ ቆይታ የፃፈችው እንድትወስዳት ይሆናል` ብሎ:: እሷ እንዲህ አይነት አይደለችም:: ምናልባት እስከዛሬ ያልፃፈችው እንዳይመስልባት ፈልጋም ይሆናል::

7

እና ቤንዚን ማድያው ሥር ከዝናብ እንደተጠለልን ያወራችኝ ነገር ደብዛዛ ከሚታይ ጭጋጋም የአእምሮዬ ወረዳ እየጐላ እየጐላ ወርውሬ የማልጥለው ቁጭት ሆነ:: የከበደኝ ቁጭት ሆነ:: በቸልታ የተነገረች የመሰለችኝን አንዲት ሐሳብ ተመልሰን ስናያት......ያቺ ቀላል ዐ.ነገር ብዙ ነገር በውስጥዋ ይዛ ነበርን?......እንላለን:: ቋንቋችን ራሱ የሚሸፋፍን ይሁን......ወይም ጆሮአችን ብዙ ወንፊት የበዛበት......

......ዝናብ እየዘነበ እንደ ተረት የመሰለ ወሬ ጀመረች:: ዝናቡ ዙሪያችን ይወድቃል:: ያምራል:: እጄ ወገቧ ላይ ነው:: ግን እስዋ ግን ተደብድባ የተነሳች ነው የምትመስለው:: ቀጫጫ ጊደኛዬ ሴት አወጣሁ ማለት ሲፈልግ `ደበደብኩ` ይል ነበር:: አስቲን ቋንቋ



@BOOKALEM

ነበር ያኔ:: አሁን ሳስበው......አሁን የቃሉን መነሻ ሳስበው......በሴትና በወንድ መሐል ያለውን የሚያምር ግኑኝነት እምባገነን ጭንቅላት ያላቸው ወንዶች ብቻ የሚገለፁበት ቋንቋ......የእነሱ ቋንቋ ብቻ መሆኑ ገባኝ:: ብዙ ጊዜ አንጠይቅም:: ብንጠይቅም አናውቅበትም......

እና የነገረችኝ ታሪክ ወይም ተረት ትዝ አይለኝም:: ብቻ እንደሚያቅፍ ጠጋ ብላ አይኖቿን ወደ መሬት ደፍታ `አንዳንድ ወንድ ሲያብዱለትም አይገባው` አለችኝ:: ሃ ሃ ሃ አልኩ:: አለ አይደል ሃ ሃ ሃ:: ይኼ ቁልፍ ዐ.ነገር፣ በአግድም በአሽሙር መነገሩ አልነበረም:: የሆነ ሁለንተናዊነት አለው:: የሆነ አጠቃላይነት አለው:: ጭንቅላት ቢኖረኝ ይሔን ሐሳብ አፈራርሼ የሁለታችንን ግንኙነት ታጥፌ ማጤን ነበረብኝ:: አላደረኩም:: ዝናብ፣ የሚያምር ንፁህ ውሐ፣ የሚጣፍጥ ትዝታዬ......በስተምዕራብ ደመናው ተከፍቶ ገላዋን እንደምታጥብ ሴት የተራቆተ ሰማይ...... የሚያምር የአፈር ሽታ:: ታዲያ ሃ ሃ ሃ አልኩ:: ያለሁበት ወቅትና ቦታ እንኳን አእምሮ የሚያንር ነበር:: ምናልባት ሌላ ሴት እያሰብኩ ይሆናል:: አልገባኝም እንጂ ሞክራ ነበር:: ናቅኳት፣ ቻላ አልኳት፣ ተሰላቸሁ፣ ጉራ ነፋሁ......

እና ከመሐል አንዳንድ ተቀናቃኝ ብልጥ ሐሳብ ይመጣብኛል:: አለ አይደለ ሐላፊነቱን የእሷ የማድረግ:: ምን ቅኔ የሚያስደርግ ነገር አለው? እያልኩ:: ያን ጊዜ ያበደች አይመስለኝም:: አላበደችም:: ሰው እንዳያያት (እኔም) ተደብቃ ለብቻዋ አብዳ ይሆናል:: ከእኔ ሌላ የምታስበው ሌላ ወንድ ወይም ነገር አይኖር ይሆናል:: የዚህ ስሙ እብደት ከተባለ ሌላ ነገር ነው:: እኔ በመሐል ካጋጠሙኝ ሴቶች ለምድ በመነሳት......በመሸራሞጥ......የእኛ ሀገር ሴቶች ባሕርይ ነው ብዬ...... አጠቃልዬ በመውሰድ እሷንም እዚህ ስሌት ውስጥ ከትቼአት ይሆናል:: ዕውቀትና ጮሌነት የተለያዩ......

ስህተቴን ለመሰረዝ አንዳንዴ ለራሴ እንዲህ እለዋለሁ: ተረት ከምታመጣ ለምን አታወራልኝም? ለምን ቀጥ አታደርገውም? ፊት ለፊት:: ታዲያ መቀኘቷን መነሻ አድርጌ አጭርና ሐላፊነቱ የእኔ አይደለም የተባለ ዳመራ አቀጣጥላለሁ:: ለአጭር ጊዜ ዳመራው እየዞረ ወይም እኔ እየዞርኩት ያሞቀኝና ይጠፋል:: እና ጠፍቶ የእሷ ደረቅ የቤንዚን ማደያ አቤቱታ ብቻ ሕሊናዬ ጆሮ ላይ ይጮሃል::

አለ አይደለ:: አለ አይደለ ሴት ለወንድ የምትሆነው ነገር አለ:: ከአፍዋ የሚወጣው ያበሳጓት የበላነው አቾሎኒ አልጋው ላይ ሁሉ ነው:: ቅርፊቱና ሳይበሉ ያመለጡት ፍሬዎች:: አታማርርም:: ሲቆረቆራት አታማርርም:: ተጠናቀን ተቆላልፈን እንደተኛን......አፌ ላይ እየተነ ፈሰች......`አቾሎኒ ላይ ነው የተኛሁት እንዴት እንደቆረቆረኝ ብታይ` ትለኛለች:: ከአልጋው ላይ መነሳት ግን አትፈልግም:: አልፈልግም:: የትንሽ ሥነሥርዐት መበላሸት ጠቅላላ

የፍቅር ኪነቱ አካል እንደሆነ የገባት ናት:: አለ አይደለ ካረጁ በኋላ ‘ድሮ አንድ ወዳጄ ነበር......አቾሎኒ ላይ የሚያስተኛኝ......ሂ ሂ ሂ’ ተብሎ ለሌላ አሮጊት ወዳጅ የሚወራ::

እና ስንለያይ እንኳን ቅር አላለኝም:: የሚገርመኝ እሱ ነው:: እንዳለች ይታወቀኛል ግን ቸልተኛነት:: እዚህ መምጣቴ የበለጠ ቀን የሚያሳልፍልኝ ድርጊት መስሎኝ ይሆናል:: እህቴ ጠርታኝ አሜሪካ ለመሔድ እንጻስብኩ ከነገርኳት በኋላ ሳይሆን አይቀርም ተስፋ የቆረጠችው:: ከምን እንደምሸሽ አላውቅም:: የፖለቲካ ችግር የለብኝም:: የኢኮኖሚ ችግር የለብኝም:: ምናልባት ከጀርባ ቀድሞ በልጅነቴ የተጫነብኝን የዝቅተኛነት ስሜት ለማሸነፍ ይሆናል:: አለ አይደለ ከላይ የደረቀ፣ የጠፋ ቢመስልም አሥሮ ከውስጥ እየገፋፋኝ:: በዚህም አዲስ ሰው ለመሆን የመፈለግ:: አለ አይደለ አንዳንድ ሰው ሴት ማብዛቴን ሲያይ ምክንያቱን እንኳን ባይረዳ ‘ድሮ እኮ እንዲህ አልነበረም በቅርብ ነው ዐይን ያወጣው’ እንዳይል......ቢልም እንኳን ዐይን ማውጣት መቼ መጀመር እንዳለበት የተወሰነ የተደነገገ ሕግ እንኳን ባይኖር......ሰላም የሚነፍገኝ ረባሽ ጥያቄ አይነት ግን ስለሚሆን......

8

እና ይህቺን ካትሪን የተባለች ክልስ ጊደኛዬን ሊፍት ላይ በሀበሻ እንግሊዘኛ ተዋወቅኋት:: አለባበስዋ በጣም የሚስብ ነው:: እንግሊዘኛዋ የሚዘንጥ ዐይነት ይመስላል:: ፈርቼአት ነበር:: ዘመናዊነቷ አስፈራኝ:: ብዙ የምታውቅ ትመስላለች:: አራዳ ትመስላለች:: ተደጋግሞ መተያየታችን አለማመደን:: እቤት ስለ እስዋ ሳወራ አበሻው ሁሉ እንድጠብሳት አበረታቱኝ:: አንድ ቀን እቤት ቡና እንድትጠጣ ጋበዝኳት:: ቀላል ነበር:: ወሬኛ ስለሆነች ወሬ ፈልጋለች:: ቡናው ፈልቶ እስኪመጣላት የእህቴን ቤት ከላይ እስከታች አጤነችው:: የሚያጋጥማትን ፎቶ ሁሉ ‘የማነው?’ እያለች ስታደርቀኝ:: በዚህ ተጀመረ:: የአፓርትመንትዋ ማማር፣ የሙታንታዋ ማማር፣ የቤቷ ዕቃ ማማር፣ የደረደረቻቸው መፃሕፍት ማማር:: አልጋ ውስጥ ከገባን በኋላ ለእኔ የኪሎዋ መክበድ ካልሆነ በተቀር የተለየች ሴት አልሆነችብኝም:: አንዳንዴ እጠገቧ ተቀምጬ በሐሳቤ አዲስ አባ የማውቃቸውን ሴቶች በቦታዋ ሳስገባ ይበልጧታል:: ‘ልዩ መሆን እወዳለሁ’ ትለኛለች:: ልዩ መሆንዋ አልታየኝም:: መጀመሪያ መጀመሪያ መስላኝ ነበር:: እየቆየ ግን......እንደው አማርኛዋ መንዝኛ ቢሆን......ምን ይውጣት ነበር እያልኩ ብቻዬን እስቃለሁ:: በእሷ ያልቀናብኝ ሀበሻ ነበር? እኔ ሳልኖር ቤት ስትመጣ የሚደረግላት እንክብካቤ ለንግስት ማንትስ እንኳን አይደረግም......



@BOOKALEM

እሁቴ በሐሳብዋ ለእሷ ሳትድረኝ አልቀረችም......

እና አንድ ቀን ማታ ላይ ከካትሪን ጋር እንድንገናኝ ተቃጠርንና ሁለት ኪሎ አቾሎኒና አፓርትመንትዋ ሊትር ኮካኮላ ገዝቼ ቤቷ ሔድኩ:: አልነበረችም:: (ገረባው ያልረገፈ) ከፍቼ ገብቼ አቾሎኒውን ከከርታሱ አውጥቼ ጠረጴዛ ላይ በተንኩት:: ቁልፍ ስለነበረኝ ቅላቱ ያምራል:: የመስታወት ጠረጴዛ ላይ አቾሎኒ ፈሶ ያየሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው:: ከመሐል ስልክ ተደወለ:: አላነሳሁም:: እስዋ ናት:: አንድ ሰዐት ዘግይታ እንደምትመጣ መቀበያ ካሴት ላይ መልዕክት ትታ ዘጋች:: ብትቀርም ግድ የሚሰጠኝ አልመሰለኝም:: መኝታ ቤቷ ገባሁ:: ትክክለኛ የሴት መኝታ ቤት ነው:: ሽቶው፣ ንፁሕ ንፁሕ የተሰቀለ ጨርቅ፣ በደንቡ የተነጠፈ አልጋ፣ ተጋድሚ ሙዚቃ የምትሰማበት ልዩ ሳውንድ ሲስተም፣ ወዘተ ወዘተ......ከዚህች ልጅ ጋር ለረዥምም ጊዜ በስነሥርዐት ነው ያሳለፍነው:: ማለቴ ስንሳሳምም ስንተኛም:: በጣም የተቆጠበች ናት:: ማለት አሰልቺ ናት:: የተስተካከለ መኝታ ቤቷን ሳይ በተቀናጀ ኪነቱ ተበጠበጥኩ:: ከእስዋ ጋር እንተኛ ሲባል ብርድ ልብሱ በቀስታ ይገፈፍና እንደ ሁለት ሴንጢዎች ተንሸራተን አንሶላ መሃል እንገባለን:: እላይዋ ላይ ሆኜ ፍትር ስሰራ የምታደርገው አንድ አስደናቂ ነገር......በቀስታ እያቃሰተች ግራና ቀኝ የሚነሳውን ብርድ ልብስ እራቁታችንን እንዳያስተረን ጀርባዬ ላይ መሰብሰብ ነው......

እና ጠረጴዛ ላይ የዘረገፍኩትን አቾሎኒ በእፍኝ በእፍኝ (በሁለት እጆቼ) እየዘገንኩ አልጋ ላይ በተንኩት:: ሁለቱንም ኪሎ አልጋ ላይ በተንኩት:: ከዚያ ቁጭ ብዬ መብላት ጀመርኩ:: ገለባውን ሆን ብዬ መሬት እጥላለሁ:: ፍሬውን እየፈለፈልኩ ገለባውን መሬት እጥላለሁ? ያምራል:: ቤዥ ምንጣፍ ላይ የአቾሎኒ ርጋፊ......ስዕል ይመስላል......የሆን የእስክንዴር ቦጎስያንን ስዕል......እና ደ'ሞ እመጣለሁ ካለችበት አንድ ሰዐት የበለጠ አረፈደች::

አቾሎኒ በኮካኮላ እያማግሁ......

ካትሪን ሁለት ሰአት ያህል አርፍዳ ስትመጣ በሙታንታና በካናቴራ ሆኜ መኝታ ቤቷን በአቾሎኒ ቅርፊት ሞልቼዋለሁ::

ጮኸች::

«አበድክ ወይ!!» አለችኝ::

አበድክ:: አበድክ........

9

እና ከዚህ በኋላ ነው አዲስአባ ላለችው ልጅ ደብዳቤ የመፃፍ ድፍረት የመጣልኝ:: ላኪልኝ ያልኳት አቾሎኒ ነው ሌላ ምን የቀረ ያያያዘን አለ? ለመምጣት ከፈለገችም ቦታው ክፍት እንደሆነ::



@BOOKALEM

እና እስዋን አግኝቼ ኦቾሎኒ ላይ እንድተኛ ነው የምፈልገው:: ይኸቺ እዚህ ያለችው ዲቃላ ባትጠላኝም ራቀችኝ::

ከወር በኋላ ያዲስ አበባዋ ኦቾሎኒ ገፈች:: ከደብዳቤዋ ጋር እንደ ኪሎ አንደኛ ደረጃ የአርባምንጭ ኦቾሎኒ......ራስዋ የቆላችው:: በጉ እርገዝመትና በመቀኛሸት ገለባው ከፍሬው የተለየ ኦቾሎኒ......እና ትዳር መስርታለች......ልጅም ልትወልድ ነው......ሴት ከሆነች ስምዋን 'ቀኖስ' ልትላት፣ ወንድ ከሆነ 'ስምዖን' ልትለው......በእኔ ስም::

— // —

1985 ሆላንድ

# ያ ሐመልማል

*(ራቁን አየኋት ምድረበዳ ቆማ*
*የተጨነቁት ነፍስ ሥጋዋ ሆኖባት አርጌ ባድማ)*

የሐንስ አድማሱ· <u>የተጨነቁት ነፍስ</u> 1955

## (ሳይሳነኝ እንዲሳነው)

**ቤ**ቴ ትልቅ መንገድ ዳር ነው:: እዚህ ዓይነት አውራ መንገድ ቤቴ ትልቅ መንገድ ዳር ነው:: ከአሥራ ሁለትና ከአሥራ ሦስት አመታት ዳር መስፈሬ ድሮ ድሮ ከአሥራ ሁለትና ከአሥራ ሦስት አመታት ዳር መስፈሬ ነበር:: ከግቢው በስተግራ ከቤቴ እንደወጣሁ ቤት የሚያስኮራ ነበር:: ከግቢው በስተግራ ከቤቴ እንደወጣሁ በግራ ቤት የሚያስኮራ ነው......ሀያ ሜትሮች እንኳን አይርቅም፣ በግራ የአውቶብስ ማቆሚያ ነው......ሀያ ሜትሮች እንኳን አይርቅም፣ ታክሲዎች የአውቶብስ ማቆሚያ ነው ሳያስኬድ ነባር፣ ነጋ ጠባ የውይይት ታክሲዎች ሁሉ ደ'ሞ ብዙም ሳያስኬድ 'የሚወልሉበት' ጣቢያ አለ:: መኪና የሚርመሰመሱበት ወያላዎች 'የሚወልሉበት' ጣቢያ አለ:: መውጣት የሚርመሰመሱበት ወደ ከተማው መሐል በቀላሉ መግባት፣ መውጣት እንኳን ባይኖረኝ ወደ ከተማው መሐል ድሮ ድሮ ከአሥራሁለት አሥራሦስት እችላለሁ:: እንዲህም ስለሆነ ድሮ ድሮ ከአሥራሁለት አሥራሦስት እችላለሁ:: እንዲህም ስለሆነ እኩራበት ነበር:: ፊት ለፊት አመታት በፊት የቤቴን አቀማመጥ እኩራበት ነበር:: ፊት ለፊት አመታት በፊት የቤቴን አጥርና የዚህን አጥር ትልቅ ቀዳዳ የሚደፍን በመንገዱ ትይዩ የግንብ አጥርና የዚህን አጥር ትልቅ ቀዳዳ የሚደፍን በመንገዱ ትይዩ የግንብ ያለው የብረት በር አለ:: ከበሩ በተቀር የግን የመሰለ ብርማ ቀለም ያለው የብረት በር አለ:: ከበሩ በተቀር የግን የመሰለ ብርማ ቀለም ሐረጉችና አበቦች የተሸፈነ ነው:: እነዚህ ይኼ የአጥር ግድግዳ በተሳቢ ሐረጉችና አበቦች የተሸፈነ ነው:: እነዚህ ይኼ የአጥር ግድግዳ በተሳቢ ሐረጉችና እንደ አረንጓዴና እንደ ቀለማም አበቦችና ሐረጉች ከግቢዬ ተርፈው እንደ አረንጓዴና እንደ ቀለማም አበቦችና ሐረጉች ከግቢዬ ተርፈው መንገድ ጠርዝ ድረስ እየተሳቡ አረፋዎች እግረኛ የሚሔድበት መንገድ ጠርዝ ድረስ እየተሳቡ አረፋዎች እግረኛ የሚሔድበት ላይ የተሰራ ቢሆንም በነዚህ ይወርዳሉ:: ቤቴ ቀና ብሎ ጉብታ ላይ የተሰራ ቢሆንም በነዚህ ይወርዳሉ:: ቤቴ ቀና ብሎ 'አረንጓዴው ቤት' እየተባለ ሐረጉች በከፊል ይከለላል:: ድሮ ድሮ 'አረንጓዴው ቤት' እየተባለ ሐረጉች በከፊል ይከለላል:: ድሮ ድሮ ሐመልማል ብዛት ብቻ ሳይሆን ነበር የሚጠራው......ግቢውን በከለለው ሐመልማል ብዛት ብቻ ሳይሆን ነበር የሚጠራው......ግቢውን በከለለው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የቤቴም ጣሪያ አረንጓዴ ቀለም በመቀባቱ:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የቤቴም ጣሪያ አረንጓዴ ቀለም በመቀባቱ:: ባሌ ከሞተ ከ ዐይን የሚስብ፣ በቦታ ምልክትነት የሚጠራ ቤት ነበር:: ባሌ ከሞተ ከ ዐይን የሚስብ፣ በቦታ ምልክትነት የሚጠራ ቀለም እየለቀቀ፣ ፣ ዓመት ወዲህ ግን የሚንከባከበው አጥቶ የጣሪያው ቀለም እየለቀቀ፣ ፣ ዓመት ወዲህ ግን የሚንከባከበው አጥቶ የግድግዳው ጡቦች የሰው ዓይን ከማይደርሰበት ከጀርባ በኩልም የግድግዳው ጡቦች የሰው ዓይን ከማይደርሰበት ከጀርባ

ወዲያና ወዲህ ጥቁር መብረቅ በመሰለ ስንጥቅ ተሸንታትረውን የግድግዳውም ቀለም እየተቀረፈና በዝናብ ታጥቦ መሬት እየወረደ ነው:: አንዳንድ የተሰበሩ የመስኮት መስታወቶቹም በፕላስተር ተያይዘው የመፈራረስ የመጀመሪያው ምልክቶች እየታዩበት ነው:: በአጥሩ ላይ የሚንገዋለልሉት ተክሎችና ሐረጎች በማርጅታቸው ተንፈትፍተው መብቀላቸውን ረስተዋል:: ዛሬ ዛሬ በመስከረም በመስከረም እንኳን አረንጓዴነታቸው በውሃ የተበጠበጠ የመሰለ ሐረጎች ከግንቡ ወደ መሬት ለመውረድ ቃጥተው አለሙበት ሳይደርሱ ተንጀላጅለው ይቀራሉ...... ዛሬ «ያ አረንጓዴ ቤት ጋ......» ቢባልም በሽበተ ዘልማድ እንጂ ግርማው ከጠፋ ባጀ......

ቤቱን ማደሻ ገንዘብ አጥቼ አልነበረም......

በዓለም ላይ አንድ ሰው ብቻ ተወዶ ያም አንድ ሰው ሲሞት ምን ይደረጋል? ቤት ለብቻው ምን ትርጉም አለው? ዛሬ ማታ ምን ከምኖርበት ሰሙ የተጠራ ግዙፍ ቤት ሳሎን ውስጥ በባለ መስታወቱ ሦፋ በር በኩል ወደ ውጭ እያለሁ:: ባሌ ከሞተ ወዲህ ይኼን 'ፍሬንች ዊንዶው' ከፍቼው አላውቅም......ተሰብሮ ሳገኘው በጠንካራ ፕላስተር ካጣበቅሁት ጊዜ በስተቀር (ምናልባት ከአራት ዓመታት በፊት):: ሁልጊዜ የምቀመጠው እዚህ ሦፋ ላይ ነው:: ግራና ቀኝ ለተመሳሳይ የጊዜ ዕርዝመት ሰው ተቀምጠባቸው የማያውቁ ሌሎች ሁለት ረጋ'ኸም ሦፋዎች አሉ:: ሁልጊዜ ባዶ ናቸው:: ያረጁ የፀደይና የእብዘርሸር መፅሔቶች ከባሌ ጋር አብረን የምናነባቸው የነበሩ......የምንስቅባቸው፣ የምንወያይባቸው......እነሱን ዛሬ ደግሞ ደጋግሜ እንብቤ አዳክመውኝ፣ ሰልችተውኝ፣ አንዳንዴም አማረውኝ እንደ አጋጠመኝ ወርውሬአቸው የወለሉ ከፊል በተገላለጠና በተከደነ እነሱ ተሸፍኖአል::

ባሌ ስሙ ምንተስኖት ይባል ነበር:: በስሙ ጠርቼው አላውቅም:: ስሙ ያንሰው ይመስለኝ ነበር:: 'የእኔ ወተት' ነበር የምለው:: (ሌላ ትርጉም አይሰጠውና) የምፈልገውን ነገር ሁሉ ከቻለ የሚያደርግልኝ ባል ነበር:: (ባል ሲባል 'በዓል' የሚለውን ቃል ያስታውሰኝ ነበር) እሱን የጠየቅሁት ጉዳይና ነገር ሁሉ ይፈፀም ነበር:: የምሻውን ምንም ነገር 'እምቢ' ብሎኝ አያውቅም:: የሚያባብለኝ......ሳይጎራብጠኝ የሚዳብሰኝ ነበር:: ሳላኩርፍ ለንቦጩን ስጥል ግንባሩን ግንባሬ ላይ አስደግፎ ያሻሽኛል ወይ ፊቴን በእጆቹ መሐል አስቀምጦ 'የእኔ ሞላጫ ማንጎ' ይለኛል:: አንገቴንም ለማማበል ከሐብሌ ጋር በሦፋ እርጥብ አፉ ይይዘዋል:: ዘፈን አይችልም ግን በሽካራ ድምፁ ሳንጎራጉር ሲል አንጀቴ ይላወሳል:: ታላቅ ደስታና የምኞት ጊዜ ነበር:: ስህተቱ ይኼ ሳይሆን ይቀራል? ስህተቴን ሁሉ በመውደድ እየሰረዘ ሲቀበለኝ ጊዜ 'ጥጋብ' የተባለው



@BOOKALEM

ነገር ተሰምቶኝ? መቼም ስለ ጥጋብ ብዙ አልተፃፈም አልተባለም እንጂ ከእኔ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን የምንቻል ሰዎች አይደለንም:: ምናልባትም 'ሰለጠነ' ከተባለው አገር ትንሽ የኖርኩትና ያነበብኩት(የለቃቀምኩት)/ለትምህርት የሆነ ምዕራብ አገር ሄጄ ነበር/ 'የሴትነት' ዕውቀት አፍቃሪዬ ላይ እንኳን ምህረት የለሽ 'ባለ ነፃነተኛ' አድርጎኝ ይሆን? ወይ ዕውቀቴን በትክክል መጠቀም አለመቻሌ? ወይስ በተፈጥሮዬ ባለጌ ሆኜ?

በተለይ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በየካቲትና በታሕሳስ በጋዎች ከቤታችን ጀርባ የሚጠቀለል ቀላል የስፖንጅ ፍራሽ መሬት ላይ አንጥፌን ገላዬን በቅባት የሚያሽኝን አልረሳም:: ዛሬ አንዳንድ ጊዜ አይኖቼን እጨፍንና እሱ እንዳለ ሁሉ ወለል ላይ በሆዴ ተኝቼ አፌን እከፍትና እጆቹ ጀርባዬ ላይ እንዲመጡ እጠብቃለሁ:: በሚያዳልጥ ሙቀታቸው እንዲዳብሱኝ እጓጓለሁ::

ታዲያ ግን ዛሬ በድብርት ዳምጠው ተተምትሜ እተጋደምኩበት እንቅልፍ ይወስደኛል:: የደረቅ ሌሊት ብርድ የመስታወት በሩንና መጋረጃውን ዘልቆ አልፎ እራቁቴን የተዘረጋሁበት ወለል ላይ ይይዘኛል ......እየተንጠራራሁ፣ እየተነጫነጭኩ ከእሱ ጋር እጋራው የነበረ አልጋ ውስጥ ገብቼ እተኛለሁ::

ጠዋት ጠዋት ፊቴን ስታጠብ በአካባቢው የድምፆች መረባበሽና መምታታት ተፈጥሮ እሱ ከኋላዬ ይቆማል:: ወገቤን በሚወዱት ወንድ ተይዞ በግድ ጉንበስ ብሎ መታጠብ የት ይገኛል? አንዳንድ ጊዜ 'ሊታጠብ አልቻልኩም' እያልኩ አባርረው የነበረው ዛሬ ይቆጨኛል::

እንዲህ የማማርርበት ምክንያት ይኼ ነው:

ለብዙ አመታት ልጅ ለመውለድ አብረን እንደዶለትን በቃ እንደ ዶለትን ሳይሆን ምንም ሳይሳካ ባለቤቴ አረፈ:: ('ሳይሳካ' ስል የአለመውለዱ ምክንያት ከእግዜር ወይ ከሰይጣን የተላከ አይመስልም?)

ዛሬ ከትዝታው......እንዲህ ከሚያስቃየኝ፣ ቲያትር ከሚያሰራኝ ትዝታው፣ ከፎቶግራፉና እንደ ቀልድ በካሴት ላይ ከቀዳሁት ድምፁ በስተቀር የቀረው ምንም የለም:: በረዥም ጊዜ ንጭንጭ፣ ተስፋ መቁረጥ......ከእሱ ትዝታ ለመራቅ፣ የእሱን ቄንሳ ለመሰረዝ በማደርገው ጥረት ልብሶቹን እንኳን ለእኔ ቢጤ ሰጥቼ የቀረኝ አንድ ኩቱ ነው:: ያም የቀረበት ምክንያት አለው......ዕውነቱን አጠንክሬ መናገር ልጀምር እንጂ......

ልጅ ለመውለድ ከእኔ ይበልጥ እሱ ይፈልጋል:: ብዙ ጊዜ ባይሆንም ደጋግሞ መውለድን፣ ልጅ መልካም ነገር መሆኑን ያነሳሳል:: እኔ ግን ልጅ ማርገዝና ማጥባት አልፈለኩም......እሱን ባሌን ብቻ ነበር የፈለኩት:: ከሁሉ ነገር እሱ ይበልጥብኝ ነበር:: አንድ ማታ ላይ ቅዳሜ



@BOOKALEM

ነው ቀኑ......ጆኒወከር ውስኪ ገዝቶ መጣና ቤታችን ፊት ለፊት ያለው ልሻ ቦታ ላይ ቆሞ እውጭ ሆነን እንድንጠጣ ጠራኝ:: እኔ በውስጥ ልብስ ቤት ውስጥ ቆሜአለሁ:: 'ፍሬንች ዊንዶው' ተከፍቶአል::

«ልብሴን ለውጬ ልምጣ» አልኩት

«እንደ እሱ ነይ:: አይበርድም» አለኝ:: ብርድ እፈራለሁ:: ብርድ ብቻ ሳይሆን ቤታችን መንገድ ዳር ስለሆነ ተንኮለኛ አላፊ አግዳሚ ድምፃችን ሰቦት በብረቱ በር ላይ ተንጠራርቶ በግማሽ የተራቆተ ሰውነቴን እንዲያይ አልፈለኩም:: ይኸቺ ቀዘባ በከፊልም ይሁን በሙሉ የምንተስኖት ናት:: ሌላ ሰው ሲያደንቀኝ ሲያተኩርብኝ ሲሞካከረኝ እንኳን አልወድም:: እንዲሁ ምንተስኖትን መሻማት የሚሻ መኖሩ እረፍት ይነሳኛል:: `አልመጣም' ስለው ፈርቼ ነው ተባት ለቀላዋጭ የሚያጋልጠኝ በቂ ብርሐን ኖሮ እንኳን አልነበረም:: አንዳንዴ ስንወድድ፣ ስንለመን፣ ለፍቅር ድሪያ በሚወደን ስንጎነጥ፣ በትንሹ በመሣደርደር ይሔን መለመን ይሔን ልምምጥ በጉላ መልክ እንድንሰማው እንፈልጋለን:: እንዲነገርልን እንፈልጋለን:: እየተግደረ ደርኩ ግን ሔድኩ:: ብርጭቆ እንኳን መያዝ እረሳሁ:: እሱ ጋ ስደርስ ለእኔ ሲል በጠርሙሱ ክዳን የቀዳትን ውስኪ `በስመአብ' ብለሽ ጠጪ ብሎ ሰጠኝ:: እሷን ጠጣሁ:: ከልጅነቱ የዕቃ ዕቃ ጨዋታ የቀዳት ነገር:: ሲያሳዝን::

«ኩቴን ልስጥሽ አይደለም?» አለኝና ኩቱን አውልቆ ትከሻዬ ላይ አደረገና በቱሙ ከጠርሙሱ ተጉነጨ::

«ዛሬ መስከር አሰኘህ?»

«ከአንቺ ጋር......ብትንትን እንበል»

«አ......ጥሩ አይደለም»

«ትንሽ ሞቅ......እ?»

«ባይሆን እሱ ይሻላል»

«ለምን አንቀመጥም»

«ይበርዳል» አልኩት

ውስኪ ባልያዘ እጁ መሬቱን ሞከረና......

«አይበርድም......እኔ እቀመጣለሁ......ጭኔ ላይ ትቀመጫለሽ»

«እምቢ......እ»

«ለምን? ነይ»

«እዚህ አይመችም፣ መጥፎ ጊዜ ነው»

«ምንም አናደርግም አይዞሽ»

«ምንም አናደርግም?»



@BOOKALEM

«ምንም:: ጉረቤቶች ያዩ ይሆናል:: ምን መሆንሽ ነው ዕብድ አደረግሽኝ?»

እንደተቀመጠ እሱ ላይ ሳይሆን እግሮቹ መሐል እግሮቼን አጥፌ ቆሞ አልኩ.....እንድ ጉልበቱን ተደግፌ:: ጠርሙሱን በቀስታ እየተቀባበልን መጠጣት ጀመርን:: ጨለማው እየከበደ በግምት ሁለት ሰዐት ሲሆን ሁለታችንንም ሞቅ አለን:: ያ ምሽት፣ ያ የጠራ ሰማይ፣ ያ የአትክልቶቹ ጠረንና ንቅናቄ፣ ያ ፀጥታ፣ ያ ቀላል ምቾት እስከ አሁን ድረስ ልቤና ሕሊናዬ ላይ ተቀርፆአል......በጠቆረ የአንጎሌ ሰማይ ላይ ሳያርፍ የሚሮጥ ሰው እንደያዘው የእጅ ባትሪ ብርሃን:: እየሞቀንና የቅዝቃዜው ጥንካሬ እየቀለለን ሲሔድ ሳሩ ላይ ጎን ለጎን ጋደም አልን:: ፊቱን ወደ ፊቴ ዞር አድርጎ በወፍራም ድምፁ የረባና የለረባ፣ የሚያስቅና የሚያሳዝን ነገር አጉተመተመልኝ:: በረፒ ተራራ ላይ ብርሃን እየሁና አልኩት:

«ያ ምን ይሆን?»

«ብቸኛ ፍቅር ትሆናለች፣ ሴቴ ብርሃን ወንዴ ብርሃኗን ስትጠብቅ......»

«ሂሂሂ ስትችልበት፣ ስታምር»

«ሰውነት ታዲያ ጠዋት የሚሆነው የወለዷት ፀሐይ ስትመጣ አይደለ»

«ሂድ ሃሃሀ ምን ይለኛል ሰው በመንገድ የሚያልፍ»

«ባዘነ ጨለማ ትሰቃለች እዛ
በሉ ጠጋ እንበል መውደድ ከእስዋ እንግዛ»

«ሂድ»

በሞቅታው ትንሽ ዞር የምትል ጭንቅላቴን ሳባብል ዓይኖቼን ለጨፍን ግርማ የሞላበት የምንተስኖት ድምፅ ከምድር ጥልቀት የመጣ መስሎኝ ነበር:: ባለማመን እጄን ወደ ተጋደመበት ስሰድ ጣቶቼን ለጨዋታ በትኩስ ጥርሶቹ ቢነክስ እንዴት ልበል ልገልፀው የማልችል ዓይነት ፍስሐ ከአንጀቴ ወጥቶ በዛ ቦታ በዛ ምሽት አረንጓዴ ግቢዩ ውስጥ አልፈሰሰም? በዚህ የፍቅር ማታ የሁለታችን ሳቅ ነበር ንጉሠነገሥት:: በዚያች ግርማ ባላት የምሽት ዙፋን ላይ የሁለታችን ስሜቶች ብቻ ይመስሉኛል ዘውድ የደፉት፣ ሐር የለበሱ፣ ሉል የያዙ......በትረ-መንግስት የተደገፉ......እየተፈላለግን ሔድንና ኩቱን መሬት ላይ አነጠፈ:: በሜዳውና በቤታችን መሃል ዕርቀቱ እንደ እጋዴን መሰለኝ:: እንዲህ መቅላት በጀመሩ ዐይኖቼ ዞር ዞር እያልኩ ሳይ ግቢያችን ከመቼውም የሰፋ መሰለኝ:: በመቃጠል ላይ ባለች አፉ ሰውነቴን ሲዳስሰኝ ኩቱ ላይ በጀርባዬ ተንጋለልኩ......የገበሩ ቦብሊን ደጤንና ወገቤን በሚጣፍጥ ቅዝቃዜው እየነካኝ:: ሰማዩ ንፁህ ጥቁር



@BOOKALEM

ነው:: ስፋቱና ጥልቀቱ ልብ ይሰውራል:: ውብ የሆንኩ መሰለኝ:: ይጋባል መሰል:: ለረዥም ጊዜ ተሳሳምን:: የውስጥ ሱሪዬን ሲያወልቅና በጋለው በሚፋጀው ሰውነቴ ላይ ቀዝቃዛ አየር ሲፈስ......ልቤን የሆነ ነገር ሰለባት......እንደ ትንሽ ልጃገረድ አፌን ከፍቼ ከንዱ ላይ ተጋደምኩ:: እሱን ተደግፌ ተኝቼ ስባንን ሁሌ ልብ የምለው የተከፈተ አፌ ነው:: ያሳፍረኛል:: ለምን ይከፈታል? እያልኩ ያሳፍረኛል:: እንዲህ የተጠጋሁት የሣሩ ጠረን፣ የእሱ ላቦት፣ የአፉ ውስኪ ሲነፍስብኝ፣ በትከሻው አሸጋግሬ ከርቀት የማያት ደቂቅ የኮኮብ ሞላ ገፅዋ ላይ ማር እየሳቀ......ከሩቅ የምሰማው የሰው ድምፅ እንደሚፈስ በገና......ማሕፀኔም እንደ ሞቂ ረግረግ......እግሬ ዳሌው ላይ አርፎ......የእኔ ዋዋዬ......

«እመቤትዬ? ለልጅ ይሁን» አለኝ:: ሰምቼዋለሁ፣ ደ`ሞ አልሰማሁትም:: የነሆለለች ልቤ እየነዳችኝ እግሮቼን ግራና ቀኝ:: ጭንቅላቴ ሣሩ ላይ አርፎ:: በዚያን ወቅት የምኖረውን የስጋ ደስታ እያሰብኩ......የጠየቀኝ ጥያቄ ትዝ አለኝና......ለልጅ? ለልጅ? የሚነድ ጦር ሲጠጋኝ ይሰማኛል ......በድንገት በርግጌ ተነሳሁና ቁጣ በተሞላው ቃል እየተንተባተብኩ ከላዩ እንዲነሳ ጠየቅሁት::

«ምነው?» አለኝ:: ፊቱንና መዳበሻ እጁ ቅር ብሎአቸው:: እንደጎዳሁት ገብቶኛል::

«ልጅ መውለድ አልፈልግም! ስንቴ ልንገርህ!?» አልኩ እየተነጫነጭኩ ተሰብስቤ ቁጭ ብዬ......ዝቅ ባለ ድምፅ......ወደ ደረቴ ጉንበስ አድርጌ እየተናገርኩ:: በልፊያ የተበታተነ ፀጉሬን እየሰበሰብኩና በእጆቼ ወደ ኋላ እያበጠርኩ::

«በእናትሽ......አንድ እንኩዋን ቢሆን እንውለድ»

«ትንሽ እንቆይ......ልጁ ከመጣ ከአንተ ጋር......መሆን አልችልም»

«ያው ነው የእኔ እመቤት» እንገቴን ሳመኝ:: ፊቴን ሳመኝ:: ሁለመናው ይለምነኛል......ግንባሩን አልቦታል......ደረቱን አልቦታል......ከንፈሮቹ ጥፋት እንደአጠፉ ልጅ ይርበተበታሉ::

«አይሆንም......እዚህ ደ`ሞ ብርድ ይገባኛል» ብዬ ተነሳሁ::

ያን ቀን ተናደደ:: አይናደድም:: ሦስት አመት ስንኖር ተናዶ አያውቅም:: መናደድ ለእሱ እንግዳ ፀባይ ነው:: ተረበሽኩ:: ለምንድነው ብዙ ጊዜ የእኛ ሴቶች የሚወደንን የማናውቀው? ስሕተታችንን ጠቅሶ ሊቆጣን እንኳን የሚፈራውን ወንድ......እንደ ደካማ የምንቆጥረው? ከላዩ ሲነሳልኝ ደስ አለኝ:: መናደዱ ቢረብሸኝም ግን ደስ አለኝ:: ተናዶ እኔን ትቶኝ ወደ ቤት ለመግባት ተነሳ:: የውስጥ ሱሪዬን ለበስኩ:: የጨርቅዋ ከርሳሳነት የሚጣፍጥ ነገር ነበረው:: ትንሽ እየተነጫነጭኩ ተከተልኩት::



@BOOKALEM

«ምነው? አታኩርፈኝ:: ምን ያስቀጣል?» አልኩት:: የሰማኝ አላመሰለኝም:: እዎ ያስቀጣል:: ማስቀጣት ያስቀጣል:: የሚወደን ወንድ ላይ ለምን ብልጥ መሆን ይቀናናል? ስሜታችንን ጠቅላላ ጠብቆልን አንድ ነገር እየሰገደ ሲጠይቀን ለምን አቅልለን እንገምተዋለን? ያውም ለማይጉዳ ነገር?

ሺት::

ቡል ሺት::

ያን ዕለት ማታ የእውነት አኮረፈኝ:: ለቲያትር፣ እኔን ለመጉዳት እንዳልሆነ አውቃለሁ:: ግን......

«ምን እንዲህ ትሆናለህ? አውቀህ ነው አይደለም?» አልኩት::

የምወደውን የሚወደኝን......እንደ ነፍሱ የሚወደኝን ሰው ቲያትረኛ አደረኩት:: 'አትወደኝም......ስታስመስል ነው' አልኩት:: አንድ ቃልም ሳይወጣው እራት በልተን ተኛን::

ጠዋት ስነሳ ጉኔ አልነበረም:: የገባኝ ያን ጊዜ ነው:: በደንብ የገባኝ ማለቴ......

አልጋዬ ላይ ብቻዬን እንደተቀመጥኩ ተርበደበድኩ:: ለዘለዓለም ትቶኝ የሔደ መሰለኝ:: እንዲህ ያለ ልምዱ ሊሊት በሰንበት ተነስቶ ሲወጣ......በሰንበት:: በሰንበትማ ከአልጋ አንወጣም:: በሰንበትማ በትራስ ስንደባደብ......አንሰላ ስንጊተት፣ ስንኩራኩር፣ ስንበሻሸቅ ነው የምናረፍደው:: ቁርስ መብላትም ትዝ አይለን:: በድንጋጤ ከአልጋዬ ተነሳሁና ሳሎን ገባሁ:: በየክፍሉ ገባሁ:: የለም:: ተመልሼ በመስታወቱ መስኮት......መጋረጃ ገልጬ ወደ ውጭ አየሁ:: የጠዋት ቀዝቃዛ ፀሐይ አትክልት ቦታው ላይ ፈሳለች:: የአጥሩ በር ላይ ጤዛ ይፈልቃል:: አትክልት ቦታው መሐል ላይ ያልተከደነ የውስኪ ጠርሙስና መሬት ላይ የተነጠፈውን ኩት አየሁ:: ያለፈውን ምሽት አስታወስኩ:: አሁን ባገኘው ተመኘሁ:: ይኼ ጊዜ ሳያልፍ እንዲያስረግዘኝ ፈለግሁ:: ውስጤን፣ ገንዳዬን በአምሳሉ እንዲሞላው ፈለግሁ::

አልመጣም:: ለዘላለም አልመጣም:: የተቀመጠበት ታክሲ ከአንድ አምቡላስ ጋር ተጋጭቶ ነው አሉ:: ከአምቡላንስ ጋር:: ከሁለት ሰዐት በኋላ ሆስፒታል ተጠርቼ ሔድኩና ሲሞት አየሁት:: ጭንቅላቱን እየነቀነቀ......

ለምን እንደነቀነቀ ይገባኛል:: እተጋደመበት ሕይወቱ ሲያልፍ...... አንጀቴን አጥፌ ሆስፒታሉ ወለል ላይ እንደአበደ ሰው ስፈራገጥ......'ዓለም ከአሁን በኋላ ትጥፋ' ስል ለምወደው ባሌ ብቻ ያለቀስኩ የመሰላቸው ብዙ ነበሩ:: ለእኔ እሱ ብቻ

አልነበረም......መወደዴ ብቻ አልነበረም......አንድ የተመኘውን ነገር ሳደርግለት ባለመፈለጌ ቆጭቶኝ ነው።

አቤት ሲቆጭ።

ወአ ሲቆጭ።

ዋይ ሲቆጭ።

አርባው ተለቅሶ እስኪያበቃ ከዚያች ከአትክልት ቦታ......ኩቱና የውስኪው ጠርሙስ ማንም ሳይነካቸው በፀሐይና በውርጭ ሲሰቃዩ ከረሙ። ማን እቤት ውስጥ እንዳስገባቸው ትዝ አይለኝም። ዛሬ ኩቱን ሳየው......ጠቅላላ ያልመረጥኩት እጣዬ እዚያ ውስጥ በጭንቀት ተጠቅሎ ሲያቃስትና የማያቆም ሞቱን ሲሞት ይታየኛል......በኩቱ እጀታ...... በኩቱ ክሳድ......ጠረኑ ቀርቶ እንደሆን ወደ አፍንጫዬ ወስጄ አፈልገዋለሁ። የለም። የሚያጋጥመኝ ጠረን......የደረቀ ሣር፣ መሽተት የጀመረ ጨርቅ፣ ከቁም ሳጥኑ የሚወጣው የብልና የአሮጌ እንጨት ጠረኖች......አልፎ አልፎ የኔ ሽቶና ላብ ጠረን---የዚያን እለት ማታ ያሳበው ቂጤ፣ ጀርባና ወገቤ የተዉት የሽቶ ጠረን......ይሁን አይሁን አላውቅም።

ዛሬ እዚህ ሳሉን ተቀምጬ......ወደ ውጭ ስመለከት......የእኔ ሕይወት አጠወላለጉ እስኪያስደነግጠኝ፣ እስኪያሳብደኝ ድረስ ተዘበራርቆና ወድቆ ሳለ እዚህች አጥሬ ዙሪያ የተንጣላጠለው የሐረግ አትክልት ሐመልማሉ ግን አግረም አላግረም ሳያቋርጥ መድመቁ፣ መተንፈሱ ይገርመኛል......

(የማንጎ ንግርት)

የምንተስኖት አባት እሱ ከመሞቱ በፊት ቤታችን ይመጡ ነበር። ዛሬም አንዳንዴ ብቻዬን እንዳልሆንኩ ሊያስታውሱኝ (እግዜር ይባርካቸውና) ብቅ ይላሉ። ሲጀመር እሱ ከእኔ የተሻለ ገንዘብ ስለነበረው አባቱ (እናቱ ሌላ አግብተው ከተለያዩ ከርመዋል) ጥቅም አሽትቼ የመጣሁ መስሎአቸው ነበር። ራቅ ራቅ ያደርጉኝ ነበር። ጨዋታ ካበረታሁባቸው እንደ ልጃቸው የምጣበሳቸው እየመሰላቸው መሰለኝ በረቀቀ ጥበብ ይሸሹኛል። ብዙ ጊዜ ስለ 'እኩያ' ያወራሉ (የገንዘብ ማለታቸው)። እኔን እንደተጠራጠሩ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ (እንዲገባኝም አድርገው) ልጅ መውለድ እንዳለብን ይሰብኩን ነበር። ግፊታቸው እንዲሰማና ሐሳባቸውን በሁልቀንአዊነት ሊጠምዱት ከሐረርጌ እስኮ የማንጎ ችግኞች አምጥተው ከቤታችን ጀርባ ያለች ተጠቅመንባት የማናወቅ ባዶ መሬት ላይ ተከሉዋቸው።

እንዲህ አሉን ያን ዕለት:

«የበሰለ የማንጎ ፍሬ ሳይ ሆድዋ አድጎ ቆዳዋ በመወጠሩ የሚያብለጨልጭ ሴትና ከእስዋ የሚወለድ ወንድ ልጅ ይታወሰኛል:: ለውነቴን ነው:: አብራችሁ ቆያችሁ ብዙ:: ሰው ጋብቻችሁ የቀልድ ይመስለዋል:: የጋብቻ አላማው የመውለድ ነው:: ሌላውማ ከውጭ አልቆ (ሳቅ ሳቅ) ማረጋገጫ ስጡን እንጂ:: ወንድም ለወንድነቱ:: ሴትም ለሴትነትዋ:: ይኼ ማንጎ ሲያብብ ልጅ ማየት እለብን:: ለውነት»

አንድ ሶስት ወር ከርሞ ምንተስኖት አረፈ:: ከዚያ በኋላ የዕውነት ሊያዩኝ አልፈለጉም:: 'ቤቱን ስጭኝ' ብለው አልተከራከሩኝም:: ጠፉ:: ኮስተር ባለ መልክ ብቻዬን እንደምኖር፣ ከወንድና ከሰው እንደ ተገለልኩ ሲያውቁና በወሬ አቀባባይ ሲነገራቸው ሊጠይቁኝ ይመጡ ጀመር:: እኔን ሰላም ብለው ትንሽ ያዋሩና ወደ ጀርባ ሔደው ማንጎ የተከሉበትን ቦታ ያያሉ:: ቆመው ሳያቋርጡ እሱን ያያሉ (ቢያንስ ለእኔ ሲመስለኝ):: ሲደጋገምብኝ ጊዜ ጠየቅኋቸው::

«ያቺን ቦታ አየሻት ማንጎ የተከልኩባት ቦታ ነበረች:: ትዝ ይልሻል? አዎ:: ስተክል በሆዴ ትንቢት እንዲበጅልኝ ትንሽ ራዕይ እንዳይ እግዜርን ለምኜው ነበር»

«ምን?»

«ልጅ የምትወልዱ ዓይነት ከሆናችሁ እንዲያብብ:: ካልሆናችሁ እንዲደርቅ:: ሚስጢሬ ነበር:: አየሽ አንድ ልጅ ነበረኝ:: አንድ ብቻ:: እሱም ዘር የለውም:: አንቺን ለመወንጀል አይደለም:: የታቀደ ነው አየሽ:: የማንም ጥፋት አይደለም:: አውቀን ከፉ አንሰራም:: ይቺ ማንጎ ለሁሉም የምትሆን ንግርት ነበረች:: ዘሪም ዘርም አይኖርም ማለትዋ ነበር:: አልበዛም ግን? እግዜር አላበዛውም ግን? እኔንም ልጄንም የዘነጋን ይመስለኛል»

የዚህ አትክልት ቦታ በየወቅቱ መለዋወጥ ያስቀናል:: እንዲህ ሁኚልኝ ነበር ያለኝ እኩ:: እንዲህ አብቢ፣ እንዲህ አፍሪ ነበር ያለኝ:: ተፈጥሮ ነበር ሁኚ ያለኝ:: እሱን በአጭር ሃግቢ፣ እኔን ግን ብልህ አደረኩ:: በአጭር አሰብኩ:: ድንክ አሰብኩና ድንክ ሆንኩ:: ያን እለት ማታ 'እሺ' ብለው ኖሮ፣ በሠላም እናድር ነበር፣ በሰላም ብናድር ኖሮ በሠላም ጠዋቱን አብረን እናረፍድ ነበር......ታክሲ የለ አምቡላንስ የለ:: አሁን እዚህ ተቀምጬ እንዳሻቸው በሚሆኑ አበቦች እቀናለሁ...... በለውጥ በሚንቦገቦጉ:: እኔ ግን በበቀል ለምለም ማሕፀኔን እያጠወለግሁ ......እግዜር ያበጀለት መረቁን በቁጭትና በተስፋ መቁረጥ በየቦታው እያዝረበረብኩ::



@BOOKALEM

(ቅዠቱ)

ብዙ ጊዜ በመስኮት ወደ ውጭ እያየሁ እተቀመጥኩበት እንቅልፍ ይወስደኛል:: እቃኘለሁ:: ሚቹ ባሴን እቃኘለሁ:: ከአትክልቱ ቦታ በልጅነት መልኩ እየመጣ መስኮቱ ዘንድ ሲደርስ አንገቱን ሰብሮ ይቆማል:: እንዳዘነ:: እንዳዘነና *'ይኸው ታዲያ ምን ጠቀመሽ?'* ዐይነት እያየኝ:: ቅዥቴ ነው:: ተራራ ሲፈነዳ፣ አውሬ ሲያባርረኝ፣ በጨለማ ስሮጥ፣ እባብ እግሬ ዙሪያ ሲጠቀለል አላይም:: የማየው ይኸቺን ብቻ ነው:: ከሰኞ እስከ እሁድ ከመስከረም እስከ ጳጉሜ:: የቅዥቱ ድባብ ግን ከባድ ነው:: በቢላ የሚቆረጥ ዐይነት ወፍራም ግራጫ ደጀን ነው:: ከዚያ ቅዥቱ መጠናቀቅ ሲጀምር ከባድ የጂኒ ወከር ውስኪ ጠረን ይሸተኛል:: እባንናለሁ::

ገላዬ በጊዜ ብዛት እየወፈረ......የመነከስ ጭኔ ብቻውን እያደገ፣ የወር አበባዬ እየመጣ ሲጠፋ፣ ጡቴ እየወደቀ፣ የሆዴ ቦርጭ እየገፋ ሽንጤ እየጠረ ሲሔድ አያለሁ:: መታጠቢያ ቤት መስታወት ፊት ለፊት ቆሜ የብቸኝነት አወዳደቄን ሳይ፣ ወተት ሳይወርደኝ፣ የዕንግዴ ልጅ ሳይጠረገኝ፣ ማሕፀኔ ሳይቆስል፣ ለአንድ ለምወደው ሰው ይኼን ሁሉ የማየውን ሥጋና ደም ስር ሳልሰጠው መቅረቴ አንጀቴን ይበላኝና ከቆምኩበት ወድቄ መሬት በጥፊ እየመታሁ አለቅሳለሁ:: በጥፊ እየመታሁ:: ይኼ ሁሉ ስቃዬ ግን ከእግዜርና ከሰይጣን በተቀር ማንም ሳያውቀው ባዶ ቤት ውስጥ ይቀራል እየመሰለኝ......

(ታዛቢ)

የውጭ ሰው እንደተጉዳሁ ከመገመት ሌላ ይኼ በምን ዓይነት ዝርዝር መልኩ እንደሚሰማኝ አይረዳም:: አንዳንድ ሰዎች ደ'ቀ በድብቅ ማንም ሳያይ ከሌላ ወንድ ጋር የምወጣ ይመስላቸዋል:: (በጀርባዬ ተሸሽጎ 'አያስኛትም እንዴ?' የሚል አይጠፋም) የውጭ ባዕድ ሰው በሚመች ቤት የምኖር፣ የሚመች ሥራ ያለኝ፣ የሚመች ደሞዝ የማገኝ በጥጋቤና በኩራቴ ብቻ ተገልዬ የምኖር አይነት ያደርገኛል::

የውጭ ሰው ዐሐይ ውስጥ ከሚያየው ቅርፊቴ ሌላ የተለየ ነገር እንደሚሰማኝ አያውቅም:: ልጤን ያደንቃል:: ቅርፊቴን ያምናል:: ልባሴን ያደንቃል: ጥሩ መልበሴን፣ መሐከለኛ እድሜ በመግባቴ ያማረ የመሰለ ገላዬን፣ ኩስታራ ሠራተኛነቴንና ቁጡ ወንዳ ወንድነቴን ያደንቃል::

ይኼ ቅርፊቴ ነው::

ይኼን አምኖ እንጂ ተጠራጠሮ......ለመስበር የሞከረ የለም:: ያገለኛል:: አገለዋለሁ:: ራቅ..........................ራቅ ........................................::



@BOOKALEM

የእኔ መደሰት የሚለካው የማሕፀኔን ጥልቀት በማስለካት ብቻ ነውን? ስህተት:: እንኳን ከሌላ ልግባባ ከራሴም መግባባት የከበደኝ ሴትዮ ነኝ......የምፈልገውን እያፈረስኩ፣ የቋመጥኩለትን እየሠበርኩ......ከልጅነቴ ጀምሮ በፍቅር፣ ከዕለታት አንድ ቀን......አድናቆት የተከናነበው ሰውነቴ ወደ ሥጋ ክምር ሊለወጥ......የምንተፍረት ፀጉሬ እንኳን ራሱ ማደግ ከብዶት ተሰባብሮ የሚወድቅ ከሰረት......እስታ እስኪመስል ድረስ......እንዲህ በቀስታ ሰልቶ......

..........ተቀምጬ ባዶ አየር ውስጥ ማፍጠጥ ደከመኝና ራቴን ተዘቃዛ እንጀራ በከክ ወጥ እናም ሻይ ጠጥቼ ለመተኛት ክፍሌ ገባሁ:: የእንግዳ ማረፊያ የምንላት:: የምትባል:: እሁድ እሁድ ጠዋት፣ ጥበቷና ሙቀቷ ውጡ ውጡ አያሰኝም ነበር:: ግድግዳዋ ለስላሳ ሰማያዊ፣ የባሪያው (የኮርኒሱ) ከርታስ ክሬም ቀለም ነው የተቀባው:: ከአምፖልዋ የሚወጣው ብርሐን የቀላ ቢጫ ነው:: በስተግራ ከአልጋው ግርጌ የደረቅ ሣር ቀለም ያለው ባለሁለት ተካፋች ትልቅ ቁምሳጥን ቆሞአል:: አልጋው አልተነጠፈም:: ትናንት እንደተኛሁበት ነው:: አልጋው አጠገብ ያለችው ትንሽ ቁምሳጥን ላይ ቀን ከሥራ ጊደኞቼ ጋር ገበያ ሔጄ ልብስ ሲገዙ እኔም በአይቅርብኝ......ደስተኛ ለመምሰል...... የገዛሁት የውስጥ ልብስ በጋዜጣ ቁራጭ ተጠቅሎ ተቀምጦአል:: በተራ ጉጉት ጋዜጣውን ተረተርኩና ጨርቁን አውጥቼ አልጋ ላይ ዘረጋሁት:: ከቅላቴ ጋር ስለሚሔድ ጥቁር ልብስ ከድሮም እወዳለሁ:: ውስጥ ልብሴ፣ የምለብሰው ቀሚስ፣ የምበላው እንጀራ፣ የምጠጣው ጠላ፣ ባሌ እራሱ ጥቁር መጋል ነበር.....ጠንካራ ፀሐይ የመታው ዕለት 'ባሪያ' የሚያሰኘው ዐይነት:: የውስጥ ልብሱ ከለስላሳ ቁስ የተሰራ ነው:: ሐር ሳይሆን አይቀርም:: ከምን እንደሆነ ግን አልተለጠፈበትም:: በእጁ ስይዘው ሳያቋርጥ ያዳልጣል:: ያመልጠኛል:: እንዳላበው የወንድ ልጅ ሰውነት.....እንዳላበው ባሌ:: ውድ እንኳን አልነበረም ጨርቁ::

ልስላሴው ጣፍጦኝ አቀፍኩት......እንደቆምኩ በጉንጬ እየዳበስኩ ልስላሴውን በጉንጬ እየታከክሁ:: ገላዬ ከላይ እስከታች ከአንገቴ ውስጥ በሚነሳ ሙቀት የተቃጠለ መሰለኝ:: አብራኬ ሲሚሚ ይሰማኛል:: ምን እየሆንኩ እንደሆነ አውቃለሁ:: መብራቱን አጠፋሁና አልጋዬ ትራስ ላይ · ግድግዳውን በጀርባዬ ተደግፌ ተቀመጥኩ:: ጨለማው ዙሪያዬን መፍሰስ፣ መንቃንቅ ሲጀምር.......ከየት እንደመጣ የማላውቀው ቁጣ እያስገመገመ ሁለመናዬን ወረረኝ:: ውስጥ ልብሱን አሽቀንጥሬ ጣልኩት:: የት እንደወደቀ አልታየኝም:: የቀን ልብሴን ሳላወልቅ እንዳለ ብርድልብሱ ሥር ገባሁ:: ዕንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም:: ገላዬ እያተኩሰ፣ ወንጀለኛነትና ለሚያልፍ የአናን ፍስሐ ለማደር መንፈሴ በመቁነጥነጥዋ ብስጭት እየተሰማኝ.....ተስፋ



@BOOKALEM

መቁረጥም በቀዝቃዛ ብረታም እጆቹ እንደ እርጥብ ዉርቅ እየጠመዘዘኝ......

መብራት አበራሁና አልጋዬ ዳር ተቀመጥኩ:: ድሮ የማውቀው የፍትወት ጠረን እንደ ባሕር ማዕበል ሰርኔን መታኝ:: ሁለት የእንግ ዘለላዎች ጉንጮቼን ሰንጥቀው ወረዱ:: ተፈናፍኜ ጠረኳቸው:: ውስጥ ልብሱ ቁምሳጥን ሥር ወድቆአል:: እሱ ላይ አፍጥጬ ብዙ ቆየሁ::

(ልዋጭ?)

በሌላ ወንድ? ሌላ ወንድ? ወንድ? ወንድ ከምንተስኖት ሌላ አልነበረም፣ ሊሆን አይችልም:: ገላዬ አይቃጣም:: ገላዬ ፈልጌ አያውቅም:: ዓለም ከአንድ ወንድና ከስድስት ቢሊዮን ሴቶች የተሰራች ይመስለኛል:: የወዳጆቼ ንዝንዝ አማሮኝ እስኪ ይሁን ብዬ መንደፋደፌ ግን አልቀረም......ቢከርምም:: ቅዕበታዊ መንደፋደፎች ነበሩ:: ኢሉሂ አምላከስ አንድ አይደለህ:: መለወጥ አልቻልኩም:: ኢሉሂ የቀሩት ወንዶች---ያውም ለወንድ ተጨንቄ ላላውቅም---ከበግይ በታችና ከምድር በላይ ጥቁር ጠይም አንድ ሰው ነበር:: የቀሩት እንደዚህ የመርካት ጩርቅ ናቸው:: ከተመሳሳይ ዕቃ ተሠርተው የወጡ......መጠናቸው ይለያይ እንጂ ውስጣቸው......

ይልቁን የሆነውን ነገር ሁሉ እንደ ጥፋቴ ቆጥሬ ይሔን የአሁኑን ሕይወቴን እንደ ቅጣት ወሰድኩት:: አጋጣሚ፣ ጊዜና እኔ ተስማምተን የተቀበልነው::

(አፈሰች)

ምንተስኖት ከሞተ ከሶስት ዓመት በኋላ አንድ ድሮ የማውቀው ግን ትንሽ ከባሌ ቁም ነገር የሚያንሰው (እንዲያጫዋውተኝ) ገብሩ የተባለ መልከ መልካም ሰውዬ ወዳጅ አደረግሁ:: በሙሉ ካንጀቴ አይደለም:: ለመሆኑ የምትወዱት በእናንተ ጥፋት ቢበደል የምትደሰቱ ማን ናችሁ? ያ መከፋትና የወንጀለኛነት ስሜት ውስጤ እንዲህ አንጀቴ ውስጥ መሟሟት እንዳልሻተ ቀዝቃዛ ሊጥ ቁጭ ብሎአል......

ገብሩ የሚሰራው ኢሲኤ[20] ነው:: ንፁሕ ለብሶ ንፁሕ የሚነዳ የጉደር ወይን መጠጣት የሚወድና 'ሰንበሌት' አጢያኝ......ያውም ዊንስተን::

ቅዳሜ ቅዳሜ ስራ ስለማይኼድ እኔ ስራ ውዬ (ያን ጊዜ ቱሪዝም ኮሚሽን ነበር የምሰራው) በዚያው ገበያ ደርሼ ትንሽ የቤት አስቤዛ ለእሱም አንድ መልካም ሸሚዝ ገዝቼ መጣሁ:: ቤት ስገባ ከመኝታ ቤት ከሆነ ሰው ጋር እየጮኸ በስልክ ሲያወራ በተራ የወሬኛ ንትርክ ዝም ብሎ በየዋሕነት ስሰልለው እንዲህ ሲናገር ሰማሁት:

[20] የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን

«ማን? እኔ? ተይ በእናትሽ እስዋ አፈሰች በይ እንጂ:: ቤት አላት ቢባል ያረጀ እኮ ነው:: ያውም ባልዋን ገላ ያገኘችው:: ምን ይጎለኛል:: ምን? ጉረኛ? ዕውነት ነው እንጂ:: የተማርኩ እንደገና ኢንተርናሽናል ኦርጋናይዜሽን የምሰራ:: መልኬ ያንሳታል? መኪናዋን ደ'ሞ አትነዳውም:: ይገርምሻል ስለ መኪናዋ አውርታ አታውቅም:: አሁን ግቢው ውስጥ ስዞር ነው ያየሁት እኮ:: ታዲያስ የቤት ቁልፍ ሁሉ በእጄ:: በቃ ቤቴ በይው......»

ታዲያ ወሬውን አቋረጥኩትና ዐይኖቹ ተበልጥጠው እያየኝ እንዲህ አልኩት:

«ገብሩ! ሰማህ? ፖሊስ ሳልጠራ ከቤት ውጣልኝ:: ሳትዋረድ ውጣልኝ......» አልኩት::

ዓይኖቹ እንደተበለቃቀጡ አፉ ወደ ታች ተከፈተ::

'በእሱ አፍህ አፈር እፈስ'

(ትንሳኤ ዘሙታን)

ኢዩኤል የተባለ ብሔራዊ ቲያትር የሚሰራ ሰው ተዋወቅሁ:: ጓደኛዬ አስተዋውቃኝ:: አብራኝ የምትሰራው ያቺ ሳራ:: ኢዩኤል ትንሽ ጉራ አለበት:: አራት ቲያትር አዘጋጅቼአለሁ ይለኛል:: እሱ አያገባኝም ግን የውሽቴን አደንቅለታለሁ:: ደስ የሚል ሰው ቢሆንም ቤቴ ላመጣው አልፈለኩም:: የገብሩ ነገር ትምህርት ሆኖኝ:: ኢዩኤል እንደውም ውጭ ውጭ ይወዳል:: ያደከመኝ ይኼ ነው:: በትዳር ቆይቶ፣ ባልሰመረ የፍቅር ጎዳና ላይ ሰከም ሰከም ካሉ የለመዱትን መረጋጋት በቀላሉ መርሳት ይከብዳል:: ለጥቂት ጊዜ አከነፈነፈኝ......ጥቂት ሰድነት ገባኝ......ከምንተስኖት ወዲህ የወንድ ፍርሐት አለብኝ:: ይሞቱብኛል ሳይሆን የለመድኩትን እንዳላጣ:: ለምዶ ማጣት:: ወዶ ማጣት:: ትንሽ ከእሱ ጋር የቆየሁት ለዚህ ይሆናል:: ይዳብሰኛል:: ከጣቶቹ ጫፍ ታዲያ የምንተስኖት ትዝታ ይፈሳል:: እፈራለሁ:: ዐይኖቼን ጨፍኜ መዳፉ ጭኖቼ መሃል ሲገባ ማልቀስ እፈልጋለሁ:: ከዚህ ከኢዩኤል ጋር ስገናኝ ዓላማዬ ለማምለጥ እንጂ ተመልሼ በከፊል ምንተስኖት፣ በከፊል ግን እንደ ወሲብ ዕቃ ወደሚቆጥረኝ ሰው ለመምጣት አልነበረም:: ጠፋሁበት:: ቢፈልግ ቢያስፈልግ ጠፋሁ:: ጠዋት ጠዋት እዚህ ብሔራዊ ቲያትር ለሥራ ሲገባና ሲወጣ አየዋለሁ:: ድርጊቴ ያሳዝነኛል:: እሱም ያሳዝነኛል:: ግን ምን ላድርግ?

(አመልካች ጣት)

ምንተስኖትን የማውቀው በቀለ ወያ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ስንማር ነው:: አስተማሪ እስኪመጣ ድረስ እተቀመጠበት እየዘፈነ



@BOOKALEM

መደነስ ስራው ነበር። አስተማሪ ሲመጣ ቀጥ። ቆይተን ቆይተን ወዳጅ ሆነን የልብ ስናወራ፡

«ለምን ወደድከኝ?» ስለው

«በምላስሽና በአመልካች ጣትሽ» አለኝ።

«እንዴት?» አልኩት።

«በቀለ ወያ ስንማር አመልካች ጣትሽን በምላስሽ እየነካሽ መፅሐፍ ስትገልጪ አየሁሽና አንጀቴን በላሽው»

«እንዴት?»

«እንደዚያ ዓይነት ንጹሕ ምላስ፣ እንደዚያም በጉጉት አምሮ የተከፈተ አፍ፣ እንደዚያም ቀጭን ጣት አላየሁም። በነዚያ ምላሶች ክፉ ንግግርና ቅጥፈት፣ ከዚያም አፍ ያልተባረከ ነገር እንደማይወጣና እንደማይገባ፣ ያም አመልካች ጣት ወዳልተረዳው እንደማይጠቁም እርግጠኛ ነበርኩ»

«ታዲያ ለምን ቆየህ?»

«በሶስት ምክንያቶች። አንድ በቂልነት። ሁለት የበለጠ ፍለጋ። ሶስት ስለፍቅር ምንም ስለማላውቅ»

«የምትወደኝ አትመስለኝም ነበር»

«ዮዲት ቀሽም። አንቺ ቀሽም። የምዘፍነው ለአንቺ ነበር»

(ግራ ቅናት)

በረንዳ ላይ እንላፋለን። ክረምት ነው። አልረሳም። አንጎሌ ሁሉ ምንተስኖት ነው። መውጫ መግቢያው ምንተስኖት ነው። ቁመቱ ከእኔ ያንሳል። ከእኔ ግን ይሰፋል። ደረቱ ሠፊ ክንዶቹ ኩቢ ሜትር ይመስሉ ነበር። ግድግዳ አስጠግቶ የውሽቴን እየተንፈራፈርኩ ድቡልቡል እጁ ወገቤን ጨምዶኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ስል ሊስመኝ አፉ እየተንሳፈፈ ሲመጣ ከለበኑ ውስጥ በአፉ ምራቅ የረጠቡ ሽፍ ያሉ ጥቁር ነጠብጣቦች አየሁ።

ቀስ እያለ ስለሚጠጋኝ በፍጥነት ቆጠርኳቸው። ስድስት። ስድስት ማሪያም የሳመቻቸው ነጠብጣቦች። ከንፈሮቼን እሱ ነክሶ እኔ ግን በሕሊናዬ 'ምን ቢቆርጣት ነው ማርያም ፍቅረኛዬን የነካችብኝ' አልኩ። ደሞም ኮርቻለሁ። እንደ እኔ ፍቅረኛቸውን ከማርያም የሚጋሩ እነማን ናቸው?

(ዐይነ ሌባ)

ይኼኛው ደግሞ መንግስቱ የሚባል። ከንፈረ ከባድ ዐይነ-ትላልቅ ፀጉሩን በቀን አሥር ጊዜ የሚያበጥር። እጄን ይዞ እያዋራ አረፍ እያለ ከመሃል ሌላ ሴት ይቀላውጣል። ትኩር ብሎ እያወራኝ ድንገት ሴት



@BOOKALEM

በአጠገባችን ከአለፉች እጆቼን ማሻሸት ያቆምና (ሳይለቃቸው) ዓይኖቹን በስየታ፣ በጥናትና በጉምዝግታ ሴቶቹ ተከለ--ገላ ላይ ይወረውራል:: ከላይ እስከታች በትኩረቱ ይዳብሳቸዋል:: ግን እንዲህ የለማፈርና ያለ ይሉኝታ እያፈጠጠ 'አላፈጠጥኩም' ለማለት ነው መሰለኝ እጆቼን በለዘብታ 'እዚህ አለሁኝ' በሚመስል ሁኔታ ይነካካቸዋል:: መዳበስ ይጀምርና ያቆማል፣ ያቆምና ይጀምራል:: ካደረገ በኋላ ቅርም አይለው:: ወደ እኔ ዞር ይልና ወሬውን ይቀጥላል- ......የቀረ ወሬ ካለው:: ወሬ የማያልቅበት:: አለበለዚያ ቁጭ ብሎ እንደ ሎሚ ያሸኛል:: ራስ ግሪል አንድ ጊዜ ራት ጋብዞኝ እንደተቀመጥን አንዲት በእርግጥ ሎጋ ቆንጆ ዓሣ የመሰለች ጠይም ኮሜርስ አብረን እንማር የነበረች ሰላምታ ሰጥታኝ ከእኔ አንድ ጠረጴዛ ርቃ ስትቀመጥ ሦስት ወር ሙሉ ያላየሁበትን መቁነጥነጥ አየሁ:: ዐይኖቹ ከእስዋ ላይ አልነሳ አሉ:: ልጅትዋ ይኼን ተረድታ ነው መሰለኝ ወይ 'ና' አትለው ነገር ወይ አትገላምጠው ነገር ብቻ በዐይንዋ እንጠልጥላ ይዛ ከእኔ አራቀችው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከተቀመጥችበት ተነስታ በዓይኖችዋ ገርምማው ቦርሳዋን አንግባ ወደ መጸዳጃ ቤት አቅጣጫ ሔደች:: እሱም ደደብ ያልገባኝ አደረገኝ መሰለኝ እስዋ ከዐይን እንደተሰወረች 'ይቅርታ' ብሎ ከጎኔ ተነሳና ወደሄደችበት ተከተላት:: እሱ ከዐይን እንደተሰወረ ቦርሳዬን ይዤ ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና ሁለቱም ወደሄዱበት ሄድኩ:: መተላለፊያ ላይ ቆመው ሲያወሩ ደረስኩ:: ሳያዩኝ ተመለስኩና የራሴን ሒሳብ ከፍዬ እሱንም ሳልነግረው ወደ ቤቴ ተመለስኩ:: እኩለ ሌሊት ላይ ተደወለ:: እሱ እንደሆነ አውቄአለሁ::

አነሳሁና ‹ሃሎ› ስል......

«ምነው አንቺ ምነው አዋረድሽኝ? ምነው ምን አደረኩሽ?»

«ከዚያች ልጅ ጋር ወጣችሁ?» አልኩት::

«አ አ አ ምን?»

ስልኩን ዘጋሁ:: ከዚያ በኋላ አልደወለም:: አንዳንዴ ሳይጠግበኝ ስለሄደ ይቆጨዋል መሰለኝ ከመስሪያ ቤት ስወጣ እንቅፋት እየሆነኝ ለማባበል ሞክሮ ነበር:: እኔ ለእሱ ትንሽ የሥጋ ቁራጭ ነበርኩ:: ሁለመናዬን በሙሉ አለማወቁ ይቆጨዋል:: ራቁቴን ቆሜ አይቶኝ አያውቅም:: ፍላጎቱን ሲናዘዝልኝ ነበር:: ምንተስኖት በፍቅር ጠቅልሎ ያየውን ነገር እነሱ ያለፍቅር ሊወስዱት ይሞክራሉ:: የሆኑ ይመስላቸዋል እንጂ ማንም አይደሉም:: ከእኔ የማሩ ሴቶች እንደ ከብት ሊያንጋጉ ይችላሉ:: ሁለመናዬን ለማየት ምንተስኖትን መሆን አለባቸው:: አይገባቸውም:: የክብር ትርጉም አይገባቸውም:: አፌን ሙሉ በሙሉ ሲስሙኝ እንዴት ነው የሚዘገንነኝ:: ምንተስኖት ሲጠፋብኝ የጠፋብኝ ከእንጦጦ ነፋስ ስልክ ከአየር ጤና ከተቤ



@BOOKALEM

የተዘረጋው የአዲስአባ ሽርሙጥና አይደለም:: የጠፋብኝ ፍቅር ነው:: መሳደቤም አይደለም፣ ራሴን መካቤም አልነበረም::

(ልጅነቴን ሳላይ)

'ልጅነታችንን እንይ' እለዋለሁ:: ልጅነቴ ልዩ እንደሆነ ሁሉ:: ልጅነቴ ከሚቹ ምንተስኖት ምን ይለያል? እኩዮቻችንን በሞት አጥተን:: እኩዮቻችንን በሽር ተነጥቀን:: በጠለፋና በምቀኝነት ተነጥቀን:: በወባና በኮሌራ ተነጥቀን:: የእኔ ልጅነት የተለየ እንደሆነ 'እሱን ልየው' አልኩት::

`ውለጂና እርጅና ይውረረኝ` ይለኛል:: ይለምነኛል:: እግሮቼ መሃል ተደፍቶ አብራኬን እንደ ውሻ እያሸተተ ይለምነኛል:: ራሴ አዋቂ የሆንኩ መሰለኝ:: ይመስላል:: ሲመች ሲመች ሰው አዋቂ የሆነ ይመስለዋል:: ሁላችን ታይታኒክ ነን:: ያቺ ጀልባ:: ባሕር ላይ ሳይሆን ቂልነት ላይ እንደቆመች ያልገባት:: ብረታ ብረቶች ቀናቸው ያልሆነ ዕለት ከደንከል ይደከማሉ:: ይኼን ከሰላ ሄዳችሁ ወይጦ ጠይቁ::

እያደረ ሲሄድ እኩያ አጣ::

'እወድሻለሁ' ይለኝ ነበር በአፉ ወርቅ ሞልቶ::

በተከረከመ ጥቁር ዕብነ በረድ ገላው፣ ከእፍረቴ ጎፈሬ ወዲያ አልማዝ ልቅበርልሽ ብሎኝ ነበር፣

`ልጅነቴ` አልኩት::

(ከቴም የእኛ ልጅነት/በስንት ዓይነት ሽብር የተዳመጠ)

ጊዜ፣ ጊዜ ግን ልኬን ነገረኝ:: ማንም አላደረገው እንደሱ ሲነጋ በጠዋት ገና ጎሕ ሲሽት በእንቅልፋም አፉ በደንብ ባልተከፈተ ከምንም ከምንም እወድሻለሁ ያለኝን፣ ከከረሜላና ከቸኮላት እወድሻለሁ፣ ከይርጋጨፌ ቡና፣ ከቴፒ ማር ከጎጃም ነጭ ጤፍ እወድሻለሁ......የማይለው አልነበረም ከራሱም ከመሥዋቱ ግርማም[21]

[21] 'መሥዋቱ ግርማ' በጎጃም ክፍለ ሃገር የሽፍታ አዛውንት እጅ የተገኘ አንድ የጥንት ብራና መፅሐፍ ውስጥ ተፅፎ የነበረ የፍቅር ውዳሴ ግጥም እንባቢ ነው:: ግጥሙን የደረሰው ስለ ማይታወቅ በእንባቢው የሬድዮ ተዋናይ በመሥዋቱ ግርማ ስም ይጠራል:: አንዳንድ አዋቂዎች ይሄ ውዳሴ ከክርስቶስ ልደት በፊት የተፃፈ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ይሰጣሉ:: ከፊል ግጥሙ እንዲህ ይላል:

«እዝሀ አገሬ ነጋ
ከዓምት እስከ ቡሌጋ
ከአዱል እስከ ኖባ
ከእንፍራንዝ እስከ ባሊ
ከዓምር እስከ ጎሮ
ከመተማ እስከ ሲያማ
ከባሕር ባሕር
ይኼው ፍቅሬ ባንነ:

ሙዳሴ ግጥም በቀስታ ያነብልኛል......ይዘፍንልኛል......እንገቴ ላይ ያገኘውን ቆዳ ነክሶ በእደረ ምራቅ እያራሰ ይገጥምልኛል፡ እሷን ብከዳ እገኝ ምቼ/ ደሟ ረግምኝ በንቀት/ እንዲህ የጠጣሁት በጥቼ......

* * *

ከጥቂት አመታት በኋላ ገላዬ ይነጥፋል:: ገላዬ ይወድቃል:: ......ጊዜ ረብሾትና ገዝቶት ቅጥልጣው ይደርቃል፣ አበባው ሲትነቴ ይጠፋል:: ያን ጊዜ የጠቅላላ አደጋውን አስቀያሚ ፊት አያለሁ:: የጠቅላላው አደጋው ነበልባል ተጉልጉሎ ይወጣል:: ቁጭቱ እንደ ገሞራ እርግማን እየተንበለበለ......እንደገና ሊያቃጥለኝ:: ይኼ ሁሉ እንደ ቁና ላይ አተር ወንድ......የተማሰለ......የማልመርጥለት......ዘሩን መጣያ አጥቶ በእብራኩ ተሸክሞ ሲዞር......ለመዝናናት......ለመደሰት......ለመደነቅ ለመወደድ ......ወንድነቱን ለማስመስከር ባጋጠመው ሲጥል......

ሰዐቴን አየሁ::

ከምሽቱ 5 ሰዐት::

ከምሽቱ ... አውልቄ አዲስ የገዛሁትን ውስጥ ልብስና ሌላ አዲስ ልብሴን አውልቄ ...ደርቤ፣ ጫማዬን ለውጬ፣ ፀጉሬን አስተካክዬ እጠር ያለ ቀሚስ ደርቤ፣ ... ወጣሁ:: (ይለኝ ነበር ምንተስኖት `ስፒል ጫማ ላይ በፍጥነት ከቤቴ ወጣሁ:: ... ይይዛል......አለ አይደለ እግሮችሽ......አለ ስትቆሚ ዓለም ትንቀጠቀጣለች ......

ከዚህች ጊጋት
ከዚህች እምነቴ በሌሊቴ ነጠላቻንንን ብቻ ደርበን
እሳሬ ሬብን ከምንምጣት
ከእናቴ ጥሬ...... መንገድ ጠፍቶብኝ የቀረሁ ዕለት፣
ከእባይ ገደል እንደ ገመድ ከጎበኝ
ከእሱም የበለጠ
ወይፈ በታነበ ጮሮው ከምጠጣው እርጎ
በፈጅነቱም መሰከረም ከፈተልኩት ቁጠማ
በእሱም የሰማን ሰፈርን፣ ምድርን በማንጻሪ ከነካዛብት ሰዓትና አፍታ
በዘባት ተነዛር ከሚቀፈፈረጥ መጣኝ
የላ ሆኚ ከእማሁት የእናቴ እሸራሩኝ
እስታርቶ እናቴን ላመለጣን ከማርከዛበት ጥር የበለጠ
በሌይ እየጋረደ ከስንዝሬን ከፈጠጋር ልጆች ቀመና
ከሚከርሸም ጨጨብባ
ከሚፈርጥ ቀጋ የምወድህ
በመተት ከዘበለ እጃ
ከፊት አደይ የበለጠ
እንደ ንፋስ የምትነፍስብህ
የምወድህ
ደህም ጠይሜ
እንደ እናቴ እንደ ሊናና
ሲትነቴ እሸቃበጠች............
(ያላለቀ)

አይደለ ባቶችሽ......እ......') ውጭው መብረድ ጀምሮአል:: መንገዱ ፀጥታ ነው:: ውሻ ከወዲያ በኩል በቀጣ ይጮሃል:: የመንገዱን ዳርገ ተከትዬ ቀስ እያልኩ መራመድ ጀመርኩ:: ፊት ለፊቴ ካለው የቢቴ ግንብ አጥር ስር ሚሖች ያበራሉ:: ቀላል ነፋስ ቀሚሴን በቀስታ እያነሳ ያጥፈዋል:: ሁለት መኪናዎች ቀጠሮ እንደደረሰበት ሰው ተቻኩለው አለፉኝ:: አቶቡስ ማቆሚያው ስደርስ እርምጃዬን ዝግ አድርጌ የተገኘው ወንድ እንዲመጣ፣ እንዲፈልገኝ የመንገድ መብራት ሥር እንደሚደንስ እያደረገኝ ቆምኩ:: በወዲያ በኩል አንድ ሰው ብቻውን እየተነጋገረ ይሔዳል:: እኔን አይቶኝ እንደተበሳጨ ሁሉ እጁን አወናጭፎ ጉዞውን ቀጠለ:: በልቤ «ና ጠይቀኝ......ያለ ችግር ውሰደኝ» አልኩ:: አልለመድኩም:: መንገድ ዳር ቆሚ ወንድም ዘርም ስለምን የመጀመሪያዬ ነው:: መለመንም አላውቅበትም:: ሩብ ሰዐት ጠበቅሁ:: የሠፈር ዘበኞች በአጠገቤ እያለፉ ከፍ ዝቅ አድርገው አዩኝ::

«ምን ያደርጋሉ በዚህ ሰዐት?» አለ አንዱ

«ሰው እየጠበቅሁ ነው» በልቤ ግን:

አንተም ና......ማናችሁም ኑ እላለሁ:: ወንድ እንደምጠብቅ ሊጠረጥሩኝ አይችሉም:: በሠፈሩ ውስጥ ጨዋ፣ ሠላማዊ፣ ያለፈላት ሴት ነኝ...... ባሌን ገድዬ የምዝናና::

«ሰዐት እላፊ እንዳይደርስብዎት» አለ ከዘበኞቹ አንደኛው

«እሺ»

እያወራን ሳለ መኪና አለፈን:: ነጂው ተገላምጦ አየኝ:: ዘበኞቹን በልቤ ረገምኩ:: አዲስአባ የአውሬዎች መኖሪያ የለም እንጂ......በዚህ ሰዐት ከዝንጀሮ ብደቅል ዕወዳለሁ:: ባልታወቀ፣ ባልተፈለገ፣ ባልተደነቀ ባልተፈቀረ የሰው ወንድ ልጅና በእንስሳነቱ ከእንስት ዘሩ የሚማስል የሴትነት ጠረኔ ጉትቶት በምወልድለት ወንዴ ዝንጀሮ መሐል ልዩነቱ ምንድነው? ፍቅር ከሌለ ምን የቀረ አለ?

ከመሐል በሐሳብ ባህር ገብቼ ስባንን......ዘበኞቹ ሲመለሱ አገኙኝ::

«እትዬ ሰዐት አልፎአል ይግቡ» አለ አንዱ::

«እንዲህ ስትዞሩ ነው የምታድሩት?» አልኩ በጨዋታ አድርጌ......

«ሥራ ነው:: ፀጥታ መጠበቅ አለበት:: ለመሆኑ የት ልሄዱ ነው?»

«አንድ ጓደኛዬ እመጣለሁ ብሎኝ እየጠበቅሁ፣ ብርዱን ትችሉታላችሁ?»

«ምን ይደረጋል:: እንጀራ እኮ ነው»

«የቀጠሩኝ ቀርተዋል......ዕንትልፍም አይወስደኝ ከአሁን በኋላ......ቤት ግቡና ሻይ ጠጡ»

«ሽሬ ጥሩ ነበረ እሱስ......የሚቆጣጠሩን አሉ፣ ካጡን ያስቀጣናል» አሉ በመገረም እየተያዩ::

«ለማንኛውም......እስከ ስምንት ዘጠኝ ሰዐት አልተኛም:: በፕሮሙስ ሰርቼ አስቀምጥላችኋለሁ» አልኩ::

«በጣም ደግ ነዎት......እንግዲህ ከተመቸን......እናንኳኳለን ካልተረበሹ»

«ግድ የለም:: አልተኛም»

በተስታ እየተራመድኩ ወደ ቤቴ ተመለስኩ:: ልብሴን አወላልቄ በውስጥ ልብስ የለመድኳት ሶፋ ላይ ተቀምጬ ወደምሽቱ፣ ወደ አጥሩ፣ ወደ ጉዳናው፣ ወደሚያስኮርፈው ሌሊት ማፍጠጥ ጀመርኩ:: ዓላማ ያላቸው ግን ቃታ መሳቢያ ባት ያጡ እነዚህ ዐይኖች:: ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዐት ሆነ:: ዘበኞች አልመጡም:: እንዴት ሁለቱንም ማስተናገድ እንዳለብኝ ሴራ እያወጣሁ ነበር:: አየር ላይ የቀረ ሴራ:: ተዳከምኩ:: ሰውነቴ ዛለ:: ሶፋዬ ላይ አንገቴን ሰብሬ ተኛሁ...... እንደበቃው......ሁለቱ እግሮቼን ሶፋው መሐል ያለው ጠረጴዛ ላይ ሰቅዬ......ውስጤን እየበረደኝ......ቅዠቴ መጣ......አሁን ምንተስኖት አይደለም:: አሁን ያ አታክልቱ ነው......ያ አረንጓዴ......ከዳር እዳር አጥሩ ዙሪያ ያለው እግር እንዳበቀለ ሁሉ......ወደ አንድ ትልቅ ለመልማል፣ ወደ አረንጓዴ ጃርት የመሰለ ኳስ ተለውጦ እየተንፏቀቀ ወጥቶ መስኮት ዳር ከውጭ ቆሞ......እንደ ሰው እያየኝ......ከላዩ ላይ ቅጠሎቹ እንደ ጥጥ እንደ ምናምን እየረገፉ......ትልልቅ ግንድና ጥራሮ ብቻ......ቤቱን በጉልበቱ ገዶ ሲገባ......መስታወቱ ያለ ድምፅ እንደ ሳውንደሪ ሳስቲክ እየተጣጠፈና ያያያዙት ብረቶች እንደ ቅቤ በንግ እየቀለጡ......የጠወለገው ሐረግም ጠረጴዛ ላይ እየተሳበ......በሰውነቴ ላይ በሚሷጥጡ ወፍራም እግሮቹ እየወጣብኝ......ከዚያ በእግሮቼ መሐል ሙቀት ፈልጎ፣ እንደ እባብ እየተነፈሰ ማሕፀኔ ውስጥ ሲገባ......ደረቅነቱ ሲገባ......ቦታ ጠቦት እንደልቃ ማጠቢያ ሽቦ ራሱን አጨማዶ ሲጠቀለል......የደረቀው ጂሮዬ እየተሳበ እየተጎተተ እየተያያዘ እየተሸመለለ እየተገመደ እየተጠመዘዘ ላያቋርጥ......ሳይደክም ውስጤ ተጠቅሎ ሲሰበሰብ......ተመቻችቶም ሊቀመጥ......

ክቅዥቴ እየተንቀጠቀጥኩ በላብ ተዘፍቄ ባነንኩ:: ጭኖቼ ልክ በእሾህ እንደተጠቀጠቀ ሁሉ እየጠዘጠዙኝ......ከውስጤ......የቀረችው በውነቴ ወጣትነት ተማምና የቆመች ተስፋ፣ ልቤ ላይ በታላቅ ድምፅ/ጩኸት ስትወድቅ እሰማታለሁ......ልክ 'ግርርር' ብላ ክንፍዋን እያማታች ዘለቃ መብረር እንዳቃታት ወፍ......በጉጉት ወደ



@BOOKALEM

ሚጠብቃት የዘመን አውሬ አፍ......በቀዝቃዛ ሳሎን ውስጥ፣ በቀዝቃዛ ሌሊት፣ ከቀዝቃዛ ሰውነቴ......ጣውላ ካረገዘ ሰውነቴ......ዕንባ መውጣት ጀመረ::

ማልቀስ ጀመርኩ......

— // —

1985 ሀገኗ



@BOOKALEM

# እግርና ዜጋ

ይኸቺ እንደአጋም የጠቆረች የስድስት ኪሎ ካምፓስ ምሽት በሚጣፍጥ ቀዝቃዛ አየሯ እሥራን ከመሣሣሚያው ኩሬ (kissing pool) ፊት ለፊት ከፍ ያለ ደረጃ መርጬ ተቀምጬአለሁ:: መኪና ሲያልፍ በጉማው እየረጨ ወደ አስፋልት ዳር የሚገፋው ደቃቅ አሸዋና ጠጠር የሱሪዬንና የውስጥ ሱሪዬን ውፍረት አልፎ ይጉራብጠኛል:: በግራ ትከሻዬ ጉርድ ከድንጋይ የተቀረፀ የአንበሳ ሐውልት ተደግፌአለሁ:: ሐውልቱ ይሞቃል:: ቀን የየካቲት ፀሐይ ነበር የዋለው፣ ሁላችንን እንደ ነጠላ ጥለት ሲቋጨን:: አልፎ አልፎ ከዕዶችና ከተለያዩ ዛፎች ላይ ነፋስ ነቅንቆ የጣላቸው ደረቅ ቅጠሎች በፀጥታና በልስላሴ ኩሬው ውሐ ላይ በሕቡዕ እንደተኩረኩሩ ደናግልት ሳቃቸውን አፍነው ይወድቃሉ:: ነፋስ እያፏሸከ ሲያልፍ......የብርሐን ፍንጥቅጣቂ የተወሸከበት የኩሬው ቡራቡሬ የፀበላ ጠለል እንደ ሐር ይርበደበዳል::

የግቢው ፀጥታ እንደግድግዳ ያገኣል......ቅርብ ሆኖ እሩቅ ነኝ ይላል:: ሩቅ ሆኖ አለሁ ይላል:: የጆሮዬ ላንፋ መሣተፍ አቁሞ እንደ ፕላስቲክ ቀልጦ ወደ ከበበው ሰርጓዳ ታጥፎ የደፈነኝ ይመስለኛል:: ግልኩ:: የእኔም የሆነ የእኔም ያልሆነ ሣል:: የጉሮሮዬን ድምፅና ትንፋሼን እንደ ሌላ ህልውና......ከእኔ ውጭ እንዳለ ዕቃ አዳምጣቸዋለሁ:: ዝምታው ሁሉን ነገር እየሰባበረው ነው::

ዛፎቹ ጥላ ሞትም ዛፍም ናቸው......ንፋስ መጥቶ እስከሚነቀንቃቸው...... ኩሬው የለም......ከመፅሐፍት ቤቱ ሕንፃ የሚመጣው ብርሐን በዛፎች ይጋረድና ይለቀቃል: ኩሬው አለ፣ የለም:: ጥላና ዕቃው አይለይም ......የትኛው ዕቃ የትኛው ጥላ እንደሆነ አይብራራም......ሁሉ እኩል ነው:: የትኛው ሀሳብ የትኛው ድርጊት



@BOOKALEM

እንደሆነ አይታወቅም:: ጠፍጣፋ ዓለም ነው:: ስርጓዳው፣ ጉብታው፣ ሜዳው......ሁሉ ሜዳ የሚመስልበት ......ወይም ኮረብታ::

ከቀኝ በኩል ሁለት ሰዎች መጡ......ከጥላቸው:: ሁለት ዐይነት ሳቅ...... መጀመሪያ የሴት፣ ቀጥሎ የወንድ:: አላዩኝም:: ከወዲያ መንገድ የሚመጣው ብርሐን ከወገባቸው በታች አግኝቶአቸዋል:: የእግራቸው ጥላ አጠገቤ ድረስ መጥቶአል:: የሚሰሩትን ማየት አልፈለግሁም:: ጥላ ሞትና ሹክሹክታ:: ሰውና ንግግር:: ሁሉ ነገር ያልዐዳ......ለማወቅ......ከጢሱ እሳቱን......ከጥርሱ ድዱን:: ከታች ወደ ላይ እግሮቻቸው በረድፍ ቆመዋል እንደዚህ......



እየለኩ የደረደሩአቸው ይመስላል:: አንዳንዴ ይነቃነቃሉ:: ጥላው አቅጥኖ ያረዝማቸዋል:: አንዳንዴ ዐይኖቼን ሲደክማቸው......እግሮቻቸው የስልክ እንጨቶች ጥላዎች መስለው ይታዩኛል:: ደ`ሞ ከዳመናዎች መሐል የቀይ ወይዘሪት ከንፈር የመሰለች ጨረቃ ወጥታ በአፍታ ደመና እየተስገበገበ ሲውጣት::

በመጀመሪያ ጥላ ሞት ነበረ......*(በእኔው ዘፍጥረት)*

ከላይኛው ከንፈሬ ለስላሳ ፍዝ ፀጉር መብቀል ጀምሮአል:: አገጬ ላይ ረዣዥም ሁለት የጢም ፀጉሮች አሉ......እግሮቼ ጭገር ጀምሮአቸዋል ......የብልቴን ደረት......ጥቁር ጥጥ እየወረረው ነው......ጥቁር...... እንደራሴ ፀጉር ጥቁር......እንደዚህ ጨለማ......እንደ ጥላ፣ እንደነዚህ ሰዎች ጥላ......

የሁለቱ ሰዎች ሹክሹክታ አቁሞአል:: እግሮቻቸው ተነባብረዋል:: እንደዚህ:



በሆዴ ብንበለበል የጫማቸውን ሶል ሥሩን አይ ይሆን? እሱም ጥላ ይሆናል......የሪጋ ጥላ......የመጠን ቁጥር ጥላ......የተረገጠ እበት ጥላ......የአፈር ጥላ......የሣር ጥላ......የጠጠር ጥላ:: የመንገዱ መብራት



@BOOKALEM

ድፍረት ዓይን ያማል:: ዙሪያዬን የለመድኩትና ያለመድኩት ተራከቦ:: ተፋሁ:: የምራቄ ኳስ መሬት ላይ ትም ስትል እሰማታለሁ:: የጥላ ኳስ ናት......በዚህ ጨለማ ጉልበቷ አይለካም......ከእኔ ራቅ ባለ ሰው የለፈንና የከንፈሮቼን አድካሚ ስፖርት ያልተገነዘበ......የከሰል ቁራጭ ያፈናጠርኩ ይመስለው ይሆናል:: የጆሮዬ ባንፋ ከተኛበት ተነስቶአል......መትፋትና ጆሮ እንደሚገናኙ......

እነዚያ እግሮች ድምፅ እሰሙ......ጥላሞቶቹ? ዞር ብዬ አየሁ እንዲህ ሆነዋል:



ጉልበት ያለው ጥላ ሞት......የሚፈነዳ መሰለኝ:: መጮህ ፈለግሁ...... ኸረ! ኸረ! ልል ፈለግሁ::

በእናቴ ማህፀን ውስጥ ግራጫ ብርሃን ነበር መሰል......የልብዋ ምትም እንደ ከበሮ እየመታ በለመደው ተራ ልፋት ሊያስተኛኝ::

የፍቅረኞች ትንፋሽ ሳያፍር እዚህ ይመጣል:: ፈጥኖአል:: የእግሮቻቸው ጥላዎች ሳያቋርጡ የተለያየ መቆላለፍ ይሰራሉ:: በእግር ጥፊ የተመቱ ትንንሽ ኩሬቶች ወደ እኔ ሲንከባለሉ እሰማለሁ......ዐይነ-እውጣ ጥላ ሞት ከደቃቃ ረቂቅነታቸው ተጣብቆ ይከተላቸዋል:: እንዲህ ሆኖም ግቢው እጅግ ፀጥ ብሎአል......

ፀጥታው ግርማ አለው:: ፀጥታው ለአትኩሮት የኀበጠ ፈሳሰፋ ይመስላል:: በዚህች ትንሽ ልቤ ውስጥ መነሻና መድረሻዋን ያልተረዳኋት ጥቁር ለጋ ቁጣ ታፍና ተኝታለች:: ማነሽ አንቺ?

ወደ ግቢው መኪና ይገባል:: ዘበኞች ይጮሃሉ:: ራቅ ብሎ ጫጫታ ይሰማል:: የልጆቹ ትንፋሽ ጠፍቶአል:: የእግራቸው ጥላ የለም:: ዞር ብዬ አየሁ:: ቦታው ባዶ ነው:: የእግራቸው ጥላ የነበረበትን ቦታ አየሁ:: ከመኮንን አዳራሽ የሚመጣ ቢጫ ጠይም ብርሃን ሰሊጥ መስሎ እወዲያ ፈሶአል::

ከወዲያ ወዲያ የመኪና በር ተዘጋ::

ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ወደ አዳራሹ መግቢያ ሔድኩ:: ግራ ቀኝ ሁለት ሐውልቶች አሉ:: አንድ የወንድ፤ አንድ የሴት:: ሐውልቶቹ ከአውሮፓ የመጡ መሆን አለባቸው:: ሴቷ ከማውቃቸው የአዲስአባ ሴቶች ጋር የሚመሳሰል ብዙ ነገር የላትም (ሁለቱም ሴት ጓደኞቼ በርጭና ያዘነበሉ ጡቶች አሏቸው):: ጡቶቿ ቆመው አየር ይወጋሉ::



@BOOKALEM

ማንሳቸው:: ሐይለሥላሴ ከብልግና ጋር ብዙ ጊዜ የሚያያዝ የሰውነት ክፍል እያዩ ቤተመንግሥታቸው ይገቡ ይወጡ እንደነበር ትዝ ሲለኝ ጥላ ሞት ያለው ሳቅ ሳቅሁ:: ምናልባት በሃሳባቸው ወደዋት ይሆናል:: እሳቸው ባይሆኑም ከመኳንንቱ ምናልባት አንዱ ነሽጦት ዳብሷት ይሆናል......በግልፅ ሳይሆን እንደ ጨዋታ፣ እንደ ኪነጥበብ ውይይት አስመስሉ:

'ከምንድነው እባካችሁ......ይኼን ሃውልት የሰሩት?' ሐውልቶቹ የተገነቡብትን ቁስ እንደሚፈትሽ እየነካካ:: ከዚያ የከበቡት መኳንንቶች:

'አሆ አሆ አሃ......አሃ አሃ......' በውሸት ሳቅ ፍርስ::

በልባቸው:

'ባለጌ......ባለጌ'

ኢትዮጵያዊ ሴት በሀበሻ አርቲስቶች እንዴት እንደምትቀረፅ መቼ አይቼአለሁ? ባይ ደስ ይለኛል:: `የመስቀል አበባ' የምትባለው የአፈወርቅ ተክሌ ስዕል ፊትና ጨርቅ ብቻ ናት:: ኢትዮጵያዊ ሴት ዳሌ ሰፊ፣ እግረ ቀጭን፣ መካከለኛ ቁመት ያላት፣ ከንፈረ-ከባድ፣ የሚሰባበሩ የውሸታቸውን የሚያፍሩ ዐይኖች......የዚህች ሴት ሐውልት የከንድዋ ጥላ ካርቦን መስሎ ጠፍጣፋ ሆድዋ ላይ ወድቆአል::

......እና ትልልቅ ጡቶች......

ታዲያ ይሔ ሁሉ ሚሊዮን የሃበሻ ሕፃን በአብሽና በፋፋ ብቻ አይቆም::

ሐውልቶቹ በእስማት እዚህ አገር የመጡ ይመስላሉ:: ምናልባት በአውሮፓ እንዲህ ዐይነት ሐውልቶች አሮጌ ተራ በርካሽ ይሸጡ ይሆናል:: የወንዱ ሐውልት ጥላ ሞት......በስተግራ ካለው አበቦች ረድፍ ላይ ወድቋል:: በቂ ብርሐን ቢኖርም......የአበቦቹ ቀለማቸው አይታይም:: የዕጌሬዳዎች የአበባ ቆብ......ግራጫ ኳስ መስሏል::

ወደ ሥር አየሁ:: ለሰከንዶች የጭንቅላቴ እድራሽ ጠፋኝ......ከጓላዬ ባለብዙ ጡት ጥላ:: ስልክ እንጨት መስሎ ወድቆአል:: ከኩሬው የድሪያ ድምፅና ሳቅ እሰማለሁ (የት ነበሩ?):: የደመና ጋቢዋ የተገለበባት ጨረቃ ለደቂቃ ያህል በራች:: ኩሬው ውስጥ ብዙ ጥላሞቶች አየሁ:: እና አየር ውስጥ የጨረቃን ብርሃን ነክሰው የያዙ ወደ መሬት በቀስታ የሚወድቁ ክንፋቸው የተመታ አምባሳይ የመሰሉ በራሪ ነገሮች...... ወረቀቶች:: ዙሪያዬን ተገላምጬ አየሁ:: ፍርሃቴ በእጄና በእግሬ ስትሮጥ እሰማታለሁ (ፍርሃት ሬሻም ቀሚስ ያደረገች መሮጥ መለፍለፍ የምትወድ ቀልቃላ ሴት ትመስለኛለች):: አወላወልኩ:: ሁለት ስዎች ውስጡ ያሉበት አንድ

መኪና በፊት ለፊቴ ሲያልፍ ወረቀት እላዬ ላይ በትኖ አለፈ፡፡ ውስጥ ሁለት ሰዎች አሉ፡፡ ወረቀቶቹን ሰብስቤ አነሳሁና አነበብኩ......ይሄ አርዕስት አለው፡

*«የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጣ የጥገና ለውጥ አያበርደውም»*

እዛ አካባቢ ባለው ብርሃን ጥቁሩን የፊደል ሰልፍ ማንበብ ለአይኖቼ ከበዳቸው፡፡ ተደብቄ ማንበብ ፈለግሁ፡፡ ተደብቆ የተበተነን ወረቀት ተደብቆ ማንበብ፡፡ ከጥላ ወደ ጥላ፡፡

ፅሑፉ ሦስት ቅጠሎች ሙሉ ነው፡፡ በእኔና በወረቀቱ መሐል እርቀት እንዳለ ይሰማኛል፡፡

ፍቅረኞቹ ከአትክልት ቦታው ወጡ፡፡ ልጅቷ ልብሷ ረጥቦአል፡፡ ርጥቡ ቀሚስ ከሰውነቷ ላይ ሌላ የተሸበሸበ ወፍራም ቆዳ ሆኖአል፡፡ ፊቷ ሲሳም የቆየ አይመስልም፡፡ ልጁ እስከ ጉልበቱ እርጥብ ነው፡፡ ወረቀት ከኩሬ ሲያወጡ ይሆናል፡፡

«ምነው?» አልኩ፡፡

«አዳለጠኝ» አለች፡፡

*ጥላሞትህ እጅግ ሲቀርብህ......እንደ እርጥብ ሳሙና ያዳልጥሃል፡፡*[22]

መኝታ ቤቴ ገብቼ ወረቀቶቹን ማንበብ ጀመርኩ፡፡ አንዳንዴ ወደ ወረቀቱ ይዘት እቀርባለሁ......ከወረቀቱ ይዘት እርቃለሁ፡፡ ስወዛወዝ ቆየሁ፡፡ ምናልባት ወረቀቱን የወረወረልኝ ጥላ ሞት ነው፡፡ እዚህ ሽው ያለ አሊጋ፡፡ ሽው ያለ ፀጥታ፣ ሽው ያለች እንቅልፍ ተንሰፍስፋ እየጠበቀችኝ......

የመጨረሻዋ ወረቀት ከአንድ ቀን በኋላ ሠላማዊ ሠልፍ እንድንወጣ ትጋብዛለች፡፡ ይሔ ሁሉ ጉድ እስከዛሬ የት እንደነበረ አይገባኝም፡፡ ቢሆንም የዚያን ቀን የምሰራው የለኝም፡፡

ወልዴ እየጮኸ ገባ፡፡

«እንዴ እንዴ!» እየጮኸ......እኔን እያየኝ

«ምነው?»

«ፖምፍሌት ማንበብ ጀመርሽ?»

«መጀመሪያ ሠላምታ በል»

«ማንን?»

[22] አንድ የሲኒየቦብ ምሽት ላይ ከአንድ ደራሲ የሰማሁት፡፡ ይኼን ከምን ጉዳይ ጋር እያያዞ እንደተናገረ ትዝ አይለኝም፡፡ ግን የሰነዘረው ምስል ጥላሞቶችን ወደሚጨበጡ ቁሶች አቅርቦልኛል፡፡



@BOOKALEM

«ማን አለ እዚህ?»

«እናቱን»

«እንብበህ ከጨረስክ እስኪ ስጠኝ» ፊት ለፊት ወንበር ላይ ተቀመጠ:: ከኮት ኪሱ ፓኬት ኬንት ሲጋራ አወጣ:: ሲጋራ እየለኩሰ:

«ከነገ ወዲያ ሰላማዊ ሰልፍ አለ......አትሔድም?»

«ምን ላደርግ ይመስልሃል?»

«የቤቴ ሽሮ ናፍቆኛል ብለህ እንዳትሔድ!» ሲጋራ ስቦ አንዳች የሚያህል ጉም ተፋ:: ጥላ ያለው ጢስ::

«እኔ እናቴን ላይ ነው የምሔደው......»

«እናቴን ገለመሌ......» አመድ የሌለበትን ሲጋራ አራገፈ:: ለመቀጠል እንደፈለገ ገብቶኛል::

ለቀቅሁት:

«እንደዛች እንደ ዕንቅልፍ ለምኔ ጠባ እንቅፋታችሁ ይበዛል......ማሩን አብረህ ብትሰርቅም እንኳን......እንዳልሰረቀ አደባባይ ወጥተህ እንደ እኔ እንደብልጡ......ሰዎቹን ሰርቃችኋል በል»

ሳቅሁ::

«ሰላማዊ ሰልፍ እኮ ማሳበቅ ነው» አልኩት::

«አኬ......ለሕዝቡ ታሳብቃለህ......`ኪስህን አወለቁልህ` ብለህ...... የሐይለሥላሴ መንግስት እንዴት እንደተደናገጠ አታውቅም?»

«ይመስላል»

«በዚህ በደነበረ በቅሎ እንደምንም ብለህ ቃጭል ማሰር ነው»

«ደም ቢፋሰስ»

«አመፅ ያለ ደም መጥቶ አያውቅም......አንዳንዱ ያለ ደም አይፀዳም ......ምን አስፈራህ ገገር አይደለህም!» ሌሎች ሁለት ልጆች ገቡ:: ፊቶቻቸው እንደጠጡ ያቃጥሩባቸዋል::

ወልዴ ወረቀቱን ተቀበለኝ:: ለማንበብ ተመቻቸ:: ፊቱ አተኮረ:: እርቦት የሚበላ ይመስላል:: ጥላሞት የለውም:: ቢኖረውም አንድ ሆነዋል:: የባዕድነት ስሜት ፊቱ ላይ የለም::

ወረቀቱ ፊቱ፤ ፊቱ ወረቀቱ ነው::

«ሠላማዊ ሰልፍ እሔዳለሁ» አልኩት ሲጋራ ለመውሰድ ስጠጋው::

* * *

ሰው እንደጀግና ምንጭ ነው......እጅ፣ እግር፣ አፍ ያለው አባይ ነው:: ጣናው ስድስት ኪሎ ይሆናል......አፋ ሜሬዊ ይወድቃል—ቤተ መንግሥት:: ተያይዞ ይወርዳል......አካሔድና ፍጥነት የቀረጠው ሰልፍ ......ዳር ይዞ በቆመ ገመምተኛ ይሞላል......ተቆላልፎ ነው......ድምፁ



@BOOKALEM

ተከፋፍሎ ሲመጣ......አንዱ ለፍካሬ፣ አንዱ ለውግዘት ሲያነሳ......ሁሉ ነገር ይደበላለቃል......የአንድ አድማ ሠልፍ......በአንጺ በአንጺ የየራሱን ጩኸት ሲጮህ ነጠላ አፍ አድራሻው ይጠፋዋል:: ወታደሮች የተፋበትን መንግስት የበለጠ ለማርጠብ ተማሪ ሁሉ ምራቁን አጠራቅሞ ወጥቷል......ወታደሮች የጮሁበትን ካቢኔ......የበለጠ ለማደንቆር ያልተጠራቀመ የወጣት ዕንጥል የለም:: ይሔ የሰው አረፄ አዲስአባ ካሉት ጥቂት ትልቅ መንገዶች በአንደኛው ላይ እንደገዛው መሬት እየተሳደበ እየተራገመ፣ እየተቸ ሲያልፍ......ሐይለሥላሴ ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው የእርጅና ቃታቸውን በጥንቃቄ ይተነፍሳሉ:: ሳብ:: ሳብ::

እኔ ሰልፉ መሐል ላይ ነኝ:: ወልዴ ዜማ አውጪ ሆኖአል:: ድባቡ ሁሉ ደስ ይላል:: የሰዎቹ ስብስብ ራሱ ድፍረት ይሰጣል:: የትክክለኛነት ቫይታሚን ይከትባል:: በዚያችው ዓለም ውስጥ ጂሙን በዘፈን ለመምራት ፋክክሩ ይግላል:: አንዱ ያወጣው ዘፈን ሳያከትም......ሌላው ከሥር ይፈለፍላል......

ሚኒስትሮቻችን ሌቦች ናቸው!!

ሰርቀው ሰርቀው መሸሻቸው!!

ትልቅ ገጣሚ የሰራት አትመስለኝም......ለብቻ ሲጮኋት፣ በህብረት ሲዘምሯት ግን ጉልበት አላት:: ከራስዋ በላይ ትሆናለች.....ትጋነንና ስም ወደሌለው ሌላ ልዩ ነገር ትለወጣለች......የሰው ጉሮሮ ይኼን ድንቅ ለውጥ የሚፈጥር አይመስልም:: የትም ወድቃ የምትገኝ ከባድ እንጎል ያልሰራት የወል ግጥም ናት፤ ግን የእንጥል ህብረት ውስጥ ስትገባና የተለያየ መጠን ያላቸው አፎች ሲከፈቱ ፍርሃትና ሽብር ትፈለፍላለች:: ጠዋት በችኩላ የበላኋቸው የማርጋሪንና የማርማላት ጉርሻዎች ሆዴ ውስጥ እንደ ትልልቅ ብዮች ቁጭ ቁጭ ብለው ይሰሙኛል:: ግማሽ መንገድ ላይ አሁን ያገሳኛል:: ወልዴ የሰልፉ ባለቤት ለመሆን ምንም አልቀረውም......አንዳንዴ.....ከሰልፉ ረድፍ አምልጬ ወጣ ብዬ የሚያስገመግመውን ድምፅ ስሰማ......አገር በድምፅ የምትሠራ ቢሆን......በድምፅ የምትቋጠር፣ የምትፈታ ቢሆን......አፍሪካ ሁሉ ከሰንሰለቷ ትሾልክ ነበር ያሰኛል:: አንዳንዴ......ሠልፉ እንብርት መሐል ስገባ የመሬቷ ንዝረት አፍሮዬን ያነቃንቀዋል:: ቅንድቤ የሚወድቅ ይመስለኛል:: የወፍጮ ቤት ሞተር እንደመደገፍ ዐይነት......የሚነቃነቅ ዳምጠው እንደመዳበስ ዐይነት......የሆነ ነገር

የሰልፉ ወገብ ቤተመንግሥት አካባቢ ሲደርስ......ሲል፣ ከወዲህ ፋነዳ:: ከወዲያ ከፊት ያለው የሰልፍ አንጓ ደንግጦ ቀጥ እንደተናደ ያለው በድንጋጤ ተገምሶ መርበትበቱን መግታት አቅቶት ዐይነት እፊቱ ካለው ሠላማዊ ሰልፈኛ ጋር ተላተመ:: ስስ ነጭ ጭስ



@BOOKALEM

ከሰዎች እናት በላይ (የፀጉር ኳሶች......ምናለ ተማሪው ባርኔጣ ቢያደርግ?) ወደ ላይ ሲነሳ ይታየኛል:: እንደገና ሌላ ፈነዳ......ደጋግሞ ፈነዳ......ሠልፉ በንፁህ ለሁለት ተቆረጠ:: የመንገዱን መሃል ይዞ ይሔድ የነበረ ሰልፈኛ ወደ ዳር ሸሸ:: ከሩቅ የምትታየው ፒያሳ......የአስፋልት ክንዶቿን ወርውራ ከዚህ ጉድ እንድትነጥቀው የማይመኝ ያለ አይመስልም::

ወልዴን ሠልፉ ውስጥ በውለብታ አየሁት:: ሌኒናዊ ጢሙ የበለጠ ረዝሞአል:: እየተጋፋ የማርንግሪት ይሮጣል:: እኔ የአስፋልቱን ጠርዝ ተከትሎ ወደ ላይ በተገነባው ግንብ ላይ በሰዎች ግፊት ተሳስሬና ተጣብቄ ሆዴ ሊፈነዳ ደርሶ ቆሜአለሁ......ሰዎች ማለፊያ ስላጡ በተለያየ አቅጣጫ ሲሮጡ ቶሎ ቶሎ ሽከሙ ሲቀለኝ ይሰማኛል...... ወልዴ የያዘውን መፈክር ጥሎ ወደ ኋላ ሲሮጥ አየዋለሁ:: ፂሙ ወደ ፊት ሾል ብሎ ወጥቶ......ከአልኔስታ የገዛት የኋላ ተካፋች ኮቱ እየተው ለበለበች......እግሩን እስከጭንቅላቱ እያነሳ ሲሮጥ:: ዓላማው ሙገር ለመድረስ ይመስላል::

ተደላድሎ ሆዴ ውስጥ ተቀምጦ የነበረው የማርማላትና የማርጋሪን ቁርሴ ወደ አፌ ሊወጣ ሲሳብ ይሰማኛል:: ግንቡን ተደግፌ ውጋቴን ሳስታምም የቦንቡ ጢስ ዐይኔን ያቃጥለኝ፣ ጉሮሮዬን ይኩረኩረኝ ጀመር:: ረኻርም ዕርቀት ስላለው በግንቡ በኩል ወደ ታች ለመዝለል ይከብዳል:: ወደ ኋላ መመለስ አለብኝ:: የኋላው መንገድ በብዙ ሰው ተዘግቶአል:: ትንሽ ራቅ ብሎ ወደ ላይ የግንቡ ከፍታ ስለሚቀንስ ተማሪው በዚያ እየተያያዘ ይዘላል:: ሴቱ፣ ወንዱ:: ቦንብ ከፈነዳበት ወዲያ ያለው የሠልፉ ቁራጭ የተረበሸ፣ የተደናገረ ጭራውን እየጐተተ ጉዞውን ቀጥሎአል:: በፍጥነት ታጥፎ ሲወርድ እየዋለሁ......ወደ ኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት ወደ......ወደ ፖሊስ ጋራዥ ወደ አምባሳደር ቲያትር ይሆናል የሚያልፈው:: ግንቡን ሳልለቅ የተበታተነውን ሰልፈኛ እየገፋሁ......እየሾለክሁ ወደ አጭሩ የግንብ ክፍል ደረስኩ:: ዘለልኩ::

የተቃወሰው፣ የዞረበት ሰልፈኛ ላይ እንደገና ሌላ የአስለቃሽ ጭስ ቦንብ ወደቀ::

ያ አካባቢ ለመጨረሻ ተከፈተ::

ከታች አሮጊቶች በጣሳ ውሐ እየያዙ ቆመዋል......

«አንተዬ......ውሐ ከፈለግህ ይሔውልህ»

«ምን አስጨነቃችሁ? አርፋችሁ ተቀምጣችሁ ብትማሩስ»

እያዘኑ ሲናገሩ ሁለት ስሜቶች ይፈጥራሉ:: የማይታገል፣ ዳር የቆመ፣ ለራሱ ችግር ሌሎች ሲሞቱለት የማይገባው ሰው እንዳለ:: ግን ደ`ሞ የተጎዳ፣ ለመርዳት አኮብኩቦ የሚጠብቅ::......አንዳንዱ ሰላማዊ ሰልፈኛ እንደመብቱ ውሐውን ከሴቶቹ ነጥቆ (ውሐ ይዘው የቆሙት



@BOOKALEM

ሁሉ ቤቶች ናቸው) ፊቱ ላይ የሚረጭ አለ:: አንዳንዱ መሐረቡን ያረጥባል:: በጉንጮቼ ላይ ዕንባ ይወርዳል:: መምጣቴን ረገምኩ:: ከወዲያ ጥግ አንዱ ፖሊስ ዱላ ይዞ አጥሩን ይዘባል......ባርኔጣው ከጎላው ቀረች......

ፖሊሱ አጭር ዱላውን እያወዛወዘ በቋጠሮ የሚሮጡ ተማሪዎች ያባርራል:: ተበታተኑበት:: ማንን እንደሚከታተል መወሰን አልቻለም:: አይን አዋጅ ሆኖበት ትንሽ ወዲያ ወዲህ ሮጦ ቆመ::

እዚህ አንዲት ሴት ውሐ በጣሳ ይዛ ለአራት ልጆች ታፈሳለች:: ብዙም ሳይርቅ የተማሪ ሰልፍ ሲጮህ ይሰማል:: ድምፁ እንደማዕበል ወዳለንበት ይገለበጣል:: ግርማ ያለው የምድር መንቀጥቀጥ የመጣ ይመስላል:: አጉንብሼ አይኔን ሳጥብ ቆየሁ:: ከሰልፉ ተመልሼ መግጠም አልፈለግሁም......ሶስቱ ልጆች ሔደዋል:: ሴትዮዋ ውሐ ያለበትን ጣሳ ይዛ አጠገቤ ቆማለች::

ያጠለቀችው ጫማ የተሰነጣጠቀ (ዙሪያውን ከንፈሮቹ) ሰማያዊ ኮንጐ ነው:: የኩሸት፣ ለጨዋታ ያደረገችው ይመስላል:: ዐይኖቼን ቀስ እያልኩ ወደ ላይ አነሳሁ:: የቀሚሷ ጠርዝ፣ የክርክም ስፌቱ ከር......ድምድማቱ ፈርሶ:: ዐይኖቼን በቀስታ ሳላቋርጥ ወደ ላይ አነሳሁ:: የቀሚሷ መነሻ (ኦሪጅናል) ቀለሙ ጠፍቷል:: ወደ ነጭነት ሊለደድ ትንሽ የቀረው አረንጓዴ ቀለም በግድ ይታያል:: ፊት ለፊቱ ያመድና የምግብ እድፍ ነው:: ወደ ላይ ሆድዋ አበጥ ያለ ነው:: የቀሚሷ የወገብ ስፌት ቦርጭዋ (እርግዝናዋ) ዳገት ላይ ቀርቷል:: ጣሳ የያዘችበት ግራ እጅዋ ወረደ:: ጣቶቿ ወፋፍራሞች......ዕሩይ የመሰለ ቆሻሻ የሞላቸው ሰንበሮች ያሉባቸው ናቸው:: ጥፍሮችዋ በልዘው ተሸራርፈዋል:: ጡቶቿ የፊኛ ቅሎች ናቸው......የደረቷ ቅላትና ንዕሕና ብቻ ያበራል:: ዐይን ለዐይን ተገጣጠምን:: ከዚያ ሁሉ መጉደፍ መሳደፍ የተረፈው ደረቷ ብቻ......

«አንተዬ ፖሊስ መጣልህ»

ዐይኔን እየቆጠቆጠኝ ቀና ብዬ አየሁ::

«ምንም አያደርገኝም» አልኳት በመረጋጋት::

«ይልቁን ሽሽት በል......እነሱ እቴ ሰው ማንገላታት ይወዳሉ» ጣሳ ውስጥ የቀረውን ውሐ ወደ መሬት እየረጨች:: ቀደም ሲል ከእርቀት አልታየኝም ነበር:: ሲቀርበኝ ግን የፖሊሱ ግንባር በግራው በኩል ደም እየፈሰሰ እንደሆነ ተገነዘብኩ:: ወደ እኔ አቅጣጫ ዱላውን እያመቻቸ መጣ:: ፊቱ ደረቅ ይመስላል:: የዘንጋዳ እንጀራ ይመስላል:: ዐይኑ ውስጥ ጨፍ፣ ጨፍ በቅሉ የሚያውቅ አይመስልም:: አፉ ወደ ሰማይ በጣም ብሎአል--ወደተፈነከተው ፊቱ ጉን::

ሴትዮዋ በፖሊሱ እንዳልመታ እንደገላጋይ በእኔና በፖሊሱ መሃል መጋረጃ ሆና ቆመች:: ግራና ቀኝ የተሰባበረ የፈራረሰ አጥር ነው......ዝሆን ያዘለች ዝሆን የሚያሾልክ:: ቢሮጥበት ግን ወደ የትም የማይሰድ:: ከጀርባ የሴትዮዋ ቤት መሰለኝ:: ቤቷ ለመግባት አልደፈርኩም:: ፖሊሱን እስኪጠጋኝ ጠበቅሁት:: ሴትዮዋ ነገሩ ስላስፈራት ወደ ግራ በትንሹ ሸርተት ብላ እጆችዋን ግራና ቀኝ ዘርግታ በእኔና በፖሊሱ መሐል እንደቆመች:

«ተው ጋሼ ተው» አለችው ፖሊሱን

«ዞር በይ»

«ተወው ይቅር......ምን አደረገህ?»

«እንዲህ ተፈንክቼ»

«እሱ እዚህ ቆየ......ምንም አላደረገም»

ሰውዬው በአንዴ ተግደርዳሪ ቁጣው ሰፋና ነብር መሰለ:: ሊያልፋት ሲሞክር ካለችበት ሳትነቃነቅ እጆችዋን ዘርግታ አቆመችው:: ከመንገዱ፣ ሰልፉ ከተበተነበት ቦታ ሰዎች ቆመው ያዩናል:: ከፊሎቹ ይሳደባሉ:: ፖሊሱ ይንቆራጠጣል:: ለሰከንዶች ያህል የማላውቀው ቦታ የመጣሁ መሰለኝ......እዚህ ያሉትን ሰዎች ሁሉ አይቼአቸው የማላውቅ:: ከደቂቃዎች በፊት የማውቃቸው......አሁን የማላውቃቸው:: ድሔ ስሜት ተፈራረቀብኝ:: ከምን እንደሚያያዝ መገመት ከበደኝ:: ሰውዬው እየቀረበ መጣ:: እኔ ወደ ኋላ እየሸሸሁ፣ እስዋም ወደ ኋላ እየሸሸች፣ ፖሊሱ ደሙ እየፈሰሰ፣ እየቀረበኝ......

ቤቱ ውስጥ የምገባ መስሎት ፈራ መሰለኝ ሴትዮዋን ወደ ጉን ገፍቶአት መጣ::

«አንተ ልጅ ቤት ግባ፣ ቤት ግባ» አለች::

ዞር ብዬ ወደ ኋላዬ ሁለት እርምጃ ዘለልኩ:: ቤቱ ውስጥ ገባሁና በሩን መለስ አደረኩት::

«በሩን ዝጋው» ስትል እሰማታለሁ:: ገርበብ አደረግሁት:: ለምን እንዳልዘጋሁት አይገባኝም:: በሩ ተበረገደና የበሩ ሥር ጠርዝ ቁርጭም ጭምቴን መታኝ......ወደ ኋላ ለመውደቅ ተንገዳገድኩ......ላለመውደቅ አጠገቤ ያገኘኋትን ትንሽ ጠረጴዛ ለመደገፍ እጄን ስዘረጋ ጠረጴዛዋ እንደ ጨርቅ ተጣጥፋ ወደቀች:: እላይዋ ላይ የነበረ ውሐ የተሞላ ጠርሙስና የጳንቴል ጨርቅ ጭንቅላቴ ላይ ወደቀ......ከወደቅሁበት ቶሎ ለመነሳት ሞከርኩ......በመጠኑ ዞር ብሎብኛል:: ዱላ የያዘው የፖሊሱ እጅ የአጭር ሰልክ እንጨት ጥላ ሞት መስሎ ወደ እግሬ ሲመጣ አያለሁ:: የሰውነቴ ሚዛን ተዘበራርቆ መሸሻ ጊዜ አልነበረኝም:: የቤቱ በር በሞገድ የተዘጋ መሰለኝ......



@BOOKALEM

* * *

ስባንን በጀርባዬ አልጋ ላይ ተኝቻለሁ:: በግድ በገለጥኳቸው ዐይኖቼ ኩርኒስ የሌለውን መላጣ የቆርቆሮ ጣሪያ አየሁ:: ዙሪያዬ በአልባሌ የጨርት መጋረጃ ተጋርዶአል:: እራሴን ለማረጋጋትና ያለሁበትን ቦታ ከትውስታዬ ለመቃኘት ዐይኖቼን ከድኜ ለማሰብ ሞከርኩ:: ቀኝ ዐይኔ ይመዘምዘኛል፣ ይጠቀጥቀኛል......ግንባሬና ፊቴ ቆዳ ሥር የጎረምሳ ጉንዳን ሠልፍ የገባ ያህል:: ማሰብ አልቻልኩም:: እንደ ሰመመን ዕንቅልፍ ተጫነኝ......ቀስ በቀስ ሰዎች ሲነጋገሩ መስማት ጀመርኩ:: ዐይኖቼን እንደገና ገለጥኩ:: የሆንኩት ነገር ቀስ በቀስ ከእርጊው ወደ አዲሱ......ከሩቅ ጊዜዉ ወደ ቅርቡ እየተያያዘ መጣ:: እዚህ ፖሊሱ መትቶኝ እንደቀረሁ ታወቀኝ:: ቀና ብዬ አልጋው ላይ ለመቀመጥ ሞከርኩ:: አልቻልኩም:: ውጋትና ጥመን በሁለመናዬ እንደ ስፒል ውሃ ይፈሳል:: ግራው እግሬ የሕመሙ ማዕከል ነው::

«እንተዬ ተነሳህ?» አለ የሴት ድምፅ::

«እዚህ በመጋረጃ አፍነሽ ልትገይው ነው? ሆስፒታል አትወስጂውም ነበር?»

«ቢያስሩትስ?»

«መንግሥት ይፈልገዋል እንዴ? የተፈቀደ ሰልፍ ነው»

«ምኑ ይታወቃል......በተፈቀደ ሠልፍ አይደለ እንድ ፍሬ ልጅ የተመታው»

«በጣም ተጉድቷል እንዴ?»

«ራሱን ስቶ ነበር»

መጋረጃው ተከፈተ:: ሴትዮዋ ፊቷን ብቻ አስገብታ......

«እሰይ ተነሣህ?»

«እ»

«እንዴት ነህ?»

«ዐይኔ ምን ሆኖአል?»

«የዐይን አምላክ ነው ያወጣህ:: ያ ፖሊስ ዕብድ ሳይሆን አይቀርም»

«ሥራው ነው» አለ ሌላ ድምፅ ከጀርባዋ በኩል

«ዝምበል አንተ ደ'ሞ......የሚለውን ትሰማለህ? አሁን ልጅ ኖሮህ እንዲህ ቢያደርጉብህ ትወዳለህ?»

«ለምን ልጅ እወልዳለሁ?»



@BOOKALEM

«ዝምበል እቴ ቁም ነገር ማውራትህ ነው?......ሰው ምን ይለኛልም አትል?»

«ጎረምሳ ነው......ምን......ጎረምሳ እንኳን ለሰልፍ፣ ጠጥቶ ተደባድቦ ይገባል»

«ይህ እቴ ምን በፈረደበት»

ቀና ብዬ እግሬን አየሁት:: በጣቶቼና በቁርጭምጭምቴ መሃል ያለው ቦታ ላይ አብጧል:: ከዛ የሚመጣው ውጋት ጉልበቴና ብሽሽቴ ድረስ ይሰማኛል:: እንዴትና በምን እንደተመታሁ ለማስታወስ አባጣው ላይ አፍጥጬአለሁ:: ሴትዮዋ ለማየት የገለጥኩትን እግሬን እየዳበሰች:

«ቤትህ የት ነው?» ሸካራና ወንዳወንድ ጣቶችዋ የዚህ ዓይነት ለስላሳ አንካከ ያላቸው አይመስሉም ነበር::

«ሩቅ ነው......ከፖፖላሬ በታች ነው»

«ልትሰጂው ነው?»

«እ?......»

እብጠቱ ላይ በማተኮርዋ አልሰማችውም::

«ልትሰጂው ነው?» አለ ደገመና ያው ድምፅ

«ታዲያ ቤቱ ይሒዳ ከተሻለው......መተኛ ቢኖረኝ......እስኪሻለው ቢቆይ ግድ የለኝም» ከንፈሮችዋን መጥጣ ጣቶችዋን ከእብጠቱ ጉብታ ላይ አነሳች::

«አሃ ሃ ሃ ሃ!!»

«ምን ያስቃል?»

«ሆ ሆ ሆ»

«እናንተ ደ`ሞ ያለሱ አታውቁም......ገና ሸንጉበት ያላበቀለ አንድ ፍሬ ልጅ ነው»

«ወደ ታችም አላበቀለም?» አለ ባለ አሃሃሃው::

«ያንሣህ እቴ......አምሮብኛል ነው? በል አንተ ሰው አትነጅሰኝ»

«ለመሄድ እሞክራለሁ» አልኳት ንትርኩ መሃል ገብቼ::

ወገብዋን ይዛ ቆመች:: አተኩራ ታየኛለች፣ በልብዋ የሆነ ነገር እየመዘነች:: ከመሃል ከውጭ አንድ ሰው ደመቅ ባለ ድምፅ ሰላምታ ብሎ ገባና:

«አንቺ ልጁ እንዴት ሆነ?» አለ

ይሄው ሰውዬ ከጆርባዋ መጥቶ ቆመና ሲያየኝ ቆይቶ:

«ስማ ልጁ.....አይዞህ......እንዴ......ይድናል......እንዴ.....እስኪ ልየው?»



@BOOKALEM

ሴትዮዋ ገለል አለችለት:: አልጋው ግርጌ ተቀምጦ የተጎዳውን እግሬን በቀስታ አገላብጦ አየው:: ወደ ራስጌ ተጠጋና ፊቴን ዞር አድርጐ የተጐዳውን ዐይነ ስቤን አየው:: ትኩረቱ የሚደንቅ ነው:: መጠጥ ያለ ፊት አለው:: የፊቱ ጢም ማደግ ጀምሮአል:: አገጩ ላይ የሙርይ መጥረጊያ የመሰለ ሸንጐበት አለው:: በአባጣውና በገላዬ ውስጥ ውስጥ የዐይኖቹ ሞገድ የሚያልፉ ይመስለኛል:: እግሬን ደግሞ እያየ በአፍንጫው ለሁላችን በጉልህ የሚሰማ የአየር አቃቂ ስቦ:

«ይኼ ቅጥቅጥ ነው ይድናል......የፊሪ ዱላ ነው (ድርጊቱን የተጠራጠረና ያልወደደ ከመጀመሪያው ሊመታኝ ያልፈለገ ፖሊስ ቢሆንስ?)...... ውሐውን አሙቂለት......» አለ::

«አልኩኝ እኩ»

«ቤትህ መሔድ ትችላለህ?»

«ዩንቨርስቲ ማደር እችላለሁ»

«የዩንቨርስቲ ተማሪ ነህ?» አለች::

ራሴን በአወንታ ነቀነቅሁ::

«አሁን ምን ይፈጠር ብላችሁ ነው......አሁን እንዲህ የምትሆኑት?»

አልመለስኩላትም::

«ተነስቶ ለመሄድም አቅም ያስፈልጋል......በል እቴ ውሐውን ላፍላ»

«ሞክረው እስኪ!» አለኝ ሰውዬው:: እየተጉተተኩ ከአልጋው ተነሳሁ:: ሰውዬው መጋረጃውን ከፈተልኝ:: በተሰበረው እግሬ መቆም አልቻልኩም ......የእግሮቼ ጣቶች እንደ ጨርቅ ሆነዋል......ከተረከዜ በስተቀር ደፍሮ መሬት የሚነካ ክፍል የለኝም::

«እኔን......ወንድሜን......እስኪ እኔን ተደገፈኝና ሞክረኝ......» አለችና ጎተት ብላ ወደ ጎኔ ተጠጋችኝ:: እጄን ትከሻዋ ላይ አድርጌ ለመቆም ሞከርኩ:: ትንሽ ይሻላል እንጂ አሁንም ደፍሬ መቆም አልቻልኩም::

«ስልክ መደወል አትችልም?»

«ስልክ የለኝም» `አለኝ' ማለት አልፈለኩም:: አባቴ ወይም እናቴ ስላማዊ ሰልፍ እንደወጣሁ እንዲያውቁ አልፈለኩም:: በልቤ ሆስፒታል ስላልወሰዱኝ ተደስቼአለሁ::

«ተቀመጥ» ብላ ደግፋ አስቀመጠችኝና መጋረጃውን ሸምልላ የተንጠ ለጠለበት ገመድ ላይ አጋደመችውና ወደ ጓዳ ሄደች:: ገላዋ እንኩሮ እንኩሮ ይሸታል:: ቀርቦ በመተከዝ የሚያየኝ ሰውዬ ድ`ሞ



@BOOKALEM

የላብና የአፈር ሽታ ይሰነፍጣል:: ከካኪ ኮቱ ላይ የሚነሳው እንደ ሚዳ ነው:: በልቤ ገበሬ ወይ ግንበኛ መሆን አለበት ጣረን በስተቀኜ ያለው በር ተከፍቶ ጨለማ ይታየኛል......የመንገድ መብራቶች ደንግጠ ያፈጠጠ የጥላ ሞት ዐይኖች መስለው ቆመዋል:: ፊት ለፊቴ ጊዳ ናት:: የሴትዮዋ ያፈነደደ ቡላ ጨርቅ የለበሰ ገላ ይታየኛል:: ውሐ በጣቶችዋ እየፈተሸች ነው::

ተመልሳ ወደተኛሁበት በታ መጣች::

«እንዴት ነው?» አለችኝ በጥልቀት እያየችኝ::

«መጥፎ ነው»

«ታክሲ ይገኛል አሁን የሚያደርሰው?» አለ አሊጋውን ተጋርዶ የነበረ እስከአሁን ሲቀናቀነኝ የነበረ ድምፅ:: የድምፅ ጥላ:: የድምፅ ጥላ ሞት::

«ቆይ መጀመሪያ ይሻለው......ከዚያ እናስባለን»

ይረዳኝ የነበረው ሰውዬ ፊት ለፊቴ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጠ ከከብር ዘበኛ ብርጭቆ ጉንጩን ሞልቶ ጠላ ጠጣና......

«ለምን አምሣ አለቃን አላመጣቸውም?» አለ::

«እሳቸው ይገኛሉ እንዴ? ደ`ሞ ሥላሴ ገቢያ ድረስ በጨለማ ምን አስኬደህ?»

«ምናለበት ልሞክር......ይሔ እኩ በትኩሱ ካልታሸ ቶሎ አይድንም»

«አይ ያንተ ነገር.....ይኼ ደግነትህ አይቆም:: ምን ቢያረጉህ ይሻላል» ወደ ጊዳዋ ገባች::

«ሊሒድ ካለ ይሒድ......አንቺ ምን ትይዢዋለሽ» አለ ሌላው ድምፅ

«አንተ ሰውዬ ጠላህን አርፈህ አትጠጣም?» አለች ድምፅዋ ጎላ ብሎ::

«ይኼን ሁሉ ጨለማ ትሄዳለህ?» አለ የመጀመሪያው ሰው:: ለላ ድምፅ አለው::

«ባላውቀውም እኩ ወገኔ ነው......ባዕድ አደረከው? ሰው ሲጎዳ ደ`ሞ ለእኔ ብሎ መርዳት ማንን ገደለ:: ይልቁን ሮጥ ብዬ ልምጣ»

«በል መቼም......ቀስ በል:: ደግሞ መንገዱ ክፉ ነው መብራት የለ:: ምን የለ......ቤታቸው ካላገኘኻቸውስ?»

«እሳቸው የት ይጠፉሉ......ንትቹ ነው የማመጣቸው:: ልጁ በርታ:: ስም የለህም?» አለ ፈገግ ብሎ......

«ፍሬው እባላለሁ» አልኩት

«በርታ አይዞህ»

«እስከትመጣ ውሐውን አወጣዋለሁ» አለች::

«ገንዘብ አይጠይቁም እሳቸው?» አለ ሰላላው ድምፅ:: ይሔ ድምፅ ከኋላ ምን እንደደበቀው አላውቅም:: የተናጋሪው አፍ ወይም ፊት ያፈራ ወይም ሁለቱም ያፈሩ ይመስላሉ::

«አንተ ምን እንዲህ አደረገህ?:: ባሰብህ:: ልጁ እንዴት እንደተጉዳ አይተኸዋል? በዐይንህ አይተኸዋል?......ራሱን ስቶ ስንት ሰዓት እንደቆየ ታውቃለህ? አንድ ነገርም ቢሆን......እንደው እኩ እናንተ»

«ምን ይሆናል? ካዘንሽ እምቡሳንስ አትጠሪም ነበር?» አለ እንዳልገባው

«ነገርኩህ? ስልክ ማግኘቱ መከራ......እሱ ከተገኘ በኋላ ደ`ሞ ማን ቁም ነገር ብሉኝ ሊመጣ......ቢያስሩትስ ደ`ሞ......እየተገላበጠ ሲተኛ ጊዜ ያው ደህና ነው ሲነሳ ይነሳ ብዬ......ከመሃል አንድ ሁለቴ ተነስቶ ውሃ ጠጣ እኮ ......ከአሁን በኋላ ምንም አትጠይቀኝ ምንም አትበለኝ፣ በአፌ መጥፎ ነገር አታስነሳኝ ......ይልቁን ዝም ብለህ ጠላህን ጠጣ»

እምሳ አለቃን ፍሊጋ የሚወጣው ሰውዬ በሩ ጋ ቆሞ ፊቱን አዞሮ

......

«ሰማሽ እታለም......ለበሽተኛው አረቄ ስጪው በእኔ ሒሳብ......ጥሩ ነው» እየሳቀ ወጣ:: ዱካው በቀስታ በተለካ ፍጥነት ሲርቅ ይሰማኛል:: ከቤቱ ውስጥ የሆነ ዓይነት ሙቀት......በማየው የጨለማ ቱቦ እየተመጠጠ የወጣ መሰለኝ:: ሴትዮዋ ፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: ከመሐላችን የተሰበረችው ጠረጴዛ ተደጋግፋ ቆማለች:: ትዝ አለችኝ::

«የሚመጡት ሰው ካስከፈሉ ትንሽ ሳንቲም አለኝ እኔ እከፍላቸዋለሁ» አልኩ -

«ኸረ ግድ የለም:: እሳቸው ጥሩ ሰው ናቸው የእዝጌር ሰው ናቸው:: ደ`ሞ የተማሪ ገንዘብ» አለች ሴትዮዋ፣ በቀላሉ ሸብ የተደረገ ፀጉሯን በሐይል እያከከች:: የለመደችውን እውነት የተናገረች ይመስላል::

«አንቺ በሰው ገቢ ምን አገባሽ? ሽማግሌው ሌላ መተዳደሪያ የላቸውም»

«አትነግረኝም ስለእሳቸው:: እስኪ ዛሬ እንኳን እረፍ እንግዳ አለ:: እሳቸው ከፈሉኝ አሉ?»

ፊቷን ዞር አድርጋ ለራሷ በሚመስል:

«ያድርቅህ እ`ቴ» አለች::



@BOOKALEM

«እንዴ ባይሉስ:: ዐይናፋርነታቸውን መጠቀም ደግ ነው?»

«እንዴ ባይሉስ:: ዐይናፋርነታቸውን መጠቀም ደግ ነው?»

ከጀርባው የማይገባኝ ነገር ያለ ይመስለኛል:: ልፈታው ግን አልቻልኩም::

«አረቄውን አትሰጪውም? ቅዱሱ ሰው እኮ ጋብዞልኛል?»

ድምፁ ወደመጣበት አቅጣጫ ትክ ብላ አየች:: ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሆነ:: የአረቄውን ጠርሙስ እንስታ መጣች::

«አልጠጣም እንዳትለኝ» አለችኝ::

«አልጠጣም ግን የሚጠቅም ከሆነ» አልኩ::

«ጥሩ ነው:: መቼም መታሸት ያማል.....አረቄው ሕመሙን ይቀንስ ልሃል:: አንድ ሦስቱን ብትጠጣ......ዮሴ የምትስክር ይመስልሃል?»

«የእንቺ አረቄ ሃይለኛ ነው:: ጋሼ ረጋሳ የእስዋ አረቄ መርዝ ነው ይላል» አለ ድምፁ::

«ተወኝ እባክህ......አረቄዬ መርዝ ሆኖ አያውቅም:: ምግብ ነው:: ወንዱን ወንድ የሚያደርግ:: ሙት:: ታውቀዋለህ:: ስም አጥፊ:: ድ'ሞ ጋሼ ረጋሣ አይወጣቸውም:: መርዝ ቢሆን እዚህች ይደርሱ ነበር? አንተ ነህ የምትለው እንዲያ»

«ንገሪዋ:: ረጋሣ ሰው መስሎሽ ነው? እኔ እንደሆን ማመስገኔ ነበር»

«አንተ ነህ ታዲያ ሰው»

አረቄ በመለኪያ ቀድታ ፊቴ መሬት ላይ አስቀመጠችልኝ::

«አልጋው ካልተመቸህ......እዚህች እንደምንም ብለህ ናና ተቀመጥ» አለችኝ ወደ አግዳሚው ወንበር እየጠቆመች:: መቆየቴን መረጥኩ::

«በይ እንግዲህ......ሴት ልጅ ፊት ሲያሳዩዋት ትሆናለች......ይልቁን ጠላ ጨምሪልኝ»

«አልቋል»

«እንዴ?»

«አልቋል»

«ተይ እንዲህ እንኳኳንም»

«ሆነናስ?»

«ትጉጂያለሽ......እንደምወድሽ ታውቂያለሽ»

«ከቴም:: የሚወድ እቴ የሚያደርገውን አናውቅም እና ነው?»

«ምን ላድርግ?»

«የሚወድ አያሽሟጥጥም:: የሚወድ አሽሙር የለውም:: የሚወድ ከአፉ ደግ፣ ደግ ነው የሚወጣው:: የሚወድ እንዲህ በጨለማ ይሔዳል:: የሚወድ ክርስቲያን ነው:: የሚወድ ተሸጉጦ እንደ ሴት አያወራም»

«ስደቢኛ»

«የሚሉሽን አልሰማሽ አሉ»

«ደ'ሞ ምን ተባለ?»

«ምን አውቅልሀለሁ»

«በይ ነገርሽን ተይኝና ጠላውን አምጪ»

«ሲነግሩት አይሰማም እንዴ? አልቋል!»

«ተይ አትከፊ»

«ክፋት አይደለም:: ለሁለታችንም ጥሩ ነው ቢያልቅ»

«ማነሽ የምትነግሪኝ?»

«ይልቁን እንነታረክ......ሒሳቡን......አስቀምጥና ሂድልኝ:: ለሽማግሌው የምከፍለው ነው»

«ካልጨመርሽ አልከፍልም»

«ይኸቺ ይኸቺ......እከክ......ይኼ ነው የቀረህ»

«እውነቴን ነው»

«ግርማ ቢኖር እንዲህ አትልም» (በኋላ እንዳወቅሁት ግርማ ወጌሻ ሊጠራ የሔደው ነው)

«ምንድነው እሱ?»

«ተወኝ በል»

«ምንድነው እሱ?»

ከተሸጉጠበት ጨለማ ባለካኪ ኩት ክንድ ወጥቶ የተከፈተውን በር ሲዘጋው አያለሁ::

«ምንድነው በሩን የምትዘጋው?......ክፈተው!»

«ምን ይሆናል......ብርዱ መጥፎ ነው......ለልጁ እግር መጥፎ ነው»

«ልጁን ለቀቅ አድርገው፣ ሰውም አያከብር እቴ......ቀላል»

«ምን?»

«ምንም አላልኩም»

«ንትርክሽን አቁሚና ጠላዬን አምጪ»

«ነገርኩህ......ሲነግሩህ አትሰማም?»

«ይኼን ብርጭቆ ታያለሽ?» ለማየት አንገቴን አሰገግሁ::

አልታየኝም::

«እናስ?»

«ምረጪ»

«ምንድነው የምመርጠው?»

«ጠላ ካላመጣሽ እሰብረዋለሁ»

«ከቴም......ጉዳይህ ከእኔ ነው?......ወይስ ከብርጭቆው?»

«ካንቺ»

«እኔን ሰበረኝ»

«አስኩናኝ......ምንሽ ይሰበራል:: ጠላሽን ከደፋሁልሽ አነሰሽ?»

«እውነትም ጠግበሃል»

«ሰው ሰም ጠሪ ማን አደረገሽ?»

«እህም......»

«ትንሽነት ነው ለእኔም በሽርሙጣ መሰደብ» አለ ሰውዬው::

ቤትዮዋ እኔን አየችኝ::

«እኔ ልጅቱ ኩሩ ነኝ......ኩርት ያልኩ:: ሙት:: ያባኝ ነው የሚያወራው:: የቆመበት ፈልጉኝ ቢያጣ ነው እንዲህ የሚያወራው»

ምን ዐይነቱ ወንድ እንደሚመኛት ለማሰብ ሞከርኩ......

«አንቺ!?»

«ብትቃጠል:: ባይሆንልህ......እኔ ልጅቱ ደሃ ብሆንም......እመርጣለሁ:: ሁሉ ወንድ እኩ እኩል አይደለ»

«አልቀመሰሽኝ»

«ዐይን ብትገባ ነው መጀመሪያውኑ»

«በዛ አሁን......ምላሳም:: ጠላውን፣ ብርጭቆሽን ይኼውልሽ»

«ይልቁን በሩን ከፈተው»

ብርጭቆ ሲሰበር እስማለሁ:: ከተቀመጥኩበት ለመነሳት ሞከርኩ::

«እንዴ!» አለች ቤትዮዋ አፍዋን ይዛ::

«እናትህን ባልለው......ጠብቀኝማ» እያለች ወደ ጓዳ ገባች::

ስትመለስ ረዥም የበር መቀርቀሪያ ይዛለች::

«በል ውጣ!......እ?......የት ሔደ?.....ይሔ ቤትላ!!»

በሩ ተከፈቶአል:: የሰው ዱካ አይሰማም:: ቤትዮዋ ወደ በሩ ሔዳ መቀርቀሪያውን ተደግፋ ወደ ውጭ በዐይኖቿ ስትፈትሽ አያታለሁ::



@BOOKALEM

የሻሸዋ የጓላ ቋጠሮ እንደ ወፍ ጅራት ማጅራቷ ላይ ወድቃለች:: በቀስታ ትወዛወዛለች::

«ትደርሳታለህ እዚህ እኔ እታለም አይደለሁም......ጨለማ በላው ልበል?» አለች ከበሩ ተመልሳ በየቦታው የረገፈውን የብርጭቆ ስብርባሪ እያነሳች::

«እንዴት ተሰበረለት እባካችሁ......ከቴም ፍቅር......ከቴም አፍቃሪ፣ ወደድኩሽ ባይ:: ቤቴን አቃጥለህ አትሔድም? የበላበትን ሰብሮ የሚሔድ:: ባለጌ:: ይኸቺ አዲስአባ ስንቱን ጉድ ይዛለች እቴ......እመቤቴ እንዲህ ያለ ወንድ ልጅ አትስጪ»

የቻለችውን ያህል የብርጭቆ ስብርባሪ ሰብስባ መጣችና:

«አረቄህን አልነካሽው አንተዬ......ይኼውልህ የእኔ ኑሮ እንዲህ ነው......ነጋ ጠባ መድረቅ ነው:: መቃጠል ነው እቴ:: ይኼን ስብርባሪ ሰው እንዳይቆርጥ ደህና ቦታ ልጣለው:: ባዶ እግሬን ሽከፍ ሽከፍ ስል እኔኑ ነው መቼም የሚቀረድደኝ»

ወደ ውጭ ወጣች:: አረቄውን ተጐነጨሁ:: ጆሮዬ የሚሰራው ሲያጣ፣ ዐይኔ የሚሰራው ሲያጣ......እንደጊዜ ማሳለፊያ መሰሉኝ:: አረቄው እተቀመጥኩበት ነቀነቀኝ:: ምላሴ የተጨማደደች መሰለችኝ:: ጉሮሮዬ ነደደ......አረቄው ወደ ሆዴ ወርዶ እንደ ሙሴ ቀጥቋጦ ሲንቦገቦግ እሰማዋለሁ:: እራቴን እንዳልበላሁ ታወሰኝ::

ፊቴን እንዳኰማተርኩ ደረሰች......እጅ ከፍንጅ ያዘችኝ::

«ሞከርከው?......ታልወደድከው ተወው»

«አይ ግድ የለም:: ደስ ይላል»

«ደግ......እህም......ይሔ ሰውዬ የሚያደርገውን አየህ?»

«ሰማሁ»

«አንዳንዱ ሰው እንዲህ ነው»

«የሚገርም ነው:: የሚፈልገው ነገር አለ እንዴ?»

«የሚገርም ነው:: የሚፈልገው ነገር አለ እንዴ?» ፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: ተያየን:: ፈርጠም ብላ አፍዋን በጣቶቿ ጋርዳ:

«እንደሰማኸው ነው......የሚፈልገው ነገር ቢኖርማ ነው......ታዲያ እንዲህ ነው የሚደረገው?»

መፈለጊን እንደወደደች ያስታውቃል:: ብርጭቆ ቢሰበርም፣ በር ቢደበደብም......ከአንጃ ግራንጃው ሁሉ ጀርባ መወደድ እንዳለ......በጥቂቱ ያፈካት ይመስላል::

«እንዲህ አይደለም:: ሥርዐት አለው:: ለእንዲህ ዐይነቱም አይደለም»

«ይወድሽ ይሆናል»

«በል ተወኝ አንተ»

ድሮ የምታውቀኝ፣ የለመደችኝ ይመስላል ስትናገር::

«ብርጭቆ እየሰበሩ ነው? ድሮ ዝሆን ገለው ሲያገቡ ነበር......ዛሬ ዛሬ ብርጭቆ እየሰበሩ ሆነ ዘይቤው?»

«እህህ» ሳቅሁ::

«አያስቅም እቴ......እንደ እኔ ሆነህ......አረቄ ሽጠህ፣ ጠላ ሽጠህ......ብታየው ያስመርራል:: ወንድ አያሰኝም:: ልቤ የሚደርስ ወንድ ጥቂት ነው:: ምን እያወራሁ ነው እባካችሁ......የእኔ ነገር»

ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ጓዳ ሔደች::

«ያ ሰው በነገር ይዞኝ፣ ውሐውን ልረሳው እኮ ነው......ልቆይ መሰለኝ.....ሽማግሌው ቢጠፉ ነው እንጂ እስከአሁን ግርማ ይመለስ ነበር»

እኔ አረቄዬን እየተከተኩ፣ እሷም የብርጭቆ ስብርባሪ እየለቀመች ብዙም ሳይቆይ ግርማ የተባለው ሰውና አንድ አጭር ሽማግሌ ተያይዘው ገቡ::

«ጎበዝ እንዴት ነህ?» አለ ገና እግሩ ሲገባ::

«ምንም አልል»

«ተቀመጡ አባባ የነገርኩዎት ልጅ ይሔ ነው:: አረፍ በሉና እዩት......እታለም!»

«እመት!......መጣችሁ?» ከጓዳዋ እየወጣች::

«እንደምን አሉ እምሣ አለቃ»

«ደኸና ነሽ?»

«ዛሬስ በደኸና ተገኙ?......መጣሁ......እንዴ? ምን ላምጣልዎት?»

«ጠላ! ጠላ ይሻላል»

«ጠላው ጥሩ አይደለም አባቴ......አሁን ሊመሽ ሲል ነው ውሐ ያገባሁበት:: አልጠራም»

«በይ አረቄው ይሁን»

ሽማግሌው እጆቻቸውን እያፋተጉ ፊት ለፊት ተቀመጡ:: እጆቻቸው ሲፋተጉ እንደ ቆዳ ይጮሃሉ:: ቢላ የሚስሉ መሰለኝ:: ፊታቸው ሰፊ ነው:: የአናታቸው ፀጉር በዕድሜ በከፊል ወደ ኋላ ተሳጭቷል:: ሰውነታቸው አጭርና ጠባብ ናት:: ፊታቸውን ግራጫ ጢም በከፊል ሸፍኖታል......አንገታቸውን ማየት አይቻልም:: በግራ ጆሮአቸው የብር የቀለበት ሎቲ አድርገዋል:: አፋቸው አትታይም::

ለሴትዮዋ መልስ ሲሰጡ የፊታቸው ፀጉር በሕብረት ይነቃነቃል:: እንደ ጃርት ጆርባ ይላወሳል:: 'አገርህን እወቅ' ጫማ ነው ያደረጉት:: ጣቶቻቸው መሬት ይመስላሉ:: የጥፍሮቻቸው ቀለም ወደ ቢጫቴ ይወስዳቸዋል:: ከላይ እስከታች እያበጠርኩ ስላየኋቸው እንዳልተመቻቸው ሰው እተቀመጡበት ተነቃነቁ::

አሳቤንና ትኩረቴን ለመስበር ነው መሰለኝ እንዲህ አሉ: «እግርህን ነው አሉ የተቀጠቀጥከው?»

ድምፃቸው የደስ አልነበረም:: ግርማ አለው:: ሸካራና የሚጋፋ ነው:: ከአፋቸው በቀስታ እንደ ግዙፍ ነገር እየተጕተተ የሚወጣ አዲስ ጋቢ ይመስላል:: ሱሪዬን ገልቤ የተጎዳሁበትን ቦታ አሳየኋቸው:: ከተቀመጡበት ተነስተው ወዳለሁበት መጡ:: እግሬን ነካኩትና:

«ያምሃል?»

«ትንሽ»

ነካኩት እንደገና::

«ያምሃል?»

«ትንሽ»

ጨበጡት:: ጮህኩ::

«ይሔ አንድ ሣምንት ሳይቆይ ይድናል:: ካልታሸ ግን ቢድን እንኳን ነው አብጦ ቢቀር?» እንዲህ አብጦ ይቀርብሃል:: ጥሩ ይሆናል......

የእሳቸው አስፈላጊ መሆን ምክንያት እንዳለው ሲነግሩኝ «ምን ጥሩ ነው» አልኳቸው

ሣቁ:: ጥርሶቻቸው አጫጭሮችና የተስተካከሉ ናቸው:: ከድዳቸው ብዙ ሳይርቁ ሔደው ይቆማሉ:: በመቀስ የተከረከሙት ይመስላል:: ግርማ ከጓዳ መጣ::

«ምን ይመስልዎታል?» አለ......ስለ እግሬ::

«ቀላል ናት......የሞቀ ውሐና ትንሽ ቅባት ነው የሚያስፈልገኝ»

«እታለም ቅባት አለሽ?»

«አይጠፋም»

ሁለት መለኪያዎችና በጠርሙስ አረቄ ይዞ ተቀመጠ:: ለእሱም ለሽማግሌውም ቀድቶ:

«አይዞህ!» አለ......ወደ እኔ ዞሮ ሳቅ እያለ::

«ምንም አይሆንም» አሉ ሽማግሌው በዐይናቸው ቂጥ እያዩኝ::



@BOOKALEM

«ይሔ ቅጥቅጥ ነው:: አያድርገውና ቢሰበርም አድነዋለሁ......ዘመዴ ነው አልከኝ?»

ግርማ እየሳቀ አየኝ::

«አዎ ዘመዴ ነው:: ዘመዴ አይደለም እታለም?»

ከጊዳ ሳቅ መጣ::

«ትቀልድብኛለህ?» አሉ ሽማግሌው የአረቄዋን መለኪያ በወፍራም ጣቶቻቸው ይዘው:: ፊታቸው ላይ ያለው ጢም የወደቀ መሰለ:: የግንባራቸው መስመር ጠፋ......ፊታቸው መሐል መልካም ሰፊ አፍ እንዳለ አሁን ይታያል:: አረቄ እንደሚወዱ ያስታውቃል::

«ሰው ለሰው ወንድሙ፣ ዘመዱ እኮ ነው» አለ ግርማ::

«እሱማ ነው» ጥርጣሬ የያዛቸው ይመስላል::

«እንቺ ክፍሌ የት ሔደ?»

«ተወኝ የእሱን ነገር ሌላ ጊዜ እጫውትሃለሁ»

«የምን ሌላ ጊዜ ነው?»

«ማነው?......ይሔ ክፍሌ?» አሉ ሽማግሌው::

«እ» ሴትዮዋ

«ተሱ ምን አገናኘሽ......ሠይጣንም አይደል እሱ»

«እሰው ቤት መጥቶ ሠይጣን መሆን አለ?»

ከውጭ የማያቋርጥ ክላክስ ይሰማል:: ትዕግስት ያስጨርሳል:: ፊት ለፊት ግድግዳ ላይ ሦስት ፎቶ ግራፎች ተራርቀው ተሰቅለዋል:: አንድ የወንድ፣ ሁለቱ የአንዲት ሴት:: ሁሉም ጉርድ ፎቶ ግራፎች ናቸው:: ባለ ጥቁርና ነጭ::

«ምንአለሽ ደ'ሞ?» አለ ግርማ

«ምን ይለኛል እሱማ......ምን እንዳሳበደው አውቃለሁ?»

«ምን ትደብቂያለሽ?»

«ብርጭቆ ሰብሮ ሔደ»

«ምን ሆነና?» አለ ግርማ

«የትም እንደረበሸ ነው» አሉ ሽማግሌው::

«ደ'ሞ የት ይረብሻል?»

«ወሬ አትሰሙም ማለት ነው?»

«ምን እኮ ቆዳው ደኸና ሰው ይመስላል»

«አላወቅሽ እቱ......ምን ስራ አለውና ሲመሽ ነገሩን የጀመረ......»



@BOOKALEM

«ምን አደረገ እባኩሀ?»

«ምን ያደርግልሻል ወሬ:: ለራስሽ ተጠንቀቂ»

«ብሰማውስ?»

«ምናለ ትስማው......»

«የበቄን ጠላ ቤት ያዞጋት እሱ አይደለ»

«ይኸቺ እዚህ መንገዱ ዳር ያለችው?»

«ታዲያስ?»

«የት ሔደች አሁን?»

«ወደ ፍልውሐ......ፖሊስ ጋራጅ አጠገብ ወርዳለች»

«ምን አደረጋት እባክዎ?»

«እሱ የሚሰራው ሥራ......(ራሳቸውን ነቀነቁ) ጠላ ሊጠጣ ሲመጣ በኪሱ በብልቃጥ የግራዋ ውሐ ይዞ ይመጣል......እንዴት እንዳሰበው ሲሆንለት......ጠላዋ ውስጥ ግራዋ ይጨምራል:: ጠላ ቤቱ ባዶ ጓላ ነው:: ሽንቱን የሚከፍል መስሎ ለካ አጠፍ ብሎ መርዙን ይጨምራል:: ሰው ግራዋ አይጠጣ:: ቢጠጣ ይታመማል:: እንዴ ይኸቺ ሴት ልትገለን ነው እንዴ? ብለው ቀሩ:: ቀስ በቀስ ገበያዋ እየቀነሰ ከሰረች»

«እንዴት ታወቀ እሱ እንዲህ ማድረጉ?»

«ተናገረዋ:: 'እስዋ ቤት እንሒድ' ብሎ ሰዎች ሲጋብዝ 'ግራዋ ቤት እንሒድ' ይላል......ደ'ሞ ሰው ጋብዞ ይሔዳል:: እሱ ደ'ሞ አረቄ ቶሎ እንዲያውቁ:: እና እንዴ ሰክሮ 'እኔ አከሰርኳት' ይልሳችኋል::» አረቂዋን ተጉነጩ::

«በስመአብ እቴ ሰይጣን!»

«የሴትዬዋ ውሽማ ካልገደልኩት ሲል ነበር»

«ምን ያገኛል እንዲህ አድርጉ እቴ?»

«ፈልጊት ነበር መሰለኝ እስዋን» የዚህን የተናገሩትን ዐረፍተነገር ትዕእና ያስተዋሉ አልመሰሉም::

«ቀድሞ 'ነብር አየኝ በይ' ሲላት ነበር አሉ......ግን አልገባትም»

«እሱም ነብር ሆነ እቴ:: ለማን ይገባል ይሔ» እያለች የተቀጠቀጠ እግሬ ስር የሞቀ ውሐ የተሞላውን ትንሽ ሳፋ አምጥታ አስቀመጠች::



@BOOKALEM

«ውሐው ውስጥ እግርህን አስገባው የእኔ ወንድም» አለች፣ ፊትዋ ስለ ክፍሌ ነገር እያሰበ ነው መሰለኝ ኩስተር ብሎ::

«መጠንቀቅ ነበረባት» አሉ ሽማግሌው::

«እርስዎ በእሷ ቦታ ቢሆኑ ይችሉበታል?»

«ማባረር! በቃ ማባረር!» አሉ ቀኝ እጃቸውን እያራገቡ::

«ሰው ልጠጣ ብሎ ሲመጣ አይከለከልም:: ደ'ሞ እንጀራዋ ነው:: ውሽቱንም መስሏት ይሆናል»

«ክፉ ሰው እንዲያ ነው......ያለውን ማመን ነው» አሉ ሽማግሊው

«ክፉ ሰው መሆኑን እንዴት ታውቃለች? ግንባሩ ላይ ምልክት የለው?» አለች::

ሦስቱም ፊት ለፊት ተቀመጡ:: እግሬን በቀስታ እንስቼ ውሐው ውስጥ ነከርኩት::

«አቆየው ውሐ ውስጥ፣ ይሙቅ፣ ይፍታታ» አሉ ሃምሳ አለቃ ኩስተር ባለ ገፅ::

«ያቃጥላል?» አለች ሴትየዋ

ራሴን እግድም ሁለቴ ነቀነቅሁ::

«እና ይሙቅ ደግሞ......ጥፋተኛዋማ እስዋም ናት» አሉ ሃምሳ አለቃ::

«ደ'ሞ ምን አጠፉች በሉ?» አለች ሴትየዋ

«ፊት እያሳየችው ነዋ»

«ኸረ ተው እባክም! ሰው የሚፈጥረው ነው»

«ብልጥ ልትሆን ወዳጅዋን ልታስቀናው»

«ምን አገናኟቸው?»

«ቀረብ፣ ሸሸት እያለች ብታስቸግረው ነው እንግዲህ»

«ግምት ነው እባክዎ» ስለራስዋ የምትናገር መሰለኝ::

«አንድ ቀን አብራው አድራለች አሉ»

«በሉ ተውኝ የማይሆን......እሱ ይሄን ቢያስወራስ»

«ከዚህ ከወዳጅዋ ጋር አንድ ሰሞን ተኩራርፈው ነበር»

«እሱም ወሬውን አምኖ?......ለምን ታዲያ ከግራዋው በኋ 'ሳልገለው' አለ»

«ምን የሴት ነገር ይታወቃል» አሉና አምሳ አለቃ ከተቀመጡበ ተነስተው በቁማቸው አረቄ ጠጥተው ወደ እኔ መጡ::



@BOOKALEM

«እስከአሁን ጥሩ ሆኖ ሳይዝናና አይቀርም» እግሬ የወለመኝን ቦታ ነካ ነካ አደረጉ:: ቤቱ ዝምታ ነው::

በአገራችን ምን የሚባል ተረት አለ:

«ሰበይቲ ዝአመነ ደበና ዝዘገነ ሐደ እዩ!! 'ሴት ያመነ ደመና የዘገነ' ማለት ነው»

«ይሔ ተረት ሴት ፊት አይወራም» አለ ግርማ::

«ሽረ ይቅር በሉኝ ነገር አሳምራለሁ ብዬ ነው እንጂ......እግር ጥገና እንጂ አፍ ጥገና አልመጣሁ መቼም» አሉ አምሳ አለቃ::

እጃቸው ያየሁት ሀይነት ሸካራ አይደለም:: እግሬ ላይ ሲያሳርፉት ጠንካራነቱ ይጠፋል:: ፊታቸው አተኩረ:: በዚህ ለስ ባለ ምሽት በትንሹ ላብ ላብ ይሸታሉ:: ዊማቸው ይሆናል......በጠላ ረጥቦ እንደ ባና ሲተነፍግ:: እጃቸው እግሬ ላይ በቀስታ እየተንሸራተተ ከፍ ዝቅ ይላል::

«ምን ስታደርግ ተሰበርክ አሉ?» አሉኝ

«ሠላማዊ ሰልፍ»

«እ......ሠላማዊ ሠልፍ»

«ለምንድነው ልጂ?» አዩኝ:: ዝም ማለቴን ሲያዩ ቀጠሉ: «ሠልፉን ማለቴ ነው»

ምን እንደምመልስ አላወቅሁም:: የጠየቁኝን ከመመለስ ይልቅ ሠላማዊ ሠልፉ መሐል የተሰማኝን ደስታና የሚጣፍጥ የስካር ስሜት ብነግራቸው ደስ ይለኛል:: ታዲያ መሠለፍ ትክክል ያልሆነ ጉዳይ ከሆነ ለምን ደስ ይላል:: ስሜቱ ደስ ካለ መነሻውም......

«እኔ እንኳን ሳሽ ብዙ አላሳምምም......አይዞህ......ስጠይቅህ አልሰማህኝም?»

«እ......ሰምቻለሁ»

«ታዲያ»

ግርማና ሴትዮዋ በዝምታ ያዩናል::

«የእንዳልካቸው ካቢኔ እንዲወርድ» አልኩ::

«ምን አደረገ አሉ?»

«ያው እንደሊሉቱ ነው፤ 'ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም' ይል የለ ተረቱ»

«መቼ ታየ? እውነቱን ነው:: ማነው ጉልቻ? ማነው ወጡ? እኔ ቦተሊካ አላውቅም......ግን አንድ ሰው መታየት አለበት:: ቁምነገረኛነቱ



@BOOKALEM

መታየት አለበት:: ጊዜ ያስፈልጋል:: በወር በሁለት ወር የአገር ሰው አይለካም:: እንደው በደሙ፣ በዘሩ......»

«አገሪቷ በዘር ነው የምትገዛው» አልኳቸው አቋርጬ::

«ተወኝ:: መልከፄኛ አበረኛ ነው»

«ምን ማለት ነው?»

«ቆንጆ ነገር እንከን አይጠፋበትም እንደ ማለት ነው»

ዝም አልኩ:: መከራከር አልፈለኩም::

«ቅባት አለሽ የእኔ ልጅ?» አሉ

ቶሎ ተነስታ ወደ ጓዳ ገባች::

«አሁን ያለው አስተዳደር ጥሩ ነው ይላሉ እርስዎ?» አልኩ እየፈራሁ እየቸርኩ::

የታመመ እግሬን ይዘዋል:: ምናልባት የማይወዱትን ነገር ተናግሬ እጃቸው አውቀትም ሳያውቀው በሃይል ቢጨምቀኝ......

«የሚረባስ አይደለም......የኖርንበት አይደል:: በዚህ ዕድሜዬ አገሬ የሰጠችኝ ነገር ሠካራምነት ነው:: ይኼን የወጌሻ ሙያ የሰጠኝ እግዜር ሰው እንድረዳበት ነው......ገንዘብ እንዳገኝበት አልነበረም:: ገንዘብ አስከፍዬበት ገንዘቡም ለጠላ ነው:: ያለዓላማህ የሚያሰራህ ዘመን ነው ያለው:: አንዳንዴ ምን እንደምመኝ ታውቃለህ? ዕውነቴን ነው ስክሬ አይደለም:: ትንሽ ራብ ሲለኝ ዱቤ መጠየቁ ሲያበሳጨኝ......ምናለ የአዲስአባን ሕዝብ እግሩን በሰበረልኝ እላለሁ:: ወድጄ አይደለም:: ለራሴም ይገርመኛል» አሉ::

እግሬን ትተው ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ:: ታጥፎ የነበረ ወገባቸውን የመለሱት ከተቀመጡ በኋላ ነው:: እኝህ ሰውዬ በዕውን አርጅተዋል::

«ለእኔ ተማሪ ሙኾ የትም የሚደርስ አይደለም......መድረሻ የለውም» አሉ::

«እንቱ ደ'ሞ ምን ያውቃሉ?» አለ ግርማ::

«ተይ ሐይለሥላሴን ቀላል አረግሻቸው?»

«ምን ይታወቃል?......እሱ የማያመጣው የለም»

«የእግዜር መንግስት ነው......እኛ በየበረሃው እየዞርን የተዋጋንላት አገር......ምንም አላደረገችልንም:: ድሮ ድሮ የግብር ጠላና ጠጅ ይጠጣ ነበር:: ዛሬ ጠላዬን እየከፈልኩ ነው የምጠጣው»

«የት ነው የተዋጉት እርስዎ?» አለ ግርማ::



@BOOKALEM

«ሸዋና ወሎ በረሐ……አታቅም እንዴ?……ጠላ ቤት አትዞርም ለካ ……የእኔ ጋዜጣ ጠላ ቤት ነው»

«ዕውነት የት ተዋጉ?»

«በጣሊያን ጊዜ……ሌላ ዝባዝንኬ ከማወራችሁ ነገር ዓለሙን ያስጠላኝን ጉዳይ ልንገራችሁ:: እንግዲህ ሲመሽ፣ ሲመሽ ነው ከቦታ ቦታ የምንሔደው:: ሁልጊዜ መልካ መንደር አለች የምናልፍባት:: ጣሊያን ወሬ ይደርሰውና ይኸቺን መንደር ወርዶ……ያቃጥላትና የሞተው ሞቶ የተረፈውን ሰው ነድቶ ኤፌሶን ያግዘዋል:: እንግዲህ እኛ አልያዝ ብለነዋል:: የሸፍታ አለቃችን አበበ የሚባል ነው:: እግሩ አያርፍም:: የሸፍታ ዱካ ነፋስ ላይ እንኳን መቅረት የለበትም እያለ……እንዳንከ ራተተን ነው:: ልብስ አይለወጥ……ቡቱቶ ነው……ፀጉሬ እዚህ ትከሻዬ ነው:: ተባይ እንደ አመድ እናራግፋለን:: በላይ በላዩ ሲገኝ ቅቤ ይመረጋል:: ይሔ አበበ ያልኳችሁ አለቃችን ከጣሊያን በፊት ባላንጣ አለው:: ይሔ ባላንጣ እዚህች መልካዋ መንደር ይኖራል:: እንደው ጊደኞቹ ያሳብቅብሃል ብለው ቢነግሩት……ናንቆት ቆየ:: አሁን (*ሙሐመ እየበረደ ነው……እግሬ ትንሽ ይጠዘጥዘኛል*)……ቆይ እያሽሁህ ላውራ መሰል……ቅባቱን አምጪው……አሁን ይኸቺ ሠፈር ስትወረር የአለቃ ችን ባላንጣ ኩረም ለጉዳይ ወጥቶአል:: ሲመለስ ሁሉ ነገር ተገለባብጦአል……ሚስቱ፣ እናቱ ሁለት ልጆቹ ኤፌሶን ተግዘው ደረሰ:: እግሩም ሳያርፍ ኤፌሶን ደርሶ ከጣሊያኖች ጋር ይስማማል:: 'ሽፍቶቹ የሚያድሩበትን አሳያችኋለሁ፣ ቤተሰቤን ልቀቁ ይላል' የተደበቅንበትን ቦታዋን ዘርዝሮ ይነግራል:: እኛ ደፍሮ ሲያሳብቅ መሔዱን ስንሰማ አለቃችንን ነገርነው……ብልጥ ነው……አውሬ……ወሎ ወጣን:: ያም ሰው ቤተሰቡን አስመለሰ:: ጣሊያን ተዋጊ ይዞ የተደበቅንበት ሲመጣ አልተገኘንም:: ይኼን ቃል የገባላቸውን ሰው አስፈራርተውት ይመለሳሉ:: ያደረገው ተሰምቶ፣ ሁሉ አውቆት ባንዳ ተብሎ ሲሰደብና (*እየተጫኑኝ ማሸት ጀምረዋል……ቅባቱን አልፎ የመዳፋቸው ሸካራ መልክአመዳፍ ይሰማኛል*) ጣሊያኖችም ሳይነኩት ይቆያል:: አንዲት ቀን ሌሊት እዚያች ሠፈር እንደተኛ ወደቅንበት:: ለፈለፈ:: ለፈለፈ:: መሪያችን ልግደለው ቢል……ቤተሰቦቹ እየወደቁ እየተነሱ ለመኑ:: ሁለተኛ እንዳይደግመው አስፈራርተን ቆላ ወረድን:: ያኔው ሌሊት እግራችን ዞር እንዳለ ኤፌሶን ወዲህ ሔዶ ለሰልዳቶ ይነግርና ጦር መርቶ ይመጣል:: እኛ ማስፈራራታችን የሚጠቅም መስሎን አገር ሠላም ብለን ጉጆአችን ውስጥ እንደተኛን ግማሻችንን አጠፉን ……ጥቂት ሆነን አምልጠን ደንከል ገባን:: ጉልበታችን ደክሞ ተበታትነን:: እኔ ስቆጣ ወጣሁ……እናቴ አገር……አለቃችን አባይን ተሻግሮ በላይ ዘለቀ

ገባ፣ የቀሩት እዛው ሸዋ ቀሩ:: ሰቆጣ አርፌ እያረስኩ ልቀመጥ ፈልጌ ይኼ ሽፍትነት፣ ልጅነት ሆኖ እዚያው አርበኛ ሆንኩ:: (*ትንሽ ሙሀኩ*) አይዞህ:: እንግዲህ ከርሞ ንጉሱ መጡ ተብሎ እኛም ወንዶች ተብለናል አዲስአባ ተያይዘን ገባን:: ማደሪያም አልነበር......እዚህ እራዳ ስንከራተት ቆየሁ:: የዚያን ጊዜ ሰው ሰው አይምሰላችሁ:: ቅዱስ ነው:: የአርበኝነት ታሪኬን እያወራሁ በቀፈፋ አመት ኖርኩ:: ተሰላቸሁ:: ተቀጥሮ በገንዘብ መስራት አልወደድኩም:: ሰቆጣ ወጣሁ:: ከርሞ ከርሞ አርበኛ የነበራችሁ ለአገልግሎታችሁ መሬት መጠየቅ ይቻላል ስለተባለ እንደው እንዲህ ወደ ታች ጅማ ወይ ወደ ባሌ መሬት ላገኝ ብዬ ከሰቆጣና ከሸዋ አርበኝነቴን አስመስክሬ መምጣት ፈለግሁ:: እርሻ እወዳለሁ:: ከእርሻ ቀጥሎ ሽፍትነት እወዳለሁ:: ከእርሻ ሌላ ክብር ነገር የለም:: ከሰቆጣ ወረቀቴን አፅፌ አስመስክሬ የተቀረውን ከሸዋ ለመውሰድ ሸዋ መጣሁ......የሚመሰክረው ማን ሆኖ አገኘሁ ያ ባንዳ:: ሊያናግረኝ ኩራ:: ሊያናግረኝ:: ተስፋ ቆረጥኩ:: አገሬ ከዚያ በኋላ እንደ ቀድሞዋ እንዳልሆነች አወቅሁ:: ያም የቀናው የጊዜው ሰው ጥቂት ቀን ደጅ አስጠናኝ......እኔ ኩሩ ነኝ ወግድ ብዬ የሰቆጣ ወረቀቴን ብቻ ይዤ አዲስአባ ገባሁ:: የአርበኞች ቀን እየተባለ በዓል ሲሆን ዳር ሆኜ ሠልፍ አያለሁ:: ሁልጊዜም እሔዳለሁ:: አንዳንዴ መረር ሲለኝ ይቆጨኛል:: እግዜርን ለምን ኩሩ አደረከኝ እለዋለሁ:: አዲስአባ ኩራት ጠፋ:: ሁሉ ነገር ገንዘብ ነው:: አዲስአባ አገር ለገንዘብም ይሸጣል:: እውነቴን ነው:: ሰው ለሰው ካልተጣላ፣ ሰው ለአገሩ ካልተጣላ እንዴት ለገንዘብ ይጣላል? አዲስአባ ሰው የለም:: ሰው ጠፍቶአል:: እኔ እራገማለሁ እንጂ ሰው አይደለሁም:: ታዲያ የኢፈሶን ፈጣጣ ባርላማ ሊመረጥ ተፎካክሮ ነበር አሉኝ:: አልቻለም:: ኩሩዎች ሞተው ሲያልቁ እሱ ባርላማ ይመረጣል:: አይቀርም:: እሱ ብልጥ መሆኑ ነው:: ከነፈሰው ጋር መንፈስ»

የቀረችዋን አረቂያቸውን በአንድ ትንፋሽ ዋጡ::

«እንዲህ አልነበርኩም አዲስአባ ስመጣ......ግንባሬን ዐይቶ ዐይኑን የማይሰብር አልነበረም:: ዛሬ ስሜ ጠፍቶ 'ሽሜ' እባላለሁ:: 'ሽሜ' ሆንኩ:: ገበሬ አይደለሁ:: ምን አይደለሁ 'ሽሜ' 'ሽሜ ጉጉ፣ ሳሩን ስጠው ለበጉ'::አንዳንዴ መሬት ብትውጠኝ ደስ ይለኛል:: እንዳንዴ ምኝ ስለሆንኩ ነው እንዴ? እላለሁ......»

«አረቄ ልጨምርሉት?»

«ደግ:: አሁን ይሔ እግርህ ይበቃዋል:: እንዲሞቀው የሆነ ነገር ጠቅልሉበት...... ጨርቅ አለሽ? (*ሴትዮዎ ወደ ጓዳ ገባች*) ይሔ ልጅ ዘመድህ ካልሆነ ምንህ ነው?......»

«አላውቀውም»



@BOOKALEM

«ምን አልክ?»

«ከፖሊስ ለማምለጥ እዚህ ቤት ገባ እዚህች ቦታ ላይ ተመታ:: ራሱን ስቶ ብዙ ቆየ......ሲሻለው ይሔዳል ብለን አስቀረነው»

«ተባረኩ»

ከተቀመጡበት ተነስተው:

«እሰይ:: እንዳንተ አይነቱን ነው ንጉሥ ማድረግ»

«ሃ ሃ ሃ......ለነፍሴ ነው የእኔ አባት......ንጉሥ ለመሆን አይደለም»

«ልቡ ያልጨከነ አለ አሁንም? እግዜር ለዚህ ይሆናል የማረን?»

«እንዴት?»

«ጥቂት ደግ ቢያይ ነው የማረን:: እግርህን ጋደም ብለህ ዘርጋው:: ተባረኩ» ሴትዮዋ ጨርቅ ይዛ መጣች:: ረዥም ጠርዞቹ የነተቡ አሮጌ ፎጣ ነው::

«ንፁሕ አይደለም......ቢሆንም ያሞቃል»

በፎጣው ያፈረች ትመስላለች:: ተቀብዬአት እራሴ ላስረው ብሞክር እምቢ ብላ እራስዋ የተሰበረው እግሬ ዙሪያ መጠቅለል ጀመረች:: ስትጠቀልለው የሚቀዝፈው አየር ወደ አፍንጫዬ የርካሽ ሽቶ ጠረን ያመጣል::

«እምሳ አለቃ ለምን ራት በልተው አይሔዱም? ቤት ያፈራውን»

«እኔ በልቻለሁ......ዳቦ የመሰለ ሽሮ ዕፀንት ቤት በልቼ ነው የመጣሁት»

«ደኸና ናት እስዋ»

«ገንትዬ? ምን ትሆናለች ደኸና ናት»

«ምን ቅርብ ሆኖ መገናኘትም የለ:: እሷ እኮ ባለውለታዬ ናት»

«ምን ውለታ?» አሉ ሽማግሌው::

«ተአገሬ ስመጣ ቤት አፈላልጋ እዚህ ያስገባችኝ እሷ ናት»

«ዘመዴ ናት በይኛ ታዲያ»

«ጥሩ ሴት ናት» ወደ ጓዳ ገባች:: ቤቱ እየበረደ መጥቶአል::

«ተአርባ ምንጭ ነው መጣሁ ያልሽኝ?»

«አዎ»

«አርባ ምንጭ ማንን ታውቂያለሽ?»

«ተረስቶአል እባክዎ»



@BOOKALEM

በባዶ መለኪያ ይጫወታሉ:: ግርማ ሊጨምርላቸው ቢፈልግ እምቢ አሉ::

«ተው በቃኝ......የጠጪም እኮ ወሰን አለው ሙት......መሸ ልሂድ እኩለ ሊሊት ሊሆን ምንም አልቀረው»

«ትንሽ በልተው ይሂዱ ፀሐይ ስትወርድ የበሉት ሆድ አይቆይ እስከአሁን»

«ጠላ ነው የጠጣሁት:: የበቴ ጠላ እኮ እንጀራ ነው:: ገብስ ነው:: ሰውነት ነው የሚሆን»

«ቆዩ እሺ መጣሁ»

«ድ'ሞ ምን ጉዳይ አለ?»

የሚከፈል ጥቂት ገንዘብ እንዳለኝ ለሽማግሌው ነገረቻቸው::

«አንተ በጥጋብህ አልተሰበርክም:: ለዓላማ ነው ልጄ:: ቢረባም ባይረባም ለዓላማ ነው:: እኔ ጥጋበኛ፣ የሚያደርገውን ያጣውን ነው የማስከፍለው:: ለሻይ ይሆንሃል:: እኔ ብወስደው ጠላ ነው የምጠጣበት:: ሆዴን ሞልቼ ማደሬ አይቀርም:: ሁሉን አየነው ልጄ......ሞት ነው የቀረን......ሞት ደ'ሞ ይፈራኛል:: ህይወቴን በሙሉ ስኖር ሞት እንደ ሸሸኝ ነው:: ይርቀኛል»

«ሞት ይመኛሉ እንዴ ደ'ሞ» አለ ግርማ

«ሞት ሐብት ነው ለእኔ»

«ይተዉ እንዲያ አይበሉ»

«ምን ቀረኝ ልጄ?......ሆዴና ቅልውጥና ናቸው......ልጅ የለኝ......የልጅ ልጅ ልይ አልል፣ ሚስት የለኝ......ሰው አለብኝ አልል:: የምረዳው የሚረዳኝ ዘመድና ልጅ የለኝ......ናፍቆት አልል:: ምን ቀረ? ሰድሜውን ኖርኩት:: እንደ እናንተ አይነቱ ሳይጠፋ፣ የሚቀብር ሳይጠፋ ቶሎ መሄድ ይሻለኛል:: እንዲህ ዐይነቱ ኀረምሳ ነው ወደፊት መኖር የሚገባው:: ገና ብዙ አላየ:: እኔ በቃኝ:: ጉዞዬ አብቅቶአል:: አንድ መኪና ፍሬኑ ከተያዘ በኋላ ሸርተት ይል የለ......የቀረችኝ መንገድ የዚያ ዐይነት ናት:: ሸርተቱ ነው የቀረኝ:: አሁን ልኑር ልኑር ይመርብኝ ብለው የሚተርፈኝ ልፋት ነው»

ቤቱ ጭር አለ:: ከጊዳ ባህኖች ሲንኳኩ ይሰማል:: ሽማግሌው ትንሽ ሲተክዙ ቆይተው ፀጥታው ያባረራቸው ይመስል ተሰናብተው ወጡ::

እታለም አልጋው አጠገብ ሰባራ ጠረጴዛዋን አስቀምጣ ግርማ አግዳሚ ወንበሩን ስቦ ለራት ተቀመጥን:: መሃላችን ያለው ትሪ ከዳር እስከዳር በተዘረጉ ሁለት እንጀራዎች ተሸፍኖአል:: ሆዴ ጮኸ:: የሰሙብኝ መሰሉኝ ቀና አልኩ:: ሰውዬው ዐይኖቹ ማዕዱ ላይ ናቸው::



@BOOKALEM

ወጊሻው ተናግረውት የሄዱት ነገር ድብርት የቀሰቀሰበት ይመስላል:: እታለም ወጥ ለማውጣት ጭልፋዋን ድስት ውስጥ አስገባች:: ወደ ላይ ስትስበው ጢሱ የሚትጉለጉል በክክ የዳበረ ሽሮ ወጥ አወጣ:: ሰሐኑ መሐል ላይ እንደ ሊጥ ዱብ አደረገችው::

«በል እንግዲህ ብላ ቤት ያፈራውን» አለ ግርማ:: ሽማግሌው ሲያወሩ በፀጥታ ሲያዳምጥ የነበረ ሰው አይመስልም:: ድምፁ የሚያዝ ይመስላል:: እንዲሰማ የሚያስገድድ ይመስላል:: በእፌ የሞላውን ምራቅ ውጬ......ያልታጠበ እጄን ሰደድኩ:: እነሱ ታጥበው እንደሆን አላውቅም:: በርበሬው እንደሚጥሚጣ ነው:: ሽሮው አፍ ውስጥ ቦታ ይይዛል:: የእንጀራው ውፍረት እንደርብራብ ከባድ ነው::

ጥቂት ጊዜ ከበላላን በኋላ ግርማ ሳል ስሉ ወሬ ጀመረ::

«ስሚ ያ ሰው ምን ሆኖ ነው ብርጭቆውን የሰበረው?»

«ጥጋብ ነዋ»

ትክ ብሎ አያት::

«ምነው አየኸኝ?......ምን አሰብክ?» ወደ እኔ ገልመጥ አለች::

«የመራሽው ነገር ቢኖር ይሆናል» አለ ግርማ

«ምን እመራዋለሁ......ነገር ፍለጋ ነው እንጂ:: ያሰበው ነገር ካለ አይናገርም? ይኸው ልጁ አልነበር እዚህ» ሰውዬው አየኝ::

እንደመሸኰርመም ሳቅሁ:: ለምን እንደሳቅሁ፣ ለምን እንደ ተሸኰረመምኩ አላውቅም:: ምናልባት በክርክራቸው መሐል ባለጌ ጉዳይ እንዳለበት ስላወቅሁ ይሆናል:: ቶሎ ብዬ:

«ሰውዬው ጥሩ አልሰራም» አልኩ::

«ፊት ካላሳየሽው ለምን ይደፍርሻል?»

«ባለጌ የሚሰራውን ያውቃል እንዴ አንተ ደ’ሞ:: እምጣ አለቃ የተናገሩትን ሰምተህ እንደሆን ለእኔ አይሰራም:: በቀለችን አይደለሁም:: አታምነኝም?»

አበላላችን ሁሉ ቀስ ብሎ-አል:: ስንጀምር የነበረው የረሐብተኛ ችኰልነት ጠፍቶ::

«ነገ እንጋግረዋለሁ» አለ ግርማ

«ተው እረፍ......ጥሩ አይደለም»

«እዚህ እንዲደርስ አልፈልግም»

«እኔ እነግረዋለሁ»

«ዕቃሽን ሰብሮ ታስገቢዋለሽ?»

«መምጣቱ አይቀር»



@BOOKALEM

«ምን ጉዳይ አለሽ ከእሱ?»

«እንድትጣላ አልፈልግም:: የእኔን ጣጣ እኔ እወጣዋለሁ»

«ከመቼ ጀምሮ ነው ብቻሽን የሆንሽው:: የአንቺ ጣጣ የእኔ ጣጣ ነው ......የእኔ ጣጣ የአንቺ ጣጣ ነው»

«በእኔ ተጣላችሁ እንዲባል አልፈልግም:: ሲጣሉባት የተከበረች የሚመስላት ሴት አይደለሁም:: እንዲት ፀጉርህ እንድትነቀል አልፈልግም......በንትርክም ይሁን በአምባጓሮ»

«እሱ እንኳን ፀጉሬን ዝንቤንም አያባርርም»

«ተወው መምጣቱ አይቀርም:: እዚህ ጠጪ ፊት......ቅዳሜ ሰው ይበዛል ......ልኩን ነው የምንነግረው»

«እንዲህ አይነቱን ሰው ማስፈራራት ይፈልጋል:: ሰው እንዳይንቅ ማስተማር ነው»

«ማነውና ምን ይንቃል:: የተናቀ ቶሎ ብሎ ናቂ ይመስላል:: ሌላ በመናቁ ብቻ ሰው የሆነ ይመስለዋል......ቅዳሜ ግን እዚህ እንዳትሆን:: ከፈለግህ ጎረቤት ሁን»

«ይሔ ሁሉ ምንድን ነው? አሁን ቤቱ ሔጄ......`እረፍ' ብለው እዚህች ዝር አይልም»

«ተወው አልኩህ ተወው......እሱ ወንድ አያስፈልገውም:: ነገረኛ በነገር ነው የሚመለሰው......ወንድ አያስፈልገውም:: ሚስቱን ይብላኝላት»

እጅዋን አወዛወዘች:: ትንሽ ጣቷ ላይ የተንጠለጠለች ሽሮ የለበሰች የእንጀራ ጓል ማሰዱ መሐል ወደቀች:: በችኮላ ለቀመቻት::

«በይ እንዳልሽ......ጠንቀቅ በይ»

«ስምህ ማነው አንተ? አመለጠኝ ቅድም» አለችኝ ከመሃል:: ነገርኩዋት::

«የየት አገር ልጅ ነህ?»

«አዲስአባ ነው የተወለድኩት»

«እዚህ አዲስአባ?»

«አዎ»

«የጎሙጎፋ ልጆች አሉ ትምህርት ቤታችሁ?»

«አሉ መሰለኝ»

«ታምሩ የሚባል ታውቃለህ?......የትኛው ጋ ነው የምትማረው?»

«ስድስት ኪሎ?»

«እሱ መሐንዲስ ነው የሚማር:: ጎረቤታችን ነበር»



@BOOKALEM

«በጣም ጥሩ ልጅ ነው» አለ ሰውዬው::

«ሌላ ቀን ብቅ ብትል ምናልባት ብትገናኙ አስተዋውቃችኋለሁ»

«ልጁ ሰው ይወዳል:: እዚህ እሷን ለመጠየቅ ሲመጣ......አምስት፣ ስድስት ሆኖ ነው:: ደስ ማለታቸው»

«እዛም እያለ የማይወደው ሰው አልነበረም:: ትሁት ነው......ኸረ እናቱን ብታያት:: ደ'ሞ ዐይናችን ሥር በአንዴ ነው ያደገው:: እኔ ከመጣሁ ከሦስት አመት በኋላ ይሆን የመጣው እቴ?» ሁላችንንም ጠየቀችን::

«አባቱ ሊያስታርቁን ነበረ እኮ ከባለቤቴ ጋር»

«ኸረ እባክሽ?» አለ ሰውዬው

«እህ:: አንዴ እዚህ ድረስ መጥተው:: አልነገርኩህም? እዚህ አዲስአባ ውስጥ ወደ ጃርት ከተለወጥኩ ያኔ እመጣለሁ...... አለበለዚያ ሰው ሆኜ ግን ያን ሰው አልችለውም አልኳቸው»

«ምን አሉ?»

«ምን ይላሉ! ሣቁ......»

«ደስታ ከየት እንደሚመጣ የሚያውቅ ጥቂት ሰው ነው» አለ ሰውዬው ወደ እኔ እያየ::

«ገንዘቡንም ክብር የሚባለውንም አይቼዋለሁ......ስላልተናኘ ይሆናል...... ለእኔ አልሆነኝም......ምነው አትበላም አንተ ልጅ አልጣፈጠህም መሰል?» አለች ቢትየዋ::

«ኸረ በላሁ:: በጣም ነው የበላሁት»

«ዋሸህ......የራሳችንን ወሬ ያዝንብህ?»

«ኸረ ግድየለም......ጥሩ ነው» አልኩ::

«ይኸውልህ ጎሙጉፋን ከመሰለ አገር ሐብታም ባልዋን ፈታ መጥታ እዚህ......(የቤቱን ጣሪያና ግድግዳ እያየ)»

«ምን ጉደለ?» አለችው እንደ ቁጣ::

«ጉደለ አልኩ?» አለ እየሳቀ

«ማለትህ ነው እንጂ ሐብት ከጭቅጭቅ ጋር ምኑ ያስደስታል ......ባለገንዘብ መሆን ያስጨክናል እንዴ? የሚሰራው አንዳንድ ነገር የሚገርም ነበር......ሰው ማስገረፍ፣ የሰው ጉዳይ ማበላሻሸት፣ እግዜር የሰጠውን መንሳት:: ምን ይባላል? የዚህ ዐይነት ሰው ሚስት ሆኜ ያን ገንዘብ ከምበላ፣ ከምጠጣ ቢቀርስ:: ደም መሆን ነው የሚቀረው:: ስሙስ? እዚህ ምን አለብኝ:: የራሴው ጌታ ነኝ......በራሴው ሐጢያት ነው የምጠራው:: 'የዚያ የጨካኙ ሚስት' መባል ራሱ መከራ ነው::



@BOOKALEM

በባሌ ጠባይ ልጠራ እንዴ? `እታለም` የሚል የለም:: ከጨንቻ አርባምንጭ `እታለም` የሚለኝ አልነበረም»

«እንዳላየ ሆነሽ መብላት»

«አይ እቴ ተወኝ......አሁን ብሔድ ትወዳለህ?»

«አሁን ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ ነው»

«ለምን እንዲቆጨኝ ትለፋለህ? ወይም ለማድረግ ትሞክራለህ? እኔ ደ`ሞ አይቆጨኝ»

«እንዳንዴ አይቆጭሽም?»

«ትዝም አይለኝ......ልጁ ትዝ ትለኛለች......እሱ ሌላ ነገር ነው»

«ለመሆኑ ሰምተሽ ታውቂያለሽ ስለ እሷ?»

«ያው አውቶብስ ግቢያ ወረቀት እልካለሁ......ይድረሳት አይድረሳት አላውቅም......'ደረሳት' ይሉኛል» ቀጠለች:

«ማሰዱን ሳንሳው......ጡር ነው......እህል ዘርግተን ወሬአችንን ስንቀጭ» ማሰዱን ይዛ ተነሳች:: ሰውዬው አጠገቡ የነበረ ግሳ አንስቶ እጁ ላይ ውሐ እያፈሰሰ እግሬን ዘፍዝፌበት የነበረው ሳፋ ውስጥ ታጠበ:: እኔን እንድታጠብ ጋበዘኝ:: ደስ የሚል ለስ ያለ ውሐ ነው::

«አሁን መተኛችንን ብናስብ» እያለ ግርማ ከተቀመጠበት ተነሳ...... ግሳውን እንደያዘ ወደ ጓዳ አለፈ......ግሳ መያዙን የረሳ መሰለኝ:: ሁለቱ ይንሾካሾካሉ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሶ መጣ::

«ፍሬው መቼም እንግዳ ነህ ሕመምተኛ ነህ......ሕመምተኛን ማጉላላት ደግም አይደል:: (*ተቀመጠ*) አንተ አልጋው ላይ ትተኛለህ» መልሴን ልናገር ስል ይዘቱን ገና ከፊቴ ላይ አንብቦ:

«ጥሩ አይደለም......እንግዳ መስማት አለበት:: እግርህ ሙቀት ያስፈልገዋል......እንዲሻልህ አሳድረን እንጂ አብሰንብህ አንሰድህም:: እግዚአብሔር ምን ይላል? ትዕዛዝ ነው እንግዲህ»

መቀበል ከበደኝ:: በጣም ከበደኝ::

«ለእኛ አታስብ......ለአንድ ቀን ምንም አንሆንም:: ከፈለግህ ልብስህን አውልቅ፣ ካልፈለግህ......» ወደ ጓዳ ተመለሰ:: እጆቼን ያስታጠበበትን ግሳ እንደያዘ ነው:: ልብሴን አውልቄ መተኛት ይታወቃል......ጭርት፣ ቋቁቻ:: ጭርት እንኳን አይጋባም:: የሴትዮዋ የእግር ቆሻሻ ያስፈራል:: በጀርባዬ አልጋዬ ላይ ተጋድሜ የአተኛኘት ፖሊሲ አወጣና አወርዳለሁ......

*ከነልብሴ እተኛለሁ ካልኩ:*

ሀ) የልብሴ እድፍ ከሰዎቹ ሰውነት የተሻለ ንፅሕና አለው እንደማለት ነው---በአቋራጭ::

ለ) በአንሶላ መሃል ተገብቶ የሚተኛበትን አልጋ ወደ ማረፊያ እንደ መቀነስ ነው:: ለምሳሌ......ጉዞ ላይ ሲደከሙ መስክ ላይ እንደሚተኙት::

*ያለልብሴ ከተኛሁ:*

ሀ) በሽታ ቢይዘኝስ ለምሳሌ ቋቁቻ፣ ቾፌ፣ የሆነ ቁምጥና......

ለ) ቢሻክረኝስ፣ ቢቀዘቅዘኝስ......

ሐ)የሆነ ነገር ቢሽተኝና ደጋግሜ ብባንንና......ሳይነጋ ቢያስመልሰኝስ::

ይሔን 'ዝባዝንኪ' ሳስብ.....ዕቃውን አነሳስተው መሬት ማንጠፍ መጀመራቸውን አላየሁም:: ዞር ብለው፣ ቀና ብለው ልብሴን ማውለቅ እንኳን አለመጀመሬን ሲያዩ ከመጠየቃቸው በፊት አፋቸውን ለማስያዝ ጃኬቴን አውልቄ ማስቀመጫ ቦታ ስፈልግ (ቀስ እያልኩ ነው የማወልቀው......ቅጥቅጣቱ ትከሻዬ ላይ ያለ ይመስል) ካልጠበቅሁት አቅጣጫ መደገፊያ ያሳት ደቃቃ የእንጨት ወንበር አጠገቤ መጥታ ቆመች::

«እዚህ አስቀምጠው» አለ ግርማ እየሳቀ::

መሬት አትተኙ ያልኳቸው ለትህትና ሳይሆን አልጋቸውን ስለፈራሁት እንደሆነ የሚያውቁ መሰሉኝ በፍርሃት......በወንጀለኛነት ስሜት ልብሴን አወላልቄ (ከካናቴራዬና ከሙታንታዬ በቀር) አልጋ ውስጥ ገባሁ::

አልጋው የሚቀፍ ስሜት ይሰጣል......አንሶላዎቹ በጣም ስላረጁ ይበርዳሉ:: ትራሱ ትንሽ ይጠጥራል:: በመጀመሪያ ፊቴን ማስደገፍ ፈርቼ በጀርባዬ እንደሆንኩ አንዳንዴ መተኛቸውን ሲያነጥፉ፣ አንዳንዴ ምንም ነገር የሌለበትን ጭስ ያጠቆረውን የቆርቆሮ ጣሪያ ሳይ ቆየሁ:: ሰውዬው ዝምታውን በሳል ሰበረና ለእታለም:

«አንቺ ያ ሬዲዮ እንዲሰራ ከወሰድሽው አስራ አምስት ቀን አልሞላውም?»

«ያልሆነ ዋጋ ጠየቀኝና የሚሻል ስሪ አስካገኝ ብዬ ተውኩት»

«ለምን አልነገርሽኝም?»

«የእኔ ሬዲዮ እኮ ነው»

«ምን ያህል ጠየቀሽ?......ስታደርቂ»

«አሥር ብር......ለአንድ አሮጌ ሬዲዮ አሥር ብር»

ግርማ የመሬት አልጋው ላይ ተቀምጦ ዝም አለ::

እዚህ ቤት ውስጥ ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር ብዙ ወሬ የለም:: የሚወራው ጉዳይ አላማውን ካጠናቀቀ በኋላ ያለ ዱካ ይሰወራል:: ለረዥም ወሬ አእምሮዬን ከፍቼ ስጠብቅ......ፀጥታ:: ምናልባት ሌላ የለመድኩት የማውቀው ቦታ የዚህ ዐይነት ጉዳይ ቢነሳ ለረዥም ጊዜ ወሬው እንደሚቀጥል አውቆ ከልምዱ ጆሮዬ መከፈቱ......እኔንም ጆሮዬንም ሳያሳፍረን አልቀረም:: ሌላ ቦታ ይሔ ጉዳይ ቢነሳ ይቀጥላል........ይረዝማል.....ይንዛዛል:: .....ካጠረ፣ ካልረዘመ.......ይፈጠራል:: የድሮው አጭር ወሬ አዲስ መረጃ እየገባበት ይወፍራል......ይደነድናል:: ........ፍርግርጉ ይመረጋል.....ይለሰናል......ሲሚንቶ ይደገፋል:: .....በድንጋይ ይታጀባል.....ቀለም ይቀባል......ዙሪያው አበባ ይደረደራል:: ......ሐረግ ይዘምትበታል.....ዕጣን ይታጠናል......ቀስ በቀስ ጉዳዩ ተረስቶ......ታሪክ ሆኖ ሰዎች......ስለሐረጉ፣ ስለአበባው ስለድንጋዩ......ወይም ሐረጉ ላይ ስላሉ ሽረሪቶች......አበባው ላይ ስለሚዞሩ ንቦች......ድንጋዩ ላይ ስለሚንሸራሸሩ እንሽላሊቶች ማውራት ይጀምራሉ::

......ይሔ መርጋት ያስፈራቸውና ነፍሳቸው ያለ ዐላማ የምትቁነጠነጥ ሰዎች ወሬ ነው:: የውሸቱን ግብ እንስቶ ይነሳል.....ዓላማው የመንገርና የመነጋገር ሳይሆን......ተያይዞ በሆነ ነገር ተሳስሮ ብቻ የመቆየት ነው ......አንዳንዱ በየራሱ ዓለም......በሐሳብ እየበረረ ተነጣጥሎ እንዳይጠፋ ከተመቸውም እንዳይሸፍት......ከንፉን ሰብሮ የዝገት ጆጎል ውስጥ የማስቀረት ነው......የዝምታን ኬላ የመቅደድ ብቻ ነው......ከዝምታ በኋላ ዝባዝንኬ ነው......የማይለበስ የወሬ ቡትቶ ነው......ለስላሳ እስር ቤት ነው:: በራሱ ሐሳብ እየጋለበ ሊያመልጥ የነበረ......አዲስ ዓለም ሊያገኝ የቃኘው ሕልመኛ......ግንባሩ ተደርምሶ ላልቶ ይቆማል:: በወሬ መሐል `አንተስ?' ይባላል:: በወሬ መሐል `በል እምጣ` ይባላል......የግሉን `ትንሽ` ደፋ ደፋ አቁሞ......የጋራ እስር ውስጥ ይገባል::

እዚህ ዝምታ ነው......ሰቃዎች እንኳን በየራሳቸው ውስጥ ያሉ ይመስላሉ ሶፊስቶች[23] ናቸው.....ጥላሞት ያላቸው አይመስለኝም......ከራሳቸው በሚነሳው ብርሐን ብቻ የታሠሩ ናቸው......ግድግዳ ላይ በተሰቀሉ መስታወቶች ውስጥ......የማየው ደብዛዛ ሌሊት ነው:: የሚስቅ ፊቷንና ፎቶዋንም እያለሁ:: መሳቂያ ምክንያትዋን የማልጋራው ነው:: ትልቅ ሐብት ነው መቼም ከዚህ ጉድባ እንደተኙ ሰው ሊረዱ እጅን መዘርጋት:: ሚስጢር::

«መጋረጃውን ብዘጋውስ?» አለች ቤትዮዋ......ልብስዋን ለማውለቅ ጀምራ የዐይኔን አቅጣጫ ካጤነች በኋላ:: መጀመሪያ አልገባኝም ነበር:: ራሴ ዘጋሁት::

---

[23] ከግሪክ ፈላስፎች/ከራስ በላይ ነፋስ ፈላስፎች፣ እጅግ ግለኞች

«ሰው ፊት ልብስ ማውለቅ ይከብደኛል» አለች......ትልቅ ችሎታ እንዳነሳት ሁሉ በማዳነቅ::

«ማንም እንዲያ ነው» አለ ሰውዬ::

«ኸረ ተው እባክህ......እዚህ በየደጃፉ አይደለ የሚታጠቡት?» አለች

«ለምድ ያስፈልግ ይሆናል»

ልብሶቻቸውን ሲያወልቁ ይሰማል......የለበሱት ድምፅ የሚበዛው ደረቅ ጨርቅ ነው......ከገላቸው ሲፋተግ፣ እርስ በራሱ ሲፋተግ:: የሰውዬውን ልብስ ኩዋኩዋታ.....ከውጭ መስማት ይቻላል......ከቤተመንግስት እያንቀላፉ መስማት ይቻላል......ስድስት ኪሎ ተቀምጦ መስማት ይቻላል......ከአራዳ መስማት ይቻላል......ከመርካቶ መስማት ይቻላል ......ከባቡር ጣቢያ መስማት ይቻላል:: ይኼን የሰማ......

ከላይ ሰፈር አንዱ: አይ የደሐ ነገር ይላል......

አላፊ አግዳሚ: ቤት እያፀዱ ነው ይላል......

አራዳ: ታች ሠፈር ድንኳን እየተቀደደ ነው ይላል......

መርካቶ: ይሔን ጨርቅ ማን ሸጠ? ይላል

ባቡር ጣቢያ ያሉት ፖሊሶች: ሌላ ረብሻ ሳይነሳ አይቀርም ፈጥኖ ደራሽ ይላክ ይላሉ......

«ፎቅ በል» አለች

«ለምን?» ሹክሹክታቸው የሚፈላ ውሐ ይመስላል

«እንዴ? ምን ትጠይቀኛለህ?»

«አንቺ ደ`ሞ»

«ቦታ አልበቃህም?......ፈቀቅ ብዬልሃለሁ! ትንሽ እንኳ አታርፍም? ጀመረህ......ለመሆኑ ማን ዕደር አለህ?»

«ለማንኛውም ብዬ ነው»

«ምንድነው `ማንኛውም`......እግርህ እንዴት ይበርዳል?»

«እንደ ሬዲዮ አንቴና አልሰበሰበው እንግዲህ......እግር ሲፈጥረው ተንቀርፎ ነው......እንደ ዐይን እንደ ጥርስ አይደለ»

«እንዴት ነው እግርህ?!» ጮክ ብላ

ለእኔ እንደሆነ አውቃለሁ:: ዝም አልኩ:: መናገር አልፈለኩም:: በጀርባዬ እንደተኛሁ ማዳመጥ ነው የፈለኩት......

«ሰማህ?......ተኛ መሰለኝ ልጁ»

«ደክሞት የለ......ምን መሆንሽ ነው?»

«አንተን ነው የማይደክምህ......ይኸቺን ቀን ብትዘላት ምን ነበረበት»

«አንቺ ትዘያለሽ?»

«አንደኛውኑ አትዘፍንልኝም»

«ለአንቺ!......ለአንቺ ስል ማሲንቆ እለምዳለሁ»

«ለማሲንቆው መንበርዬን አልጠራውም»

«እሱ ለማንም......ጠላና ጠጅ ባየበት የሚዘፍን ነው»

«ልጁን እንዳንተሰቅሰው ቀስ ብለህ አውራ»

መብራት ሲጠፋ እሰማለሁ::

ለአጭር ጊዜ ቤቱ ፀጥ አለ......እጅግ ፀጥ አለ:: እንደ አምላክ ቤት......የሰላም ድምፅ ብቻ እንደጠፈጠፍ ከጨለማው ጣሪያ በግርማው ይወርዳል ......ይጫናል:: ንፋስ ከውጭ ቤቷን በቀስታ ይንጣታል......ሰማይ መሃል......መሳዕክት መዳፍ ሥር የገባሁ መሰለኝ......ከዐይኖቼ ጀርባ የማላውቃት ሚስጢር ራስዋን ለመግለጥ......ከለበሰችው ነት ውስጥ ታጮልቃለች:: የማይቆም የማይዘል ወንዝ ላይ እንደወደቅሁ ሁሉ ነው......ፀባየ መልካም ፀባይ ላይ......ሽጋ አዋሽ ላይ:: ያናወዘ ተከዜ ላይ:: ከሩቅ የማያቸው ተራራዎች በፀሐይ ብርሃን ይቀልጣሉ......ዓሦች ከጉኔ ራቁታቸውን ያለ ድምፅ ይዘላሉ:: ውሐው በእርጥብ ሳንባዎች ይተነፍሳል......ከወንዙ ዳርቻ የአጋም ዛፍ ያንጉራጉራል......በከንዶቹ ውስጥ እገባለሁ......እሾኩቹ እንደ ጥጥ አፈን እየዳበሱ ጨለማ የሚመስሉ ፍሬዎች በአፌ ቀዳዳ ይጥላሉ......ደም ስሬ ይታየኛል...... የደሜ ጎርፍ ሲሮጥ ይሰማኛል......ደም ስሬ ውስጥ ከደሜ ጋር እሮጣለሁ......ረዥም......ረዥም ቀጭን ቱቦ ነው......ከወዲያ ጥግ አዲስ ሳንቲም የመሰለች ክብ ብርሃን አያለሁ......አብረውኝ ሰዎች ይሮጣሉ ......አብረውኝ ይሮጣሉ......እታለምም ትሮጣለች......እግሯ አያስሮጣትም ......ሣንቲሙ ይሰበኛል......ቀዳዳው ይሰበኛል......ሁለት ሣንቲሞች ይታዩኛል......ሦስት ሣንቲሞች ይታዩኛል......አራት ሣንቲሞች ይታዩኛል......መዓት ሣንቲሞች ይታዩኛል......ግዙፍ የብርሃን ስሌዳ ፊቴ ይገተራል......አብሮኝ ማንም የለም.....በፍርሃቴ ብዛት......ባነንኩ:: አልቦኛል.........ትንፋሼ ይጋልባል:: ከሩቅ ዶሮ ሲጮህ እሰማለሁ::



@BOOKALEM

ሞላላ ነገር ትዝ አለኝ.........

«ቀስ በል» ትላለች ሲትዮዋ::

«እ»

የትገሮቴን ጣጣ እረስቼ ጆሮዬን አቆምኩ::

ልብስ ሲንኮሻኮሽ እሰማለሁ:: ስልት ባለው ንቅናቄ.......(የውና እዚያ ማዶ ያገዳ ጎገር፣ ፍቅር ገባና ተጀነጀነ) በአንድ በኩል.......የደሜ ጉዞ.......በአንድ በኩል የዶሮ ጬኸት.......በአንድ በኩል የሰዎች ድምፅ.......ዐይኖቼን ስመመን ይወትባቸዋል:: ......ኩኩሉ.......ሩጫ.......ኡፍ .......ኡፍ.......ዶሮ.......እሩጫ.......መቼ ይፈለፈሉ ይሆን? ይኸቺ እንቁላል....አዲስአባን የሞላት ዶሮ የሚጥለው እንቁላል.......መቼ ይፈለፈላል? መቼ ጫጩት ሆና በቸርቻር ጎዳና ሸር ይላል?.......መቼ ቢጫ ቢጫ ላባ የለበሱ ሞላዎች በአድዋ መንገድ ጡብ ጡብ ይላሉ?.......ስባንን ......

«ለምን እንጋባም?»

«እ»

«ለምን እንጋባም?»

«ምን ትጨቀጭቀኛለህ አሁን»

«ንገሪኝ»

«እ»

«ንገሪኝ»

«እምቢ»

«እ»

«ኡፍ»

የዚህ ሠፈር ውሻ ከአፍ ብቻ የተሰራ ይመስላል:: አሳጥሮ በእጭሩ የሚንቃቃ ውሻ አለ.......እግሩ ላይ እንደቆሙበት:: አርዝሞ የሚያላዝን አለ......እንደ ጥላሁን ገሠሠ.......ፍቅር እንደያዘው፣ እንደ እሱ...... የቀዳውም ፍቅር ከእናቱ የወረሰው የሞላ ከዳ እንደፈሰሰበት:: ሳያቋርጡ የሚንጫጩ አሉ.......ፀጉራቸውን እንደሚነጩባቸው ውሪ:: ዝቅ አድርጉ የሚጮህ አለ.......እራቱን እንደቀሙት ሀይኑ-አፋር:: ሴት ዶሞ የምትመስል አለች ወጧን እንደተቼባት ትርቡት የምትነጫነጭ:: ቡችሎችም አሉ.......የጥምቀት ቀሚስ እንደሚጠይቁ

አንተ አራም ጥተም

ልጃገረዶች...... እየተለማመጡ እየተሽኮረመሙ......እያለቃቀሱ:: አንዴ አባርቆ ዝም የሚል አለ......በጥፊ እጩለው ሊያባብሉት እንዳቀፉት:: እኝ እኝ የሚል አለ......ጥርሶቹ ወልቀው እንዳለቁበት......በድዱ የሚጥር......

የዚህች አዲስአባ ውሻዋ ሳይቀር ተወሳስቦአል::

በዚህ በሌሊት የጎረቤት ሬዲዮ የሚጉረጉር አለ? ዩንቨርስቲ መሰለኝ:: ሰንቅልፍ እምቢ ሲለው ሌላውን በሬድዮ ጉርጎራ የሚረብሽ አለ:: ተማሪም እዛም ካምፓስ ዐይነት አለው ቢቢሲ ልስማ ይልና በደረቅ ሌሊት......ስለቀኑ ረብሻ የሚያጠና......ቢጨንቀው ለዕንቅልፍ ባይታደል:: ጠዋት ላይ ቀድሞ ያወራል......እየኩራ......`የቢቢሲ ኮሚንት`[25] እያለ:: ቢቢሲ ይኸቺን ሴት ያውቃል? አሁን እዚህ ምን እንደምትሰራ ያውቃል? ጆናታን ዲምቢልቢ......ሽሮ በክክ ቀምሶአል? የሚጮህ ደረት ካኪ ይለብሳል? አመዳም መሬት ላይ `ከስዊት ኸርቱ`[26] ጋር ይተኛል? አረቂ ሽጦ ያውቃል?......ያውም በአንድ ማታ አንድ ገበያተኛ ያለበት......እሱም ብርጭቆ ሰብሮ የሚሔድ......እንዲህ የውሻ ጩኸት የሞላበት ሠፈር ውስጥ ኖሮአል? ከዚያ......`ቢቢሲ ወሬውን እንዴት ያገኘዋል እባካችሁ?` ይባልና ለቁርስ ተያይዘን እንወጣለን......ነጭ......ትርፌቷ የምትጣፍጥ ዳቦ በመርመሳት...... በሰንቁላል ፍርፍር......በሻይ በወተት......ከዚያ `ዘ ጋርድያን`[27] ወይም ሌላ እናንብብ ይባላል......ጋዜጣው ፊት ለፊት የሆነ የፕሬዝዳንት ፎቶ ......ተቀምጠ......ወይም እጁን አንስቶ ሲጮህ......አዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በኢንፍሪዮሪቲ ኩምፕሌክስ[28]......በየመሳብያው ተጣጥፈው ይወድቃሉ......ቀናቸው ሳያልፍ ያልፋሉ......ገልባጭ ምሁር ገና ጥጃውም መሲናዋም ኮርማውም ኮሌጅ ግቢ እንደ ከብት አፈንድደው የፈረንጅ የመረጃ ሳር ሲግጡ...

..ከዛ ደ`ሞ ኢምፔሪያሊዝም ጨቋኝ ነው ይባልና እሱ ካልተደመሰሰ እንማርም አንተኛም አንበላም (ፒያሳ ወጥተን ግን ፓስታ መንፋታችን የት ይቀራል?) አንተኛም ተብሎ ኃይለሥላሴም ይሰደባሉ: *ለአሜሪካን ጭፍራ ለእስራኤል ቡችላ/አይገዛም ሕዝቡ ከዛሬ በኋላ*......ይዘባርቃሉ አይገባቸውም......የዞረባቸው ማዞሪያዎች......የማን እራስ እንደሆነ የማይታወቅ......በየቀኑ የሚሸራሞጥ......የብዕር

[25] የቢቢሲ ግምገማ
[26] ፍቅረኛውጠ/ከንፈር ወዳጁ
[27] የእንግሊዝ ጋዜጣ
[28] በዝቅተኛነት ስሜት



@BOOKALEM

ጥላሞት......ሲፈልግ የሚረዝም ሲፈልግ የሚያጥር......ሆድቃው በምኞት ገንዘብ የተሞላ:: በአንጉሉ የዕለት እንጀራውን የሚለምን ፀሐፊ......አቃጥሮ የሚያድር...... `ምን ላድርግ......ሥራዬ ነው` በተባለ ልባስ ስር ምኞቱን በሚስጢር የሚቀጭ......በአንድ ዐይኑ ወደ ረብሻው......በአንድ ዐይኑ ለመኳንንት የስልክ ጥሪ የሚቸኩል......በሆዱ የሚመራ......ውስኪ ዝናብ ሥር አፉን ወደላይ ከፍቶ ወደ ፊት የሚሮጥ......ይኼ ካፊያ ሲያጥርበት ተንደፋድፎ የሚቆም......

እዚህ......

ሀበሻው ሃፍረቱን የሚያስጥል ቤት ውስጥ ያድራል:: እኔ ቆዳዬን አዋድዳለሁ:: ቆዳዬን አከብራለሁ:: ሥጋዬን አከብራለሁ......ሕልሙ የከዳው ሥጋ ልጁን መቆንጠጥ ያቃተው ሥጋ:: ያልረባ ሥጋ፣ አፍንጫ የሚበጥስ ሥጋ:: ቂራ:: የንኡስ ከበርቴ ቂራ:: ተረት ሠፈር ብብት...... የቤተመንግስት ጉድፍ በሚስጢር በሚዘረገፍበት ቦይ ስር አዳሩን የሚቀጭ......

እዚህ......

የቀሃን የተልፈሰፈሱ ካሮቶች......ከጉልት መደባቸው ተንሸራተው እንደወረዱ እግረኛ እግር ስር የወደቁ:: እኛ......ሀሁ የቆጠርን እግረኞች ነን......ፊታችንን በመስታወት ከማየት መፅሐፍ የምናገላብጥ......

እዚህ......

ዜጋ በአፍጢሙ አፈር ይጠጣል:: የደሃነትን ውበት ያላየን......የማይጠላ ደሃነትን ያላየን......የማይጠላ ደሃነትን `የንቃት ዕጥረት` ያልን......:: ከውጭ የልዑላን (የደምና የፊደል) እንኩርፍት የነፋሱን አቅጣጫ ያጥፋል......ከውሻ ጩኸት ይሻማል::

እዚህ......

የድስታቸው አድማስ ጠባብ ናት:: የሞሰባቸው ሰማይ ቅርብ ናት:: ብርጭቆአቸው መለኪያ ናት:: እንሥራቸው ማሰሮ ናት:: እንሶላቸው አቡጀዲ ናት:: ብርድልብሳቸው በርኖስ ናት:: እዚህ ብርድልብስ ስር ፍቅር እንደሚተነፍስ ዘንግተናል......ድህነት ሁሉ ገንዘብ እንዳልሆነ ዘንግተናል::

እዚህ......

ሌሊት ሌሊት ረኀም እግራቸው ከቤታቸው ውጭ ያድራል...... እየፈተሽን እነዚህን እንግዳ እግሮች እንደ ባህሉ እኛ እናጥብ ይሆን ወይስ ኢምፔሪያሊዝምን ልናግ......ፊውዳሊዝምን ልንሸረድድ......

ሰማሽ አዲስአባ!

ከሞንዶን ዛፎችሽ ጋር ረቂቅ ዕርግማን ተሣፍሮ መጥቶአል እንዴ? ወይስ ተራሮችሽ እፊያ ናቸው ከጎድጓዳቸው ውስጥ እንደእኔ የመሰለ የማይበላ እርግማን የደበቁ.?

* * *

ጠዋት ተነስቼ ልብሴን እየለበስኩ የተጉዳውን እግሬን ፈተሽኩት:: ውጋቱ ቀንሶአል:: ጊዳ ዕቃ ሲተራመስ እሰማለሁ:: መራመድ ብችልም ብዙ ምቾት የለውም:: ከውጭ ፀሐይዋ ወርቅ መስላ ትበራለች:: ሳሉን መሐል የተነጠፈው ንጣፍ ተነስቶ ሁሉ ነገር በስልቱ ተደርድሮአል:: እታለም ከጊዳ መጣች......

«ደኅና አደርክ?»

«ደኅና:: ደኅና አደርሽ?»

«እንደ መሬት የሚመች የለም» መሬት በማደራቸው እኔ ቅር እንዳይለኝ ይሁን ወይ እውነቷን እንጃ::

«ግርማ የት ሔደ?»

«ሥራ ሊሊት ነው የወጣው»

«አዲስአባ አይደለ የሚሰራው?»

«እቃቂ ነው......ግንበኛ ነው......የመጀመሪያው አውቶብስ ካመለጠው አይደርስም»

«አቃቂ ሔዶ ይሰራል?»

«ሁለት ወር ሲመላለስ ነበር እዚያ:: ከአንድ ወር በኋላ አዲስአባ እፈልጋለሁ ሲል ነበር»

«ቶሎ ስላልተነሳሁ ረበሽኳችሁ?»

«ኧረ ምናለ ብትተኛ»

«ስንት ሰዐት ይሆናል?»

በበሩ የገባውን ጨረር አይታ:

«ወደ አራት ይቀርባል»

«እግሬም ደኅና ነው»

«ብዙ አትንቃንቅበት»

......ትንሽ ቤቱ ውስጥ እየተራመድኩ አሳየኋት::

«ቁርስ በልተህ ሂድ......ጉበዝ እኮ ናቸው ሃምሳ አለቃ:: የምር:: እጃቸው መድሐኒት ነው»

«ግድ የለም ስለ ቁርሱ» አልኩ::

«አይ ደግ አይደለም......ቁርስ የሚበላው የታደረበት ቤት ነው» አለች

መከራከር አልፈለኩም:: ተነስቶ መውጣትም ጥሩ ስርዐት አይደለም::

«አንድ ነገር ልጠይቅሽ?»

«ምን?»

«ለምንድነው ያሳደራችሁኝ?......ለምንድነው እንዲህ ያስተናገድሽኝ?»

«እግዜር ነው ያስተናገደህ......እየህ አጋጣሚ አመጣህ»

«`ሒድ` ማለት ትችይ ነበር......መንገድ ድረስ አውጥተሽ ትጥይኝ ነበር»

«ብዙ ነው ታሪኩ ልጄ»

«ብዙ ታሪክ ነው?»

«አዎ»

«እንዴት?»

ከቆመችበት የጊዳው በር እተጋደምኩበት መጥታ ተቀመጠች:: ፊት ለፊት እያየችኝ:

«የምነግርህ......» አቆመች::

«ግድ የለም ንገሪኝ»

«ሥሜ ዐይንአለም ነው......እታለም አይደለም»

«እና»

«አርባ ምንጭ ተወልጄ ነው ያደግሁት:: አባቴ ራሱን የቻለ ሐብት ያለው ሰው ነበር:: ሁልጊዜ እንድማርለት ይፈልጋል:: እናቴ ደ`ሞ አግብቼ እንድሔድ ትፈልጋለች:: ከመሐል እንግዲህ እንዲህ እንደአሁኑ ጊዜ አይደለም ትልቅ ሆኜ ነው ት/ቤት የገባሁት:: ያኔ አንድ ልጅ እወዳለሁ አብሮኝ ይማር የነበር:: ወላጆቼ ወሬውንም፣ ምኑንም ሲሰሙ `ተዚህ ከደሐ ጋር` ብለው ከአገር ሊያባርሩኝ ሲሰናዱ......በኋላ ይሔ ባሌ የሆነው ሐብታም ሰው ለካስ ሲሰልለኝ ኖሮ......`ላግባት` ይላል:: `ተገኝቶ ነው ወይ′ ይባልና......እሰጣለሁ:: 18 ይሆነኛል ልበል ያኔ? አይሞላኝም:: ብቻ ኑሮ አትበለው:: ያው



@BOOKALEM

ከዚያ የወደድኩት ልጅ አገሩ ጠባብ ነው......እዚያው አርባ ምንጭ እንገናኛለን:: አንዳንዴ ገበያ አንዳንዴ መንገድ ላይ......ባሌ ከዚህ ልጅ ጋር የነበረኝን ታሪክ ያውቃል ሊገለኝ ደረሰ:: ገበያ መውጣት አልችል......የትም መሔድ አልችል......ያው እሱን ተከትዬ ካልሆነ:: ወይም የሚያምነውን ጠባቂ ሰዶ:: ጨካኝ ነው:: ጠዋት፣ ማታ ስድቡ......ፊልጉ ያገባኝ አይመስልም:: የተገደደ ነው የሚመስለው:: ሲሆ፣ ሩብ የሚያሳርሳቸው ሰዎች አሉ......እነሱን ጠዋት ማታ እንደቀጣ፣ እንዳስገረፈ ነው......አንዳንዴ በረት አስሮ ያሳድራል......ለረባ ጉዳይ አይደለም......ለአንድ ጆንያ በቆሎ......ለአንድ ጆንያ ስንዴ ነው:: ሰው ከእሱ ጋር አብሮ ጠላኝ፣ አብሮ ፈራኝ:: ትንሽ ደግ ነገር ከወጣኝ......ሊገለኝ ይደርሳል:: ልብስ በየቀኑ ነው የሚገዛልኝ:: መልበሱ አስጠላኝ:: መሽቀርቀር አስጠላኝ:: በዚያ ዐይነት ገንዘብ ሰው ልቡ ሳያዝን ማደሩ ይገርመኛል:: ቤተክርስቲያን ስሔድ......`እግዚያብሔርን ከእሱ አትደባልቀኝ` እላለሁ:: ያው ልጅ ወለድኩ...... ምን የመሰለች......ንጭንጬ ቢቀልልኝም......ንጭንጩ ቢቀር ጥርጣሬው:: አላመነኝም......`እኔ ከብዙ ሴት ሞክሬ ያልወለድኩት እንዴት ከአንቺ እወልዳለሁ......የዚያ የጎረምሳ የውሽማሽ ይሆናል......` እያለ:: ሁለት ዓመት ያህል አቃጠለኝ:: ባለቅስ እሪ ብል አላመነም:: በልቡ የራሱ ልጅ እንደሆነ ያውቃል:: ግን እንዴት ይጨቅጭቀኝ? እንዴት የእኔን አንጀት ይበጥስ? አንዳንዱ ሰው ክፉ በባይ ይሆ ይወለዳል መሰለኝ:: ወደ ቤተሰቦቼ ደጋግሜ ብሔድ መለሱኝ:: `እባው ባልሽ እኛ ምን እናውቃለን`:: በዓመት እንግዲህ ቀለብ ቢኖራቸውም ይሠፈርላቸዋል፣ ማር ይጭንላቸዋል፣ እሱ አይሰራው፣ አያርሰው......ልጅ ይከዳል ለእዚህ?......ለእህል......ለግብር-......ለግብግቦ:: ሲከርም፣ ሲከርም ተስፋ ቆረጥሁ:: አንድ ቀን ሰውዬዬ ለመሬት ጨንቻ ክርክር እንደወጣ ......ያለችኝን ገንዘብ ሰብስቤ ተዚያ ሁሉ ጨርቅ አንድ ሻንጣ ብቻ ይዤ አዲስ አባ መጣሁ:: ማንንም አላውቅም:: ፊት በር አንድ ዘመዳችን እንዳለች አውቃለሁ......በወሬ ነው:: እግዜር ሲረዳኝ...... እስዋን አፈላልጌ አገኘኋት......አዲስአባ ደርሼ እስዋን እስካገኘኋት የደረሰብኝን ባወራህ ራሱ አንድ ታሪክ ነው:: ደገኙቿ ዘመዴ የምላት ብዙ አንተዋወቅም......የሩቅ ዘመድ ነን:: ሌላውም አንዳንድ ባዕድ ሰው ......የሰራልኝን ደግ ነገር ብዘረዝርልህ ብዙ ነው:: ከእኔ የሚያገኙት ምርቃት ብቻ ነበር:: ሌላ ነገር አልነበረም:: ደገኙቿ ያልኩህ ዘመዴ ሰፀገነት የምትባል ወዳጅዋ ረድታት......ደገኙቿን ቤት ፈልጋ ተከራየኋትና ጠላ መጥመቅ ጀመርኩ:: እና እኔ የምልህ ያቺ የችግር ጊዜ ብዙ አስተማረችኝ......ለሰው ደግ ነገር ስታደርግ፣ አንተም ሰውዬውም ደስ



@BOOKALEM

ይለዋል:: ሁሉም ደስ ይለዋል:: እግዚአብሔር ደስ ይለዋል:: ራስ ወዳድነት እዚያው ነው የሚቀረው:: እና ሺህ ሰው ቢመጣ ይኸቺ ቤት ጠንካራ ነፋስ ቢመጣ የሚጥላት ናት:: እዚህ ሰው ቢጠለል ምናለበት:: ባሌን ትቼው የመጣሁት ከፍቶብኝ አኩ ነው......» አፍዋን ይዛ ለረዥም ጊዜ ዝም አለች:: ማልቀስ የዳዳት መሰለች::

«ልጅሽስ?»

«ትልቅ ሆናለች አሉ:: አንዳንዴ ሳስታውሳት አንጀቴ......»ዐይኖችዋ ዕንባ አቀረሩ:: ወደ ጓዳ ገባች:: ለማልቀስ ይሆናል::

«ብዙ ነገር አሳሰብኩሽ......ይቅርታ»

«አሳሰብኩሽ? ተወኝ እቴ......ሁልጊዜም ነው የማስባት:: ልጅ እኩ ናት......ሥጋ ናት:: የተዘረፍኩ ይመስለኛል» ፊቷን እየጠረገች መጣች:: በሌላ እጅዋ በሳህን ቁርሴን ይዛለች::

«በዘይትና በሽንኩርት ጥሩ ሆና የተሰራች የእንጀራ ፍርፍር ናት» ሰባራዋን ጠረጴዛ ጉትታ ሰሐንዋን አስቀመጠችባት::

«ኸረ ግድ የለም»

«እህት አለህ?»

«አዎ»

«ይብላኝላት»

«ምነው?»

«ለሴት እባክህ ኑሮ ጥሩ አይደለም......ሴት ከመውለድ ቢቀር ይሻላል»

«እንዴት?»

«አንዳንዴ......'ባልወለድስ' እላለሁ......አንዳንዴ......መወለድ ጥሩ ነው ግን ለምን ሴት አደረከኝ ጌታዬ እላለሁ......አንዳንዴ......ኑሮ ከበድ ሲለኝ......ልጂ ስትናፍቀኝ......የዚያን ሰው ጭቅጭቅ ችዬ በኖርኩ እላለሁ» ተቀምጣ በነጠላ ጫማዋ ትጫወታለች:: ፍርፍሩ ግሩም ነው::

«ጥሩ ነው ፍርፍሩ?»

«አዎ ጥሩ ቁርስ ነው»

ሌላ ጥያቄ ልጠይቃት ፈለኩ:: ዋጥኩት:: ከዚህ በላይ መጠየቅ ወዳጅነት ሳይሆን ስለላ የሚሆን መሰለኝ::

«ከአንድ ወር በኋላ ትምህርት አለህ?»

«ምነው?»



@BOOKALEM

«ይኖራል?»

«እንጃ»

«ከግርማ ጋር ቀለበት ማድረግ አስበናል ብትመጣስ?»

«ያለኝ አይመስለኝም፣ በረብሻው ካልቆመ፣ ቢቆምም እመጣለሁ:: አዲስአባ ነኝ ያለሁት»

«ደግ ለታምሩም መልዕክት እልክበታለሁ:: ከእሱም ጋር ትተዋወቃላችሁ»

«በዐይን አውቀውም ይሆናል»

«ይቀላል እሱማ......በል በወሬ ጠመድኩህ:: ብላ»

......ቁርሴን አጠናቀቅኳት:: የሳሕንዋ ነጭ ደረት በዘይት ቅባት ቀይ መስታወት እስኪመስል:: ሳንባዬ ስር ጉድጓድ ያለ ያህል ይሰማኛል:: ብዙ ነገር መብላት የምችል ይመስለኛል:: አንዳንድ ጊዜ የዓለም ሆዶች ማዕከል የሆንኩ ይመስለኛል......እንደ አዙሪት......ወደ ራሴ ውስጥ ሁሉን ነገር መሳተት የምችል......ሁሉን ነገር መብላት የምችል:: መንገዶችን እንደ ፓስታ፣ ቤቶችን እንደ ድፎ ዳቦ ቁራጭ፣ ስልክ እንጨቶችን እንደማሪሲሊ፣ ሰዎችን እንደ ሥጋ፣ ጠጠሮችን እንደቆሎ፣ ጨርቆችን እንደ እንጀራ፣ ዛፎችን እንደጐመን፣ ግንዱን እንደ ሽንኩርት፣ ውሐውን እንደ ውሐ፣ አፈሩን እንደ እንደ ድርቆሽ ፍርፍር......አሁን አፈሬን::

......እታለምን ተሰናብቻት ከቤቷ እያነከስኩ ስወጣ......እንደገና የተወለድኩ መሰለኝ:: ከሆነ ማሕፀን......በፍቅርና በጉጉት እየተገፋሁ የወጣሁ መሰለኝ:: ይኸቺ ፀሐይ ደ`ሞ ክንፍዋን አልብሳኝ......ማር ወደ ሰነገ ሳንቡሳ ልትለውጠኝ ትችላለች:: ሣቅ ሣቅ አለኝ:: ልቤ ስትዘል ጆሮዬ ከቆመበት ይሰማታል:: ጠብ ጠብ ስትል:: ታክሲ ማግኘት እንዲመቸኝ በአንዲት አጭር ኮረኩንች ዳገት ወጣሁ:: የመነንን መንገድ አስፋልት የመፈከር ወረቀቶችና ጥቂት የወላለቁ ጫማዎች ሸፍነውታል:: መንገዱ ዳር......አንዳንድ ጎረምሦች ተቀምጠዋል......ጫማቸውን የሚያስጠርጉ አሉ:: ትናንት እዚህ ቦታ የሆነ ትርምስ እንደነበረ የሚጠቁም ደማቅ ፍንጭ የለም:: ግምት ካልተፈጠረ:: ግምት ደግሞ ቸል ብሎ በሚረማመድ፣ ቸል ብሎ በሚያልፍ......የራሱ ጉዳይ በሚያጣድፈው ሰው አትሰራም:: ምናልባት ወሬው የደረሰው ሰው ከሚያየው ጨረፍታ ተነስቶ ሙሉውን የትላንት ሁኔታ ለመገንባት የሚሞክር ይኖራል:: ያለው አማራጭም ያ ብቻ



@BOOKALEM

ወስላል:: ከቦታው የቀረኝ ትዝታ ትንሽ መዝሙርና ራ......የተተራመሰ ሕዝብና......ስባራ እግሬ ብቻ ናቸው::

በያንዳንዱ ሰው ልብ ምን እንዳለ ምንስ እንደሚንፈለፈል ነውቃል? በጅምላ ሐረግ ሥር መቼም መሞት ለምደናል......መደነት ደናል......ማውራት ለምደናል:: እኚያ እግሬን ያሹኝ ሽማግሌ ጠገቤ ሲያልፉ ብጠራቸው አልሰሙኝም......ዐይተውኛል......ግን ነወቁኝም:: ማን እንደሆንኩ እንዲያስታውሱኝ ወደ እታለም ቤት ታ መመለስ አለብኝ......ያውም እንደገና ተሰብሬ:: እዚህ ዐሐይ ብጥ፣ ጉዳና ላይ፣ እየተራመድኩ፣ በቁመናዬ ፊቴ እየሟቀ ግን ያውቁኝም::

ለምን ወልዴ ሮጠ?

በልቡ 'ለእሙኛዬ ልኑርላት' ብሎ ይሆናል::

በልቡ 'ምን አዳረቀኝ' ብሎ ይሆናል::

በልቡ ገና ሲጀመርም 'ከዚህ ሠልፍ እንዴት ተሎ ልገላገል' ብሎ ይሆናል::

ቆሜ ታክሲ መጠበቅ ብችልም የንፋሱ ደርባባነትና ጠቅላላ የቀኑ ውበት ይስበኛል......በቀስታ መጉተቻው እስማት ነው......በዚህች በይነት ውብ ዐሐይ ሥር የሰው ልጅ ለምን እንደሚራብሽ አይገባኝም:: ምነው ይሔ አስፋልት ሜዳ በሆነ፣ መስክ በሆነ፣ በሬንጅ ምትክ ሣር በሆነ፣ እነሆ በጀርባዬ ተኝቼ ለብዙ ዘመናት የበራችውን ዐሐይ እጠጣለሁ:: ችል ብለነው፣ የማያረካ የሴራ ትንግርት ላይ ስናተኩር በጣቶቻችን መሐል ስንት ደስታ ይሾልካል? ሐይለሥላሴ መሬቱን አካፍለው......ሁላችንም ምናለ ጠዋት ጠዋት ፍርፍር ብንበላ::

አንዱ እዚህ ሊስትሮ ይራገማል:: ሊስትሮ ምኑ ይረገማል? አጠገቡ ሌሎች ሊስትሮዎች በሳቅ ይፈነዳሉ:: ትንንሽ ሳጥናቸው ዙሪያ እየተንከተከቱ መከፈያ እንደሚፈልግ ቡችላ ይዞራሉ:: ቤተመንግሥቱ በጥ ብሎአል:: ምናልባት ጠ/ሚኒስተሩ እግሩን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ አሜሪካንኛ ያወራል:: ወረድ ብሎ ዐይንአለም የሙሽርነቷን ሱዳን ሽቶ ትሞክራለች:: እዚህ አስፋልት ላይ የጀርመን መኪናዎች ይዘንጣሉ:: ውስጣቸው የጣሊያን ኩት ያደረጉ አፍሮአቸው የቆመ ጎረምሶች......ፓሪሞድ ያደረገች ሃና የተባለች ወይዘሪት......ከሚኒስከርትዋ ያመለጠ ጭኗ መንገድ ዳር እያለከለከ የሊጋ ጎረምሶች ጫማ ሲበላ......መስኮቱ ከተከፈተ ዚታዎ መያዣው የወለቀ ነጭ ገንጥላ የመሰለ ምራቅ አስፋልቱ ደርዝ ላይ



@BOOKALEM

ይለጠፋል……ከመኪና ጀርባ ጎማ ስር የቆመ ሾፌር ሽንቱን ይሸናል:: ሽንቱ ከአራት ኪሎ ፓርላማ መስቀል አደባባይ ለመውረድ ጭድና አቧራ እያግበሰበሰ መንገድ ጀምሮአል……በስተግራዬ ካሉ ሻይ ቤቶች ዘፈን ይፈሳል……በር ላይ ከተሰካ ስንደልም……ፈትል የመሰለ ጭስ ይወጣል:: የአራት ኪሎ ነፋስ በማይጠግብ ምላሱ ይልሰዋል:: የሬይ ቻርለስ ዘፈን በአየር ውስጥ ይራመዳል ቸኮል ብሎ……

Unchain my heart[29]

Baby let me go

እዛ ሻይ ቤት በር ስር የተቀመጠ ጎረምሳ ጀርባ ቆራጤ በሻይ ይነፋል……

Unchain my heart

ቀጥሎ ፀጉር አስተካካይ የራሱን ፂም ይከረክማል……የምገባ መስዬው ዞር ብሎ አየኝ:: እያነከስኩ አፍሮዬን ፋቅሁ:: አፍሮ ከሚተቹ ሰዎች የመጀመሪያዎቹ ፀጉር አስተካካዮች ይመስሉኛል:: ወይም በመሳባነቱ የተሸሙዋጠጠ ሽማግሌ::

'ባህላችንን ጠባቂ ነኝ' በሚል ሰበብ ነጋ ጠባ የሚታረብ:: የግድ ገዳይ ብቻ ማጉፈር አለበት ማን አለ? አይከብድ:: እንደው ቅናት::

Unchain my heart

Baby let me go……

የሀበሻ የፀጉር ባህል ምን · ይመስላል ቢሉአቸው አያውቁም……እጅግ ብናሳጥረው ድ`ሞ ያኩርፉን ይሆናል……ልጅ ስለሚያስመስለን::

Unchain my heart

Baby let me go

ይኸው ፀጉሩ ቢቀር እግራችንን እየሰበርን ነው……

Unchain my heart

Baby let me go

ከዚህቺ አገር የጥቁር አፈሯ ዝግት……የዕንቁ ዛፎች ይበቅላሉ:: ዕርግብ ዐይነአለም……ጎጆዋን ከሐር ላባ መስራት አለባት:: የከፋት ቅርፊት……በሐምሌ ሞገድ……ታጥቦ……እታለም ንግሥት እንድትሆን:: አዲስ ሥርወ—መንግሥት

Unchain my heart

[29] ልቤን ፍችልኝ! ልሂድበት ፍቅሬ



@BOOKALEM

......የቀረችን የደግነት ሐብት አለች::

......የቀረችን ማርያም አለች

......የቀረች ምርቃት አለች......ዘመን አልፋ የመጣች ተሽራርፋ ያላለቀች::

......የቀረችን መውደድ አለች

......የቀረችን ሠላም አለች

......የቀረችን እታለም አለች......

baby its alright[30]

oh! its alright

ሄ ሄ ሄ......ዬ......

በእግሬ ስድስት ኪሎ ገባሁ......

ጥላው በተገፈፈ፣ ፀዳል በሚያፈስ ዝዋራዬ ተከብቤ፣

እናም እንካሳዬ ዳንስ መሰሉ::

— // —

መስከረም 1981 ሆላንድ

---

[30] ምንም አይደል ፍቅሬ፤ አ! ምንም አይደል



@BOOKALEM



አዳም ረታ ቀደም ሲል ባሳተመው "ግራጫ ቃጭሎች" በተሰኘው ረዥም ልብ ወለድና በሌሎች በርካታ የአጫጭር ታሪክ መድበሎች ከአንባቢያን ጋር ተዋውቋል። አሁን ደግሞ "እስንጋ ምስር" የተባለውን የትረካዎች ስብስብ ይዞላችሁ ቀርቧል።

"ስለ "ግራጫ ቃጭሎች" የተሰጡ አስተያየቶች

"የአዳም ረታ "ግራጫ ቃጭሎች"ን ለአምስት ጊዜ ያህል ደጋግሜ አንብቤዋለሁ፣ ባነበብኩት ቁጥር አዲስ ትርጉም፣ አዲስ መረጃ ይሰጠኛል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ ጊዜ ባገኘሁ ቁጥር በወትር ሳነበው የምናፍቀው የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት ነው። ... "ግራጫ ቃጭሎች"ን ከፍቅር እስከ መቃብር ማወዳደር፣ ማበላለጥም ይቻላል።

አቶ የሺው ተሰማ - ደራሲና ሃያሲ የኮተቤ መምህራን ኮሌጅ መምህር
አዲስ ነገር ጋዜጣ፣ መስከረም 2 ቀን 2001

... ዳኛቸው 'ወርቁ' 'አደፍርስ' የኢትዮጵያ ሕግጋትን አጋምሶ ለማስቀመጥ ከሞከረ ወዲህ በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ በኢትዮጵያ ተሟልቶ የተገኘ ድርሰት "ግራጫ ቃጭሎች" ነው። .... "ግራጫ ቃጭሎች" ከዝብ-ባህሪው አኳልና ...ለቡና አሳሳል አልፈን ደንቶ ዓላማውን፣ ቋንቋውንና የሕይወት ...ናውን ስንመለከት የአዳም ረታ እውቀትና ልምድ ጠንከር - ጠጠር ብሎ ...ብሎ በኩል ሲያስተጋባ ነው የምንመለከተው።...

ዓለማየሁ ገላጋይ - ደራሲና ሃያሲ
ልሚድ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 02 ግንቦት 1998

"ግራጫ ቃጭሎች" .....በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ አዲስ ትርዒት ለማምጣቱ ... ጥርጥር የለኝም። ... አዳም ረታ በልዩ ተሰጥኦው አዳዲስ አቀራረቦችን ሲሞክር የቆየ ደራሲ ነው። ... ልጅነትን በልጅነት አምሮ ሳይበረዝ ሳይከለስ ለማሳየት የሞከረ፣ ሞክሮም የተሳካለት ደራሲ ነው። ...

በዕውቀቱ ሥዩም - ገጣሚና ደራሲ
ስምማር መጽሔት ቅጽ 01 ቁጥር 02 ጥቅምት 1999

ርኆቦት አታሚዎች

ብር 45

@BOOKALEM



public channel

Info

t.me/BookAlem

Invite Link

@BOOKALEM